# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች





## ቅጽ 18

## የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የፌዴራል ጠቅላይ
# ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ-18

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ጥር 13, 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ



**<u>የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤትፕሬዚዳንትመልዕክት</u>**

የሰበር ውሳኔዎችን ለሕዝብ ለማዳረስ እየተደረገ ያለው ጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች እየታዩበት ነው። ከሰበር ውሳኔዎች አስገዳጅነት አንጻር ውሳኔዎቹ እንደተሰጡ ወዲያውኑ ለሥር ፍ/ቤቶች ሆነ ለሌሎች አካላት መድረስ ይኖርባቸዋል። አትሞ ማሰራጨት የቱንም ያህል ለማፋጠን ቢሞከር ጊዜ መውሰዱ አይቀርም ።በአሁኑ ጊዜ የኢንተርኔት አገልግሎት እስከ ወረዳ ድረስም ስለደረሰ ውሳኔዎቹ በተሰጡ ጥቂት ቀናት ውስጥ በፍ/ቤታችን ድረ ገጽ በመጫን ተደራሽ ለማድረግ እየሰራን ነው፤የዚህን እትም ውሳኔዎችና የበፊቶቹንም በድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል። እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ አገልግሎታችንን ለማሻሻል የሚረዱ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ ነን።

**ተገኔ ጌታነህ**

**የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

**ፕሬዚዳንት**

# የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 18/

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አሠሪና ሠራተኛ | | | | 1 |
| 1. | አንድ ሰራተኛ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ካለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረቱ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ አሰሪው በዚሁ ምክንያት ሰራተኛውን ካለማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበተው ስለመሆኑ በደብዳቤ ሳይገልፅ መቅረቱ የሥራ ውሉ በሕግ አግባብ አልተቋረጠም ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1) (ለ) | 104862 | አቶ መልካሙ አረጋ<br>እና<br>ተስፋዮ ለገሰ ጠቅላላ ስራ ተቋረጭ | መጋቢት 3 ቀን 2007ዓ.ም | 2 |
| 2. | አንድ አሠሪ ሠራተኛው ህጋዊ የመብት ጥያቄ በማቅረቡ ምክንያት የስራ ውሉን ማቋረጥ ህገወጥ ተግባር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 26(2)(ሐ) | 105921 | ፒተርድስ ፕሮዳክተስ ማኑፋክቸሪንግ (አ.ማ)<br>እና<br>እነ ይፍቱ ስራ ነጋሽ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 14 ቀን 2007ዓ.ም | 6 |
| 3. | የአንድ ድርጅት ሠራተኛ በሠራው ጥፋት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉ ቢቋረጥም ያልወሰደው የዓመት እረፍት ካለ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈል የሚገባው ስለመሆኑና የፕሮቪደንት ፈንድም በከፈለው ልክ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ፣ | 102994 | ዳሽን ባንክ<br>እና<br>እነ ተፈሪ አሳልፈው /ሦስት ሰዎች/ | ሚያዚያ 30 ቀን 2007 | 10 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 4. | የአንድ ድርጅት ሠራተኛ ለአሰሪው የስራ መልቀቂያ አስገብቶ የስራ መልቀቂያው በአሰሪው ምክንያት በወቅቱ ሣይሠጠው ቆይቶ ሰራተኛው የስራ ግዴታውን እየተወጣና የስራ ግንኙነታቸው በተግባር ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ ከረጅም ጊዜ በኋላ አሰሪው ሰራተኛው ቀደም ብሎ ያስገባውን የስራ መልቀቂያ መሰረት በማድረግ የስራ ውሉን ቢያቋርጥ የስራ ውሉ የተቋረጠው በህገወጥ መንገድ ነው ሊባል የሚችል ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጁ ቁ.377/96 አንቀፅ 4/1/፣23፣26፣30፣31፣33፣39፣40/2/፣43/4/ሀ/፣ 35/1/ለ/፣38 | 104465 | ወ/ሪት ሸዊት ሀይሉ<br>እና<br>መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ | መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም | 16 |
| 5. | አንድ ሠራተኛ በአሰሪው የሚሰጠውን ትእዛዝ የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑና ሳይፈጽም ቢቀር ካለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት በቂ ምክንያት ስለመሆኑ<br><br>አዋጅ 377/1996 አንቀፅ 13/1/2/ እና /7/ እና 27/1/ ሸ/ | 108789 | ሴንቸሪ ጀኔራል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ ገስጥ ንጉሴ | ሚያዚያ 10/ ቀን 2007 ዓ.ም | 20 |
| 6. | በየመስሪያ ቤቱ የሚቋቋሙ የዲሲፕሊን ኮሚቴዎች በህግ አግባብ የሚቋቋሙና የሰራተኛው ጥቅም ያለአግባብ እንዳይጎዳ ተገቢው መጣራት ተደርጎ እርምጃ እንዲወሰድ እገዛ የሚያደርጉ ናቸው ተብሎ የሚታመን ስለሆነ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ዋጋ ሊያጣ የሚገባው ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ህጋዊ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 1/ሸ/ እና አንቀፅ 12/2/(7) | 105834 | የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ኮንፌደሬሽን<br>እና<br>ወ/ሮ እመቤት ኤርሚያስ | ሚያዚያ 28 ቀን 2007ዓ.ም | 24 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 7. | አንድ አሰሪ ሰራተኛው ያቀረበውን የስራ መልቀቂያ ጥያቄ ተቀብሎ ሰራተኛውን ካሰናበተ በኋላ የተለያዩ የክፍያ ጥያቄዎች በሰራተኛው ሲቀርብለት ወደኋላ ተመልሶ የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያት አግኝቻለሁ በማለት ሌላ ደብዳቤ በመጻፍ ለሰራተኛው የሚገባውን ክፍያ አልፈፅምም ማለት አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1/ለ/፣25 | 106610 | አቶ ካብራክ ተኮላ<br>እና<br>የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክስ | ግንቦት 14 ቀን 2007 ዓ.ም | 31 |
| 8. | በአንድ አሰሪ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ መሠረት በአንድ የሥራ መደብ ላይ የውጪ ሰው የሚቀጠረው መጀመሪያ ለቦታው የሚመጥን የውስጥ ሠራተኛ ካለ ለውስጥ ሠራተኛው እድል ከሰጠ ለኋላ ከሆነ አሠሪው ድርጅት ይኽን ደንብና መመሪያ ተላልፎ የውስጥ ዕድገት ማስታወቂያ ሣያወጣና ለሠራተኞች ዕድል ሳይሰጥ የውጪ ቅጥር ቢፈጸም ድርጊቱ ህገወጥ ተግባር ስለመሆኑና ቅጥሩ ሊሠረዝ የሚገባው ስለመሆኑ፣ | 107002 | ሲስተር ትዕግስት ፈቃድ<br>እና<br>የኤድስ መከላከያ ማህበራዊ አገልግሎት ድርጅት | ግንቦት 14 ቀን 2007 ዓ.ም | 35 |
| 9. | አንድ በሹፌርነት የተቀጠረ ሠራተኛ አሰሪው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ጥንቃቄ ማድረግ ከሚገባው ነገር አንዱ መኪናውን የሚያሽከረክርበት አግባብ ከአካባቢው አየር ሁኔታና ከመልከዓ ምድሩ ጋር ባገናዘበ መልኩ መሆን ያለበት ስለመሆኑና ይህንን ሳያደርግ ቀርቶ አደጋና ጉዳት ቢደርስ ከባድ ቸልተኝነት እንዳደረሰ ተቆጥሮ የስራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13/3/፣27/1/ሸ/ | 111839 | ፒ ኤስ አይ ኢትዮጵያ<br>እና<br>አቶ እሸቱ ካሣ | ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም | 41 |
| 10. | የቅርብ አለቃውን ሰብአዊ ክብርና ሞራል የሚነካ የስድብና ማዋረድ የፈጸመ እና በስራ ቦታ የጠብ አጫሪነትን የፈጠረ ሰራተኛ የሥራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ | 110615 | ኃብተሚካኤል ኃ/የተ/የግል/ማሕበር<br>እና | ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም | 45 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ 377/96 አንቀፅ 32/1/ሀ<br>አዋጅ 377/96 አንቀፅ 13/2/ እና 27 | | አቶ ታመነ ታደሰ | | |
| 11. | አንድ ሠራተኛ መብትና ጥቅሙን ሳይነካ ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ወይም የስራ መደብ በማዛወር ማሠራት የአሰሪው አስተዳደራዊ ሥልጣን ነው ሲባል ዝውውሩ ያለህጋዊ ምክንያትና በህብረት ስምምነቱ ከሠፈረው አሰራር ውጪ ይከናወናል ተብሎ ሊተረጎም የማይገባው ስለመሆኑ፣ | 105997 | ወ/ሪት ሉሊት አያሌው<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሚያዚያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም | 50 |
| 12. | ሰራተኛው በስራ ላይ በደረሰበት የሞት አደጋ ምክንያት የሰራተኛው ባለቤትና ሌሎች ጥገኞች የሚያቀርቡት የካሣ ክፍያ ጥያቄ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 1 | 108785 | ዩሴፍ ተክሌ ህንፃ ሥራ ተቋራጭ<br>እና<br>ወ/ሮ ወርቅነሽ ጌታቸው በራሳቸው እና ሞግዚት በሆኑላቸው /እነ ሕፃን ረዲኤት/ | ሐምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም | 54 |
| 13. | አንድ ሰራተኛ በስራ መዘርዝሩ በግልጽ የተሰጠውን /የተቀመጠለትን/ ግዴታዎቹን አለመወጣቱ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ፡-<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7) | 108933 | ሠላም ቦሌ ሸማቾች ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር<br>እና<br>አቶ እሸቱ አደፍርስ | ሐምሌ 30 ቀን 2007ዓ.ም | 56 |
| 14. | አንድ ሰራተኛ ለአሠሪው በሥራ ክርክር ምክንያት ያወጣውን ወጭና ኪሳራ የመክፈል ግዴታ የሚጣልበት በክርክሩ ተረች በመሆኑ ምክንያት ብቻ ሳይሆን ሠራተኛው በአሠሪው ላይ ያቀረበው ክስ ሀሰተኛና በተጭበረበረ | 109055 | አቶ ጌትነት ከበደ<br>እና<br>ሃያት ሜድካል ከሌጅ | ሐምሌ 29 ቀን 2007 ዓ.ም. | 60 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ስለመሆኑ<br><br>የፍትሐ ብሔር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 463 ፣465 (1)<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 161 | | | | |
| 15. | አንድ የመንግስት ሠራተኛ በአሠሪው የመንግስት መ/ቤት ጥፋት በሆነ ምክንያት የስራ ውሉ ተቋርጦ ቆይቶ በኂላ በፍርድ ሠራተኛው ወደ ስራው ሲመለስ ውሉ ተቋርጦ በቆየበት ጊዜ ያለው ደሞዝ ጭምር ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የተሻሻለው የአ/ብ/ክ/መ/የመግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 አንቀጽ 81/2/፣87/1 | 104351 | ወ/ት ክምክም እማኛው<br>እና<br>የደቡብ አቸፈር ወረዳ ሲቪልሰርቪስ ጽ/ቤት | ሠኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም | 64 |
| **የፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት** | | | | | 69 |
| 16. | አንድን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት ፍርድ ቤት በቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ አግባብነት ያላቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ወይም አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ሳይቀርቡ በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ መስጠት የማይቻል በሚሆን ጊዜ ፍ/ቤቱ እነዚህ ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት ትእዛዝ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ፡-<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(1) እና 245(1) | 105869 | አቶ ደብሬ ቡልቲ<br>እና<br>ዳንሹቱ ዋጋሪ | መጋቢት 15 ቀን 2007ዓ.ም | 70 |
| 17. | ለክርክሩ መነሻ የሆኑ እና በተከሳሽ እጅ የሚገኙ ንብረቶች እንዳይሸጡ፣ እንዳይለወጡና በማንኛውም መንገድ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ በታገዱበት ሁኔታና ተከሳሽ በንብረቶች ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተከሳሽን ተጨማሪ ዋስ አቅርብ ማለት አግባብነት የሌለውና የስነ | 99642 | ቴራ ኮንስትራክሽን<br>እና<br>አቶ ሚካኤል ነገሠ | ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም | 75 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስርዓት ህጉን ዓላማ ያላገናዘበ ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 151 | | | | |
| 18. | አንድ ተከራካሪ ወገን ሌላ ተከራካሪ ግለሰብ ወደ ክርክር እንዲገባ በህጉ አግባብ መጠየቁ ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ከግለሰቡ መብት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት ህጉ ዓላማና ግብ አንፃር ጭምር ስለመሆኑ፣ | 96943 | እነ አቶ ተስፋዬ ወርቁ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>እነ ወ/ሮ የምስራች ገ/መስቀል /አራት ሰዎች/ | ሚያዚያ 16 ቀን 2007 ዓ.ም | 78 |
| 19. | በመርህ ደረጃ በህግ አግባብ የተቋቋመ ፍ/ቤት የሠጠው ውሳኔ በህግ አግባብ በተቋቋመ የበላይ ፍ/ቤት በህጉ በተዘረጋው ስርዓት እስካልተለወጠ ድረስ የማይፈጸምበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378፣372፣392 | 101345 | አቶ ፀጋዬ ብርሃኑ<br>እና<br>ወ/ሮ መሠረት ተገኝ | መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም | 83 |
| 20. | ለአንድ የመንግስት ተቋም የተላከ መጥሪያ መጥሪያው በአግባቡ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ካልደረሰ በስተቀር መጥሪያው ለተቋሙ መዝገብ ቤት ገቢ በመሆኑ ብቻ መጥሪያው እንደደረሠ ተቆጥሮ ክርክሩ ተቋሙ በሌለበት ሊታይ የማይገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ሥ/ህ/ቁ 70/ሀ/፣78/2/፣96፣102 | 100673 | አቶ አዳነ መንገሻ<br>እና<br>የጋሪ ማዘጋጃ ቤት | ሠኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም | 88 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 21. | በሌለሁበት የተሰጠ ውሳኔ /ትእዛዝ/ ይነሳልኝ በማለት የቀረበ አቤቱታው ውሳኔው/ትእዛዙ ከተሰጠ በ30 ቀን ውስጥ በቃል መሀላ ለሬጅስትራር የቀረበ ሆኖ እያለ አቤቱታው ለችሎት የቀረበው ከ30 ቀን በኂላ መሆኑ በህግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ /ይርጋ/ አላሟላም ሊያስብል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78/1/ | 101478 | የረር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ባልቻ | ሰኔ 29 ቀን 2007ዓ.ም | 92 |
| 22. | በወጪና ኪሳራ ጉዳይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 466 | 98593 | አቶ ክንፈ ወልደሰንበት<br>እና<br>እነ አቶ ስለሺ በቀለ (ሰበት ሰዎች) | ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም | 96 |
| 23. | በካሳ ጉዳይ ካሳ የጠየቀው ወገን ገንዘቡን በማስረጃ ባላረጋገጠበት ሁኔታ ሌላኛው ተከሳሽ ወገን ዝም በማለቱ ብቻ እንዳመነ ተቆጥሮ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢ ያለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 83 | 111599 | እነ አቶ መላኩ ካሳዬ<br>እና<br>ወ/ሮ ሱሲ አሲ | ቀን 29/11/2007 ዓ.ም | 100 |
| 24. | የአንድ ክስ ዝርዝር ይዘቱ ሳይታይ እርስቱ ብቻ ታይቶ የፍርድ ቤት የሥረ ነገር ዳኝነት የሚወሰንበት የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ ስርዓቱን ጠብቆ አቤቱታ እስከቀረበበት ድረስ ሊፀና የማይገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(ለ) | 102543 | ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 አስተዳደር ፅ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሮ አሰለፈች ወልዴ | ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. | 104 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 25. | የፍትሐ ብሔር ክርክር በሂደት ላይ እያለ ከሰሽ ወይም ተከሳሽ በሞት ሲለይ የክርክሩ አካሄድ በምን አኳኃን መመራት እንዳለበት ልንከተለው ስለሚገቡ ሁኔታዎች<br><br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 48፣49 እና 50 | 105626 | አቶ ለገሰ ደበባ ተተኪ ሚስት ወ/ሮ ክቡ ዳሜ<br>እና<br>ኢትዮጵያ ሜዲዩስ ኃለ/የተ/የግ/ማህበር | ሐምሌ 28 ቀን 2007ዓ/ም | 108 |
| **ቤተሰብ** | | | | | 112 |
| 26. | ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ለሚኖሩ ሰዎች የሚፈለገው ማስረጃ ወንዱና ሴትየዋ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሠቡ እንደተጋቢ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው የሚገምቷቸው መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ፣<br>በአንድ ወንድና ሴት መካከል ለተወሰነ ጊዜ የፍቅር ግንኙነት መኖሩ ብቻ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ናቸው ሊያስብል የማይችል ስለመሆኑ ፣<br>አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 97፣98፣99 እና 106/2/ | 96853 | አቶ ጆቫኒ ላሮዛ<br>እና<br>ወ/ሮ አዳነች ተስፋዬ | መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም | 113 |
| 27. | አንድ ወንድና ሴት ሲጋቡ በጋብቻ ውላቸው ንብረትን በተመለከተ ካደረጉት ስምምነት ላይ "ከወለደች የግል የለባትም " ፣ " ሀብትሽ ሀብቴ ነው " ተብሎ የተፈጸመው የውል ሀረግ ካለና ልጅ ከወለዱ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን የግል ንብረት የጋራ ለማድረግ እንደተስማሙ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣ | 98029 | ወ/ሮ ልዩሴት ሥዩም<br>እና<br>አቶ ሽዋፈራ ንጉሴ | ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም | 121 |
| 28. | በጋብቻ ፍቺ ጊዜ ለፍችው ምንክያት የሆነው በደል ተፈጽሞባታል ተብሎ ለአንደኛው ወገን ካሣ የሚከፈለው እንዲከፍለው ዳኝነት ሲጠይቅና | 101552 | ወ/ሮ ትርንጎ መስፍን<br>እና | ሠኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም | 126 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ካሣውም የሚወሰነው ለፍትህ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 81/2/፣84 | | አቶ ሙሉጌታ መኳንንት | | |
| 29. | አንድ ልጅ ሲወለድ ከልጁ እናት ጋር በጋብቻ ተሳስሮ የነበረው ሠው በህጉ ግምት መሠረት የልጁ አባት ስለመሆኑና ይህን የህጉን ግምት ማስተባበል የሚችለው እሡ ወይም በህግ የተፈቀደላቸው ሰዎች አባት አለመሆኑ እንዲወሰን የመካድ ክስ በማቅረብ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ህ/ቁ. 682፣741፣ የፌደራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 167 | 99954 | እነ ህጻን ዘውዴ ሚካኤል<br>እና<br>አቶ ዝናዬ ወ/ሚካኤል | ሠኔ 5 ቀን 2007 ዓ.ም | 130 |
| 30. | አንድ ሞግዚት አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ በማስተዳደር ስልጣኑ ክርክር የሚደረግበት ጥቅም ከ300 ብር ያነሰ ካልሆነ በቀር ያለ ቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፈቃድ ምንም ግልግል መፈጸም የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ህ/ቁ. 301 | 100426 | እነ ዶ/ር ጥላሁን ኪሮስ /2ሰዎች/ እና<br>እነ ህጻን ሰናይ የማነኪሮስ /2ሰዎች/ | ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም | 135 |
| 31. | ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ባንደኛው ተጋቢ ተገዝቶ ነገር ግን ስመሀብቱ ከ3ኛ ወገን ሻጭ ሳይዛወር የቀረ መሆኑ ንብረቱ የተጋቢዎች የጋራ ሀብትነው ከመባል የሚያስቀረው ስላልመሆኑ፣ | 94811 | አቶ ታረቀኝ ጥሩነህ<br>እና<br>ወ/ሮ ሰናይት ታደሰ | ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. | 140 |
| 32. | ባል እና ሚስቶች ሲጋቡ ለጎጆ መውጫ ተብሎ በቤተሰባቸው ፍቃድ የተሰጣቸው መሬት ሲገለገሉበት የቆዩ በሆነ ጊዜ ንብረቱ የጋራ ሀብት ሆኖ በፍቺ ጊዜ እኩል ሊካፈሉት የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የመሬት አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀጽ 5/5/,2/7/ | 107840 | ወ/ሮ ዘምዘም ሽረፋ እና እነ ወ/ሮ አታላ ሐሰን | ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም | 144 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 33. | አንድ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ስምምነት ፈርሶአል ሊባል የሚችለው የፍቺ ስምምነቱ ተደርጎአል በተባለበት ቀን ሳይሆን የፍቺ ስምምነቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ባገኘበት እና በጸደቀበት ጊዜ ስለመሆኑ፡- <br><br> የተሻሻለው የፌድራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 76(1) | 109731 | ወ/ሮ ሄና አሰፋ <br> እና <br> አቶ ክፍይበሉ አሰፋ <br> (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 1 ቀን 2007ዓ.ም | 147 |
| **ውርስ** | | | | | **152** |
| 34. | በአንድ የጋራ የሆነ የውርስ ንብረት ላይ አንደኛው ወራሽ ብቻውን ያወጣው ወጪ ካለ ወጪውን ሁሉም ወራሾች ሊጋሩት የሚገባ ስለመሆኑ፣ <br> የጋራ የሆነ የውርስ ንብረትን በተመለከተ ወራሾች የሚስማሙ ከሆነ ክፍያው በስምምነታቸው መሠረት የሚፈጸም ስለመሆኑ፣ <br> ወራሾች ንብረቱን ስለሚካፈሉበት ሁኔታ ካልተስማሙና ንብረቱ በአይነት ለወራሾች ለማካፈል የማይቻል ከሆነ ንብረቱ በሀራጅ ተሸጦ ሊከፋፈሉ የሚገባ ስለመሆኑ፣ <br> የፍ/ህ/ቁ 1079/1/፣ 1086/1/፣1092፣1093 | 102932 | እነ አቶ አፈወርቅ ደረጫ /ሁለት ሰዎች/ <br> እና <br> ወ/ሮ ሠራዊት ደረጫ | ሠኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም | 153 |
| 35. | የውርስ የይዞታ መሬትን እኩል መብት ካላቸው ወራሾች መካከል አንደኛው አስቀድሞ ይዞ ወደ ልጁ ስም ማዞር የወራሾችን መብት መንጠቅ ስለመሆኑ፣ <br> የኦሮሚያ የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 <br> ደንብ ቁጥር 151/2005 | 108106 | አቶ አዱኛ ጉታ <br> እና <br> እነ ወ/ሮ በሻዱ ጉደታ | መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም | 158 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 36. | ፍ/ቤቶች የወራሽነት ማስረጃ ወይም የምስክር ወረቀት ብቻ እንዲሰጡ ማመልከቻ ሲቀርብላቸው ውርስ እንዲጣራ የሚሰጡት ትእዛዝ የማይገባና አላስፈላጊ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሕ/ 996/1/ | 110022 | አ/ቶ ትሻገር ምህረቴ<br>እና<br>የለም | ሐምሌ 29 ቀን 2007 ዓ.ም | 162 |
| 37. | በስጦታ ሰጪ ላይ በተደረገ የመንፈስ መጫን የተደረገ የስጦታ ውል ይፍረስልን ጥያቄ መቅረብ ያለበት ስጦታው በተደረገ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ<br>አጠቃለይ የሥጦታ ውልን በመቃወም የይፍረስልን ጥያቄ መቅረብ ያለበት በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ.2441፣በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1845 | 105652 | እነ ወ/ሮ አሰፉ ዘለቀ (ሰባት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ዳዊት በርሄ | 30/11/2007ዓ.ም | 165 |
| 38. | ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት ወራሽ መሆኑን በማስረጃ ያረጋገጠ ሰው ከአውራሹ ተነጥሎ ለጊዜው ውጭ ሀገር ሄዶ መመለሱ በሕጉ “ለቤተሰብ አባል” የተቀመጠውን ትርጉም አላሟላም በሚል በቤተሰብ አባልነት መሬቱን ሊወርስ አይገባም ማለት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የአ/ብ/ክ/መ አዋጅ ቁጥር 133/98 ፣ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/7/ሀ/ | 109697 | ዘሙ አስፋው<br>እና<br>መሀመድ አስፋው | ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም | 169 |
| **ውል** | | | | | |
| 39. | አንድ ሥራ ተቋራጭ በሠራው ህንጻ ላይ የተከሠተ እርግጠኛ የአሰራር ጉድለት በሌለበት ሁኔታ ወደፊት የሚታይና የሚከሰት የአሰራር ጉድለት ሊኖር ይችላል በሚል ምክንያት ሥራ ተቋራጮች ለሰሩት ሥራ የመጨረሻ ክፍያ የማግኘት መብት መከላከል አግባብነት የሌለው ስለመሆኑና የህንጻ ተቋራጩን በፍትሐብሄር ጉዳይ ማንም ሰው ኃላፊ ነው ተብሎ ያለመገመት | 101378 | የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን<br>እና<br>ናሰው ኮንስትክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር | ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም | 172 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | /presumption of non liablity/ መሠረታዊ መርህ ስለመሆኑ፣<br><br>የፍትሐብሔር ህግቁጥር 3268፣3282/1/<br>የመሠረት ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በ1996 ዓ.ም አሻሽሎ ያወጣውን የመንግስት ግንባታ ስለ አፈጻጸም መመሪያ አንቀፅ 8፣ | | | | |
| 40. | ተወካይ የጥቅም ግጭት ባለበት አኳኋዋን የፈጸመውን ተግባር ለማፍረስ ወካዩ ይኸው ድርጊት መፈጸሙን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ሕ/ቁ 2187 | 82725 | እነ አቶ ከበደ ተሰማ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ፀሀይነሽ ገ/አምላክ /ሁለት ሰዎች/ | ሠኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም | 178 |
| 41. | አንድ የሽያጭ ውል በፍርድ ፈራሽ ነው ተብሎ ተዋዋዮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ከተወሰነ ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰው ንብረቱን ለውጦ ወይም በዚህ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ከዚህ መለዋወጥ ወይም ወጪ የተነሳ ያለውን መብት በተመለከተ አለአግባብ መበልጸግ በሚለው የህጉ ክፍል መሠረት የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ህ/ቁ 1818፣የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 392/1/ | 99634 | አቶ ተስፋአለም አረፋ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አማረች ጉደታ /ሁለት ሰዎች/ | ሠኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም | 182 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 42. | ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠርን አለመግባባት በዘመድ ዳኛ የመጨረስ ስምምነት ማድረግ የሚችሉ ስለመሆኑ፡-<br>የዘመድ ዳኛ አለመግባባቶችን አይቶ የመወሰን ስልጣን የሚመነጨው ተገልጋዮቹ በግልፅ እና በማያሻማ ሁኔታ በሚሰጡት ሥምምነት ላይ ብቻ ስለመሆኑ፡-<br>የፍ/ሕ/ቁ 3325፣3326-3346 | 97021 | መርዕድ ታደሰ ገ/መደህን ህንፃ ተቋራጭ<br>እና<br>ኦክስፎርድ አመልጌት ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ሐምሌ 28 ቀን 2007ዓ.ም | 187 |
| 43. | የማማከር የስራ ውል ልዩ ፎርም የሚያስፈልገው ሥለመሆኑ፡-<br>የፍ/ሕ/ቁ 1719፣2612(1)፣1882 | 103541 | ቢ.ውቲ ግሪን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግ/ማህበር<br>እና<br>ቪክስ ሰመር ፍላወር | ሐምሌ 3 ቀን 2007ዓ.ም | 193 |
| 44. | ባዶ መሬትን ለማስተላለፍ የሚደረግ የሽያጭ ውል /የመሬት ግብይት ውል/ ፍሬ ነገሩ ሕገወጥ ሥለመሆኑና እና የዚህን አይነት ውል ከጅምሩ እንደሌለ ወይም እንዳልተደረገ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ህገመንግስት አንቀፅ 40(3)<br>የፍ/ሕ/ቁ.1716(1) | 100671 | l አለቃ ጌትነት ርቆ<br>እና<br>ወ/ሮ ጀሚላ አሊ | ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም | 197 |
| 45. | በተዋዋይ ወገኖች የነበረን ውል አንዱ ለሌላኛው የውል መለዋወጥ ጥያቄውን ማቅረቡ በፍሬ ነገር ደረጃ ሳይረጋገጥ ውሉ ተራዝሟል ሊባል የማያስችል ስለመሆኑ፡-<br>የውሉ አጻጻፍ ፎርም ወይም ዓይነት በሕግ የታዘዘ ሆኖ እንደ ትዕዛዙ ባይፈጸም ፈራሽነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፡- | 102778 | ስማድል ኮሙኒኬሽን ተርሚናል ፋብሪካ ኃ.የተ.የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ የሺጥላ ደሳለኝ | ሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም | 201 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሕ/ቁጥርየፍ/ሕ/ቁ 1684፣1722፣1678(ሐ)) | | | | |
| **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | | 208 |
| 46. | ለአንድ ጉዳት ወይም አደጋ መድረስ ጉዳት የደረሰበት ሰው አስተዋፅዋኦ ካለው የጉዳት አድራሹ ኃላፊነት በከፊል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ህ/ቁ 2098/1/፣ 2097/2/፣2095 | 106450 | የኢት/ኤሌ/ኃይል አገልግሎት ትመቂ ዲስትሪክት<br>እና<br>እነ በሳናናማ<br>/ሦስት ሰዎች/ | ሚያዚያ 15 ቀን 2007 ዓ.ም | 209 |
| 47. | በአንድ ንዑስ የስራ ተቋራጭ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራ ሰራተኛ ለሚደርስበት ጉዳት ዋናው ሥራ ተቋራጭ ከውል ውጪ በኃላፊነት የሚጠየቅበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ህ./ቁ 2027-2136 | 106147 | እሸት ኢንጂነሪንግሀ /የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ፋንታዬ ቢያድግልኝ | ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም | 213 |
| 48. | በአንድ ተቋም /መንግስታዊም ሆነ በባለስልጣን የተፈቀደለት/ ባለቤትነት የሚያካሄደው አደገኛ ተግባራት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ በሆነ ጊዜ ድርጅቱ ስራው በህግ የሚጠበቅበትን ደረጃ ያሟላ ስለመሆኑ እና በከፊልም ሆነ በሙሉ የተጎጂ ጥፋት መኖሩን እስካላስረዳ ድረስ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2069/1/ /2/ እና 2086/2/ | 101229 | የኢት/ኤሌ/ኃ/ኮ<br>እና<br>አቶ ጣሂር ሣፋይ | ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም | 216 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 49. | በሌላ ሰው የስራ ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አለአግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠን ለባለሃብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው ይህ አድራጎት ባደረሰበት ጉዳት መጠን ኪሳራ መክፈል የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ.2162 | 90529 | አቶ ኃ/እየሱስ መንግስቴ<br>እና<br>አማኑኤል ፀጋ የከተማ ሱቅ ቤቶች ልማት አክሲዮን ማህበር | ሐምሌ 2 ቀን 2007 ዓ.ም | 221 |
| **ወንጀል** | | | | | **229** |
| 50. | አንድ ሰው የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመው ከሌላ ሰው ስምምነት በማድረግ ከሆነ እንደማክበጃ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 ከመውጣቱ በፊት በተፈፀመ ወንጀል ቅጣትን ለመወሰን ለተከሳሹ የሚጠቅመውን የቅጣት መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>ወ.ሕ/ቁ. 38(1) እና 84(1)(መ) | 105289 | አቶ ተፈሪ ጥላሁን<br>እና<br>የፌድራል ዓቃቢ ህግ | መጋቢት 15 ቀን 2007ዓ.ም | 230 |
| 51. | በተደጋጋሚ በተፈፀመ የወንጀል ድርጊት የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው የወንጀል ድርጊት ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ድርጊት ለረጅም ጊዜ ሲፈፀም የቆየ ከሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የወንጀል ድርጊቱ ካቆመበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ<br><br>ወንጀል ህግ ቁጥር 219(2) | 105406 | አቶ ሃይሉ ወልዴ መኮንን<br>እና<br>የፌድራል ዓቃቢህግ | መጋቢት 14 ቀን 2007ዓ.ም | 235 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 52. | በወንጀለኛ ህግ አንቀፅ 692(1) መሰረት የማታለል ተግባር ተፈፅሟል ለማለት መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎች<br>አንድ ሰው ለወንጀል ድርጊት ኃላፊ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው ወንጀሉ መሰራቱ ወይም መፈፀሙና ተሰራ ወይም ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(4)፣32፣40፣57 እና 58(1)<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ/. 141፣142 እና 149 | 104923 | ወ/ሮ አበባ አረፋይኔ<br>እና<br>የትግራይ ክልል ዓቃቢ ህግ | መጋቢት 28 ቀን 2007ዓ.ም | 240 |
| 53. | የተከሰሱ ሰዎች በህግ የተጠበቀላቸው የመሰማት መብት ቀሪ የሚሆነው ህጉ በዘረጋው ስርዓት ባለመብቱ ሳይጠቀምበት ሲቀር ብቻ ስለመሆኑ<br>በህግ የተዘረጋ የክርክር አመራር ሳይሟላ የሚሰጥ ዳኝነት የግልፅነት መርህን የሚቃረንና በውጤቱም የተከራካሪ ወገንን መሰረታዊም ሆነ ሥነ-ሥርዓታዊ መብት የሚጎዳ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ስላለመሆኑ ፣<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 20/4/፣9/4/፣13/1/2/<br>የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አለም አቀፍ ቃልኪዳን አንቀፅ 14/3/ለ/ | 95921 | አቶ ብርሃኑ ኑርጋ<br>እና<br>የፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን | ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም | 246 |
| 54. | አንድ በወንጀል የተከሰሰ ተከሳሽ መጥሪያ ባስመዘገበው የመኖሪያ አድራሻ እንደደረሰው ሳይደረግ ወይም በዚሁ አድራሻ ተፈልጎ ሊገኝ አለመቻሉ ሳይረጋገጥ መጥሪያ በጋዜጣ እንዲወጣ አድርጎ ጉዳዩን በሌለበት ማየት የስነ ስርዓት ህጉን ያልተከተለ ስለመሆኑ፣ | 104220 | አቶ አታክልቲ አብርሃ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም | 252 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበባቸውን ምስክሮች የመለየት፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀፅ 20/4/<br>የወ/መ/ሥ/ሥነሥርዓት አንቀፅ 199 /ሀ/ ፣ 123፣202/3/፣ | | ሁመራ ቅርንጫፍ | | |
| 55. | አንድ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠበት የህግ ድንጋጌ ስር ከተቀመጠው የቅጣት አማራጭ ውጪ የሚሰጠው የቅጣት ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ፣ | 97291 | አቶ ጎሹ ዮሐንስ<br>እና<br>የፌ.የሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ | ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም | 256 |
| 56. | በወንጀል ጉዳይ መነሻ ቅጣቱ በቅጣት መመሪያው ውስጥ በተለያዩ እርከኖች የሚወድቅ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ፍ/ቤቱ ዝቅተኛውን እርከን መምረጥ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የቅጣት መመሪያ 2/2006 አንቀጽ 19/11/ | 103775 | ሀብቱ ቱሉ ዳዲ<br>እና<br>የፌደራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | ሰኔ 15 ቀን 2007ዓ.ም | 264 |
| 57. | አንድ ሰው በሌለበት በወንጀል የተፈረደበት እንደሆነ ፍርድን ባወቀ በሠላሳ ቀናት ውሥጥ ፍርዱ ወድቅ እንዲደረግለት የማቅረብ መብቱን ሬጂስትራሉ አቤቱታውን አልቀበልም በማለት ሊከለክለው የማይችል ስለመሆኑ፡- | 98014 | አቶ ያረጋል ተስፋ አባተ<br>እና<br>ቤንሻንጉል ጉምዝ ክ/ዓ/ህግ | ሐምሌ 14 ቀን 2007ዓ.ም | 270 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.198፣200 እና 201<br>የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 20 | | | | |
| 58. | አንድ የወንጀል ድርጊት ሊወድቅ የሚችልበት የህግ ድንጋጌ የተለያዩ የማክበጃ ነጥቦች በያዘ ጊዜ እና ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት አንቀጽ /ድንጋጌ/ ስር ያሉት ንዑስ ድንጋጌዎች የሚደነግጉት የቅጣት መጠን ተመሳሳይ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በዚያው የህግ ድንጋጌ ስር ድርጊቱ በይበልጥ ያሚላቸውን የማክበጃ ነጥቦች ወደ ያዘው ንዑስ ድንጋጌ መለወጥ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ | 107219 | አቶ አህመድ ሰይድ መሀመድ<br>እና<br>የፌደራል ዐ/ህግ | ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም | 277 |
| 59. | ደረጃ እና እርከን ላልወጣላቸው ወንጀሎች ቅጣት ስሌት ሲሠራ በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል ስር ያሉት አንቀጽ 106/1/ እና 109/1/ ድንጋጌዎች ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ስለመሆኑ፣<br>አንድ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ወንጀሉን ስለመፈጸሙ ሙሉ በሙሉ ባላመነበት ሁኔታ በከፊል ማመኑ ብቻ ራሱን ችሎ እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ ሊወሰድለት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/ቁ 82/ ሠ | 111006 | ዲቦ ገልግሎ ቴራ<br>እና<br>የፌ/ን/ስ/ላ ዐ/ሕግ | ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም | 283 |
| 60. | ፍርድ ቤቶች በተከሳሽ ላይ በዕምነት ክህደት ላይ በመመስረት የጥፋተኝነት ውሳኔን ከመወሰናቸው በፊት ቃሉ ከወንጀሉ ዝርዝር እና ከተከሰሱበት የህግ ድንጋጌዎች አነጋገር አንጻር ወንጀሉን ማድረጉን ሙሉ በሙሉ አምኗል የሚያስብል እና ቃሉ የእምነት ክህደትን ቃል የሚያቀቋቁም መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባቸው ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 132/1/ እና /3/ | 111742 | እነ ኮሎኔል ተክሉ ፍሰሀ<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ዐ/ሕግ | ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም | 287 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 61. | ፍ/ቤቶች የተከሳሽን የመከላከል መብት የማክበርና የማስከበር ህገ-መንግስታዊ ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ህገ መንግስት አንቀፅ 13(1)፣13(2)፣20(4)<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 142(1)<br>ዓለም አቀፍ የማህበራዊና ፖለቲካ መብቶች ሥምምነት አንቀፅ 14(3)(ረ) | 100860 | አቶ ፋንቱ ቡቼ<br>እና<br>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ዓቃቤ ህግ | ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም | 291 |
| 62. | የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196(1) ለሰበር ሥርዓትም ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑ | 101056 | አቶ አይሸሽም ገብሬ<br>እና<br>የፌድራል የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሺን | ሐምሌ 30 ቀን 2007ዓ.ም | 298 |
| 63. | የወንጀለኛ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 75 (1)ዋስትናን በመፍቀድ በሚሰጥ ትዕዛዝ ላይ ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ እንዳያቀርብ ሕጉ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ከልክሏል በሚል አግባብ መተርጎም የሌለበት ስለመሆኑ<br>ዋስትናን በመፍቀድ በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ከሳሽ /ዐቃቤ ህግ/ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ | 110969 | አቶ ሀብታሙ ደጁ<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቢ ሕግ | ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም. | 308 |
| **ጉሙሩክ/ታክስ** | | | | | **311** |
| 64. | ገቢውን በሚደብቅ ፣አሳንሶ በሚያሳውቅ፣ በሚያጭበረብር ወይም በማናቸውም መንገድ ግብር ሳይከፍል በሚቀር ግብር ከፋይ ላይ በተጨባጭ መረጃ በመደገፍ ሪፖርት ያቀረበ ሰው ከተደበቀው ግብር እስከ 20% ድረስ ግብሩ ሲሰበሰብ ማግኘት የሚገባው ስለመሆኑ፡- | 95157 | የኢትዮ.ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>እነ አቶ ቅባቱ ወ/ሰንበት(ሦስት ሰዎች) | ሐምሌ 15 ቀን 2007ዓ.ም | 312 |

| ተ. ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀፅ 84(1) | | | | |
| 65. | አንድ ተከሻሽ የጉሙሩክ አዋጅን በመተላለፍ በፈፀመው ድርጊት ጥፋቱ የመጨረሻ ውሳኔ እስከላገኘ ድረስ ሥራ ላይ ከነበረው የጉሙሩክ አዋጅ ይልቅ አዲሱ የጉሙሩክ አዋጅ ለተከሳሽ ቅጣትን የሚያቀል በሚሆን ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ የተሻለው ህግ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ<br><br>የኢፌድሪ ህገመንግስት አንቀጽ 22 /2/ ፣የወ/ህ/ቁ/ 6<br>የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001፣ አዲሱ የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 | 112032 | የኑስ አህመድ /ሁለት ሰዎች/ እና የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት | ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ/ም | 318 |
| **የዳኝነት ሥልጣን** | | | | | 324 |
| 66. | አንድ በፌደራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ድርጅት በክልል ቅርንጫፍ ከፍቶ የንግድ ሥራ መስራቱና ቅርንጫፍ በክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ፅ/ቤት መመዝገቡ በፌደራል መንግስት የተቋቋመ የንግድ ድርጅት በመሆኑ ላይ የሚያሳድረው ለውጥ የሌለ ሥለመሆኑና ድርጅቱ ተካፋይ የሆነበትንም ክርክር በዳኝነት አይቶ ለመወሰን ሥልጣኑ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀፅ 6/2/ /3/ /4/ ፣ አንቀፅ 5/2/ | 97083 | ገአትኮ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የትግራይ ክልል መንገድ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ | ሚያዚያ 14 ቀን 2007 | 325 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁጥር 25/1988/6/<br>የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀፅ 80/2/ /4/ | | | | |
| 67. | የግለሰብ ዓለምአቀፍ ህግን / private international law/ የሚመለከቱ ጉዳች ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 25/1988 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 11/2/ /ሀ/ | 100290 | ወ/ሮ መሠረት አለማየሁ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ እመቤት ሙሉጌታ<br>/ሁለት ሰዎች/ | ሚያዚያ 1 ቀን 2007 ዓ.ም | 329 |
| 68. | የአንድ የእምነት ተቋም አስተዳደራዊ ስራዎችን ለማከናወን የተሰጠ ሹመትና የሽረት ጉዳይ ከሀይማኖት ተቋሙ መሰረታዊና ተፈጥሯዊ ባህሪ ተነጥለው ለብቻቸው ሊታዩና ሊወሰኑ የማይችሉ በመሆናቸው በፍርድ ሊወሰኑ የማይገባቸው ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገመንግስት አንቀፅ 11 እና 37 | 97009 | አቶ ኤልያስ አዳሙ<br>/ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የኢ/ትወንጌል ብርሃን ቤተ/ክርስቲያን | ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም | 334 |
| **ንብረት** | | | | | **340** |
| 69. | በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብትን ከባለይዞታው ጋር የስጋ ዝምድና ለሌለው ሰው ማስተላለፍ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የስጦታ አደራረግን አስመልክቶ በፍትሐ ብሔር የተመለከቱ ድንጋጌዎች በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም፣የማስተላለፍ እና አስተዳደር ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ክርክሮች ተፈፃሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ፡-<br>የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ. 130/1999 አንቀፅ 6 | 105092 | አቶ ብርሃኑ ከበደ<br>እና<br>አቶ ኢብራሂም ሹካ | መጋቢት 1 ቀን 2007ዓ.ም | 341 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፌድራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር አጠቃቀም አዋጅ.ቁ 456/19 | | | | |
| 70. | ከቤተሰባዊ ቅርርብ የተነሳ ውለታ ሳደረገ ሰው አንደኛው ወገን ካለው መሬት ውርስ ቆርሶ በስጦታ መልክ እንዲጠቀም ሰጥቶት በሁለቱ መካከል አለመግባባት ቢፈጠር በሥጦታ ተቀባዩ ወገን በመሬቱ የመብት ክርክር ቢያነሳ የመሬት ይዞታ ስጦታው ሊፀና የሚችለው የክልል የመሬት አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት ሥልጣን ባለው አካል ዘንድ ቀርቦ የስጦታ ውሉ መመዝገቡ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡<br>/የኦሮሚያ ክልል የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 | 109829 | አቶ ረታ አበበ<br>እና<br>ወ/ሮ ተሬ ደማ ተወካይ ሙሉጌታ አበበ | ግንቦት 18 ቀን 2007 ዓ.ም | 345 |
| 71. | የገጠር መሬት ወራሽነትን በሚመለከት በአንድ ወቅት በቤተሰብ አባልት መመዝገብ ብቻውን የሚችን የእርሻ መሬት በቀዳሚነት የመውረስ መብትን የማያጎናጽፍ ስለመሆኑ በውርስ ለማግኘት ወራሹ አርሶ አድርና ከእርሻ መሬቱ ከሚገኘው ገቢ የሚተዳደር የቤተሰብ አባል መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ 456/97 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 5<br>የኦሮሚያ የመሬት አዋጁ 130/99 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 13 እና 16/ | 109776 | እነ ወ/ሮ ይርጋለም<br>እና<br>ወ/ሮ አሰፉ ዘውዴ | ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ.ም | 349 |
| 72. | ፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ክፍል የተሰጠ የቤት ካርታ የተሰጠበት ወይም የተሻረበት ስርዓት እና አስተዳደራዊ ውሳኔው ህግና መመሪያ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን በማጣራት ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ህ/ቁ 1196፣የ.ኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 32 | 99071 | ወ/ሮ አብረኸት ድክሪያ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል | ሠኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም | 354 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| **ንግድ** | | | | | **358** |
| 73. | የሽርክና ማህበር በህግ አግባብ ተቋቁሞ እየሠራነው ለማለት በጽሁፍ ውል መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ተዋዋይ ወገኖች በጋራና በተናጥል በመተባበር በመስራት ከጥቅሙም ይሁን ከእዳው በጋራ ሲጋሩ እንደነበር መረጋገጥ ያለበት ሥለመሆኑ፣<br>አንድ የሽርክና ማህበር በህጉ አግባብ ተቋቁሞ ለማለት የሚቻለው ተዋዋይ ወገኖች ተነጻጻሪ ሣይሆን ተደጋጋፊ የሆነ ግብ ይዘው መዋጮ በማውጣት አብረው በመስራትና በመተባበር ትርፍና ኪሣራም በህጉ አግባብ እየተጋሩ ኢኮኖሚያዊ ተግባር ማከናወናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>የንግድ ህግ ቁጥር 211፣229፣269/1/ | 94481 | ወ/ሪት ፀሐይነሽ በቀለ<br>እና<br>ወ/ሪትንግስት ተክላይ | ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም | 359 |
| 74. | የሽርክና ውል ስምምነት አለ ለማለት መሟላት ሥለሚገባቸው መስፈርቶች<br>የንግድ ህግ 5፣10(1)፣210(1)፣211፣215 እና 229(2) | 96990 | አቶ አያሌው ወልዴ ዮሃንስ<br>እና<br>አቶ ጀማል ሰማን ኑር | ሐምሌ 01 ቀን 2007ዓ.ም | 364 |
| 75. | በሞተ ሰው ሥም የተመዘገበን የአክስዮን ድርሻ ላይ ሟቹ እንደተገኘ ተቆጥሮ የሚተላለፍ ውሳኔ አግባብነት የሌለው ሥለመሆኑ እና ተፈፃሚነት ያለው በንግድ ህጉ የተቀመጠው የሦስት ወር ጊዜ ሳይሆን በፍ/ሕ/ቁ 1845 የተመለከተው የአስር ዓመት ይርጋ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ.416<br>የፍ/ሕ/ቁ.1845 | 100621 | አቶ ልዑልሰገድ ሞጆ<br>እና<br>እነ አንድነት ቅቤና ቅመማ ቅመም ነጋዴዎች | ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ.ም | 368 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 76. | በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት በልዩ ሁኔታ በንግድ ቤት ተጠቃሚ ለመሆን ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔዎች | 102725 | እነ አቶ ዲንሳፋ ያዕቆብ/ሦስት ሰዎች/ እና ወ/ሮ አየለች በቀለ | ሓምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም | 372 |
| 77. | የህብረት ሥራ ማህበራት በመሰረታዊነት ለትርፍ ተብሎ የሚቋቋሙ ሳይሆን የአባላቱን ፍላጐት በአነስተኛ ወጪ ለሚሟላት የሚቋቋሙ በመሆኑ ለትርፍ ስራ የሚሰሩ የንግድ ስራዎች የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ፋቃድ እንዲያወጡ የሚገደድበት አግባብ የሌለ ሥለመሆኑ<br><br>የኃብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ማሻሻያው አዋጅ ቁ. 402/96 አንቀጽ 6 | 103717 | የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሰራተኞች ሸማቾች ህብረት ስራ ኃ.የተ.የግል ማህበር እና የአዳማ ወረዳ ንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት | ሐምሌ 03 ቀን2007 ዓ.ም | 378 |
| **አፈፃፀም** | | | | | 384 |
| 78. | ለአፈፃፀም መነሻ የሆነን ፍርድ ይግባኝ በመጠየቅ ሳያሽሩ ወይም ሳያሻሽሉ በዋናው ጉዳይ ሊነሱ የሚገባቸውን የክርክር ነጥቦች በአፈፃፀም በተያዘው መዝገብ የክርክር መሰረት ማድረግ ተገቢ ስላለመሆኑ | 98347 | ወ/ሮ በድሪያ መሐመድ እና አቶ አደም ዑመር | ሐምሌ 13 ቀን 2007 ዓ.ም | 385 |
| 79. | በሃራጅ ጨረታ ያሸነፈ አንድ አካል ያሸነፈውን ንብረት በስሙ ካዘወረና ካስተላለፈ በኂላ የሃራጅ ሽያጩ ሙሉ በሙሉ ከተፈፀመለት በኂላ፣ ንብረቱ በሃራጅ ከተሸጠበት ዋጋ ላይ እንዲቀነስለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፡- | 96588 | እነ ወ/ሮ አልማዝ አርዓያ(አራት ሰዎች) እና አቶ አሸናፊ አልታየ | ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም | 388 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.429፣441 እና 447 | | | | |
| 80. | የአፈፃፀም ችሎቶች ስለፍርድ አፈፃፀም የተዘረጉትን ሥርዓቶች በመከተል እንደ ፍርዱ ከመፈፀም በቀር የአንድ ፍርድ ይዘትን በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆነ በማስፋት ረገድ ፍርድን የመተርጎም ሥልጣን የሌላቸው ሥለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 372፣378 | 96814 | አቶ አብዶሽ አዲሽ እና ወ/ሮ ሰብለ ዘውዴ | ሐምሌ 14 ቀን 2007ዓ.ም | 393 |
| 81. | እኩል እንከፋፈል በሚል በፍ/ቤት የፀደቀን የቦታና ቤት ስምምነት እኩል ለማካፈል የከተማ አስተዳደሩ የፕላን ስታንዳርድን አያሟላም በተባለ ጊዜ የባልና ሚስትን የጋራ ሀብት በሀራጅ ተሸጦ ይካፈሉ ብሎ መወሰን የግራ ቀኙን በቤቱ የመጠቀም ፍላጎት /ነጻነት የሚገደብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ 277/1/,325,392 የአማ/ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ 79/95 አንቀጽ 73,74 101-103 | 104521 | ወ/ሮ ታንጉት ሠጠ እና አቶ ፋንቱ ትኩ | ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም | 399 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | **404** |
| 82. | ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦታ በሊዝ ለገዛ ሰው ቦታውን ለግንባታ ምቹ አድርጎ ማስረከብ ያለበት ስለመሆኑና በወቅቱ ካላስረከበ ካስረከበበት ጊዜ ጀምሮ የሁለት አመት የችሮታ ጊዜ ለገዥው ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ፣ መመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 14/3/ ፣ 37/6/ለ/ ፣ 38/8/ ደንብ ቁጥር 48/2004 አንቀፅ 11/1/ ፣ አንቀፅ 12/2/ | 97829 | አቶ ሁሴን ሰይድ እና የየካ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ፅ/ቤት | ሚያዚያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም | 405 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 83. | የጥብቅና አገልግሎት የሚሠጥ ጠበቃ በደንበኛው የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጸምለት ለተፈጸመው ክፍያ ደረሰኝ አለመስጠት የዲሲፕን ግድፈት ስለመሆኑ<br>አዋጅ 199/92 አንቀፅ 30/2/<br>ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 8/1/ | 107442 | አቶ ሞገስ ናደው እንዳይላሉ<br>እና<br>የኢፌድሪ ፍትህ ሚኒስቴር | መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም | 410 |
| 84. | የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ለመወሰን በልምድ የዳበረውና በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘው የአከፋፈል መርህ ጉዳዩ የወሰደው ጊዜ፣ የሚጠይቀው ድካም፣ የጉዳዩ ውስብስብነት የክርክርን ግምት ታሳቢ በማድረግ ስለመሆኑ፣ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ያለምንም ገደብስምምነት የሚደረግበት አለመሆኑን ከስነ ህግ እና የፍርድቤቶች አሰራር የዳበረ ስለመሆኑ፣<br>የአብክመ የጥብቅና ስራ ፈቃድ አሰጣጥ ምዝገባ የጠበቆች ስነ-መግባር ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 75/1994 አንቀፅ 50፣51፣52<br>የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 462 | 105765 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አቶ ግርማ ሞገስ | ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም | 416 |
| 85. | አንድ የፖለቲካ ድርጅት የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባል የሆኑ ሰዎችን አባልነታቸው ህጋዊ በሆነ መልኩ ሳይቋረጥ ወይም ቀሪ ሳይሆን እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አንድ ሰው በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ የሁለት የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 532/199 አንቀፅ 46፣102/4//ለ/፣አዋጅ ቁጥር 632/2002 አንቀፅ 7 | 112091 | አንድነት ለፍትህና ዲሞኬራሲ<br>እና<br>ሠማያዊ ፓርቲ | ሚያዚያ 28 ቀን 2007 ዓ.ም | 420 |

# ኸሠፈና ሠፉተኛ

የሰ/መ/ቁ.104862

መጋቢት 3 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች**፡-አቶ መልካሙ አረጋ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡-ተስፋዬ ለገሠ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ - ጠበቃ ይትባረክ መኮንን ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በ09/12/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሽ ከጥር 30 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 8,076 ደመወዝ እና ብር 100 አበል እየተከፈላቸው በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በዶዘር ኦፕሬተርነት የስራ መደብ ተቀጥረው በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ከ01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ በእርሳቸው ምትክ ሌላ ሰራተኛ በመቅጠር የስራ ውላቸው በቃል ያቋረጠባቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የስንብት እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች እና ያልተጠቀሙበትን የዓመት ዕረፍት ክፍያ በድምሩ ብር 106,381.00 ተከሳሽ እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ11/02/2006 ዓ.ም በሰጠው መልስ ከሳሽ በራሳቸው ከስራ ከመቅረታቸው ውጪ ተከሳሽ ያላሰናበታቸው መሆኑን፣ሁሉም ሰራተኞች ለተረከቡት የድርጅቱ ንብረት ዋስትና እንዲያቀርቡ ተከሳሽ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ ከሳሽ ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን፣ዋስትና ለማቅረብ ያላቸውን ፈቃደኝነት ከ21/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ እንዲያስታውቁ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ቢገለጽላቸውም ከሳሽ ይህንን ከማድረግ ፋንታ ከ21/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ በተከታታይ ከስራ መቅረታቸውን፣በ03/11/2005 ዓ.ም ቢሮ ተገኝተው ተመሳሳይ መልዕክት ቢነገራቸውም ያልፈጸሙ እና እንደገና ከ03/11/2005 ዓ.ም እስከ 08/12/2005 ዓ.ም ድረስ ስራ ላይ

አለመገኘታቸውን፣ከዚህ በኃላ ከሳሽ በ08/12/2005 ዓ.ም ቢሮ ቀርበው ስራቸውን በፈቃዳቸው መልቀቃቸውን በመግለጻቸው የተዘጋጀላቸውን ክፍያ እና የስራ ልምድ እንዲወስዱ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን፣በከሳሽ ምትክ ሌላ ሰራተኛ የተቀጠረው ከዚህ ሁሉ በኃላ በ05/01/2006 ዓ.ም. መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ የከሳሽ ምስክሮች ቃል ተከሳሽ ከሳሽን በቃል ከስራ እንዳሰናበተ የሚያስረዳ አለመሆኑን፣ከሳሽ ዋስ የሚጠሩ መሆን አለመሆኑን እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ እንዲያስታውቁ፣ይህ ካልሆነ ግን ስራቸውን በራሳቸው ፈቃድ እንደለቀቁ ተቆጥሮ የስራ ግንኙነቱን እንደሚያቋርጥ ተከሳሽ በ21/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ማስታወቂያ በይዘቱ ከሳሽ እስከተባለው ቀን ድረስ ሀሳባቸውን ካልገለጹ ተከሳሽ ከ30/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሉን እንደሚያቋረጥ የሚያመለክት መሆኑን፣የስራ ውላቸው ከ30/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እንደተቋረጠ የሚቆጠር ከሆነ ደግሞ ከዚህ ቀን በኃላ ከሳሽ በስራ ቦታው የሚገኙበት ምክንያት ስለማይኖር ከሳሽ በተጨማሪ ከ03/11/2005 ዓ.ም እስከ 08/11/2005 ዓ.ም ድረስ ስራ ላይ አልተገኙም በማለት ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ከሳሽ ከ21/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ በመደዳው ከስራ መቅረታቸው የተረጋገጠ ቢሆንም ተከሳሽ ይህንን ድርጊት የማሰናበቻ ምክንያት አድርጎ በደብዳቤ እስካልገለጸ ድረስ ከሳሽ የተሰናበቱት በመደዳው ከአምስት የስራ ቀናት በላይ ከስራ በመቅረት በራሳቸው አነሳሽነት ነው ሊባል የሚችል አለመሆኑን፣በአጠቃላይ ከሳሽም በራሳቸው አነሳሽነት ሰራቸውን ስላልለቀቁ እና ተከሳሽም ስላላሰናበታቸው ስንብቱ ሕገወጥ መሆኑን ገልጾ በክሱ ከተጠየቀው ክፍያ ውስጥ ተከሳሽ ብር 79,189.66 ግብር ከተቀነሰ በኃላ ለከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሹ ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተከሳሽ በ21/10/2005ዓ.ም የሰጠው ማስታወቂያ በማስረጃነት የቀረበው በከሳሽ ሳይሆን በተከሳሽ በኩል ሆኖ እያለ እና የማስታወቂያው ይዘትም የስራ ውሉ በተከሳሽ አነሳሽነት መቋረጡን የማያረጋግጥ ሆኖ እያለ እንዲሁም ከሳሽ በመደዳው ከአምስት የስራ ቀናት በላይ ከስራ መቅረታቸው ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው በተከሳሽ አነሳሽነት ነው፣ስንብቱም ሕገወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በማሻሻል ተከሳሽ ከሕግ ውጪ የስራ ውሉን አቋርጧል በሚል የተሰጠውን እና ሕገወጥ የስራ የስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሽሮ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት

በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ዋስ ካልጠሩ ተጠሪው የስራ ውላቸውን እንደሚያቋርጥ ገልጾ የጻፈላቸው መሆኑ በተረጋገጠበት እና አመልካች ዋስ አለማቅረባቸው ባልተካደበት ሁኔታ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ክስ ያቀረቡት ተጠሪው ከ01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ በእርሳቸው ምትክ ሌላ ሰራተኛ በመቅጠር የስራ ውላቸውን በቃል ያቋረጠባቸው መሆኑን በመግለጽ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ አመልካችን እንዳላሰናበተ እና በራሳቸው ከስራ እንደቀሩ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡በመሰረቱ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ለክርክሩ ምክንያት የሚያደርጋቸውን ፍሬ ነገሮች የማስረዳት ሸክም እንዳለበት የሚታወቅ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ የአመልካች የምስክሮች ቃል ተጠሪው አመልካችን በቃል ከስራ እንዳሰናበተ የሚያስረዳ አለመሆኑን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተቀብሎ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በክሳቸው መሰረት አስረድተዋል ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡በአሰሪው በቃል ከስራ ተሰናብቻለሁ በሚል ክስ የሚያቀርብ ሰራተኛ ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43610 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪው ከ 01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ እንደሚያሰናብተኝ በ 21/10/2005 ዓ.ም በጻፈው ማስታወቂያ አረጋግጦ እያለ ስንብቱ ሕገወጥ አይደለም ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ አይደለም በማለት አመልካች ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ከ21/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ ከስራ መቅረታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ፣በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ለ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል ምክንያት በመሆኑ፣በዚህ ምክንያትም አመልካች የስራ ውላቸውን ከ30/10/2005 ዓ.ም በፊት በራሳቸው አነሳሽነት እንዳቋረጡ የሚቆጠር በመሆኑ እና ይህም ተጠሪው በ21/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ማስጠንቀቂያ ከ01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ የአመልካችን የስራ ውል እንዳቋረጠው የሚያመለክት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ የማንሳትን እና የመመርመርን አላስፈላጊነት የሚያስከትል በመሆኑ ተጠሪው የስራ ውሌን ከ01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ እንዳቋረጠው ሊቆጠር ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡አንድ ሰራተኛ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ካለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረቱ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ አሰሪው በዚሁ

ምክንያት ሰራተኛውን ካለማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበተው ስለመሆኑ በደብዳቤ ሳይገልጽ መቅረቱ በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) (ለ) መሰረት የስራ ውሉ በሕግ አግባብ አልተቋረጠም ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተደረሰበትን የተሳሳተ መደምደሚያ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማረሙ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል ይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 80816 በ 30/03/2006 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139450 በ 12/12/2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከለተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

**ሃ/ወ**

የሰ/መ/ቁ. 105921

ቀን 14/07/2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች**፡- ፒተርድስ ፕሮዳክስት ማንፋክቸሪንግ (አ.ማ) አልቀረቡም

**ተጠሪች**፡- 1. ወ/ሮ ይፍቱስራ ነጋሽ } ጠበቃ ኤሊያስ አበበ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ገነት ወንድሙ

**ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል**

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ አንደኛ ከሳሽ ፤ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነችው ወ/ሪት መድሀኒት ሙቃ ሁለተኛ ከሳሽ ሁለተኛ ተጠሪ ሶስተኛ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾች ተከሳሽን ለምንድን ነው ለእኛ የቦነስ ክፍያ የማይከፈለን በማለት በእረፍት ሰዓት በመጠየቃችን ከስራ አግዶ አቆይቶ ሚያዝያ 2 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ከህግ ውጭ ያሰናበተን ስለሆነ የካሳ ክፍያ ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ፣ ክፍያ የዘገየበት ክፍያና ወጭና ኪሳራ እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ሆኖ ቀርቦ ከሳሾች ህገ ወጥ የስራ አድማ እንዲያደርጉ ሌሎች ሠራተኞችን በማስተባበርና በመቀስቀስ ፤ የአድማ ስራ በመሆንና ረብሻና ሁከት የመፍጠር ሙከራ ማድረጋቸው ተረጋግጦ ከስራ የተሰናበቱ በመሆኑ ስንብቱ ህግን መሰረት ያደረገ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

2. የስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ በኩል ያቀረቡትን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተከሳሽ ከሳሾችን ከስራ ያስናበታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ሸ) መሰረት በመሆኑ ስንብቱ ህግን መሰረት ያደረገ ነው በማለት የከሳሾችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ተጠሪዎች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት አቅርበው የሰማቸውን ምስክሮች ቃል በሰፊው ፤ ከዘረዘርና ከመርመር በኋላ አመልካች የቦነስ ክፍያ የማይከፈል መሆኑን በማስታወቂያ በመግለጽ ፤ ሰራተኞች ለምን አይከፈለንም የሚል ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን ፣ አመልካች ሰራተኞችን በሁለት ከፍሎ ማነጋገር እንደጀመርና ይግባኝ ባዮች (ተጠሪዎች) መብታችን ይከበር በማለት መግለፃቸውን ፣ አመልካች ይህንን በመናገራቸው ምክንያት አድማ ቀስቅሰዋል በማለት ይግባኝ ባዮችን (ተጠሪዎችን) ከስራ ያገደና ያስናበታቸው መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ እንደሆነ ገልፆና አንደኛ ይግባኝ ባይ (አንደኛ ተጠሪ) ዘግይተው ወደስራ የገባች መሆኑና እሷ ስራ ከመግባቷ በፊት ሌሎች ሰራተኞች ቦነስ ለምን አይከፈለንም የሚል ጥያቄ ማንሳታቸውን በአመልካች (መልስ ሰጭ) ምስክር የተረጋገጠ መሆኑን በውሳኔው አስፍሮ ፣ በዕለቱ ይግባኝ ባዮች ፣ የተናገሩት ንግግር የመብት ጥያቄ እንጅ ህገ ወጥ የስራ ማቆም አድማ ቅስቀሳ አይደለም፡፡ ይግባኝ ባዮች ረብሻና ሁከት የመፍጠር ተግባር አልፈፀሙም በማለት ስንብቱ ህገ ወጥ ስለሆነ መልስ ሰጭ (አመልካች) ለይግባኝ ባዮች (ለተጠሪዎች) የስራ ስንብት ክፍያ ፣ የካሳ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች ጥቅምት 3 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ፣ በዕለቱ አመልካች ምርት ባለማምርቱ ፣ ኪሳራ እንደደረሰበት ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች ምስክሮች ቃል ተዓማኒነትና ክብደት በአግባቡ ሳይመዝን ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች ጥር 12 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ተጠሪዎች ህገወጥ አድማ ሰራተኛ ያነሳሳን ስለመሆኑ በማስረጃ እንዳላስርዳ በማረጋገጥ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የካቲት 5 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ያስናበተው ከህግ አግባብ ውጭ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የህግ መሰረት አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ፣ ማስርጃ የመመርመርና የመመዘን ስልጣኑን በመጠቀም

የደርሰበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ህገ ወጥ አድማ ተደርጓል በሚልበት ቀን ፣ የቦነስ ክፍያ እንደማይከፍል ማስታወቂያ በመለጠፍ ፣ የድርጅቱ ሰራተኞች ለምን ቦነስ አይከፈለንም? የሚል ጥያቄ ማንሳታቸውን ፣ አመልካችም በሰራተኞች ጥያቄ ምላሽ በመስጠትና ሰራተኞችን በሁለት ክፍሎ ያነጋገረ መሆኑን ፣ አመልካች ሰራተኞችን በሚያነጋግርበት ጊዜ ተጠሪዎች ፣ መብታችን ይከበር በማለት መናገራቸውን ፣ ከዚህ ውጭ ተጠሪዎች የፈጸሙት ፣ ተግባር የሌለ መሆኑንና አንደኛ ተጠሪ ወደ ስራ የገባችው ዘግይታ እንደሆነ አመልካች በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ስህተት በይግባኝ የመመርመርና የማረም ስልጣኑን በመጠቀም የደረሰበት የፍሬ ጉዳይና የማስርጃ ምዘና መደምደሚያ ያሳያል፡፡

6. ይህንን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የደረሰበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያን አመልካች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል ተአማኒነትና ክብደት ሲመዝን ፈጽሞታል የሚለውን ስህተት ፣ በሰበር ፣ የማየትና የማረም ስልጣን ለዚህ ሰበር ችሎት በህገመንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 አልተሰጠውም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የደርሰበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ዕውነት ነው ብለን በመቀበል ፤ ተጠሪዎች አመልካች ሰራተኞች በሁለት ቡድን ከፍሎ ሲያወያይ ፣ መብታችን ይከበር በማለት ሀሳባቸውን መግለፃቸው ወይም መናገራቸው የህገወጥ የስራ ማቆም አድማ መሪና የረብሻና የሁከት መፍጠር ሙከራ ነው ተብሎ ተጠሪዎችን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያበቃ ምክንያት መሆኑን አግባብነት ካላው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

7. ሰራተኞችን አመልካች ቦነስ ክፍያ ስለማይከፈልበት ምክንያት በሁለት ከፍሎ በሚያነጋግርበት ወቅት ተጠሪዎች መብታችን ይከበር የሚል ንግግር መናገራቸው ፤ ህጋዊ መብታችን ነው የሚሉት የቦነስ ክፍያ እንዲከፈላቸው ሀሳባቸውን የገለጹ መሆኑን እንጅ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ሸ) መሰረት በአሰሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው በማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት የማድረስ ጥፋት የፈፀመ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ አንድ አሰሪ ሰራተኛው ህጋዊ የመብት ጥያቄ በማቅረቡ ምክንያት የስራ ውሉን የሚያቋርጥ ከሆነ ህገወጥ ተግባር እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 26(2) ሐ) ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ያስናበተው ከህግ አግባብ ውጭ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪዎች የካሳ ክፍያ ፣ የስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ ከላይ የጠቀሳቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139262 ሀምሌ 30 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 15 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገበ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአመስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሃ/ወ**

የሰ/መ/ቁ.102994

ሚያዝያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች-፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ዳሸን ባንክ አክሲዮን ማህበር - ነ/ፈጅ ሰለሞን አያኖ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ተፈሪ አሳልፈው
2. አቶ አየለ ገብረሃና
3. አቶ በኃይሉ ዓለማየሁ

} ከጠበቃ ሳህሉ ሀብቴ ጋር - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ በ07/08/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሾች በተከሳሽ ድርጅት ተቀጥረው ቄራ አካባቢ በሚገኘው መጋዘን በመስራት ላይ እያሉ ከመጋዘኑ ግቢ ያልወጣን ንብረት "ለግል ጥቅማችሁ አውላችኃል" በማለት ከ13/07/2005 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸውን ያቋረጠ መሆኑን፣ከሳሾቹ ንብረት ከመመዝገብ በስተቀር ንብረት የመያዝም ሆነ የመጠበቅ ኃላፊነት እና የስራ ድርሻ የሌላቸው መሆኑን፣ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠው ሠራተኛ በስሩ የሚገኘውን ንብረት ለአጠባበቅ ያመቸኛል በማለት ከመደበኛ ቦታ ውጭ በማስቀመጡ ድርጅቱ እርምጃ መውሰድ የሚገባው ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘው ሠራተኛ ላይ ብቻ ሆኖ እያለ ከሳሾቹን ጭምር በማሰናበት የወሰደው እርምጃ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27 (1) (መ) እና የድርጅቱን የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 36 (1.3) የሚቃረን መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የስራ ስንብት እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ድርጅቱ ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደስራ እንዲመልሳቸው፣ይህ

የሚታለፍ ከሆነም ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን እና ተዛማጅ ክፍያዎችን እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ17/10/2005 ዓ.ም በሰጠው መልስ ከሳሾቹ ከብር 180,000 በላይ ዋጋ ያላቸውን የተለያዩ ዕቃዎች እርስ በርስ በመመሳጠር በስቶር ክለርክነት ከሚሰሩበት የዕቃ ግምጃ ቤት ሰርቀው በመውሰድ በመጸዳጃ ቤት ውስጥ በመደበቅ እና የመጸዳጃ ቤቱን በመቆለፍ የቆጠራ ሠራተኞች እንዳያገኟቸው ያደረጉ መሆኑን፣ንብረቶቹ ለተለያዩ የአካባቢ ባንኮች እና የስራ ክፍሎች የተሰራጩ ተደርገው የሚታወቁ መሆኑን፣ከሳሾቹ ንብረቶቹን ከሚሰራጩት ዕቃዎች ቀንሰው ያጠራቀሟቸው እንደሆነ መረጋገጡን፣ስለጉዳዩ ሲጠየቁም እርስ በርስ የሚጋጭ መልስ መስጠታቸውን፣እንዲሰናበቱ የተደረገውም በፈጸሙት የስርቆት እና የማጭበርበር ድርጊት በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) (ሐ) እና (ተ) እና በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 36 /1.1 እና 36 /1.2/ መሰረት በአግባቡ መሆኑን፣የሚፈለግባቸውን ዕዳ በማቻቻል ተራፊ ገንዘብ ካለ ከሁለት ዓመት በላይ ያልተላለፍ የዓመት ዕረፍታቸውን ድርጅቱ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆኑን፣የፕሮቪደንት ፈንድ የለም እንጂ አለ ከተባለ ድርጅቱ ክፍያውን ለመክፈል የሚገደደው ከሳሾቹ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ በመወጣት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ብቻ በመሆኑ ከሳሾቹ ይህንን ግዴታ ተወጥተው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጥያቄ ባላቀረቡበት ሁኔታ ድርጅቱ የሶስት ወር ደመወዝ ለመክፈል የሚገደድበት ምክንያት አለመኖሩን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የተከሳሽ ድርጅትን ሶስት ምስክሮች ከሰማ በኃላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ በስቶር ውስጥ በነበረው ዕቃ ጉድለት ያልተገኘ ቢሆንም ከሳሾች በመመካከር ዕቃዎቹ ከመጸዳጃ ቤት ውስጥ እንዲቀመጡ ማድረጋቸውን ተከሳሽ ድርጅት ያስረዳ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ይህ መሆኑ ከሳሾቹ ዕቃዎቹ ትርፍ መሆን አለመሆናቸው ወይም በመጠየቂያ መሰረት ያልተሰጡ ዕቃዎች መሆን አለመሆናቸው እስኪለይ ድረስ አስቀምጠናቸዋል በማለት ለተከሳሽ ድርጅት ምስክሮች በቃል እና በጽሁፍ ከሰጡት መግለጫ አንጻር ከሳሾቹ ዕቃዎቹን ከመደበኛ ቦታቸው ውጪ መጸዳጃ ቤት ውስጥ ማስቀመጣቸው አግባብ አይደለም ከሚባል በቀር ከሳሾቹ በመመካከር ዕቃዎቹን ለግል ጥቅማቸው ለማዋል በማሰብ ከሚላኩ ዕቃዎች ቀንሰው አውጥተው ወስደዋል ለማለት የሚያስችል አለመሆኑን ገልጾ ከሳሾቹ የስርቆት እና የማጭበርበር ድርጊት ፈጽመዋል በማለት ተከሳሽ ድርጅት የወሰደው የስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት ለእያንዳንዳቸው የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩል የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የተሰጠውን ውሳኔ ሲያጸናው ተጠሪዎቹ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራ እንዲመለሱ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ግን በመሻር ሕገወጥ የስራ ስንብት

የሚያስከትላቸው ክፍያዎች፣የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲሁም ያልተጠቀሙበት የዓመት ዕረፍት ክፍያ ለ1ኛ ተጠሪ የ27 ቀናት፣ለ2ኛ እና ለ3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው የ15 ቀናት ክፍያ ተፈጽሞላቸው እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪዎች በነበራቸው የስራ ግንኙነትና አጋጣሚ የአመልካች የሆኑ ለልዩ ልዩ ቅርንጫፎች የሚታደሉ በመጋዘን ውስጥ የነበሩ ንብረቶችን ከመጋዘን አውጥተው በግቢው ውስጥ ባለ መጸዳጃ ቤት ውስጥ አስቀምጠውት የነበረው ንብረት በጠቋሚዎች አማካኝነት በፍተሻ መያዙን የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማስረጃ ካረጋገጠ በኃላ ንብረቶቹን መጋዘኑ ካለበት ግቢ አውጥተው ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ አድራጎታቸው እንደስርቆት እንደማይቆጠር ገልጾ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የመወሰኑን እና ውሳኔውም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጽናቱን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈለኝ የሚገባው የዓመት ዕረፍት የ71 ቀናት ሆኖ ሳለ የ27 ቀናት ብቻ ታስቦ የ44 ቀናት የታለፈብኝ አላግባብ ነው በማለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መስቀልኛ የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች መልስ እንዲሰጥበት በ13/06/2007 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በመስቀልኛ አቤቱታው ጉዳይም አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች፡-

1. አመልካች አቤቱታ ያቀረበበት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?
2. 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መስቀልኛ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡበት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ ጉዳዩን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪዎቹ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ይሰሩ የነበሩት በስቶር ክለርክነት መሆኑ፣በዚሁ የስራ መደብ ከሚሰሩበት የዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ ተደርገው ለባንኩ የተለያዩ አካባቢዎች እና የስራ ክፍሎች እንደተሰራጩ ተደርገው የተመዘገቡትን የተለያዩ ዕቃዎች ከንብረት ጠባቂው ጋር በመተባበር ከሚሰራጩት ዕቃዎች ቀንሰው በመጸዳጃ ቤት ውስጥ በመደበቅ እና የመጸዳጃ ቤቱን በመቆለፍ የቆጠራ ሰራተኞች እንዳያገኟቸው ያደረጉ መሆኑ፣ንብረቶቹን ለተለያዩ የአካባቢ ባንኮች እና የስራ ክፍሎች የተሰራጩ እንደሆኑ አድርገው የመዘገቡትም እነዚሁ ተጠሪዎች መሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ

ጉዳዮች መሆናቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ተጠሪዎቹም እኛ ንብረት ከመመዝገብ ባለፈ ንብረቱን የመያዝ እና የመቆጣጠር የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት የሌለን ስለሆነ ለዕቃዎቹ በመጸዳጃ ቤት ውስጥ ተደብቀው መገኘት በኃላፊነት የምንጠየቅበት ምክንያት የለም፣ዕቃዎቹም የተገኙት ከግቢው ሳይወጡ ነው፣በግቢው መውጫ ላይ የሚደረገው ፍተሻ ዕቀዎቹን ከመጋዘኑ ግቢ ለማውጣት የሚያስችል አይደለም በሚል ከመከራከር በቀር በስር ፍርድ ቤቶች ስለተረጋገጡት ከላይ ስለተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች ያቀረቡት የማስተባበያ ክርክር የለም፡፡ከንብረት ጠባቂው ጋር በመሆን ዕቃዎቹን ከመደበኛ ቦታቸው ውጭ በመጸዳጃ ቤት ውስጥ ቆልፎ ለማስቀመጥ ያስቻላቸው ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ምክንያት ስለመኖሩም ገልጸው አልተከራከሩም፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ይዘቱ ከላይ የተመለከተው ፍሬ ነገር መረጋገጡን ከተቀበሉ በኃላ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ለማለት የቻሉት በዋነኛነት ዕቃዎቹ የተገኙት በግቢው ውስጥ እንዳሉ በመሆኑ ተጠሪዎቹ ዕቃዎቹን ወስደዋል ማለት አይቻልም በማለት መሆኑን ከውሳኔዎቹ ይዘት ተገንዝበናል፡፡በእርግጥ ዕቃዎቹ በመጸዳጃ ክፍል ውስጥ ተቆልፈው እንዳሉ በጥቆማ ተይዘዋል ከመባሉ በስተቀር ከግቢ ውጪ አልተወሰዱም፡፡አመልካችም ቢሆን ዕቃዎቹ ከግቢ ውጪ ተወስደዋል በማለት አልተከራከረም፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪዎቹ ዕቃዎቹን ወጪ ተደርገው ለተለያዩ የባንኩ ቅርንጫፎች እና የስራ ክፍሎች እንደተሰራጩ አድርገው በመመዝገብ እና ከተሰራጩት ዕቃዎች በመቀነስ ከመደበኛ የዕቃ ማከማቻ ቦታ ውጭ በመጸዳጅ ክፍል ውስጥ ቆልፈው ያስቀመጡበት ሕጋዊ ምክንያት መኖሩን አስካላስረዱ ድረስ የፈጸሙት አድራጎት በድርጅቱ ላይ የተፈጸመ የማጭበርበር ድርጊት ነው ሊባል የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡ዕቃዎቹ ከግቢው ሳይወጡ ድርጊቱ በሙከራ ደረጃ ላይ እንዳለ የተደረሰበት መሆኑ እና በግቢው መውጫ ላይ ፍተሻ የሚደረግ መሆኑም ተጠሪዎቹ ዕቃዎቹን ከግቢው አውጥተው ለግል ጥቅማቸው የማዋል ሀሳብ አልነበራቸውም ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል አይደለም፡፡በመሆኑም ተጠሪዎቹ ዕቃዎቹን ከመደበኛ ቦታቸው ውጪ መጸዳጃ ቤት ውስጥ ማስቀመጣቸው አግባብ አይደለም ከሚባል በቀር በመመካከር ዕቃዎቹን ለግል ጥቅማቸው ለማዋል በማሰብ ከሚላኩ ዕቃዎች ቀንሰው አውጥተው ወስደዋል ለማለት እና በስራቸው ላይ የስርቆት እና የማጭበርበር ድርጊት ፈጽመዋል ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በክርክሩ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጭ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡ እንደጥፋቱ ክብደት ሰራተኛው በስራው ላይ የሚፈጽመው የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ደግሞ ካለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 27 (1) (ሐ) ስር ተመልክቷል፡፡በመሆኑም የመጀመሪያው

ጭብጥ ሲጠቃለል ስንብቱ ሕገወጥ ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ የ27 ቀናት የዓመት ፈቃድ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል በሚል ውሳኔ የሰጠው ተጠሪው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ላይ ያላቸው የዓመት ፈቃድ ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው በደፈናው ከመጠየቅ ውጭ ያላቸውን የዓመት ፈቃድ መጠን ጠቅሰው እና ለይተው አለማቅረባቸውን በመግለጽ እና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 77 (1)፣(5) እና 79 (5) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ ተገቢ ነው ያለውን ግምት በመውሰድ ነው፡፡በሰበር ክርክራቸውም ቢሆን ያላቸውን የዓመት ፈቃድ መጠን በክሳቸው ለይተው አቅርበው የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገቡን ግልባጭ እና የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት አድርጎ ለተጠሪው ሊከፈል የሚገባው የዓመት ዕረፍት መጠን የ27 ቀናት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 08897 በ15/04/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139478 በ09/10/2006 ዓ.ም. ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች የተወሰደው የስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. በተጠሪዎቹ መፈጸሙ የተረጋገጠው ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 27 (1) (ሐ) ድንጋጌ መሰረት የስራ ውላቸውን ካለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. ስንብቱ ሕጋዊ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪዎቹ የካሳ ክፍያ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
5. አመልካች ለተጠሪዎቹ የዓመት ዕረፍት ወደገንዘብ ቀይሮ እንዲከፍላቸው የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

6. አመልካች ለተጠሪዎቹ የፕሮቪደንት ፈንድ ሊከፍል የሚገባው ተጠሪዎቹ ባዋጡት መጠን ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡
7. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14377 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ17/11/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
8. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
9. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
10. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

የሰመ/ቁ/ር 104465

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ሽዊት ኃይሉ - VC - ስላልሰራ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

**ተጠሪ፡-** መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራዝ - ነ/ፈጅ ደረጀ ከበደ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሰረት አድርጎ የቀረበ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በደጉዓ ተምቤን ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በካሼር የስራ መደብ ላይ በወር ብር 1744.00 እየከፈላቸው ከሰኔ 27 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሀምሌ 25 ቀን 2005 ድረስ ቀጥሮ ሲያሰራቸው እንደቆዩና ከህግ ውጪ የስራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ በአሰሪው ድርጅት የተቋረጠ መሆኑን ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም፡- የስራ ውሉ የተቋረጠው አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ባቀረቡት መልቀቂያ መሰረት መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ባስገቡት የስራ ውል መነሻ ግንኙነቱ መቋረጡን ገልጾ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁኗ ተጠሪ ለምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበውም ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ስንብቱ በአመልካች ጥያቄ መሰረት የተደረገ በመሆኑ ሕጋዊ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በድምጽ ብልጫ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ስራውን ለመልቀቅ ለተጠሪ ድርጅት መልቀቂያ አስገብተው ቆይ ተብለው ለሰባት ወራት ያህል ስራ እንዲሰሩ ከተደረገ በኋላ የስራ ውሉን ከሰባት ወራት በፊት በቀረበ ማመልከቻ መነሻ ተቋርጧል ተብሎ ስንብት መደረጉና ሁሉም ክፍያዎች ውድቅ መደረጋቸው ያላግባብ ነው የሚል

ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረውን የስራ ውል ያቋረጠው በአመልካች የስራ መልቀቂያ ጥያቄ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ17/04/2005 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ የስራ መልቀቂያ እንዲሰጣቸው ለተጠሪ ጥያቄ አቅርበው ተጠሪም የአመልካችን ጥያቄ አቆይቶ አመልካች ለሰባት ወራት ምድብ ስራቸው ላይ እየተገኙ ስራውን እንዲሰሩና ግዴታቸውን እንዲወጡ ሲያደርግ ቆይቶ ከነሐሴ ወር 2005 ዓ/ም ጀምሮ የአመልካች የወር ደመወዝ ሳይያዝና ስማቸው ከአቴንዳንስ ተሰርዞ በአመልካች የስራ መደብ ላይ ሌላ ገንዘብ ያዥን በመመደብ አመልካች በ17/04/2005 ዓ/ም ያስገቡትን የስራ መልቀቂያ በመጥቀስ የስራ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የስራ ውል ሁለት ወገኖች አንዱ አሰሪ ሌላኛዉ ሠራተኛ ሆነው በአሠሪው ቁጥጥር እያደረገ ሠራተኛው ለሚሰራለት የጉልበት ወይም የዕወቅት ስራ ደሞዝ የሚከፍልበት የስራ ግንኙነት የሚፈጥር ስምምነት ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 4/1/ ስር ከተደነገገው ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ የህጉ የትርጉም ይዘት መሰረት ከሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች አንዱ በሕጉ መሰረት አሠሪ ነው ተብሎ የሚወሰድ ሲሆን ይህ ወገን ለሚያገኘው አገልግሎት ተገቢውን ደሞዝ የሚከፍልና አገልግሎቱም በእርሱ ቁጥጥር የሚመራ መሆኑ፣ሠራተኛ ደግሞ በአሠሪው ቁጥጥር መሠረት አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስራ ውሉ መኖሩ ደግሞ በማናቸውም አይነት ሊረጋገጥ የሚችል ነው፡፡ በሕጉ አግባብ የተመሰረተ የስራ ውል ደግሞ የሚቋረጥባቸው መንገዶች ስለመኖራቸው ሕጉ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የስራ ውል ስለሚቋረጥበት ምክንያቶችና ሁኔታዎችን በአንቀጽ 23 ስር ተመልክተዋል፡፡ እነዚህም በሰራተኛው አነሳሽነት የሚደረግ፣ በሕግ በተደነገገው መሰረት፣በህብረት ስምምነት መሰረት እና በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የሚደረግ የውል ማቋረጥ ሲሆኑ ዝርዝር ምክንያቶቻቸውና ሁኔታዎችንም ህጉ አስቀምጧል፡፡ በአሰሪው አነሳሽነት የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ እንደየሁኔታው በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊደረግ የሚችል ሆኖ የምክንያቶቹ ዝርዝር እና አፈጻጸሙ በአዋጁ አንቀጽ 26 እስከ 30 ባሉት ድንጋጌዎች ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ሌላው በህጉ በዝርዝር የተቀመጠው የስራ ውል ማቋረጥ ስርዓት በሰራተኛው አነሳሽነት የሚደረገው ሲሆን ይህም በአሰሪው አነሳሽነት ሊደረግ እንደሚችለው በማስጠንቀቂያ እና ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሰራተኛው የሚያቋርጥበት መንገድ ስለመኖሩና ውሉን

ለማቋረጥ የሚቻልባቸው ሁኔታዎቹና ምክንያቶቹን ዘርዝሮ የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎችና ምክንያቶቹ በአዋጁ ከአንቀጽ 31 እስከ 33 ድንጋጌዎች ስር በግልጽ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡

እንግዲህ ሕጉ የስራ ውሉ ሊቋረጥ የሚችልባቸውን መንገዶች በዝርዝር ከአስቀመጠ በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ሲነሳም ውሉ የተቋረጠበትን መንገድ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ ተለይቶ ዳኝነት መሰጠት ያለበት በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ ከሰኔ 27 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ህጋዊ የስራ ውል መኖሩ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ሲሆን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይ ይኼው ውል የተቋረጠው በማን አነሳሽነት ነው? የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ያስገቡትን የስራ መልቀቂያ መሰረት አድርጎ የስራ ውሉን ማቋረጡን ያልካደው ሲሆን አመልካችም ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም የስራ መልቀቂያ ማስገባታቸውን ሳይክዱ መልቀቂያው ሳይሰጣቸው ቆይቶ የስራ ግዴታቸውን እየተወጡ እስከ ሰኔ ወር 2005 ዓ/ም ድረስ ያለው ደመወዝም እየተከፈላቸው ስራቸውን ሲሰሩ የቆዩ መሆኑን ገልጸው የስራ መልቀቂያ ጥያቄአቸው በተጠሪ ምክንያት ተግባራዊ ያለመሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የተጠሪ የስራ ስንብት የተከናወነው አመልካች የስራ መልቀቂያ ከአስገቡ ከሰባት ወራት በኂላ መሆኑንና መልቀቂያው ለሰባት ወራት የቆየው በአመልካች ፍላጎት ስላለመሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ አመልካች መልቀቂያውን ያነሱ ስላለመሆናቸው በተጠሪ በኩል የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ የአመልካች የስራ መደብ ላይ ተገቢው ሰራተኛ ባለመገኘቱ ሰራተኛ እስከሚገኝ ድረስ አመልካች በስራቸው ላይ እንዲቆዩ የተደረጉ ስለመሆኑና ሰራተኛው ሲገኝ መልቀቂያው የሚሰጣቸው ሰለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረበ ግልጽ ክርክርና ማስረጃ ያለመኖሩን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አመልካች የስራ መልቀቂያ ከአስገቡ በኂላ ለረዥም ወራት እንደ ሰራተኛነታቸው በሕጉ የተጣለባቸውን የስራ ግዴታ ሲወጡ መቆታቸውና ተጠሪም ለአመልካች ስራ እየሰጠና ደመወዝም እስከ ሰኔ ወር 2005 ዓ/ም ድረስ እየከፈለ መቆየቱ ሲታይ ግራ ቀኙ በነጻ ፍላጎታቸው የቀደመውን የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት እንዲቀጥል የተስማሙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ አግባብ እንዲቀጥል የተደረገ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ደግሞ በተግባር ቀሪ በሆነው የስራ መልቀቂያ ጥያቄ በሕጉ የተቀመጠውን ስርዓት ሳይከተል ሊቋረጥ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አንፃር መመልከት ሲገባቸው አመልካች ስራውን የለቀቁት በራሳቸው ተነሳሽነት ነው በሚል የሰጡት ውሳኔ የስራ ውል አመሰራረት፣ውሉ የሚቋረጥባቸውን ሁኔታዎችና ምክንያቶችን እንዲሁም በሕጉ የተቀመጡትን ስርዓቶችን ያላገናዘበ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በደጉዓ ተምቤን ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02582 ህዳር 23 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥ 06144 ጥር 01 ቀን 2006 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 64078 ግንቦት 23 ቀን 2006 ዓ/ም በአብላጭ ደምጽ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተው በራሱ ተነሳሽነት እና ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39 እና 40(2) መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ፣ በአንቀጽ 43(4(ሀ)) መሰረት የካሳ ክፍያ፣ በአንቀጽ 35(1(ለ)) መሰረት የማስንጠቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና በአንቀጽ 38 መሰረት ክፍያ ለዘገዬበት ክፍያ የሁለት ወር ደመወዝ  እንዲከፍል ብለናል፡፡
3. ሌሎች ክፍያዎች ማለትም ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተጠየቁት የትርፍ ሰዓት እና ህዝባዊ ባዕላት ክፍያዎች ግን በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያልተጣሩ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና በማስረጃ አጣርቶ ተገቢውን ሊወሰን ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይፃፍ፡፡
4. ብር 518.00 የዳኝነት ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ሊተኩ አይገባም ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

**መ/ተ**

የሰ/መ/ቁ.108789

ሚያዝያ 13 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች-፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡-ሴንቸሪ ጄኔራል ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ አሰፋ ዓሊ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡-አቶ ገስጥ ንጉሴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በ11/09/2006 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሽ ከ09/03/2006 ዓ.ም ጀምሮ በአሽከርካሪነት የስራ መደብ ላይ በወር ያልተጣራ ብር 1,900 (አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ) ደመወዝ እየተከፈላቸው በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ድርጅት ካለአንዳች ምክንያት በ19/07/2006 ዓ.ም ከስራ ካገዳቸው በኃላ በ24/08/2006 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የስራ ስንብት እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን እና ተዛማጅ ክፍያዎችን በድምሩ ብር 21,850 (ሃያ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ) ድርጅቱ እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ26/09/2006 ዓ.ም. በሰጠው መልስ የከሳሽ የስራ ውል እንዲቋረጥ የተደረገው ከሳሽ ስራቸውን ለመስራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፣አሮጌ ተሽከርካሪ አላሽከረክርም በማለታቸው፣ከድርጅቱ ሰራተኞች ጋር ለመስራት ባለመቻላቸው፣በዚህም ምክንያት የድርጅቱ ሰራተኞች በከሳሽ ሾፌርነት በድርጅቱ ተሽከርካሪ ከመጠቀም ይልቅ በታክሲ መጠቀም ይሻለናል በማለታቸው እና ከሳሽ ተደጋጋሚ ምክር እና ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ሊታረሙ ባለመቻላቸው በመሆኑ የስራ ውላቸው የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13(2) መሰረት በአግባቡ ነው፣እስከሰሩበት መጋቢት 19 ቀን 2006 ዓ.ም. ድረስ ያለው ደመወዝ ተከፍሏቸዋል

፣ያልሰሩበት የሚያዝያ ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፣የዘገየ ክፍያ የለም፣ በመሆኑም ክሱ ውድቅ ሊደረግልን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ከሳሽ ባላቸው የማሽከርከር ሙያ በተቀጠሩበት የስራ መደብ ሰራተኞችን ወደ ስራ ቦታ በሰዓቱ ወስደው በሰዓቱ መመለስ እና የሚሰጣቸውን ትዕዛዝም መፈጸም እንዳልቻሉ እንዲሁም ተሽከርካሪው መስራት የሚችል ሆኖ እያለ በአሮጌ ተሽከርካሪ አልሰራም በማለት አቁመው እንደሄዱ ከግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል መገንዘብ መቻሉን፣አንድ ሰራተኛ በአሰሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13 (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑን፣ይሁን እንጂ ከሳሽ መፈጸማቸው የተረጋገጠው ጥፋቶች በአዋጁ አንቀጽ 27 መሰረት ካለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብቱ አለመሆኑን ገልጾ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት ተከሳሽ ድርጅት ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች ለከሳሽ እንዲከፍል እና የስራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13 የተመለከተውን ግዴታ ሊፈጽም ያልቻለ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም የዚህ ግዴታ መጓደል ካለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 27(1) ስር ስላልተካተተ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ትርጉም አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በአንድ በኩል ተጠሪው ባላቸው የማሽከርከር ሙያ በተቀጠሩበት የስራ መደብ ሰራተኞችን ወደ ስራ ቦታ በሰዓቱ ወስደው በሰዓቱ መመለስ እና የሚሰጣቸውን ትዕዛዝም መፈጸም እንዳልቻሉ እንዲሁም ተሽከርካሪው መስራት የሚችል ሆኖ እያለ በአሮጌ ተሽከርካሪ አልሰራም በማለት አቁመው እንደሄዱ በግራ ቀኙ ምስክሮች መረጋገጡን እና አንድ ሰራተኛ በአሰሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13 (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑን በውሳኔው ላይ ከገለጸ በኃላ በሌላ በኩል ግን ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት ለተጠሪው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ውሳኔ የሰጠው ተጠሪው መፈጸማቸው የተረጋገጠው ጥፋቶች በአዋጁ

አንቀጽ 27 መሰረት ካለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብቱ አይደሉም በማለት ነው፡፡በመሰረቱ የስራ ውል ማለት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት ግዴታ የሚገባበት ውል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 4 (1) ስር የተመለከተ ሲሆን የዚህ ዓይነት የውል ግዴታ የገባ ሰራተኛ በስራ ውሉ ላይ የተመለከተውን ስራ ራሱ የመስራት፣በስራ ውሉ እና በስራ ደንቡ መሰረት በአሰሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ መፈጸም እና የአዋጁን ድንጋጌዎች፣የሕብረት ስምምነትን፣የስራ ደንብን እና በሕግ መሰረት የሚተላለፉ መመሪያዎችን እና ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 13 (1) (2) እና (7) ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡በተጠሪው መፈጸማቸው በግራ ቀኙ ምስክሮች እንደተረጋገጡ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተገለጹት ፍሬ ነገሮችም ተጠሪው ከላይ በተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ግዴታዎች መፈጸም አለመቻላቸውን በግልጽ የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ተጠሪው እነዚህን ግዴታዎች ለመፈጸም ፈቃደኛ አለመሆናቸው ደግሞ ከአመልካች ጋር የገቡትን የስራ ውል መሰረታዊ ዓላማ እና ይዘት የሚጻረር እና የስራ ውሉን ተግባራዊነት የሚያሰናክል ከመሆኑም በላይ ድርጊቶቹም በባህሪያቸው ሆን ተብለው የሚፈጸሙ በመሆኑ እንደተራ ጥፋት ተቆጥረው በቀላሉ ሊታለፉ የሚገባቸው አይደሉም፡፡ በተጠሪው መፈጸማቸው የተረጋገጡት ጥፋቶች ካለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብቱ ናቸው ተብለው በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) ስር ከተዘረዘሩት ጥፋቶች ውስጥ በግልጽ ባይጠቀሱም በአሰሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው በማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ካለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናበት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) (ሸ) ስር ተመልክቷል፡፡በመሰረቱ …"የአሰሪው ንብረት…" በሚል በዚህ ድንጋጌ ስር የተቀመጠው አገላለጽ መተርጎም የሚገባው ግዙፍነት ያለው ቁሳዊ አካል ብቻ ተደርጎ ሳይሆን ለአሰሪው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሌላ ነገር በሚያካትት አግባብ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ በተጠሪው መፈጸማቸው የተረጋገጡት ጥፋቶች የአሰሪውን የስራ እንቅስቃሴ የማስተጓጎል ውጤት ያስከተሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ይህ መሆኑ ደግሞ ተጠሪው ሆነ ብለው በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በመሆኑም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ተጠሪው በአዋጁ አንቀጽ 13 (1) (2) እና (7) ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ግዴታዎች አለመወጣታቸው የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤት በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) (ሸ) ስር ከተመለከተው ድንጋጌ አንጻር አይቶ መተርጎም ሲገባው ተጠሪው በአዋጁ አንቀጽ 13(2) ስር የተመለከቱትን ግዴታዎች አለመፈጸማቸው ካለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችሉ ናቸው ተብለው በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) ስር ከተዘረዘሩት ጥፋቶች ስር በግልጽ አልተጠቀሱም ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ስንብቱ ሕገወጥ ነው

በማለት የሰጠው እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት ሕገ ወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪው እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለው  ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት ሕገ ወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪው እንዲከፍል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13619 በ29/11/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 155925 በ20/04/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች የተወሰደው የስራ ስንብት እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13 (1) (2) እና (7)  እና 27 (1) (ሸ) መሰረት ሕጋዊ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የተጠሪውን የስራ መደብ፣የደመወዝ መጠን እና የአገልግሎት ዘመን በመጥቀስ አመልካች የስራ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኝ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ. 105834

ሚያዚያ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ኮንፌደሬሽን -

ጠበቃ እሸቴ ጓንጉል - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ እመቤት ኤርሚያስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካች የስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጽናቱ በውሳኔው ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሰረት ያደረገ የግል የስራ ክርክር ሁኖ አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ የዲስፕሊን ጥፋት ፈፅሟል ተብሎ ከስራ ያለማስጠንቀቂያ የሚሰናበትበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የተጠሪ ክስ በአመልካች ማህበር ውስጥ በወር ብር 4,500.00 (አራት ሺህ አምስት መቶ) እየተከፈላቸው በሂሳብ ሰራተኝነት የስራ መደብ ከመስከረም 05 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ሲያገለግሉ ቆይተው አመልካች ማህበር የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽመዋል በሚል ምክንያት በሕገ ወጥ መንገድ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ዘርዝረው ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የካሳ፣የስራ ስንብት፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ክፍያ ለዘገዬበት ክፍያ እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን ያሳያል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ የተለያዩ የዲስፕሊን ጥፋቶችን መፈፀማቸውን በመግለጽ ጥፋቶችም፡- ተጠሪ የስራ መደባቸው አካውንታት ሆኖ እያለ ከስራ ድርሻቸው ውጪ መጠኑ ብር 9000.00 (ዘጠኝ ሺህ ብር) የሆነ ገንዘብ ከአምስት ወራት በላይ በእጃቸው ላይ ያቆዩ መሆናቸውን፣ተጠሪ ይህን በእጃቸው ያቆዩትን ብር 9000.00 (ዘጠኝ ሺህ ብር) በስራ ላይ እንደዋለ በማስመሰል የተሳሳተ ሪፖርት ማቅረባቸውንና ይህንኑ በእጃቸው

የቆየውን ገንዘብ ባንክ እንዲያስገቡ ሲታዘዙ ትዕዛዝ ያለመቀበላቸው፣የስራ አመራር ቦርድ ሳይፈቅድ የአመልካች ማህበር ተ/ዋና ስራ አስኪያጅ ለሆኑት አቶ ተሾመ ዴሬሳ በየወሩ ከሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 2005 ዓ.ም ድረስ ብር 430.00 በድምሩ ለአራት ወራት ብር 1720.00 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ብር) መክፈላቸው፣ለፌዴሬሽኑ አትክልተኛ ለአቶ መዝገቡ ገላው ሐምሌ ወር 2004 ዓ.ም ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) መክፈላቸው፣ለአመልካች ማህበር የሕዝብ ግንኙነት ሰራተኛ አቶ ደረሰ ታደሰ ከሰኔ ወር 2004 ዓ.ም እስከ መስከረም 2005 ዓ.ም ብር 130.00 በየወሩ በድምሩ 520.00 (አምስት መቶ ሃያ ብር) ጭማሪ በማድረግ መከፈላቸው፣በአመልካች የክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስተባባሪዎች እጅ ብር 9000.00 (ዘጠኝ ሺህ ብር) የያዘ ሰደን ከሚያዝያ 19 ቀን 2004 ዓ.ም እስከ ህዳር 14 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ ሳያወራረድ እንዲቆይ በቃል መፍቀዳቸው፣ተጠሪ በተለያዩ ግለሰቦች ክፍያ ሲፈፅሙ ተቀናሽ የሚደረግ ዊዝሆልዲንግ ታክስ 2 %) ከሐምሌ ወር 2003 ዓ.ም እስከ መስከረም ወር 2005 ዓ.ም ድረስ ብር 17,092.70 (አስራ ሰባት ሺህ ዘጠና ሁለት ብር ከሰባ ሳንቲም) በወቅቱ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ገቢ ያለማድረጋቸው፣ህዳር 04 ቀን 2005 ዓ.ም ከቀኑ 11፡00 ከአስተደደርና ፋይናንስ ኃላፊ ቢሮ በኮምፒዩተር ላይ ተሰክቶ የነበረ 4GB የፍላሽ ዲስክ ያለ አመልካች ማህበር ፈቃድ መውሰዳቸው፣የቅጥር ውል ላልተፈፀመላቸውና ላልታደሰላቸው ሰራተኞች ደመወዝ መክፈላቸው፣ግዥዎች በእቅድ ከተያዘው በጀት በላይ እንዲፈፀሙ ማድረጋቸው፣ከፋይናንስ ውጪ ሰነድ ማዘጋጀታቸው፣ከአለም አቀፍ የሥራ ድርጅት የተገኘውን ብር 184,206.00 “ወርልድ ለርኒግ” ከተባለ ድርጅት የተገኘ በማስመሰል በጀት ምንጩን በማሳሳት መመዝገባቸው፣አመልካች ድርጅት ምንም እዳ ሳይኖርበት በስራ ማስኪያጃ 19,000.00 (አስራ ዘጠኝ ሺህ ብር) ከተለያዩ ወጪዎች ብር 162,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ ሁለት ሺህ) እዳ ያለበት መሆኑን አስመስለው መግለፃቸው፣ተጠሪ የአመልካችን ብር 500.00 እዳ እያለባቸው ለአንድ አመት ያህል ገቢ ያለማድረጋቸው ስለመሆናቸው ዘርዝሮ እና ከእነዚህ ጥፋቶች በዲስፕሊንና ኮሚቴ ውሳኔና በኦዲት ሪፖርት መረጋገጣቸውን ጠቅሶ የስራ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የፌዴሬሽን ተ/ዋና ስራ አስኪያጅና አትክልተኛ ደመወዝ እንዲጨመር ከሚመለከታቸው አካላት የደረሳቸውን የደመወዝ ዝርዝርና በአመልካች መስሪያ ቤት ይገኛል የተባለውን ሰነድ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሰነዱ ከቀረበለትና ከተጠሪ እጅ ያለውን ቀሪ ሁሉ ከተመለከተ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የፈፀሙት የዲስፕሊን ጥፋት የለም ወደ ሚለው ድምዳሜ ደርሶ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የካሳ ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ክፍያ ለዘገዬበት ክፍያና የሁለት አመት ፈቃድ እንዲከፍላቸው፣የስራ ስንብት ግን የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚና የተከፈላቸው በመሆኑ አይከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው፡፡ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈል ተብሎ በተወሰነው የውሳኔ ክፍል ቀጥተኛ የይግባኝ አቤቱታ፣ተጠሪ ደግሞ በድርጅቱ ከአስራ አምስት አመት በላይ አገልግለው ለሰባት አመታት ለአገለገሉት ጊዜ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆናቸው ለቀሪዎቹ አመታት የሥራ ስንብት ክፍያ እንዳገኙ መደረጉና የአመት ፈቃድም ሲተላለፍ የቆየ ሁኖ እያለ የሁለት አመት ብቻ ታስቦ እንዲከፈላቸው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው  በሚል መስቀለኛ የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ ስራቸውን ሲሰሩ ከአስራ አምስት በላይ የዲስፕሊን ግድፈት የፈፀሙ ስለመሆኑ በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጦ እያለ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ በስራቸው ላይ ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆኑ በኦዲት ሪፖርትና በአመልካች መስሪያ ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ ተረጋግጦ ሳለ የሥር ፍርድ ቤቶች ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎች ለተጠሪ እንዲከፈሉ የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ከግራ ቀኙ ክርክር፣ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪን አሰናበትኩ የሚለው አስራ አምስት ያህል የዲስፕሊን ግድፈቶችን ተጠሪ ስለመፈጸማቸው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ሲሆን ይህንኑ ለማስረዳትም የፌዴሬሽኑ የአስተዳደር ማኑዋል በሚያዘው መሰረት የተቋቋመው የዲስፕሊን ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔና የኦዲት ሪፖርት ሰነድ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል የቀረቡትን እነዚህን የሰነድ ማስረጃዎች የማስረጃነት ዋጋ ሳይሰጡ አልፈዋል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የዲስፕሊን ኮሚቴውን የውሳኔ ሰነድ ያልተቀበሉት ተጠሪ ሰነዱን ባለማመን ፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸውን በመጥቀስ ሲሆን የኦዲት ሪፖርቱን ደግሞ የስራ ስንብቱ ከተደረገ በኃላ የተጠቃለለ በመሆኑ የተጠሪ የዲስፕሊን ግድፈት መኖሩ ታውቆ ስንብቱ ተደርጓል በማለት የሚያስችል አይደለም የሚለውን አብይ ምክንያት ከአሰፈሩ በኃላ በተጨማሪነት የኦዲት ሪፖርቱ ከቀድሞ ሰራተኛ ያልተሰራ ስራ መኖሩን ገልጾ በተተኪ ሰራተኛ ሊሰራ እንደሚገባ መገለጹ ከሂሳብ

አሰራር ጉድለት ጋር ተያያዥ የሆኑትን ሰራተኛ ማንነት የማይገልጽና የማያብራራ ነው፣ኦዲት ሪፖርቱ በተራ ቁጥር 4.8፣4.3 እና 4.9 የተዘረዘሩት ካልሆነ በስተቀር ቀሪዎቹ የኦዲት ሪፖርት ይዘቶች ከቀረቡት መከራከሪያ ነጥቦች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተያያዥነት የሌላቸው ናቸው፣የኦዲት ሪፖርት ተራ ቁጥር 5 ስር የሂሳብ ሰራተኛዋ የብቃት ችግር ያለባቸው መሆኑን መግለጹም ለስንብቱ ምክንያት የተባለው የዲስፕሊን ጉድለት በመሆኑ አግባብነት የሌለው ነው የሚሉትንና የደመወዝ ጭማሪ አከፋፈል በተመለከተ ደግሞ ተጠሪ በሚመለከተው አካል ተፈቅዶ የፈፀሙት መሆኑን አረጋግጠዋል የሚሉ ምክንያቶችን አስፍሮ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድን ፍሬ-ነገር ለማስረዳት በተከራካሪ ወገኖች ተቆጥሮ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ በህጉ ተቀባይነት የለውም (inadmissible) ወይም ከተያዘው ፍሬ-ነገር ጭብጥ ጋር አግባብነት የለውም እስካልተባለ ድረስ ሰነዱ በማስረጃነት ተመርምሮ እንዲሁም ከሌሎች ማስረጃ አይነቶች ጋርም በአንድነት ታይቶና ተመዝኖ የሚገባው ዋጋ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ምክንያቱም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 138 ስር እንደተመለከተው በህግ አግባብ የተቆጠረው ማስረጃ በዝምታ የሚታለፍበት ወይም ከሕግ ውጪ የማስረጃነት ዋጋ ሳይሰጥ ውድቅ የሚሆንበት አግባብ የለምና፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንኑ በፍትሐብሄር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ደንብ ያለፈው በአመልካች በኩል የቀረበው የዲስፐሊን ኮሚቴ ውሳኔ የሰነድ ማስረጃ በተጠሪ እምነት ያላገኘና ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበበት ጉዳይ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ያቀረበው ይኼው ሰነድ የፌዴሬሽኑ የአስተዳደር ማኑዋል በሚያዘው መሰረት በተቋቋመው ኮሚቴ ተጠሪ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡበት ተደርጎና ተገቢነት አላቸው የሚሏቸው ማስረጃዎች ቀርበው በተጠሪ ተፈጸሙ የተባሉትን ጥፋቶች መኖራቸውን፣ተጠሪም በዲስፐሊን ኮሚቴው ጥፋቶችን ማመናቸውን በማረጋገጥ የተሰጠ መሆኑን የሰነዱ ይዘት በግልፅ ያሳያል ፡፡ ይህ ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው  ማስረጃ ሲሆን የማስረጃነት ዋጋ ሊያጣ የሚችለው ተጠሪ በፍርድ ቤት ክስ በማቅረባቸው ወይም ሰነዱን ባለማመናቸው ሳይሆን ሰነዱ በፌዴሬሽኑ የአስተዳደር ማኑዋል መሰረት ባልተቋቋመ የዲስፐሊን ኮሚቴ የተዘጋጀ፣ወይም ዲስፐሊን ኮሚቴው ከሕግ ውጪ ማስረጃውን በመስማትና በመመዘን ያልተገባ ድምዳሜ ይዞ የሰጠው ውሳኔ መሆኑን ተጠሪ በፍርድ ቤት ላይ በሚያቀርቡት ክርክርና ማስረጃ የአመልካችን ማስረጃ ሲያስተባብሉ እንጂ እንዲሁ በደፈናው ማስረጃውን አላመኑም፣ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል በሚል ምክንያት አይደለም፡፡ በየመስሪያ ቤቱ የሚቋቋሙ የዲስፐሊን ኮሚቴዎች በሕግ አግባብ የሚቋቋሙና የሰራተኛው ጥቅም ያላግባብ እንዳይጎዳ ተገቢው መጣራት ተደርጎ እርምጃ እንዲወሰድ እገዛ የሚያደርጉ ናቸው ተብሎ የሚታመን ሲሆን የዲስፐሊን ኮሚቴ ውሳኔ በማስረጃነት ዋጋ ሊያጣ የሚገባው ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ሕጋዊ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች መስሪያ ቤት ያቀረበውን የዲስፐሊን ኮሚቴ የውሳኔ ሰነድ የማስረጃነት ዋጋ

ያሳጡት ተጠሪ ተገቢውን ማስረጃ አቅርበው ሰነዱ ሕገ ወጥ መሆኑን ሳያስረዱና ይህንኑ ለማስረዳትም በሕግ አግባብ የቀጠሩት ማስረጃዎች ሳይኖር ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ አስቀርበን ከጠቅላላ የግራ ቀኙ የክርክር ሂደት ተገንዝበናል፡፡

የኦዲት ሪፖርቱን በተመለከተም ኦዲት የተደረገው እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1/2011 እስከ ኦክቶበር 31/2012 ድረስ ያለው የአመልካች ማህበር ዝርዝር ሂሳብ ሁኖ ሪፖርቱ በተጠቀሱት 22 ወራት ውስጥ የታዬውን የሂሳብ አያያዝ ችግር ከዝርዝር ከማስቀመጡ በፊት የ2012 በቀድሞዋ የሂሳብ ሰራተኛ ያልተሰራ መሆኑ፣በተተኪው ሰራተኛ ሊሰራ የሚገባ እና ይህም የተጀመረ መሆኑን በመግቢያው ላይ ያሰፈረ መሆኑን ሰነዱ ያሳያል፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ የተጠቃለለው በእርግጥ ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም ስለመሆኑ ሰነዱ የሚገልጽ ሲሆን ስንብቱ የተከናወነው ደግሞ ጥር 10 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን የስንብት ደብዳቤው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት በተደረገበት ጊዜ የሂሳብ ስራው  የሚመለከተው ተጠሪን ስለመሆኑ አመልካች በክሱ የጠቀሰ ሲሆን ተጠሪም ቢሆኑ የኦዲት ስራው ራሳቸውን የሚመለከት ሁኖ በውጤቱ ግን ተጠያቂ ያላደረጋቸው መሆኑን ጠቅሰው አመልካች አለኝ የሚለው ይሄው የሰነድ ማስረጃ በፍርድ ቤት እገዛ እንዲቀርብላቸው በማስረጃ ዝርዝር መግለጫቸው ላይ የጠቀሱ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ውስጥ ያሉት ሰነዶች የሚያሳዩት ሐቅ ሲሆን የስንብት ደብዳቤው መሰረት ያደረገው የዲስፕሊን ኮሚቴውን ውሳኔ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሲታይ በዚህ ውሳኔ መሰረት ተጠሪ በ17 የዲስፕሊን ክሶች ተከሰው በ15ቱ ጥፋተኛ ሁነው የዲስፕሊን ኮሚቴ ማግኘቱን፣ጥፋቶቹም ከባድ መሆናቸውን ጭምር የሚገልጽ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ላይ ክስ ያቀረቡት መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ.ም እንደመሆኑ መጠን አመልካች ስንብቱ ሕጋዊ ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች በዲስፕሊን ኮሚቴው ውሳኔና ይህንኑ የሚደግፉትን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችን በማስረጃነት ቢያቀርብ ከስንብቱ በኃላ የተገኘ ማስረጃ ነው ተብሎ የማስረጃነት ዋጋ የሚያጣበት የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ደንብ የለም፡፡ አንድ ማስረጃ ለአንድ ጉዳይ ሊቀርብ አይገባም ተብሎ ውድቅ መደረግ ያለበት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሁኖ ሲገኝ ወይም በሕጉ ለማስረጃነት እንዲቀርብ ተለይቶ የተቀመጠ የማስረጃ አይነት መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሳኔን እና የኦዲት ሪፖርት ማስረጃዎችን ውድቅ ያደረጉት ተገቢውን የማስረጃ አቀራረብና አቀራረብ ስርዓት ተከትሎ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች የማስረጃነት ዋጋ አላቸው ከተባሉ ደግሞ በማስረጃዎቹ የተረጋገጡት የዲስፕሊን ጥፋቶች ከባድ መሆናቸውንና የተደጋገሙ መሆኑን የሚገልፁና ተጠሪ ስራቸውን በአግባቡ የማይወጡ የነበሩ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ተጠሪ ከባድ የዲስፕሊን ግድፈቶች ሲፈጽሙ የነበረ ከሆነና ጥፋቶችም ተደጋጋሚ መሆናቸው ግልጽ ከሆነና አመልካች በተጠሪ የስራ ግዴታቸውን በአግባቡ ባለመወጣት ስራው በአግባቡ ያልተሰራለት፣በገንዘብ ጥቅሙ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ከተረጋገጠ በአመልካች ማህበር የገንዘብ ጥቅም ላይ ጉዳት ያለመደረሱን የማስረዳት ግዴታ የተጠሪ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ተጠሪ የአመልካች የሠነድ ማስረጃዎች የተጠሪን ጥፋት የሚያረጋግጡ አይደሉም ከማለት ውጪ ይህንኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ያለማቅረባቸውን የሥር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ በማስቀረብ ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ የፈፀሙት ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1/ሸ/ የሚሸፈንና የተጠሪን የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪ የተፈፀመ ጥፋት የለም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲሉ የሰጡት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/ እና አንቀጽ 12(2) (7) ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት፣መንፈስ አላማ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የተጠሪን የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1(ሸ)) እና 12(2)(7) ድንጋጌዎች መሰረት ሕጋዊ እንጂ ሕገ ወጥ ተግባር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42383 ህዳር 19 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 139394 ሐምሌ 30 ቀን 2006 ዓ.ም ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ ሕጋዊ ነው፣አመልካች ለተጠሪ ካሳም ሆነ የሥራ ስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡
3. የዓመት እረፍት የ57 ቀናት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ብር 8,550.00 (ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ብር) እና ይህንኑ ክፍያም ያላግባብ ያዘገዬ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ መሰረት የአንድ ወር ደመወዝ ብር 4,500.00 (አራት ሺህ አምስት መቶ) ይክፈል ብለናል፡፡
4. ለክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

# <u>ት እ ዛ ዝ</u>

ጥቅምት 26 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**የ/ማ**

የሰ/መ/ቁ106610

ግንቦት 14 ቀን 2007

ዳኞች - አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ ካብራክ ተኮላ - ጠበቃ ጋር ቀረበ

**ተጠሪ** ፡-የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጆስቲክስ - ነ/ፈ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት ከታህሳስ 26/2000 - ጥር 29/2005 ዓ.ም ድረስ ለ5 አመት ከ1 ወር ስሰራ ቆይቼ ስራዬን በራሴ ፍቃድ ብለቅም፤ የስንብት፤ ለዘገየበት እና አበል አልተከፈለኝም በማለት እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ አመልካች ያለደሞዝ የወሰዱት እረፍት ከተጠናቀቀ ከህዳር 17/2005 ዓ/ም ጀምሮ ወደ ሥራ ያልገቡ መሆኑን በመረዳቱ ከህዳር 17 /2005 ዓ/ም ጀምሮ ውላቸው መቋረጡን ፤ እና 5 አመት ያልሞላቸው በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ስለሆነ ስንብት አይገባቸውም፤ ይገባቸዋል ከተባለም የማስጠንቀቂያ ግዜ 1 ወር ደሞዝና የቦንድ መግዣ ተቀንሶ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም ተጠሪ የአመልካችን የስራ መልቀቅ ጥያቄ ከ29/6/2005 ጀምሮ ከተቀበለ እና ካሰናበታቸው በኂላ የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያት መፈጸሙን አረጋግጫለሁ በማለት ሌላ ደብዳቤ በመጻፍ ክፍያ አልፈጽምም የሚልበት ምክንያት አይኖርም በመሆኑም የ5 አመት ከ1 ወር የስንብት ክፍያ የቦንድ ተቀንሶ ተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በቀጣይነት ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም ተጠሪ አመልካችን የመልቀቂያ ጥያቄ ተቀብሎ ቢያሰናብተውም፤ ድርጊቱ ስህተት ነው ብሎ ካመነበት ስህተቱን ለማረም ይችላል፤ አመልካችም ከህዳር 17 ቀን 2005 ጀምሮ በስራ ላይም አልተገኙም፤ በመሆኑም ተጠሪ ውል ማቋረጫ ምክንያት አግኝቻለው በማለት የስንብት አልከፍልም ማለቱ ባግባቡ ነው፤ በማለት የስር ውሳኔን ሽሮታል፡፡ የአመልካች አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ፤ ስራዬን የለቀቅኩት በጥር 29/2005 በጻፍኩት ደብዳቤ ሲሆን

ተጠሪም የስንብት ደብዳቤ በሚያዝያ 11/2005 ሰጥቶኛል፡፡ ይሁን እንጂ በ17/03/2005 ነበር ወደ ስራ መመለስ የነበረብህ፤ ግንቦት 8/2005 ስህተት መፈፀሜን ተረዳሁ በማለት ጥር 29/2005 ያስገባውን ደብዳቤ አልቀበልም በማለት ከእረፍት በኋላ ወደስራ አልገባህም በማለት ከ ህዳር 17/2005 ጀምሮ ነው፤ መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ የተጠቀሰውም የሰበር ውሳኔ ቁ 45889 ከተያዘው ጉዳይ አይመሳሰልም፡፡ ሰራተኛውና አሰሪው የስራ ውላቸው ጸንቶ ባለበት የሚደረግ እርምት እንጂ፤ ከስራ በገዛ ፍቃዱ ለለቀቀ ሰራተኛ ኪሊራንስ ተሰጥቶት ከ4 ወር በኋላ ስህተትን ማረም አይደለም፡፡ በመሆኑም በፍቃዴ ከተሰናበትኩ በኋላ ግንቦት 8/2005 የተጻፈውን፤ የተጠሪን ደብዳቤ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተቀብሎት፤ አመልካች ከህዳር 17/2005 በኋላ ወደስራ ያለመግባቱ ተረጋግጦ እርማት መደረጉ ባግባቡ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

በዚህም መሰረት ችሎቱም አመልካች የሥራ መልቀቂያ ለተጠሪ ሚያዝያ 11/2005 ዓ.ም ከሰጠው በኋላ፤ እንደገና ያለደሞዝ የወሰድከው ዕረፍት የተጠናቀቀው በ17/3/2005 ሆኖ ወደሥራ አልገባህም በማለት ከዚሁ ግዜ ጀምሮ የስራ ውሉን ማቋረጡ፤ እና ጥር 17/2005 ክሊራንስ እንዲያዞር ከመፍቀዱ አኳያ ስንብቱ ህጋዊ ነው መባሉን በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙ በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ እንዲቀባበሉ በማድረግ አከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በሰበር መልሱ የሚከራከረው፡- አመልካች እረፍታቸውን ጨርሰው ካልተመለሱ ማስታወቂያ በማውጣት ጥሪ በማድረግ ካልመጡ ውል ማቋረጡ የተሻለ ይሆን ነበር፤ ይህ ያለመደረጉ ምንም መብት አይፈጠርላቸውም እንጂ፤ ሌላው ኪሊራንስ የተሰጣቸው አስተዳደሩ ስራ ላይ ነበሩ በሚል እምነት ነው፤ አመልካች ወደ ስራ መመለስ ከነበረባቸው 17/3/05 ጀምሮ እስከ ጥር 30/2005 ድረስ ወደስራ አልተመለሱም፤ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27/1/ ለ መሠረት ከ5 ቀን በላይ ስለቀሩ መሰናበታቸው ባግባቡ ነው፤ በመሆኑም ተጠሪ የፈጸመውን ስህተት ባወቀበት ጊዜ ማረሙና አመልካችን ማሰናበቱ አግባብነት ያለው በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው መባሉ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት ይከራከራል፡፡ አመልካች በበኩሉ፡- ከተጠሪ ጋር በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 25 መሰረት በስምምነት የስራ ውላችንን ካቋረጥን በኋላ እና ተጠሪ ጥያቄዬን ተቀብሎ፤ ክሊራንስ አዞሬ እንድወጣ ከፈቀደና ውሉ ከተቋረጠ ወድያ የሚታረም ነገር አይኖርም በማለት የስር ክርክሩን በማጠናከር የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ እኛም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

በመሆኑም ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የክርክሩን አጠቃላይ ሂደትና የስር ውሳኔዎችን እንዳየነው አመልካች በራሳቸው ፍቃድ የስራ መልቀቂያ በመጠየቅ ተጠሪም በጥያቄው መሰረት እንዲፈጸም ፈቅዶና አመልካችን ካሰናበተ በኋላ፤ ያለማስጠንቀቂያ የሚያሰናብት ምክንያት አገኘሁ በማለት አስፈላጊውን ክፍያ አልከፍልም በማለቱ ነው፡፡ እንግዲህ ተጠሪ የሚለው አመልካች እረፍት በ17/2/2005 ወስደው ወደስራ መመለስ የነበረባቸው በ17/3/2005 ሆኖ ሳለ በቦታው ተገኝተው ስራ ባለመጀመራቸው እና በስህተት በጥር 30/2005 የቀረበውን የአመልካች መልቀቂያ ጥያቄ ተቀብለን ሚያዝያ 11/2005 እንዲፈጸም ብናደርግም ስህተት መሆኑን በመረዳታችን ከህዳር 17/2005 ጀምሮ ማሰናበታችን ባግባቡ ነው የሰበር ሰሚው ውሳኔ 45889 አሰሪው ስህተቱን ማረም የሚችል መሆኑን ወስኗል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ያየው ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የስራ መልቀቂያ ተቀብሎ ካሰናበተው በኋላ ሌላ ምክንያት አገኘሁ በማለት ድጋሜ ደብዳቤ መጻፍ ተገቢነት የለውም በማለት የስንብት ክፍያ ለአመልካች እንዲከፈላቸው ቢወስንም፤ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ካየው በኋላ ተጠሪ ስህተቱን ማረም ይችላል ሲል የአመልካች ስንብት ባግባቡ ነው በማለት የስር ውሳኔን ሽሮታል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ሊያርሙት የሚችሉት ስህተት የትኛውን አይነት ስህተት ነው የሚለውን ስናይ የሰበር ውሳኔ ቁ. 45889 ከተያዘው ጉዳይ የማይገናኝ በመሆኑ መከራከሪያ ሊሆን አይገባም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን የመልቀቂያ ጥያቄ ተቀብሎና ለአግባብነቱም ምላሽ ሰጥቶ ካሰናበታቸው እና የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለት ከወራት በኋላ ወደኋላ ተመልሶ ስህተት መፈጸሜን ተረዳሁ ማለቱ ባለቀ ጉዳይ ስህተት ማፈላለግ ካልሆነ በቀር፤ ተጠሪን የመሰለ ድርጅት አስተዳደራዊ ስራውን ባግባቡ ባለመወጣት በፈጸመው ጉዳይ የአዋጁን ቁ 377/96 አንቀጽ 27/1//ለ/ን ጠቅሶ ለመከራከር መሞከሩ አግባብነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ እረፍት የሰጠውን ሰራተኛ በተባለው መመለሻ ጊዜ ካልገባ ምን ሊደረግ እንደሚገባ ሳያውቅ የአመልካችን መልቀቂያ ያስተናግዳል ተብሎም የሚታሰብ አይሆንም፡፡ ባጠቃላይ የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ በፍሬ ነገር ደረጃ በማረጋገጥ ክፍያ እንዲከፈላቸው የወሰነው ውሳኔ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አግባብነት የሌለው አሰሪ ስህተቱን ማረም ይችላል ተብሎ የተወሠነው አስገዳጅ ውሣኔ ተጠቅሶ መሻሩ ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡

በመጨረሻም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከስንብት በኋላ የተሰጠውን የውል ማቋረጫ ምክንያት በመቀበል ተጠሪ ስህተቱን ማረም ይችላል በማለት የስር ውሳኔን መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.139381 በቀን 13/12/06 ዓ/ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 09937 ህዳር 16/2006 የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአመልካች የስንብት ክፍያ ብር 7,540.50 ይከፈላቸው በማለት የወሰነው ጸንቷል፡፡
3. የግራቀኙ የወጪ ኪሳራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ማ/አ**

የሰ/መ/ቁ. 107002

ግንቦት 14 ቀን 2007ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ሲስተር ትዕግስት ፈቃድ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኤድስ መከላከያ ማህበራዊ አገልግሎት ድርጅት አልቀረበም

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 177544 መስከረም 22 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 197235 ህዳር 17 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣራቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ መደብ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በምዕራብ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ውሳኝ ቦርዱ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ፡፡

1- አመልካች በተከሳሽ (ተጠሪ) ድርጅት በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በነርስ ካውንስለር ሰባተኛ ደረጃ ተቀጥሬ በመሥራት ላይ እያለሁኝ የቤተሰብ ችግር ስላጋጠመኝ በራሴ አቤቱታ አቅራቢነት በደረጃ ሶስት የነርስ ካውንስለር የሥራ መደብ ወደ ነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተዛውሬና ተመድቤ በመሥራት ላይ እገኛለሁ ፡፡ ሆኖም ተከሳሽ እኔ በፊት ተቀጥሬበት የነበረው ሰባተኛ ደረጃ ነርስ ካውንስለር ለመመደብ መስፈርቱን የሚያሟላ የውስጥ ሠራተኛ የለም አግባብ ባልሆነ መንገድ የመሥሪያ ቤቱን መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ ከአምስት ዓመት በፊት የሥራ ስንብት ክፍያና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ከፍሎ ያሰናበታትን ሠራተኛ በመጥራት ያለምንም ውድድር በመቅጠር ደረጃ ሰባት ነርስ ካውንስለር አድርጎ መድቧታል፡፡ ከሳሽ መስፈርቱ የሚማላ የውስጥ ሠራተኛ እያለሁ የውስጥ ሠራተኞች ተወዳድረው በእድገት በሚመደቡበት የሥራ መደብ ላይ የነቀምቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እኔን በቦታው ላይ መመደብ ሲገባው የውጭ ማስታወቂያ በማውጣት ቅጥር መፈፀሙ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ የሚጥስና የእኔን መብት የሚያጣብብ

በመሆኑ፣ቅጥሩን በመሰረዝ እኔን በቦታው ላይ እንዲመድቡኝ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት የምዕራብ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ክስ አቅርባለች፡፡

2- ተከሳሽ (ተጠሪ በበኩሉ ከሳሽ በሶስተኛ ደረጃ ነርስ ካውንስለር የሥራ መድብ ተመድባ የምትሠራ ሠራተኛ ናት ከሳሽ አራት ደረጃዎችን በመዝለል ደረጃ ሰባት ነርስ ካውንስለር ሥራ መደብ ላይ መመደብ አለብኝ በማለት ያቀረበችው ክስ የህግ ስህተት የለውም ፡፡ ከሳሽ ለደረጃ ሰባት የሚመጥን የሙያ ብቃት ስነምግባርና የሥራ አፈፃፀም የላትም ፡፡ ባለው የሥራ መደብ ፤ሥራውን ለመሥራት የሚችል ሠራተኛ በዕድገት ወይም በቅጥር የመመደብ መብት ያለው አሠሪው (ድርጅቱ) እንጅ ሠራተኛው አይደለም ፡፡ ከሳሽ ያለምንም ውድድር የሥራ መደቡ እንዲሰጣት ያቀረበችው ክስ ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

3- የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ከሳሽ በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ፣ተመድባ ስትሠራ የነበረ መሆኑ በተከሳሽ አልተካደም ከሳሽ ወደ ወለጋ ቅርንጫፍ የተዛወረችውና በደረጃ ሶስት የሥራ መደብ ላይ ተመድባ ለመሥራት የተስማማችው በቤተሰብ ችግር ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል ፡፡ ተከሳሽ ከሳሽ በዲሲፒሊን ችግር ምክንያት ወደ ደረጃ ሶስት ብቅ ብላ የተመደበች ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ስለዚህ ተከሳሽ ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ተመድባ ስትሠራ የነበረችውን ተከሳሽን ሣያሳውቅ ከውጭ ሌላ ሰው የቀጠረው ከሳሽ ቦታውን እንዳታገኝ ለማድረግ በማስብ በክፋ ልቦና ነው፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ከሳሽን በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ መድቦ የደመውዝን ልዩነት አስቦ ሊከፍል ይገባል በማለት በድምፅ ብልጫ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4- የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሠኘት ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ መልስ ሰጭ (አመልካች) ያለውድድር በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ እንድትመደብ የሰጠው ውሳኔ የመሥሪያ ቤቱን የሥራ አመዳደብ መመሪያ መሠረት ያላደረገ ነው በማለት ቦርዱ የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል ፡፡ አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርባለች ፡፡ የክልሉ የሰበር ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም ፡፡

5- አመልካች ህዳር 18 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በአንድ የሥራ መደብ ላይ የውጭ ሰው የሚቀጠረው በመጀመሪያ ለቦታው የሚመጥን የውስጥ ሠራተኛ ካለ እድል ከሰጠ በኃላ መሆን እንዳለበት በግልፅ ያስቀምጣል ፡፡ አመልካች በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ተመድቤ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ስሰራ እንደነበር ተረጋግጧል ፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት አመልካች

በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ልትመደብ አይገባትም በማለት የሰጡት ውሳኔ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክታለች ፡፡ ተጠሪ መጋቢት 23 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ያለውድድር በቀጥታ ለመመደብ ጥያቄ ያቀረበችበት ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ለመወዳደር የሚስፈልገው የትምህርት ደረጃ አድቫንስድ ዲፕሎማ ሲሆን አመልካች ያላት ድፕሎማ በመሆኑ ለቦታው ለመወዳደር አትችልም አመልካች አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ደረጃ ሰባት ተመድባ የነበረው በድሮው መዋቅር ነው፡፡ ስለዚህ ያለምንም ውድድር በደረጃ ሰባት እንድትመደብ የተሰጠውን ውሣኔ መሻሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሚያዚያ 8/ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ በነርስ ሙያ ዲፕሎማና ዲግሪ የትምህርት መርሃ ግብር እንጂ አድቫንስድ ዲፕሎማ የሚባል የትምህርት መረሃ ግብር የለም በነርስ በአድቫንስ ዲፕሎማ የተመረቀ ባለሙያ የለም ፡፡ ተጠሪ ዕውነትነት የሌላቸውን መስፈርቶች በማንሣት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክራለች፡፡

6- ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት ግራቀኙ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት አመልካች በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መስፈርቱን የማሟላው ሠራተኛ ሣልወዳደር የደረጃ እድገት ሣይሰጠኝ ተጠሪ ቅጥር በመፈፀም የሥራ መደቡን ማስያዙ ሕገ ወጥ ስለሆነ ቅጥሩ ተሰርዞ እኔ በቦታው ላይ እንድመደብ በማለት ያቀረበችውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምረናል ፡፡

7- ጉዳዩን እንደመረመርነው በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ክፍት የሥራ መደብ ሲኖር ድርጅቱ ሌላ ሠራተኛ ከመቅጠሩ በፊት መስፈርቱን የሚያሟሉ የድርጅቱ ሠራተኞች ካሉ ተወዳድረው በእድገት በቦታው ላይ እንዲመደቡ እድል መስጠት ያለበት መሆኑ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና የሰው ሀይል አመዳደብ መመሪያ በግልፅ የተደነገገ በመሆኑን አመልካችና ተጠሪ የሚተማመኑበት ነጥብ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጭብጥ አመልካች ተጠሪ የመተዳደሪያ ደንቡንና መመሪያውን በመጣስ ለደረጃ ሰባት የሚያስፈልገውን መስፈርት የማሟላ ሠራተኛ እኔ እያለሁ ለእኔ እድል ሣይሰጠኝ ከውጭ ሠራተኛ በመቅጠር የስራ መደቡን ማስያዙ ህገወጥ ነው በማለት ያቀረበችውን ክስ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ በመካድ በነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የነበረውን ደረጃ ሰባት የስራ መደብ በቅጥር ሰው ያሟላሁት ካሉኝ ሠራተኞች ለሥራ መደቡ የሚያስፈልገውን መስፈርት የሚያሟላ ሠራተኛ ስለሌለኝ ነው፡፡ አመልካችም ለደረጃ ሰባት የሚያስፈልገውን መስፈርት አታሟላም የሚል ክርክር በማቅረቡ ነው፡፡ ይህም የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 በሚደነግገው መሠረት ፣ተጠሪ ደረጃ

ሰባት የሥራ መደብ በውጭ ቅጥር ያሟላው የሥራ መደቡ የሚያስፈልገውን መስፈርት የሚያሟሉ ሠራተኞች እንዲወዳደሩ እድል ከሰጠ በኋላ መስፈርቱን የሚያሟላ ሠራተኛ ባለማግኘቱ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው አከራካሪ ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡

8- ተጠሪ በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላይ የውጭ ቅጥር በመፈፀም በሥራ መደቡ ላይ ሠራተኛ ከመመደቡ በፊት የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና የሰው ሀይል ምደባ አፈፃፀም መመሪያ በሚደነግጉት መሠረት በሥራ መደቡ የሚያስፈልገውን የትምህርት ዝግጅት፣የሥራ ልምድና ሌሎች መስፈርቶች የሚያሟሉ ሠራተኞች ማስረጃውን በማቅረብ እንዲወዳደሩ እና እንዲመዘገቡ የእድገት ማስታወቂያ ያላወጣና መስፈርቱን የሚያሟሉ ሠራተኞች እንዲወዳደሩ እድል ያልሠጠ መሆኑን የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሣኔ ተረድተናል ፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ አመልካችና ሌሎች የድርጅት ሠራተኞች ለደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ለመወዳደር የሚያስችላቸውን ማስረጃ በማቅረብ እንዲወዳደሩ የውስጥ የእድገት ማስታወቂያ ሣያወጣና መስፈርቱን ለሚያሟሉ ሠራተኞች እድሉን ሣይሰጥ ፣ሠራተኛ በመቅጠር በደረጃ ሰባት ላይ መመደቡ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብና የሰው ሀይል አመዳደብ መመሪያ መሠረታዊ መርህ የሚጥስና ህጋዊ ዕውቅና ሊሰጠው የማይገባው ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡

9- ተጠሪ የራሱ የሆነ የሥራ መዋቅር ፣አደረጃጀትና የሥራ መደብ ያለው ድርጅት መሆኑ አያከራክርም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ በተለያዩ አካባቢዎች በራሱ የሆኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያሉት መሆኑንና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹም ያላቸው ተመሳሳይ የሥራ መደቦች የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጅት፣የሥራ ልምድና ሌሎች መስፈርቶች ተመሣሣይነት ያላቸው እንደማይሆኑና በተመሣሣይ የሥራ መደብ ተመድበው ለሚሠሩ ሠራተኞች የሚከፈለው ደመወዝና ሌሎች ሁኔታዎች ተመሣሣይነት ያላቸው እንደሚሆኑ ከተጠሪ ድርጅታዊ ተፈጥሮአዊ ባህሪና መተዳደሪያ ደንብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ ሰባት ነርስ ካውንስለር የሥራ መደብ ላይ ለመመደብ የሚያስፈልገው መስፈርትና በነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ ሰባት ነርስ ካውንስለር የሥራ መደብ የሚያስፈልገውን መስፈርት አንድ አይነትና ተመሣሣይ መስፈርቶች መሆናቸውን በመካድ ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ መስፈርት በሟሟላት ተመድባ ስትሠራ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ አዲስ አበባ የነበራትን ደረጃና ደሞወዟን በመቀነስ ወደ ነቀምት ቅርንጫፍ የተዛወረችው በነበረባት የቤተሰብ ችግር ምክንያት አመልካች ጥያቄ በማቅረቧ ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተመድባ ስትሠራበትና ደመወዝ ስትበላበት ለነበረው ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ለመወዳደር

የሚያስፈልገውን መስፈርት አታሟላም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሠረት ያለው መከራከሪያ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ ለአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ያላቀረበውን አዲስ የፍሬ ጉዳይ መከራከሪያ በዚህ ሰበር ችሎት በማንሣት ለደረጃ ሰባት የሚያስፈልገው የነርስ አድቫንስድ ዲፕሎማ ነው የሚልና መዋቅሩ ስለተለወጠ መስፈርቱም ተለውጧል በማለት ያቀረባቸው መከራከሪያዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀፅ/1/ የሚጥስ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው መከራከሪያ ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ተጠሪ የነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ባለው ደረጃ ሰባት ክፍት የሥራ መደብ ለመወዳደር አትችልም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

10- አመልካች በተጠሪ ድርጅት ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላይ ተመድባ በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስትሠራ የነበሩ መሆኑንና አመልካች ይህንን የሥራ መደብ ለቅቃ በነቀምት ጽ/ቤት በደረጃ ሶስት የሥራ መደብ የተመደበችው በራሷ ጥያቄ አቅራቢነት መሆኑ ፣ተጠሪ በነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላለው ክፍት ቦታ ለመወዳደር የሚያስችላት ቢሆንም ፣ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ሣትወዳደር የሥራ መደቡን ለማግኘት የሚያስችላት አይደለም ፡፡ ከዚህ አንፃር የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ አመልካች ከሌሎች ሠራተኞች ጋር በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ የመወዳደር እድል እንዲሰጣት ውሣኔ መስጠት ሲገባው አመልካች ያለምንም ውድድር ደረጃ ሰባት ላይ እንድትመደብ የሰጠው ውሳኔ የተጠሪን መተዳደሪያ ደንብና የሰው ሀይል አመዳደብ መመሪያ ያልተከተለ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት አሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ አመልካች ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላይ ያለምንም ውድድር እንድትመደብ የሰጠውን ውሣኔ መሻራቸው ተገቢ ቢሆንም ፣ተጠሪ አመልካችና ሌሎች ሠራተኞችን በማወዳደር የውስጥ እድገት ማስታወቂያ ሣያወጣና ለሠራተኞች እድል ሣይሰጥ የውጭ ቅጥር መፈፀሙ ህገወጥ ተግባር በመሆኑ ፣ተጠሪ የፈፀመው ቅጥር ተሰርዞ አመልካችንና ሌሎች ሠራተኞችን በማወዳደር በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ በእድገት እንዲመደብ ውሣኔ ሣይሰጡ ማለፋቸው አመልካች ያቀረበችውን ግልፅ የዳኝነት ጥያቄና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀፅ 2 ያላገናዘበና በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የምዕራብ ኦሮሚያ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ የውስጥ እድገት ማስታወቂያ ሣያወጣና አመልካችና ሌሎች ሠራተኞች ተወዳድረው በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ለማደግና ለመመደብ የሚያስችላቸውን እድል ሣይሰጥ የውጭ ቅጥር በመፈፀም ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላይ መመደቡ ሕገወጥ ተግባር በመሆኑ ተጠሪ በደረጃ ሰባት ላይ የፈፀመው ቅጥር ሊሠረዝ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች በደረጃ ሰባት የስራ መደብ ለመወዳደር የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን የምታሟላ በመሆኑ ፣ተጠሪ አመልካችንና ሉሎች መስፈርቱን የሚያሟሉ ሠራተኞችን በማወዳደር የውስጥ እድገት ሊሰጥ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለያራሳቸው ይቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

የሰ/መ/ቁ. 111839

ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ፒ.ኤስ አይ ኢትዩጵያ - ጠበቃ አላምነህ ስንሻው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ እሸቴ ካሳ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ሐምሌ 24 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ክስ በአመልካች ድርጅት በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባለበት ሁኔታ ያላግባብ ከስራ መሰናበታቸውን ገልፀው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ የድርጅቱን መኪና ባግባቡ የመንዳት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ.ም ሰው ገጭቶ ጉዳት ማድረሱንና ከዚህ በኋላም ሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ/ም ከደሴ ወደ መቐሌ በሚሄድበት ጊዜ በግድየለሽነት በማሽከርከር በመኪናው ላይ ጉዳት ከማድረሱም በላይ በተሽከርካሪው ውስጥ በነበሩት የድርጅቱ ሰራተኞች ላይ ቀላል የመቁሰል አደጋ ማድረሱንና ይህም በክፍሉ የትራፊክ ፖሊስ መረጋገጡንና አመልካችም ተገቢውን ኮሚቴ አቋቁሞ በማጣራት ከአረጋገጠ በኋላ ስንብቱን ያከናወነ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ/ም ደረሰ የተባለው አደጋ በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ የስራ ስንብት ማከናወኛ ምክንያት ያልሆነ በመሆኑ በይርጋ እንዲሚታገድ፣ ሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ/ም ደረሰ የተባለው አደጋ ደግሞ በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት በመኖሩ የደረሰ ነው ቢባልም በከባድ ቸልተኝነት የደረሰ ነው ሊባል የሚችል ያለመሆኑን ጠቅሶ የአመልካችን የስንብት እርምጃ ሕገወጥ መሆኑን በመደምደም ተጠሪ የአምስት ወር ከስድስት ቀናት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም። የአሁኑ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 24 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- የተጠሪ ድርጊት በሕጉ አግባብ ሲጣራ ቆይቶ ተጠሪ ከባድ ቸልተኝነት ያለባቸው መሆኑ ከተረጋገጠ በኂላ ለተፈፀመው እርምጃ ድርጊቱ በይርጋ የታገደ ነው መባሉ አሰሪ የሰራተኛውን ጥፋት በትክክል አወቀ ሊባል የሚችልበትን አግባብና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/1/ ስር ስለ ከባድ ቸልተኝነት የተመለከተውን የህጉን ድንጋጌ ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው። የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም ሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ.ም ደረሰ ለተባለ አደጋ የተጠሪ ቸልተኝነት ከባድ ሊባል የሚችል አይደለም ተብሎ የስንብቱ እርምጃ ሕገወጥ ነው መባሉ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባለበት ወቅት ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ.ም መንገደኛ በነበረው ሰው ላይ ጉዳት አድርሰዋል፣ሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ.ም ደግሞ የአመልካች ድርጅት ሰራተኞችን ከደሴ ወደ መቐሌ ለስራ ይዞ በመሄድ ላይ እያለ መንገዱ ጠመዝማዛና የአየሩ ሁኔታም ዝናብማ ሁኖ እያለ ከጥንቃቄ ጉድለት መኪናውን እንዲወድቅ በማድረግ በመኪናው ላይ ጉዳት አድርሷል፣በሰራተኞች ላይም ቀላል የመቁሰል አደጋ አድርሷል ተብሎ ስንብቱ የተከናወነ መሆኑንና የስር ፍርድ ቤቶች ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ.ም ተፈጸመ የተባለው ጥፋት በሰላሳ ቀን የይርጋ ጊዜ መታገዱን፣የሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ.ም ጥፋት ግን በወቅቱ ዝናባማ የአየር ሁኔታ በነበረበትና መንገዱ እርጥበታማና ቁልቁለታማ በሆነበት አካባቢ የተፈፀመ ቢሆንም በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት ነበር ከሚባል በስተቀር በአዋጁ በተመለከተው አግባብ ከባድ ቸልተኝነት ነበር ሊባል የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች የወሰኑ መሆኑን ነው። በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የተጠሪ አድራጎት በከባድ ቸልተኝነት ስር ሊወድቅ ይችላልን? የሚለው ነው።

በመሠረቱ አንድ ሠራተኛ ለስራው የተሰጡትን መሣሪያዎችና እቃዎች ሁሉ በጥንቃቄ የመጠበቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 13/3/ ስር የተመለከተ ሲሆን በአሠሪው ንብረት ወይም

ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 27/1/ሸ/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ሆኖም ከባድ ቸልተኝነት የሚለውን ቃል መለኪያ በተመለከተ ሕጉ በግልጽ አያሣይም፡፡ ይሁን እንጂ ቸልተኝነት የጥንቃቄ ጉድለት እንደመሆኑ መጠን የጥንቃቄ ዓይነትና ደረጃ እንደየድርጊቱና አድራጊው የስራ ድርሻ አኳያ በመመልከት ምላሽ ለማግኘት እንደሚገባ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 41115 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የጥፋት ደረጃ "ከባድ ቸልተኝነትን" ሊያቋቁም የሚችል መሆን አለመሆኑን ከስራቸው ባህርይ አንፃር መመልከቱ የግድ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ስራቸው ሹፌር ሲሆኑ ከስራቸው በተያያዘ ሁኔታ ጥንቃቄ ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ መኪናውን የሚያሽከረክሩበትን አግባብ ከአከባቢው አየር ሁኔታ እና ከመልክዓ ምድሩ ጋር በአገናዘበ መልኩ መሆን ያለበት መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡በመሆኑም በዝናባማ የአየር ሁኔታና ጠመዝማዛና ቁልቁለታማ በሆነ መንገድ በዝግታና በጥንቃቄ ተሽከርካሪን ማሽከርከር ከአንድ አሽከርካሪ የሚጠበቅ ሙያዊ ግዴታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ መኪናውን ዝናባማ በሆነ የአየር ሁኔታ ውስጥ በጠመዝማዛና ቁልቁለታማ በሆነ መንገድ ላይ ተጠሪ ማርሹን በተመጣጣነ ማርሽ አስሮ ባለማሽከርከሩ አደጋው መደረሱ በክፍሉ ፖሊስና አመልካች ባቀረባቸው ሌሎች ማስረጃዎች የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ማስተባበያ ማስረጃ ያላቀረበበት ጉዳይ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶችም ተጠሪ ሲያሽከረክሩት የነበረው መኪና በተጠቀሰው የአየር ሁኔታና መልክዓ ምድር ላይ ሲሽከረከር ተጠሪ ተገቢውን ማርሽ አስሮ ሲሽከረክር ነበር በማለት የደመደሙት ፍሬ ነገር ያለመኖሩን የውሳኔያቸው ይዘት ያስገነዝባል፡፡

ተጠሪ መኪናውን ሲያሽከረክሩ የነበረበት ሁኔታ ከላይ የተገለጸው ነው ከተባለ ደግሞ ትክክለኛ አእምሮ ባለው ሰውና በተጠሪ የግል ሁኔታ መመዘኛ መሠረት ከባድ ቸልተኝነትን ሊያሣይ የሚችል አይደለም ሊባል የሚችልበትን አግባብ አላገኘንም፡፤፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪ ጥፋት ከባድ ቸልተኝነት አይደለም ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ሁኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.10762 ታህሳስ 06 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.19554 የካቲት 19/ 2007 ዓ.ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-10681 መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡

3. በዚህ ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ተ**

የሰ/መ/ቁ. 110615

ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** ኃብተሚካኤል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር -

ሥራ አስኪያጅ አቶ ተካልኝ ሁንዴ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ታመነ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22279 ሐምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 187457 የካቲት 9 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው የሰበታ ሀዋሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሕግ አግባብ ውጭ የሥራ ውሌ ተቋርጧል በማለት ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ አመልካች ሆነው ተከራክረዋል፡፡

1. ከሳሽ (ተጠሪ) ከተከሳሽ (አመልካች )ድርጅት ጋር በሠራተኝነት ተቀጥሮ ሲሰራ ተከሳሽ ከሕግ አግባብ ውጭ የሥራ ውሉን ያቋረጠው መሆኑን ገልፆ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡
   አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ በጥቅምት 2 ቀን 2006 ዓ.ም አደም ገረመው ከሚባል ሠራተኛ ጋር በመደባደብ በሥራ ቦታ ሁከት የፈጠረ መሆኑንና ህዳር 25 ቀን 2006 ዓ.ም የድርጅቱን ሥራ አስኪያጅ አልታዘዝም ከማለቱም በላይ “ዝም በል አንተ አሽሻም ፡፡ አሽሽ

አጭስህ መጥተሕ አፍህን አትክፈት፡፡ አእምሮ የሚያደነዝዝ አሽሽ ወስደህ ደንዝዘህ መጥተህ አታደንዝዘን" በማለት የተሳደበና ችግር የፈጠረ መሆኑ ከሥራ የተሠናበተ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል ፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የከሳሽንና የተከሳሽን ምስክሮች ሰምቷል የከሳሽ አንደኛው ምስክር ከሳሽ ከቅርብ አለቃው ጋር መጣላቱን የመሰከረ መሆኑንና የተከሳሽ ምስክሮች ጥቅምት 7 ቀን 1986 ዓ.ም ከሳሽ የድርጅቱን አንድ ሠራተኛ የደበደበ መሆኑንና 25/03/2006 ዓ.ም ከሳሽ የቅርብ አለቃውን ሀሽሻም ሀሽሽ አጭሰህ መጥተህ ትናገረናለህ ጠብ እና ግርግር ያነሳ መሆኑን በማረጋገጥ እንደመሰከሩ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሮ ተጠሪ /ከሳሽ/ አለቃውን አልታዘዘም ማለቱንና መስደቡ የተረጋገጠ በመሆኑ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት የተጠሪ /ከሳሽን/ ክስ ውድቅ አድርጎታል ፡፡

2. ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል ፡፡ የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክረክር ከሰማ በኃላ አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ተጠሪ አለቃውን ሰብዓዊ መብቱን በሚነካ መልኩ ስለሰደበው መሆኑ እንደተረጋገጠ ገልፆ አመልካች ተጠሪው ለፈፀመው ለዚህ ጥፋት ማስጠንቀቂያ መስጠት ሲገባው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጡ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌ መስፈርት የሚያሟላ አይደለም በማለት ስንብቱ ከሕግ አግባብ ውጭ የተፈፀመ ነው ተብሎ አመልካች ብር 8,284.24 /ስምንት ሺ ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከሃያ አራት ሳንቲም ) ለተጠሪ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል ፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የተጠሪ አድርጎት "ጠብና"አንባጓሮ ማንሣት ነው ተብሎ ሊያዝ አይገባም በማለት የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል ፡፡

3. አመልካች የካቲት 24 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የቅርብ ኃላፊውን አንድ ሠራተኛ ወደሌላ ቦታ ሄዶ እንዲሠራ ትዕዛዝ ሲሰጥ ትዕዛዙን ከመቃወም አልፈው የቅርብ አለቃውን አንተ ሀሽሻም በማለት የተሳደበና አምባጓሮ የፈጠረ፤ በዚህ ምክንያት የምርት ሥራው እንዲገታ ያደረገ መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል ፡፡ ይህ የተጠሪ አድራጎት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1/ረ መስፈርት አያሟላም በማለት የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል ፡፡ተጠሪ በበኩሌ ሚያዚያ 6 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ እኔ አለቃዬን አልተሳደብኩም ፡፡ ሁከትም አልፈጠርኩም ፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል ፡፡ አመልካች ሚያዝያ 20 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕጉን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ተጠሪ ህዳር 25 ቀን 2006 ዓ.ም በሥራ ቦታ ያሳየውን ባህሪይና የፈፀመውን አድራጎት በተመለከተ ፍሬጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የወረዳው ፍርድ ቤትና የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደረሱበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ ህዳር 25 ቀን 2006 ዓ.ም ተጠሪና ሌሎች አራት ሠራተኞች ሥራ እየሰሩ እያለ የቅርብ አለቃቸው ከእነሡ መካከል አንድ ሠራተኛ ወደ ሌላ የሥራ ክፍል እንዲሄድና ቀሪዎች አራቱ ቀሪውን ሥራ እንዲያከናውኑ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑ በዚህ ጊዜ ተጠሪ የቅርብ አለቃውን የሥራ ትእዛዝ ከመቃወም አልፎ ሀሽሻም ሀሽሽ አጭስህ መጥተህ ትናገረናለህ በማለት የተሳደበ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑንና የተጠሪ ማስረጃ ይህንን በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ ያላስተባበለ መሆኑን የወረዳው ፍ/ቤት በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል ፡፡

6. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው ተጠሪ የሥራ ትዕዛዝ ባለመቀበሉና የቅርብ አለቃውን ክብረ ነክ የሆነ ስድብ በመሳደቡ ምክንያት ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የደረሰበትን የፍሬ ጉዳይ ማጣሪትና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው በማለት የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተቀበለው መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22279 ሀምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በአራተኛው ገፅ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ይዘት ከተነተነ በኃላ ‹‹ በአጠቃላይ የመልስ ሰጭ ድርጅት ይግባኝ ባይን ከሥራ ያባረረው እሱ አለቃውን ሰብዓዊ ክብሩን መንካቱን በሚነካ መልኩ ስለሰደበው እንደሆነ ከመዝገቡ ውስጥ የምንረዳው ጉዳይ ነው በማለት በመጨረሻው ፓራግራፍ ካሰፈረው የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ ህዳር 25 ቀን 2006 ዓ.ም በቅርብ አለቃው የተሰጠውን የሥራ ትዕዛዝ ከመቃወም አልፎ የቅርብ አለቃውን አንተ ሀሽሽ አጭሰህ መጥተህ አትናገረን "በማለት የተሣደበ መሆኑን ፍሬጉዳይ ያማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩነት የላቸውም፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተለያዩት ይኸ የተጠሪ አድርጎት አመልካች ህዳር 26 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ በማቋረጥ ለወሰደው እርምጃ በቂና ህጋዊ

ምክንያት ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው የህግ ጥያቄ በሚመረምሩበትና መዝነው ውሣኔ በሰጠበት ጊዜ እንደሆነ ከውሣኔያቸው ለመረዳት ችለናል ፡፡

8. ሠራተኛው ከሥራ ውል የተመለከተውን ሥራ ራሱ የመሥራትና የሥራ ውሉና ደንቡ መሠረት በአሠሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታ ያለበት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1(1)እና ንዑስ አንፅ 2 ተደንግጓል ፡፡ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት በስራው ቦታ አንባጓሮ ወይም ጠብ አጫሪነት ጥፋት በፈፀመ ጊዜ አሰሪው ሰራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብተው የሚችል መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ(1)ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ የቅርብ አለቃው ከተጠሪ ጋር ከሚሠሩት አምስት ሠራተኞች አንድ ሠራተኛ ወደ ሌላ ሥራ ክፍል ለማሰማራት የሰጠውን ትዕዛዝ የተቃወመና በአዋጅ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 አሠሪው በሥራ ውሉና ደንቡ መሠረት የሰጠውን የሥራ ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ና አሠሪው ሌሎች ሠራተኞች የሥራ ትዕዛዝና ስምሪት የመስጠት መብት በመጋፋት የቅርብ አለቃውን “አንተ ሀሽሻም ሀሽሽ አጭሰህ መጥተህ አትናገረን “በማለት የተሳደበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

9. አመልካች የቅርብ አለቃው ላይ የስድብና ማዋረድ ተግባር የፈፀመው በወንጀል ሕግ ማንም ሰው እንዳይዘውና እንዳይጠቀም ክልክላ የተደረገበትን ሀሽሽ አጭሰህ መጥተህ ነው የምትናገረን በማለት እንደሆነ ተረጋግጧል ፡፡ ተጠሪ በቅርብ አለቃው ላይ የፈፀመው የስድብና ማዋረድ ተግባር፣በህግ የተከለከለ ተግባር ፈጽመሀል በማለት ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡም የሚያወግዘውንና የሚጠየፈውን ተግባር የቅርብ አለቃው ፈጽሞ መጥቶ ሰራተኞችን እንደሚበጠብጥ አድርጎ ሌሎች ሰራተኞች እየሰሙ በመግለፅ እንደሆነና ይህም የተጠሪ አድርጎትና ተግባር የአሠሪው ወኪል የሆነውን የቅርብ አለቃውን ሰብዓዊ ክብር በሚነካ ሁኔታ ተጠሪ የስድብና ማዋረድ ተግባር የፈፀመና በዚህ ምክንያት የተጠሪ የቅርብ አለቃ ስሜት ውስጥ እንደገባና ለጠብና ለድብድብ እንዲነሳሳ ለማድረግ አስቦና መርጦ የተናገረው መሆኑን ከግራቀኙ ክርክርና ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመረዳት ይችላል ፡፡ ይህንን የተጠሪ አድርጎት በአዋጅ ቁጥር 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ድንጋጌ ጋር በማነፃፀር ስንመለከተው “አሠሪው የሠራተኛውን ሰብዓዊ ክብርና ሞራልን የሚነካ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሠረት የሚያስቀጣ ሌላ አድርጎት የፈፀመ እንደሆነ ሠራተኛው የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ እንደሚችል ይደነግጋል

10. በዚህ መዝገብ እየታየ ያለው ጉዳይ ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ የተገለፁት ተግባራት በአሠሪው ሣይሆን በሠራተኛው የተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ተጠሪ የቅርብ አለቃው የሠጠውን የሥራ ትዕዛዝ አልፈፅምም ከማለት አልፎ አንተ ሀሽሻም ሀሽሽ አጭሰህ መጥተህ አትናገረን በማለት የቅርብ አለቃውን የሰደበና ያዋረደ መሆኑን በዚህ ምክንያት

ከቅርብ አለቃው ጋር ጠብ የተፈጠረ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሳያል ከዚህ አንፃር በአዋጅ ቁጥር 32 ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ) የተገለፀ ሁኔታ ሠራተኛው የቅርብ አለቃውን ሰብዓዊ ክብርና ሞራል የሚነካ የስድብና የማዋረድ ተግባር በመፈፀሙ ወይም ሌላ ህገወጥ ተግባር በመፈፀሙ ምክንያት በሥራ ቦታ በሠራተኛውና በቅርብ የሥራ ሀላፊው መካከል ጠብ የተነሳ መሆኑ ከተረጋገጠ አሠሪው በአዋጅ ቁጥር 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) በተደነገገው መሠረት የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ እንደሚችል የአዋጁን አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2፣የአዋጅ አንቀጽ 32(2) ሀ ከሚደነግገው በሚቃረን ሁኔታ ሠራተኛው የቅርብ የሥራ ሀላፊውን ሰብዓዊ ክብርና ሞራል የሚነካ ተግባር መፈፀም ሊያስከትል የሚችለውን ህጋዊ ውጤትና የአዋጁን አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 1(ረ) ድንጋጌ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪ በቅርብ አለቃው የተሰጠውን የሥራ ትዕዛዝ ከመቃወም አልፎ የቅርብ የሥራ ሃላፊውን አንተ ሀሽሻም ሀሽሽ አጭሰህ መጥተህ እኛን አትናገረን በማለት በመሳደቡና ከቅርብ አለቃው ጋር መጣላቱ የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በቂና ህጋዊ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰበታ ሀዋሳ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል የቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 እና በአንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 1(ረ) መሠረት በመሆኑ የሥራ ስንብቱ በሕግ አግባብ የተከናወነ ነው በማለት ወስነናል ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ 105997

ሚያዚያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ሉሊት አያሌው ማሞ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ማህሌት ዓለሙ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከሰራተኛ የስራ መደብና ቦታ ዝውውር ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም፡- የተጠሪ ድርጅት አመልካች የኢንዱስትሪ ሰላም አላግባብ ንትርክ እየፈጠሩ መረባሻቸውን ሳያረጋግጥ በ26/08/2005 ዓ/ም በፃፈው የአመልካችን የግል ታሪክ በሚያጎድፍ ደብዳቤ ከኦዲት ወደ ማርኬቲንግ ክፍል ያላግባብ በማዘዋወር እርምጃ መውሰዱን ጠቅሰው የተወሰደው እርምጃ እንዲነሳና ወደ ኦዲት ክፍል እንዲመለሱ እንዲሁም የዝውውሩ ደብዳቤ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም፡- አመልካች ከኦዲት ሰራተኞች ጋር ባላቸው አለመግባባት የተነሳ የኢንዱስትሪ እና የስራ ቦታ ሰላም ለመጠበቅ ሲባል የአመልካች የስራ ደረጃ እና ደመወዝ ሳይነካ ዝውውሩ መፈፀሙንና ክሱ ከተመሰረተ በኂላም የአመልካችን ደመወዝ ብር 10,759.00 ማድረጉን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን በመመርመር የሥራ መደብ ዝውውሩ ሕጋዊ ነው፣ የዝውውር ደብዳቤም ሊሰረዝ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካች ለኢንዱስትሪ ሰላም የፈጠሩት ችግር ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ እና በስራው ላይ ያስከተሉት ችግር መኖሩ በተጠሪዎች ምስክሮች ባልተነገረበት ሁኔታ ዝውውሩ ህጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክርና ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ ዝውውሩ ሕጋዊ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት አመልካች ከአቀረበው ክርክር ይዘትና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ለማየት ይቻል ዘንድ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር ብቻ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡
ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁን አመልካች ሥራዬን በአግባቡ እየተወጣሁ እያለ አሠሪው ወደ ሌላ የሥራ መደብ ተዛውረሻል በማለት ደብዳቤ ጽፎልኛል፣ ዝውውሩ ከፍላጎቴና ከህብረት ስምምነቱ ውጪ የተደረገ ከመሆኑም በላይ በግል ማህደሬ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል ነው በማለት ገልጸው ተከራከረው ተጠሪ ዝውውሩ የተደረገበትን ምክንያቶችን ዘርዝሮ በሕግ ከተሠጠው ስልጣን የመነጨ መሆኑንም ጭምር ጠቅሶ መከራከሩን ነው፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የተጠሪ ምስክሮች ቃል አመልካች ከሰራተኞች ጋር ብሎም ከሃላፊዎች ጋር ግጭት የሚፈጥሩ፣የሚሰጣቸውን ስራውም በአግባቡ የማይሰሩ ስለመሆኑ፣የስራ ባልደረቦቻቸው አብረዋቸው ለመስራት የማይመርጧቸው ሰው እንደሆኑ፣ ስራቸውን በአግባቡ ስለማይሰሩ የጊዜ ብክነት፣ አላስፈላጊ ውጪና ያልተቃና ስራ መከሰቱን መመስከራቸውን፣ የአመልካች ምስክር ደግሞ አመልካች በስተመጨረሻ የኦዲት ስራ የሰሩባቸው ሶስት ቅርንጫፎች አስመልክቶ የተፈጠረ ችግር ሳይኖር ስራውን ከአመልካች ጋር መስራታቸውን ገልጸው መመስከራቸውን በውሳኔ ላይ ከአሰፈረ በኋላ የአመልካች ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች አሉባቸው የተባሉትን ከስራው ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮችን ፈጽሞ የሌሉባቸው ስለመሆኑ አስረድተዋል ለማለት የሚያስችል አይደለም፣ አመልካች ስራው ላይ ያሳያሉ የተባሉት ባህርይ በስራ ቅልጥፍና፣ በውጤታማነትና በኢንዱስትሪ ሰላም ላይ አሉታዊ ተእፅኖ የሚፈጥሩ በመሆናቸው ተጠሪ ድርጅት የአመልካችን ደመወዝ፣ የስራ ደረጃና ሌሌች ጥቅማጥቅሞችን ሳይነካ የፈፀመው የሥራ መደብ ዝውውር ሕጋዊ ነው በማለት ደምድሟል፡፡
ከተጠሪ የሥር ክርክርም ሆነ በዚህ ሰበር ደረጃ ከሰጠው መልስ መገንዘብ የተቻለው ደግሞ በአንድ በኩል ዝውውሩ የተፈጸመው በአመልካች ጥያቄ መነሻ መሆኑን ጠቅሶ የተሻለ ደመወዝ አመልካች እንዲያገኙ ማድረጉን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአመልካችን ተገቢ ያልሆነ ባህርይ መነሻ በማድረግ ለኢንዱስትሪና ለስራ ቦታ ሰላም የተደረገ ነው በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ አሰሪ አንድን ሰራተኛ ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ የስራ መደብ የማዛወር አስተዳደራዊ ስልጣኑ ነው ተብሎ የሚታመነው አሰሪው ስራንና ሰራተኛን ለማገናኘት የሚችልበት አግባብ ነው በሚል ምክንያት ሆኖ ዝውውሩም ተቀባይነት የሚያገኘው የሰራተኛውን መብትና ጥቅም በማይነካ መልኩና ተመሳሳይ ወደሆነው የስራ መደብ ተከናውኖ ሲገኝ እንጂ ይህንኑ በሚቃረን መልኩ ሊሆን እንደማይገባ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎችን በመመርመር በሰ/መ/ቁጥር 40938 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ የፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ አመልካችን ከኦዲት ክፍል ወደ ማርኬቲንግ የስራ መደብ ያዛወራቸው መሆኑን ሳይክድ አዲሱ የስራ መደብ አመልካች ቀድሞ ይሰሩበት ከነበረው የስራ መደብ ጋር ተመሳሳይ የሆነና የአመልካችን መብትና ጥቅም በማይነካ መልኩ መከናወኑንና ለዝውውሩ አብይ ምክንያትም የአመልካች ባህርይ ሁኖ ለኢንዱስትሪ ሰላም ሲባል አመልካች እንዲዛወሩ ከተደረገበት የስራ ቦታ በጡረታ የወጣ ሰራተኛ አመልካች እንዲተኩ ለማድረግ ሲባል መከናወኑን ጠቅሷል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ድርጅት ለዝውውሩ ምክንያት ያደረጋቸው እነዚህ ምክንያቶች ባንድ በኩል ከአመልካች ባህርይ ጋር እንደተያያዙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአመልካች ጥያቄ መነሻና በጡረታ የተገለሉ ሰራተኛን የሥራ መደብ እንዲሸፈኑ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ መሆኑን የሚገልጹ በመሆናቸው ይዘታቸው ሲታይ እርስ በራሳቸው የሚቃረኑ ምክንያቶች መሆናቸውን የሚያስገነዝብ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ አንድ ሰራተኛ በባህርይ ችግር ለኢንዱስትሪ ሰላም አስቸጋሪነቱ ከተረጋገጠ በሕጉ አግባብ ተገቢው ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ተደርጎ እንዲታረም ማድረግ የሚቻልበት አግባብ መኖሩ የሚታወቅ ሲሆን በባህርይ ችግር ተዛወረ የተባለን ሰራተኛ ደግሞ የስራ መደቡ ክፍት በመሆኑ እንዲዛወር ተደርጓል በሚል የሚቀርብ ክርክር ዝውውሩ ስራንና ሰራተኛን ለማገናኘት የተደረገ ነው ብሎ ለመደምደም የማያስችል ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን በየጊዜው የሚያዛውራቸው ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት መገለጹም ሲታይ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ስራንና ሰራተኛን ለማገናኘት ሲባል ባልተደረገ የሥራ ውል ደግሞ የስራ ውል የሚሻሻልበት አግባብ ያለመኖሩን ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 15 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ የስራ መደቡ ዝውውሩ ሕጋዊ ነው ብሎ የሚያቀርባቸው ምክንያቶች እርስ በራሳቸው የሚቃረኑ በመሆናቸው ተጠሪ ዝውውሩ በህጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያከናወነው ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ዝውውሩ ሕጋዊ መሆኑን ያሳያሉ የተባሉት የተጠሪ ምክንያቶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ናቸው ከተባለ የአሰሪው የዝውውሩ እርምጃ የአስተዳዳሪነት ሥልጣኑን በዘፈቀደ ለማከናወን መነሳቱን ያሳያል ከሚባል በስተቀር የዝውውሩን ህጋዊነት በምንም መመዘኛ አያሳዩም፡፡

ስለሆነም አንድን ሰራተኛ መብትና ጥቅሙን ሳይነካ ከአንድ የስራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ወይም የስራ መደብ በማዛወር ማሰራት የአሰሪው አስተዳደራዊ ሥልጣን (Administrative prerogative) ነው ሲባል ዝውውሩ ያለ ሕጋዊ ምክንያትና በሕብረት ስምምነቱ ከሰፈረው አሰራር ውጪ ይከናወናል ተብሎ ሊተረጎም የማይገባው ስለመሆኑ ከአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አጠቃላይ መሰረታዊ አላማና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 57117፣77113 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ሁኖ ስለአገኘን ተጠሪ አመልካችን ያዛወረበት ሁኔታ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መሰረዝ ሲገባው በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ ያከናወነው ዝውውር ሕገ ወጥ ነው ከተባለም የአመልካችን ባህርይ በተመለከተ በዝውውር ደብዳቤው የገለፀበት አግባብ ከአመልካች የግል ማህደር ጋር ሊኖር የማይገባ በመሆኑ ሊሰረዝ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10179 መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 139826 ነሐሴ 07 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ዝውውር ሕገ ወጥ ነው፣ ሊሰረዝ ይገባል ብለናል፡፡ አመልካች ይሰሩበት ከነበረው የኦዲት የስራ መደብ ወደ ማርኬቲንግ የስራ መደብ ሊዛወሩ አይገባም፣ የዝወውሩ ደብዳቤም ሙሉ በሙሉ ሊሰረዝ ይገባል ከአመልካች ማህደር ሊያያዝ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ተ**

የሰ/መ/ቁ 108785

ሀምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነአ ቂጣታ

**አመልካች** ፡- ዩሴፍ ተክሌ ህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጠበቃ ብሥራት መኮንን ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ ጌታቸው በራሳቸው እና ሞግዚት በሆነችላቸው እነ ሕፃን ረዲኤት ታምራት ከጠበቃ አቶ ፋንቱ አስፋው ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

? ? ?

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ለሚስትና በሌሎች ጥገኞች የሚከፈል የካሣ ገንዘብ ጥያቄ የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነው ተጠሪ ባለቤቷ የሁለት ልጆች አባት የሆነው ታምራት ሀይሌ አሠሪው በመደበው መኪና ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ሲጓጓዝ መኪናው ተገልብጦ ሚያዝያ 23 ቀን 2005 ዓ.ም ህይወቱ ያለመሆኑን ገልፆ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ለእርሷና ለህፃናቱ ካሣ እንዲከፈላቸው ውሣኔ እንዲሰጥላት ጥር 25 ቀን 2006 ዓ.ም ጠይቃለች ፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንሁስ አንቀፅ 4 የተደነገገው የስድስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ አልፏል በማለት መቃወሚያ አቅርቧል ፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን ሰጥቷል ፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባ፣ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ ነው ፡፡ ስለዚህ ክሱ የቀረበው በዚህ ድንጋጌ የተጠቀሰው

የይርጋ የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በመሆኑ በይርጋ አይታገድም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ሽሮታል ፡፡

3. አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ይህንን የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ተጠሪ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን የሕግ ስህተት የሌለበት መሆኑን ገልፃ ተከራክራለች እኛም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይርጋ አይታገድም በማለት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንሁስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሰጠውን ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል ፡፡

4. ጉዳዩን እንደመረመርነው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንሁስ አንቀፅ 4 የተደነገገው የስድስት ወር ይርጋ ተፈፃሚ የሚሆነው አሠሪው በሠራተኛው ላይ ወይም ሠራተኛው በአሠሪው ላይ ለሚያቀርበው የደመወዝ፣ የትርፍ ሠዓት ሥራ ክፍያ፣በአል ቀናት ክፍያ ጥያቄና ለመሳሰሉት የክፍያ ጥያቄዎች መሆኑን ከድንጋጌው አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት ይቻላል በአዋጅ አንቀፅ 4 በይዘቱም ሆነ በአቀራረፅ ፣የሰራተኛው በስራ ላይ የደረሰበት የሞት አደጋ የሰራተኛው ባለቤትና ሌሎች ጥገኞች በአዋጁ አንቀጽ 110 መሠረት የሚያቀርቡትን የካሣ ክፍያ ጥያቄ በስድስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ ለመገደብ ታስቦ የተደነገገ ድንጋጌ አይደለም ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በአዋጅ አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ተጠሪ ክስ ያቀረበችው በአዋጁ አንቀጽ 162 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በመሆኑ የተጠሪ ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል ፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139907 ህዳር 25 ቀን 2007 ዓ.ም የሰ ጠውን ውሣኔ ፀንቷል ፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረበት ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ወስነናል ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ይቻቻሉ
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ 108933

ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ሠላም ቦሌ ሽማቾች ኃ.የተ.የህብረት ስራ ማህበር - የቀረበ የለም ከተባለ በኃላ ጠበቃ መለሰ ግርማይ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ እሸቱ አደፍርስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግል ስራ ክርክር ሲሆን የተጀመረውም ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ሰኔ 02 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ፡-ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከ7/00/2003 ዓ/ም ጀምሮ በጉልበት ሰራተኝት የስራ መደብ ተቀጥረው በወር ብር 770.00 እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እንዳሉ የአሁኑ አመልካች ከስራ መደባቸው ውጪ የሆነ ስራ ተጠሪ እንዲሰሩ በማድረጉ ተጠሪ የአመልካችን ትዕዛዝ ከስራ መዘርዝራቸው ውጪ ነው በሚል በመቃወማቸው ምክንያት ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ዘርዝረው ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቸ ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ የታዘዙት ከስራ መደባቸው ጋር ተያያዥነት ያለውንና በስራ መዘርዝሩ በተጠቀሰው አግባብ መሆኑን እንዲሁም በተደጋጋሚ በቅርብ አለቃቸው ሲታዘዙ ትዕዛዙን የማይቀበሉ መሆኑን ጠቅሶ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ከአሰሪው የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ያለመፈጸማቸው አከራካሪ ያለመሆኑን፣ተጠሪ የሚፈፅሟቸው ተግባራት በስራ መዘርዝሩ በግልጽ መመልከታቸውን፣በዚህም መሰረት ተጠሪ ውሃ ያላቸውን ለስላሳ ጠርሙሶችን ከስቶር ወደ

ባር፣ባዶ ጠርሙሶችን ደግሞ ከባር ወደ ስቶር እንደሚመልሱ በስራ መዘርዝሩ ላይ ከመገለፁም በላይ በዚሁ ሰነድ ተራ ቁጥር 8 ስርም ከቅርብ አለቃቸው ሲታዘዙ ማንኛውንም የጉልበት ስራ ሊሰሩ እንደሚችሉ መጠቀሱን ከሰነዱ ይዘት መመልከቱንና ከዚህም ተጠሪ የታዘዙት ከስቶር ወደ ባር ውሃ ያለበትን ጠርሙስ ወስደው ከባር ወደ ስቶርም ውሃ ያለበትን ጠርሙስ እንዲመልሱ በመሆኑ ስራው የስራ ድርሻቸው የሆነው የጉልበት ስራ መሆኑን መረዳቱን ከአረጋገጠ በኂላ ይህ ተግባር የስራ ውልን ያለማስንጠቀቂያ ሊያቋርጥ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን ጥያቄ በማንሳት በስራ መዘርዝሩ መሰረት ያለመስራት ስራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አይደለም በማለት ደምድሞ የአመልካችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 1540.00፣የካሳ ክፍያ ብር 4620.00፣የስራ ስንብት ክፍያ ብር 781.25፣የአመት ፈቃድ ክፍያ ብር 377.3 የገቢ ግብር ተቀንሶ እንዲከፈላቸውና የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-ተጠሪ በስራ መዘርዝራቸው መሰረት የታዘዙትን ስራ ለመስራት ፈቃደኛ ያለመሆናቸው ተረጋግጦ እያለ ተግባሩ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል አይደለም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች የተወሰነው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13(2) ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው የሚል ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ በመሆኑ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ተጠሪ በስራ መዘርዝሩ መሰረት ስራቸውን ያለመስራታቸው ተረጋግጦ እያለ ተግባሩ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡

የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን በተመለከተ አመልካች አላግባብ ከስራ አስናብቶኛል በማለት ተጠሪ ላቀረቡት ክስ አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪው ከስራ ማሰናበቱን አምኖ ያሰናበተው ግን ተጠሪው እንደሚሉት አላግባብ ሳይሆን የተጠሪ የቅርብ አለቃ በሰጣቸው ትዕዛዝ እና በስራ መዘርዝሩ መሰረት ተጠሪ የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪው የተሰናበቱት በስራ መዘርዝሩ በተገለፀው አግባብ የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በመሆኑ ውጤቱ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13(2) እና (7) ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ እንዲሁም አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረታዊ አላማ መታየት ያለበት

ነው። ተጠቃሹ አዋጅ መሰረታዊ አላማ ከያዛቸው ነገሮች ውስጥ የኢንዱስትሪ ሰላምን በማስፈን ምርትና ምርታማነትን በማሳዳግ ለአገር ኢኮኖሚ እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ መሆኑን የአዋጁ መግቢያ ያሳያል። ይህንኑ ለማሳካትም ሕጉ በአሰሪውም ሆነ በሰራተኛው ላይ ለይቶ ያስቀመጣቸው ግዴታዎች መኖራቸውን የአዋጁ አንቀጽ 12 እና 13 ድንጋጌዎች ያሳያሉ። በመሆኑም አሰሪውም ሆነ ሰራተኛው በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለውና ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለውን ነጥብ በተመለከተ ስናይም አዋጁ ሰራተኛው በአሰሪው የተሰጠውን ሕጋዊ የስራ ትዕዛዝ በአግባቡ የመወጣት ግዴታ ያለበት መሆኑን በአንቀፅ 13(2) እና (7) ስር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። ሌላው አዋጁ አካቶ ከያዛቸው ጉዳዮች መካከል የስራ ውል የሚቋርጥባቸው መንገዶችና ምክንያቶች ይገኙበታል። የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችልባቸው ምክንያቶች በአዋጁ አንቀፅ 27(1) ስር በግልጽ ተቀምጠዋል። በዚህ ድንጋጌ ስር የተመለከቱት የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ግን አንድ ሰራተኛ የስራ ግዴታውን ያለመወጣቱ ሲረጋገጥ የስራ ውሉን ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ መስጠትን በቅድመ ሁኔታነት የሚያስቀምጡ አይደለም። ስለሆነም ግልጽ ደንብ ወይም መመሪያ መኖሩ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሰራተኛው የስራ ግዴታውን ካልተወጣ አሰሪው ሰራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ የማያሰናብትበት ምክንያት የለም። ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም ተጠሪ በስራ መዘርዝራቸው በግልጽ የተቀመጠመውን ግዴታቸውን ያለመወጣታቸው ተረጋግጦ የተከናወነው ስንብት ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7) ድንጋጌዎች እና ከአዋጁ መሰረታዊ አላማ አንፃር ሲታይ ህጋዊ ነው ከሚባል በስተቀር ሕገ ወጥ የሚባልበትን አግባብ አላገኘንም። በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አንፃር መመልከት ሲገባቸው ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረታዊ አላማ በመውጣት የስራ ግዴታውን ያለመወጣቱ የተረጋገጠውን ተጠሪ መሰናበት የነበረበት በማስጠንቀቂያ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 90184 ሐምሌ 03 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 155790 ታህሳስ 20 ቀን 2007 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል።
2. ስንብቱም ህገወጥ ነው በማለት በስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የውሳኔ ክፍል ተሽሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ብለናል።

3. አመልካች ለተጠሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የስራ ስንብት ክፍያና የካሳ ክፍያ ለመክፈል አይገደድም፣ የአመት ፈቃድ ክፍያ ብር 377.3 ግን ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል፣የስራ ልምድ ምስክር ወረቀትም ሊሰጥ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ተ**

የሰ/መ/ቁ.109055

ሐምሌ 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

አዳነ እንደሻው

ቀነዓ ቂጤታ

**አመልካች** ፡- አቶ ጌትነት ከበደ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች** ፡- ሃያት ሜድካል ክሊጅ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. ጉዳዩ የቀረበው የአመልካች የጠበቃ አበልና ወጭና ኪሳራ ብር 6000/ስድስት ሺ ብር/ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የስራ ውሉ ከህግ አግባብ ውጭ ተቋርጧል የሚል ክስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቦ፣ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ በሚደነግገው መሰረት መሆኑን ገልጾ በመከራከሩ፣ የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪ የአመልካችን የስራ ውል ያቋረጠው በህግ አግባብ ነው በማለት አመልካች /ከሳሽ/ ለተጠሪ ለተከሳሽ የጠበቃ አበል ብር 5000 / አምስት ሺ ብር/ እና ኪሳራ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ በድምሩ ብር 6000 /ስድስት ሺ ብር/ ይክፈል ማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
2. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ /ተጠሪ/ ለአመልካች የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ የስራ ውሉን አቋርጧል፡፡ ስለዚህ መልስ ሰጭ /ተጠሪ/ ለአመልካች የሁለት ወር ደመወዝ ብር 10,697.96 /አስር ሺ ስድስት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከዘጠና ስድስት ሳንቲም/ ግብር ተቀንሶ የመክፈል ሃላፊነት አለበት፡፡ በሌሎች ነጥቦች የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ አልተነካም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች ጥር 17 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው በህግ ከተደነገገው ውጭ መሆኑን ካረጋገጠ በኃላ የሁለት ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ብቻ እንዲከፈለኝ የሰጠው ውሳኔና የስር ፍርድ ቤት ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነብኝን የጠበቃ አበል እና ኪሳራ ሳይሻር መቅረቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ/ም በሰጠው መልስ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 161 ሰራተኞቹን የዳኝነት ክፍያ ከመክፈል ነፃ የሚያደርግ እንጂ በአሰሪው ወጭና ኪሳራ እንዳይከፍሉ የሚያደርግ ድንጋጌ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ጉዳዩ በዚህ ሰበር ችሎት የተያዘው ጭብጥ፤ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ይዘትና ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም አመልካች ለተጠሪ ብር 6000 /ስድስት ሺ ብር/ የጠበቃ አበልና ኪሳራ እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ ነጥብ መርምረናል፡፡

5. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ለያዝነው ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ እና የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ተራቸው ስራቸው ኪሳራና ወጭ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ሊያዝ እንደሚችልና ኪሳራ በቁጥር የተወሰነለት ወገን የተወሰነለትን የኪሳራ ገንዘብ፣ የወጭ ዝርዝር እንደሚያቀርብ የተፈቀደለት ደግሞ የወጭና ኪሳራ ዝርዝር አቅርቦ ለመጠየቅ የሚችል መሆኑን ከፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 463 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸ የሥነ - ሥርዓት ህጉ ድንጋጌ አዋጅ 377/96 ቁጥር 161 ንዑስ አንቀጽ 2 "ማንኛውም ሰራተኛ ወይም የሰራተኛ ማህበር ፍርድ ቤት ለሚያቀርበው የስራ ክርክር ጉዳይ ከክፍያ" ነፃ ነው በማለት ካስቀመጠው ድንጋጌ ጋር ተጣጥሞ መታየት ያለበት ነው፡፡

6. የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ከዳኝነት ክፍያ ነፃ ነው በሚል መንገድ ሳይሆን "ከክፍያ ነፃ ነው" በማለት የሚደነግግ መሆኑን ከድንጋጌው አቀራረጽና አውድ ንባብ ለማየት ይቻላል፡፡ ድንጋጌው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ህጋዊና ሰላማዊ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የመፍጠር፤ የኢንዱስትሪ ሰላምን የመፍጠር፤ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚነሳ ክርክር በተቀላጠፈ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ የማድረግ አላማዎቹን በሚያሳካ ሁኔታ መተርጎምና ስራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ ከላይ የተገለጹትን አላማዎች ለማሳካት፤ ሠራተኞች በግልም ሆነ በጋራ መብታችን በአሠሪው ተጥሶብናል ብለው ሲያስቡ ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ለሚሰጥ ፍርድ

ሰጭ አካል ከህግ አግባብና ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲታይላቸው ለመጠየቅ የሚችሉበትን ተደራሽና ቀልጣፋ የዳኝነት ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

7. ከዚህ አንፃር ሲታይ ሠራተኛው በፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ 465 ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት ሠራተኛው ሀሰተኛና የተጨበረበረ ክስና ማስረጃ በአሰሪው ላይ ማቅረቡ ካልተረጋገጠ በስተቀር ከህግ አግባብ ውጭ ተጥሶብኛል የሚለውን የመብት ጥያቄ ለፍ/ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል /አሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ/ አቅርቦ በሙሉ ወይም በከፊል ተረች በሆነ ጊዜ ሁሉ አሰሪው ለክርክሩ ያወጣውን ወጭና ኪሳራ እንዲከፍል በሚያስገድድ መንገድ የአዋጅ አንቀጽ 161 ድንጋጌዎች ከተተረጎሙት ሠራተኞች ተጥሶብናል የሚሉትን መብት ለማስከበር ክስ አቅርበን በፍርድ ቤት ተከራክረን ብንረታ አሰሪው ለጠበቃና ለክርክሩ የወጣውን ወጭ እንድንከፍል ሊወሰንብን ይችላል በሚል ፍራቻና ስጋት መብታቸውን በፍርድ ከመጠየቅ የሚገደቡበትን ሁኔታ የሚፈጥር ይሆናል፡፡ ይህም ከላይ የገለጽናቸውን የአዋጁን መሰረታዊ ዓላማዎች የሚያሳካ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሰራተኛ ለአሰሪው በስራ ክርክር ምክንያት ያወጣውን ወጭና ኪሳራ የመክፈል ግዴታ የሚጣልበት በክርክሩ ተረች በመሆኑ ምክንያት ብቻ ሳይሆን ሰራተኛው በአሰሪው ላይ ያቀረበው ክስ ሀሰተኛና በተጭበርበረ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ሲገኝ መሆን እንዳለበት የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 463 የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 465 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 161 ድንጋጌ ጋር በሚጣጣም መንገድ በመተርጎም ለመረዳት ይቻላል፡፡

8. በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከህግ አግባብ የስራ ውሉ ተቋርጦብኛል በሚል እምነት ክስ ያቀረበ መሆኑና በክርክር ሂደት አሰሪው /ተጠሪ/ያቀረበው ማስረጃ ከሰራተኛው /አመልካች/ የተሻለ ሆኖ ስለተገኘ የስር ፍርድ ቤት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የወሰነ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካችንና የተጠሪን ክርክር በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን የስራ ውል ከማቋረጡ በፊት የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ መስጠት ነበረበት በማለት ተጠሪ ለአመልካች የሁለት ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የወሰነ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ ተረድተናል፡፡ ይህም አመልካች በክርክሩ ሙሉ ለሙሉ ተረች አለመሆኑንና በከፊል መብት ያለው መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠለት መሆኑን ያሳያል፡፡

9. ከላይ በዝርዝር ከሰጠነው የህግ ትርጉምና አመልካችና ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ካቀረቡት ክርክር መሰረታዊ ባህሪ አንፃር ሲታይ፣ አመልካች ለተጠሪ የጠበቃ አበል ብር 5000/ አምስት ሺ ብር/ ኪሳራ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ በድምሩ ብር 6000

/ስድስት ሺ ብር/ እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139696 ታህሳስ 8 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች የሁለት ወር ደመወዝ ብር 10697.96/ አስር ሺ ስድስት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከዘጠና ስድስት ሳንቲም/ ግብር ተቀንሶ እንዲከፍል በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ የጠበቃ አበል ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ኪሳራ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ በድምሩ ብር 6000 /ስድስት ሺብር/ እንዲከፍል የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ አመልካች ይህንን ገንዘብ ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ተ**

የሰ/መ/ቁ.104351

ሰኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ወ/ት ክምክም እማኛው - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የደቡብ አቸፈር ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት - ዐ/ሕግ ዘላለም ተስፋዬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ቅጥር ውሉ የተሰረዘው አላግባብ ነው ተብሎ ወደ ስራው እንዲመለስ የተወሰነ የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛ ውዝፍ ደመወዝ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-አመልካች በደቡብ አቸፈር ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት በ10/02/2004 ዓ.ም ተቀጥረው ሲያገለግሉ ከቆዩ በኃላ በቅጥር ውድድሩ ጊዜ ያቀረቡት የስራ ልምድ ማስረጃ ለተቀጠሩበት ፕሳ-3 የስራ ደረጃ የሚጠየቀውን አግባብነት ያለው የስምንት ዓመት የስራ ልምድ መስፈርት የሚያሟላ አይደለም በሚል የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ በ04/12/2004 ዓ.ም. የአመልካችን ቅጥር መሰረዙን፣አመልካች በዚህ የስረዛ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ማጣቱን፣ ይግባኙ ቀጥሎ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅጥሩን የሰረዘው የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ መጥሪያ ደርሶት መልስ ባለማቅረቡ በሌለበት ጉዳዩን መርምሮ ቅጥሩ ከተፈጸመ ከዘጠኝ ወራት በኃላ ቢሮው የቅጥር ፎርማሊቲ አልተሟላም በሚል ምክንያት ቅጥሩን በመሰረዝ የወሰደው እርምጃ ከክልሉ አዋጅ ቁጥር 171/2002 ውጭ መሆኑን፣ አመልካች ያቀረቡት የስራ ልምድ ማስረጃ ሀሰተኛ ነው ያልተባለ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 23 የተመለከተው ድንጋጌም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በመሻር አመልካች ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ውሳኔ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታቸውን ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ

ሰበር ችሎት ያቀረቡት አመልካቿ ሲሆኑ የአቤቱታቸው ይዘትም ቅጥሩ የተሰረዘው ከሕግ አግባብ ውጭ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ስራዬ እንድመለስ ተወስኖልኝ እያለ ቅጥሩ ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ስራ እንድመለስ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለኝ ሳይወሰን የታለፈው አላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ አመልካች ለሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ጭምር እንዲከፈላቸው አለመጠየቃቸውን፣ ይግባኙ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሚቀርበውም በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ብቻ መሆኑን እና በዚህም ምክንያት ለአስተዳደር ፍርድ ቤት በቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ ዳኝነት ያልተጠየቀበትን ጉዳይ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ ሰበር ችሎቱ ተቀብለው ውሳኔ ሊያሳርፉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ አለመኖሩን ገልጾ አቤቱታውን ባለመቀበል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ለሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ቅጥራቸው ፀንቶ እንዲቀጥል ከመጠየቃቸውም በተጨማሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ላይ በክርክር ላይ ለነበሩበት ጊዜ ያለው ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ጥያቄ አቅርበው እያለ ዳኝነት አልተጠየቀበትም ተብሎ የውዝፍ ደመወዝ ጥያቄው ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. አመልካች ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ጭምር እንዲከፈላቸው ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የለም በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም?
2. ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ወደስራቸው እንዲመለሱ ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያለው የአመልካች ደመወዝ ሊከፈላቸው የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ቅጥሩ አላግባብ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ወደ ስራ እንዲመለስ ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያለው ደመወዝ እንዲከፈለኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያለፈብኝ አላግባብ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ሳይቀበል

የቀረው ደመወዙ ሊከፈል የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት መኖሩን መሰረት በማድረግ ሳይሆን ይልቁንም አመልካች ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የለም በማለት መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ቅጥሩ የተሰረዘባቸው አላግባብ መሆኑን ገልጸው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ካቀረቡት ጥያቄ በተጨማሪ ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት በ24/12/2004 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ በተራ ቁጥር ስምንት ላይ ጠቅሰው መጠየቃቸውን እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በ19/02/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ በተራ ቁጥር አስራ ሁለት ላይም ተመሳሳይ ዳኝነት መጠየቃቸውን በመግለጽ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ ላቀረቡት ክርክር ተጠሪው በመልሱ የሰጠው ግልጽ ማስተባበያ ካለመኖሩም በላይ በአጣሪው ችሎት በኩል ከዚህ መዝገብ ጋር እንዲያያዙ የተደረጉት ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ እና ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረቡት የሁለቱ የይግባኝ ማመልከቻዎች ይዘትም የአመልካቿን የክርክር ነጥብ የሚያረጋግጥ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የለም በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ  የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከላይ በመጀመሪያው ጭብጥ ትችት ላይ እንደተገለጸው አመልካች ቅጥሩ የተሰረዘባቸው አላግባብ መሆኑን ገልጸው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ካቀረቡት ጥያቄ በተጨማሪ ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር በአስተዳደር ፍርድ ቤትም ሆነ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዳኝነት መጠየቃቸው የተረጋገጠ ሲሆን የአስተዳደር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ ቅጥሩ የተሰረዘው አላግባብ መሆኑን በመግለጽ አመልካች ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ውሳኔ የሰጠው የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጥያቄ አቅርበው የነበረ ስለመሆኑም ሆነ ጥያቄውን አቅርበው ነበረ ከተባለም ውሳኔ ሳያሳርፍበት የቀረው በምን ምክንያት እንደሆነ በውሳኔው ላይ የገለጸው ነገር አለመኖሩን ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት በሰጠው መልስ የስራ ቅጥሩ የተሰረዘበት ሰራተኛ በፍርድ ቤት ወደ ስራው እንዲመለስ ቢወሰንለት ቅጥሩ ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 ላይ የተደነገገ ነገር አለመኖሩ ሕግ አውጭው የዚህ ዓይነቱ ውዝፍ

ደመወዝ እንዳይከፈል መፈለጉን የሚያሳይ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ እንደተባለው ቅጥሩ ለተሰረዘበት እና በፍርድ ቤት ውሳኔ ወደ ስራው እንዲመለስ ለተወሰነለት ሰራተኛ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ በአዋጁ በግልጽ የተቀመጠ ፈቃጅ ድንጋጌ የሌለ ሲሆን በአንጻሩ የዚህ ዓይነቱ ደመወዝ ሊከፈል የማይገባው ስለመሆኑም በአዋጁ በግልጽ የተቀመጠ ከልካይ ድንጋጌም የለም፡፡ይልቁንም ከዲሲፕሊን ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሁኔታ የመንግስት ሰራተኛው የተላለፈበት ውሳኔ በይግባኝ ከተሻሻለለት ወይም ከተሰረዘለት ውሳኔው ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ታስቦ ያለወለድ የሚከፈለው ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 81 (2) ስር የተመለከተው ድንጋጌ የሠራተኛው የስራ ውል ተቋርጦ የቆየው የሠራተኛው ባልሆነ እና ይልቁንም የመንግስት መስሪያ ቤት በሆነ ጥፋት ምክንያት መሆኑ በፍርድ ተረጋግጦ ሰራተኛው ወደ ስራው እንዲመለስ ሲወሰን የስራ ውሉ ተቋርጦ በቆየበት ጊዜ ያለው ደመወዝ ጭምር ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ በአዋጁ ተቀባይነት ያገኘ መርህ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ በአዋጁ መሰረት የቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ሌላ ጥቅም የተሰረዘበት የመንግስት ሠራተኛ በማታለል ወይም በማጭበርበር ያገኘው ካልሆነ በቀር የስረዛው እርምጃ እስከተወሰደበት ጊዜ ድረስ የተከፈለውን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች እንዲመልስ የማይጠየቅ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 87 (1) የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ቅጥሩ የተሰረዘበት ሠራተኛ ወደስራው እንዲመለስ በፍርድ ቤት ሲወሰን ውዝፍ ደመወዙ ጭምር እንዲከፈል ሕግ አውጭው አለመፈለጉን አዋጁ ያመለክታል በማለት በደፈናው ከመከራከር በቀር የዚህ ዓይነት ትርጉም የሚሰጠው ወይም የዚህ ዓይነት ግምት ለመውሰድ የሚያስችለው የአዋጁ ድንጋጌ የትኛው እንደሆነ ተጠሪው በግልጽ ለይቶ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡በመሆኑም ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ወደስራቸው እንዲመለሱ ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያለው የአመልካች ደመወዝ ሊከፈላቸው የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ስራቸው እስኪመለሱ ደረስ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ በዝምታ በማለፍ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ጭምር እንዲከፈላቸው ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የለም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 30581 በ21/09/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤትም ሆነ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ ላይ ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር የዳኝነት ጥያቄ አቅርበዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34488 በ05/06/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
4. በተራ ቁጥር ሶስት ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ቅጥራቸው የተሰረዘው አላግባብ በመሆኑ አመልካች ወደስራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
5. በተራ ቁጥር ሶስት ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ በዝምታ በማለፍ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
6. ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ከ04/12/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ እስከተወሰነበት 05/06/2005 ዓ.ም. ድረስ ያለው የአመልካች ደመወዝ ያለወለድ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
7. የውሳኔው ግልባጭ በውሳኔው መሰረት ማስፈጸም ያስችለው ዘንድ ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት፣ እንዲያውቁት ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና አመልካች ለሚሰሩበት የመንግስት መስሪያ ቤት ይላክ፡፡
8. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
9. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ይ**

# ፍትሐ ብሔር
# ሥነ - ሥርዓት

የሰ/መ/ቁ. 105869

መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ ደበሬ ቡልቲ - ተወካይ ታከለ ደበሬ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ዳንሹቴ ዋጋሪ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጋራ የእርሻ ይዞታ ላይ የተደረገ ውል የይፍረስልኝ ጥያቄን መሰረት አድርጎ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት እና የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ባልተደረጉት ባለቤታቸው እና 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ በ07/10/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-በወንጪ ወረዳ በደጎዬ ጋለይ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው እና አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰው ሁለት ጥማድ መሬት የከሳሽ እና የባለቤታቸው የ1ኛ ተከሳሽ የጋራ ይዞታ ሆኖ እያለ ከከሳሽ እውቅና ውጪ ተከሳሾቹ በ21/01/2004 ዓ.ም.የከሳሽን መብት የሚጋፋ የመሬት ቅያሪ ውል ማድረጋቸውን የሚገልጽ ሆኖ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ በክሱ መሰረት ቢወሰን ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡2ኛ ተከሳሽ በበኩላቸው በ25/10/2005 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ በተከሳሾቹ መካከል በ21/01/2004 ዓ.ም የተደረገው ውል የድንበር ግጭት ማስወገጃ ስምምነት እንጂ የመሬት ቅያሪ ውል አለመሆኑን፣ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የመሬት ቅያሪ ያደረጉት በ1994 ዓ.ም መሆኑን፣2ኛ ተከሳሽ በቅያሪ ባገኙት መሬት ላይ አንድ የሳር ቤት የሰሩበት እና በርካታ አትክልት ያለሙበት መሆኑን፣1ኛ ተከሳሽም በቅያሪ ባገኙት መሬት ላይ አንድ የሳር ቤት የሰሩበት መሆኑን እና የመሬት ቅያሪው ከተደረገ ከአስራ አንድ ዓመታት በኃላ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና በ21/01/2004 ዓ.ም በተደረገው ውል ላይ የነበሩትን ሶስት ምስክሮች አስቀርቦ ከሰማ በኃላ የ1ኛ ተከሳሽ ባለቤት ከሆኑት ከከሳሽ ስምምነት ውጪ ሁለቱ ተከሳሾች በ21/01/2004 ዓ.ም ያደረጉት ውል ሕጋዊ አለመሆኑን ገልጾ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ሁለት ቀርጥ መሬት ከሳሽ ይጠቀሙበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 2ኛ ተከሳሽ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ከሳሽ ክሱን ያቀረቡት ለክሱ መነሻ የሆነው የመሬት ለውጥ ውል መደረጉን ካወቁ ስድስት ወር ካለፈው በኃላ መሆኑን ገልጾ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ክሱ በስድስት ወር ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የስር ከሳሽ በዚህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ባለመስማማት በተራቸው ያቀረቡትን ይግባኝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዘግቶ ያሰናበተው ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ተከሳሾች ሁለት ጥማድ መሬት የተቀያየሩ መሆኑ እና የመሬት ቅያሪ ውሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 “ም” ሆነ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 መሰረት ስልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ መሆኑ በግራ ቀኙ ያልተካደ መሆኑን፣የስር ከሳሽ በ21/01/2004 ዓ.ም. የተደረገውን ውል ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስካቀረቡበት ቀን ድረስ ስድስት ወር ያለፈው ስለመሆኑ የስር 2ኛ ተከሳሽ ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን፣የመሬት ቅያሪ ውል የይፍረስልኝ ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበትን የይርጋ ዘመን የሚያመለክት በክልሉ የቤተሰብ ሕግም ሆነ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 እና ደንብ ቁጥር 151/2005 ውስጥ የተካተተ ድንጋጌ አለመኖሩን ገልጾ የሁለቱን የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር እና በአንጻሩ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሁለቱን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከሻረ በኃላ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በአሁኑ አመልካች የቀረበውን ክርክር አጣርቶ ይወስን ዘንድ ጉዳዩን ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይመልስ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ጭምር ውሳኔ የመስጠቱን አግባብነት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 ድንጋጌ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው የስር ፍርድ ቤቶች በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ የሰጡት ለጉዳዩ አወሳሰን አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በአግባቡ እንዲጣሩ ካደረጉ በኃላ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ የስር ፍርድ

ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት ተጠሪዋ በወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት ባለቤታቸው 1ኛ ተከሳሽ ከአመልካቿ እውቅና ውጪ ከአሁኑ አመልካች ጋር ያደረጉት የሁለት ጥማድ የእርሻ መሬት ቅያሪ ውል በፍርድ ኃይል እንዲፈርስላቸው በመጠየቅ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው ከይርጋ መቃወሚያ በተጨማሪ መሬቱን የተለዋወጡት በ1994 ዓ.ም መሆኑን፣ በ2004 ዓ.ም የተደረገው የድንበር ስምምነት እንጂ የመሬት ቅያሪ ውል አለመሆኑን፣ሁለቱም ወገኖች በ1994 ዓ.ም በተደረገው ለውጥ መሰረት በእጃቸው በገባው መሬት ላይ የሳር ቤት መስራታቸውን እና አመልካች በተጨማሪም በመሬቱ ላይ ቋሚ አትክልቶችን ማልማታቸውን በመግለጽ ተከራክረዋል።በሌላ በኩል በ21/01/2004 ዓ.ም በተደረገው ውል ላይ የነበሩት ምስክሮች ውሉ የመሬት ቅያሪ ውል መሆኑን እና የተደረገውም በአንድ ጥማድ መሬት ላይ መሆኑን በመግለጽ የመሰከሩ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው ደግሞ ተጠሪዋ በሁለቱ ጥማድ እንዲጠቀሙ በማለት ከመሆኑም በላይ የተጠሪዋ ባለቤት በቅያሪ አግኝተዋል ስለተባለው መሬት በውሳኔው ላይ ያሰፈረው ነገር አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።የመሬት ቅያሪው የተደረገው በ1994 ዓ.ም ስለመሆኑ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መሬቱ የሚገኘው በአመልካች እጅ ስለመሆኑ የወረዳው መሬት አስተዳደር እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በቁጥር WLBEN/525/06 በ25/02/2006 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ የገለጸ ስለመሆኑ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የገለጹትን ፍሬ ነገር ተጠሪዋ በመልሳቸው በዝምታ ከማለፍ በቀር ማስተባበያ ያልሰጡበት ከመሆኑም በላይ የወረዳው መሬት አስተዳደር እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ቁጥሩ እና ቀኑ ከላይ በተጠቀሰው ደብዳቤ ሰጠ ስለተባለው መግለጫ ሁሉም የስር ፍርድ ቤቶች በውሳኔያቸው ላይ የገለጹት ነገር የለም።

በመሰረቱ ማንኛውም ፍርድ ቤት ባለጉዳዮችን ማከራከር የሚገባው የተለያዩበት የሕግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ምን እንደሆነ አረጋግጦ ለጉዳዩ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ ስለመሆኑ፣የነገር ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያመነውን የሕግ ወይም የነገር አግባብ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በማስተባበል የካደ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ፣ፍርድ ቤቱ ጭብጥን ለመመስረት የሚችለውም ከግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሰረት በሚደረግ ምርመራ በተከራካካሪ ወገኖች የሚሰጠውን መልስ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የጭብጥ አመሰራረትን በሚደነግጉ ከቁጥር 246 እስከ 248 በተመለከቱት የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በክርክሩ የተያዘው ጭብጥ ምን እንደሆነ እና ጭብጡ በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የተወሰነበትን ምክንያት

በውሳኔው ላይ መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ የፍርድ አጻጻፍን በሚመለከተው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 182(1) ስር በአስገዳጅነት ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከተው ፍርድ ቤት ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ አስቀድሞ በመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦች ላይ ውሳኔ መስጠት ያለበት ቢሆንም ለመቃወሚያ ክርክሩ አወሳሰን አግባብነት ያላቸው ምስክሮች ሳይሰሙ እና አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ሳይቀርቡ በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ ለመስጠት የማይቻል በሆነ ጊዜ ግን ፍርድ ቤቱ በመቃወሚያ ነጥቦች ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ የሚሰጥ ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 244(1) እና 245(1) ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡በተያዘው ጉዳይም አግባብነት ያለውን የይርጋ ዘመን ከመለየት በተጨማሪ ይርጋው መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ለይቶ ለማወቅ የሚቻለው የመሬት ለውጡ የተደረገው መቼ ነው? የሚለው የክርክር ነጥብ በማስረጃ ተጣርቶ ከታወቀ በኃላ ነው፡፡የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በሁለቱ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ ያልተቀበለው ከሆነም ውሳኔውን ሽሮ በፍሬ ጉዳይ ረገድ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመለስ የሚገባው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 ድንጋጌ የሚያመለክት ሆኖ እያለ አመልካች በፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ረገድ ያላቸውን የይግባኝ መብት በሚያጣብብ ሁኔታ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ጭምር ጉዳዩን አጠቃሎ ውሳኔ መስጠቱ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ያልተደረጉት ከአመልካች ጋር ውሉን አድርገዋል የተባሉት የስር 1ኛ ተከሳሽም የክርክሩ ውጤት በቀጥታ የሚመለከታቸው በመሆኑ በቀጣይ የክርክር ሂደት የክርክሩ አካል መደረግ የሚገባቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ አወሳሰን አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በተገቢው ስነ ስርዓታዊ አግባብ እንዲጣሩ ሳይደረግ የስር ፍርድ ቤቶች በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች ሁለት ጥማድ መሬት ለተጠሪ እንዲለቁ በወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10986 08/12/2005 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ፣ይህንን ውሳኔ በመሻር ክሱ በስድስት ወር ይርጋ የታገደ ነው በማለት በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29851 በ03/04/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 170870 በ02/07/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ እና

የሁለቱን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 184750 በ26/01/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ከላይ በውሳኔው ይዘት ውስጥ በተገለጸው መሰረት በአከራካሪው የቅያሪ ውል መሰረት በአመልካች እጅ የገባው መሬት ምን ያህል ነው? አንድ ጥማድ ወይስ ሁለት ጥማድ? ቅያሪው የተደረገው አመልካች እንደሚሉት በ1994 ዓ.ም. ነው ወይስ ተጠሪ እንደሚሉት በ21/01/2004 ዓ.ም. በተደረገው ውል ነው? ከይርጋ አቆጣጠር አንጻር ተጠሪ የለውጥ ውል መደረጉን ያወቁት ወይም አውቀዋል ሊባሉ የሚችሉት መቼ ነው? የቅያሪውን ጊዜ አስመልክቶ በማስረጃ በሚረጋገጠው እና ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው ወይስ አይደለም? የመሬት ቅያሪ ውሉ በሚመለከተው አካል የተመዘገበ እና ዕውቅና የተሰጠው ነው ወይስ አይደለም? አመልካች እና የተጠሪ ባለቤት የተቀያየሩትን መሬት በይዞታቸው ስር አድርገው የቆዩት ለምን ያህል ጊዜ ነው? በተለዋወጡት መሬት ላይ አመልካች ቤት መስራታቸው እና ቋሚ አትክልቶችን ማፍራታቸው የሚረጋገጥ ከሆነ ይህ ሁኔታ በጉዳዩ አወሳሰን ላይ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት አለ ወይስ የለም? በ21/01/2004 ዓ.ም. የተደረገው ውል ሙሉ ይዘት ምንድነው? ቅያሪው የተደረገው በ1994 ዓ.ም. መሆኑ የሚረጋገጥ ከሆነ በ21/01/2004 ዓ.ም. የተደረገው ውል ዓላማ ምንድ ነው? የቅያሪ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚባል ከሆነ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? የሚሉትን እና ከእነዚሁ የሚመነጩ ተያያዥ ነጥቦችን እንደየአግባብነቱ በግራ ቀኙም ሆነ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በሚቀርቡ ማስረጃዎች በማጣራት እና የስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ታከለ ደበሬ የክርክሩ ተካፋይ ሆነው እንዲቀጥሉ በማድረግ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሰረት ወስነናል፡፡

3. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲሁም እንዲያውቁት ለደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡

4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

5. ውሳኔ ያገኝ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ. 99642

ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** ቴራ ኮንስትራክሽን ባለቤቱ ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** አቶ ሚካኤል ነገሰ ደበበ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በክርክር ባለው ጉዳይ ዋስ እንዲጠራ በተሰጠው ትዕዛዝ ተገቢነት የተመለከተ ነው፡፡ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን እየተከራከሩ ነው፡፡ አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ በሆኑ ማሽነሪዎች ሊያደርሰው ይችላል የተባለውን ጉዳት ለመከላከል ወይም ለማካካስ የብር 8 ሚሊዮን ዋስ እንዲጠራ የተሰጠው ትዕዛዛ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ የሚል አቤቱታ በማቅረቡ ምክንያት የዚህ ትዕዛዝ ሕጋዊነት ለመመርመር የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ ክፍሉ ያሰፈረው ፍሬ ነገር ግራ ቀኙ እያከራከሩ ያሉትን ማሽነሪዎች በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ በአመልካች ይዞት ሥር ያሉ ናቸው፡፡ ምንአልባት ተጠሪ እንደሠጋው የማሽነሪዎቹ የተለያዩ ወሳኝ አካላቶች ቢፈታቱ ወይም ከጥቅም ውጪ ቢሆኑ በእርግጥም በተጠሪ ላይ ከፍ ያለና የማይተካ ጉዳት ሊደርስ የሚችል በመሆኑ ማሽነሪዎችን በተመለከተ አመልካች ለብር 8 ሚሊዮን /ስምንት ሚሊዮን/ የሚበቃ ዋስ እንዲጠራ ወይም ገንዘቡን በሞዴል 85 እንዲያሲዝ ማዘዙን ያሳያል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ከዚህ በተጨማሪ ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ማሽነሪዎች እንዳይሸጡ እንዳይለወጡ እንዲሁም በማናቸውም መንገድ ለሌላ 3ኛ ወገን ሳይተላለፉ ታግደው እንዲቆዩ መታዘዙን የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታ

የቀረበውም ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካችም የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘት ማሽነሪዎቹ በታገዱበት ሁኔታ ተጨማሪ ዋስትና እንዲጠራ መደረጉ ተደራራቢ ዋስትና መሆኑ፣ የተጠቀሰው ገንዘብ ማስያዝ እንደማይችል የጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ ይግባኝ የለም በማለት ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ሊታረም ይገባል የሚል ነው። ተጠሪ ጥሪ ተደርጐለት ቀርቦ በሰጠው መልስ አመልካች ዋስ እንዲጠራ መታዘዙ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ለመከላከል አስፈላጊ መሆኑ፣ ገንዘብ የሚያስያዝ በቂ ሀብት ያለው ስለመሆኑ ትዕዛዙ ሊጸና የገባል በማለት ተከራክረዋል። የአመልካች የመልስ መልስ በዋናነት አቤቱታውን የሚያጠናክር ቢሆንም በሰበር ከተያዘው ጭብጥ በዘለለ በፍሬ ነገር ክርክር ሲነሱ የሚገባቸው ነጥቦች ያካተተ በመሆኑ ታልፏል።

ከሥር የጉዳይ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመላኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያደረጉት ክርክር በሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ትዕዛዝ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር ለማዛመድ እንዲሁም ጉዳዮ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዮን እንደሚከተለው መርምሮታል።

እንደመረመርነውም አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው ማሽነሪዎች ባሉበት ሁኔታ በፍ/ቤት ትዕዛዝ የታገዱ በመሆኑ በድጋሚ ዋስ እንዲጠሩ ወይም ገንዘቡ በሞዴል 85 እንዲያሲዝ መታዘዙ ድርብ ዋስትና እንዲጠራ የሚያስገድድ ትዕዛዝ መሆኑን ይገልፃል። ተጠሪ በአንፃሩ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ማሽነሪዎች በአመልካች እጅ የሚገኙ በመሆናቸው በመጨረሻ ረቺ መሆኑ በፍ/ቤት ቢወሰን ጉዳዩን ለማስፈፀም የሚያስችል ሀብት ከሌለ የተጠሪ ክርክር መና የሚያስቀር በመሆኑ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ተገቢ መሆኑን ይከራከራል።

በመሰረቱ ከፍርድ በፊት ንብረት የሚከበርበት ወይም ዋስ የሚጠራበት ሥርዓት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 151 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ተፈላጊው ዕቃ ወይም ንብረት ለማቅረብ የሚሰጠው ዋስትና ከተከሳሽ ድርጊት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች መፈፀማቸው ሲረጋገጥ ነው። በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.151/1/ እንደተመለከተው ተከሳሽ /አመልካች/ ክሱን ለማሰናከል ማቀድ ወይም የተሰጠው ትዕዛዝ እንዳይፈፀም ዘዴ መፍጠሩ የሚመለከት በቃለ ማህላ የተደገፈ አቤቱታ ከቀረበ ፍ/ቤቱም በድንጋጌው የተዘረዘሩትን መሰረታዊ ነጥቦች አንደኛው አመልካች ንብረቱ በሙሉ ወይም በከፊል ለማሸሽ ወይም ለማባከን ማቀዱን ፣ሁለተኛ ከፍ/ቤቱ የዳኝነት ክልል ንብረቱ ለማሸሽ ማቀዱን ሲረዳ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል ተደንግጓል። በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ማሽነሪዎች እንዳይሸጡ፣ እንዳይለወጡ፣ እንዲሁም በማንኛውም መንገድ ለሌላ 3ኛ ወገን እንዳይተላለፉ ታግደው እንዲቆዮ ክርክሩ እየተመለከተ ያለው ፍ/ቤት አዟል። የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች እጅ ያለውን ንብረት ከማሳገድ በተጨማሪ ዋስ እንዲጠራ የተጠየቀበት

ምክንያት ምንአልባት አመልካች የማሽነሪዎቹ የተለያዩ ወሳኝ አካላቶች ቢፈታቱ ወይም ከጥቅም ውጭ ቢሆኑ የሚል ስጋት በመኖሩ ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ የተነሳው ግምታዊ ስጋት ወደ እውነታ የተጠጋ ስለ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ስለመሆኑ የሰጠው ትዕዛዝ አያሳይም፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ማሽነሪዎች በማናቸውም ሁኔታ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፉ በታገዱበት ሁኔታ ወይም ንብረቱ በተከበረበት ሁኔታ በተጠሪ ላይ ተጨማሪ ኪሳራ እንደሚደርስ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች የብር ስምንት ሚሊዮን ዋስ እንዲጠራ ወይም በሞዴል 85 እንዲያሲዝ ማዘዙ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 151 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ያገናዘበ አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ ሁሉ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ዋስ እንዲጠራ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ አተገባበር ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዮን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 138130 ጥር 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.99240 መጋቢት 29 ቀን 2006 ዓ.ም የስምንት ሚሊዮን ዋስትና በተመለከተ የሰጠው ትዕዛዝ ክፍል ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የብር ስምንት ሚሊዮን ዋስ እንዲጠራ ወይም በሞዴል 85 እንዲያሲይዝ አይገደድም ብለን ወስናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት በሌሎች ጉዳዮች የሰጠው ትዕዛዝ አልተነካም፡፡
4. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ወ/ከ**

የሰ/መ/ቁ 96943

ሚያዝያ 16 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካቾች**፡- 1ኛ አቶ ተስፋዬ ወርቁ ጠበቃ በረከት ቡሽራ - ቀረቡ

2ኛ ተስፋሽ ሪል እስቴት ኃ/የተ- የግል ማህበር

**ተጠሪዎች**፡- 1ኛ ወ/ሮ የምስራች ገ/መስቀል

2ኛ ሰመረ ባህሩ ወ/ሩፋኤል - ቀረቡ

3ኛ መቅደስ ባህሩ ወ/ሩፋኤል

4ኛ ህፃን በረከት ባህሩ ወ/ሩፋኤል

**መዝገቡ መርምራን ተከተዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ ጉዳይ በሰበር ሰሚ ችሎት ሊመረመር ይገባል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ አንደኛ አመልካች በተከሰሱበት በንብረት ላይ ደረሰ በተባለው ጉዳይ ካሣ ጥያቄ ግንባታውን ፈፅመዋል የተባለው ብራይት የኮንስትራክሽን ድርጅት የክርክሩ ተካፋይ ሊሆን ይገባ ነበር በማለት ያቀረቡት ጥያቄ የመታለፉ አግባብነት ከፍ/ህ/ቁ. 2136 አንፃር ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካቾች ተከሳሾች ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች ነበሩ፡፡ ጉዳዩም በመኖሪያ ቤት ላይ በደረሰው ጉዳት ቤቱን በድጋሜ ለመገንባት የሚያስፈልግ የገንዘብ መጠን የተመለከተ ክርክር ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ዋና ይዘቱ፡- በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 የቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 21 የቤት ቁጥር 711/2 የሆነ በካርታ ቁጥር 20521 በሟች አቶ ባህሩ ወ/ሩፋኤል ስም የተመዘገበው እና 1ኛ ተጠሪ የሟች ሚስት እንደሆኑ ከ2-3 ያሉት ደግሞ የሟች ወራሾች መሆናቸው በመ/ቁ. 854/93 እና 206/93 ያረጋገጡበት ቤት የተከሳሾች ይዞታ ከከሳሾች ይዞታ ጋር ወሰንተኛ /ኩታ ገጠም/ በመሆኑ ተከሳሾች በቦታቸው ላይ ህንፃ ለመሥራት ላደረጉት ቁፋሮ መሬቱ ተንዶ የከሳሾች ቤት መሠረቱ በመጋለጡ ያለድጋፍ በመንጠልጠሉ እና ቤቱ

ስለተሰነጣጠቀ ቤቱ ከመደርመሱ በፊት ተከሳሾች በራሳቸው የቀጠሩት አማካሪ መሃንድስ ባቀረበው ሐሳብ መሰረት ችግሩ ወደ ባሰ ደረጃ ሳይደርስ የመከላከያ ዕርምጃ እንዲወሰዱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ልማት ቢሮ አሳውቋል፡፡ ተከሳሾች በመሃንዲስ የቀረበው ምክረ ሐሳብ ባለመሥራታቸው ቤቱ መደርመሱ፣ ሳሎኑ ደግሞ ያለድጋፍ መንጠልጠሉ በአጠቃላይ ቤቱ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ከሳሾች ቤቱን መልቀቃቸው፤ የአዲስ አበባ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ልማት ቢሮ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በመጀመሪያ የድጋፍ ግንቡን ከሰሩ በኃላ ቀጥሎ የከሳሾች ቤት እንዲሰሩ የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ተግባራዊ አላደረጉም፡፡ በወንጀል ያቀረቡት ክስም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የፈረሰውን ቤት መልሶ ለመሥራት ብር 764,154.20 /ሰባት መቶ ስልሳ አራት ሺ አንድ መቶ ሃምሳ አራት ከሃያ ሳንቲም/ እንደሚያስፈልግ በቦታው ተገኝቶ ኢትዮ አማካሪ አርክቴክቶችና መሐዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተባለ ገለልተኛ ድርጅት ስለአረጋገጠ ይህንኑ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ተከሳሾች እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ከሳሾች ቤቱ ተሰርቶ እስከሚገቡ በየወሩ ብር 8,000 የቤት ኪራይ እንዲወሰንላቸው ወጪና ኪሳራ የጠበቃ አበል ጭምር መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡

ተከሳሾች የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ፤ በፍሬ ጉዳዩ መልስ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ይዘው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው መቃወሚያ ሥራውን የሚሠራው ብራይት ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ ማህበር በመሆኑ በክሱ ገብቶ እንዲከራከር የሚል ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ከሳሾች ክስ ያቀረቡት ቤቱን አንገዛም ስላልናቸው ከቅን ልቦና ውጭ በለቀቁት ጎርፍ መሆኑን፣ የወንጀል ክስም ማቅረባቸው ተጠሪዎች ከቤቱ ውስጥ እየኖሩ ነው፡፡ በአካባቢው የተመሳሳይ ቤት ኪራይ ከ1000-2000 ብር ብቻ ነው፡፡ በተከሳሽ ከሳሽነት ቤቱ ለአደጋ የተጋለጠው ከሳሽ በለቀቁት ፈሳሽ መሆኑን በከሳሽ በተፈፀመው ድርጊት ምክንያት የቤቱ መሠረት ሲፈርስ አንድ ሠራተኛ መሞቱ፣ መከላከያ ግንብ ለመገንባት፤ ለድንጋይ ለጠጠር፣ ለአናጢ፣ ሚስማር በድምሩ 200,000 እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው የተከሳሽ ከሳሽነት አቅርበዋል፡፡

ከሳሾች ለቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት መልስ ያቀረቡ ሲሆን የከሳሾች ቤት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ መሆኑ በባለሙያ መረጋገጡ፤ ጉዳት የደረሰውም በተከሳሾች ጥፋት መሆኑን የወንጀል ክስም ውድቅ መደረጉ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙ የቃል ክርክር አዳምጧል፡፡ ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ (ቤቱ በማን ጥፋት ፈረሰ? ተከሳሾች ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል? ኃላፊነት አለባቸው ከተባለ መጠኑ ምን ያክል ነው?) በመመስረት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ቤቱ ሊፈርስ የቻለው የተከሳሾች የግንባታ ሥራውን ለማከናወን ባደረጉት ቁፋሮ በፍ/ህ/ቁ.1210 የተጣለባቸው ግዴታ ወደ ጎን በመተው እና አስፈላጊ ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው በፈጸሙት ጥፋት እንደሆነ ፍ/ቤቱ መገንዘቡን፤

ተከሳሾች ቤቱን ሊፈርስ የቻለው በአንደኛ ከሳሽ ጥፋት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የተከሳሽ ከሳሽነትን በተመለከተም ተከሳሾች ወጪ አውጥተው የድጋፍ ግንብ መሥራታቸውን ገልፀዋል ይህ የሚያመለክተው ደግሞ የከሳሽ ተከሳሾች ቤቱ ለአደጋ የተጋለጠው እነሱ በፈጸሙት ጥፋት መሆኑን እምነው መቀበላቸው ነው፡፡ በዚህ አግባብ የፈጸሙት ክፍያ የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡ ቤቱ መልሶ ለመሥራት የሚያስፈልገው ወጪ ብር 764,154.20 መሆኑን ኢትዮ አማካሪ አርክቴክቶችና መሐንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተባለ ገለልተኛ አካል ገምቶ አቅርበዋል፡፡ የግምቱ መጠን የተጋነነ ነው የሚለው መከራከሪያ በብይን ውድቅ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በገለልተኛ አካል ተገምቶ የቀረበው ብር 764,154.20 ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ የቤት ኪራይ በተመለከተ በራሳቸው ቤት ስለሚኖሩ አልተቀበለውም ፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ፍርድ ቤቱ ቤቱ የፈረሰው በአመልካቾች ጥፋት መሆኑ የክርክሩ ተካፋይ ሊሆን ይገባ ነበር የተባለው የስራ ተቋራጭ ከሰው ከሚጠይቁ በስተቀር አሁን ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት የሚመለስበት የህግ ምክንያት እንደሌለ፣ የካሳ መጠኑም በገለልተኛ ባለሙያ ተገምቶ የቀረበ ነው የሚነቀፍ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ካነሱዋቸው መሠረታዊ ነጥቦች፡- ህንፃው ገና ያልተገነባ በመሆኑ የኃላፊነት መሰረቱ በአግባቡ ያልታየ መሆኑን፤ የስራ ተቋራጩ ጣልቃ እንዲገባ የቀረበው ጥያቄ መታለፉ ተገቢ አለመሆኑን፤ የካሳው አወሳሰን ሥርዓትና መጠን አወሳሰን የተጋነነ ስለመሆኑ የሚገልጽ ነው፡፡ ተጠሪዎች የበኩላቸውን መልስ አቅርበዋል ፡፡ ዋና ፍሬ ነገሩ ቤቱ እየተገነባ ያለው በአመልካቾች መሆኑን ቤቱን በሙሉ ለመገንባት ግዴታ ገብቷል፡፡ ቤቱ የፈረሰው በቁፋሮ ላይ ነው የህንፃ ተቋራጩ መሥራቱን አያሳይም፡፡ የተከሳሽነት ከሳሽ ያቀረቡት በራሳቸው ስለሚሰሩት ነው፡፡ በአስተዳደሩ የድጋፍ ግንብ እንዲሰሩ ታዘው ነበር፡፡ የወንጀል ክስም ውድቅ ተደርጓል፡፡ የካሳው ዘዴና መጠን አሁን ቤት ለመሥራት የሚያስፈልገውን ወጭ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ቤቱ ለመሥራት ግዴታ ገብቷል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታቸው የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው የጉዳት ካሳ ጥያቄ በተመለከተ ግንባታ ለማከናወን የሥራ ተቋራጭ የነበረው ብራይት ኮንትራክሽን የክርክሩ ተካፋይ

ሊሆን ይገባ ነበር የሚል ክርክር በአመልካች ቀርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካቾች ግንባታው በራሳቸው የሚያከናውኑት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አጣርቶ በመወሰኑ አመልካች መክሰሳችን በአግባቡ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ከሥር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት ለመረዳት እንደተቻለው አመልካቾች የተጠሪዎች ቤት ላይ የመከለከያ ግንብ እንዲገነቡ፤ ጉዳት ከደረሰ በኃላም ቤቱን ሙሉ በሙሉ እንዲገነቡ በአዲስ አበባ አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ልማት ቢሮ መታዘዛቸው፤ አመልካቾችም ቤቱን ለመገንባት ግዴታ መግባታቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ሥልጣናቸው የተጠሪዎች ቤት ሊፈርስ የቻለው በአመልካቾች ጥፋት ስለመሆኑ አረጋግጠዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃ ምዘና ውጤት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳለ የሚቀበለው ነው፡፡ ምክንያቱም የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ሥልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን ያለመሆኑን መመርመር ብቻ ስለመሆኑ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የሥር ፍርድ ቤቶች ከሁለቱም ለጉዳዩ ኃላፊ ማን ነው? የሚለው በሥር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር እና የቀረበው ማስረጃ መሠረት በማድረግ አመልካቾች ቤቱን በማፍረስ ረገድ ጥፋት መፈጸማቸው ከድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ቤቱን አፍርሰዋል ባሉት ግለሰብ ላይ ክስ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራቀኙ ክርክር ማስረጃ በመመዘን ኃላፊ መሆናቸው ካረጋገጠ ግንባታው ለመሥራት ውል ገባ የተባለው የስራ ተቋራጭ የክርክሩ ተካፋይ ካልሆነ ልንጠይቅ አይገባም የሚለው ክርክር ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ድርጊት የተፈጸመው በሥራ ተቋራጭ ነው የሚሉ ከሆነም ለተጠሪዎች ተገቢ ተብሎ የተወሰነው ካሣ ከፍለው በሥራ ተቋራጩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚከለከሉበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡

የአመልካቾች የስራ ተቋራጭ የክርክሩ ተካፋይ ይሁን ጥያቄ በፌዴራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ተደርጓል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍርድ ሐተታው ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱ ተገቢነት እንደሌለው ገልጸዋል፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን ሌላ ተከራከሪ ግለሰብ ወደ ክርክሩ እንዲገባ በሕጉ አግባብ መጠየቁ ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ከግለሰቡ መብት አንጻር ብቻ ሳይሆን ከፍትሐብሄር ስነሥርዓት ሕግ ዓላማ ግብ ጭምር ነው፡፡ የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ዓላማና ግብ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ፍትሐዊ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ ውሳኔ እንዲያገኙ/ economic and efficient resolution of dies puts/ ማድረግ ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የህጉ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በተጠሪዎች የቀረበው የቤታችን ፈረሰብን ጥያቄ እንደገና በሥር ፍርድ

ቤት ክርክር ቀርቦ እንዲወሰን ማድረግ ጉዳዮች ከበቂ ጊዜ በላይ እንዲጓተቱ በማድረግ በተከራካሪዎች ጊዜ፤ ወጪና ጉልበት ከፍተኛ ጉዳት ማድረስ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች የሥራ ተቀራጩን ለመጠየቅ የሚከለክል የህግ አግባብ በሌለበት ሁኔታ ጉዳዩን በአዲስ ክርክር እንዲመራ መጠየቅ ከላይ የተመለከተው የፍትሐብሔር ህግ ዓለማና ግብ የሚያሳካ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች የሥራ ተቋራጭ የክርክሩ ተካፋይ ይሁንልን ጥያቄ ውድቅ ማደረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍረድ ቤት በመ/ቁ. 108002 በ18/05/2005 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 88156 በ30/03/2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች የተጠሪዎች ቤት መልሶ ለመሥራት የሚያስፈልገውን ብር 764,154.20 ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ገንዘብ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ጋር በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. በዚህ ፍ/ቤት የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሩ/ለ**

የሰ/መ/ቁ. 101345

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሴ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ ፀጋዬ ብርሃኑ - ወኪል ይርጋ ብርሃኔ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መሰረት ተገኝ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የፍትሐብሔር ጉዳይ ፍርድ እና አፈጻጸሙን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ለአፈጻጸሙ መሰረት የሆነው ውሳኔ የተሰጠው ደግሞ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 128082 ነው፡፡ በዚህ መዝገብ የተሰጠው የውሳኔ ይዘት ዋናው ክርክር የጀመረው በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስና የዳኝነት ይዘቱ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 166 የሆነ የመንግስት ቤት ከአሁኗ ተጠሪ ተከራይተው ሲሰሩበት የነበረ መሆኑ በመመሪያው መሰረት ክፍለ ከተማው አምኖበት የኪራይ ውል በስማቸው አዙሮ ካበቃ በኋላ ቤቱን እንድትለቅ በማለት ሁከት የፈጠረባቸው መሆኑን ዘርዝረው ሁከቱ እንዲወገድላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ክሱን መጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም የአራዳ ክፍለ ከተማውን በተከሳሽነት ፣ የአሁኗን ተጠሪ ደግሞ በጣልቃ ገብነት አከራክሮ ጉዳዩን መርምሮ ጣልቃ ገብ በመመሪያው መሰረት ልዩ ተጠቃሚ መሆናቸውን የማስረዳት ሸክም ያለባቸው መሆኑን፣ ይህን የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው ህጋዊ ተቋም የተሰጠ ማስረጃ ስላላቀረቡ ቤቱንም የእድሳት ፈቃድ አውጥተው በማደስ እየሰሩ እያለ ለጣልቃ ገብ ይገባል በማለት

ተረጋግተው እንዳይሰሩ ማድረጉ ሁከት ተግባር በመሆኑ ሁከቱ ሊቆም ይገባል በማለት የወሰነ ሲሆን በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪና ክፍለ ከተማው ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በመ/ቁጥር 128082 እና 128271 በሆኑት የአሁኑን አመልካች በመልስ ሰጪነት ሰይሞ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮ ተፈጻሚነት ባለው የውሳኔው ክፍል በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 166 የሆነውን ክርክር የተነሳበትን ቤት ለወ/ሮ መሰረት ተገኝ ይመለስላቸው፣የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ወስኗል፡፡

ይህንኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመያዝና የፍርድ ባለመብት በመሆን የአሁኑ ተጠሪ በመ/ቁጥር 213768 በሆነው አፈፃፀሙን የቀጠሉ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም በፍርድ ባለእዳነታቸው ቀርበው ፍርዱን እንዲፈፅሙ ተጠይቀው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊፈጸም አይችልም በማለት መዝገቡን የዘጋበትን ማስረጃ አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በችሎቱ አፈጻጸሙ አይቀጥልም በማለት የገለፀ መሆኑ አፈጻጸሙን አያግድም በማለት በመ/ቁጥር 128082 የተሰጠው ውሳኔ እንዲፈጸም ለአፈጻጸም መምሪያ ውሳኔውን በማያያዝ ትዕዛዙን አስተላልፎአል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128082 የሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤት ያለ ስልጣኑ ሁከት ነው ተብሎ የተሰጠ ነው የሚል ሆኖ እያለ የሚፈጸም ውሳኔ አለ ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ፍርድ ያረፈበት ንብረት ማዕድ ቤት እንጂ ስድስት ክፍል ቤቶች፣ ባህር ዛፎችና ጽድ ያለበት ቦታ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ መፈፀም ያለበት እንደ ፍርዱ መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 ድንጋጌ መረዳት የምንችለው ጉዳይ ሲሆን ደረጃውን ጠብቆ በቀረበው የአፈፃፀም ጉዳይ ላይ በአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውን የፍርድ ይዘት አድማስ በማስፋት ወይም በማጥበብ ፍርድን ለማስፈፀም የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ስለፍትሐብሔር ጉዳይ አፈጻጸም ከተደነገጉትና የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ

ነው። በአንድ የፍትሐብሔር ጉዳይ ፍርድ የሚሰጠው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182 እና 183 በተደነገገው አግባብ ሲሆን በዚህ አኳኃን የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 እና 372 መሠረት ሥልጣን ያላቸው የአፈፃፀም ችሎቶች ስለ ፍርድ አፈፃፀም የተዘረጉትን ሥርዓቶችን በመከተል እንደ ፍርዱ ከመፈፀም በቀር የአንድ ፍርድ ይዘትን በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆን በማስፋት ረገድ ፍርድን የመተርጎም ሥልጣን ያልተሰጣቸው መሆኑም ግልፅ ነው። ድንጋጌዎች በግልፅ የሚያስገነዝቡት አቢይ ነጥብ የፍርድ አፈፃፀም ስርዓት ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለውጥበት ሥርዓት መሆኑን ነው። በሌላ አገላለፅ የድንጋጌዎች አቀራረፅ፣ ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ ሲታይም የፍርድ አፈጻጸም ስለፍርድ አፈጻፀም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርድን በተግባር መተርጎም እንደመሆኑ መጠን የአፈጻጸም ሥርዓቱ ህጉን መሰረት ማድረግ ያለበትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን መሠረታዊ ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአነስተኛ ወጪ፣ጊዜና ጉልበት በተፋጠነና ፍትሓዊ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም በሚያስችል አግባብ ሕግ አውጪ ያስቀመጣቸው መሆኑን የምንረዳው ጉዳይ ነው።

በመሆኑም በሕግ አግባብ የተቋቋመ ፍርድ ቤት አከራክሮ መወሰን ብቻ ሳይሆን የወሰነው ውሳኔ ውጤት ባለው መልኩ ወደ ተግባር መለወጡን ጭምር ማረጋገጥ አቢይ ሐላፊነትና ተግባሩ በመሆኑ ይህንኑ በሕግ የተሰጠውን ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርግ ግን ሕጉንና ሕጉን ብቻ መሠረት ማድረግ አለበት። የአፈጻጸም ጉዳይ ደግሞ የሚመራበትን አግባብ ሕጉ ዘርግቷል። በሕጉ ከተዘረጉት ስርዓቶች አንዱ ደግሞ አፈጻጸሙ ሊመራ የሚገባው እንደዋናው ፍርድና ተገቢ ሁኖ ሲገኝም ፍርዱን ለማስፈፀም በሚያስችል አግባብ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና 392 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው።

ስለሆነም በሕግ አግባብ የተቋቋመ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በሕጉ አግባብ በተቋቋመ የበላይ ፍርድ ቤት በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሠረት እስካልተለወጠ ድረስ የማይፈፀምበት አግባብ የለም። ከላይ እንደተጠቀሰው በመርህ ደረጃ የተሰጡት የፍርድ ቤት ውሣኔዎች እንደፍርዱ ተፈፃሚነት እንዲያገኙ ማድረግ ህጉ የግድ የሚለው ጉዳይ ሲሆን አልፎ አልፎ ሊፈፀም የማይቻል ፍርድ ሊኖር እንደሚቻል ከፍታሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን መገንዘብ ይቻላል። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392(1) መሠረት አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ሊፈፀም የሚቻል ውሣኔ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ማረጋገጥ እንዳለበት ያመለክታል። ፍርዱ የማይፈፀምበት ህጋዊ ምክንያት ካለ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.392(2) መሠረት ይሄንኑ በማመልከት ሊፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚቻል ያስገነዝባል።

ከዚህ አንጻር የተያዘው ጉዳይ ስንመለከት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ዋና ክርክር በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሁከት ይወገድ ተብሎ ከተወሰነ በኃላ ጉዳዩ በይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በመ/ቁጥር 128082 እና 128271 በሆኑት የአሁኑን አመልካች በመልስ ሰጪነት፣ የአሁኗን ተጠሪ እና ክፍለ ከተማውን ደግሞ በይግባኝ ባይነት ሰይሞ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮ ተፈፃሚነት ባለው የውሳኔው ክፍል ደግሞ በአራዳ ክፍለ ከተማ 5 የቤት ቁጥር 166 የሆነውን ክርክር የተነሳበት ቤት ለወ/ሮ መሰረት ተገኝ ይመለስላቸው፣ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት በግልጽ ወስኗል ፡፡ ይህ ውሳኔ በግለጽ የሚያሳየው ቤቱ ለተጠሪ እንዲመለስላቸው እንጂ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያለስልጣኑ የታየ ነው በሚል የተደመደመ ያለመሆኑን ነው፡፡ ውሳኔው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ስለመለወጡ በአመልካችም በኩል የቀረበ ክርክር የለም እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ራሱ አፈጻጸሙን የማይመራ መሆኑን ጠቅሶ አመልካችን ከማሰናበቱ በስተቀር በመ/ቁጥር 128082 የሰጠው ውሳኔ የማይፈፀም መሆኑን ገልፆ አፈጻጸሙን ማቆሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አለማቅረቡን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳይል ፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ትዕዛዝ ለአፈጻጸም መነሻ ከሆነውና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128082 ከተሰጠው ዋና ውሳኔ ይዘት እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር የተጣጣመ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም ፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 213768 መጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 150831 ግንቦት 04 ቀን 2006 ዓ/ም በተሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128082 በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ሊፈጸምላቸው ይገባል ተብሎ አፈጻጸሙ ለአፈፃጸም መምሪያ መመራቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

ሰኔ 02 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

**ሃ/ወ**

የሰ/መ/ቁ. 100673

ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ አዳነ መንገሻ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የጋዘር ማዘጋጃ ቤት ተወካይ ዓ/ሕግ አሰግድ አድማሱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ይግባኝ ባይ ተጠሪ መልስ ሰጪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ተነስቶ ወደ ክርክር እንዲገባ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በሚል ያቀረበው ቅሬታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

ለዚህ አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የንብረት ግምት የተመለከተ ሲሆን አመልካች የጋዘር ማዘጋጃ ቤት ባለሙያ ባልሆነ ግለሰብ የአትክልት ግምት ብር 14,772 መወሰኑ በሕጉ አግባብ ባለመሆኑ ለደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረቡ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የአመልካች ይግባኝ ያስቀርባል ያለው በመሆኑ ለተጠሪ መጥሪያ ልከዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ 08867 በ09/05/2005 ዓ.ም በተፃፈ የላከው መጥሪያ ለተጠሪ ጽ/ቤት መዝገብ ቤት ገቢ የተደረገ ሲሆን የመዝገብ ቤቱ ሠራተኛ የሆኑት ወ/ሮ ዘውዲቱ ፀጋዬ ፈርመው እንደተቀበሉት እንዲሁም መተማመኛ ሰጥተው ከፍ/ቤቱ መዝገብ ተያይዟል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.70 /ሀ/ መሠረት ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩን የተመለከተው ሲሆን በባለሙያ ተሰራ የተባለው ግምት ውድቅ በማድረግ ተጠሪ ብር 128,700.00 ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች በክርክር ሂደት አወጣሁት ያለውን ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለው ጉዳዩን ለወሰነው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የመከላከያ መልሱ እንዲያቀርብ መጥሪያ የተላከለት ሲሆን በ25/06/2005 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው አቤቱታ አቅርበው አመልካችም መልስ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ለሥልጠና ሄደው እንደነበር፤ የኃላፊ ተወካዩም ቀበሌዎች ለማስፋፋት ሥራ የሄዱ በመሆኑ በሌሉበት የተሰጠው ፍርዱ ሊነሳ እንደሚገባ ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ለተጠሪ ጽ/ቤት መዝገብ ቤት ገቢ የሆነውን መጥሪያ በጽ/ቤቱ የመዝገብ ቤት ሠራተኛ ተፈርሞ መተማመኛ የተሰጣቸው በመሆኑ ተጠሪ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ የሚነሳበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብሏል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አንድ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ሊነሳ የሚችለው በቂ ምክንያት መኖሩን ሲረጋገጥ ነው፡፡ የተጠሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ባይኖርም ሌላ ሰው ተወክሎ መከራከር ይችል ነበር፡፡ የተጠሪ ጽ/ቤት የመዝገብ ቤት ሠራተኛ የሆኑት ወ/ሮ ዘውዲቱ ፀጋዬ መጥሪያው በ10/05/2005 ፈርመው ከተቀበሉ በኋላ ፈቃድ የወጡት በ13/05/2005 ዓ.ም ነው፡፡ ጽ/ቤቱ ለሠራተኛዋ የዓመት ፈቃድ ስትወጣ ተተኪ ሠራተኛ መኖሩን ሳያረጋግጥ ፈቃድ እንደማይሰጥ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የሚያሳምን በቂ ምክንያት አልቀረበም በማለት የተጠሪ አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ብይን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙ ካከራከረ በኋላ መጥሪያው ለጋዘር ማዘጋጃ ቤት መዝገብ ቤት ገቢ መደረጉን አልተካደም፡፡ ጉዳዩ ተቋማዊ ይዘት ያለው በመሆኑ የጽ/ቤቱ ሠራተኛ የተቀበለችው ቢሆንም ለጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊ መጥሪያው አልደረሰም፡፡ መጥሪያው የተቀበለችው ሠራተኛ በሎከር ውስጥ የቆለፈችው እና ለሌሎች ሠራተኞች ወይም የበላይ አመራር ካላደረሰች መ/ቤቱ በቸልተኝነት ወይም ህግን በመናቅ ትተዋል ለማለት አልተቻለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በጥልቀት መርምሮ አስፈላጊ ከሆነ ተጠሪ በቂና ተመጣጣኝ ኪሳራ እንዲከፈል ተደርጎ ወደ ክርክር ሊገባ ይገባ ነበር፡፡ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/2/ መሠረት ወደ ክርክር ለመግባት ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ መደረጉ ተቀባይነት የለውም በማለት ሽሮታል፡፡ አመልካች የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ በመሆኑ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ቀርቦ የበኩሉን መልስ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- ከፍርድ ቤት ወጭ የተደረገው መጥሪያ ለተጠሪ ጽ/ቤት መድረሱ፤ በጽ/ቤቱ ማህተም የተረጋገጠ መተማመኛ አቅርቦ ሳለ ፍርድ ተሽሮ ተጠሪ ወደ ክርክር እንዲገባ መደረጉ አግባብነት የለውም የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል የቀረበው መልስ ዋና ፍሬ ነገሩ፡- ከፍ/ቤት

የላከው መጥሪያ ለሚመለከተው ኃላፊ አለመድረሱ፤ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን እንዳልነበረው፤ መጥሪያው የሥነ ሥርዓት ሕጉ በደነገገው አግባብ አለመድረሱን መሠረት ተደርጎ ውሳኔው መሻሩ በሕጉ አግባብ ነው ሊጸና ይገባል የሚል መሆኑን ተረድተናል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም አቤቱታውን የሚደግፍ ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፍ/ቤት የተላከው መጥሪያ ለተጠሪ በሕጉ አግባብ አልደረሰውም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስለመጥሪያ አደራረስ የተመለከቱት መሠረታዊ ድንጋጌዎች ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፍ/ቤት መጥሪያ ለተጠሪ ጽ/ቤት ገቢ መሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክርክር መጥሪያው ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች እንዲቀርብ አልተደረገም፡፡ የሥራ ኃላፊዎቹ መጥሪያ መድረሱን ሳያውቁ ቀጠሮ አክብረው አልቀረቡም ሊባል አይቻልም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች መጥሪያ ማድረሱና ስለመድረሱም በተጠሪ ጽ/ቤት ክብ ማህተም የተረጋገጠ መተማመኛ ለፍ/ቤት ማቅረቡ መሠረት በማድረግ በሌሉበት የተሰጠው ፍርድ ለመሻር የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም የሚል ክርክር ስለማቅረቡ ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሰረቱ አንድ ተከሳሽ የፍርድ ቤት መጥሪያ ተልኮለት መጥሪያውም በአግባቡ ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይና የሚወሰን ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70/ሀ/ ሥር ተመልክቷል፡፡ የፍ/ቤት መጥሪያ ለሚመለከተው ተከራካሪ ወገን የሚሰጥበት ሥርዓትም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 96 እና 102 ሥር ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል ከፍ/ቤት የተላከው መጥሪያ በሕጉ አግባብ ለሚመለከተው ተከራካሪ ወገን ካልደረሰ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ የሚነሳበት ስርዓት መኖሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78/2/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለጽ/ቤት መጥሪያ መድረሱ በማመን ነገር ግን መጥሪያው ተቀበሉ የተባሉት የመዝገብ ቤት ሠራተኛ መጥሪያ ስለመቀበላቸው ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ባለማቅረባቸው ምክንያት ቀርበው ለመከራከር አለመቻላቸውን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡ ኩነቶች /facts/ የተጠሪ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ትዕዛዙን ገቢ በሆነበት ጊዜ በሌላ ቦታ ስልጠና እና ሥራ የነበሩ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች መጥሪያው ለጽ/ቤቱ መዝገብ ቤት ገቢ አድርገው መተማመኛ ከመውሰዳቸው በቀር መጥሪያ ለመቀበል አግባብ ላለው ሰው መጥሪያውን ስለማደረሳቸው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በፍርድ ሐተታው እንደገለጸው

መጥሪያውን የተቀበለችው ዘውዲቱ ፀጋዬ የተባለችው የተጠሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ መሆኗ ከመገለጹ ውጭ ነገረ ፈጅ ወይም መዝገብ ቤት ሹም መሆኗ አልተረጋገጠም፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ እንደተረዳነው መጥሪያው አግባብነት ያለው ሠራተኛ ተቀብሎት ለመሥሪያ ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች መቅረቡን የተረጋገጠ አለመሆኑን ነው፡፡ ከፍርድ ቤት የተላከው መጥሪያ ለሚመለከተው ተከራካሪ ወገን በሕጉ በተዘረጋው የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት መደረሱን ካልተረጋገጠ በስተቀር በሌለበት የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ ተደርጎ መሠረታዊ የሆነውን መከራከር መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል፡፡ የክ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት ለተጠሪ የተላከው መጥሪያ በአግባቡ አልደረሰም በማለት የደረሰበት ድምዳሜው እና ለድምዳሜው መነሻ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣኑ መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት በድጋሜ የሚመረመርበት ሥርዓት አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ሥልጣን መሠረታዊ የህግ አተረጓጐም ስህተት የተፈጸመባቸው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ብቻ መርምሮ መወሰን ስለመሆኑ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/3//ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ በመሆኑም የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንዲገባ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን አያሳይም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍረድ ቤት የደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. ተጠሪ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክር እንዲገባ መወሰኑ በሕጉ አግባብ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/አ**

የሰ/መ/ቁ.101478

ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** የረር ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ጌታቸው ለማ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተስፋዬ ባልቻ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንድ ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ እንዲነሳለት አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ክርክር ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት ተከሳሽ በነበረው የአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች የጽሁፍ መልሱን እንዲያቀርብ በተያዘለት የ30/07/2005 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ መልሱን ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ መሆኑን፣ ክሱን ለመስማት አስቀድሞ በተያዘው የ17/08/2005 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ በአመልካች በኩል የቀረበው ሰው ተገቢ ተወካይ ባለመሆኑ ፍርድ ቤት ለመከራከር የውክልና ስልጣን የተሰጠው የአመልካች ተወካይ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠት ለ01/09/2005 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱን፣ በዚህ ቀነ ቀጠሮም የአመልካች ተወካይ ባለመቅረቡ ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 70 (ሀ) መሰረት አመልካች በሌለበት ክሱን ከሰማ በኃላ የተጠሪውን ምስክሮች ለመስማት ለ19/10/2005 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱን፣በዚህ ቀነ ቀጠሮ የአመልካች ተወካይ አመልካች በሌለበት የተሰጠበት ትዕዛዝ ተነስቶ ወደ ጉዳዩ ገብቶ ለመከራከር እንዲፈቀድለት በ30/09/2005 ዓ.ም የተጻፈ እና በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቃለ መሀላ ስለመፈጸሙ በዚሁ ዕለት ምልክት የተደረገበትን ማመልከቻ ይዞ እንደቀረበ በችሎት መመዝገቡን፣ፍርድ ቤቱም የተጠሪው ምስክሮች እንዲመለሱ አድርጎ በቃለ መሀላ አቤቱታው ላይ የተጠሪውን የጽሁፍ አስተያየት ከተቀበለ በኃላ አቤቱታውን መርምሮ

አመልካች የቃለመሀላ አቤቱታውን ያዘጋጀው እና በሬጅስትራር ጽ/ቤትም ቀርቦ የመሀላ ቃል የፈጸመው በ30/09/2005 ዓ.ም ቢሆንም የቃለ መሀላ አቤቱታውን ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው ግን በ19/10/2005 ዓ.ም. መሆኑን እና ይህም ጉዳዩ አመልካቹ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ከተሰጠበት ከ01/09/2005 ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጠር የአንድ ወር ጊዜ ያለፈው መሆኑን ገልጾ የቀረበውን የቃለመሀላ አቤቱታ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (1) መሰረት በ01/11/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትዕዛዝ ውድቅ በማድረግ የተጠሪውን ምስክሮች ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ  በዚህ ጉዳይ አመልካች በሌለበት የተሰጠበት ትዕዛዝ እንዲነሳለት ትዕዛዙ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አላመለከተም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትዕዛዝ በሬጅስትራሩ ፊት የተመዘገበውን ማስረጃ መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታው የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ እና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አንድ ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ውሳኔው ወይም ትእዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትዕዛዙ ወይም ውሳኔው እንዲነሳለት ሊያመለክት እንደሚችል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (1) ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ጉዳዩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠው በ01/09/2005 ዓ.ም ሲሆን አመልካቹ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ የተሰጠበት ትዕዛዝ እንዲነሳለት የቃለ መሀላ አቤቱታ ያዘጋጀውም ሆነ በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ በተወካዩ አማካይነት የመሀላ ቃል የፈጸመው በ30/09/2005 ዓ.ም መሆኑ የተረጋገጠ እና የስር ፍርድ ቤትም የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ጥያቄው በቁጥር 78 (1) ድንጋጌ መሰረት በአንድ ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ የቀረበ አይደለም ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው አመልካች አቤቱታውን ያዘጋጀውም ሆነ በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ በተወካዩ አማካይነት የመሀላ ቃል የፈጸመው በ30/09/2005 ዓ.ም ቢሆንም አቤቱታውን ለፍርድ ቤቱ (ለችሎቱ) ያቀረበው ግን በ19/10/2005 ዓ.ም መሆኑን እና ከአንድ ወር የጊዜ ገደብ በኃላ የቀረበው አቤቱታ ሊስተናገድ የማይገባው መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ የሚከራከረው በአቤቱታው ላይ በ30/09/2005 ዓ.ም በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ በተወካዩ አማካይነት መሀላ ከፈጸመ እና ቀኑን ጭምር የሚገልጽ ምልክት ካስደረገበት በኃላ የቃለ መሀላ

አቤቱታውን ለችሎቱ ያቀረበው በዚያኑ ዕለት መሆኑን እና የችሎቱ ዳኛ የቃለ መሀላ አቤቱታውን ከተቀበሉ እና ከመሩበት በኃላ በዕለቱ ስራ በዝቶባቸው ስለነበረ በ19/10/2005 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ እንዲቀርቡ ነግረው ያሰናበቷቸው መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡የቃለ መሀላ አቤቱታው ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ለችሎት እንዲቀርብ በቃለ መሀላ አቤቱታው ላይ በዳኛው በጽሁፍ የተመራበት እና የተፈረመበት መሆኑን እና የተመራበትን ቀን ግን ያልተገለጸበት መሆኑን አመልካች አቅርቦ በአጣሪው ችሎት ካያያዘው የቃለመሀላው ቅጂ እና ቀርቦ በተያያዘው ዋናው መዝገብ ውስጥ ከሚገኘው የቃለመሀላው ቅጂ መገንዘብ ተችሏል፡፡በመሰረቱ እያከራከረ ያለው የቃለ መሀላ አቤቱታው ለችሎት የቀረበው መቼ ነው? የሚለው የጊዜ ጉዳይ ሲሆን የችሎቱ ዳኛ የቃለመሀላ አቤቱታውን ተቀብለው ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ እንዲቀርብ የመሩበትን ቀን በመሩበት ጽሁፍ ላይ ካልገለጹ ቃለመሀላው ለችሎቱ ዳኛ የቀረበው በ19/10/2005 ዓ.ም መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ አይኖርም፡፡ ይልቁንም አመልካች የቃለመሀላ አቤቱታውን በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ መሀላ የፈጸመው በ30/09/2005 ዓ.ም መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ አመልካች የቃለመሀላ አቤቱታውን ለችሎቱ አቅርቧል ተብሎ ሊወሰድ የሚገባው ቀን ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ጉዳዩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠው በ01/09/2005 ዓ.ም ሲሆን አመልካቹ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ የተሰጠበት ትዕዛዝ እንዲነሳለት የቃለ መሀላ አቤቱታውን ያዘጋጀውም ሆነ በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ በተወካዩ አማካይነት የመሀላ ቃል የፈጸመው እና ለችሎቱም ያቀረበው በ30/09/2005 ዓ.ም. መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ አቤቱታው የቀረበው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (1) ስር የተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ከማለፉ በፊት በመሆኑ አመልካች አቤቱታውን ያቀረበው የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኃላ ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 82332 በ01/11/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139139 በ21/09/2006 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የቃለ መሀላ አቤቱታውን ያቀረበው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (1) ስር የተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ከማለፉ በፊት ነው በማለት ወስነናል፡፡

3. አመልካች በክርክሩ ሊሰማ በተያዘው ቀጠሮ ቀርቦ መከራከሪያውን ያላሰማው ወይም መልስ ያልሰጠው በቂ በሆነ ምክንያት መሆን አለመሆኑን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (2) መሰረት መርምሮ ተገቢውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) መሰረት ወስነናል፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በውሳኔው መሰረት ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**የ/ማ**

የሰ/መ/ቁ.98593

ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካች፡-** አቶ ክንፈ ወልደሰንበት - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-**

1. አቶ ስለሺ በቀለ - የቀረበ የለም
2. ወ/ሮ ፍቅርተ በቀለ - ቀረቡ
3. አቶ ልየው መብራቴ - ቀረቡ
4. አቶ አስረስ አሊ - ተወካይ ወ/ሮ ወርቂ ግዛው ቀረቡ
5. አቶ አሰፋ በቀለ - ቀረቡ
6. አቶ ኃይሉ ቸርነት - የቀረበ የለም
7. የካ ክፍከ ከተማ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተዘጋ ነው የተባለን መንገድ በፍርድ ኃይል ለማስከፈት ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደቅደም ተከተላቸው ከ1ኛ እስከ 6ኛ ተከሳሾች በነበሩት የአሁኖቹ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ተጠሪዎች ላይ በ11/10/2004 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የአሁኑ 7ኛ ተጠሪ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ ወደ ጉዳዩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን ነው፡፡ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሾቹ ከይዞታቸው ውጪ በመውጣት አስር ሜትር ስፋት ያለውን መንገድ አጥረው በመያዝ በከሳሽ ላይ ችግር መፍጠራቸውን የሚገልጽ ሆኖ በክፍለ ከተማው ፕላን መሰረት የያዙትን አስር ሜትር መንገድ እንዲለቁ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ተከሳሾቹ በበኩላቸው የመንገዱ ስፋት አስር ሜትር ሳይሆን ስምንት ሜትር መሆኑን እና ከሕጋዊ ይዞታቸው በመውጣት አጥር በማጠር መንገድ ያላጣበቡ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቶ

የነበረ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት ውሳኔውን ሽሮ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚመለከተውን የአሁኑን 7ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ በማስገባት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ በመለሰው መሰረት ጣልቃ ገቡ በ26/04/2005 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ከሳሽ በቂ መተላለፊያ መንገድ ያላቸው መሆኑን፣በፕላኑ ላይ ያለውን መንገድ ለመስራት በቂ የሆነ ዝግጅት የሚፈልግ እና በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣ከሳሽ አቤቱታቸውን ማቅረብ የነበረባቸው ለአስተዳደሩ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ከሚመለከተው የክፍለ ከተማው የአስተዳደር ክፍል ተገቢው ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኃላ ተከሳሾቹ ለውስጥ ለውስጥ መንገድ የተጠናውን አስር ሜትር አጣብበው ወደ ይዞታቸው ያጠሩ መሆኑን፣ይሁን እንጂ መንገዱ የተጠናው ተከሳሾቹ ቦታውን በሕጋዊ መንገድ ከያዙ በኃላ እንደሆነ እና በካርታ ተከልሎ ከተሰጣቸው ይዞታ ውጪ የያዙት ቦታ እንደሌለ ከሚመለከተው የአስተዳደሩ አካል ተጣርቶ በተላከው ደብዳቤ የተረጋገጠ መሆኑን፣በፀደቀው የክፍለ ከተማው ፕላን መሰረት የተጠናውን መንገድ ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደወሰን ማስከበር፣የካሳ ክፍያ እና መሰል የቅድመ ዝግጅት ተግባራት መከናወን የሚገባቸው መሆኑን፣እንደነዚህ ዓይነት ተግባራትን ደግሞ አስተዳደሩ የሚያከናውነው በራሱ ዕቅድ እና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንጂ በግለሰቦች አነሳሽነት አለመሆኑን ገልጾ ክሱን ውድቅ በማድረግ እና ለተከሳሾቹ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ጭማሪ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የከተማው ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የቀረበላቸውን እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ዘግተው በማሰናበታቸው ሲሆን ለዚህ ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ዳኝነት የተጠየቀበት መንገድ አላግባብ መዘጋቱ ተረጋግጧል ከተባለ በኃላ ተጠሪዎቹ ሊለቁ አይገባም መባሉ፣እንዲሁም አመልካች በመንገዱ መዘጋት ተጎጂ መሆናቸው ከታወቀ ተጠሪዎቹ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር እንዲያቀርቡባቸው የመወሰኑን ተገቢነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው ለግዴታው መኖር ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2001 (1) እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 258 እስከ 261 ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳይ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በክርክሩ ረቺ ሊሆን የሚችለው በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ክርክሩን ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን በተሻለ ሁኔታ አስረድቶ በተገኘ ጊዜ

መሆኑም የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክስ የመሰረቱት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከይዞታቸው ውጪ በመውጣት አስር ሜትር ስፋት ያለውን መንገድ አጥረው በመያዝ በከሳሽ ላይ ችግር መፍጠራቸውን በመግለጽ ነው፡፡ይሁን እንጂ በጸደቀው የክፍለ ከተማው ማስተር ፕላን መሰረት አስር ሜትር የውስጥ ለውስጥ መንገዱ የተጠናው ተጠሪዎቹ አሁን ይዘው የሚገኙትን ይዞታ በሕጋዊ መንገድ ከያዙ በኃላ መሆኑ እና ይዘው በሚገኙት የይዞታ መጠን ላይም በሚመለከተው አካል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ የተሰጣቸው መሆኑ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡ይህም ተጠሪዎቹ አስር ሜትር መንገዱን አጥረው የያዙት ከሕጋዊ ይዞታቸው ውጪ በመውጣት ስለመሆኑ አመልካች በክሳቸው መሰረት ማስረዳት ያልቻሉ መሆኑን ነው፡፡ክስ ካስነሰው መንገድ ውጪ አመልካች በቂ የመተላለፊያ መንገድ ያላቸው መሆኑም በክርክሩ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች በዚህ ረገድ በሰበር አቤቱታቸው  ያቀረቡት ግልጽ የማስተባበያ ክርክር የለም፡፡በማስተር ፕላኑ መሰረት የውስጥ ለውስጥ መንገዱ የጸደቀ ቢሆንም ተግባራዊ የማድረግ ስራው የስር ፍርድ ቤቶች እንደገለጹት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል አማካይነት ዝግጅት ተደርጎበት እና አስፈላጊ የቅደመ ሁኔታ ስራዎች ከተከናወኑ በኃላ የሚፈጸም እንጂ ማስተር ፕላኑን መሰረት አድርገው ግለሰቦች የጸደቀው የውስጥ ለውሰጥ መንገድ ጉዳይ በሕግ አግባብ እንደተሰጠ በሚገመተው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በተረጋገጠው ሕጋዊ ይዞታቸው ውስጥ በሚገኝ ሌሎች ግለቦች ላይ በሚያቀርቡት የመንገድ ይከፈትልኝ ክርክር እልባት ማግኘት የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡የተጠናው አስር ሜትር መንገድ በተጠሪዎቹ የተያዘ መሆኑ መረጋገጡ ደግሞ ብቻውን መንገዱ ወዲያውኑ እንዲከፈት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል አይደለም፡፡በመሆኑም የአመልካቹን ክስ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

የወጪና ኪሳራ ጉዳይን በተመለከተ በሌላ አኳኃን እንዲፈጸም በግልጽ ካልተደነገገ በቀር በክስ ምክንያት ስለሚከፈለው ስለማናቸውም ወጪና ኪሳራ የሚከፍለውን ወገን፣የወጪንና የኪሳራውን ልክ፣የሚከፈልበትን ሀብት ምንጭ፣የአከፋፈሉን ሁኔታ እና ሌላውንም ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ፍርድ ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 462 ስር ተመልክቷል፡፡ይህም የተከራካሪ ወገኖችን የክርክር አቋም፣የረቺ እና ተረቺ ወገኖችን ማንነት እና መሰል ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ወጪና ኪሳራን የመወሰን ስልጣን በመሰረቱ ጉዳዩን ለሚወስነው ፍርድ ቤት የተሰጠ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በወጪና ኪሳራ ጉዳይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑም በስነ ስርዓት ሕጉ ቁጥር 466 ስር ተመልክቷል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች በክርክሩ ተረቺ ወገን መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡የተጠሪዎቹን የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ በስር የመጀመሪያ

ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ጭምር ተቀባይነት አግኝቷል፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በሕግ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት በአግባቡ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**_ው ሳ ኔ_**

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05149 በ21/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በከተማው ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 21346 በ17/04/2006 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 21533 በ27/05/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ሰለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

የሰ/መ/ቁ111599

ቀን 29/11/2007

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃም መሠለ

**አመልካቾች፡-** 1ኛ. አቶ መላኩ ካሳዬ
2ኛ. አቶ ደነቀው ደሳለው
3ኛ. አቶ ጋሻው ፀሐይነው
4ኛ. አቶ ሳንጃው አየለ
5ኛ. ወ/ሮ የሮም ካሳዬ

} ጠበቃ አቶ አላና ፉፋ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሱሲ አሊ ጠበቃ አቶ ኤቢሳ ሶቦቅሳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የእርሻ መሬትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል አመያ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት ከባለቤቴ እቶ ሸለማ አንገሣ ጋር በፍቺ ምክንያት በፍ/ቤት መዝገብ ቁጥር 12615 ተወስኖልኝ በ6/12/2003 እጄ ገብቶ የይዞታ ምስክር ወረቀት ያለኝን 5.5 ሄክታር መሬት የማሣ ኮድ ቁ. 2020፣2022፣2025 እና 2029 የሚታወቀውን ይዞታ መሬቴን አመልካቾች በጉልበት ይዘውብኛል የማሳ ኮድ 2025 የሆነውን መሬት 2004 ለ 2005 ዓ.ም የምርት ዘመን ለራሳቸው አርሰውታል የዚህ የምርት ዘመን ውጤት 32 ኩንታል ጤፍ ብር 30,000 ከፍለውኝ መሬቱ እንዲለቁልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች በበኩላቸው ተጠሪ ክስ የመሰረተችበትን መሬት ይዛው አታውቅም የተፈጠረ ሁከት የለም የሷ አይደለም የእሷ ቢሆን የመሬቱን አዋሳኝ አልጠቀሰችም፡፡

የምርት ውጤት መጠየቁ ስህተት ነው ከባለቤቷ በውሳኔ የተከፈላት መሬት 4.5 ሄክታር ነው ድርሻዋ 2.5 መሆኑን ውሳኔው እና አፈፃፀሙ ተመልክቶ እያለ ያቀረበችው አቤቱታ ተገቢ አይደለም ብለው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ካሳ እንድትከፍል ተደርጋ ከተራ ቁ.1-4 የተጠቀሱ አመልካቾች ቀደም ሲል ከሰጡት መልስ ጋር በተመሣሣይ መልስ ማቅረባቸው በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ 5ኛ አመልካች ወደ ክርክሩ የገቡት በጣልቃ ገብነት ተጠሪ ክሱ የመሰረቱት የጣልቃ ገብን ይዞታ በመጨመር መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪ የፍ/ቤቱ ውሳኔን ሽፋን በማድረግ ያልተወሰነላትንና ያልተፈፀመላት ፍ/ቤት የወሰነላት በማስመሰል እጅ ገብቶ ያላዘዘችበትን መሬት ጨምራበት ሌሎች ሰዎች የፈጠሩትን ሁከት አመልካቾች (የስር ተከሳሾች) እንደፈፀሙ አስመስላ ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ለደቡብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አዋሳኙን ጠቅሳ ክስ የመሠረተችበት በኮድ 0220፣2022፣2025 እና 2029 የሚታወቀው መሬት ተጠሪ ከባለቤታቸው ጋር በመ/ቁ.12615 በሆነው መዝገብ በነበራቸው ክርክር የመሬት ስፋት 4.5 ሄክታር ነው ተብሎ መሬቱን እኩል እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡ ይህን ውሳኔ መሠረት በማድረግ በአፈፃፀም በ/መ/ቁ. 12837 ተጠሪ ውሳኔው እንዲፈፀምላቸው በስር ፍ/ቤቱ ጠይቀው በውሳኔው መሰረት በማስፈፀም ውጤቱን ለፍ/ቤቱ እንዲያሳውቁ በፍ/ቤቱ የታዘዙ የቀበሌው አስተዳደር የሚመለከታቸው አካላት በአዋሳኝ ተጠቅሶ ውሳኔ የተሰጠበትን መሬት ለተጠሪ እና ለባለቤታቸው እኩል ለማካፈል ሲለኩት ውሳኔው ላይ እንደተመለከተው 4.5 ሄክታር መሬት ሳይሆን 11 ሄክታር መሬት መሆኑን ለፍ/ቤቱ አሳውቀው እንዲካፍሉ በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት ለተጠሪ 5.5 ሄክታር መሬት አካፍለው ለክተው ለፍ/ቤቱ ሪፖርት በማድረግ የአፈፃፀሙን መዝገብ የዘጋው መሆኑን ከስር ፍ/ቤት መዝገብ እንዳረጋገጠ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ገልፆ በውሳኔ ላይ የተጠቀሰው ይዞታ መሬት አዋሳኝ እና ኮድ ቁጥሩ ባልተቀየረበት ውሳኔው ላይ ከተመለከተው ስፋት በላይ ስለሆነ በማለት የተጠሪ አቤቱታ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ አይደለም የአሁኑ አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት ይቁም፡፡ በማሣ ኮድ 2029 ከሆነው የተጠሪ ይዞታ መሬት ተጠሪ ያጣችውን የአንድ ዓመት ምርት ብር 30,000 ከ1-6ኛ ያሉት (የስር መልስ ሰጭዎች) ይክፈሉ በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

በዚህ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ የአሁን አመልካች ቅሬታቸውን ለማሳረም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ በመቀጠልም የሰበር አቤቱታቸውም ለሰበር ሰሚው ችሎት ቢያቀርቡም ከፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ተፈፀመ ያሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ እንዲታረምላቸው አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ ይገባል የተባለው ለተጠሪ የተወሰነው 2.5 ሄክታር ነው ተብሎ የተፈፀመው 5.5 ሄክታር ድርሻ አለኝ በሚል መነሻ ከእጁ ያልገባ ይዞታ ላይ አመልካቾች ሁከት ፈጥረዋል መባላቸውንና ካሳ እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡
ግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክር አድርገዋል፡፡
ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሊመረመር ይገባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ ጋር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ መሬት በአዋሳኝ ተጠቅሶ እና በኮድ ቁጥር ተለይቶ (ተጠቅሶ) ተጠሪ ከባለቤታቸው ጋር ቀደም ሲል በነበራቸው የጋብቻ ፍቺ ውጤት ክርክር የመሬቱ ይዘት 4.5 ሄክታር መሆኑ ተገልፆ ተጠሪ ከባለቤታቸው ጋር እኩል እንዲካፈሉ በፍ/ቤት ውሳኔ አግኝቷል፡፡ ይህን ውሳኔ ተከትሎ ተጠሪ እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ፋይል ፍርድ ቤት አስከፍተው በውሳኔው መሠረት ለማስፈፀም የተላኩ የአስተዳደር አካላት በውሳኔ ተለይቶ የተመለከተውን መሬት ሲለኩ ስፋቱ በውሳኔው ላይ የተጠቀሰው 4.5 ሄክታር ሳይሆን 11 ሄክታር መሆኑንና ለፍ/ቤቱ ገልፀው 11 ሄክታር መሬት ለተጠሪ እና ለባለቤታቸው እኩል እንዲካፈል በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት ለተጠሪ 5.5 ሄክታር መሬት በድርሻ የተሰጣቸው መሆኑ ከስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተመልክቷል፡፡ በአንፃሩ የአሁን አመልካቾች ለክርክር ምክንያት የሆንው ይዞታ መሬት ሕጋዊ ይዞታ መሬታቸው መሆኑን የሚያስረዳ የተሻለ ማስረጃ አቅርበው አልተከራከሩም ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት በአዋሳኝ እና በኮድ ቁጥር ተለይቶ ይዞታው የተጠሪ እና የባለቤታቸው ነው እኩል ይካፈሉ ተብሎ ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ ውሳኔው ላይ የተመለከተው እና እንዲፈፀም በተደረገው መሬት ላይ የይዞታ መብት አለን የሚሉ ከሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ ላይ በተመለከቱ አግባብነት ባላቸው ድጋጌዎች መሠረት አመልካቾች መብታቸውን ጠብቀው ሳይከራከሩ በውሳኔው ላይ የተመለከተው የመሬት ሰፋት እና በአፈፃፀም የተከፈለው የመሬት ስፋት ልዩነት አለው በሚል ያደረጉት ክርክር ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች ይህን ይዞታ መሬት አልያዝንም ወይም በሕጋዊ መንገድ ያገኘነው ነው ብለው ያቀረቡት መከራከሪያም የለም፡፡

ስለዚህ በተጠሪ ይዞታ ላይ የአሁን አመልካች ሁከት መፍጠራቸውን ገልፆ የክልሉ ከፍ/ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚቻል አይደለም ብለናል፡፧

ሌላው በወረዳ ፍ/ቤት ላይ በማሣ ኮድ 2025 በሚል በተጠቀሰው በከፍ/ፍ/ቤት መዝገብ ውሳኔ ላይ ደግሞ በማሣ ኮድ 2029 በሚል በተጠቀሰው ይዞታ መሬት ላይ 2004 -2005 ዓ.ም የምርት ዘመን ተጠሪ ያጡት ምርት ብር 30,000 አመልካቾች ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነውን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 83 የካሳ ጉዳይ ካልሆነ እና ካልተካደ በስተቀር በክሱ የተጠየቀው ገንዘብ እንዲተመን ይጣራል በሚል ከተመለከተው የሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው በካሣ ጉዳይ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ዝም ማለቱ እንደታመነ ተቆጥሮ በካሣ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚያሰጥ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶችም ይህን ሥነ-ሥርዓታዊ ድንጋጌ በማለፍ የአሁን አመልካቾች በካሳው ጉዳይ ክደው አልተከራከሩም እንዳመኑ ይቆጠራል በማለት ተጠሪው ገንዘቡን በማስረጃ ባላረጋገጡበት ሁኔታ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. ለተጠሪ አመልካቾች ብር 30,000 ካሣ ይክፈሉ በማለት የተሰጠው የስር ፍ/ቤቶች የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

   አመልካቾች የተጠቀሰውን የካሳ ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም፡፡ ብለናል፡፡

2. የክልሉ ከፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ/ 32269 በቀን 8/12/2006፣ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ቁ. 196121 እና በመ/ቁ. 20370 በቀን 8/07/07 በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ ከዚህ በላይ በተራ ቁ. 1 ከተጠቀሰው የውሳኔ ክፍል ውጭ ያለው አከራካሪው ይዞታ መሬት የአሁኑ አመልካቾች ሁከት ድርጊት ፈፅመዋል ብለው የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ወጪ ግራ ቀኙ ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**የ/ማ**

የሰ/መ/ቁ.102543

ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-**ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 አስተዳደር ፅ/ቤት - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-**ወ/ሮ አሰለፈች ወልዴ - ጠበቃ ሙሉጌታ ዱላ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግስት የንግድ ቤት የተከራይነት መብትን የሚመለከት ክርክር ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ3/03/2005 ዓ.ም በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ፡- ተጠሪ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 123 የሆነውን የንግድ ቤት ከአመልካች ተከራይተውና በቤቱ ላይ የንግድ ፈቃድ አውጥተው ይነግዱ ከነበሩት ከወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረጋ ገርቢ ተከራይተው ክስ እስከአቀረበቡት ጊዜ ድረስ ሲነግዱበት የነበረ መሆኑን፣በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት ተጠሪ ተጠቃሚ መሆናቸውን፣ሆኖም የአሁኑ አመልካች ተጠሪን የመመሪያው ተጠቃሚ መሆናቸውን እየገለፀ ሲያመላልሳቸው ከቆየ በኋላ ሕዳር 01 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ ማስጠንቀቂያ የቤቱን የተከራይነት መብት ለተጠሪ ማከራየት እንደማይችል በመግለፅ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ቤቱን እንድታስረክቢ በማለት ያሳወቃቸው መሆኑን፣ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል አድርገው የነበሩት ግለሰብ አመልካችን ሳያሳውቁ ለሶስተኛ ወገን ቤቱን አከራይተው መገኘታቸው ተጠሪን በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውና አመልካችም ከተጠሪ ጋር በመመሪያው መሰረት ውል የመዋዋል ግዴታ ያለበት መሆኑን፣በመመሪያው መሰረት አመልካች ከተጠሪ ጋር የኪራይ ውል የመዋዋል ግዴታ እያለበት ቤቱን አስረክቢ በማለት የገለጸላቸው የሁከት ተግባር መሆኑን ዘርዝረው የተፈጠረው ሁከት ተወግዶላቸው አመልካች ከተጠሪ ጋር

በመመሪያው መሰረት ውል እንዲዋዋል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም አከራካሪው ቤት አብነ ቡድን ለተባለ የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት የተሰጠ እንጂ ተጠሪ መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑንና የአመልካች ተግባር ሁከት ነው ሊባል የማይችል መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ አመልካች ቤቱን ለፈለገው ሰው የማከራየት መብት ያለው መሆኑን፣የአብነ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት አባል የነበሩት ወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረጋ የተባሉ የማህበሩ አባል የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የተቋቋሙበትን ዓላማ በሚፃረር መልኩ ለተጠሪ አስተላለፈው የተገኙ በመሆኑ ቀድሞውኑም ባልነበራቸው መብት ሊሰሩበት የሚችሉበት አግባብ የለም የሚሉትን ምክንያቶችን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አልፎ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ደግሞ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ቤቱን ከአመልካች እውቅና ውጪ ከወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረጋ ተከራይተው ሲሰሩበት የነበረ መሆኑ መረጋገጡንና መመሪያው ደግሞ በዚህ አግባብ የመንግስት ቤትን ተከራይቶ ሲሰራ የነበረ የተከራይ ተከራይ ተጠቃሚ እንደሚሆን የደነገገ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ አመልካች የሁከት ተግባር ፈፅሟል፣ሁከቱ ሊወገድ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ አሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ተግባር የሁከት ተግባር ነው በማለት መወሰናቸው የአመልካችን ቤት ለፈለገው ሰው የማከራየት መብቱን ያላገናዘበና ቤቱ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተሰጥቶ እነዚህ ድርጅቶች ወደ መካከለኛ ደረጃ ሲተላለፉ በሌላ ተቋም አግባብነት ባለው መመሪያ መሰረት የሚተላለፍ ሁኖ እያለ ይህ ታልፎ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መመሪያ መሰረት ተደርጎ የተጠሪ የተከራይነት ተጠቃሚነት ሊረጋገጥላቸው ይገባል ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌደራል ፍርድ ቤቶች ነው? ወይስ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው? የሚለውን ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም አመልካች የሁከት ተግባር ፈጥሮብኛል በማለት ተጠሪ የሚከራከሩት ተጠሪ አከራካሪውን የንግድ ቤት የአመልካች ተከራይ ከሆኑት ከወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረጋ ተከራይተው በመስራት ላይ እያሉ መመሪያ ቁጥር 4/2004 መውጣቱንና በዚህም ምክንያት የተከራይነት መብት ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት ተጠሪ ሁነው እያለ አመልካች ተጠሪን ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ በማለት ማስጠንቀቂያ መፃፉ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሁከቱ ሊወገድ ይገባል፣የመመሪያው ተጠቃሚነትም ሊረጋገጥልኝ ይገባል በማለት ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶችም የግራ ቀኙን ክርክር መርምረው የአከራካሪው ቤት ተከራይ ማን እንደሆነ፣ ወደ ተጠሪ ይዞታ የገባበት አግባብ ምን እንደሆነ፣ተጠሪ ቤቱን የተከራዩበት አግባብ ከአመልካች እውቅና መሆኑ፣በዚህ አግባብ የተላለፈ የንግድ ቤት የተከራይነት መብት ተጠቃሚ የሚሆነው ደግሞ የተከራይ ተከራይ ስለመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6 ስር መመልከቱን መሰረት በማድረግ የአመልካችን ተግባር ሁከት ነው በማለት መወሰናቸውን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በቀጥታ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ የአመልካች ነበር በተባለው የንግድ ሱቅ የገቡት አመልካች እንደሚከራከሩት በቤቱ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት በተመደበበት ነው? ወይስ የንግድ ቤቱ ለጥቃቅን አነስተኛ ተቋማት አገልግሎት ከተመደበበት አላማ ውጪ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረጋ ወይም የእብነ ቡድን አባላት በመከራየታቸው ነው?የሚለው አከራካሪ ጭብጥ ጭምር ከመመሪያው አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚታይ እና ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ግንኙነቱ የንግድ መደብር ኪራይን መሰረት ያደረገ ነው የሚል ክርክርም የላቸውም፡፡ የንግድ ቤቱ ተከራይ ከነበሩት ከወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረጋ ከአብነ ቡድን አባለት እና ከተጠሪ መካከል በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት የተከራይነት መብት ሊያገኝ የሚገባው ማነው? የሚለው ጥያቄ በመሰረቱ በመመሪያው ላይ የተመለከቱትን ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት አድርጎ ምላሽ የሚያገኝ የመመሪያ አፈጻጸም ጉዳይ ከሚሆን ውጪ ከሁከት ድርጊት ጋር ግንኙነት ያለው ጉዳይ አይደለም፡፡ የአንድ ክስ ዝርዝር ይዘቱ ሳይታይ እርስቱ ብቻ ታይቶ የፍርድ ቤት የሥረ ነገር ዳኝነት የሚወሰንበት የሕግ አግባብ የሌለ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በጉዳዩ ላይ የሥረ ነገር ዳኝነት ያለው መሆን ያለመሆኑን ተከራካሪ ወገን ባያነሳውም ራሱ ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ//ቁጥር 9 እና 231(ለ) ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ክስ እርስቱ የሁከት ይወገድልኝ የሚል ቢሆንም ዝርዝር ይዘቱ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሲሆን መመሪያውን የሚያስፈጽሙት ደግሞ እንደ አመልካች ያሉት የከተማው አስፈጻሚ አካላት ናቸው፡፡

መመሪያውን መሰረት አድርጎ የሚነሳ የንግድ ቤት የተከራይነት መብት ጥያቄ ከከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣን እና ተግባር ጋር እንዲሁም የከተማው

አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር የተያያዘ እስከሆነ እና የከተማው አስተዳደር አካልም በተከሳሽነት የተሰየመ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ተቀብሎ የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር በአንቀጽ 41(1) (ለ) እና (ረ) ስር በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ የዚህ ዓይነቱ ክስ የሁከት ስም ተሰጥቶት በመቅረቡ ብቻ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ሊወድቅ የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡

በመሆኑም ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌደራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ሁኖ እያለ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን አይቶ ዳኝነት መስጠቱ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑና ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ ደግሞ ስርዓቱን ጠብቆ አቤቱታ እስከቀረበበት ድረስ ሊፀና የማይገባው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 200149 በ17/08/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137735 በ02/08/2006 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጥያቄው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ብለናል፡፡ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ጥያቄአቸውን ከማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. የዚህን ችሎት ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

    መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ይ**

የሰ/መ/ቁ. 105626

ሀምሌ 28 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መለሰ

**አመልካች፡-** አቶ ለገሰ ዲባባ ተተኪ ሚስት ወ/ሮ ክቡ ደሜ ጠበቃ አብዲ ፈይሳ ቀርቡ

**ተጠሪ፡-** ኢትዮጵያ ሜዲዩስ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ አቶ ሚሊዮን አለሙ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር የተያያዘ የጉዳት ካሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ በ27/01/2006 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በአጭሩ ከ01/01/2000 ዓ/ም ጀምሮ በግሪን ሃውስ በብረት ስራ ተመድበው በቀን ደመወዝ ብር 20 እየተከፈላቸው በወር 600 እየሰሩ በጨመሩት 8 ሜ. ብረት ላይ የግሪን ሃውስ ላስቲክ እየሰሩ እያሉ በ17/09/2005 ዓ/ም ብረቱን ወይም ላስቲኩን እንስተው ሁለት እግራቸው ሸባ ሆኖ ተሰብሮ መራመድ ያልቻሉና የጀርባ አጥንታቸው ተሰብሮ ሽንትም ሆነ ሰገራ መቆጣጠር ያልቻሉና ካሳና ሞራል ክፍያ እንዲሁም የተቋረጠባቸው ደመወዛቸውና ካሳ ከልዩ ልዩ ክፍያዎች ጋር ተጠሪ ሊከፍላቸው ሲገባ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ውሃ እንኳን የሚገዙበት አጥተው አልጋ ላይ ሁለት ሰዎች ተሸክመው የሚያስተኗቸው እና የሚያነሷቸው መሆኑን እያወቀ ሃኪም ቤት ሳይወስዳቸው በመቅረቱ ተከሳሽ ድርጅት በአሰሪ እና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 494/98 የስራ ስንብት ክፍያ ክፍያ ለዘገየበት የሦስት ወር ደመወዝ የጉዳት ካሳ የህክምና ወጪ ለወደፊት ህክምና ወጪ የሞራል ካሳ የተለያዩ ክፍያዎች በድምሩ 289,390 ብር ተከሳሽ ድርጅት እንዲከፈላቸው ክስ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በቀን 21/02/2006 ዓ/ም የተፃፈ መልስ ደግሞ ድርጅቱ አደጋ እንዳይደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ የሚያስፈልጉ ቀበቶ የሰጠ እና ስልጠና በየወቅቱ እንደሰጠ ከሳሽ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ሆን ብሎ በራሱ ጉዳት ያደረሰ ስለሆነ ልጠየቅ

አይገባም፡፡ ሃላፊነት አለ ካለ ደግሞ የጡረታ ተመዝጋቢ ስለሆኑ የተከፈለ መዋጮ ያለ ስለሆነ ተጠያቂ ሰራተኞች ጡረታ ኤጀንሲ ነው፡፡ አደጋው የደረሰው 2005 ዓ/ም ሳይሆን 2004 ዓ/ም ግንቦት 17 ቀን ነው፡፡ ጉዳት ከደረሰባቸው ቀን ጀምሮ የአንድ ዓመት ሙሉ ደሞዛቸው የከፈላቸው መሆኑ የህክምና ወጪ የሸፈነ መሆኑ የዘገየ ክፍያ እንደሌለ የዓመት እረፍት 24 ቀን አላቸው ግን 37 አይደለም፡፡ የህክምና ክፍያ በማስረጃ የተረጋገጠ አይደለም በማለት ክሳቸው ውድቅ ተዳርጎ በነፃ እንድሰናበት ብለዋል፡፡ ከሳሽም የመልስ መልስ የሰጡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ መዝኖ አጣርቶ በከሳሽ የደረሰው ሙሉ ዘላቂ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ተከሳሽ ሃለፊነት እንዳለበት በማረጋገጥ በድምሩ ብር 288,940 እንዲሁም የወጪና ኪሰራ ብር 500 እንዲከፈላቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ቅሬታ በይግባኝ ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር ከሰማ በኃላ የወረዳ ውሳኔ አፅንቷል፡፡

ተጠሪ አሁንም ቅሬታው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ተቀባይነት ስላገኝ ከሰሽ መልስ እንዲሰጥበት ትዕዛዝ ተሰጥቶበት ነገር ግን በሞት ስለተለዩ ባለቤታቸው የሚሰነትታቸው አረጋግጠው ስለቀረቡ መልስ እንዲሰጡና የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናላቸው በመልሳቸው ገልፀዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ክርክሩ ከቀጠለ በኃላ ፍርድ ቤቱ የሟች ባለቤት ስለሆኑ ሊከፈላት የሚገባው ካሳ መሆን አለበት ወይ የሚለው ጭብጥ በመያዝ ጉዳት የደረሰባቸው መደበኛ ስራቸው እየሰሩ በዚህም አደጋ የሞቱ ስለሆነ ተጠሪ ሃላፊነት አለበት በማለት አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 110 በመጥቀስ ብቸኛ ጥገኛ ስለሆነች ለጥገኞች ከሚከፈላቸው 50% የወር ደመወዝ 600x12x5x50/100 =18,000 ብር ድርሻቸው ብቻ ነው፡፡ ባለቤታቸው ስለሞቱ የስር ፍርድ ቤት የስራ ስንብት ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 40 የመዘግየት ክፍያን በአንቀፅ 36 እና 38 መሰረት የእረፍት ክፍያ በአንቀፅ 77 ቀርቷል የተባለውን ደመወዝ ለወደፊቱ ህክምና የሚያስፈልጋቸውን ክፍያ በአንቀፅ 106 እና የሞራል ካሳን አስመልክቶ የሰጡት ውሳኔ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ እንደተደረገ ነው፡፡

በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ለሰበር በቀን 04/05/2007 ዓ/ም የተፃፈ አቅርበው ተቀባይነት ስለአገኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ ክርክር ተካሂዷል፡፡ ባለቤታቸው ተተከተው ያቀረቡት አቤቱታ ባለቤቱ እየተከራከረ የነበረውን በሞት ምክንያት እንዳይቋረጥ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.49 መሠረት ተክቼ የገባሁ ሲሆን የተጠየቀውን ወደ ጎን በመተው ማንም ተከራካሪ ባላነሳው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182 (2) በሚቃረን መልኩ የጥገኞች ነው በማለት የሞት ካሳ ክፍያ ላይ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ በንብረት አስተዳዳሪነቴ ሥነ-ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት ተክቼ ነው የገበሁት ባለቤት ያልጠየቀውን ዳኝነት ጠይቄ የራሴ መብትና ጥቅም

ለማስከበር አይደለም፡፡ የጥገኞች የሞት ካሳ አልነበረም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናልኝ ነበረ የጠየቅሁት በስር ፍርድ ቤት የነበረውን በመተው ክርክር ያልተከሄደበት ጉዳይ ራሱ ማንሳቱ ስህተት ነው፡፡ በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ እንዲሻር አመልክቷል፡፡

በተጠሪ በኩል የቀረበ መልስ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182 (2) የሚቃረን አይደለም ካመነበት ማናቸውም ሌላ ማንሳት ይችላል፡፡ ጉዳት ከደረሰበት ግዜ ጀምሮ የአንድ ዓመት ደመወዝ የተከፈላቸው ስለሆነ ያልተከፈላቸው ክፍያ የለም የዘገየ ክፍያ የለም፣ የህክምና ወጪ ተሸፍኗል፡፡ የ100,000 ካሳ ክፍያ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2116(3) መሠረት የለውም ብለን ተቃውሞ አቅርበናል፡፡ የአመልካች ባለቤት መሞቱ የክርክሩ ጭብጥ መቀየሩ ስህተት የለውም ለአመልካች የሚከፈሉ ክፍያዎች ውስጥ መካተት ስለሌለባቸው የሰበር ሰሚ ችሎት ክፍያዎችን ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ የመስቀለኛ ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ጥያቄያቸው በትዕዛዙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በሰበር አጣሪ እንዲመረመር የተያዘው ነጥብ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሟች ወራሾች ካሉ ጠርቶ ሳያከራክር የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለውጦ መወሰኑ ሥነ-ሥርዓታዊ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉ እና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦችን ለመመርመር እንዲቀርብ የተደረገው ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘት ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ሥነ-ሥርዓታዊ ግድፈት አለ ወይ የለም የሚሉና ተያያዥ ጉዳዩች እንደሚከተለው ተመርምረዋል፡፡

ሟች ከተጠሪ ድርጅት ሰራተኛ እንደነበረ እና መደበኛ ስራተኛው እየሰሩ እንዳሉ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ዘላቂ ሙሉ አካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ በፍሬ ነገር የማጠራት ስልጣን ባለባቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነው፡፡ ተጠሪ ለጉዳቱ ሃላፊነት እንዳለበት የተለየዩ ክፍያዎች እንደተወሰነ ነው፡፡

ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከደረሰ በኃላ ከሳሽ የነበሩት መልስ ሳይሰጡ በመሞታቸው ነው ባለቤታቸው ተክተው በክርክሩ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

በክርክሩ ሂዳት እያለ ከሳሽ ወይ ተከሳሽ በሞት ብለይ የክርክሩ አካሄድ በምን አኳኃን እንደሚመራ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 48,49,50 ተመልክቷል፡፡ ፍ/ብ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 48(1) ክርክሩ እንዲቀጥል የሚያስችለው መብት የሚያቋርጥ ከሆነ የከሳሽ ወይ የተከሳሽ መሞት ክርክሩ እንዲቆም

አያደረገውም እንዲሁም አንቀፅ 49 50 የሚች መብት የሚታለፈው ከሆነ የሚች ከሳሽ ተከሳሽ ንብረት አስተዳደር ተተክቶ ክሩክሩ እንዳሚቀጥል ተደንግጓል፡፡

ስለዚህ ከዚህ የሥነ -ሥርዓት ድንጋጌ የምንረዳው የተጀመረው ክርክር የሚቋረጠው የሚተላለፍ መብት ከሌላ የሚተላለፍ ከሆነ ደግሞ ክርክሩ እንደሚቀጥል ነው ከዚህ ውጭ አዲስ ጭብጥ ተመስርቶ ክርክር ይዘት የሚለውጥበት ምክንያት የለም ክርክር የሚቀጥል ከሆነ በቀረበው ቅሬታ መሠረት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተፈፀመ ስህተት አለ የለም የሚለው ነው መጣራት የሚኖርበት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአሁኑ ተጠሪ የቀረበው አቤቱታ ሀላፊነት የለብኝም የተለያዩ  ክፍያዎች በአግባቡ አልተወሰነም በማለት ነው መልስ ሰጪ የነበሩት መልስ እንዲሰጥበት ትዕዛዝ በተሰጠበት ሂዳት በሞት መለየታቸው በስር ፍርድ ቤቶች የነበረው ጭብጥ ተለውጦ ጉዳዩ የጥገኞች ክስ የሚመለከት ሆኖ ተገኝቷል በማለትና የተቀሩት የተለያዩ ክፍያዎች ውድቅ በማድረግ ውስኗል ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅሬታ የተነሳባቸው የተፈፀመ የህግ ስህተት አለ የለም ብሎ መወሰን ሲገባው ከባለ ዋና ጉዳዩ (ሟች) መብት የሚተላለፍ ወይ የማይተለለፍ መሆናቸው አረጋግጦ የሚተላለፍ መብቶች አሉ ከተባለ በተጀመረው ክርክር መርምሮ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 48፣49፣50፣ በሚፈቅደው መሠረት ማጣራት ሲገባው በስር ፍርድ ቤት ክርክር ባልተነሳበትና ባልተካሄደበት ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(2) በሚቃረን መልኩ ሰለሞት ክፍያ መሰረት አድርጎ የተሰጠ ውሳኔ ሥነ-ሥርዓቱ በሚፈቅደው ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህታት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ፣ 185129 በቀን 05/01/2007 ዓ/ም የተሰጠ ውሳኔ በወ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348 (1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. በጉዳዩ ከተጠሪ ሌላ የሚገቡ ወራሾች ካሉ በማስገበት የከፍተኛ እና ወረዳ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ቅሬታ የቀረበበት ላይ መሠረት በማድረግ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖሩን ወይም አለመኖሩን መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348 (1) መሠረት ጉዳዩ ለኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲመለስ ወስነናል፡፡ በዚሁ ውሳኔ እንዲፈፀም ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርም አለበት፡፡**

**ሩ/ለ**

# ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ. 96853

መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ጀቫኒ ላሮዛ - ጠበቃ ስንታየሁ ብርሃኑ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አዳነች ተስፋዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል በሕግ ጥበቃ ሊደርግለት የሚችል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አለ ለማለት የሚቻልበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የክስ ይዘትም ከአሁኑ አመልካች ጋር ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ እስከ መስከረም ወር 2003 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ቆይተው መስከረም ወር 2003 ዓ/ም ግንኙነቱ መቋረጡንና ልጅ ባይወልዱም የተለያዩ የሚንቀሳቀሱም ሆነ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በግንኙነቱ ጊዜ ያፈሩ መሆኑን ጠቅሰውና የንብረቶቹን አይነትና ብዛት ዘርዝረው አመልካች ንብረቶቹን እኩል እንዲያካፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጡት መልስም በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የጀመሩት ከጥር 1999 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑን፣በዚህ ጊዜም ተጠሪ ይኖሩ የነበሩት በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/112 የቤት ቁጥር 539 እና 612 ውስጥ ሁኖ አመልካች ደግሞ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14/15 በቤት ቁጥር አዲስ ውስጥ መሆኑንና አብረው እንደባልና ሚስት ሁነው አለመኖራቸውን፣አመልካች በቱሪስት ቪዛ በ1998 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሐምሌ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተመልሰው መውጣታቸውን፣ነሐሴ 27 ቀን 1998 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ደግሞ ጥቅምት 11 ቀን 1993 ለሶስተኛ ጊዜ ሲመጡ ያረፉት በሴንትራል ሸዋ፣በሀሌዳይ፣በገነት ሆቴል፣በጊዮን ሆቴሎች እና ለሶስት ወራት በአቶ ሽመልስ ወ/ስላሴ ቤት መሆኑን፣ ከተጠሪ ጋር ጓደኝነት የጀመሩት ታህሳስ 29 ቀን 1999 ዓ/ም ሁኖ የቆዩትም እስከ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ/ም

ድረስ መሆኑን፣ግንኙነታቸውም አልፎ አልፎ እንደነበርና ተጠሪ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ/ም በኃላ ጣሊያን አገር አመልካች እንዲወስዷቸው ጠይቀው አመልካች ወስዷቸው ሳለ ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ፈጥረው ለመመለስ ባለመፈለጋቸው በመሀከላቸው ያለመግባባት በመፈጠሩ ግንኙነቱ መቋረጡንና ይህንም ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ/ም ኢትዩጵያ ከተመለሱ በኂላ ለጣሊያን ኢምባሲ አመልክተው ከዚያ በኂላ ነሐሴ 1999 ዓ/ም እስከ ሚያዚያ 2001 ዓ.ም ድረስ በፍቅር ጓደኝነት ከወ/ሮ መቅደስ አራጌ ጋር ለሁለት አመታት ከቆዩ በኂላ ከወ/ሮ እመቤት ጋሻው ጋር በፍቅር ጓደኝነት እየኖሩ እንደሚገኙ ዘርዝረው ከተጠሪ ጋር ከአምስት ወር በላይ በጓደኝነት ባልቆዩበት ሁኔታ በጣሊያን አገር እያሉ ያፈሩት ገንዘብ በኢትዩጵያ ባንክ በኩል ተላልፎላቸው ኢትዩጵያ ውስጥ ያፈሩትን የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት ተጠሪ ሊካፈሉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም ሲሉ ተከራክረዋል። የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኂላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከ1999 ዓ/ም እስከ መስከረም 2003 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ይዞ ንብረቶቹን በተመለከተም ግራ ቀኙ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት ወስኗል። በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ተጨማሪ ማስረጃ ከሰማ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የለም ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል። ከዚህም በኂላ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ይዞ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪ ምስክሮች ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭና ታዓማኒነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነት እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ነው ተብሎ የሚወሰድ አለመሆኑን እንደ ህጉ የማያስረዳ ሁኖ እያለና እንዲሁም የአመልካች ምስክሮች በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ግንኙነት በተመለከተ የሰጡት የምስክርነት ቃል ያላግባብ ውድቅ መደረጉ ተገቢውን የማስረጃ ምዘና ስርዓት ያልተከተለ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።እንዲሁም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዋና መዛግብት እንዲመጡ ተደርገው የግራ ቀኙ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘቱ ታይቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አለ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ዋና ነጥብና  ውጤቱ ምንድነው? የሚለው ተያያዥ ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ክስ ሲመሰርቱ በመካከላቸው ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ እስከ መስከረም ወር 2003 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት አብረው መኖራቸውን የገለፁ ሲሆን አመልካች ደግሞ ከተጠሪ ጋር ከአምስት ወር በላይ በጓደኝነት ያለመኖራቸውን ጠቅሰው ግንኙነቱ የሕግ ጥበቃ የሌለው መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ መልሳቸውን ሰጥተው ግራ ቀኙ አሉን ያሏቸውን ማስረጃዎችን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ የግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል የሰጡት የምስክርነት ቃልም በአጭሩ እንደሚከተለው የተመዘገበው ነው፡፡

ወ/ሪት ሳራ ተስፋዬ የተባሉት የተጠሪ 1ኛ ምስክር የተጠሪ እህት መሆናቸውን ገልጸው አመልካችና ተጠሪ ከ1998 ዓ/ም ክረምት ወራት ጀምሮ  እስከ  2003 ዓ/ም ድረስ ለአምስት አመታት ያህል በትዳር መቆየታቸውን፣ይህንኑ ሊያውቁ የቻሉትም አመልካችና ተጠሪ ወደ ምስክሯ ቤት  አብረው ሲሄዱና አመልካችና ተጠሪ አብረው ሲኖሩ ስለነበር መሆኑን፣አመልካች ወደ ውጪ ይሄዱ በነበሩበት ጊዜ ምስክሯ ይሄዱ እንደነበርና አመልካች ውጪ ሄደውም ሁለት፣ሶስት ወራት ይቆዩ እንደነበር፣አመልካችና ተጠሪ ቤት ገዝተው እስከ ተጣሉበት ጊዜ ድረስ አንድ ቤት ሲኖሩ እንደነበር፣አመልካችና ተጠሪ አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ቤት፣መኪና እና የቤት ቀሳቁሶችን ገዝተው እንደነበር፣አመልካችና ተጠሪ ከክረምት 1998 ዓ/ም ጀምሮ በጓደኝነት መስሪያ ቤት መጥተው እንደተዋወቁ እንደሚያወቁና ለአምስት ተከታታይ አመታት ያለማቋረጥ መኖራቸውን፣ቤት፣መኪና እና የቤት ቁሳቁሶች ሲገዙ ምስክሯ እንዳልነበሩ ገልፀው መስክረዋል፡፡ወ/ሮ እቴነሽ ተስፋዬ የተባሉት ሁለተኛ የተጠሪ ምስክርም የተጠሪ እህት መሆናቸውን ገልጸው የሰጡት የምክርነት ቃል በይዘቱ ከ1ኛ ምስክር ቃል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ወ/ሮ ዳግማዊት ደርቡ የተባሉት የተጠሪ ሶስተኛ ምስክር የተጠሪ የአክስት ልጅ መሆናቸውን ገልጸው ከውጪ አገር ቆይተው በ1999 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ተጠሪ ከጣሊያን አገር የመጣ የውጭ ሰው አግብተው እየኖሩ መሆኑን ወላጅ እናታቸው የነገሯቸው መሆኑን፣አመልካችና ተጠሪ በምስክሯ ወላጅ እናት ቤት በ2000 ዓ/ም እራት ሲጋበዙ አንድ ጊዜ መመልከታቸውንና አመልካችና ተጠሪ አንድ ላይ በአንድ ቤት ሲኖሩ እንደነበር ራሳቸው ተመልክተው የተረዱት ሳይሆን ሰው ነግሯቸው ያወቁት ሁኔታ መሆኑን፣አመልካችና ተጠሪን እንደባልና ሚስት መኖራቸው ሊያውቁ የቻሉት በቤተሰብ ሰርግም ሆነ ለቅሶ ወይም ልደትና

ክርስትና ላይ እንደባልና ሚስት ሁነው  በመሆኑ ምክንያት መሆኑን መስክረዋል፡፡ ወ/ሮ ሀረጓ በየነ የተባሉት የተጠሪ 4ኛ ምስክር በበኩላቸው በግራ ቀኙ መካከል ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ገልጸው አመልካችንና ተጠሪን በ1999 ዓ/ም ክረምት ውስጥ አግኝተዋቸው ተጠሪ አመልካችን ለምስክሯ ባለቤቴ ነው ብላ ያስተዋወቻቸውና አመልካችም ይህንኑ የተጠሪዋን ንግግር ይሰማና አመልካችም ጆቫኒ እባላለሁ ብሎ የመለሰላቸው መሆኑን እንዲሁም ቀኑን፣ወሩንና አመተ ምህረቱን በማያስታውሱት ጊዜ አመልካችና ከሌሎች ሴቶች ጋር ሲመለከቷቸው እንደነበር ገልጸው የመሰከሩ ናቸው፡፡  አቶ ተፈራ ሲሳይ የተባለው የተጠሪ አምስተኛ ምስክር በበኩላቸው በግራ ቀኙ መካከል ዝድምና የሌላቸው መሆኑን ገልፀው አመልካችና ተጠሪ መኪና ለመከራየት ወደ ምስክሩ በ1999 ዓ/ም  መሄዳቸውን መኪና ተከራይተው መሄዳቸውን፣ከዚያ በኋላም በሚያዚያ ወር 2002 ዓ/ም  መኪናቸውን በብር 80,000.00 ሸጠው  ቴሮስ መኪና በብር 172,0000.00 የገዙ መሆኑን እንደሚያውቁ፣አመልካችና ተጠሪ በሚመጡበት ጊዜ እንደባልና ሚስት ሁነው እንደሚረዷቸው የመሰከሩ ናቸው፡፡ወ/ሮ አስናቀች ደስታ የተባሉት የተጠሪ ስድስተኛ ምስክር ደግሞ ከግራ ቀኙ ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ተጠሪ የጓደኛቸው እህት መሆናቸውንና እርሳቸውም ከተጠሪ ጋር ጥቂት ጊዜ አብረው የሰሩ መሆኑን፣ጽጌ የተባለችው የተጠሪ እህት ተጠሪ ከውጭ ሀገር ዜጋ ጋር ተዋውቃ አብራ መኖርም የጀመሩ መሆኑን ለምስክሯ የነገረቻቸው መሆኑን፣ከዚህ በኋላ 1999 ዓ/ም ገና አልፎ  በሳምንቱ ፅጌ ቤት በእንግድነት ሂደው ለመጀመሪያ ጊዜ አመልካችና ከተጠሪ ጋር መጥተው እንደተመለከቷቸውና ከዚያ በኋላ ወንድሚ ተስፋዬ ሲያገባ አመልካችና ተጠሪ አብረው በሰርጉ ላይ በ2000 ዓ/ም መጥተው እንደነበር በሳምንቱ በሙሽሪት ቤት መልስ ላይ ተገናኝተው እንደነበር፣አመልካችና ተጠሪ ቤት እንዳላቸው የሰሙ መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ በተለያዩ ዝግጅቶች ሲመጡ ባልና ሚስት ተብለው መሆኑን እንደሚያውቁ መስክረዋል፡፡ወ/ት ሸዋእመቤት ተስፋዬ የተባሉት የተጠሪ 7ኛ ምስክር የተጠሪ እህት መሆናቸውን ገልጸው የሰጡት የምስክርነት ቃልም በይዘቱ ከተጠሪ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ቃል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች አሉኝ ያሏቸው ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሲታይም እንደሚከተለው የተመዘገበው ነው፡፡

አቶ ማርቆስ የተባለው የአመልካች 1ኛ ምስክር ከግራ ቀኙ መካከል ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ገልጸው አመልካችንና ተጠሪን ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ ጎረቤቶቻቸው ሁነው እንደሚያውቋቸው ጠቅሰው ለተወሰኑ ወራት ብቻ ተጠሪን ከአመልካች ጋር ከአዩ በኋላ ከአመልካች ጋር መቅደስ የሚባሉ ሴት ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ እንደሚያዩ እና ወደ እርሳቸው ቤትም እኚህ ሴት ሲሄዱ የነበሩ መሆኑን፣አመልካች በራሳቸው ስም በሚታወቅ ቤት ሲኖሩ ምስክሩ ደግሞ ከወንድማቸው ቤት ከአመልካች ጋር በጉርብትና ይኖሩ እንደነበር እንዲሁም አመልካችና ተጠሪ በ2000 ዓ/ም

መጀመሪያ አከባቢ አንድ ሲመለከቷቸው የነበሩ ከመሆኑ ውጪ አመልካችን ከወ/ሮ መቅደስ እና ከወ/ሮ እመቤት ጋር ሲመለከቷቸው እንደነበር የመሰከሩ ናቸው፡፡አቶ አሊ ሰይድ የተባሉት የአመልካች ምስክር ደግሞ ግራ ቀኙን ያወቁበትን ጊዜ ለይተው አመልካችና ተጠሪ ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ በጓደኝነት እንደሚኖሩ የሚያውቁ መሆኑን፣ይህንኑ ሊያውቁ የቻሉትም ወደ ጣሊያን አገር ሲሄዱ ምስክሩ በአመልካች ቤት ውስጥ የጥበቃ ስራ ሲሰሩ ስለነበሩ መሆኑን፣የጥበቃ ስራውን የሰሩትም እስከ 2001 ዓ/ም ሁኖ አመልካች በሰኔ ወር 1999 ዓ/ም ከጣሊያን አገር ከተመለሱ በኋላ ከተጠሪ ጋር ያላዩዋቸው መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ በነበሩበት ጊዜ ተጠሪ ወደ አመልካች ቤት መጥተው የሚሄዱ መሆኑንና ብዙ ጊዜ ተጠሪ በአመልካች ቤት ውስጥ ያልኖሩ መሆኑን እንዲሁም አመልካችን ከወ/ሮ መቅደስ ጋር ምስክሩ እንደሚያያቸው እና በ2001 ዓ/ም ግን ምስክሩ ከጥበቃ ስራ ስለለቀቁ የሚያውቁት ነገር ያለመኖሩን ገልጸው የመሰከሩ ናቸው፡፡ወ/ሪት ተሰረ አሰግደው የተባሉት የአመልካች ምሰክር ደግሞ ከግራ ቀኙ ጋር ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው ግራ ቀኙን ከመስከረም ወር 2001 ዓ/ም ጀምሮ በቤት ሰራተኛነት በአመልካች ቤት ገብተው ስለነበር እንደሚያውቋቸው ገልጸው አመልካችና ተጠሪ አብረው ሁነው ከደላላው ቤት ምስክሯን ማስመጣታቸውን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ ከአመልካች ቤት ውስጥ ያልነበሩ፣የማይመጡ የነበረ መሆኑን፣ ምስክሯ በአመልካች ቤት እስከ መስከረም ወር 2004 ዓ/ም ድረስ እንደቆዩ፣በዚህ ጊዜ ውስጥም መቅደስ የሚባሉ ሴት ከአመልካች ጋር ይኖሩ እንደነበርና እኚህ ሴትም ከአመልካች ጋር ምስክሯ እስከ ቆዩበት ጊዜ እንዳልቆዩና እመቤት የተባሉ ሴት ከአመልካች ጋር እንደነበሩ የመሰከሩ ናቸው፡፡ ወ/ሮ እመቤት ጋሻው የተባሉት የአመልካች 4ኛ ምስክር በበኩላቸው የአመልካች የፍቅር ጓደኛ መሆናቸውን ገልጸው አመልካችን ከመጋቢት ወር 2002 ዓ/ም ጀምሮ እንደሚያውቋቸውና ከአመልካች ጋር አብረው የማይኖሩ ቢሆንም በሳምንት ሶስት ቀንና እረፍት በሚሆንበት ጊዜ ከቤቱ ሄደው እንደሚያድሩ፣ስራ በሌላቸውና ስራ ባቆሙ ጊዜም ሁለት ወር የሚሆን ከአመልካች ቤት ሂደው እንደሚቆዩና በዚህ ጊዜ ተዘሩ የምትባል የቤት ሰራተኛ እንደነበረችና የአሁኗ ተጠሪ ወደ ቤቱ መጥተው እንደማያውቁ እንዲሁም ከአመልካች ጋር ጓደኝነት ከጀመሩ ጊዜ ጀምሮ ግንኙነቱ ቀጥሎ ያለ መሆኑን የመሰከሩ ናቸው፡፡አቶ ግዛቸው አምዴ የተባለው የአመልካች አምስተኛ ምስክር ደግሞ ከግራ ቀኙ ጋር ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው አመልካችና ተጠሪ ከሐምሌ ወር 1999 ዓ/ም ጀምሮ በጉርብትና እንደሚያውቋቸውና ተጠሪን ደግሞ ከ1999 ዓ/ም መጨረሻ ጀምሮ እስከ ጥር ወር 2000 ዓ/ም ድረስ ብቻ እንደሚያውቋቸው ገልጸው በዚህ ጊዜ ውስጥም ተጠሪን ሁለት ጊዜ ብቻ ያገኟቸው መሆኑን፣ ከአመልካች ጋር ከጥር ወር 2000 ዓ/ም በኋላ የሚያገኟቸው ወ/ሮ መቅደስን ስለመሆኑና እሳቸውም ቢሆን ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2003 ዓ/ም ድረስ አልፎ አልፎ እንደሚመለከቱ ገልፀው መስክረዋል፡፡ ዋና ሳጅን እልፍነሽ ግርማ የተባሉት የአመልካች 6ኛ ምስክር ደግሞ አመልካች ሲ.ኤም.ሲ አካባቢ ቤት ተከራይተው በነበሩበት ጊዜ ተጠሪን እስከ ሰኔ

ወር 1999 ዓ/ም የተመለከቷቸው መሆኑን በግንቦት ወር 1999 ዓ/ም አመልካች ተጠሪን ወደ ጣሊያን አገር ይዘው ሄደው ከሁለት ወር ቆይታ በኋላ አመልካች መምጣቱን ለምስክሯ ከነገሯቸው በኋላ ምስክሯ አመልካችን ተጠሪ ደህና መሆናቸውን ሲጠይቁ አመልካች ከተጠሪ ጋር ተጣልተው እንደተለያዩ አመልካች ለምስክሯ የነገሯቸው መሆኑን፣ምስክሯ ከተጠሪ ጋር አንድ ቀበሌ ይኖሩ ስለነበርም ከአመልካች ጋር ለማስታረቅ በሚፈልጉበት ጊዜ ተጠሪ ከአመልካች ጋር መታረቅ የማይፈልጉ መሆኑን ለምስክሯ እንደነገሯቸው፣ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አመልካችና ተጠሪ ተገኛኝተው እንደማያውቁና ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች መቅደስ ከምትባል ሴት ጋር ተዋውቀው ወደ ምስክሯ ቤት ይዘው ሄደው እንደነበርና መቅደስ ጋር ደግሞ አመልካች በግምት ለሁለት አመታት ያህል አብረው የቆዩ መሆኑንና ከመቅደስ ጋር ከተለያዩ በኋላ ደግሞ እመቤት የሚባሉ ሴት ጋር በጓደኝነት እየኖሩ እንደሚገኙ መስክረዋል፡፡አቶ ወንደወሰን ተሰማ የተባሉት የአመልካች ሰባተኛ ምስክር በበኩላቸው ከግራ ቀኙ ጋር ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው በአከባቢው የጥበቃ ኃላፊ ሁነው ሲሰሩ አመልካችንና ተጠሪን ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ እንደሚያውቋቸው፣ተጠሪ አመልካች ወደ ገዙት ቤት 1999 ዓ/ም መጨረሻ አካባቢ ከተጠሪ ጋር አልፎ አልፎ ሲመጡ እንደነበር፣ተጠሪ እስከ መስከረም 2000 ዓ/ም ድረስ ያዩአቸው እንደነበርና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ ከአመልካች ጋር እንዳላያቸውና አመልካች ከሌሎች ሴቶች ጋር ይታዩ የነበረ መሆኑን የመሰከሩ ናቸው፡፡የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለተጨማሪ ማስረጃነት የሰማቸው ምስክሮች ቃልም በይዘቱ ከላይ የተጠቀሱት የአመልካች ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል የሚደግፍ መሆኑን መዝገቡ የሚያሳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡እንግዲህ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች እነዚህ ከሆኑ ከሕጉ አገናዝቦ ግንኙነቱ በሕጉ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል መሆን ያለመሆኑን መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

በመሰረቱ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 98፣ 99 እና 106 በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ አለ የሚባለው መቼ እንደሆነና የግንኙነቱ መኖር በምን አይነት መንገድ ማስረዳት እንደሚቻል ያመላክታል፡፡የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 106/2/ ድንጋጌ ሲታይም ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ለሚኖሩ ሰዎች የሚፈለገው ማስረጃ ወንዱና ሴትየዋ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው የሚገምቷቸው መሆኑን ማሳየት እንደአለበት ያመለክታል፡፡በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የሚቀርበው ማስረጃ ጋብቻ መፈፀሙን እንዲያረጋግጥ የማይጠበቅ ሲሆን ሕጉ ለይቶ ያስቀመጠው የማስረጃ አይነት ስለሌለ በማናቸውም ማስረጃዎች ስለግንኙነቱ ማስረዳት ይቻላል፡፡ በጉዳዩ ላይ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የሚያሳዩ፣ሕጋዊ ውጤቱ የሚኖረው ሶስት አመትና ከዚያ በላይ አብሮ መኖሩ ሲረጋገጥ መሆኑና ምስክሮች

የሚያረጋግጡት ሶስት አመትና ከዚያ በላይ አብሮ መኖራችንና በትዳር መልክ አብሮ መኖርን ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች እና ተጠሪ የነበራቸው ግንኙነት ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ሲታይ በተጠሪ ምስክሮች ቃል አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የማያሳዩ፣ በሕጉ ግንኙነቱ ሕጋዊ ውጤቱ የሚኖረው ሶስት አመትና ከዚያ በላይ አብሮ መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የተመለከተውን የተጠሪ ምስክሮች ጊዜውን በትክክል ለይተው ያልመሰከሩ እና አመልካችና ተጠሪ በትዳር መልክ አብሮ መኖርንም ያላረጋገጡ መሆኑን ከአመልካች ምስክሮች ጋር ተዳምሮ ሲታይ የምንገነዘበው ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ህጉ ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ለሚኖሩ ሰዎች የሚፈለገው ማስረጃ ወንዱና ሴትዩዋ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው የሚገምቷቸው መሆኑን ማሳየት እንደአለበት የሚያመላክት ሲሆን አመልካችና ተጠሪ ይኖሩበት ነበር በተባለ አከባቢ ያሉት የአመልካች ምስክሮች ቃል አመልካችና ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ ግንኙነት እንደነበራቸው፣አመልካች ከሌሎች ሴቶች ጋር አንድ ላይ ይኖሩ እንደነበር፣ተጠሪ ከሌሎች ሴቶች ጋር የቀጠለው የአመልካች ግንኙነት እያለ ከአመልካች ግንኙነት ያልነበራቸው መሆኑን ጭምር የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጠሪ ምስክሮች ቃል በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነት በትዳር መልክ ቀጣይነት የነበረው መሆኑን ባልመሰከሩበትና በአንፃሩ የአመልካች ምስክሮች ስለጉዳዩ የሰጡት የምስክርነት ቃል የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት በትዳር መልክ ሳይሆን ጊዜያዊ የፍቅር ግንኙነት የነበረ መሆኑን በአረጋገጡበት አግባብ የተጠሪ ምስክሮች የተጠሪ ቤተዘመድ በመሆናቸው ብቻ አይታመኑም ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መርህ መሰረት ያላደረገና በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 97፣98፣99 እና 106(2) ድንጋጌወች መሰረታዊ አላማ፣ይዘትና መንፈስ ውጪ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት  ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 88241 ጥቅምት 09 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 91809 ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 128087 ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ብ**

የሰ/መ/ቁ 98029

ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ ልዩሴት ሥዩም ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሽዋፈራ ንጉሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በበረኸት ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው አመልካች የነበሩት የአሁኑ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የመሠረቱት ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ ይፍረስልኝ እና የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ መነሻ ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው የቆዩና አንድ ልጅ የወለዱ ቢሆንም ጋብቻው ውስጥ ተግባብተው መኖር ያልቻሉ መሆኑን ጠቅሰው ጋብቻው ፈርሶ የጋራ ንብረት ያካፍለኝ በማለት የንብረቶቹን አይነት እና ብዛት ዘርዝረው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው መኖራቸውንና ልጅ መውለዳቸውን ሳይክዱ የጋራ ንብረትን በተመለከተ በአመልካች ተዘርዝረው ከቀረቡት ውስጥ መኖሪያ ቤቱንና ካዝናው ከጋብቻ በፊት የተፈሩ መሆናቸውን ገልጸው የግሌ ናቸው ያሉ ሲሆን ሌሎችን የጋራ መሆናቸውን አምነው መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች ተጠሪ የግሌ ናቸው በማለት የጠቀሷቸው ንብረቶች ግራ ቀኙ ሐምሌ 23 ቀን 1997 ዓ/ም ባደረጉት የጋብቻ ውል ሀብትሽ በሃብቴና ከወለደች የግል የለባትም በማለት መስማማታቸውን ገልጸው ንብረቶች የጋራ ናቸው ሲሉ ተከራክሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የጋብቻ ውሉ ይዘት አመልካች "ከወለደች የግል የለባትም" የሚል ሐረግ መያዙ ንብረቶቹን የጋራ ሊያደርግ የማይችል መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም የክፍሉን ማዘጋጃ ቤት ጠይቆ አከራካሪው ቤት በ1995 ዓ/ም መሰራቱን ያረጋገጠ ሲሆን የጋብቻ ውሉን ይዘትና መንፈስ ለመረዳት ደግሞ በውሉ ያሉትን የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከተሰሙት ሶስቱ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ከጋብቻ በፊት የተፈራውን ንብረት የማይመለከት መሆኑን የሚያሳይ ስለመሆኑ ጠቅሶ በጋብቻ ውሉ ላይ አመልካች "ከወለደች የግል የለባትም" የሚለው ሐረግ ቤቱ

ከጋብቻ በፊት የተፈራ የተጠሪ የግል ንብረት በመሆኑ ለአመልካች ተጠሪ የሚያካፍልበት ምክንያት የለም ሲል በዚህ ንብረት ላይ የቀረበውን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ካዝናውንና ሌሎች ንብረቶችን የጋራ ናቸው በማለት ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ የወሰነ ሲሆን የልጅ ቀለብን በተመለከተም ተጠሪ በየወሩ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የወረዳው ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ያለመሆኑን ምክንያቱን ዘርዝሮ ያጸናው ሲሆን የልጁን ቀለብ በተመለከተ ግን መጠኑ ያነሰ መሆኑን ገልፆ ተጠሪ በየወሩ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ከዚህም በኋላ አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል "ሀብትሽ ሀብቴ ነው አመልካች ከወለደች የግል የለባትም" ተብሎ የተቀመጠው ሐረግ ከጋብቻው በፊት የተፈራውን የተጠሪን ንብረት የጋራ ለማድረግ ታስቦ የገባ ሁኖ እያለ በውሉ ላይ ያለው ይኼው ሐረግ ከጋብቻ በኋላ የሚገኘውን ንብረት የጋራ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች መተርጎሙ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት የጋራ ስለመሆኑ ሕጉ ጥበቃ ያደረገውን መብት ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ በ18/08/95 ዓ.ም በተደረገ የፍቺ ስምምነት አንጻር ሊፈጸም የሚገባው እንጂ ዳግም ዳኝነት የሚጠየቅበት አይደለም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 1997 ዓ/ም ባደረጉት የጋብቻ ውል "ሀብትሽ ሀብቴ ነው አመልካች ከወለደች የግል የለባትም" የሚል ሐረግ አስገብተው ስምምነት መደረጉን፣ ጋብቻው በዚህ እለት ተፈጽሞም አመልካችና ተጠሪ አንድ ላይ ሲኖሩ አመልካች አንድ ልጅ ለተጠሪ የወለደችላቸው መሆኑን፣ ተጠሪ ቤቱን ከጋብቻ በፊት ያፈሩት መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን፣አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይም የጋብቻ ውሉ ላይ " ከወለደች የግል የለባትም" ተብሎ የተቀመጠው ሐረግ አመልካች

ለተጠሪ ልጅ ስለወለዱላቸው ከጋብቻ በፊት የተፈሩ ንብረቶችን የጋራ የማድረግ ውጤት ያለው መሆን ያለመሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኃላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው የሚያገኟቸው ንብረቶች በጋብቻ ዘመንም የግል ሆነው እንደሚቀሩ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 68(1) በግልጽ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ንብረቶቹ በጋብቻ ውል የጋራ እንደሆኑ ስምምነት ከሌለ ብቻ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የጋብቻ ውል ስምምነት "ሀብትሽ ሀብቴ ነው ልጅ ከወለደች የግል የለባትም" የሚል ሐረግ የያዘ ነው፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ጋር በዚህ መልኩ ያደረጉት የጋብቻ ውል ስምምነት ውጤቱ ከጋብቻ በኂላ የሚፈሩትን ንብረቶች የጋራ የሚያደርግ ነው ይበሉ እንጂ የውሉ ይዘትና መንፈስ እንደ አመልካች ክርክር ነው እንዳይባል የቤተሰብ ሕጉ ባልና ሚስት ንብረታቸውንና የግል ግንኙነታችን በተመለከተ የሚያደርጓቸው ስምምነቶች በህጉ በአስገዳጅነት የተቀመጡ ድንጋጌዎችን በሚፃረር መልኩ ሊሆን አይገባም ተብሎ በሕጉ ከተቀመጠው ድንጋጌ ጋር አብሮ የማይሄድ ነው፡፡ ሕጉ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረትን በተመለከተ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በሚል በአስገዳጅ መልኩ ደንግጓልና፡፡ በመሆኑም በሕጉ ጥበቃ በተደረገው መብት ላይ የጋብቻ ውል ስምምነት ሕጉን በሚፃረር መልኩ ማድረግ በሕጉ የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር የውል ስምምነቱ በግልፅ በጋብቻ በፊት በተፈሩት ንብረቶች ላይ መደረጉን የሚያሳይ መሆኑን ከግራ ቀኙ ስምምነት ይዘት፣ የቤተሰብ ሕጉ በጋብቻ ጊዜ ስለሚፈሩ ንብረቶች ከአደረገው ጥብቃና ከውል ሕግ የአተረጓጎም ደንቦች መንፈስ የምንረዳው ነጥብ ነው፡፡ የጋብቻ ውል ስምምነት ይዘት ትርጉም አከራካሪ ከሆነ ስምምነቱ የግራቀኙን የንብረትን መብት የሚገዛ እንደመሆኑ መጠን ከውል አይነቶች አንዱ ሊባል የሚችል ስለሆነና አተረጓጎምን በተመለከተ ልንከተለው የሚገባ ደንብ በቤተሰብ ሕጉ በግልፅ የተቀመጠ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677/1/ ድንጋጌ መሠረት በጠቅላላ ውል ስለውሎች አተረጓጎም የተቀመጡትን ደንቦች ማለትም ከፍ/ሕ/ቁጥር 1731 እና ተከታዩቹን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የግራቀኙ ሐሳብና ፍላጐት ምን እንደነበር መመርመር የግድ የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ በውል ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ድንጋጌዎች ግልጽ ባልሆኑ ጊዜ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1732፣ 1735-1738 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር በሰፈሩት ደንቦች መሠረት መተርጎም የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ደንቦች በፍ/ሕ/ቁጥር 1734 እና 1736 ሲሆኑ ተዋዋዩች ውላቸውን ከመዋዋላቸው አስቀድሞ ወይም ከተዋዋሉ በኃላ የነበሩበትን ሁኔታዎች የፈጸሙትን ተግባር በማመዛዘንና ሐሳባቸው ምን

እንደነበር ለማወቅ መሞከር እና የውሎችን ቃሎች አንዱን ከአንዱ ጋር እያዛመዱ በመመልከት ለውሉ ጉዳይ አግባብ ያለውን ትርጉም በመስጠት አዎንታዊ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ በ23/11/1997 ዓ.ም አደረግን የሚሉት የጋብቻ ውል ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተፈራ የተጠሪ የግል ንብረት መሆኑን ተጠሪ እያወቁ አመልካች ጋር ሲጋቡ ግን "ሀብትሽ ሀብቴ ነው ልጅ ከወለደች የግል የለባትም" በማለት ስምምነት ማድረጋቸው አስቀድሞም ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት የግል ስለመሆኑ በህግ የተጠበቀላቸውን መብት በመተው አመልካች ልጅ እስከወለዱላቸው ድረስ የተጠሪን የግል ንብረት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ለማድረግ አምነው ልጅ ከማግኘት በመነጨው ፍላጐት የግል ንብረታቸውን የጋራ ለማድረግ ተስማምተዋል ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ አገላለፅ በጋብቻ ውሉ አመልካች ልጅ ከወለደች የግል የለባትም ተብሎ የተቀመጠው ሐረግ ሀብትሽ ሀብቴ ነው ከሚለው ሐረግ ጋር ተሳስሮ ሲታይ ግራቀኙ የነበራቸው ሀሳብ አመልካች ልጅ በመውለድ ሁኔታ ላይ የተገደበ ሁኖ ልጅ ከወለዱ ግን ከጋብቻ በፊት የተፈራ የተጠሪ የግል ሀብት የግላቸው ሁኖ የሚቀር ንብረት ስለመሆኑ የሚያሳይ ሳይሆን የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ስለመሆኑ መስማማታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ "ሐብትሽ ሀብቴ ነው" የሚለው የአማርኛ ሐረግም የሚታወቀው ተጋቢዎች በግል የነበራቸውን ሀብት የጋራ ለማድረግ በማሰብ የሚጠቀሙበት ስለመሆኑ ከነባራዊ ሁኔታ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ "ከወለደች የግል የለባትም" የሚለው ሐረግ በጋብቻ ጊዜ የሚፈራውን ንብረት የጋራ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ ነው እንዳይባል በጋብቻ ወቅት የሚፈሩ ንብረቶቹን ሕጉ የጋራ ስለመሆናቸው በአስገዳጅ ሁኔታ የደነገ በመሆኑ የጋብቻ ውል ሲደረግ ይኼው በሕጉ አስቀድሞ በአስገዳጅ ሁኔታ ጥበቃ ያገኘ ጉዳይ በስምምነት ውስጥ የሚካተትበት አግባብና በህግ ጥበቃ የሚያገኝበት ምክንያት አይኖርም፡፡ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ያፈሯቸው ንብረቶች የግላቸው ሁነው የሚቀጥሉ መሆኑም በሕጉ የተደነገ በመሆኑ ይህንኑ በህግ ጥበቃ ያገኘ መብት መኖሩን እያወቁና ውጤቱን እየተረዱ የጋብቻ ውል ስምምነቱ ሲደረግ "ሀብትሽ ሀብቴ ነው" "ከወለደች የግል የለባትም" የሚሉትን ሐረጋትን በስምምነቱ እንዲገቡ ያደርጋሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡

ሲጠቃለልም ስምምነቱ መኖሩ ግራ ቀኙን ያላከራከረና ይዘቱም አንዱ ሀረግ ከአንዱ ጋር ተሳስሮ ሲታይ ከጋብቻ በፊት የተፈሩ ንብረቶችን የጋራ የሚያደርግ መሆኑን የሚያሳይ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ስምምነቱ በጋብቻ ውስጥ ለተፈራ ንብረት ተፈፃሚነት ያለው እንጂ ከጋብቻ በፊት ለተገኘ ንብረት አይደለም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አከራካሪውን ቤት አስመልክቶ በበረኸት ወረዳ ፍ/ር/ቤት በመ/ቁጥር 01316/05 ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0113001 ጥር 09 ቀን 2006 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 030-4591 የካቲት 19 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት "በድምፅ ብልጫ" ተሽሯል፡፡

2. አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 1997 ዓ/ም ባደረጉት የጋብቻ ውል አመልካች "ከወለደች የግል የለባትም" በማለት ያስቀመጡት የውሉ ሐረግ በውሉ ሀብትሽ ሀብቴ ነው ተብሎ ከተቀመጠው የውሉ ሀረግ ጋር ተሳስሮ ሲታይ አመልካች ለተጠሪ ልጅ ከወለዱ ከጋብቻ በፊት በነበረው የተጠሪ የግል ንብረት ላይ የጋራ ባለሃብት እንዲሆኑ በማስብ ያስቀመጡት ነው በማለት አመልካችና ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን ቤት እኩል ሊካፈሉ ይገባል፣ ክፍፍሉም በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በተቀመጠው ስርዓት ሊሆን ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ በሌሎች ንብረቶች በወረዳው ፍርድ ቤት፣ ስለ ልጅ ቀለብ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች አልተነኩም፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

## የሀሳብ ልዩነት

እኔ በሁለተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተገለፀው ዳኛ አመልካች እና ተጠሪ ያደረጉት የጋብቻ ውልና የተሰሙት ምስክሮች ቃል የጋብቻ ውላቸው አመልካች ልጅ ከወለደች ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ያፈራውን የግል ንብረቱን የጋራ ሀብት እንዲሆን የተስማማ መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ አይደለም ፡፡ የጋብቻ ውሉ የተጠሪን ግልፅ ስምምነት የማያሣይ ከሆነ ፤የጋብቻ ውሉ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1738 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በማድረግ ባለዕዳውን የተጠሪን በሚጠቅም መንገድ መተርጎም ይኖርበታል ብዬ ስለማስብ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

**የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ. 101552

ሰኔ 01 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ትርንጎ መኮንን - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሙሉጌታ መኳንንት - ታልፏል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ክርክር ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ እንዲፈርስ በፍርድ ቤቱ ከተወሰነ በኂላ አመልካች ጥር 18 ቀን 2001 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 553/ለ/ የሆነና በተጠሪ ስም የተመዘገበ ቤት፣ በተጠሪ ስም የተመዘገበና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-205229 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ፣ በተጠሪ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀመጠ ጥሬ ገንዘብ፣ የቤት ቁሳቁሶች /ሙሉ ሶፋ፣ ኮንትሮል ቡፌ፣ ፍሪጅ፣ አንድ ዘመናዊ አልጋ፣ ባለቀለም ቴሌቪዥን ከእነ ዴኩ/፣ 35 ግራም የአንገት ሃብል በተጠሪ እጅ የሚገኝና ከወላጆች በውርስ ያገኙት ብር 40,000.00 /አርባ ሺህ/ በተጠሪ እጅ የሚገኘው ንብረቶችን ዘርዝረው የጋራ የሆኑትን ቤት፣ መኪና፣ባንክ ውስጥ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብና የቤት ቁሳቁሶችን እንዲያካፍሏቸው፣ የግል የሆኑትና 35 ግራም ወርቅና 40,000.00 ጥሬ ገንዘብ ደግሞ ተጠሪ እንዲመልስላቸው እና ካሳም እንዲከፈል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ቤቱ የጋራ መሆኑን፣ መኪናውን አሰርተው ለጋራ እዳ መክፈያነት የሸጡ መሆኑን፣ ባንክ ውስጥ ያለው ገንዘብ 320.667 መሆኑን፣ የቤት ቁሳቁሶች

በአመልካች እጅ እንደሚገኙ፣ 35 ግራም ወርቅና ብር 40,000.00 በተመለከተ ግን የሚያውቁት ነገር የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ስለመኪናው ተገቢውን አካል ጠይቆ ማስረጃ እንዲቀርብለት ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ቤቱን በተመለከተ አመልካች ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት አመልካች ልጆችን ይዛ እንድትጠቀምበት እና በኋላ ለልጆቻችን እንዲተላለፍ ተስማምተናል ቢሉም ስምምነቱ የቴምበር ቀረጥ ያልተከፈለበትና ፈቃደኝነታቸውን የገለፁበት ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ግራቀኙ እኩል እንዲካፈሉ፣ የቤት ቁሳቁሶችንም ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በማለት የወሰነ ሲሆን መኪናው የግራ ቀኙ ጋብቻ ጸንቶ ባለበት ጊዜ የተሸጠና በሌላ ሰው ስም የሚገኝ መሆኑ መረጋገጡን፣ የካሳ ጥያቄ ፍቺ ሲወሰን ያልቀረበ የዳኝነት ጥያቄ መሆኑን፣ ወርቅና የውርስ የተባለውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ ያለመኖሩን ጠቅሶ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የልጅ ቀለብን በተመለከተም ተጠሪ ሊቆርጡ የሚገባውን ቀድሞ ወስኖና ተጠሪ ስራ በማቋረጣቸው ምክንያት ቀለብ የመቁረጥ ግዴታ ቀሪ እንዲሆንላቸው ቢያመለክቱም ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም፡፡ አመልካች ቤቱ ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በተወሰነውና መኪናውን፣ ወርቁንና የውርስ የተባለውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ መኪናው ላይ ብቻ የቀረበውን ቅሬታ በመቀበል መኪናው በብር 70,000.00 /ሰባ ሺህ/ የተሸጠ መሆኑ ቢረጋገጥም ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም እንዳልዋለ ተረጋግጧል፡፡ በሚል ምክንያት ተጠሪ ለአመልካች ብር 35,000.00 /ሰላሳ አምስት ሺህ/ እንዲተኩላቸው ሲል ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ቤቱ የጋራ ቢሆንም ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት አመልካች እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ ድረስ ተጠቅመው ከዚያ በኋላ ለጋራ ልጆቻችን እንዲተላለፍ ስምምነት ተደርጎ እያለ መታለፉ ያላግባብ ነው፣ ካሳውን በተመለከተም ተጠሪ በሴሰኝነት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ መባላቸው ተረጋግጦ እያለ በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 84 መሰረት ካሳ እንዲከፈል የቀረበው ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሁለቱም ነጥቦች ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ይዘት ተገቢነት በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በሕግ አግባብ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በመኖሪያ ቤቱና ካሳን አስመልክቶ በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው የውሳኔ ክፍል

መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በሕጋዊ ጋብቻ ተሳስረው ቆይተው ጋብቻው በፍቺው ውሳኔ ታህሳስ 24 ቀን 2001 ዓ/ም መፍረሱን፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 553/ለ የሆነና በተጠሪ ስም የተመዘገበ ቤት የጋብቻ ውጤት መሆኑ ተረጋግጦ የግራ ቀኙ ነው ተብሎ የተወሰነ ሲሆን አሁን አመልካች ቅሬታ የሚያቀርቡት ቤቱ የጋራ ቢሆንም ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት አመልካች ቤቱን ልጆችን ይዘው እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ እንዲጠቀሙበትና በኋላም ለልጆች እንዲተላለፍ የተደረገ ሁኖ እያለና ተጠሪም በዚህ ረገድ ሰነዱን በመካድ ያቀረበው ክርክር ሳይኖር በአመልካች በተጠሪ መካከል ክፍፍል እንዲደረግ ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን፣ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር ያለፉት ስምምነቱ የቀረጥ ቴምብር ያልተከፈለበትና በነጻ ፈቃዳቸው የተደረገ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው።

በመሰረቱ የተጋቢዎች የፍቺ ውጤቶች በስምምነት፣ በሽማግሌዎች ወይም ባለሙያዎች ሊወሰን እንደሚችልና በዚህ አግባብ የተወሰነ የፍቺ ውጤት ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ስለመሆኑ የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀጽ 77 እስከ 80 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 83/3/ ድንጋጌ በጣምራነት ሲነበቡ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው። በተያዘው ጉዳይ ተጋቢዎቹ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን መኖሪያ ቤት በተመለከተ ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም ስምምነት ያደረጉ መሆኑን አመልካች ቢከራከሩም የፍቺ ውሳኔ በ24/04/2001 ዓ/ም ከተሰጠ በኋላ የተደረገና ስምምነቱ ፍርድ ቤት ቀርቦ ያልጸደቀ፣ ይህን የንብረት ክፍፍል ስምምነት አስመልክቶ በግልጽ ፈቃዳቸውን ሰጥተው ስለመስማማታቸው ያልተረጋገጠ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው። ተጠሪም በስር ፍርድ ቤት የክፍፍል ጊዜ ቤቱ የጋራ መሆኑን ጠቅሰው ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት የጠየቁበት ከመሆኑም በላይ በይግባኝ ደረጃም በቤቱ ላይ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ክፍል ተገቢ ነው በማለት ሲከራከሩ የነበሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል። ስለሆነም አመልካች አለ የሚሉት ሰነድ በፍርድ ቤት ያልጸደቀና የግራ ቀኙን ፈቃዳቸው መኖሩ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ቤቱን አስመልክተው የሚያቀርቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ አግባብ አላገኘንም።

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚራከሩት የካሳ ጥያቄ መታለፉ ያላግባብ ነው በሚል ነው። የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ያለፉት አመልካች የፍቺ ውሳኔ

እንዲሰጣቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ይህንኑ አልገለፁም በሚል ነው፡፡ በእርግጥም አመልካች የፍቺ ጥያቄ ሲያቀርቡ የካሳ ጥያቄ አላቀረቡም፡፡ ሆኖም ሕጉ የፍቺ ጥያቄ ሲቀርብ ለፍቺ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ መግለፅ የሌለባቸው መሆኑን በአንቀጽ 81/2/ ስር የተደነገገ ቢሆንም ካሳውን ግን በንብረት ክፍፍል ጊዜ ዳኝነት ሊያቀርቡ የሚችሉ መሆኑን ይህንኑ ድንጋጌ ከአንቀጽ 84 ጋር አገናዝበን ስንመለከተው የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ለፍቺ ምክንያት የሆነውን በደል ለፍቺ ምክንያትነት መጥቀስ በሕጉ ግዴታ ያልተጣለባቸው ቢሆንም ካሳ የሚወሰነው ለፍትህ አስፈላጊ ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲያምንበት መሆኑን አንቀጽ 84 በግልጽ ስለሚደነግግና የበታች ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ ካሳ መወሰኑ ለፍትህ አስፈላጊ መሆኑን ያላመኑበት መሆኑን በተለይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ የገለፀ ስለሆነ በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ከአንቀፁ አቀራረፅና ይዘት አንጻር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 64612 ታህሳስ 26 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 119293 ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ/ም ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/አ**

የሰ/መ/ቁ.99954

ሰኔ 5 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** 1. የህፃን ዘውዱ ወ/ሚካኤል
2. የህፃን አስቴር ወ/ሚካኤል
3. የህፃን አስንቀ ወ/ሚካኤል
4. የህፃን እመቤት ወ/ሚካኤል
5. የህፃን ሰላም ከልሴ ሞግዝት ወ/ሮ አስናቀች አሰፋ

} ጠበቃ አቶ ዘውዱ ከበደ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዝናየ ወ/ሚካኤል - ጠበቃ ደምሰው ዘገየ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 178480 ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 117887 ጥር 23 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዮ ከህጋዊ ጋብቻ የተወለድኩ የሟች ወልደሚካኤል ታረቀኝ ልጅ መሆኔ በፍርድ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ በማለት የቀረበን ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ /አመልካች/ተጠሪዎች ተከሳሽ /ተቃዋሚ/ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም ፅፎ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ አባታቸው አቶ ወልደሚካኤል ታረቀኝና እናታቸው ወ/ሮ እቴነሽ ወ/ፃድቅ ሚያዝያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም የጋብቻ ሥርዓታቸውን ፈፅመው በትዳር ተሣስረው አብረው እየኖሩ እያለ መጋቢት 7 ቀን 1972 ዓ.ም ተወልጃለሁ፡፡ ስለዚህ የአቶ ወልደ ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ መሆኔ ይወሰንልኝ የሚል የዳኝነት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ተጠሪዎች በተከሳሽነት ቀርበው ሟችና የከሳሽ እናት ሚያዝያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም አድርገውታል

ተብሎ በቀረበው የጋብቻ ውል ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የሚች ፊርማ መሆኑን ስለምንክድ ይመርመርልን ፡፡የአርሲ ነገሌ ማዘጋጀ ቤት ከሳሽ የሚች ልጅ መሆናቸውን በመግለፅ የሰጠው የልደት ማስረጃ ተገቢነት የለውም፡፡ከሳሽ በጋብቻ ውሉ ስማቸው ያልተጠቀሱ ሰዎች በምስክርነት መቁጠሩ ተገቢ አይደለም፡፡የኦርቶዶክስ ቤቴክርስቲያን ስለከሳሽ ልደትና ጥምቀት የሰጠችው ማስረጃ ተገቢነት የለውም በማለት ከሳሽ/ተጠሪ/ የሚች ልጅ አለመሆኑንና ሚች ልጅ የሌላቸው መሆኑን ገልፀው ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ የሚያሳይ እንደሆነ በማንሳት ተከራክረዋል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ህጋዊ ጋብቻ የተወለደ የሚች ወ/ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት ወላጅ እናቱንና ወ/ሮ እቴነሽ የተባሉ ሴት በምስክርነት አቅርቦ አሰምቷል ተጠሪዎች ምስክሮቻቸውን ባለማቅረባቸው ምስክር የማሰማት መብታቸውን በማለፍ፣የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረና ከመዘነ በኃላ በጋብቻ ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የሚች ወልደሚካኤል መሆኑን በፎረንሲክ ለማስመርመር በቂና አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤቴክርስቲያን ስለ ከሳሽ ልደት ፣ጥምቀት የሰጠው ማስረጃና የአርሲ ነገሌ ማዘጋጃ ቤት የሰጠው የልደት ማስረጃ ተዓማኒነት ያላቸውና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ናቸው፡፡የከሳሽ እናትና አባት ከሚያዝያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1978 በጋብቻ ተሳስረው መኖራቸውና ከሳሽ አባትና እናቱ በፀና ጋብቻ በነበሩበት ወቅት መጋቢት 2 ቀን 1972 ዓ.ም የተወለደ በመሆኑ የሚች ወልደሚካኤል ታረቀኝ ልጅ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል ፡፡

3. በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካችዎች ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ተጠሪ /መልስ ሰጭ/ መልስ እንዲሰጡ ካደረገና የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የጋብቻ ውሉ ሲፈረም ምስክር የነበሩ ሰዎች እንዲቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቶ፣ምስክሮቹ በሞት የተለዩ በመሆኑ ስለተገለፀለት ለሎች ጋብቻቸው ሥርዓት ላይ ነበሩ የተባሉ ምስክሮች ቃልና የተጠሪን ወላጅ እናት የምስክርነት ቃል በድጋሚ ሰምቷል፡፡ወ/ሮ ጥጋብነሽ ሙላቱ የተባሉ ሴት ሚችና የተጠሪ ወላጅ እናት የጋብቻ ሥርዓት ሲፈፅሙ እንደነበሩና ተጠሪ ጋብቻው ከተፈፀመ በኃላ መወለዱን እንደመሠከሩ ሁለተኛው ተጨማሪ ምስክር ሆነው የተሰጡት አቶ የማታው ወርቁ የሚች አክስትና የልጅ ልጅ መሆናቸውን ገልፀው ሚች የተጠሪን እናት በደብረብርሃን ከተማ እንዳገባቸውና ተጠሪን እንደወለዱ የነገሯቸው መሆኑን ገልፀው መስክረዋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡ ማስረጃዎችና በትዕዛዝ አስቀርቦ የሰማቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች ቃል ከመዘነ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሚች ወ/ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

4. አመልካቾች 12/07/2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ሚች ልጅ የሌላቸው መሆኑን በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት ግልፅ ኑዛዜ አድርገዋል፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች በጋብቻ ውሉ ላይ ያሉው ፊርማ እንዲመረመር ያቀረብነውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግና ሌሎች አግባብነት የሌለባቸውን ከኦርቶዶክስ ቤቴክርስቲያን እና ሌሎች ማስረጃዎች በመቀበል የDNA /ዲኤንኤ/ ምርመራ ሳይደረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 13 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሚች በጋብቻ የወለደው ልጅ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ ልጅነቱን ያስረዳ መሆኑን ገልፃ አመልካችዎች ያቀረቡት የፊርማና ዲኤንኤ ይመርመርልን ክርክር የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካችዎች ሰኔ 26 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ከዚህ በፊት ተስፋዬ ወልደሚካኤል የተባለ የሚች ልጅ መሆኑን ገልፆ የልጅነት ክስ አቅርቦ ይኸ ሰበር ችሎት የሚች ልጅ ነው በማለት ወስኗል፡፡ሚች በአንድ ከተማ ውስጥ ሁለት ሴቶችን አግብቶ በተመሣሣይ ጊዜ የሁለት ልጅ አባት የሚሆንበት አጋጣሚ የተጠሪን ጥያቄ እጅግ አጠራጣሪ የሚያደርገው በመሆኑ ዲ.ኤን.ኤ ሊመረመር ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡
5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ የሚች አቶ ወ/ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ሕግን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመያዝ ጉዳዩን ምርምረናል፡፡
6. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የተወለደው አባቱ አቶ ወልደሚካኤል ታረቀኝና እናቱ ወ/ሮ እቴነሽ ወ/ፃድቅ ሚያዚያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም የጋብቻ ሥርዓታቸውን ፈፅመው በጋብቻ ተሣስረው በሚኖሩበት ወቅት መሆኑ ነው ተጠሪ ባቀረባቸው ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑ ለፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡የጋብቻ ሥርዓቱ ለሕዝብ ይፋ በሆነበት ፣የአካባቢው ነዋሪዎች በተጋበዙበትና በተሳተፉበት ሁኔታ የተከናወነ መሆኑን በተጠሪ እናትና አባት የሠርግ ሥርዓት ላይ የተገኙትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረባቸው ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ የተጠሪ ወላጅ እናት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የምስክርነት ቃልና ሌሎች ደጋፊ የሰነድ ማስረጃዎች የተጠሪ ወላጅ እናትና አባት ሚያዚያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም የጋብቻ ሥርዓታቸውን ፈፅመው እስከ 1978 ዓ.ም ድረስ በጋብቻ ተሣስረው እንደኖሩ ተጠሪ መጋቢት 12 ቀን 1972 ዓ.ም የተወለደ መሆኑና እናቱና አባቱ የሚከተሉት የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ቀኖና በሚያዘው መሠረት በአርባ ቀኑ የጥምቀት ሥርዓት የተከናወነበት መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡የተጠሪ እናትና አባት የጋብቻ ውል ሲዋዋሉ ምስክር የነበሩት ሰዎችን በሕይወት የሌሉ በመሆናቸው የምስክርነት ቃላቸውን ለመቀበል

ያልተቻለ ቢሆንም በጋብቻ ሥርዓት ላይ የነበሩ ሰዎችም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰማ በመሆኑ አመልካችዎች በጋብቻ ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የሟች መሆኑ በፎርንሲክ አልተረጋገጠም በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

7. ተጠሪ የተወለደው አባቱና እናቱ በጋብቻ ተሣስረው በሚኖሩበት ጊዜ ውስጥ መሆኑ ከተረጋገጠ፣የተጠሪ አባት ተጠሪ ሲወለድ ከተጠሪ እናት ጋር በጋብቻ ተሣስሮ ሲኖሩ የነበሩት አቶ ወልደሚካኤል ታረቀኝ ናቸው ብሎ ሕግ ግምት የሚወስድ መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀፅ 741 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ የሟች ልጅ ነው የሚለውን የህጉን ግምት ለማስተባበል የሚቻለው ሟች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት ባደረገው ግልፅ ኑዛዝ እኔ ከአብራኬ የወጣ ልጅ የለኝም በማለት ያደረገውን ግልጽ ኑዛዜ ሣይሆን፣በወቅቱ ሥራ ላይ በነበረው የፍትሐ ብሔር ሕግ 682 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እና በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 167 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት የመካድ ክስ በማቅረብ ተጠሪ የሟች ወ/ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ አለመሆኑን በፍርድ በማስወሰን ነው ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ የሟች ልጅ አለመሆኑ እንዲወሰንለት ሟች ወይም የመካድ ክስ እንዲያቀርቡ በሕግ የተፈቀደላቸው የሟች የቅርብ ዘመዶች ለፍርድ ቤት አቅርበው የተወሰነ ውሣኔ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ የሟች ልጅ መሆኑን በሕግ ግምት የተረጋገጠው ልጅነት ከአብራኬ የወጣ ልጅ የለኝም ብሎ የኑዛዜ ቃል ተናዝዞ በመሞቱ ብቻ የሚስተባበል አይደለም፡፡

8. ከዚህ አንፃር ሲታይ ይኸ የአመልካችዎች መከራከሪያ የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑና አንድ ሰው በኑዛዜ የሚፈፅማቸው ተግባራት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 909 የተደነገጉ በመሆናቸው የአመልካችዎችን መከራከሪያ አልተቀበልነውም፡፡

9. አመልካዎች በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት የመልስ መልስ በመዝገብ ቁጥር 95410 አቶ ተስፋዬ ወልዴሚካኤል የተባለ ሰው የተሰጠን ውሣኔ በማንሣት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችዎች በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ይህንን ፍሬ ነገር መከራከሪያ አድርገው ያላቀረቡትና በማስረጃ ያላረጋገጡት አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329/1/ መሠረት አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የሟች ወልደሚካኤል ታረቀኝ በህጋዊ ጋብቻ የተወለደ ልጅ ነው በማለት አግባብነት ያለውን የቤተሠብ ሕግ ድንጋጌ የሕግ ግምት መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

**መ/ብ**

የሰ/መ/ቁ. 100426

ሰኔ 17 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካቾች፡-** 1ኛ ዶ/ር ጥላሁን ኪሮስ } ጠበቃ ፅጌ ሐዋስ ቀረቡ

2ኛ አቶ ሐዱሽ ኪሮስ

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ ህፃን ሰናይ የማነ ኪሮስ

2ኛ ህፃን ፍዩሪ የማነ ኪሮስ } ሞግዚት ወ/ሮ ሄለን ያቆብ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉደዩ የውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ የመንግስት የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች ተከሳሾች ተጠሪዎች ከሳሾች በመሆን ነው የተከራከሩት፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ የሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን የሚለውን ክርክር አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት ወላጅ አባታቸው አቶ የማነ ኪሮስ በ17/01/1996 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩ ሟች አባታቸው ከወላጅ እናታቸው ወ/ሮ ደስታ ረታን ተክተው ከእህት ወንድሞቻቸው የወረሱት ቤትና ቦታ አዋሳኙ በምስራቅ አቶ በላይ አርአያ በሰሜን ወ/ሮ ኪሮስ ታደሰና ወ/ሮ በላይነሽ ታረቀ፣ በምእራብ መንገድ፣ በደቡብ መንገድ የሚዋሰን ስፋቱ 333 ካሬ ሜትር ተከፍሎ እንዲሰጣቸው የማይካፈል ከሆነ በጨረታ ተሸጦ እንዲካፈሉ የሚጠይቅ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካቾች በተጠሪዎች ለቀረበው ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ዋናው ፍሬ ነገሩም፡፡ የተጠሪዎች ሞግዚት በስ/ፍ/መ/ቁ. 52/97 በ30/02/97 ዓ.ም ሞግዚትነት በፍርድ ቤት አጽድቀው ቤቱና ቦታው በሽማግሌ ወደ አንድ መቶ ሺህ ተገምቶ ከ1ኛ አመልካች ብር 25,000.00 /ሃያ አምስት ሽህ ብር / ተቀብለዋል፡፡ በውልና ማስረጃ በ06/01/1997 ዓ.ም ጽድቋል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ በዕርቅ እልባት አግኝቶ ያደረ መሆኑን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244/2//1/

መሠረት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ በተጠሪዎች ጠበቃ በሰጡት መልስም ዕርቁን ፈጽመዋል የተጠሪዎች ወ/ሮ ሄለን ያዕቀብ የፈፀሙት ዕርቅ በ6/01/97 ዓ.ም ነው፡፡ ሞግዚት ሆነው የተሾሙት በ30/02/97 ዓ.ም በመሆኑ ዕርቁን በፈፀመበት ወቅት ሕጋዊ ተግባር ለመፈፀም መብት አልነበራቸውም ሞግዚቱ ሳይሾም ሕጋዊ ተግባር መፈፀም ስለማይችሉ እርቁ ከሕግ ውጭ ነው፡፡ ዕርቅ የመፈፀም ሥልጣን አላቸው ቢባል እንኳ አንድ ሞግዚት ከ300 ብር በላይ በሆነው የንብረት ጥቅም ላይ ስለህፃን ሆኖ መዋዋል አይችልም፡፡ የፍ/ሕ/ቁ. 301 እና 3707 ጋር የሚቃረን ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ አመልካቾች እና የተጠሪዎች ሞግዚት በሽማግሌዎች በ6/01/97 ዓ.ም ባደረጉት ስምምነት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የ4 ወራሾች የነበረ በዘመድ ሽማግሌ ብር 100,000.00 ተገምቶ የከሳሾች ሞግዚት የአመልካች ድርሻ 25,000.00 በተጠሪዎች ስም ተቀብለው ለወደፊቱ ምንም ዓይነት መብት እንደሌላቸው በሽማግሌዎች ፊት ተስማምተው ፈርመው በመቀሌ ከተማ ውልና ማስረጃ ቀርቦ ለህግና ሞራል ሰለማይቃረን ፀድቋል የተጠሪዎች ሞግዚት ከዚህ በኃላ በ30/02/97 ዓ.ም ሞግዚትነት አረጋግጠዋል በ6/01/97 ዓ.ም የተደረገው ስምምነት ለህግና ለሞራል ይቃረናል ተብሎ እንዲፈርስ የቀረበ ጥያቄ የለም፡፡ የተጠሪ ልጆች እናት ባለቤታቸው እንደሞቱ በሕግ እንደ ሞግዚት ነው የምትቆጠረው በፍ/ህ/ቁ.205 በተሰጣቸው ስልጣን የአውራሻቸው የውርስ ሀብት እንደምትቀበል በፍ/ህ/ቁ.298 ተመልክቷል፡፡ በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈፀመ ጉዳይ ደግሞ ለክርክር መነሻ ሊሆን ስለማይችል ክሱ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2//ረ/ መሠረት በዕርቅ እልባት አግኝቶ ያደረ ነው ፡፡ በማለት ክሱ በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ወ/ሮ ሄለን ያዕቆብ ዕርቅ የፈፀሙት በ06/01/07 ዓ.ም ሲሆን ሞግዚት ሆነው የተሾሙት ደግሞ በ30/02/97 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ በሞግዚትነት ስልጣን ከመውሰዳቸው በፊት እርቁን መፈፀማቸው ነው፡፡ የተጠሪዎች እናት በፍ/ህ/ቁ.205 በህግ ሞግዚቶች እንደሆኑ ይሁን እንጂ የተጠሪዎች የውርስ ሀብቱ አስመልክተው ዕርቅ ለማድረግ የቤተዘመድ ጉባኤ የሰጣቸው ስልጣን የለም፡፡ የቤተዘመድ ጉባኤ ሥልጣን ቢሰጣቸው እንኳን ከብር 300 በላይ ከህፃናቱ ጥቅም ጋር በተያያዘ ክርክር ውስጥ ከገባ በሽምግልና መስማማት እንደማይችሉ በፍ/ሕ/ቁ.301 በአስገዳጅነት መልኩ ተቀምጠዋል፡፡ ወ/ሮ ሄለን ያዕቆብ የፈፀሙት ስምምነት መጠኑ ብር 25,000.00 ነው ይህ የሚያሳየው ደግሞ ወ/ሮ ሄለን ያዕቆብ ከስልጣናቸው ውጭ የተጠሪዎች የውርስ ሁብት ስምምነት እንደፈጽሙ ነው፡፡ ወ/ሮ ሄለን ያዕቆብ ፈጽሙት የተባለው የሽምግልና ስምምነት ከሥልጣናቸው ውጭ በቤተዘመድ ጉባኤ ባልተፈቀደላቸው ነው፡፡ ባልተሰጣቸው ስልጣን ለፈጸሙት ስምምነት ደግሞ ውጭ ተጠሪዎች / ህፃናት / ስምምነቱ ይፍረስልን ብለው አስቀድመው የሚጠይቁበት ምክንያት የለም፡፡ ስምምነቱ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠው የህፃናት መብት የሚጋፋ ፈራሽ ነው፡፡ ስምምነቱ ፈራሽ ነው፡፡ ከተባለ ደግሞ ህፃናቱ ስምምነቱ ይፍረስልን የሚሉበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ አከራክሮ ውሳኔ ይስጥበት በማለት ብይኑ ለመሻር በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 በነጥብ ለሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ በጽሑፍ ክርክር አድርጓል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ያነሱዋቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች የተጠሪዎች እናት ሕጋዊ ሞግዚት ናቸው ስምምነቱም እንዲፈርስ ጥያቄ አልቀረበም ተጠሪዎች በሽማግሌዎች ግምት መሠረት ድርሻቸውን ወስደዋል የሚል ይዘት አለው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በግራ ቀኙ የዕርቅ ስምምነት ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም አለመጠናቀቁ የእርቅ ሰምምነቱም የህፃናት መብትና ጥቅም የሚጎዳ ስለመሆኑ የተጠሪዎች ሞግዚት ዕርቅ ለማድረግ የቤተሰብ ጉባኤ ፍቃድ አልሰጣቸውም ተጠሪዎች የጠየቁት ሀብት ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት መሆኑ በፍ/ህ/ቁ 205 መሠረት ከወላጆቹ አንዱ በማይኖርበት ወይም ችሎታ ባጣበት ወቅት የማሳደግ፣ የማስተማር፣ የመንከባከብና የማስተዳደር ስልጣን እንጂ ንብረት የማስተላለፍ ሀላፊነት እንደማይሰጠው በመጥቀስ መልስ አቅርበዋል የአመልካቾች የመልሰ መልስም የሰበር አቤቱታው የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ለማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመረውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚያስፈለገው ጭብጥ የሥር ፍርድ ቤቶች በተጠሪዎች ሞግዚት ተደረገ የተባለው የዕርቅ ስምምነት ከመሾማቸው በፊት የተደረገ በመሆኑ ተጠሪዎችን የሚያስገድዱ አይደለም በማለት መወሰናቸው በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክር ሂደቱ መረዳት እንደተቻለው አመልካቾች ከተጠሪዎች ሞግዚትነት ጋር ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት መስከረም 6 ቀን 1997 ዓ.ም ዕርቅ ስምምነት አድርገው በሽማግሌዎች ግምት መሠረት 25.00.00 ብር እንደወሰዱ እና ሌላ እንደማይጠይቁ መግለፃቸው፤ተጠሪ የሞግዚትነት ስልጣን የወሰዱትም ጥቅምት 30 ቀን 1997 ዓ.ም ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካቾች ተጠሪዎች ሞግዚት ያደረጉ ስምምነት ለህግና ሞራል የማይቃረን መሆኑን ተረጋግጦ በሚመለከተው አካል ቀርቦ መመዝገቡን ይከራከራሉ ተጠሪዎች በበኩላቸው ሞግዚቱ እንደገና ሞግዚቶቻቸው በቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ያልጸደቀ በመሆኑ አደረጉት የተባለው ዕርቅ እንደማያስገድዳቸውና የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለመሆኑ መከራከራቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው የተጠሪዎች ሞግዚት የሞግዚትነት ሥልጣን ከማግኘታቸው በፊት ከአመልካች ጋር ዕርቅ ማድረጋቸው ነው፡፡ በተጠሪዎች ሞግዚት የተደረገው ስምምነትም ለቤተዘመድ ምክር ጉባኤ አቅርቦ ስለመጽደቁም በአመልካቾቹ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ አመልካቾች ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩት በተጠሪዎች ሞግዚት የተደረገው ስምምነት ለህግና ለሞራል የሚቃረን አይደለም በሚል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዕርቅ ስምምነቱ እንዲፈርስ ክስ እንዳልቀረበ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ያቀረቡት ቅሬታ ያመለክታል፡፡ በመሠረቱ የልጅ አስተዳደግ እና ንብረት አስተዳደር ባልና ሚስት በጋብቻ ተሳስረው በሚኖርበት ጊዜ በጋራ እንደሚያከናውኑት በማንኛውም ምክንያት ከወላጆች አንዱ ተግባሩን ማከናወን ካልቻለ ሌላኛው ኃላፊነቱን እንደሚሸከም ከፍ/ህ/ቁ.204 እና 205 ጭምር ጥምርንባብ የምንረዳው ነው፡፡

ሞግዚት አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት በማስተዳደር ሥልጣን እንዳለው ከፍ/ህ/ቁ. 280 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ሞግዚቱ የልጅን ሀብት በሚያስተዳድሩበት ጊዜ እና ሁኔታ በፍ/ህ/ጉ የተመለከቱትን መሠረታዊ ድንጋጌዎች ባስከበረ መልኩ መሆን እንዳለበት ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት አላማና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የውርስ ሀብት ያገኘ እንደሆነ ሞግዚቱ ከቤተዘመድ ምክር አባሎች መካከል ምስክሮች ባሉበት

ንብረቱም የዋጋ ግምት መግለጫ ሊዘጋጅለት እንደሚገባ ልጅ ከውርስ ሀብት የሚደርሰው መጠን ጉድለት እንዳይኖርበት ሞግዚቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ልጅን ወክሎ እንደሚቀበል፣ ለአውራሽ ዕዳ የማይበቃ ካልሆነ በቀር አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ በውርስ የደረሰው ሀብቱ የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ካልተፈቀደለት በቀር ሞግዚቱ ለመተው እንደማይችል ከፍ/ህ/ቁ. 282/1/፣/2/ እና 298/1/ እና /2/ ጥምር ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ከላይ የተመለከተናቸው ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና አላማ መረዳት እንደተቻለው ሕግ አውጭው የህፃናት መብት በተመለከተ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረጉን የሚያሳይ መሆኑን ነው ከዚህ ጋር በተያያዘም ሞግዚቱ የልጅን መብትና ጥቅም በተመለከተ የሚያደርገው ሕጋዊ ግንኙነት የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፍቃድ የሚጠይቅ ስለመሆኑ ነው፡፡ የፍ/ህ/ቁ.301 ድንጋጌ ሙሉ ይዘቱ ሞግዚቱ ክርክር የሚደረግበት ጥቅም ከሦስት መቶ የኢትዮጵያ ብር ያነሰ ካልሆነ በቀር አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅሞች በሚመለከት ነገር ከቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ካልተፈቀደለት ምንም ግልግል ለመፈፀም አይችልም፡፡ በማለት ደንግጓል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪዎች ሞግዚት ለዕርቅ ስምምነት አድርጉ የተባለው በቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ከመሾማቸው በፊት ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ በአመልካቾች እና በተጠሪዎች ወኪል ተደረገ የተባለው የገንዘብ መጠንም ከ25,000.000 ብር ያላነሰ ነው፡፡ በአንጻሩ ሕግ አውጭው ሞግዚቱ ስለ ህፃኑ የሚያደርገው ግልግል ከ300.00 ብር በላይ ከሆነ የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ይሁንታ እንደ ቅድመ ሁኔታ መቀመጡን ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ በተያያዘው ጉዳዩ የተጠሪዎችም ሞግዚት ዕርቅ ለማድረግ ቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፋቃድ ስለማግኘታቸው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ነገር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የህፃናቱ መብትና ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ሞግዚቱ ከ3ኛ ወገን በሕጉ ከተፈቀደው ውጭ የመስማማት ሥልጣን አልተሰጠውም የተጠሪዎች ሞግዚት በሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጭ የተደረገ የቤተዘመዱ ምክር ጉባኤ ፍቃድ ሲያገኙ ተጠሪዎች ከአውራሻቸው የሚያገኙት የውርስ ሀብት ድርሻ በተመለከተ ያደረጉት ስምምነት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪዎችም በሞግዚታቸው የተደረገው ዕርቅ መጀመሪያ እንዲያፈርሱ የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች ከዚህ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት አለው በማለት የጠቀሱት አስገዳጅ የሰበር ውሳኔ ሰ/መ/ቁ. 43226 በክርክሩ ይዘት ባህሪ እና ለውሳኔ የተያዘው ጭብጥ ከዚህ ጉዳይ ጋር የሚዛመድ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ወረዳ እና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳዩ እንዲከራከሩ የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

- የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ. 61548 በ23/03/2006 የሥር የወረዳና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 96934 በ10/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጽንቷል፡፡
- የተጠሪዎች ሞግዚት ከአመልካች ጋር አደረጉት የተባለው ስምምነት የሞግዚትነት ሥልጣን ሳይሰጣቸው እና በቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፍቃድ ያላገኘ በመሆኑ በሕግ ፊት የሚጸና አይደለም ተብሎ በሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
- የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ ፍ/ቤት 03 ሰኔ 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

**ወ/ክ**

የሰ/መ/ቁ.94811

ሰኔ 15ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ታረቀኝ ጥሩነህ - የቀረበ የለም } በአካልም በV.C ም ከሀዋሳ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሰናይት ታደሰ - የቀረበየለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ የቀረበ የጋራ ንብረት ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በዚህ መዝገብ አከራካሪ ሆኖ ከቀረበው ጉዳይ መካከል በጭብጥነት የተያዘው ተጋቢዎቹ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት ነው የተባለ የአንድ ባጃጅ ተሽከርካሪ ጉዳይ እና ተጠሪዋ በ02/07/2004 ዓ.ም.ከባንክ ውጪ አድርገው መውሰዳቸው የተረጋገጠው የብር 34,000 (ሰላሳ አራት ሺህ) ጉዳይነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/ መንግስት በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ተከሳሽ በነበሩት በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ጋብቻቸው በተከሳሹ ጥፋት እና በካሳ ውሳኔ ጭምር የፈረሰ መሆኑን ገልጸው በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ ናቸው ያሏቸው የማይንቀሳቀስ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ለክሱ መልስ ከመስጠታቸው በተጨማሪ በተጠሪዋ እጅ የሚገኝ ነው ያሉት ጥሬ ገንዘብ በድርሻቸው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው የበኩላቸውን የዳኝነት ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ በመዝገብ ቁጥር 00906 በ05/09/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ የክፍያ ጥያቄ ለቀረበባቸው ንብረቶች ሁለት የተለያዩ ውሳኔዎችን ሰጥቷል፡፡ በአሁኗ ተጠሪ ጠያቂነት ውሳኔ ከተሰጠባቸው ንብረቶች መካከል ለሰበር ክርክሩ ለተያዘው ጭብጥ ምክንያት የሆነው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ የአሁኑ አመልካች ገዝተው ስመሀብቱን ሳያዛውሩ ሲሰሩበት ነበር የተባለው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 1-1420 ደሕ የሆነን ባጃጅ ተሽከርካሪ ሲሆን በአሁኑ አመልካች ጠያቂነት ውሳኔ ከተሰጠባቸው ንብረቶች መካከል ለሰበር ክርክሩ ለተያዘው ጭብጥ ምክንያት የሆነው ደግሞ

ተጠሪዋ በ02/07/2004ዓ.ም.ከአቢሲኒያ ባንክ ወጪ አድርገው መውሰዳቸው የተረጋገጠው የብር 34,000 (ሰላሳ አራት ሺህ) ጉዳይ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. አመልካች ገዝተው ስመ ሀብቱን ሳያዛውሩ ሲሰሩበት ነበር የተባለው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ1-1420 ደሕ የሆነው ባጃጅ ተሽከርካሪ የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
2. ተጠሪዋ በ02/07/2004 ዓ.ም. ከአቢሲኒያ ባንክ ወጪ አድርገው መውሰዳቸው የተረጋገጠው ብር 34,000 (ሰላሳ አራት ሺህ) ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠር ነው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ጋብቻው ጸንቶ በነበረበት ጊዜ አመልካች አንድ ባጃጅ ተሽከርካሪ ገዝተው ነገር ግን ስም ሳያዛውሩ ሲሰሩበት የነበረ ስለመሆኑ ገልጸው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ተጠሪዋ ላቀረቡት ክስ አመልካች ስለተባለው ባጃጅ ተሽከርካሪ የሚያውቁት ነገር አለመኖሩን እና ባጃጁ የተገዛበትን ውልም ሆነ በአመልካች ስም የተመዘገበበትን የባለቤትነት ማስረጃ ሳያቀርቡ ተጠሪ ያቀረቡት የድርሻ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ገልጸው በመሸሽ መልክ መልስ ከመስጠታቸው በቀር ባጃጅ ተሽከርካሪውን ያልገዙ እና ሲሰሩበትም ያልነበሩ ስለመሆኑ በግልጽ የሰጡት የማስተባበያ መልስ አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ባጃጁን በተመለከተ ተጠሪዋ ስለራሳቸው 1ኛ ምስክር በመሆን በሰጡት ምስክርነት አመልካች አንድ ባጃጅ ተሽከርካሪ ገዝተው ነገር ግን ስም ሳያዛውሩ ሲሰሩበት የነበረ ስለመሆኑ ገልጸው መመስከራቸውን ፤የተጠሪዋ 2ኛ ምስክር አመልካች ባጃጁን ሲገዙ እንዳላዩ፤ነገርግን ያሽከረክሩ እንደ ነበረ እና ያሳድሩ የነበረውም በግቢአቸው ውስጥ እንደሆነ በመግለጽ መመስከራቸውን እና የተጠሪዋ 3ኛ ምስክር ደግሞ አመልካቹ ባጃጁን ያሽከረክሩ እና በቤታቸው ያሳድሩ የነበረ ከመሆኑ በተጨማሪ ባጃጁን የገዙት ስለመሆኑም ጭምር እንደነገሯቸው ገልጸው መመስከራቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች ስለባጃጅ ተሽከርካሪው የማውቀው ነገር የለም፤በስሜም አልተመዘገበም፤የሽያጭ ውሉም አልቀረበም በማለት በደፈናው ከመከራከር በቀር በተጠሪዋ ምስክሮች የተሰጠውን ምስክርነት ለማስተባበል ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ባጃጅ ተሽከርካሪ የእኔ ነው በማለት የቀረበ ወገን ስለመኖሩም የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡

እንዲህ ከሆነ ደግሞ በአመልካቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 235 መሰረት በመሸሽ መልክ የተሰጠውን የመከላከያ መልስ እና በተጠሪዋ ምስክሮች የተሰጠውን ምስክርነት መሰረት በማድረግ አመልካች ጋብቻው ጸንቶ በነበረበት ጊዜ ገዝተው ነገር ግን ስም ሳያዛውሩ ሲሰሩበት የነበረው ባጃጅ ተሽከርካሪ የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ሕጉን እና የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መሰረት አድርጎ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት የዳኝነት ጥያቄ ያቀረቡት ተጠሪዋ ከአቢሲኒያ ባንክ ብር 34,000 በ02/07/2004 ዓ.ም.ወጪ አድርገው በዚያኑ ዕለት የተለያዩ ዕቃዎችን ይዘው ከቤት የወጡ በመሆኑ ከዚህ ገንዘብ ወስጥ ግማሹን ሊያካፍሏቸው የሚገባ መሆኑን በመጠየቅ ሲሆን ተጠሪዋ በበኩላቸው መልስ የሰጡት አመልካች የእናታቸውን ለቅሶ ጎንደር ደርሰው ከተመለሱ በኃላ የገንዘብ እጥረት እንዳጋጠማቸው በመግለጽ ለሚያካሄዱት የበርበሬ ንግድ ስራ ለማዋል ያስችላቸው ዘንድ ገንዘቡን ወጪ አድርገው እንዲሰጧቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ተጠሪ ገንዘቡን በ02/07/2004 ዓ.ም. ወጪ አድርገው በዚያኑ ዕለት የሰጧቸው መሆኑን እና አመልካቹም ለበርበሬ ግዥ ያዋሉት መሆኑን፣ገንዘቡ ከባንክ ወጪ ተደርጎ ከተሰጣቸው ከአምስት ቀናት በኃላ በ07/07/2004 ዓ.ም አመልካች ጠብ ፈጥረው ተጠሪዋን ከቤት ያባረሩ መሆኑን በመግለጽ እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይህንን የክርክር ነጥብ ለማስረዳት ግራ ቀኙ ካቀረቡት ማስረጃ መካከል በተጠሪዋ በኩል የቀረበው ማስረጃ የራሳቸው ምስክርነት ሲሆን በአመልካቹ በኩል የቀረበው ማስረጃ ደግሞ ከአመልካቹ ምስክርነት በተጨማሪ ተጠሪዋ ከቤት የወጡት በ05/07/2004 ዓ.ም ስለመሆኑ በሌሎች ሁለት ምስክሮች የተሰጠው ምስክርነት ነው፡፡ ተጠሪዋን ብረት ይዘው ከቤት የወጡት በ02/07/2004 ዓ.ም.ስለመሆኑ አመልካች በ03/07/2004 ዓ.ም.ለአካባቢው ፖሊስ ጽ/ቤት አመልክቻለሁ በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ለፖሊስ ያመለከቱት በርግጥም በ03/07/2004 ዓ.ም.መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ የቀረበ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ በመሰረቱ አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው ለግዴታው መኖር ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2001(1) እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 258 እስከ 261 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች እንደ አቤቱታቸው አስረድተዋል ሊባል የሚችለው ተጠሪዋ ከቤት የወጡት ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ብር 34,000 ከባንኩ ባወጡበት በ02/07/2004 ዓ.ም. መሆኑን ማስረዳት ቢችሉ ኖሮ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህንን ነጥብ ደግሞ ማስረዳት አልቻሉም፡፡ ይልቁንም አመልካች ያሰሟቸው 2ኛ እና 3ኛ ምስክሮች ያረጋገጡት ተጠሪዋ ከቤት የወጡት በ05/07/2004 ዓ.ም.መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ብር 34,000 አስመልክቶ አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ሳይቀበሉ የቀሩትም

ከግራቀኙ ማስረጃ መካከል የተሻለ ክብደት ያለው ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ገንዘቡን ለትዳር ጥቅም ያዋሉ ስለመሆኑ በተጠሪዋ በኩል የቀረበው ማስረጃ መሆኑን መሰረት በማድረግ ነው። በመሆኑም ተጠሪዋ በ02/07/2004 ዓ.ም. ከአቢሲኒያ ባንክ ውጪ አድርገው መውሰዳቸው የተረጋገጠው ብር 34,000(ሰላሳ አራት ሺህ) ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠር ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም።

ሲጠቃለል ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

## ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 00906 በ05/09/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሀዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14065 በ23/11/2005ዓ.ም. በፍርድ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59978 በ15/02/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓትሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል።
2. በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01512 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ05/03/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተሰጥቷል።
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ።
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ብ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 107840

ቀን ሐምሌ 28/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘምዘም ሽረፋ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ኢታለ ሐሰን -ቀረቡ

2. አቶ ተቂቶ መሐመድ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባል እና ሚስት ንብረት ክርክር መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በወረዳ ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ፡፡ በ1ኛ ተጠሪ የቀረበው ክስ በቀን 03/06/2006 ዓ.ም የተፃፈ ክስ ዝርዝር ይዘቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን በመግለፅ የተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የመሬት ይዞታ አንድ የቆርቆሮ ቤት አንድ የሳር ክዳን ቤት እንዲሁም በጓሮ የጫት ተክል ፣ቡና ፣ሙዝ ተክል ያለበት አንድ በሬ አንድ ጊደር አንድ ጥጃ እና የውሃ ጀኔሬተር የጋራ የባል እና ሚስት ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ ድርሻቸውን እንዲያካፍሏቸው የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡

በ2ኛ ተጠሪ የተሰጠ መልስ የጋራ ንብረት የለንም በክሱ የተጠቀሱት የእናታቸውን ወይም የጣልቃ ገብ መሆኑ በመግለፅ መልስ ሰጥቷል፡፡በአሁን አመልካች ጣልቃ ገብተው ለክርክር ምክንያት ሆኑት የመሬት ይዞታ ፣ ቀንድ ከብቶች እና የውሃ ጄኔሬተር የራሳቸው መሆናቸው

የከሳሽ እና የተከሳሽ ንብረት አይደሉም በማለት መቃወሚያ አቅርበው የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ተሰምቶ ክርክሩ ተጠናቋል፡፡

ፍርድ ቤትም በመ/ቁ. 08575 በቀን 25/07/06 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሁለት ጥማድ በጣልቃ ገብ ለጎጆ መውጫ የተሰጣቸው መሆኑ በማረጋገጥ እኩል ባልና ሚስት እንዲካፈሉ አንድ በሬ አንድ ጊደር  አንድ ጥጃና የውሃ ጀነሬተር ተጠሪዎች በእኩል እንዲካፈሉ ተወሰነ፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታ በአመልካች በመቅረቡ፣ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እንዲካሄድ በማድረግ በመ/ቁ. 10375 በቀን 19/10/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት በውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አሁንም አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ችሎቱ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች በቀን 13/04/2007 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ በማድረግ የፅሑፍ ክርክር አድርገዋል፡፡ ከአመልካች ክርክር ይዘት ተጠሪዎች እንዲከፈሉ የተወሰነው የመሬት ይዞታ፣ቀንድ ከብቶችና የውሃ ጀነሬተር የግሌ ንብረቶች ናቸው፡፡ ተጠሪዎች ምንም መብት የላቸውም ሲሉ የመሬት ይዞታው በስሜ ግብር ካርኒ የሚቆረጠው በሌለባቸው ንብረት የተሰጠ ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአንደኛ ተጠሪ የተሰጠ መልስ ጎጆ ስንወጣ በአካባቢው ባህል የተለመደ 4 ጥማድ ይዞታ ሰጥተውን አንድ አነስተኛ የሳር ቤት ሰርተን ቋሚ ተክሎች በመትከል ለ 11 ዓመት ባልና ሚስት በጋራ ስንጠቀምበት የነበረ ነው፡፡ ይህንን በማስረዳት ነው የተወሰነው፡፡ ቀንድ ከብቶች ጀነሬተር የባልና ሚስት የጋራ ሃብቶችን በትዳር ውስጥ ያፈራናቸው መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ የተወሰነ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስለሌለው በውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ በ2ኛ ተጠሪ የተሰጠ መልስ ደግሞ የጋራ የሆነ መሬትና ንብረት የለንም፡፡ አብረን ባልና ሚስት የተጠቀምንበት ሁኔታ የለም፡፡ ለጎጆ መውጫ ተብሎ ከአመልካች የተሰጠ ስጦታ የለም፡፡ የምንተዳደረው የነበረው ለእኩል እርሻ እያረስኩ በማገኘው ገቢ ቤተሰቤን አስተዳድር ነበር፡፡ በአመልካች የቀረበ አቤቱታ በአግባቡ ነው በማለት መልሳቸው አቅረበዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪዎች ለ11 አመታት በጋብቻው ቆይታው ጋብቻው በፍቺ በመፍረሱ ምክንያት በ1ኛ ተጠሪ በጋራ ያፈሩትን ሃብት ድርሻቸው እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ክስ በ2ኛ ተጠሪ የጋራ የሚባል ሃብት

እንደሌላቸው ሲከራከሩ የአሁኑ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ንብረት የግላቸው መሆኑን ተከራክሩ በፍሬ ነገር ደረጃ ማጣራት የሚገባው በክሱ የተጠቀሱትን ንብረቶች የባልና ሚስት ናቸው ወይስ የአመልካች ናቸው የሚለውን ጭብጥ በማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ሆኖ በመገኘቱ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ይችላል፤ አመልካች ለተጠሪዎች ጎጆ መውጫ ከይዞታቸው የሰጡ መሆናቸው ተጠሪዎችና በዚሁ የተሰጣቸው በጋራ ይጠቀሙበት እንደነበር በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ነው፡፡

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ/ የመሬት አዋጅ ቁ 110/1999 አንቀፅ 5/5/ ላይ የተደነገገው ባልና ሚስት ጋብቻው ወቅት አብረው ይጠቀሙ የነበረው ይዞታ በፍቺ ጊዜ የመጠቀም መብት አይከላከልም፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 2/7/ በጋራ ይጠቀሙበት የነበር ይዞታ በፍቺ ወቅት እኩል የመካፈል መብት ይሰጣል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት በአመልካች ለተጠሪዎች ለጎጆ መውጫ የተሰጣቸው መሆኑን በስር ፍርድ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለዚህ አመልካች በፍቃዳቸው የሰጡት ይዞታ ተጠሪዎች በጋራ 11 አመት ይጠቀሙበት የነበር ይዞታ

በእኩል እንዲካፈሉ እንዲሁም የቀንድ ከብቶችና የውሃ ጀነሬተር የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ናቸው በማለት በተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በዚህ ጉዳይ በስር ፍርድ ቤቶች ማለትም የደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 62532፣ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 08575 በቀን 19/10/06ዓ.ም እና የስልጤ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 08575 በቀን 25/07/06/ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ያደረጉት ወጪና ኪሳራ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በቀን 27/04/2007ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተነስተዋል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ109731

ሐምሌ 1 ቀን 2007ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች ፡-** ወ/ሮ ሃና አሰፋ -ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ከፍይበሉ አሰፋ -ቀረቡ

2. አቶ ሽፈራው ከበደ---መብታቸው ታልፎአል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት ለስረ ነገሩ ፍርድ ምክንያት የሆነው የብድር ገንዘብ ባለቤታቸው በነበሩት በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የተወሰደው ጋብቻቸው ከፈረሰ በኃላ በመሆኑ የአመልካቿ የግል ንብረት የሆነው የሰሌዳ ቁጥር 2-38341 ተሽከርካሪ ለአፈጻጸሙ የተያዘው አላግባብ መሆኑን ገልጸው ተሽከርካሪው እንዲለቀቅላቸው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 418 መሰረት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡- 2ኛ ተጠሪ በ05/13/2000 ዓ.ም. ከ1ኛ ተጠሪ የወሰዱትን የብድር ገንዘብ መመለስ በነበረባቸው ጊዜ ሳይመልሱ በመቅረታቸው 1ኛ ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 104139 ክስ መስርተው 2ኛ ተጠሪ ብር 41,000 (አርባ አንድ ሺህ) ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ በ30/05/2005 ዓ.ም ውሳኔ ማሰጠታቸውን፣ይህንን ፍርድ ለማስፈጸም 1ኛ ተጠሪ ባስከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 108770 ላይ የ2ኛ ተጠሪ ባለቤት ናቸው በተባሉት የአሁኗ አመልካች ስም ተመዝግቦ የሚታወቀው የሰሌዳ ቁጥር 2-38341 ተሽከርካሪ ለአፈጻጸሙ እንዲውል ያቀረቡትን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ተሽከርካሪው በሐራጅ ተሸጦ ለዕዳው መክፈያ እንዲውል በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተሽከርካሪ ለአፈጻጸሙ የተያዘ መሆኑን፣አመልካቿ የአፈጻጸም ትዕዛዙን

ለሰጠው ፍርድ ቤት መቃወሚያ ያቀረቡትም ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም መሆኑን፣በ24/11/2006 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት መቃወሚያ ይዘትም የአመልካች እና የ2ኛ ተጠሪ ጋብቻ በመዝገብ ቁጥር 74753 በ08/03/2002 ዓ.ም. በተሰጠ ውሳኔ የፈረሰ በመሆኑ በማይመለከታቸው ዕዳ የተያዘው የአመልካቿ የግል ንብረት የሆነው ተሸከርካሪ እንዲለቀቅ የተጠየቀበት መሆኑን፣በመቃወሚያው ላይ 1ኛ ተጠሪ በ16/03/2007 ዓ.ም. በሰጡት መልስ የብድር ዕዳው የተገባው አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ በጋብቻ ተሳስረው በነበረበት ጊዜ መሆኑን እና የንብረት ክፍፍልም ያላደረጉ መሆኑን በመግለጽ መቃወሚያው ውድቅ ተደርጎ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል መጠየቃቸውን፣2ኛ ተጠሪ በሞት ተለይተዋል በመባሉ በእርሳቸው በኩል የቀረበ አስተያየት አለመኖሩን፣ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ የብድር ዕዳው በ2ኛ ተጠሪ የተገባው በ05/13/2000 ዓ.ም. ሆኖ ጋብቻው የፈረሰው ደግሞ በመዝገብ ቁጥር 74753 በ08/03/2002 ዓ.ም. በተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ መሆኑን፣አመልካቿ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ የተጋቢዎቹ የጋራ ዕዳ አይደለም የሚል እና የፍርድ ባለዕዳው ዕዳውን ለመክፈል የሚያስችል አቅም አላቸው የሚል ዝርዝር ክርክር ያላቀረቡ መሆኑን፣ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ እያሉ ለጋራ ጥቅም የተበደሩት ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ሊከፈል እንደሚችል፣ ከጋራ ሀብታቸው ሊከፍሉ ካልቻሉ ዕዳው ከአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት ሊከፈል እንደሚችል እንዲሁም አንደኛው ተጋቢ በግሉ የተበደረውን ገንዘብ በግል መክፈል ካልቻለ ከተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ላይ እንደሚከፈል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 70 የተደነገገ መሆኑን እና በአጠቃላይ ተሸከርካሪው ለዕዳው መክፈያ ሊውል የማይችልበትን ሕጋዊ ምክንያት አመልካች ያላስረዱ መሆኑን ገልጾ የቀረበለትን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ከቀድሞ ባለቤታቸው 2ኛ ተጠሪ ጋር የፍቺ ስምምነት ያደረጉት በ15/08/2000 ዓ.ም. መሆኑን እና ፍርድ ቤቱም በ08/03/2002 ዓ.ም. ያጸደቀው ይህንኑ ስምምነት ከመሆኑ አንጻር እና ብድሩ በ2ኛ ተጠሪ ተወስዷል የተባለው ደግሞ የፍቺ ስምምነቱ ከተደረገ በኃላ በ05/13/2000 ዓ.ም ከመሆኑ አንጻር የብድር ውሉ አመልካችንም የሚመለከት ነው ተብሎ አፈጻጸሙ በግል ንብረታቸው ላይ እንዲቀጥል የተሰጠውን ትዕዛዝ አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ የ2ኛ ተጠሪ መልስ የመስጠት መብት የታለፈ ሲሆን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ግን የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ፍርድ ቤቱ በ08/03/2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ያጸደቀው በ15/08/2000 ዓ.ም. የተደረገውን የፍቺ ስምምነት በመሆኑ ጋብቻው በስምምነት ፈርሷል ሊባል የሚችለው ስምምነቱ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ እንጂ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ከጸቀበት ቀን ጀምሮ አይደለም፣2ኛ ተጠሪ የብድር ውሉን አድርገዋል የተባለውም ጋብቻው በስምምነት ከፈረሰ በኂላ በመሆኑ ብድሩ አመልካችን የሚመለከት ሊሆን አይችልም በማለት መሆኑን የክርክራቸው ይዘት ያመለክታል፡፡አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ጋብቻችንን በስምምነት አፍርሰናል በሚሉበት ቀን እና ስምምነታቸውን ለፍርድ ቤት አቅርበው ባጸደቁበት ቀን መካከል ያለው ጊዜ አንድ ዓመት ከሰባት ወር መሆኑን ከላይ ከተመለከተው የጊዜ ቅደም ተከተል መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሰረቱ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ሊወሰን ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑ እና ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ስለመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 76 (1) ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አነጋገር በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው አንድ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ስምምነት ፈርሷል ሊባል የሚችለው የፍቺ ስምምነቱ ተደርጓል በተባለበት ቀን ሳይሆን የፍቺ ስምምነቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ባገኘበት እና በጸደቀበት ቀን መሆኑን ነው፡፡ብድሩ በ2ኛ ተጠሪ ተወስዷል የተባለው ደግሞ የፍቺ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ከአንድ ዓመት ከሶስት ወራት በፊት መሆኑ አላከራከረም፡፡በመሆኑም ጋብቻው በስምምነት ፈርሷል ሊባል የሚችለው ስምምነቱ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ እንጂ ስምምነቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ አይደለም በማለት አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ የፍቺ ስምምነትን ሲያጸድቅ ተጋቢዎቹ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉትንም ስምምነት አብሮ የሚያጸድቅ ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 80 (2) ስር ተመልክቷል፡፡ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ የመሰረቱት በ1994 ዓ.ም. እንደሆነ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ያቀረቡት የፍቺ ስምምነት የሚያመለክት ሲሆን በፍቺ ስምምነቱ ላይ ተጋቢዎቹ ልጅ እንዳላፈሩ ከመገለጹ በቀር የጋራ ንብረት ያፈሩ ወይም ያላፈሩ ስለመሆኑ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ይህም በፍርድ ቤት ቀርቦ ጸድቋል የተባለው የፍቺ ስምምነት የተሟላ አለመሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡አመልካች የጋራ ንብረት ያላፈራን ስለመሆኑ በፍቺ ስምምነቱ ላይ ተገልጿል በማለት በሰበር አቤቱታቸው ላይ ያቀረቡት ክርክርም የስምምነቱን ይዘት መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ የፈረሰበት ስምምነት በፍርድ ቤት ጸድቋል ከተባለበት ቀን ከአንድ ዓመት በኃላ 2ኛ ተጠሪ እና አመልካች ባልና ሚስት መሆናቸውን በመግለጽ ከሶስተኛ ወገን ጋር የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውል የፈጸሙ ስለመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡትን የክርክር ነጥብ በተመለከተ ባልና ሚስት ከተፋቱ በኃላ

እንደገና ከመጋባትም ሆነ የጋራ ንብረት ከማፍራት የሚከለክላቸው ነገር የለም ከማለት በቀር አመልካች ግልጽ የማስተባበያ ክርክር ያላቀረቡበት መሆኑን የክርክራቸው ይዘት ያመለክታል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በትዕዛዙ ላይ እንደገለጸው አመልካች የብድር ዕዳው የተገባው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ በስምምነት ከፈረሰ በኃላ በመሆኑ ዕዳው አይመለከተኝም ከማለት በቀር 2ኛ ተጠሪ የወሰዱት ብድር ለትዳር ጥቅም የዋለ አይደለም በማለት አልተከራከሩም፡፡የዚህ ዓይነት ክርክር በሰበር አቤቱታቸውም አላቀረቡም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 71 በተመለከተው መሰረት ዕዳው ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ ግምት የሚወሰድበት ይሆናል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ እንደገለጹት ለአፈጻጸሙ የተያዘው ተሸከርካሪ አመልካች ከጋብቻው በፊት ያፈሩት የግል ሀብታቸው መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ዕዳው የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ነው እስከተባለ እና ለፍርዱ አፈጻጸም ሊውል የሚችል የ2ኛ ተጠሪ የግል ወይም የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብትም ቢሆን ለአፈጻጸሙ ሊውል የሚችል ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 70 (2) ድንጋጌ ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ሲጠቃለል በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘው የሰሌዳ ቁጥር 2-38341 ተሸከርካሪ ለአፈጻጸሙ ሊውል አይገባም በማለት አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 108770 በ09/04/2007ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 163553 በ15/05/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 108770 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ20/06/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ይጻፍ፡፡

3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

***መ/ይ***

# ውርስ

የሰ/መ/ቁ.102932

ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካቾዎች፡-**1. አቶ አፈወርቅ ደርጫ ቀረቡ

2. አቶ አበባው ደርጫ ወኪል አንደኛ አመልካች ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሠራዊት ደርጫ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾዎች የአርባምንጭ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15601 ጥቅምት 29 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታህሣሥ 1 ቀን 2006 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 23114 የሰጠው ትዕዛዝና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03770 ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾዎች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው የተከራከሩ ሲሆን፣ ጉዳዩ የውርስ ሀብት ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካቾዎች ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካቾዎች ወላጅ እናታቸው ሟች ብዙነሽ በየነ በአርባ ምንጭ ከተማ ውሃ ምንጭ ቀበሌ በካርታ ቁጥር 2689 የሚታወቅና የቤት ቁጥሩ 911 የሆነ ቤት ሠርታ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች መሆኑን ገልፀው፣ የቤቱ ግምት ብር 60,000 /ስልሣ ሺ ብር/ በመሆኑ ለተከሳሽ /ተጠሪ/ የሚደርሳትን ብር 20,000/ሃያ ሺ ብር/ ከፍለናት ቤቱን እንድታስረክበን ውሣኔ ይስጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርባ እናቷ ቤት ስትሠራ በገንዘብ ያገዝኳትና ቤቱን በጋራ ተጋግዘን የሠራነው በመሆኑ የከሳሾች ክስ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ሟች ቤት ስትሠራ ተከሳሽ በግሏ አውጥቻለሁ የምትለው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ በውርስ አጣሪ በኩል ተጣርቶ

እንዲቅርብለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የውርስ አጣሪው ተጠሪ ብር 13,284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ሟች ቤት ስትሰራ ከግል ገንዘቧ አውጥታ እናቷን የረዳች መሆኑን በማረጋገጥ መግለጫ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ከሳሾች/አመልካችዎች/ ገምተው ካቀረቡት ብር 60,000 /ስልሣ ሺ ብር/ ውስጥ ተጠሪ ያወጣችው ብር 13284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ተቀንሶ ብር 46715.50 /አርባ ስድስት ሺ ሰባት መቶ አስራ አምስት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ለአመልካችዎችና ለተጠሪ/ሶስቱ ወራሾች እኩል ይካፈሉ፡፡ ተከሳሽ /ተጠሪ/ የአመልካችዎችን ድርሻ ብር 31143.66 /ሰላሣ አንድ ሺ አንድ መቶ አርሳ ሶስት ብር ከስልሣ ስድስት ሣንቲም/ ከፍላ ቤቱን ታስቀር በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

2. አመልካችዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችዎችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካችዎች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ በፎርም በሰጠው ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካችዎች ሀምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ተጠሪ ቤቱ ስትሰራ አውጥቻለሁ በማለት የጠየቀችው ገንዘብ የአባታችን ገንዘብ እንጂ የተጠሪ ገንዘብ አይደለም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ከግል ገንዘቧ አውጥታለች በማለት ከውርሱ ንብረት ዋጋ ላይ ተቀንሶ እንድከፈላት የተሰጠው ውሣኔ እውነታውን የማያንፀባርቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካችዎች ያቀረብነው የዳኝነት ጥያቄ እኛ ለተጠሪ ድርሻዋን ከፍለናት ቤቱን ትልቀቅልን የሚል ሆኖ እያለ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ድርሻችሁን ትክፈላችሁና ቤቱን ታስቀር በማለት የሰጡት ውሣኔ፣ እኛ ያቀረብነውን የዳኝነት ጥያቄ ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ እንዲሻርልን በማለት አመልክተዋል ፡፡

3. ተጠሪ ህዳር 5 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠችው መልስ ቤቱ እድሳት የተደረገበት በእኔ ገንዘብ እንደሆነ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ቤቱን እኔ ይዤ ስኖርበት ቆይቻለሁ፡፡ ተጠሪ አዲስ ቤት በገንዘቤ ሠርቻለሁ፡፡ ቤቱን በአመልካችዎች ፈቃድና ስምምነት የሰራሁ በመሆኑ ቤቱን መያዝ የሚገባኝ እኔ ነኝ፡፡ ቤቱን ብር 60,000/ስልሣ ሺ ብር/ ገምተው ያቀረቡት አመልካችዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀናልኝ በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካችዎች ታህሣሥ 4 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ እናታችን ቤቱ ውስጥ ልጆቼ ይኑሩ የሚል ኑዛዜ ትታለች፡፡ ተጠሪ አወጣሁ ያለችው ወጭ አመልካችዎች በሌለንበት የወጣ ዕውነትነት የሌለው ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ የአመልካችዎችን ድርሻ ከፍላ የውርስ ቤቱን እንድታስቀር የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በሚች ስም ያለውን የውርስ ቤት ለማደስ ጠቅላላ ዋጋው ብር 13284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ያወጣች መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውርስ አጣሪ በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የውርስ ንብረቱን ለማደስ ብር 13,284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ከግል ገንዘቧ አውጥታለች በማለት የደረሰበትን መደምደሚያ፣ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተስማምቶበት በትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡ ይህም ተጠሪ የውርስ ቤቱን ለማደስ ብር 13,284.50 ከግል ገንዘቧ ማውጣቷ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካችዎች የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን የደረሱበት መደምደሚያ ስህተት መሆኑንና ቤቱ አባታቸው በላከው ገንዘብ የታደሰ መሆኑን በመግለፅ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም አመልካችዎች ያቀረቡት ይህ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር ለዚህ ሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 የተሰጠውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር አይቶ የማረም ሥልጣን ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የውርሱን ንብረት ለማደስ ከግል ገንዘቧ ያወጣችው ብር 13,284.50 የውርስ ንብረት ክፍፍል ሲደረግ ሊተካለት ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረተዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

6. በዚህ መዝገብ መታየት ያለበት አከራካሪ የሰበር ጭብጥ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የአመልካችዎችን ድርሻ ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር የተሰጡት ውሣኔ የውርስ ሃብት ክፍያ ደንቦችን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ከሳሽ የሆኑት አመልካችዎች ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ፣ ከእናታቸው በውርስ ያገኙት ቤት ግምቱ ብር 60,000 መሆኑን ገልፀው ለተጠሪ ድርሻዋን ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ ከፍለናት ቤቱን እንድታስረክበን ይወሰንልን የሚል ይዘት ያለው መሆኑን ከወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ ይህም አመልካችዎች የውርሱን ንብረት ተጠሪ የእነርሡን ድርሻ ከፍላ እንድታስቀር የዳኝነት ጥያቄ ያላቀረቡ መሆኑንና ተጠሪ በበኩሏ ቤቱን ማስቀረት ያለብኝ እኔ ነኝ በማለት የተከራከረች መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም አከራካሪውን የውርስ ንብረት አመልካችዎችና ተጠሪ ለማስቀረት ፍላጎት

ያላቸው በሆነበት ሁኔታ የውርሱ ንብረት /ቤቱ/ የሚች ወራሾች እንዴትና በምን ሁኔታ ሊካፈሉ ይገባል የሚለውን ነጥብ መመርመር ይጠይቃል፡፡

7. የውርስ ንብረት የሚከፈለው በወራሾቹ መካከል በሚደረግ ስምምነት እንደሆነ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1089 ንዑስ አንቀፅ 1 የሚደነግግ ሲሆን ውርሱ በአይነት መከፋፈል ከሆነ ወራሾቹ የውርሱን ንብረት በአይነት የሚካፈሉ መሆኑ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1086 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡ የውርሱ ሀብት በአይነት ለመከፋፈል የማይችል በሆነ ጊዜና ከወራሾቹ መካከል ይህንን ሊካፈል የማይችለውን ንብረት ሊወስድ የሚገባው የትኛው እንደሆነ በስምምነት ለመወሰን ያልቻሉ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ ገንዘቡ ለወራሾቹ የሚከፋፈል መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1092 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች ከላይ በገለፅናቸው የውርስ ንብረት ክፍያ ደንቦች ሣይከተሉ፣ አመልካችዎች ተጠሪ የውርሱን ቤት እንድታስቀር ባልተስማሙበት ሁኔታ፣ ተጠሪ የአመልካችዎችን ድርሻ ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር የሰጡት ውሣኔ ከላይ የገለፅናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚቃረንና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፣ በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአርባ ምንጭ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ፣ የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የውርሱን ንብረት ለማደስ ከግል ገንዘቧ ያወጣችው ብር 13,284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ከውርስ ንብረት ዋጋ ተቀንሶ ለተጠሪ እንዲተካለት የሰጡት የውሣኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. የውርስ ንብረት የሆነውን ቤት ክፍያ በተመለከተ፡ ተጠሪ የአመልካችዎችን ድርሻ ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

 3/ሀ/ የውርስ ንብረት የሆነው ቤት የሶስቱም ወራሾች ስለሚካፈልበት ሁኔታ አመልካችዎች እና ተጠሪ የሚስማሙ ከሆነ ክፍያው በስምምነታቸው መሠረት እንድፈጽም በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1079 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ወስነናል፡፡

 /ለ/ አመልካችዎችና ተጠሪ ቤቱ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ካልተስማሙና ቤቱ በአይነት ለአመልካችዎችና ለተጠሪ ለመካፈል የሚችል ከሆነ፣ አመልካችዎች ተጠሪ ቤቱን የጠገነችበትን ገንዘብ ሁለት ሶስተኛውን ለተጠሪ ከፍለው ቤቱን በአይነት እንዲካፈሉ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1086 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ወስነናል፡፡

/ሐ/ አመልካችዎና ተጠሪ ቤቱን ስለሚከፈልበት ሁኔታ ካልተስማሙና ቤቱ በአይነት ለወራሾቹ ለማካፈል የማይቻል ከሆነ ቤቱ በሀራጅ ከተሸጠ በኂላ፣ ተጠሪ የውርስ ቤቱን ለማደስ ያወጣችው ገንዘብ በመጀመሪያ ተከፍሎ፣ ቀሪውን የቤቱን ዋጋ አመልካችዎችና ተጠሪ ለሶስት እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1092 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1093 መሠረት ወስነናል፡፡

4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/አ**

የሰ/መ/ቁ. 108106

መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** አቶ አዱኛ ጉደታ የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** እነ 1. ወ/ሮ በሻዱ ጉደታ - የቀረበ የለም

2. ወ/ሮ ባንቹ ጉደታ

3. ወ/ሮ ሙሉ ጉደታ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ፤ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጣልቃገብ ነበሩ፡፡ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ እናቴ ወ/ሮ ኩሊ ቦኩ በ10/03/04 ዓ/ም ባደረባት ህመም ሞተዋል፤ በህይወት በነበሩበት ወቅት በተለያዩ አካባቢዎች የመሬት ይዞታ የነበረ ሲሆን መሬቱ በአመልካች እጅ የሚገኝ በመሆኑ የሌሎች ወራሾች ድርሻ ወጥቶ ድርሻዬን ያካፍለኝ በማለት በመጠየቃቸው፤ አመልካች በሰጡት መልስ የግል እንጂ የውርስ ንብረት አይደለም፡፡ ከ1967 ጀምሮ ከእጄ ሳይወጣ ስጠቀምበት ቆይቻለሁ በማለታቸው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ይዞታው የቤተሰቦቻችን እንጂ የአመልካች ብቻ አይደለም በማለት ጣልቃ ገብተው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን በማከራከርና ምስክሮችን በመስማት ተጠቃሹ ይዞታ 6.5 ሄክታር መሆኑን እና ይዞታውም በሟቾች ስም የነበረ እና ከእናታቸው ሞት በኃላ (2004 ) መሬቱን አመልካች በልጃቸው ስም አስመዝግቦ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ መስተዳድሩ ጭምር በመግለፁ በገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ.130/99 አንቀጽ 16 እና በደንብ ቁ.151/2005 መሠረት ከሟቾች ጋር አብረው ሲኖሩ የነበሩት አሁንም እዛው

ያሉት አመልካች ናቸው፡፡ ተጠሪዎች በአሁኑ ጊዜ ሌላ ቦታ ወጥቶ ያሉ በመሆኑ በይዞታው ላይ የቅዲሚያ መብት ያላቸው አመልካች በመሆኑ የተጠሪዎች ክስ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ በቀጣይነት ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም ተጠሪዎች የቤተሰብ አባል በመሆን በይዞታው ሲጠቀሙ ያልነበሩ ሲሆን አመልካች አሁንም በይዞታው እየተጠቀሙ በመሆኑ አመልካች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል መባሉ ባግባቡ ነው በማለት የስር ውሳኔን አጽንቶታል፡፡ በመጨረሻም ጉዳዩን ያየው የክልሉ ሰበር ችሎትም መዝገቡን በመመርመር፤ አመልካች ይዞታው የግላቸው መሆኑን እነጂ የቅድሚያ መብት እንዳላቸው አልተከራከሩም፤ ተጠቃሹም ደንብ ቢሆን ቅድሚያ የሚሰጠው አመልካች ድርሻን እንዲወስዱ እንጂ ተጠሪዎችን መብት የሚከለክል አይሆንም፣በመሆኑም አመልካች ለብቻቸው 6.5 ሄክተር ተጠቃሚ መድረጉ ከአዋጁ አላማ ውጭ በመሆኑም ተጠሪዎች ወራሾች በመሆናቸው እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ በመሆኑም አመልካችም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልፁ፡- ይዞታው የተጠሪዎች እናት ሳይሆን በአዋጅ ቁ.31/67 መሰረት በ1967 ዓ/ም በምሪት ያገኘሁት ነው፡፡ በስሜም ተመዝግቦ በእጄ ተለክቶ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ከተጠሪዎች ጋር ተካፈሉ መባሉ ባግባቡ አይደለም፡፡ በመሬቱ ብቸኛ ተጠቃሚ እና ከዚህ ገቢ የሚተዳደር መሆኔ እየታወቀ ከአዋጅ ቁ.130/99 አንቀጽ 9(2) ውጭ የተወሰነ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሠረት ችሎቱ የደንብ ቁ.151/2005 አንቀፅ 10(10) መሠረት አመልካች የቅድሚያ መብት ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት አላነሳም ተብሎ መታለፉን በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙን በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰበር መልሳቸው የሚሉት፡- አመልካች ያቀረቡት መልስ ይዞታው የግላቸውና በ1967 በህግ ተመርተው ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን ነው፡፡ በምስክር እና በመስተዳደሩ የተረጋገጠው ግን የቤተሰባችን እና ሚች እስከ 2004 ዓ/ም ድረስ የሚጠቀሙ መሆኑን ነው? አመልካች ቤት ስለቀሩ እና እኛ ባል በማግባታችን የቤተሰባችን ንብረት ልናጣ አይገባም የደንብ ቁ151/2005 አንቀፅ 10(10) ትክክለኛ ፍቺ ያለማወቅ የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በደንብ ቁ.151/2005 አንቀጽ 10(10) መሠረት ብቸኛ ተጠቃሚ መሆን ሲገባኝ ከተጠሪዎች ጋር ተካፈል መባሉ ሊታረም ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ይህን ይመስላል፡፡ እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንፃር መዝገቡን መርምረናል፡፡

ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ያከራከረውን የይዞታ ጉዳይ እንዳየነው የአመልካች አብይ ክርክር የነበረው ይዞታውን በ1967 በአዋጅ በእጇ አስገብቼ ስጠቀምበት የነበረና የውርስ ንብረት ሳይሆን የግሌ ይዞታ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን ከክርክር ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ይዞታው የግራቀኙ ወላጅ እናታቸው እስከ እለተሞታቸው 2004 ዓ/ም ድረስ ስጠቀሙበት የነበረና አመልካች በልጁ ስም (በአስናቀ) ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን በመስተዳደሩ የተገለጸ ነው፡፡ እንግዲህ ከጅምሩም በአመልካች የውርስ መሆኑ ባልታመነበትና በክርክር ሂደት የተጣራ መሆኑ እየታወቀ በስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ይዞት ቆይቷል ቤተሰብ ሆኖ ሲጠቀምበት ነበር በማለት የክልሉን ደንብ ቁ.151/አንቀጽ 10(10) በመጥቀስ የቅድሚያ መብት ያለው አመልካች ነው በማለት ይዞታውን ጠቅልሎ እንዲወስድ በመወሰናቸው ምክንያት የክልሉ የሰበር ችሎት ጉዳዩን በማጣራት አመልካች ባላነሳው ክርክር የቅድሚያ መብት አለው ተብሎ 6.5 ሄክታር ለብቻው እንዲወስድ መወሰን የለበትም አከራካሪው ይዞታ የግራ ቀኙ ወላጆች መሆኑ እስከ ተረጋገጠ ድረስ ድርሻቸውን ሊነፈጉ አይገባም፡፡ ተጠቃሹ ደንብ ቁ. 151/ 10(10) ለአመልካች መብት ይሰጠዋል ቢባልም እንኳ እንዲቀር የመውሰድን እንጂ ተጠሪዎችን በማሳጣት ባጠቃላይ ይዞታውን ለአመልካች እንዲቀር የሚያደርግ ሊሆን ተደርጎ ሊቶረጎም የሚገባው አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማረም ተከራካሪዎች ከአመልካች ጋር እኩል ድርሻ አላቸው ተብሎ መወሰኑ ይህ ችሎትም የሚቀበለው ነው በአጠቃላይ አመልካች ከሟች ጋር እስከ 2004 ዓ/ም በመኖሩ ብቻ አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች ሌላ ገቢ ይኑራቸው አይኑራቸው ባልተረጋገጠበት አመልካች ቀድሞ ይዞ ወደ ልጁ ስም ማዞሩ ብቸኛ ተጠቃሚ ሊያደርገው አይገባም የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ 130/99ም ሆነ ተጠቃሹ ደንብ ቁ. 151/2005 በዚህ መልኩ ሊተረጎሙ የሚገባቸው አይደሉም፡፡

በመጨረሻም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የወረዳውን እና የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ተጠሪዎች በአከራካሪው የውርስ መሬት እኩል ድርሻ አላቸው ሲል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 32850 በቀን 1/7/06 ዓ/ም የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 22061 በ20/8/2006 የሰጡትን ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተሽሮ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር እኩል ድርሻ አላቸው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የግራ ቀኙ የወጪ ኪሳራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ.110022

ሐምሌ 29 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡-ወ/ሮ ትሻገር ምህረቴ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት የሚች እናቴ የወ/ሮ ማሚቴ ደሳለኝ ወራሽ መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ ጥያቄው የቀረበለት አምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ በትዕዛዝ ውድቅ ያደረገው የሚወረስ ንብረት ስለመኖሩ ተጣርቶ የቀረበ ነገር የለም በማለት ሲሆን የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም እንደቅደም ተከተላቸው በፍርድ እና በትዕዛዝ ያጸኑት ይህንኑ ትዕዛዝ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ቀድሞ የወሰድኩት የወራሽነት ማስረጃ ስለጠፋብኝ በድጋሚ ወራሽነቴን ላረጋግጥ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት አጣርቶ ለመወሰን ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የአመልካች ጥያቄ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህ መሰረት አመልካች ለወረዳው ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው በመጠየቅ ሲሆን ጥያቄውን ሊያቀርቡ የቻሉት ደግሞ የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ እንደማይነበብ ተደርጐ ስለተበላሸ መሆኑን በመግለፅ ያቀረቡት ክርክር የተመዘገበው በከፍተኛ

ፍርድ ቤት ነው፡፡ የቀድሞ የወራሽነት ማስረጃ የተሰጠበት መዝገብ ቁጥር 76/83 መጥፋቱ በመረጋገጡ ምክንያት ለአመልካቿ የቀድሞው የወራሽነት ማስረጃ ቅጂ እንዲሰጥ ማድረግ ያልተቻለ ስለመሆኑም ይግባኝ ሰሚው የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ አመልክቷል፡፡ በመሰረቱ ወራሽ የሆነው ሰው ለሟቹ ወራሽ መሆኑ እና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመለክቱ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡት ዳኞችን ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 996(1) ይደነግጋል ፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እንዲሰጣቸው ጥያቄው ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ ብቻ ነው፡፡ ከውርሱ ላይ የሚያገኙት ድርሻ የሚያመለክት የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ የለም፡፡ አንድ ሰው ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመለክት የምስክር ወረቀት ጥያቄ መስጠት የሚቻለው ውርሱ እንዲጣራ ከተደረገ በኂላ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን የወራሽነት ማስረጃ ወይም የምስክር ወረቀት ለመስጠት ግን የውርስ ማጣራት ሂደት በቅድሚያ መከናወን የሚገባው ስለመሆኑ ሕጉ የሚጥለው ግዴታ የለም፡፡ ወራሽ የሆነው ሰው ለሟቹ ወራሽ መሆኑ እና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመለክት የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡት ዳኞችን ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 996/1/ የተመለከተው ድንጋጌም የሟች ወራሽ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ ብቻ እንዲሰጠው ወይም ደግሞ ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ ጭምር የሚያመላክት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጠው የመጠየቅ አማራጭ ለጠያቂው ወገን የተተወ እንጂ ሕጉ ሁለቱም አይነት ማስረጃዎች ሊጠየቁ እና በፍርድ ቤት ሊሰጡ የሚችሉት ሳይነጣጠሉ በአንድነት ስለመሆኑ በአስገዳጅነት አልደነገገም፡፡ የወራሽነት የምስክር ወረቀት የማግኘት እና የውርስ ማጣራት ሂደት ሁለት የተለያዩ ሂደቶች ስለመሆናቸው እና የተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 996/1/ ድንጋጌው ውርሱ ካልተጣራ በቀር የወራሽነት ማስረጃ ሊሰጥ አይችልም በሚል አግባብ ሊተረጎም የሚገባው ስላለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35657 በ06/02/2001 ዓ.ም የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ለቀረበው ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታው የቀረበለት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 39306 በ11/03/2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቀደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 02827 በ08/05/2007 ዓ.ም በፍርድ እና በመዝገብ ቁጥር 202020 በ05/06/2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ውርሱ እንዲጣራ ሳይደረግ የወራሽነት የምስክር ወረቀት መስጠት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 996 (1) ድንጋጌ አይከለክልም በማለት ወስነናል፡፡
3. የአመልካቿን ጥያቄ አስተናግዶ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1)መሰረት ለአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. የውሣኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈፀም ያስችለው ዘንድ ለአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲያውቁት ደግሞ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. ውሣኔ ያገኝ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ግ**

የሰ/መ/ቁ. 105652

ቀን 30/11/2007ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃም መሰለ

አመልካቾች፡- 1ኛ. ወ/ሮ አሰፉ ዘለቀ

2ኛ. ወ/ሮ ብርቱካን ዘለቀ

3ኛ. ወ/ሮ ሰላማዊት ዘለቀ

4ኛ. ወ/ሪት አምሳሉ ዘለቀ — ጠበቃ አበበ ደገ

5ኛ. ወ/ሮ ተስፋነሽ ዘለቀ

6ኛ. ወ/ሪት ወርቁሀ ዘለቀ

7ኛ. ተማሪ ራሄል ዘለቀ

ተጠሪ፡- አቶ ዳዊት በርሄ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የይርጋ ተፈጻሚነትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ሃዋሳ ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች በተጠሪ እና 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት ወላጅ እናታቸው ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የአመልካቾች የክስ ይዘት፡- ሟች አባታችን አቶ ዘለቀ ባዲቦ በንግድ ስራ ተሰማርቶ እያለ በሞት ሲለይ ለአቅመ ሄዋን አልደረስንም፡፡ እናታችን ሞግዚት ሆና የካቲት ወር 1988ዓ.ም ወራሽነታችንና የሷን ሞግዚትነት በፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ በአባታችን የውርስ ሃብት ስታስተዳድረን ነበር ተጠሪ የእናታችን ወንድም ልጅ በመሆኑ ቤተሰብ ነው፡፡ 1ኛ

ተከሳሽ (ተጠሪ) ከ2ኛ ተከሳሽ (የአመልካቾች እናት) ጋር በመመሳጠር የውርስ ሃብታችን እንደሆነ እያወቀ በአመልካቾች የውርስ ሀብት ላይ የመዋዋል ስልጣን ሳይኖረው ሃምሌ 2ቀን 1999 ዓ.ም 2ኛ ተከሳሽ ከሆነችው እናታችን ጋር የስጦታ ውል እንደተዋዋሉ ተረድተናል፡፡ የስጦታ ውሉ በተደረገበት ጊዜ ሁለት አመልካቾች ለአቅመ ሄዋን አልደረስንም፡፡ 2ኛ ተከሳሽ ከንብረቱ ግማሹ የአመልካቾች የውርስ ንብረትን በስጦታ የማስተላለፍ ስልጣን አልነበራትም በራሷም መብት ሲሆን ልጆቿን አለአግባብ ከውርስ መንቀል አትችልም፡፡ በተጠሪው እና በ2ኛ ተከሳሽ (የአመልካቾች ወላጅ እናት) መሀከል የተደረገው የስጦታ ውል ለህግና ለሞራል ተቃራኒ እና 2ኛ ተከሳሽ የግል ንብረቷ ባልሆነ ንብረት ላይ የተደረገ የስጦታ ውል በመሆኑ በህግ ፊት የማይጸና ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልን፡፡ በ2ኛ ተከሳሽ ስም የተዘዋወረው ንብረት ስመ ባለቤትነት ተሰርዞ ወደ አመልካቾች ይዛወርልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም የሚል እና ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭ መልሳቸው ክርክር ያስነሳው ቤት በስጦታ ውል ለ1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) በተላለፈበት ጊዜ ንብረትነቱ በ2ኛ ተከሳሽ በስማቸው የባለሃብትነት ማስረጃ አውጥተው የአመልካቾች አባት ባለቤት ናት ወደ 2ኛ ተከሳሽ ከተዛወረ በኂላ የስጦታ ውሉ የተደረገ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ለህግም ሆነ ለሞራል ተቃራኒ ነው ሊባል አይገባም፡፡ 2ኛ ተከሳሽ ባለሃብትነቱን በስማቸው አዛውረው ለባንክ ያስያዙትን ንብረት እዳውን ከፍዬ ስጦታውን እንድቀበል ሳደርግ አመልካቾች ሳይቃወሙ የስጦታ ውሉ ተደርጎ 7ዓመት ከሆነ በኂላ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም የሚል ነው ፍ/ቤቱ በተጠሪ የተነሳውን መቃወሚያ በብይን አልፎ የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኂላ ለክርክር ምክንያት ከሆነው ሆቴል ግማሹን 50% 2ኛ ተከሳሽ ለተጠሪ በስጦታ ማሳለፋቸው ወይም መስጠታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአመልካቾች የውርስ ድርሻ የሆነውን ግማሹን 50% የአመልካቾች ያልተከፋፈለ የውርስ ሃብትን ጠቅላላው ለ1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) የሰጡ በመሆኑ የሥጦታ ውሉ በከፊል ይፍረስ፡፡ ወደ ነበሩበት መመለስ የማይቻል ስለሆነና ንብረቱን በስምምነት መካፈል የሚችሉ ከሆነ ይካፈሉ ካልቻሉ በሃራጅ ሸጠው እኩል ይካፈሉ ከባንክ በብድር የተወሰደውን ብር 600,000 አመልካቾች 300,000 ብር ለተጠሪ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኝ ቅሬታቸውን ለሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 377 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

በስር ፍ/ቤቶች በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ይታረምልኝ በማለት ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የተጠሪዎች (የአሁኑ አመልካቾች) ጥያቄ ይዘት በእናታቸው የተደረገ የሥጦታ ውል እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡ ተጠሪዎች ስጦታው ከተደረገበት ቀን አንስቶ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ያላቀረቡ በመሆኑ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441(1) መሰረት በሁለት አመት ይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በዚህ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈጸመ ያሉትን መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ አመልካቾች አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ያስቀርባል የተባለው የአመልካቾች የስጦታ ውል ይፍረስልን ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441(1) ውሉ ከተደረገ ጀምሮ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም በይርጋ ይታገዳል የይርጋው ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 በ10ዓመት የይርጋ ጊዜ አይታይም መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው የግራ ቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንዲሁም አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር የአመልካቾች የመብት ጥያቄ የሚኙ አባታችን የውርስ ድርሻ እና በስር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ የሆነችው ወላጅ እናታችን የሚስትነት ድርሻ ያለበትን ንብረት የስር 2ኛ ተከሳሽ የወንድሟ ልጅ ለሆነው ተጠሪ በስጦታ ውል አሳልፋ መስጠት አትችልም የተደረገው የስጦታ ውሉ ለሞራል እና ለሕግ ተቃራኒ በመሆን ይፍረስልን የሚል ነው፡፡ አንድ ሰው በስጦታ ለሌላ ሰው መስጠት የሚችለው የራሱ የሆነውን ንብረት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2427 ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች የስጦታ ውሉ ይፍረስልን በሚል ክስ የማቅረብ መብታቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441(1) መሰረት በሁለት አመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል በሚል የሰጠው ውሳኔ የተጠቀሰው የፍ/ሕግ ድንጋጌ መነሻ የሚያደርገው ፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 2439 ስለመንፈስ መጫን የሚለውን በመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በስጦታ ሰጪ ላይ በተደረገ የመንፈስ መጫን የተደረገ የስጦታ ውል ይፍረስልን የሚል ባለመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ይርጋ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1845 የተመለከተው መሆን ሲገባው የፍ/ሕ/ቁ. 2441(1) ጠቅሶ የአመልካቾች አቤቱታ በሁለት አመት ይርጋ ታግዷል (ቀሪ ሆኗል) በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የደ/ብ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ር ሰበር 62649 በቀን 21/01/2007ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441(1) ሳይሆን በፍ/ሕ/ቁ. 1845 የተመለከተው ነው ብለናል፡፡
3. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ከይርጋ ክርክር ውጭ ባሉ በግራ ቀኙ ክርክሮች የመሰለውን ውሳኔ ይስጥበት ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ቅጂ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይላክ

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

**መ/ይ**

የሰ/መ.ቁ.109697

ቀን 30/11/2007

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃም መሠለ

**አመልካች፡-** ዘሙ አስፋው አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** መሀመድ አስፋው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ይዞታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው አማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ሀብሩ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች በተጠሪ ላይ አቅርበውት የነበረው ክስ ይዘት አያቶቼ ከሆኑት ሟቾች አቶ አስፋው ሸኩር እና እናት ሠይድ ጋር በ1983 ዓ.ም መሬት በተሰጣቸው ወቅት በቤተሰብ አባልነት ተመዝግቤ እኖር ነበር፡፡ ለአያቶቼ በተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ላይ ስሜ በቤተሰብነት ተመዝግቧል፡፡ የቤተሰብ አባል ስለሆንኩ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ ተጠሪ /ተከሳሽ/ ድርሻ ይዞታ መሬት ያካፍለኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች መሬት የተተመነችው ከአያቶቿ ከእኔ ወላጆች ሳይሆን ከወላጆቿ ጋር ነው፡፡ የወላጆቼ ወራሽ በመሆኔ ይዞታው በስሜ ተዛውሯል አመልካች ለክስ ምክንያት ከሆነው መሬት ድርሻ የላትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ለክርክር ምክንያት በሆነው ይዞታ ደብተር ላይ በቤተሰብ አባልነት የተመዘገበች በመሆኑ እና የወራሽነት ማስረጃ ያቀረበች በመሆኑ ከተጠሪ ጋር መሬቱን የመካፈል መብት አላት ብሎ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ያለውን ቅሬታ ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በይግባኝ አቅርቦ ግራቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ስር ፍ/ቤት ከሳሽ /የአሁኑ አመልካች/ የሚቾቹን ገቢ በቋሚነት እየተጋራች የምትኖር መሆኑን የራሷ ገቢ ያልነበራት መሆኑን ማጣራት ሲገባ ክክርክሩ መሬት እንደተቻለው መልስ ሰጭ በራሳቸው የሚተዳደሩ እና የራሳቸውን ገቢ ለማግኘት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ከሟቾች በመለየት ሣውዲ አረቢያ የኖሩ መሆኑ ራሳቸው ያመኑት ፍሬ ነገር በመሆኑ በአ.ቁ.133/98 ለቤተሰብ አባል የተሰጠውን ትርጉም የማያሟሉ በመሆናቸው የሚቾችን መሬት በቤተሰብ አባልነት ስም ሊወርሱ አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ችሎት አያስቀርብም በማለት ተዘግቶባቸዋል፡፡

አመልካቿ በስር ፍ/ቤቶች ተፈፀመ ያሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታረምላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አቤቱታቸው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል የተባለው አመልካች በቤተሰብ አባልነት መመዝገቡ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግንዛቤ ከተወሰደ በኋላ ወደ ሣውዲ አረቢያ መሄዷን ብቻ ምክንያት በማድረግ ቋሚ ስራ እንዳላት አድርጐ መወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡

ግራቀኙ የፅሑፍ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ ጋር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች ስለክርክር ምክንያት በሆናቸው ይዞታ መሬት የይዞታ ደብተር ላይ በቤተሰብ አባልነት የተመዘገበች መሆኑ እና አረብ ሐገር እስከሄደችበት 1996 ዓ.ም ድረስ ከሟች አያቶቿ ጋር ትኖር የነበረ መሆኑ አረብ ሐገር እንዳለች አያቶቿ የሞቱ መሆኑ እና ከአረብ ሀገር ተመልሳ ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት ወራሽ መሆኗን በአዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀፅ 11/7//ሀ/ መሠረት በማረጋገጥ ማስረጃ ያቀረበች መሆኑ ደርሶናል ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች በ1996 ዓ.ም ከአያቶቿ ተለይታ ሣውዲ አረቢያ የኖረች መሆኑ ሌላ ማስረጃ ሳያስፈልገው አመልካች በአዋጅ ቁ.133/98 ለቤተሰብ አባል የተሰጠውን ትርጉም አታሟላም በማለት መደምደሚያ ላይ መድረሱ ከአዋጁ ትርጉምና ዓላማ የራቀ ነው፡፡

አመልካች ለጊዜው ወደ አረብ ሐገር መሄዷ በአዋጁ አንቀፅ 133/98 ለቤተሰብ ከተሰጠው ትርጉም ውጭ የሚያደርጉት አይሆንም ከአረብ ሐገር ከተመለሰች በኋላ ቀደም ሲል ስትኖርበት በነበረው ይዞታ መሬት ድርሻዋን ወስዳ በግብርና ለመተዳደር መብቷን ለማስከበር ያቀረበችው አቤቱታ አረብ ሐገር ሄዳ በመመለሷ ብቻ የራሷ መተዳደሪያ እንዳላት እና ለክርክር ምክንያቶች ከሆነው መሬት መጠቀሚ ተቋርጧል የቤተሰብ አባል አይደለችም፡፡ ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት ድርሻ የላትም ተብሎ መወሰኑ የክልሉን አዋጅ ቁ.133/98 ዓላማን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ በስር ከፍ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይህን ተከትሎ በይግባኝ እና በሰበር ችሎቱ የተሰጡ ውሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሰሜን ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.11603 በቀን 19-11-03 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ----- /ይ/መ/ቁጥር 03-09093 በቀን 1/03/07 ዓ.ም እና ጠ/ፍ/ቤት በጠ/ፍ/ሰ/ይ/መ/መ/ቁ. 03-09714 በቀን 24/4/2007 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ብለናል፡፡
2. የወረዳው ፍ/ቤት በመ/ቁ.11-902 በቀን 7/08/2006 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ --- ቁ.348/1/ መሠረት ፀንቷል ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ የውሳኔው ትክክለኛ ቅጅ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
   - መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

# ውሉ

ሰ/መ/ቁ.101378

ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች**፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ነገረ ፈጅ አርአያ ካሣ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ናሰው ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -ጠበቃ ውቡ አስነቀው - ቀረቡ

**መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 134164 ሚያዚያ 2 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 100813 ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የግንባታ ሥራ የመጨረሻ ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. ከሳሽ (ተጠሪ) የተከሳሹን የምስራቅ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትና የሰሜን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንፃ ሰርቶ ለማስረከብ ውል የተዋዋለና ከውሉ በተጨማሪ የስሚንቶ የብረትና የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ መሠረተ ልማት ባወጣው መመሪያ መሠረት ክፍያ እንደሚፈፀም መስማማቱን በደብዳቤ ቁጥር W5PP/861/08 ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ/ም በደብዳቤ ገልፆልን ዋናውን ውል እንድንፈርም የቀረበልኝን ጥያቄ ተቀብዬ ውሉን በመፈረም በውሉ መሠረት የህንፃዎቹን ግንባታ አጠናቅቄ ህንፃዎቹን ለከሳሽ /አመልካች/ አስረክቤያለሁ ተከሳሽ ከሳሽ የሠራቸው ሥራዎች በተቆጣጣሪ መሀንዲስ ተረጋግጠ እየቀረበለት ክፍያ ሲፈፅም ቆይቷል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ሰኔ 26 ቀን 2004 ዓ/ም በአማካሪ መሀንዲስ ተረጋግጦ የቀረበለትን ብር 4,623,938.76 ( አራት ሚሎዮን ስድስት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰባ ስድስት ሣንቲም) አልከፈለም፡፡ ከሳሽ ተከሳሹ ክፊያውን እንድፈፅም ማስጠንቀቂያ

ብሰጠውም ያልከፈለ ስለሆነ ከሰኔ 26 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

2. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ተከሳሽ በዋናው ውል ያልተፈቀደ ለነዳጅ ለሲሚንቶና ብረት የዋጋ ጭማሪ የከፈለው ብር 1,829,661.15 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺ ስድስት መቶ ስልሣ አንድ ከአሥራ አምስት ሣንቲምና) እና ለተጨማሪ ሥራዎች የከፈለው ብር 3,696,219.55 (ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ አምስት ሣንቲም) የፋይናንስ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አሳውቋል፡፡ ስለዚህ ይኸ ገንዘብ ሊቻቻልልን ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽና ከሳሽ የህንፃውን የመጨረሻ ርክክብ ያልፈፀመ በመሆኑ ከሳሽ የመጨረሻ ክፍያ ሊጠይቀኝ አይገባም የሚል የመከላከያ መልስ አቅርቧል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቷል የሥር ፍርድ ቤት የተከሳሽ (አመልካች) አማካሪ መሃንድስ ቀርቦ የሰጠውን የምስክርነት ቃል ከሰማ በኃላ አመልካች ያቀረበውን የመቻቻል ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የመጨረሻ ርክብክብ ሣይደረግ ክፍያ አልከፍልም በማለት ያቀረበው ክርክር የህንፃ ሥራ ውሉ የሚተዳደርበት የኮንስትራክሽን ዘርፍ መመሪያ መሠረት ያላደረገ ክርክር መሆኑን ገልፆ ተከሳሽ ከሳሽ ለሠራውና ሥራው ተረጋግጦ በአማካሪ መሃንድሱ ፀድቆ የቀረበለትን ክፍያ የማይከፍልበት ህጋዊ ምክንያት የለበትም በማለት ተከሳሽ ከሳሽ በክሱ የጠየቀውን ገንዘብ ክስ በተመሠረተበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

4. አመልካች ግንቦት 28 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አማካሪ መሃንድስ ሳይወስን የተደረገው የዋጋ ንረት ስምምነት መሠረት የተከፈለው ክፍያና ለተጨማሪ ሥራ የተከፈለው ክፍያ የፋይናንስን ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ ተጠሪ ከቀረበው ጥያቄ ጋር ተቻችሎ ቀሪው ተራፊው እንዲመለስልን ያቀረብነው ጥያቄ አላግባብ ውድቅ ተደርጎብናል፡፡ ተጠሪና አመልካች የመጨረሻ ርክብክብ ሣያደርጉ የመጨራሻ ክፍያ እንድንከፍል የተወሰነው ውሳኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1757 ድንጋጌን የሚጥስ ነው፡፡ አመልካች ስህተቱን ማረም እንደሚችል ይኸ ሰበር ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም የበታች ፍርድ ቤቶች ማለፋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መስከረም 28 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ አመልካች ለተጠሪ ክፍያ የከፈለው ተጠሪ የሠራው ሥራ ተቆጥሮ፣ ተለክቶና ተረጋግጦ አማካሪ መሀንድሱ ባፀደቀው ክፍያ ሰነድ መሠረት ነው፡፡ አመልካች ያልተሠራ ሥራ የከፈለው ክፍያ

የለም። የዋጋ ንረት ሥምምነቱም አመልካች ስምምነቱን ሰጥቶ የውል ግዴታ የገባበት ነው። ተጠሪ ከህግ አግባብ ውጭ ከአመልካች የተከፈለው ክፍያ ሌላ በመሆኑና አመልካች ያቀረበው ይቻቻልልኝ ጥያቄ የህግ ሥርዓቱን የማያሟላ ሆኖ በመገኘቱ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው። የመጨረሻ ክፍያ የሚፈፀመው የህንፃው የመጨረሻ ርክብክብ ሲደርግ ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበው መከረከሪያ የህግ መሠረት የለውም አመልካች ህንፃዎቹን ተረክቦ እየተጠቀመ ይገኛል። በህንፃ ላይ ለሚከሰት ጉድለት ማስተካከያ የሚሆን የመያዥያ ክፍያ ይዟል። ከዚህ ውጭ የመጨረሻ ክፍያ የመጨረሻ ርክብክብ እስኪደረግ አልከፍልም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የሌለው ስለሆነ ውድቅ ይደረግልኝ፡፡ አመልካች ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት ከግራ ቀኙ የቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የመቻቻልና የመጨረሻ ርክብክብ ካልተፈፀመ የመጨረሻ ክፍያ እንድከፍል አልገደድም የሚል መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ለተጠሪ በክሱ የጠየቀውን ገንዘብ እንድከፍል የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

6. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ህዳር 30 ቀን 2001 ዓ/ም የግንባታ ሥራ ውል ከመዋዋሉ በፊት የግንባታ ዕቃ ላይ በሚፈጠር የዋጋ ግሽበት ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች አሠሪው (አመልካች) የሚሸፍንበት ድንጋጌ በዋናው ውል እንዲካተት ህዳር 19 ቀን 2001 ዓ/ም ጥያቄ አቅርቦ፤ አመልካች ተጠሪ ባቀረበው ሀሳብ የሚስማማ መሆኑን ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በመግለፁ ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም በዋጋ ግሽበት ምክንያት በሚፈጠረው ጭማሪ ላይ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች የጋራ መግባባት ኖሯቸው የግንባታ ሥራ ውሉ የተፈረመ መሆኑን አመልካችና ተጠሪ አልተካካዱም፡፡ የህንፃው አሰሪ የሆነው አመልካች በግንባታ ዋጋ ንረት የሚመጣን ጭማሪ ዋጋ ለመሸፈን ሙሉ ስምምነቱን ከሰጠ በኃላ፣ ስምምነቱን ከመስጠቱ በፊት ያላሟላው ሥርዓት ያለ መሆኑ በኦዲተር በመተቸቱና አመልካች በተጨማሪ ሥራዎች እንዲሠሩ የሥራ ትዕዛዝ ሲሰጥና ክፍያ ሲፈፅም አንድ የአሠራር ጉድለት ያለ መሆኑ በድርጅቱ የበጀት አጠቃቀምና የፋይናንስ አያያዝና አወጣጥ ሥርዓት በመጀመሩ ኦዲተሮች መተቸቱ አመልካችና ተጠሪ ዋናውን የሥራ ውል ከመዋዋላቸው በፊት ባደረጉት የደብዳቤ ልውውጥ የተስማሙበትን የዋጋ ንረት ጭማሪ ክፍያ ስምምነትና በአመልካችና በአማካሪ መሀንዲስ በተሰጠው ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዝ መሠረት ተጠሪ ሥራው የግንባታ ሥራ መጠንና ጥራትና ዋጋ ተረጋግጦ ለሠራው ሥራ የተከፈለውን ገንዘብ ህገ ወጥ የማድረግ ውጤት የሚያስከትል አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው የግንባታ ዕቃዎች የዋጋ ንረት ጭማሪ ክፍያ ስምምነትና ተጠሪ በተሰጠው ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዝ መሠረት ለሠራው ተጨማሪ ሥራ የተከፈለው

ገንዘብ እንዲመለስለት ያቀረበው የመቻቻል ጥያቄ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንፁስ አንቀፅ 1 ገዥ መርህ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3252 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍተብሔር ህግ ቁጥር 3266 ንዑስ ድንጋጌዎች ይዘትና ህጋዊ ውጤት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

7. አመልካች ተጠሪ ግራ ቀኙ ካደረጉት ውል ውጭ በተጭበረበረ ሀሰተኛ የክፍያ ሰነድ ተጠሪ ክፍያ የወሰደ መሆኑን ወይም ተጠሪ በግንባታ ሥራ ውሉና ከውሉ ጋር በአባሪነት በተያያዘው የግንባታ ሥራ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ግንባታውን በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ባለማጠናቀቁና ግንባታው በመዘግየቱ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ኪሣራ ወይም ቅጣት ገንዘብ ያለ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው በቂ የህግና የክስ ምክንያት ያለው የበሰለ የመብት ጥያቄ ሳይኖር ከተጠሪ ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት በማድረግ ለተጠሪ የዋጋ ንረት ጭማሪ ክፍያና የተጨማሪ ሥራ ክፍያ ተጠሪ እንዲመለስ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የፍተብሔር ስነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 236 እና በፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 238 ንዑስ አንቀፅ 2 መስፈርት የማያሟላ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የቀረበውን የመቻቻያ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 30 እና የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት ከተጠሪ የሚጠይቀውን የገንዘብና ተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልስ ኃላፊ የሚሆንበትን ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ኃላፊነት በመግለፅ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አላቀረበም፡፡ በመሆኑም አመልካች አለኝ የሚለውን መብት በፍርድ ለማስወሰን ሕጉ የዘረጋቸውን ሥርዓት ያሟላ ክርክርና የመብት ጥያቄ ያላቀረበ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

8. አመልካች አማካሪ መሀንድሱ ለተጠሪ ያፀደቀለትንና ተጠሪ ክስ ያቀረበበትን የመጨረሻ ክፍያ የህንፃው የመጨረሻ ርክብክብ ከመደረጉ በፊት የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት ያቀረብኩት ክርክር ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል የሰበር አቤቱታና ክርክር አቅርቧል፡፡ ይህንን የአመልካችን ክርክር ህጋዊነት ለመመርመር አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የሥራ ውል ልዩ ሁኔታና የግንባታ ሥራው የሚመራበትን ጠቅላላ ሁኔታ እንደዚሁም ስለ መጨረሻ ርክብክብና የክፍያ አፈፃፀም የተደነገጉትን አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች መመርመር ያስፈልጋል፡፡

9. አመልካች ተጠሪ የገነባቸውን ህንፃዎች ተረክቦ እየተገለገለባቸው መሆኑን ግራ ቀኙ በሥር ፍርድ ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ያሳያል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው ልዩ የግንባታ ሥራ ውል ሁኔታ፣ ለህንፃው ተቋራጭ ለተጠሪ የመጨረሻው ክፍያ የሚከፈለው የህንፃው የመጨረሻ ርክብክብ ከተፈፀመ በኃላ መሆኑን ተስማምተው ስምምነታቸውም በውሉ ልዩ ሁኔታ ውስጥ የተገለፀ መሆኑን በመግለፅ የቀረበው ክርክር

የለም እንደዚሁም አመልካች ህንፃውን በጊዚያዊነት ከተረከበ በኃላ በህንፃው ላይ የሚታይ ጉድለት መኖሩንና በህንፃው ላይ የሚታየውን ጉድለት ለማስተካከል በግንባታ ሥራ ውሉና በግንባታ ሥራዎች ላይ ተፈፃሚነት ባላቸው ደንቦች መሠረት በየወቅቱ ተጠሪ ከሚከፈለው ክፍያ እየቀነሰ በመያዣነት የያዘው የጉድለት ማስተካከያ የመያዥያ ገንዘብ የማይበቃው መሆኑንና ጉደለቱን ለማስተካከል ለተጠሪ ከሚከፈለው የመጨረሻ ክፍያ ክፊሉን ወይም ሙሉን የሚጠይቅ ስለመሆኑ የቀረበው ክርክር የለም፡፡

10. አመልካች ከላይ የተገለፁትን ሁለት መከራከሪያዎች ሳያቀርብ ተጠሪ ህንፃዎቹን ሥራ ለማጠናቀቅና ህንፃዎች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የሥራው የማጠናቀቂያ ሥራዎች መጠንና ጥራት ዋጋ በአማካሪ መሀንድሱ ተረጋግጦ የፀደቀውን ክፍያ አልከፍልም በማለት ይዞ የሚቆይበት በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር ክፍያ ለመፈፀም ተጠሪ የሠራቸው ሥራዎች አመልካች በመደበው አማካሪ መሀንድስ መመርመር መለካትና በሥራው የሚከፈለው ነጠላዎች ጥቅል ዋጋ በአማካሪ መሀንድስ ፀድቆ መቅረቡ አስፈላጊ ሁኔታ መሆኑን አመልካችና ተጠሪ ከተዋዋሉት የግንባታ ስራ ውል እና ግራ ቀኙ ከሚያቀርቡት ክርክር የተረዳ መሆኑን ገልፆ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔው አስፍሮታል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ተጠሪ ሥራውን ከሠራ በኃላ ክፍያ ለመፈፀም አስፈላጊ የሆነውን የምርመራና የማረጋገጡ ሥራ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ መፈፀምና ክፍያውም የምርመራና የማረጋገጡ ውጤት እንዲታወቅ መፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3268 ድንጋጌዎች እና የመሠረተ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር 1996 ዓ/ም አሻሽሎ የወጣውን የመንግስት ግንባታ ሥራ አፈፃፀም መምሪያ አንቀጽ 8 በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከላይ ከጠቀስናቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ አመልካች የመጨረሻ ርክብክብ ሣይደረግ ለተጠሪ የመጨረሻ ክፍያ የመፈፀም ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

11. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ተጠሪ የገነባቸውን ህንፃዎች ለተጠሪ አስረክቦ ህንፃዎቹ በተጠሪ ቁጥጥርና ይዞታ ስር ሆነው እየተገለገለባቸው እንደሚገኝ ተረጋግጧል አመልካች ከተጠሪ ጋር የመጨረሻ እርክብክብ ለማድረግ ያላስቻለው በቂ ምክንያት ያለ ስለ መሆኑ በክርክሩ አልገለፀም፡፡ የህንፃው የመጨረሻ ርክብክብ ተጠሪ ስለሚፈልገው የሚፈፀም ተግባር አይደለም፡፡ አመልካች የመጨረሻ እርክብክብ በማድረግ ሊስተካከል ይገባቸዋል የሚላቸውን ጉድለቶች ለተጠሪ የማሳወቅ እንዲስተካከሉ ማድረግና ርክብክቡን በህጉ መሠረት ለመፈፀም ፍቃደኛና ዝግጁ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ ተጠሪ በገነባቸው ህንፃዎች ላይ ለሚከሰት የአሠራር ጉድለት አመልካች ህንፃዎቹን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አስር ዓመት መድህንና ኃላፊ እንደሚሆን በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3282 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል ይህም አመልካች የመጨረሻ ርክብክብ ለመፈፀም ያጋጠሙትን ችግሮች ሣያስረዳ የመጨረሻ ርክብክብ ሣይደረግ

ቀሪ ክፍያ አልከፍልም የሚለው ክርክር ህጋዊ ዕውቅናና ውጤት ከተሰጠው በአራቱ የሚገኙ የሥራ ተቋራጮች ከባንክ ወይም በሌላ መንገድ ያገኙትን ካፒታል በመጠቀም ለሠሩት ሥራ ወዲያውኑ ክፍያ እንዳያገኙ የማያደርግና ይህም በምላሹ በህንፃ ተቋራጩና በኮንስትራክሽን እንዱስትሪ ላይ የፋይናንስና የኢንቨስትመንት እጥረት እንዲከሰት የሚያደርግ ይሆናል፡፡ የሥራ ተቋራጩ በሠራው ህንፃ ላይ የተከሰተ እርግጠኛ የአሠራር ጉድለት በሌለበት ሁኔታ ወደ ፊት የሚታይና የሚከሰት የአሠራር ጉድለት ሊኖር ይችላል በሚል መነሻና ግምት ሥራ ተቋራጮች ለሠሩት ሥራ የመጨረሻ ክፍያ የማግኘት መብት አግባብ መከልከል ገንዘቡ በህንፃ አሠሪዎች በእጅ ያለ በቂ ምክንያት ታስሮ እንዲቀመጥ የሚያደርግና የህንፃ ተቋራጩን በፍትሐብሔር ጉዳይ ማንም ሰው ኃላፊ ነው ተብሎ ያለመገመት /presumption of non liablity) መሠረታዊ መርህ የሚጥስ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የመጨረሻ ርክብክብ ያልተፈፀመ በመሆኑ ተጠሪ የጠየቀውን ክፍያ መክፈል የለብኝም ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በትዕዛዝ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

12. አመልካች ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57049 የሰጠውን የሕግ ትርጉም በመጥቀስና ለሥር ፍርድ ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ ሆኖም በሰበር መዝገብ ቁጥር 57049 የተነሳው የተረጋገጡ የፍሬ ጉዳይና የህግ ጭብጦች ከዚህ መዝገብ ጋር ተመሣሣይነት የሌላቸው ናቸው በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57049 የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመግለፅ የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በትዕዛዝ ማፅናቱ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከላይ በዝርዝር ለገለፅናቸው ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ለሠራው ሥራ መክፈል የሚገባውንና በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ይህ ፍርድ ቤት ግንቦት 29 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ የተነሳ መሆኑ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ.82725
ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ከበደ ተሰማ } ጠበቃ አቶ ሰለሞን ሐብቴ ቀረቡ

2. ወ/ሮ መሰሉ አበበ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ፀሐይነሽ ገ/አምላክ - ቀረቡ

2. አቶ መኮንን ኃ/ጽዮን - አልቀረቡም

***መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡***

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የይርጋ ድንጋጌዎችን አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ለይርጋ ድንጋጌዎች አፈፃፀም መነሻ የሆኑት የፍሬ-ነገር ክርክሮች ሁለቱም ወገኖች እንደ ክርክር አቀጣጫቸው በስር ፍ/ቤቶች አቅርበዋል፡፡

እኛም በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ በሥር ፍ/ቤቶች ሲከራከሩ በክርክር ሂደት በስር ፍ/ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች በመነሳት ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የይርጋ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የድንጋጌዎችን አፈፃፀም እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የጉዳዩ መነሻ የሆነው ክስ በአሁን ተጠሪዎች በፌዴራል የከፍተኛ ፍ/ቤት አማካኝነት የቀረበው ሲሆን፤ ይዘቱም በድንገት ወደ ኤርትራ ስወጣ በአ/አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 20 በቤት ቁጥር 2024 በካርታ ቁጥር 12926 የታወቀውን እና በ520 ሜትር ካሬ ስፋት በ175 ሜትር ካሬ ላይ ያረፈውን ባለ ቤዝመንት ባለ አንድ ፎቅ ከዕቃው ጋር ለአሁን 1ኛ አመልካች በውክልና አስረክቤ ከአገር ከወጣሁ በኋላ በግንቦት 01/2001 መንግስት ባወጣው መመሪያ መሰረት ወደ አገር ተመልሼ እንዲያስረክበኝ ብጠይቀው ንብረቱን ለመሸጥ ያስገደደው ሁኔታ ሳይኖር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2208 እና 2211 ከተደነገገው ውጭ ሚስቱ ለሆኑት ለአሁን 2ኛ አመልካች

በብር 380,000.00 /ሶስት መቶ ሰማንያ ሺ.ህ ብር/ በሆነ ዋጋ በሽያጭ ስም የእራሳቸው የጋራ ያደረጉ በመሆኑና እንደገናም ሁለቱም በአንድነት ሆነው ጥር 19 ቀን 2000 ዓ.ም በብር 3,300,000.00 /ሶስት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺ.ህ ብር/ በስር ፍ/ቤት ሁለተኛ ጣልቃ ገብ ለሆኑት ለወ/ሮ ደስታ ተመስገን ሸጠው የተጠቀሙ ስለሆነ ሁለቱም የሽያጭ ውሎች ፈራሽ ሆነው ንብረቱ ካስገኘው የኪራይ አላባ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካቾችም ለቀረበባቸው ክስ በመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ክርክርነት ካቀረቧቸው የመከራከሪያ ነጥቦች አንዱ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የይርጋ ክርክር ሲሆን ይዘቱም ከሀገር እንዲወጡ ባደረገው መመሪያ መሰረት ንብረቱ በወከላቸው በአሁን 1ኛ አመልካች አማካኝነት የተሰጠው ጥቅምት 01 ቀን 2003 ዓ.ም ነው፡፡ በነበረን የስልክ ግንኙነት እንዲያውቁትም ተደርጓል፡፡ የውል ይፍረስልኝ ክስ የቀረበውም ታህሳስ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ስለሆነ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው የሚለውን በመጥቀስ የቀረበ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ከዚህ በላይ በተመለከተው የይርጋ ጉዳይ ላይ ተመርኩዞ

1ኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁን አመልካች በተሰጣቸው ልዩ የውክልና ስልጣን መሰረት ንብረቱን የሸጡት ጥቅምት 01 ቀን 1993 ዓ.ም ሆኖ እያለ ይህንኑ የሽያጭ ውል ለማስፈረስ ክስ የቀረበው ደግሞ ታህሳስ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ስለሆነ በሁለቱ ጊዜያቶች መካከል ያለፈው ጊዜ ሲሰላ የ10 ዓመት ጊዜ አልፎታል 1ኛ ተከሣሽ የፈፀመውን የሽያጭ ድርጊት በመቃወም የሽያጭ ውሉን ለማስፈረስ የሚቀርበው ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 መሠረት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ሲገባው ይህ ጊዜ ካለፈ በኃላ የቀረበ ክስ ሆኖ ስለተገኘ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ብይን ሰጥቶበታል፡፡

ይህንኑ ብይን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የሥር ፍ/ቤት ስለይርጋው ክርክር የሰጠውን ዳኝነት አግባብነት በሚመለከት ጉዳዩን መርምሮ፤

1ኛ አመልካች ስለ ቤቱ ጉዳይ ልዩ የውክልና ስልጣን የተሰጠው ለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም ሆኖም በዚህ የውክልና ስልጣን መሠረት ተክቶ ቤቱን የሸጡ መሆኑ ከሣሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ወደ ኢትዮጵያ ሐገር ከመግባታቸው በፊት ሻጩ ያሣወቋቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ቤቱ መሸጡን ያወቁት ኢት/ያ ውስጥ ከገቡ በኃላ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ስለመሆኑ በማስረጃ ያልተደገፈ እና ማስተባበያ ያልቀረበበት ስለሆነ ቤቶቹን መሸጡን ካወቀበት፤ ወደ ሀገር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ

እስከተመሠረበት እስከ ታህሣስ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲሰላ 6 ወር ብቻ መሆኑን 10 ዓመት ይቀርና 1 ዓመት የሞላው አይደለም ስለዚህ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ሽሮ በቀሪዎች ክርክሮች ላይ አስፈላጊውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት መዝገቡን በመመለስ ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውም ይኸው የጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ በጉዳዩ ላይ የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ሲሆን የዚሁኑ ፍርድ አግባብነት ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ባቀረቡት የጽሑፍ ክርክር እና ከላይ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ከተሰጠው ዳኝነት ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ በሆነው ክሣቸው ላይ ለክሱ መሠረት አድርገው ያቀረቡት የክስ ምክንያትና ለጠየቁት ዳኝነት እንደ ክሣቸው በማስረጃ ቢያረጋገጡ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ክፍል በውክልና ሕግ ሥር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2187 እና 2188 የተመለከተውን ስለመሆናቸው በክሣቸው ዝርዝር የጠቀሷቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2208 እና 2211 ጠቅሰው ማቅረባቸው አስረጂ ከመሆኑም በላይ ተወካዩ ከቤቱ ትክክለኛ ዋጋ በታች ለሚስታቸው ሸጠው የጋራ ተጠቃሚ ከሆኑ በኃላ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ዋጋ መልሶ ለሶስተኛ ወገን ሸጠዋል የሚለው የፍሬ ነገር ክርክራቸውም አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም በግራ ቀኙ መካከል ለተነሣው የይርጋ ክርክር ጉዳይ አግባብነት እና ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ በውክልና ሕግ የተመለከተው የፍ/ሥ/ሕ/ቁ. 2187 እንጂ ውሎች በጠቅላላው በተመለከተው የሕግ ክፍል የሚገኘው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1845 ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህም ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ድንጋጌ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2187 ድንጋጌ መሠረት ተወካዩ የጥቅም ግጭት ባለበት አኳኃን የፈፀመውን ተግባር ለማስፈረስ ወካዩ ይኸው ድርጊት መፈፀሙን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ተመልክቷል፤

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የቀረበለትን የይግባኝ ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት በሚሰጥበት ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ የክርክር ሂደት በሙግት የክርክር ደረጃ በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች ከቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ የተረጋገጠበትን ፍሬ ነገሮች ለይቶ ለማውጣት በተሰጠው ማስረጃን የመመዘንና የማስረጃን የማስረዳት ክብደት የመለካት ዳኝነታዊ ተግባሩ ተጠቅሞ የአሁን ተጠሪ ቤታቸው የተሸጠ መሆኑን መቼ አወቁ መቼ ተረዱ? የሚለውን ለድንጋጌው አፈፃፀም መነሻ የሆነው የፍሬ ጉዳይ ያረጋገጠው መሆኑን ተረድተናል፤

በዚህ ረገድ የአሁን አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ እንዲታረምላቸው ያቀረቡት እና የጠየቁት ክርክር እና ዳኝነት ከላይ በተመለከተው የፍሬ ነገር እና ማስረጃ ጉዳይ ላይ ያተኮረ እንጂ ከህግ ጥያቄ ጋር የተገናኘ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ሊታገድ የሚችል አይደለም በሚል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፤

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ77515 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ፀንቷል፡፡
2. ስለይርጋ ጉዳይ የአሁን አመልካች ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት ያለው ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤
3. የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፤

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፤

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ል/ተ**

የሰ/መ/ቁ.99634

ሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ ተስፋዓለም አረፋ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ አማረች ጉደታ } ጠበቃ እዮኤል ጀረነ -ቀረቡ

2. አቶ ጫላ ኃይሌ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ።

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 181329 ሚያዝያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135064 ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ በአፈፃፀም የተሰጠን ትእዛዝ ህጋዊነት የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ የአፈፃፀም ከሳሽ ፣አመልካች የአፈፃፀም ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

1. የፍርድ አፈፃፀም ሂደቱ ወደ ፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ከተመራ በኃላ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ፍርዱን ለማስፈጸም እየተከተለ ያለው ሂደት ተገቢነት የሌለው ስለሆነ፣ሂደቱ እንዲለወጥ ትእዛዝ ይሰጥልን በማለት ለሥር ፍርድ ቤት አመልካች /የፍርድ ባለዕዳ/ ጥያቄ አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ሚያዝያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ትአዛዝ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ አፅንቶታል፡፡
2. አመልካች ሚያዝያ 3 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ውሉ ፈርሶ አመልካችና ተጠሪዎች ወደነበርንበት እንድንመለስ ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ይህም ውሣኔ የተሰጠው እኔ ድርጅቱን ከተረከብኩበት ሚያዝያ 24 ቀን 1998 ወዲህ ልዩ ልዩ ንብረቶችን በቦታው

በማስፈር ምክንያት ነው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሚያዚያ 24 ቀን 1995 በቦታው ላይ ያሰፈርኩትን ንብረት ዘርዝሬ እንዳቀርብ ካደረገ በኃላ በቦታው ላይ አመልካች አፍርቻለሁ በማለት የጠየቅሁትን ንብረት በተመለከተ አዲስ ክስ አቅርቤ እንድጠይቅ የሰጠው ትእዛዝ የሰበር ችሎት የሰጠውን ውሣኔ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንድታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በእኛና በአመልካች መካከል ተደርጎ የነበረው የድርጅት ሽያጭ ውል ከማድረጋችን በፊት ወደ ነበርንበት ሁኔታ እንድንመለስ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡አመልካች ድርጅቱን ከእኛ የተረከበው ድርጅት እንጂ ባዶ ቦታ አይደለም ስለዚህ ፍርድ አፈፃፀም መምሪያ አመልካች ድርጅቱን ከእኛ ከተረከበ በኃላ ያፈራው ንብረት የሌለ መሆኑን በማረጋገጥ ድርጅቱን ለእኛ እንዲያስረክብ የተሰጠው ትእዛዝ በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ መሠረት ያደረገና የሕግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ የሰበር አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግልን በማለት አመልክተዋል፡፡አመልካች ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ ይኸ ከሰበር ችሎት የሰጠውን ውሣኔና አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
4. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪዎች ሻጭ አመልካች ገዥ በመሆን ሚያዚያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም የቡልኬት ማምረቻ ድርጅት ውል ተዋውለው የነበረ መሆኑንና በአንደኛ ተጠሪ ክስ አቅራቢነት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152619 ህዳር 12 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ፍርድና ውሣኔ የድርጅት ሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ስም የሚገኘውን የሲሚንቶ ውጤቶች አምርቶ መሸጫ የንግድ ድርጅት ከሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት ከነበረበት ሁኔታ በአንደኛ ተጠሪ/ከሳሽ/ እንዲያስረክብ ከሳሽ አንደኛ ተጠሪ በቅድሚያ ክፍያ የወሰዱትን ብር 10,000/አሥር ሺ ብር / እስከ ቀረበበት ሀምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ግምት ወለድ ጋር ለተከሳሽ / አመልካች/ እንዲከፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
5. ከዚህ በኃላ አንደኛ ተጠሪ ድርጅቱን ከቦታው ላይ ካለው አጥርና ቤት ድረስ እንድረከብ ትእዛዝ ይሰጥልኝ የሚል ጥያቄ አቅርባ ውሉ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ይመለሱ ተባለ እንጅ ከሳሽ በተከሳሽ የተመራን ንብረት ሊረከቡ አይገባም በማለት በመዝገብ ቁጥር 152619 የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የፌዴራል የመጀሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት በተከሳሽ /በአሁን አመልካች/ ጥያቄ አቅራቢነት፣አመልካች ሚያዚያ 24 ቀን 1998 በተደረገው ውል የገዛው የድርጅት ቦታ

እንጅ ንብረት የሌለበት በመሆኑ ውሣኔውን በዚህ መልኩ እንዲፈፅም በማለት ታህሣሥ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

6. የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት አንደኛ ተጠሪ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው፣የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በመዝገብ ቁጥር 108282 ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በማፅናቱ አንደኛ ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች፡፡ይህ የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 72262 ሀምሌ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ፍርድ ሰጥቷል፡፡ይህ የሰበር ችሎት በሰጠው ፍርድ የሥር ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብት /አንደኛ ተጠሪን/ ክርክር ሣይሰማ ታህሣሥ 18 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝ በማረም ታህሣሥ 24 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን የመጀመሪያ ጭብጥ አድርጎ በመያዝ ፍርድ ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ከሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ የያዘውን ንብረት የማስረከብ ግዴታ ያለበት መሆኑንና ሌሎችን ጉዳዩች በተመለከተ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 392/1/ መሠረት ማዘዝ እንደሚገባቸው ገልፃ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡትን የአፈፃፀም ትእዛዝ ሽሮታል፡፡

7. ከዚህ በኃላ አፈፃፀሙን የቀጠለው የሥር ፍርድ ቤትና ፍርዱን የሚያስፈፅመው የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152619 የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 108282 ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ በመሻር የአሁኑ አመልካች /ተጠሪ/ ለአመልካች ለማስረከብ የሚገደዱት ከሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት በሽያጭ ውል ምክንያት የያዙትን ንብረት ነው በማለት በመዝገብ ቁጥር 72262 ሀምሌ 2 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት አጣርቶ አመልካች ለተጠሪዎች ቦታ ብቻ ሣይሆን በቦታው ላይ ያለውን ንብረት እንዲያስረክብና አመልካች ሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በቦታው ላይ አፍርቻለሁ የሚለውን ንብረት ውሃና መብራት ለድርጅቱ ወጭ አውጥቼ አስገብቻለሁ የሚሉትን በተመለከተ በሌላ መንገድ ይጠይቁ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

8. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የድርጅት ሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ በፍርድ ተወስኗል፡፡አመልካች የገዛሁት ባዶ ቦታ ስለሆነ እንድመልስ የምገደደው ባዶ ቦታ መሆን አለበት በማለት ጠይቆ ፣ይህንን ጥያቄውን የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ታህሣሥ 24 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች በሽያጭ ያስረከብኩትን ድርጅትና ንብረት እንድረከብ ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበችውን ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ በማድረግ የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በዚህ ሰበር ችሎት ተሽሮ አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች የሸጠችውን ድርጅትና ንብረት የመረከብ መብት ያላት

መሆኑ ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡ከዚህ አንፃር አመልካች በቦታው ላይ በራሱ ወጭ ያፈራሁት ንብረት አለ በማለት የሚከራከር ቢሆንም፣ይህ የአመልካች ክርክር ጥያቄ በፍርድ ባለመብቷ አንደኛ ተጠሪ የታመነ አይደለም፡፡

9. አመልካች ድርጅቱን ሚያዚያ 24 ቀን 1998 ከተረከበ በኃላ ድርጅቱ ውሃ መብራት ለማስገባት ያወጣው ወጭ አለ ወይስ የለም?አመልካች ድርጅቱን ከተረከበ በኃላ በገንዘቡ የሠራው የግንባታ ሥራ አለ ወይስ የለም?አመልካች የሠራው የአጥርና የቤት ግንባታ ሥራ አለ ቢባል በአመልካች የተሠሩ ሥራዎች በወቅቱ በነበረው የግንባታ ዋጋ ምን ያህል ያወጣሉ?የሚሉት ጭብጦች በአፈፃፀም ሂደት በተደረገው ማጣራት ግልፅ የሆነ ምላሽ ለማግኘት የማይቻል በሆነ ጊዜና እነዚህ ጭብጦች የግራ ቀኙን ሙሉ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ ሊወሰኑ የሚገባቸው ሆነው አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ቢያገኛቸው አመልካች ቦታው ላይ ካለው ንብረት ጋር ድርጅቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ ትእዛዝ በመስጠት የፍርድ ባለዕዳው የፍርድ ባለመብት ከተረከባቸው ንብረት ውስጥ ሚያዚያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በኃላ በአመልካች ወጭ ያወጣበትና የተሠራ ነው የሚለውን ራሱን የቻለ ክስ አቅርቦ እንድጠይቅ የሰጠው ትእዛዝ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር.392 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መሠረታዊ ዓላማ ያገናዘበ የአፈፃፀም ትእዛዝ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. አመልካች ድርጅቱን ከተረከበ በኃላ ለመብራትና ለውሃ አውጥቻለሁ ያለው ወጭ ሠርቻለሁ የሚለው ተጨማሪ ግንባታ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ የማያስለውጥ ወይም የፍርዱን ተፈፃሚነት የሚያስቀር ምክንያት አይደለም በአንፃሩ ውሉ ከመፍረሱ ወይም ከመሰረዙ በፊት የተነሳ ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰው ንብረቱን ለውጦ ወይም በዚሁ ላይ ወጭ አድርጎ እንደሆነ ከዚህ መለዋወጥ ወይም ወጭ የተነሳ ያሉት መብቶች ወይም ግዴታዎች በዚህ ሕግ አላግባብ በመበልፀግ በሚመለከተው ምዕራፍ ውስጥ በተወሰኑት ድንጋጌዎች መሠረት የሚመራ መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1818 በግልፅ ተደንግጓል፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትእዛዝ አመልካች ውሉ ፈርሶ ተጠሪዎች ድርጅቱን በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት ሲረከቡ፣እሱ ድርጅቱን ሚያዝያ 24 ቀን 1998 ሲረከብ ያልነበረ ንብረት ወይም በአመልካች ወጭ መብራትና ውሃ የገባ ተጠሪዎች አላግባብ የበለፀጉ መሆኑን በዝርዝር ገልፆ መብቱን እንዲጠይቅ የሚያመላክትና ውሉ ፈራሽ በመሆኑ አመልካች በሽያጭ ውል መነሻ የተረከበውን ድርጅትና ንብረት እንዲፈፅም የሚያስገደድ ትእዛዝ በመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 392 ንዑስ አንቀፅ 1 መሥፈርት የሚያሟላ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትእዛዝና ውሣኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

# ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 181329 ሚያዚያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135064 ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ይህ ውሣኔ አመልካች ተጠሪዎች በአፈፃፀም በተረከቡት ድርጅት ላይ አውጥቸዋለሁ የሚለውን ወጭና ተጠሪዎች አላግባብ በልፅገዋል የሚልበትን ምክንያት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1818 እና ለሎች አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ጥያቄ ከማቅረብ የሚገድበው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ብ**

የሰ/መ/ቁ. 97021

ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡-ተሻገር ገብረሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካች**፡-መርዕድ ታደሰ ገብረመድህን ህንጻ ስራ ተቋራጭ - ጠበቃ ጸጋዬ አሰፋ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡-ኦክስፎርድ አመልጌትድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ ጠበቃ ታረቀኝ ተፈራ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረበው በፍርድ ባለመብትነት ተሰይሞ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ እና በፍርድ ባለዕዳነት ተሰይሞ በነበረው የአሁኑ አመልካች መካከል የነበረውን የፍርድ አፈጻጸም ክርክር የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕግ አግባብ የተሰጠብኝ እና የምፈጽመው የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የለም በማለት በፍርድ ባለዕዳነት ተሰይሞ በነበረው የአሁኑ አመልካች ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ ባለዕዳው በግልግል ዳኝነት ውሳኔው መሰረት ፈጽሞ እንዲቀርብ የሰጠው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አሰሪ በሆነው የአሁኑ ተጠሪ እና የስራ ተቋራጭ በሆነው የአሁኑ አመልካች መካከል በታህሳስ ወር 2004 ዓ.ም በተደረገው የጫማ ማምረቻ ፋብሪካ ህንጻ የግንባታ ውል መሰረት በአሰሪው በአማካሪ መሀንዲስነት የተሰየሙት እና በገላጋይ ዳኝነት ጭምር እንዲያለግሉ በውሉ ተመርጠዋል የተባሉት ግለሰብ የስራ ተቋራጩ በውሉ መሰረት ባለመፈጸሙ ምክንያት አድርሶብኛል ላለው ጉዳት ተቋራጩ በድምሩ ብር 14,391,813.61 (አስራ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሶስት ከስድሳ አንድ ሳንቲም) ካሳ እንዲከፍለው ለማስወሰን አሰሪው ያቀረበውን ክስ የተከሳሽ ስራ አስኪያጅ መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነም በሚል አማካሪ መሀንዲሱ ጉዳዩን ተቋራጩ በሌለበት ከተመለከተ በኃላ

1. ተቋራጩ ካከናወነው የስራ መጠን በላይ በእላፊ የወሰደውን ገንዘብ ብር 691,625.56/ ስድስት መቶ ዘጠና አንድ ሺ ስድስት መቶ ሃያ አምስት ከሀምሳ ስድስት ሳንቲም/
2. ተቋራጩ ለፈጸመው የውል አፈጻጸም መዘግየት በውሉ መሰረት ኪሳራ እና የገደብ መቀጫ ብር 1,287,692.80 / አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሰባት ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከ80/100
3. ተቋራጩ ሳያጠናቅቅ የቀረውን ስራ በሌላ ተቋራጭ ለማሰራት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ወጪ ብር 1,072,495.25
4. ተቋራጩ ስራውን በወቅቱ ቢያጠናቅቅ ኖሮ አሰሪው ሊያገኝ ይችል የነበረውን የታጣ ገቢ ብር 1,701,000

በድምሩ ብር 4,752,813.61 (አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሶስት ከስልሳ አንድ ሳንቲም) ክሱ ከቀረበበት ከ06/12/2005 ዓ.ም.ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ እና ከ10% የጠበቃ አበል ጋር የስራ ተቋራጩ ለአሰሪው እንዲከፍል በ09/02/2006 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣ተጠሪው በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲፈጸምለት ያቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ መሆኑን፣አመልካች በበኩሉ አማካሪ መሀንዲሱ ውሳኔ የተሰጠበትን ዓይነት ጉዳዮች አይቶ ለመወሰን በግንባታ ውሉ ላይ በገላጋይ ዳኝነት ያልተመረጠ በመሆኑ በግራ ቀኙ ስምምነት በገላጋይነት ያልተሰየመ ሰው የሰጠውን ውሳኔ ለመፈጸም እንደማይገደድ እና ውሳኔው ተሰጠ የተባለውም የስራ ተቋራጩ ሳይጠራ እንደሆነ በመግለጽ የአፈጻጸም አቤቱታው ውድቅ ተደርጎ መዝገቡ እንዲዘጋ መከራከሩን፣ፍርድ ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኃላ የፍርድ ባለዕዳው ያቀረበው ክርክር ሊስተናገድ የሚገባው በስረ ነገሩ ክርክር ጉዳይ ላይ እንጂ በአፈጻጸም ደረጃ አለመሆኑን ገልጾ ክርክሩን ውድቅ በማድረግ እንደፍርዱ ፈጽሞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱን እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይግባኙን ዘግቶ ማሰናበቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መሰረት አማካሪ መሀንዲሱ በሁለቱ ወገኖች በገላጋይ ዳኝነት ሳይመረጥ ሰጠ በተባለው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም የተሰጠው ትዕዛዝ ከሕግ እና ከውል ስምምነታችን ውጪ ነው በሚል በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ከመሆኑም በላይ በ20/06/2007 ዓ.ም በተለዩት ነጥቦች ላይ በ29/7/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቃል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ሊቋቋሙ እንደሚችሉ በአንቀጽ 37 (1) እና 78 (4) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 79 (1) ስር የተደነገገ ሲሆን ከዝርዝር ሕጎች መካከልም በሌላ አኳኃን እንዲፈጸም በሕግ ካልተገለጸ ክስን ተቀብሎ ለማከራከር ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 4 ይደነግጋል፡፡ይህ ማለት ግን በሰዎች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱ አለመግባባቶች ከፍርድ ቤቶች ውጪ በሌላ አግባብ ሊስተናገዱ እና እልባት ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ አይኖርም ማለት አይደለም፡፡ይልቁንም ግልጽ የሕግ ክልከላ ካለባቸው ጉዳዩች ውጪ ሰዎች በመካከላቸው የተነሱ ወይም የሚነሱ አለመግባባቶች ከፍርድ ቤቶች ውጪ እልባት እንዲያገኙ በስምምነት ሊወስኑ ይችላሉ፡፡በዚህ አግባብ ከሚደረጉ ስምምነቶች መካከል አንዱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3325 ስር ትርጉም የተሰጠው ክርክርን በዘመድ ዳኛ የመጨረስ ስምምነት ነው፡፡የዚህ ዓይነቱ ስምምነት አፈጻጸምም ከቁጥር 3326 እስከ 3346 ባሉት ድንጋጌዎች የተመለከተ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች ከተመለከቱት መሰረታዊ መርሆዎች እና መብቶች አንዱ እና ዋነኛው  የተገላጋዮቹ የየራሳቸውን የዘመድ ዳኛ የመምረጥ መብት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ በመካከላቸው ካቋቋሙት የግንባታ ውል አፈጻጸም የሚመነጩ አለመግባባቶችን በዘመድ ዳኛ ለመጨረስ በግንባታ ውሉ በአንቀጽ 38 ስር ስምምነት ማድረጋቸው ያልተካደ ጉዳይ ሲሆን አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የአንቀጹ አነጋገር አተረጓጎም፣በተለይም የአንቀጹ አነጋገር በአሰሪው የተሰየመው አማካሪ መሀንዲስ በአማካሪ መሀንዲስነቱ ከሚያከናውናቸው መደበኛ የምህንድስና ሙያ ተግባራት በተጨማሪ የዘመድ ዳኛ ስልጣን ጭምር እንዲኖረው ግራ ቀኙ ስምምነት ማድረጋቸውን የሚያመለክት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ዓቢይ ነጥብ ነው፡፡

“አለመግባባትን በግልግል ስለመፍታት” የሚል ርዕስ የተሰጠው የውሉ አንቀጽ 38 “ከውሉ በመነጨ ወይም ውሉን በማስተካከል ምክንያት ወይም ማንኛውንም ዓይነት አለመግባባቶች ወይም ልዩነቶች በሚከሰትበት ወቅት በስራው አፈጻጸም ሂደት ወቅት ስራው ከተጠናቀቀ በኃላ ወይም ከተቋረጠ በኃላ ወይም ውል የማፍረስ ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት በመሐንዲሱ አማካኝነት ከሁለቱ አካላት በአንዱ የጽሁፍ ማስታወቂያ በደረሰ በ21 ቀናት ውስጥ ሁኔታውን ለመፍታት ይሞከራል፡፡ውሳኔውንም ለቀጣሪው እና ለኮንትራክተሩ የሚያሳውቅ ይሆናል፡፡

ይህ ውሳኔ በቀጣሪው እና በኮንትራክተሩ መሀል ያለው አለመግባባት የመጨረሻ ውሳኔ ሲሆን በውሳኔው መሰረት ከውሳኔው በኃላ ሌላ የገላጋይ ሂደትን ቢፈልጉም እንኳን ኮንትራክተሩም ሆነ ቀጣሪው ስራውን ማስፈጸም መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡

አማካሪው ውሳኔውን ለቀጣሪው በጽሁፍ ካሳወቀ በኃላ እና ኮንትራክተሩም ሆነ ቀጣሪው ማስታወቂያ በደረሳቸው በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኝ ካልጠየቁ የተወሰነው ውሳኔ የመጨረሻ እና በቀጣሪና በኮንትራክተሩ መካከል የጸና ይሆናል፡፡መሀንዲሱ ይህንን ውሳኔ በተጠየቀ በ21 ቀናት ውስጥ ያላሳወቀ እንደሆነ ወይም ኮንትራክተሩም ሆነ ቀጣሪው በውሳኔው ያልተስማሙ ከሆነ ቀጣሪው ወይም ኮንትራክተሩ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሳቸው ወይም የመጀመሪያው 90 ቀናት ካለፉ በኃላ ጉዳዩ ወይም ጉዳዮቹ ለሚመለከተው ኮሚቴ በመምራት መፍትሄ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ኮሚቴው አምስት አባላትን የያዘ ሲሆን እያንዳንዱ ወገን ሁለት ሁለት አባላትን ያቀርባል፡፡ሊቀመንበር ከሁለቱ ወገኖች መሀል በስምምነት የሚሾም ይሆናል፡፡የዚህ ኮሚቴ ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሆን ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ለውሳኔው ተገዢ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡"በሚል የሚነበብ ሲሆን "Settlement of Disputes Arbitration" የሚል ርዕስ ያለው የአንቀጹ የእንግሊዝኛ አነጋገርም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው፡፡

እንደሚታየው የድንጋጌው አነጋገር በአንድ በኩል ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት በአማካሪ መሀንዲሱ እንዲወሰን የተስማሙት በስራው አፈጻጸም ሂደት ወይም ስራው ከተጠናቀቀ በኃላ ወይም ከተቋረጠ በኃላ ወይም ውል የማፍረስ ሁኔታ ከተከሰተ በኃላ የሚነሳ ማናቸውም ዓይነት አለመግባባት እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን በሌላ በኩል ግን አለመግባባቶችን አይቶ የሚወስን በግራ ቀኙ በጋራ የሚመረጥ የግልግል ኮሚቴ ስለመኖሩ በውሉ ተገልጸ መገኘቱ፣እንዲሁም ከአማካሪ መሀንዲሱ ውሳኔ በኃላ "...ሌላ የገላጋይ ሂደትን ቢፈልጉም እንኳን ኮንትራክተሩም ሆነ ቀጣሪው ስራውን ማስፈጸም መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡" በሚል የተቀመጠው የውሉ ኃይለ ቃል ግራ ቀኙ የተስማሙበት የአማካሪ መሀንዲሱ ስልጣን የግንባታ ውሉ አፈጻጸም በሂደት ላይ በሚገኝበት ወቅት የሚነሱ እና በዘርፉ በተለመደው አግባብ በአማካሪ መሀንዲስ የሚወሰኑ የምህንድስና ዘርፍ ውሳኔ የሚሹ አለመግባባቶችን መርምሮ በመወሰን የተገደበ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ውለታዎች ግልጽ ባልሆኑ እና የሚያሻሙ በሆነ ጊዜ ደግሞ ለክርክሩ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው በታወቁ እና በፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 1732 እስከ 1739፣እንዲሁም በሌሎች ድንጋጌዎች በተመለከቱት የውል አተረጓጎም መርሆዎች መሰረት ውሉን ውጤት ባለው አግባብ በመተርጎም ነው፡፡አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ አማካሪ መሀንዲስ የግልግል ዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በተመሳሳይ ጉዳይ በመዝገብ ቁጥር 36577 በ16/10/2001 ዓ.ም የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ክርክር ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ በመሰረቱ አስቀድሞ በቀረበለት ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ቀጥለው በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው በሁለቱ ጉዳዮች ለክርክር የቀረቡት የሕግ እና የፍሬ ነገር ነጥቦች ተመሳሳይነት ባላቸው ጊዜ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በተጠቀሰው መዝገብ ቁጥር

36577 አማካሪ መሀንዲሱ የግልግል ዳኝነት ስልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም? የሚለው ነጥብ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ተዋዋዮቹ የውላቸው አካል ካደረጉት የባትኮዳ ደንቦች አንጻር ሲሆን በዚህ መዝገብ በተያዘው ጉዳይ ግን ግራ ቀኙ ስለአማካሪ መሀንዲሱ የስልጣን ወሰን የሚከራከሩት ውላቸውን መሰረት አድርገው በመሆኑ እና የባትኮዳ ደንቦችንም የውላቸው አካል ያላደረጉት በመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 36577 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ለቀረበው ክርክር ተፈጻሚነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ግራ ቀኙ አለመግባባቶች እንዲወሰኑ የተስማሙት በአማካሪ መሀንዲሱ እና በግራ ቀኙ በጋራ በሚመረጥ ኮሚቴ ነው፡፡በአማካሪ መሀንዲሱ የሚሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኙ በጋራ ለሚመረጥ ኮሚቴ በይግባኝ የሚቀርብ ስለመሆኑ ስምምነቱ አያመለክትም፡፡ይልቁንም የአንቀጹ አነጋገር የሚያስገነዝበው ኮሚቴው አለመግባባቶችን አይቶ የሚወስነው በመጀመሪያ ደረጃ ክርክር መሆኑን ነው፡፡ይህም በአንድ በኩል በአሰሪው በተሰየመው አማካሪ መሀንዲስ እና በሌላ በኩል ደግሞ በግራ ቀኙ በጋራ በሚመረጠው ኮሚቴ ታይተው እንዲወሰኑ ግራ ቀኙ የተስማሙት የተለያዩ ጉዳዮችን መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በሌላ አነጋገር የውሉ አንቀጽ 38 አቀራረጽ እና ይዘት ግራ ቀኙ የአማካሪ መሀንዲሱ ስልጣን የግንባታ ውሉ አፈጻጸም በሂደት ላይ በሚገኝበት ወቅት የሚነሱ እና በዘርፉ በተለመደው አግባብ በአማካሪ መሀንዲስ የሚወሰኑ የምህንድስና ዘርፍ ውሳኔ የሚሹ አለመግባባቶች በአሰሪው በተሰየመው አማካሪ መሀንዲስ ታይተው እንዲወሰኑ እና የውል ግንኙነቱ በቀጠለበት ጊዜም ሆነ ከተቋረጠ በኃላ የሚነሱ ሌሎች አለመግባባቶች ግን በግራ ቀኙ በጋራ በሚመረጠው ኮሚቴ ታይተው እንዲወሰኑ መስማማታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡የውሉን አንቀጽ 38 ይዘት በዚህ አግባብ መተርጎሙ ከአንቀጹ ዓላማ እና አነጋገር ጋር ብቻ ሳይሆን ክርክርን በዘመድ ዳኛ የመጨረስ ስምምነትን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ካሉት ድንጋጌዎች ጋርም የሚጣጣም በመሆኑ ተገቢነት ያለው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አማካሪ መሀንዲሱ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች ዓይነት እና ይዘት በግራ ቀኙ ስምምነት መሰረት ለአማካሪ መሀንዲሱ ቀርበው እንዲታዩ የተወሰኑ የምህንድስና ዘርፍ ውሳኔ የሚሹ አለመግባባቶች ሳይሆኑ ይልቁንም ከዚህ ያለፉ እና ከምህንድስና ውጪ የሌላ ዘርፍ ዕውቀትን የሚሹ በግራ ቀኙ በጋራ በሚመረጠው ኮሚቴ ታይተው እንዲወሰኑ ግራ ቀኙ የተስማሙባቸው አለመግባባቶች ናቸው፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዘመድ ዳኛ አለመግባባቶችን አይቶ የመወሰን ስልጣን የሚመነጨው ተገላጋዮቹ በግልጽ እና በማያሻማ ሁኔታ በጽሁፍ ከሚሰጡት ስምምነት ነው፡፡በመሆኑም በውሉ እንዲወስናቸው ከተመለከቱት አለመግባባቶች ዓይነት እና ወሰን በማለፍ እና የዘመድ ዳኛ አድርጎ ባልመረጠው አማካሪ መሀንዲስ ተሰጠ በተባለው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጽም አመልካቹ ሊገደድ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት

አይኖርም፡፡ፍርድ ቤቶች በፍርዱ መሰረት እንዲፈጸም ትዕዛዝ ከመስጠታቸው አስቀድሞ በሕግ አግባብ የተሰጠ የሚፈጸም ውሳኔ መኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 392 (1) ድንጋጌ አነጋገርም ይህንኑ የሚደግፍ ነው፡፡ባልተስማማበት እና ባልመረጠው የዘመድ ዳኛ ተሰጠበት የተባለውን ውሳኔ ለማስለወጥም አመልካች ይግባኝ እንዲያቀርብ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 350 ድንጋጌ ግዴታ አይጥልበትም፡፡

ሲጠቃለል የአመልካቹን ክርክር ውድቅ አድርጎ አመልካች በግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ መሰረት እንዲፈጽም ይገደዳል በማለት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142388 በ23/03/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 95728 በ18/04/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ በግራ ቀኙ ስምምነት እና በሕጉ የተመለከተውን ስርዓት ተከትሎ የተሰጠ ሊፈጸም የሚችል የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ተ**

የሰ/መ/ቁ 103541

ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** ቢውቲ ግሪን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ እንየው ለማ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ቪክስ ሰመር ፍላወር ኃ/የተ/የግ/ማህበር አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 197636 ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 147228 ሰኔ 9 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በውል መሰረት ለተሰራ ስራ ክፍያ እንዲፈፀም ይወሰንልኝ በማለት የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ ከተከሻሽ ጋር ባደረገው የስራ ስምምነት መሰረት ለተከሳሽ የምክር ስራ ለመስራትና ተከሻሽም በወር 4000 ዩሮ /አራት ሺ ዩሮ/ ሊከፍለኝ ተስማምተን እንደአውሮፖዊያን አቆጣጠር 15/10/2011 እስከ 16/01/2012 አገልግሎት ሰጥቻለሁ፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ በውሉ መሰረት መክፈል ያለበትን ክፍያ ከነ ተጨማሪ እሴት ታክስ በወቅቱ በነበረው ምንዛሬ ታስቦ ብር 313,200 /ሶስት መቶ አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ብር/ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቀርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከከሳሽ ጋር ያደረግነው የፅሁፍ ውል የለም፡፡ ውል ነው ተብሎ የቀረበው ሰነድ በሁለት ምስክሮችና በተዋዋይ ወገኖች አልተፈረመም፡፡ የውሉ አለመፈረም ተዋዋይ

ወገኖች ያልተስማሙ መሆናቸውን የሚያመለክት በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

2. የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ ይዞት ከመረመረ በኋላ በግራ ቀኙ መካከል በቃል የተደረገ የማማከር ስምምነት አለ፡፡ በዚህ ስምምነት መሰረት ከሳሽ ሠራተኞችን ቀጥሮ የተከሳሽን እርሻ የማስተዳደር ስራ የሰራ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ከሳሽ በውሉ መሰረት ለሰጠው አገልግሎት ተከሳሽ መክፈል የሚገባውን ገንዘብ፣ ማለትም ከሳሽ በክሱ የገለፀውን የገንዘብ መጠን ተከሳሽ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች ሀምሌ 25 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ የማማከር ውል የለም፡፡ አመልካችና ተጠሪ የማማከር ውል ለመዋዋል በፅሁፍ ረቂቁን ካዘጋጁ በኋላ ባለመስማማታቸው፣ ረቂቁ ሣይፈርም ቀርቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህንን በማለፍ በመካከላቸው በቃል የተደረገ ውል አለ በማለት የሰጠው ውሳኔ እርስ በርሱ የሚቃረን የተጠሪን ምስክሮች ቃል መሰረት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ህዳር 24 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካችና ተጠሪ የተስማሙት በፅሁፍ ሣይሆን በቃል መሆኑን በማስረጃ አስረድተናል፡፡ ቀደም ብለን በቃል ባደረግነው ስምምነት መሰረት ስራዎችን እየሰራን፣ ስምምነቱን ወደ ፅሁፍ ለመቀየር ረቂቅ ውል ተዘጋጅቶ የአመልካች ስራ አስኪያጅ ወደ ኢትዮጵያ ባለመምጣታቸው ረቂቁ ሣይፈረም መቅረቱ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ታህሳስ 23 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቀርቧል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሁፍ ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ከሳሽ /ተጠሪ/ ከአመልካች ጋር በቃል ባደረገው የምክር ግልጋሎት የመሰጠን የስራ ውል መሰረት ከሳሽ /ተጠሪ/ የሰራው ስራ ተከሳሽ ክፍያ ይፈፀም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የማማከር ስራ ውል በቃል ተዋውሎ በጉራጌ ዞን በሚገኘው የአመልካች እርሻ ቦታ የመገኘት የማማከር ስራውን የሚሰሩ ሰራተኞች ቀጥሮ ሰራተኞች የማማከር ስራ የሰሩ መሆኑንና ለሰራተኞች የአራት ወር ደመወዝ የከፈለ መሆኑን፣ ረቂቅ የፅሁፍ ውል ተዘጋጅቶ የነበረው በቃል የነበረውን ውል በፅሁፍ አድርገው ለማስቀጠል በመስማማታቸው መሆኑንና ረቂቁ የፅሁፍ ውል ያልተፈረመው የተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ወደ ኢትዮጵያ ባለመምጣታቸው መሆኑን በማስረጃ

ያረጋገጠ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ረቂቅ የውል ሰነዱ አመልካችና ተጠሪ የማማከር ስራ ውል ለመዋዋል በሚያደርጉበት ወቅት፣ ባለመስማማታቸው ረቂቁ ያልተፈረመ መሆኑን የሚያስረዳ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ ሆኖም አመልካች ከተጠሪ ጋር የማማከር ስራ ውል ለመዋዋል ድርድር ጀምሮ እንደነበር፣ በድርድሩ ሂደት ስምምነት ላይ ባለመደረሱ ረቂቁ ሣይፈረም የቀረ በመሆኑና ረቂቅ ውሉ ከመዘጋጀቱ በፊት በቃል ያደረጉት የስራ ውል የሌለ መሆኑንና ተጠሪም በስራ ውሉ መሰረት የፈፀማቸው ተግባራት የሌሉ መሆኑን የሚያስረዳ በቂና አሳማኝ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

6. አመልካችና ተጠሪ በቃል ያደረጉት የማማከር ስራ ውል መኖሩ ብቻ ሣይሆን በተጠሪ በቃል በተደረገው የማማከር ስራ ውል መሰረት ለአራት ወራት ያህል ሰራተኞች ቀጥሮ ደመወዝ እየከፈለ የአመልካችን እርሻ ያስተዳደረና ሌሎች የምክር አገልግሎቶችን የሰጠ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ በዚህ መዝገብ የሚከራከሩበትን አይነት የስራ ውል ለመዋዋል፣ የአሰሪው /የአመልካች/ ጥያቄውን ማቅረብና የተጠሪ ጥያቄውን መቀበል ብቻ በቂ እንደሚሆን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1779፣ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2610 እና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2612 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች የማማከር የስራ ውል በፅሁፍ ካልተደረገ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖች በቃል ባደረጉት ስምምነት ሊቋቋሙት እንደማይችሉ በመግለፅ የሚያቀርበው ክርክር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1882 ንዑስ አንቀፅ 1፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2610፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2612 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን ይዘት ያላገነዘበና የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

7. ተጠሪ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2610 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ከአመልካች ጋር በቃል ባደረገው የስራ ውል መሰረት የማማከር ስራውን ከሰራ፣ አመልካች በስራ ውሉ ላይ በቁርጥ የተወሰነውን ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2624 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ለአመልካች በውሉ መሰረት ለአራት ወራት ያህል ለሰጠው የማማከር ስራ በቁርጥ የተወሰነውን ገንዘብ እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውንና ከላይ የተገለፁትን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች አመልካች ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበውን ክስና ማስረጃ በቂና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የማስተባበል ግዴታውን በአግባቡ ያልተወጣ መሆኑን የአመልካች የውሉን ፎርም አለተሟላም በማለት ተጠሪ ለሰራው ስራ ክፍያ ለመፈፀም እንቢተኛ

መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ የሰጡት ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ይ**

የሰ/መ/ቁ. 100671

ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ሻለቃ ጌትነት ታርቆ - ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ጀሚላ አሊ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው፡፡ ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 08573 በቀን 21/10/2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞር ከፍተኛ ፍርድ ቢያፀናውም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 2665 በ09/08/2006 ዓ.ም በመለወጥ በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካች መሰረታዊ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የውል መፍረስን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በጎንደር ከተማ ቀበሌ 17 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር 7662/03 በእኔና በባለቤቴ ወራሾች በሆኑት ህፃናት ልጆች ስም የተመዘገበ ቤትና ቦታ ላይ እኔ ቦታ ተጠሪ ደግሞ ገንዘብ ችሎ ባለ 3 ፎቅ ህንፃ ሰርተን እኩል ልንካፈል እና ተጠሪ ከፎቅ ጀርባ መኖሪያ ቤት ሰርቶ ሊሰጠኝ በ21/06/03 ውል አድርገን እሱባለው ሆነ ኃ/የተ/የግ/ማ በማቋቋም ተስማማን፡፡ በውሉ መሰረት እንዲፈፀም በወረዳ ፍርድ ቤት ከሶኝ ውሳኔ አሰጥቶብኛል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካች የቤትና ቦታው ካርታ ወደ ማህበሩ እንዲዞር የሽያጭ ውል መፈፀም አለብን በሚል የአሁኑን ተጠሪ አታሎ የልጆቼን መብት በሚጎዳ መልኩ የሽያጭ ውሉ ላይ አስፈርሞኛል በመሆኑም ውሉ የፈቃድ ጉድለት ያለበት

በመሆኑ ይፍረስልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነት ቀርቦ በሰጠው መልስ ቀደም ሲል በ21/06/03 ዓ.ም የተደረገው ውል በ2/07/03 ዓ.ም በተደረገው ውል ተተክቷል የአሁኑ ተጠሪ ጋር ውል አልፈፀምኩም በ8/07/03 ዓ.ም የተደረገውን ውል የአሁን ተጠሪ የማድረግ ስልጣን አላት ምክንያቱም የልጆቹ ሞግዚትና ብቸኛ ወኪል ነች ውሉን ያደረግነው በአሁን ተጠሪ ጠያቂነት ነው ውሉ ፀድቆ ተመዝግቦ ስም ተዛውሯል፡፡ በአሁኑ ተጠሪ ስም የነበረው ካርታ ቁጥር 7662/03 በአዲስና በአሁን አመልካች ስም በወጣና ቁጥር 7668/03 በሆነ ካርታ ተለውጧል፡፡ በመሆኑም ክሱ በሌላ መብት የቀረበ ነው ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የአሁን ተጠሪ በ25/06/03 ዓ.ም የመንደር ውል ካደረጉ በኋላ በ8/7/03 ዓ.ም የአሁኑ አመልካች ጋር የሽያጭ ውል በማድረግ ውሉን አስመዝግበው ስም ወደ አሁኑ አመልካች እንዲዛወር አድርገዋል፡፡ ይህንን ሲያደርጉ ደግሞ ተገደው መሆኑን አላስረዱም ወደውና ፈቅደው መዋዋላቸውን ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም በ8/7/03 ዓ.ም የተደረገው ውል ሊፈርስ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁኑ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይኸው ፍርድ ቤት በ8/10/04 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህ በኋላም የአሁኗ ተጠሪ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረሙ ይገባል በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርባ ይኸው ችሎትም በዋናነት የሽያጭ ውሉ ህጋዊነት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አከራካሪ የሆነው የሽያጭ ውል የተደረገው በ7/7/03 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ ቤትና ቦታ ላይ ቀደም ሲል በአሁን ተጠሪ ባለቤት ስም የነበረው ካርታ በአሁን ተጠሪና ልጆቻቸው ስም ዞሮ ቁጥር 7662/03 የሆነው ካርታ የተሰጣቸውም በዚሁ ዕለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ከ1 ወር ከ15 ቀናት በኋላ ይኸው የሽያጭ ውል ተደረገበት በተባለ ቦታ ላይ በግራ ቀኙ ስም ሻለቃ ጌትነት ታርቆ እና ጀሚላ ዓሊ /PIC/ በሚል ስም በ23/7/03 ቁጥር 7668/03 የሆነ ካርታ ተሰጥቷል ይህም የሆነው ግራ ቀኙ በ23/5/03 ዓ.ም በተፈራረሙበት የንግድ ድርጅት የጋራ ሕንፃ በመገንባት ውል መሰረት እና ማህበሩም እሱባለው ሆነ ኃ/የተ/የግ/ማ ተብሎ እንዲመዘገብ በጋራ በ24/08/03 ዓ.ም እና በ02/06/03 ዓ.ም ለሚመለከተው አካል ካመለከቱ በኋላ ነው፡፡ ይህንንም የአሁኑ አመልካች ራሱ በስር ፍ/ቤት ካቀረባቸው ሰነዶች ማየት ይቻላል የአሁን አመልካችም ቦታውን በ7/7/03 ዓ.ም በተደረገ ውል ቢገዛ ኖሮ ከዚህ በኋላ ይኸው ቦታ ላይ የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት በሆነ ድርጅት ስም ካርታ ሲወጣ ዝም ይላል ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም የሽያጭ ውሉ በክፉ ልቦና የአሁን ተጠሪን በመደለል የተደረገ ውል ነው፡፡ የሽያጭ ውሉም የተደረገው በባዶ ቦታ ላይ በመሆኑ ሕገ/ወጥ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም ቢሆኑ የሕፃናት ልጆቻቸውን ድርሻ የሆነን ቦታ የመሸጥ ከሕግ የመነጨ

መብት የላቸውም የሚሉ ምክንያቶችን በማስቀመጥ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ ባለመስማማት መሰረታዊ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሞባቸዋል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የሽያጭ ውሉ በተጠሪ ፈቃድ የተደረገና በሚመለከተው አካል ተረጋግጦ የተመዘገበ መሆን ውሉ የተደረገው ቤት የነበረው ቦታ ላይ እንጂ ባዶ ቦታ ላይ አለመሆኑን የሽያጭ ውሉ ከመደረጉ በፊት የተቋቋመ ማህበር አለመኖሩን ተጠሪ የሸጡት የራሳቸውን ድርሻ ብቻ መሆኑን ተጠሪ የሽያጭ ዋጋውን ፈርመው መቀበላቸውን ዘርዝረው ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርመሮ አመልካች የሽያጭ ውል የፈፀመው በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ሆኖ ካርታ በስሜ ዞሮ የግንባታ ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ የስር ሰበር ችሎት ውሉ የተደረገው ባዶ ቦታ ላይ በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት ያልተከራከርንበትን ነጥብ በማንሳት መወሰኑን ያለአግባብ ነው በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ለመመርመር በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የአሁን ተጠሪ የተጠሩ ሲሆን ቀርበው ሐምሌ 4 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በግራ ቀኙ መካከል በ22/05/03 ዓ.ም የንግድ ድርጅት የጋራ ህንፃ ግንባታ ውል መዋዋላቸውን ይህም ውል የተመዘገበ መሆኑን ይህንን ውል ለማስፈፀም ሲባል ህንፃው የሚሰራበት ቦታ ላይ የነበረው ቤት ፈርሶ ነፃ መሆኑን ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካች የቦታውን ስመ ሀብት ወደ ጋራ ማህበሩ ለማዞር የሽያጭ ውል መደረግ አስፈላጊ ነው በማለት በ07/7/03 ዓ.ም የባዶ ቦታ ሽያጭ ውል እንዲፈርሙ ያደረጋቸው መሆኑን በኋላ የተሰጠው ካርታ ቁጥር 7668/03 ግን በአመልካች ስም ሳይሆን በድርጅቱ ስም መሆኑን የሽያጭ ውሉን የገቡት የቦታውን ስመ ሀብት ወደ ድርጅት ዞሮ ግንባታ ይጀመር በማለት አመልካች ስለደለላቸው እንጂ የመሸጥ ሀሳብ ኖሯቸው አለመሆኑን ዘርዝረው የስር ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ራሱ አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረበውን ማስረጃዎች መርምሮ በመሆኑ የፈፀመው የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል አመልካችም ሐምሌ 7 ቀን 2006 ዓ.ም የመልስ መልሳቸውን አቤቱታቸውን በማጠናከር ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ

መርመሮታል፡፡ እንደመረመረውም የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው በግራ ቀኙ መካከል የሽያጭ ውሉ ከመደረጉ በፊት የአሁኑ ተጠሪ የሚኖሩበት ቤት ፈርሶ በቦታው ላይ የአሁኑ አመልካች ህንፃ ግንባታውን ለመጀመር ተዘጋጅተው እንደነበር በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ውሉ የተደረገው /የሽያጭ ውሉ/ በባዶ ቦታ ላይ መሆኑን ያሳያል፡፡ ባዶ መሬት ደግሞ የማይሸጥ የማይለወጥ መሆኑና የኢትዮጵያ ብሔርብሔረሰቦች ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ ሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 40/3/ የተመለከተ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ድንጋጌ በመተላለፍ የተደረገ የመሬት ግብይት ውል ፍሬ ነገሩ /Object/ ሕገ ወጥ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ውል ደግሞ ከጅምሩ የሌለ ወይም ያልተደረገ /Voide/ ውል መሆኑን የፍ/ህ/ቁ 1716/1/ ያስቀምጣል፡፡ በዚህ ሁኔታ ደግሞ ፍርድ ቤት ህግን የማስከበር ኃላፊነትም ጭምር ያለበት በመሆኑ ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም እንኳን ሕገ- ወጥ ውል ሲያጋጥመው ውሉ ከጅምሩ ፈራሽ መሆኑን በመግለፅ ውሳኔ መሰጠት አለበት፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኛችን ያልተከራከርንበትን ጉዳይ በራሱ በማንሳት ውሉ ከጅምሩ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ አይደለም የሚለው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም መሰረት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ከጅምሩ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 26665 በቀን 09/08/06 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

የሰ/መ/ቁ.102778

ሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** ስማድል ኮሙኒኬሽን ተርሚናል ፋብሪካ ኃ.የተ.የግል ማህበር

**ተጠሪ፡-** አቶ የሺጥላ ደሳለኝ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በሰ/መ/ቁጥር 102777 ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት ስላለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11 መሰረት መዝገቦችን አጣምረን በመመርመር ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ የውል ክርክር በፍርድ ቤት የሚታይበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥር 10 ቀን 2005 ዓ/ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም፡-አመልካች በኢትዩጵያ ውስጥ የሚገጣጥማቸውን ስማድል ተንቀሳቃሽ ስልኮችን የአሁኑ ተጠሪ ለአንድ አመት ብቸኛ ወኪል በመሆን በኢትዩጵያ ውስጥ ለማከፋፈል በ03/12/2003 ዓ/ም በተፈረመ ውል ስምምነት መደረጉን፣አመልካችም የሚያመርተውን ምርት ለተጠሪ የንግድ መደብር የሺጥላ ሞባይል ሴንተር እያስረከበ ተጠሪ እቃዎቹን እየሸጠ ክፍያውንም እየፈፀመ ቀሪ ሒሳብ ማመዛዘኛ(ባላንስ) እየተሰራ የውሉ ዘመን መጨረሻ ድረስ እቃ እየወሰደ የውሉ ጊዜ መጠናቀቁን፣ ተጠሪ በውሉ ዘመን የተረከባቸውን እቃዎችን ዋጋ ቀስ በቀስ ለአመልካች ገቢ እያደረገ እስከ ውሉ ዘመን ማብቂያ ማለትም እስከ 03/13/2004 ዓ/ም ድረስ ያለውን ሒሳብ አጠናቅቆ መከፍሉን፣ተጠሪ የብቸኛ ወኪልነቱን ዘመን ከተጠናቀቀ በኂላ ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ የማከፋፈል ስራውን እስከአቋረጠበትና የመጨረሻ ክፍያ እስከተፈፀመበት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ የብር 4,663,730.00(አራት ሚሊዩን ስድስት መቶ ስልሳ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ብር) እቃዎችን

በንግድ መደብሩ ሰራተኞች መረከቡን፣ ተጠሪ ከውሉ ዘመን ማብቂያ በኋላ ለወሰደው እቃ የመጨረሻ ሂሳብ ጥቅምት 03 ቀን 2005 ዓ/ም ገቢ አድርጎ በልዩነት የተገኘው ተራፊ ገንዘብ ብር 131,155.00(አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ብር) ታሳቢ ተደርጎ እስከ ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ ብር 2,322,815.80(ሁለት ሚሊዩን ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አስራ አምስት ብር ከሰማንያ ሳንቲም) ገቢ ማድረጉን፣ ይህ ገንዘብ ከብር 4,663,730.00 ላይ ተቀናሽ ሲደረግ በልዩነት ብር 2,340,914.50 (ሁለት ሚሊዩን ሶስት መቶ አርባ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ተጠሪ ለአመልካች መክፈል ይጠበቅበት እንደነበር፣አመልካች በወቅት ባልተሸጡ እቃዎች ላይ የዋጋ ቅነሳ ስላደረገ ያልተሸጡ እቃዎች ላይ ቆጠራ ተደርጎ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 05 ቀን 2012 ብዛታቸው 1000 ለሆኑ ሞባይል ስልኮች ለተጠሪ የብር 52,425.00(ሃምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ሃያ አምስት ብር) ተቀናሽ መደረጉን፣ተጠሪ ቅናሽ ከተደረገለት በኃላ ለአመልካች ብር 2,288,489.40(ሁለት ሚሊዩን ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከአርባ ሳንቲም) እንዲከፍል የሚጠበቅበት መሆኑንና የወሰዳቸውን እቃዎችን እንዲመልስ ወይም ገንዘቡን እንዲከፍል ቢጠየቅ ፈቃደኛ ያለመሆኑን ዘርዝሮ ተጠሪ የሚፈለግበትን ብር 2,288,489.40 ከ18/03/2005 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ፣ከክሱ ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ተከሳሽነቱ ቀርቦ ለአመልካች ክስ በሰጠው መልስም፡- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበው ነጥብ የፍርድ ቤቱን ስልጣን የሚመለከት ሲሆን ይኼውም በግራ ቀኙ መካከል በ03/12/2003 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት በውሉ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ አለመግባባት ቢፈጠርና ይህም አለመግባባት በስልሳ ቀናት ውስጥ በስምምነት መፍትሔ ሊያገኝ ካልቻለ ጉዳዩ ሶስት ገላጋይ ዳኞች(አርቢትሬተርስ) ለሚሰየመው አለም አቀፍ የንግድ ምክር ቤት ቀርቦ መፍትሔ እንደሚሰጠው፣የግልግል ዳኝነቱ የሚደረገውም በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሆንግ ኮንግ እንደሚሆንና ጉባኤውም የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን በውሉ አንቀፅ 10 ስር ስምምነት መደረጉን፣ከዚህም በተጨማሪ አለመግባባቱ የሚታየው በኢትዩጵያ ሕግ እንዳልሆነና በ2000 ዓ/ም አለም አቀፍ የንግድ ድንጋጌዎች(ኢንተርናሽናል ኮሜርሺያል ተርምስ፤ኢንኮተርምስ) አማካኝነት እንደሆነ ተፈፃሚነት ስላለው ሕግ በሚደነግገው የውሉ አንቀጽ 11 ስር ግራ ቀኙ መስማማታቸውንና ይኼው በውሉ የተመለከተው የአለመግባባት አፈታት መንገድ በውሉ በተመለከተበት አግባባብ ከሚታይ በቀር ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት የሚወሰድበት አግባብ ያለመኖሩና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 16896 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑን ጠቅሰው ጉዳዩን ፍርድ ቤቱ ሊመለከተው አይችልም በማለት

መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በዚህ የተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ በግልግል እንደሚታይ ግራ ቀኙ በውላቸው ላይ ያስቀመጡ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጎ አመልካች የከፈለውን የዳኝነት ገንዘብ በደንቡ መሰረት እንዲመለስለት፣ተጠሪ ደግሞ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት አለው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ወጪና ኪሳራን በተመለከተም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች ለተጠሪ ብር 37,760.07(ሰላሳ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) እንዲከፍል በማለት ጥር 14 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡ስልጣንን አስመልክቶ በተሰጠ ብይን አመልካች፣ በወጪና ኪሳራ ላይ በተሠጠው ውሳኔ ደግሞ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ችሎቱ ስልጣኑን አስመልክቶ የቀረበውን ክርክር መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ያለው ውል ተራዝሟል፣ያለመራዘሙን አመልካች አልካደም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሲያፀናው ወጪና ኪሳራን በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች ለተጠሪ በክሱ ገንዘብ መጠን 3% የጠበቃ አበል እንዲከፈል በማለት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ብይንና ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ03/12/2003 ዓ/ም በተደረገ ውል ያለመግባባቱ የሚፈታበት አግባብ የተቀመጠው እስከ 03/13/2004 ዓ/ም ላለው ጊዜ ተፈፃሚነት ለሚኖረው ውል ሁኖ እያለና በዚህ ጊዜ ውስጥ ደግሞ ውሉ አብቅቶ የግራ ቀኙ በፅሑፍ ያደረጉት ስምምነት ሳይኖር ግንኙነቱ ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም በመቀጠል ለተፈፀመ የሞባይል ግብይነት የቀረበውን የክፍያ ጥያቄ የቀደመው ውል እንዲቀጥል በግራ ቀኙ መካከል በጽሑፍ የተደረገ ውል በሌለበትና ቀዳሚው ውል ጊዜው ባበቃበት ሁኔታ የመጀመሪያው ውል ተፈጻሚነት እንዳለው ተደርጎ ያለመግባባቱ በፍርድ ቤት ሳይሆን በግልግል የሚታይ ነው መባሉም ሆነ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ አመልካች ለተጠሪ እንዲተካ ተብሎ መወሰኑም ረቺና ተረቺ ባልተለየበት ሁኔታ በመሆኑ ያላግባብ የተወሰነ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥም፡- በአመልካችና በተጠሪ መካከል

የተደረገው ውል ጳጉሜ 03 ቀን 2004 ዓ/ም ከተጠናቀቀ በኃላየተደረጉ ግብይቶችን አስመልክቶ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት የመዳኘት ስልጣን በፍ/ብ/ቁጥር 1684 መሰረት ውሉ የተራዘመ በመሆኑ የሽምግልና ዳኞች ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለኝም ያለበትን አግባብነትና እንዲሁም በግልጽ በውሉ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኂላ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1684 ትርጉም ተሰጥቶ ውሉ መራዘሙ በሽምግልና ዳኝነቱ ስልጣን የሚኖረውን ውጤት ለመመርመር ተብሎ በመሆኑ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች የክስ ይዘት አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገጣጥማቸውን ስማድል ተንቀሳቃሽ ስልኮችን የአሁኑ ተጠሪ ለአንድ አመት ብቸኛ ወኪል በመሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማከፋፈል **በ03/12/2003** ዓ/ም በተፈረመ ውል ስምምነት የተደረገ ሲሆን የውሉ ዘመን ማብቂያ እስከ 03/13/2004 ዓ/ም ድረስ ስለመሆኑ፣በመጀመሪያ ውል መሰረት መከፈል የሚገባውን ሂሳብ ተጠሪ አጠናቅቆ ለአመልካች ከፍሏል በማለት አመልካች ክሱን መመስረቱን፣ተጠሪ የብቸኛ ወኪልነቱን ዘመን ከተጠናቀቀ በኂላ ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ የማከፋፈል ስራውን እስከአቋረጠበትና የመጨረሻ ክፍያ እስከተፈፀመበት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ ያለው ግብይት ላይ ያልተከፈለው ሒሳብ መኖሩን ዘርዝሮ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ መመስረቱና ተጠሪም የመጀመሪያው የውሉ ጊዜ ከአበቃ በኂላ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ግንኙነት ቀድሞ በጽሑፍ በተደረገው ውል አግባብ ሊገዛ ይገባል በሚል ምክንያት ጉዳዩ በግልግል እንጂ በፍርድ ቤት የሚታይበት አግባብ የለም የሚል ክርክር አንስተው የበታች ፍርድ ቤቶችም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት ውሉ በመራዘሙ ምክንያት ቀድሞ በተደረገው የውል ግንኙነት አግባብ መገዛት አለበት በሚል ድምዳሜና የፍ/ሕ/ቁጥር 1684 እና 1731(1) ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ጉዳዩን ፍርድ ቤት ለማየት ስልጣን የለውም ሲሉ የወሰኑ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1711 በግልጽ የደነገገ ሲሆን በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ደግሞ ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ የሕግን ያህል ኃይል ያላቸው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ስር ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም በሕግ እስካልተከለከለ ድረስ ተዋዋይ ወገኖች አንድን ጉዳይ ከፍርድ ቤት ውጪ በሌላ የሙግት መፍቻ ዘዴ ለመፍታት ስምምነት ማድረግ እንደሚችሉና ስምምነቱ መኖሩና ሕጋዊ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ደግሞ ተዋዋዮቹ በስምምነታቸው መሰረት መገዛት እንደአለባቸው፣ፍርድ ቤቱም ሕጋዊ ውል መኖሩን አረጋግጦ ውሉ እንዲፈጸም ማድረግ ያለበት መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም፡፡

ከክርክሩ ሂደት በግልፅ መገንዘብ የሚቻለው በ03/12/2003 ዓ/ም በግራ ቀኙ በጹሑፍ የተገባው ውል የተሻሻለ ስለመሆኑ አለመረጋገጡን ነው፡፡የውል መለወጥ ሥርዓት በሕጉ የተዘረጋ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1722 ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት ዋናውን ውል የመለወጥ ጉዳይ በዚሁ ውል በተደነገገገው አፃጻፍ (ፎርም) መሰራት ያለበት መሆኑ በተጠቃሹ ድንጋጌ ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጹሑፍ ያደረጉትን ውል በፁሑፍ የለወጡ መሆኑን አላስረዱም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ በዚህ ረገድ የሚከራከሩትና የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር የቀድሞ ውል ጊዜው ከአለቀ በኂላ ሁለቱ ወገኖች በቀድሞ ውል መሰረት ግንኙነታቸውን የቀጠሉ መሆኑ እንጂ አመልካች ወይም ተጠሪ ያቀረቡት የውል አቀራረብ ጥያቄ ኑሮ ሌላኛው ወገን በዝምታ ግንኙነቱን የቀጠለ ስለመሆኑ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ወይም ተጠሪ አንዱ ለሌላኛው የውል መለዋወጥ ጥያቄውን ማቅረቡ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳየው ጉዳይ ከመሆኑም በላይ የውል መለወጥ ሊከተለው የሚገባውን ስርዓት በመከተል ውሉ ስለመለወጡ ያልተረጋገጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የተጠሪ ክርክርም ሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም በ03/12/2003 ዓ/ም የተደረገው ውል በአመልካችና ለተጠሪ መካከል ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 18/03/2005 ዓ/ም ድረስ ነበረ ለተባለ ግንኙነት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም፡፡

በሌላ በኩል ግን በ03-12-2003 ዓ.ም የተደረገው ውል እና በውሉ የተቀመጠው የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ በሕጉ አግባብ አልተለወጠም፣ ቀዳሚው ውል ተጠናቋል ከተባለ ተጠሪ በ03-12-2003 ዓ.ም በተደረገው ውል ከገባው ግዴታ በኂላ ነበር ለተባለ የግራ ቀኙ ግንኙነት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል አለ ተብሎ የ03/12/2003 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን ውል ለክሱ ምክንያት ሊሆን የሚችልበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ውል ተራዝሟል ብሎ ለመደምደም መነሻ ያደረገው በ03/12/2003 ዓ/ም ተደረገ የተባለውንና አመልካች ለማስረጃነት ያቀረበውን ሰነድ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ እንዲሁም አመልካች ይህ ውል ከተጠሪ ጋር ከ5/13/2004 ዓ/ም በኃላ የፅሑፍ ውል የለም ብሎ ለመከራከር እንደማያስችለውና ውል የለም ካለ ደግሞ ክሱን የመሰረተበት አግባብ ምን እንደሆነ ጠቅሶ ያቀረበው ክርክር የለም በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በውሳኔው ላይ ማስፈሩን ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ የአንድ ግዴታ ምንጭ ውል ወይም ሕግ ሲሆን አንድ መብት አለኝ በማለት ክስ የሚያቀርብ ሰውም የመብቱን ምንጭ ማሳየት እንደሚጠበቅበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33፣80፣231 እና በሌሎች ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው የክስ አመሰራረት ስርዓት ያስገነዝባል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካችም በተጠሪ ላይ ክስ ሲመሰርት በመካከላቸው ቀድሞ በፅሑፍ የሆነ ውል የነበረ

መሆኑና በዚያ ውል  ተጠሪ ያለባቸውን ግዴታ የተወጡ መሆኑን አሳይቶ ለክሱ መሰረት የሆነው ግን ከቀዳሚው ውል ጊዜ ማብቃት በኋላ በነበራቸው ግንኙነት መሰረት ተጠሪ አልተወጡም የተባለው ግዴታ ነው፡፡ በመሰረቱ በጠቅላላ ውል በሕግ ፊት የጸና ውል አለ ለማለት መሟላት ከአለባቸው ነገሮች አንዱ በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠ ፎርም ካለ ይህንኑ ማሟላት ሲሆን በአመልካችና በተጠሪ መካከል ነበር የተባለው የተንቀሳቃሽ ስልክ በወኪልነት የማከፋፈል ውል ፎርምን በተመለከተ በሕጋችን ለተዋዋይ ወገኖች ነፃነት የተተወ ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1719(1) በሁለቱ ወገን ተዋዋዮች በማናቸውም ሁኔታ የተደረገ ስምምነት ውል ለማድረግ በቂ ነው በማለት  የተቀመጠው ድንጋጌ የሚያስገነዝበውም ሕጉ ይህን ነፃነት መጠበቁን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የውሉ አጻጻፍ ፎርም ወይም ዓይነት በሕግ የታዘዘ ሆኖ እንደ ትዕዛዙ ባይፈጸም ፈራሽነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ሐ)) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ሆኖም የተንቀሳቃሽ ስልክ በወኪልነት የማከፋፈል ውልን በተመለከተ ግን በግልጽ የተቀመጠ የፎርም ግዴታ ባለመኖሩ ተዋዋይ ወገኖች በመሰላቸው መልኩ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የተንቀሳቃሽ ስልክ በወኪልነት የማከፋፈል ውል በቃል፣ በድርጊት፣ ወይም በጽሑፍ ሊፈጸም ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች አቀረበ የተባለውን ሰነድ ከ05/13/2004 ዓ/ም በኋላ እስከ 18/03/2005 ዓ/ም ድረስ ላለው ጊዜ የቀረበ ማስረጃ ስለመሆኑ ሳያረጋግጥና የውሉ ጊዜ ያበቃ ስለመሆኑ አመልካች ጠቅሶ እየተከራከረ የግራ ቀኙ ግንኙነት በፅሑፍ ያለውን ውል መሰረት ያደረገ ነው፣ ውሉ ተራዝሟል በማለት ያሰፈረው ድምዳሜ የአመልካችን የክርክር ይዘትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1719 ድንጋጌን ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 16896 የተሠጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምም በመዝገቡ ተከራካሪ የነበሩ ወገኖች በመካከላቸው የተሻሻለ ውል መኖር ያለመኖሩ አካራካሪ ባልሆነበትና በሕግ ፊት የፀና አንድ ውል መኖሩና በዚህ ውል ደግሞ ግራ ቀኙ ያለመግባባትን በግልግል ለመፍታት የተስማሙ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ በመሰረታዊ የክርክር ነጥቦች አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት የሌለው በመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠሪ የሚያቀርቡት ክርክር ከአስገዳጅ የሕግ ትርጉም አተገባበር አንፃር ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ሲጠቃለልም በአመልካችና በተጠሪ የተነሳው ክርክር በ03/12/2003 ዓ/ም የተደረገው ውል ከአበቃ በኋላ ግራ ቀኙ በዚሁ ውል ለመገዛት በፍ/ሕ/ቁጥር 1684 እና 1722 ድንጋጌዎች አግባብ ያራዘሙት ውል ሳይኖር በአዲስ መልክ የተፈጠረውን ሌላ ውል መሰረት ያደረገ በመሆኑ በ03/12/2003 ዓ/ም በተደረገ ውል መሰረት በግልግል እንዲታይ የሚደረግ ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፤፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 130429 በ06/03/2006 እና 14/06/2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 96463 በ24/8/2003 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 97137 በ24/08/2006 ዓ/ም የተሻሻለው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 18/03/2005 ዓ/ም ድረስ ያለውን ግንኙነት የመዳኘት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካችን የዳኝነት ገንዘብ ተመልሶለት ከሆነ ተገቢውን እንዲፈጽም በማድረግ ክርክሩን በመ/ቁጥር 130429 እንዲቀጥል አድርጎ ጉዳዩን በሕጉ አግባብ አጣርቶ ተገቢውን ሊወሰን ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ተጠሪን ለወጪና ኪሳራ ዳርጓል የተባለና በጉዳዩ ላይ የተሰጠ ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ አሁን ባለው የክርክር ደረጃ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሚገደድበት ወጪና ኪሳራ የለም ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

# ክውሉ ውጭ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁ. 106450

ሚያዝያ 15 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ኢትዮጵያ ኤ.ኀ/አገልግሎት መቂ ዲስትሪክት - ነ.ፈ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ በሳ ናናማ - ጠበቃ - ደነቡ ጠይሶ - ቀረቡ

2. አቶ ባንቄ መኤሶ

3. ወ/ሮ አዩሌ መገርሳ

**መዝገቡ መርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪዎች ከሳሽ ነበሩ፡፡ተጠሪዎች የሟች ቱፋ ቤንቄ ቤተሰብ መሆናቸዉን በመግለጽ በመኖሪያ ቤቱ አጠገብ ባለዉ የኤሌክትሪክ ሽቦ መሀከል ትልቅ ዛፍ በመኖሩ ድርጅቱ (አመልካች) በተለያዩ ጊዜ ቆርጦ እንዲያነሳለት ቢጠይቅም ባለማንሳቱ ሟች በልጆቼ ላይ ሊወድቅ እና ሊይዝብኝ ይችላል በማለት ዛፉን ሲቆርጥ ኤሌክትሪኩን በመንካቱ ሊገድለዉ ችሏል፡፡ ሁለት ቀርጥ መሬት እያከራዩ ከአንዱ ቀርጥ ላይ 10 ኩንታል ቦቆሎ ሲያገኝ ከሁለቱም ቀርጦች 20 ኩንታል የሚያገኝ ሲሆን የ1 ኩንታል በቆሎ ዋጋ 500 ብር ሲሆን በ1 አመት 10,000 ብር ያገኝ ነበር፣ ለወደፊቱ ሊኖር የሚችለዉ ለ36 አመት ስለሚሆን በዚህ ሂሳብ 360,000 ብር እንዲከፈለን በማለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በሰጠዉ መልስ ፤ሟች ከኤለክትሪክ ርቆ ቤቱን መስራት ሲኖርበት የአዋጅ 464/97 ድንጋጌን በመተላለፍ፤እራሱ የተከለዉን እንጨት አጥር ለመስራት ሲቆርጥ ጥንቃቄ ባለማድረጉ በመሞቱ ልንጠየቅበት አይገባም፤ይህ የኤሌክትሪክ መስመር ለብዙ አመት አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ እና እስካሁን ችግር ፈጥሮ አያዉቅም፣በመሆኑም ተጠያቂ

ልንሆን አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡በመቀጠልም ሟች ያገኝ ነበር የተባለዉም ገቢ የተጋነነ ነዉ ፤የወንድ አማካይ እድሜም 55 አመት በመሆኑ ሟች ለወደፊት ይኖራል ተብሎ የቀረበዉ ትክክል አይደለም፤ ዉድቅ ሊሆን ይገባል ብሏል፡፡ ጉዳዩን ያየዉ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት እንዲሁም ተገቢ ነው ያለውን ማጣራትም ከአደረገ በኋላ ሀላፊነትን በተመለከተ አመልካች የኤሌክትሪኩ ሽቦ ከሟች ቤት 4 ሜትር ርቆ የነበረና መቁረጥ የማያስፈልግ ነበር ቢልም፤ በተደረገዉ ማጣራት ሟችን የገደለዉ የኤሌክትርክ ሽቦ 2.85 ርቆ እንዳለ በማረጋገጥ አመልካች እንጨቱን መቁረጥ ነበረበት፣ ይህን ባለማድረጉ ለደረሰዉ አደጋ ተጠያቂነት አለበት በማለት የፍ.ህ.ቁ 2095 ድንጋጌን ጠቅሶ ወስኗል፡፡በመቀጠልም የታጣን ገቢ በተመለከተ ሟች ሁለት ቀርጥ መሬት አከራይቶ በአመት 20 ኩንታል ያገኝ ነበር ቢባልም ተጠሪዎች መሬቱ በእጃቸዉ ስለሚገኝ ስራተኛ ቀጥረዉ መጠቀም ስለሚቻል በርትዕ በወር 200 ብር መቅጠር ስለሚችሉ፤እና የሟችም ዕድሜው 24 አመት የነበረና ለወደፊቱ 32 አመት ሊኖር ይችላል ተብሎ ስለሚገመት 32×12×200 = 76,800 ብር እና የሞራል 1000 ብር ጨምሮ 77,800.00 ብር ለተጠሪዎች ይከፈላቸዉ በማለት ወስኗል፡፡በቀጣይነት ጉዳዩን ያየዉ ፍርድ ቤትም ቅሬታዉን ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡

የአመልካች አቤቱታም የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ቅሬታዉን ሲገልጽ፡- የኤሌክትሪክ መስመሩ ከ1972 ጀምሮ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ነዉ፤ ሟች ኤሌክትሪክ በእርጥብ እንጨት ከነኩት ሊገድል እንደሚችል በሚገባ ያዉቃል 4 ሜትር ርቆ ያለዉን መስመር በቸልተኝነት እንጨት በመቁረጥ በተፈጠረዉ አደጋ የሞተ በመሆኑ ሀላፊነት የለብንም ፤ሟች እንጨቱ እንድቆርጥለት ድርጅቱን በተደጋጋሚ ጠይቋል ቢባል እንኳ የሰዉን ንብረት ለመቁረጥ መብትም የለንም፤ ባጠቃላይ ተጠሪዎችም ቢሆኑ እራሳቸዉን ችለዉ ሰርተዉ መኖር የሚችሉ በመሆኑ ተጠቃሹን ገንዘብ እንድንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

በዚህም መሰረት ችሎቱ ጉዳቱ የደረሰዉ ሟች በፈጸመዉ ጥፋት ነዉ ሲል አመልካች ያቀረበዉ ክርክር ታልፎ የመወሰኑን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙን በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰበር መልሳቸዉ የሚሉት የተቆረጠዉ ዛፍ ከመስመሩ 4 ሜትር ርቆ ነዉ ያለዉ የሚለዉ ክርክር ሀሰት ነዉ በስር ፍርድ ቤት 2.85 በአጣሪዉ ኮሚቴ በመረጋገጡ ክርክሩ ውድቅ ሊሆን ይገባል፤ሟች በተደጋጋሚ አመልካች ዛፉን እንዲቆርጥ አመልክቷል፤ የመቁረጥም ሀላፊነት ነበረበት፤ ይህን ባለማድረጉ ሀላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ይከራከራሉ፤፤ አመልካች በበኩሉ ሟች ዛፉን ሲተክልና ቤቱን ሲሰራ በኤሌክትርክ መስመር አጠገብ መስራት አልነበረበትም ፤ዛፉም ቢሆን ባይቆረጥም አደጋ አያመጣም ነበር፡፡

ያመጣል ብሎ ቢያስብም ለመቁረጥ ሙያ ያላቸዉን ማማከር ነበረበት ይህን ባላደረገበት ኃላፊነት አለባቸዉ ልንባል አይገባም ዉሳኔዉ ሊሻር ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸዉን ሲመስል፡- እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

በመሆኑም ከተያዘዉ ጭብጥ አኳያ አጠቃላዩን የክርክሩን ይዘት እንዳየነዉ፡- ተጠሪዎቸ የሟች ሚስትና ወላጆች በመሆናቸዉ በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸዉ ጉዳት ካሳ ጠይቀዋል፡፡ እንግዲህ የተያዘዉም ጉዳይ ሟች ቤቱ አጠገብ የነበረዉ የኤሌክትርክ መስመርና ዛፉ በቅርበት በመኖሩ ቢወድቅ በልጆቹ ላይ ሊያደርስ የሚችለዉን ጉዳት በማሰብ ድርጅቱ (አመልካች) ቆርጦ እንዲያነሳለት ቢጠይቁም ባለመቆረጡ በራሳቸዉ ጊዜ በመቁረጥ ላይ እያሉ ኤሌክትሪኩን በመንካት ሕይወታቸዉ አልፏል፡፡ይህን ተከትሎ በተጠየቀዉ የካሳ ክፍያ ሟች 32 አመት ሊኖሩ ይችላል፤በርትዕ ተጠሪዎች በወር በ2ቱ ቀርጥ መሬት ሰራተኛ 200 ብር ቀጥረዉ ሊያሰሩ የሚችሉ መሆናቸዉን በመጥቀስ ባጠቃላይ የሞራል ካሳን ጨምሮ ብር 77,800 የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት በመወሰኑ፤ አመልካችም ሀላፊነት የለብኝም ሟች አደጋ የማያደርስና ከመስመሩ የማይገናኘዉን ዛፍ ሲቆርጥ ነዉ የሞተዉ መቁረጥ እንኳ አስፈላጊ ቢሆን እንኳ ሙያ ያለዉን ቆራጭ በማማከር በጥንቃቄ መቁረጥ ሲገባዉ ለብዙ አመት ያለችግር አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘዉን የኤሌክትርክ መስመር መንካቱ የራሱ ጥፋት እንጂ ሊያስጠይቀን የሚገባ አይደለም፤ ሟች ቤቱን ሲሰራም ሆነ ዛፉን ሲተክል ወደ መስመሩ መጠጋት አልነበረበትም፤በተጨማሪም ሟች የተከለዉን ዛፍ እንድንቆርጥ አልጠየቁም እንጂ ቢጠይቁም የሰዉ ንብረትን የመቁረጥ መብት የለንም በዚህ ሁሉ ምክንያት ሟችን የመካስ ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክረዋል፡፡እንግዲህ የአመልካችን ኃላፊነት በተመለከተ መስመሩ 2.85 ቅርበት ላይ መኖሩ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ አመልካች እንደሚለዉ በ 4 ሜትር ላይም አይደለም፤ሊደርስ ይችላል ተብሎ የተገመቱትን ነገሮች ሪፖርት ሲደርሰዉም ሆነ በራሱ ክትትል አደጋን የማስቀረት ወይም የመቀነስ ሙሉ ኃላፊነት እና የህግ ግዴታ ያለበት መሆኑ ግልጽ ነዉ በመሆኑም የቤቱን ግንባታና የመስመሩን ቅደም ተከተል እንደዋነኛ መከራከሪያ ሊያቀርበዉ የሚገባ አይደለም፤ኃላፊነት የለኝም ሲል አመልካች የሚያቀርበዉን የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ረገድ አጣርቶ ኃላፊነት አለበት ማለታቸዉ የሚነቀፍ አይደለም ብለናል ፡፡ይሁን እንጂ ሟችም ቢሆን በዛፉ ምክንያት ኤሌክትሪክ አደጋ ሊያደርስ ይችላል በማለት ያሰበዉን ከመቁረጡ በፊት ሊያደርስ የሚችለዉን ጉዳት ማሰብና አግባብ ያለዉን ቆራጭ በመያዝ ሊቆርጥ ሲገባ በእርግጥ አደጋ ስለማድረሱ ሳያረጋግጥ ዛፉን በቸልተኝነት መቁረጡ የሟች አስተዋጽኦ የለበትም ለማለት አይቻልም በመሆኑም የፍብ.ህ/ቁ 2097(2) መሰረት ተበዳዩ በማስተዋል ቢሰራ ኖሮ የደረሰበትን ጉዳት ሊያቀለዉ ወይም ሊያግደዉ የሚችል ሲሆን በደረሰበት ጉዳት በሙሉ ካሳ መጠየቅ

የማይችል መሆኑን ይደነግጋል ፤በተያዘዉም ጉዳይ ጥንቃቄ በተሞላበት እና በማስተዋል ቢሰራ ኖር አደጋዉን ይቀንስ ነበር የሚለዉን ግንዛቤ ይዘናል፡በዚህ ሁሉ ምክንያት ለደረሰዉ አደጋ የሟች አስተዋጽኦ አለ፤ ካልን በፍ.ብ/ህቁ. 2098 (1)መሰረት በከፊል ሀላፊነት አለበት ማለት ነዉ፤ በመሆኑም አመልካች አለበት የተባለዉን የጉዳት ካሳ መጠን በማሻሻል 38,400 ሊሆን የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡የሞራል ጉዳት ካሳው ግን የሚነካ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ፡፡

በመጨረሻም በኦሮሚያ ክልል አዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሟችን ለጉዳቱ መድረስ የነበረዉን የቸልተኝነት ከፊል አስተዋጽኦ ሳያገናዝቡ አመልካችን ሙሉ በሙሉ ሀላፊ በማድረግ ተጠቃሹን የገንዘብ መጠን ካሳ እንዲከፍል መወሰናቸዉ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ፡፡በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ዉ ሳ ኔ**</u>

1. በኦሮሚያ ክልል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 37792 በቀን 05/13/2006 እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመ.ቁ.189401 በቀን 4/2/07 የሰጡት ዉሳኔዎች ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች ለደረሰበት አደጋ በከፊል ሃላፊነት ነበረበት ብለናል፡፡በመሆኑም አመልካች ለተጠሪዎች ሊከፈል የሚገባው የጉዳት ካሳ መጠን ብር 38,400.00፣ የሞራል ካሳ ደግሞ ብር 1000.00 በድምሩ ብር 39,400.00 (ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ብር ) ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የግራቀኙ የወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
4. በህዳር 08/2007 ተሰጥቶ የነበረዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ዉሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

*የ/ማ*

የሰ/መ/ቁ. 106147

ቀን ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** እሸት ኢንጅነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ፋንታዬ ቢያድግልኝ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 4585 ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3033 መስከረም 5 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ክስ የአመልካች ሠራተኛ የሆነ ልጃቸው አመልካች የንፅህና መጠበቂያ ውሃ ባለማቅረቡ ምክንያት፣ሥራ ውሉ፣ አዋሽ ወንዝ ውስጥ ገብቶ ሲታጠብ ስለመሆኑ በሥራ ላይ እያለ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ስለዚህ የአምስት ዓመት ደመወዝ ብር 270,000 /ሁለት መቶ ሰባ ሺ ብር/ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ሟች የድርጅቱ ሠራተኛ አይደለም ሟች ከአመልካች ንዑስ የሥራ ውል ተዋውሎ የሚሠራው ድርጅት ሠራተኛ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ከንዑስ የሥራ ተቋራጭ ሠራተኞች ውሃ የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት ተከሳሽ /አመልካች/ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ሚች የሥራ ውል ግንኙነት የላቸውም፡፡ ሆኖም ከንዑስ ተቋራጩ ሠራተኞች ውሃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት አመልካች መሆኑ በውሉ የተገለፀ በመሆኑ፣ ተከሳሽ ለሚች ከውል የመነጨ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብሎ ብር 31,000 /ሰላሣ አንድ ሺ ብር/ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡
3. አመልካች ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ሚች የተጠሪ ሠራተኛ አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ባልተከራከርንበት እና በማስረጃ ያልተረጋገጠ ጭብጥ በማንሣት፣ አመልካች፣ ውሃ የማቅረብ ግዴታውን አልተወጣም ብለው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ አመልካች በውል የገባውን ውሃ የማቅረብ ግዴታ መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች የተጠሪ ልጅ በአዋሽ ወንዝ ገብቶ ሲታጠብ ለደረሰበት የሞት አደጋ ኃላፊ ነው ተብሎ ካሣ እንድከፍል የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ክስ ያቀረበው ሚቹ ልጁ የአመልካች ሠራተኛ ነው፡፡ በሥራ ላይ እያለ ጉዳት ደርሶበታል በማለት ነው፡፡ የተጠሪ ልጅ የአመልካች ሠራተኛ አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ልጅ የአመልካች ሠራተኛ ሣይሆን ከአመልካች ንዑስ የሥራ ውል ተዋውሎ የሚሠራው ንዑስ የሥራ ተቋራጭ ድርጅት ሠራተኛ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ መሆኑን ውሣኔው ያሳያል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 110 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አመልካች ካሣ እንድከፍለው ለመጠየቅ የሚችልበት የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተጠሪ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ መሠረት በማድረግ የቀረበው የካሣ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡
6. የተጠሪ ልጅ የንዑስ ሥራ ተቋራጭ ሠራተኛ ነው ከተባለ፣ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚችለው በንዑስ ሥራ ተቋራጩ ላይ እንጅ በአመልካች ላይ ሊሆን አይችልም፡፡ አንድ ሰው በአንድ ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው፣ ከሕግ ከውልና ከውል ውጭ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆንበት ህጋዊ መሠረት ሲኖር ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ለንዑስ ተቋራጩ ሠራተኞች ውሃ የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነው በማለት አመልካች በተጠሪ ልጅ ላይ ለደረሰው ጉዳት ከውል

የመነጨ ኃላፊነት እንዳለበት በመግለፅ ወስነዋል፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቶቹ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሱት በአመልካች በንዑስ ሥራ ተቋራጩ መካከል የተደረገውን ውል በዝርዝር ሣያዩና፣ ተጠሪ በንዑስ ሥራ ተቋራጩ ላይ የቀረበው ክስ ሣይኖር፣ ንዑስ ሥራ ተቋራጩ ክስ ቀርቦበት አመልካች ውል ጋር ያደረገውን ውል እንደመከላከያ ባላቀረበበት ሁኔታ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በውል የገባውን ግዴታ ባለመወጣቱና በተጠሪ ልጅ ሞት መካከል፣ ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት ያለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በተጠሪ በኩል ስለመቅረቡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ አያሳይም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ልጅ ሞት ከውል የመነጨ ኃላፊነት አለበት በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

7. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ በተጠሪ ልጅ ላይ የሞት አደጋ የደረሰበት አመልካች ከውል ውጭ ስለሚመጣ ኃላፊነት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2027 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2136 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት፣ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ አያሳይም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የተጠሪ ልጅ አዋሽ ወንዝ ገብቶ ሲታጠብ ለደረሰበት የሞት አደጋ ከውል ውጭ በኃላፊነት የሚጠየቅበት የሕግ መሠረት የሌለ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች ከሕግ፣ ከውልና ከውል ውጪ የተጠሪ ልጅ አዋሽ_ወንዝ ገብቶ ገላውን ሲታጠብ ለደረሰበት የሞት አደጋ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ምክንያት ሣይኖር፣ የአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ ከላይ የጠቀስናቸውን ድንጋጌዎች የሚጥስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአውሲራሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሸሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ብ

የሰበር መ.ቁ.101229

ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች** :- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች:-** የኢት/ኤሌ/ኃ/ኮ/ ነገሌ ቦረና ዲስትሪክት - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ:-** አቶ ጣሂር ሣፋይ - የቀረበ የለም፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፣ የአሁኑ አመልካች የስር 2ኛ ተከሳሽ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ ደግሞ የቻይና ኤም.ሲ.ሲ 17 መንገድ ስራ ድርጅት ነበር፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ፡- በአመልካች ድርጅት እየሰራሁ ሳለ ሳፋ በሚባል ዕቃ መንገድ እያሳየሁ እያለሁ ይህ ብረት የኤሌክትሪክ ሽቦ በመንካት ባደረሰብኝ ጉዳት ግራ እግሬ ተቆርጦ በሌላ አካሌ ላይ ጉዳት ስላደረሰብኝ ሰርቼ የመኖር አቅም ሙሉ በሙሉ አጥቻለሁ፡፡ በመሆኑም የስር 1ኛ ተከሳሽ በአዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 27(3) 96(3) ፣ 97(መ) ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ በፍ.ብ.ህ.ቁ 2027፣ 2028 መሰረት ኃላፊነታቸው እንዲለይላቸው፣ የካሳውን መጠን በተመለከተም በቀን 35 ብር እንደሚያገኙና ዕድሜአቸዉ 20 ሲሆን እስከ 40 አመት ሊኖሩ እንደሚችሉ ዘርዝረው ባጠቃላይ ብር 499,996.80 እና የሞራል ካሳ ይከፈላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ ሀላፊነት የለበትም ተብሎ ከክሱ ሲወጣ አመልካች በሰጠዉ መልስ:- የኤሌክትሪክ መስመሩ ደረጃዉን የጠበቀ ነው፣ተጠሪ ስራዉን ሲሰራ ጥንቃቄ ባለማድረጉ እና የያዘዉን ብረት ወደ የኤሌክትሪክ ከፍ በማድረግ ያስነካዉ መሆኑን አልካደም፣ በመሆኑም በፍ.ብ.ህ.ቁ 2086 (2) መሰረት አያስጠይቀኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮና አመልካች የኤሌክትሪክ ሽቦዉን በምን

ያክል ከፍታ ላይ እንደዘረጋ እና መዘርጋት ያለበት በምን ያክል ከፍታ እንደሆነ የቅርንጫፉ ድርጅት እንዲገልጽ ከአደረገው በኋላ ፍርድ ቤቱ በጠየቀዉ መሰረት ከቀበሌዉ መስተዳድር ጋር በመሆን በቦታዉ በመገኘት የከፍታዉ ስታንደርድ 5.2 ሜትር ሲሆን አደጋዉ ሲደርስ በ5 ሜትር ከፍታ ላይ እንደነበረ አጣርቶ በደብዳቤ ቁ 397/7/05 በቀን 21/6/ 05 ዓ/ም ከተገለፀለት በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ስታንደርዱን ጠብቆ ሽቦዉን ባለመዘርጋቱ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ በፍ.ብ.ህ.ቁ 2069 (1) (2) መሰረት ኃላፊነት አለበት በማለት ጀምሮ የካሳውን መጠን በተመለከተ ደግሞ የጉዳት መጠኑ 45% መሆኑ በመረጋገጡ ይሄው የጉዳት መጠን ከተጠሪው የወደፊት አማካይ እድሜ 40 አመት ጋር ተነጻጽሮ ሲታይ ብር 219,373.6 እንደሚሆን፣ በዚሁ ገንዘብ የሞራል ካሳን 1000 ብር ሲጨመር ባጠቃላይ ብር 220,378.60(ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከስልሳ ሳንቲም) እንዲከፈለዉ ወስነዋል፡፡ በቀጣይነት ጉዳዩን ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን በማከራከር በድምጽ ብልጫ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ባግባቡ ነዉ በማለት አጽንቶታል፡፡

የአመልካች ቅሬታም ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ቅሬታዉን ስገልጽ ፡- የኤሌክትሪክ ሽቦ ከምሰሶ ወደ ምሰሶ በአግባቡ የተወጠረ ሲሆን የመጣዉ ልዩነት የ 20 ሳንቲ ሜትር ደግሞ ከመሬት አቀማመጥ ሊከሰት ይችላል፣ ፍርድ ቤቱ ይህን ከግምት ሳያስገባ መወሰኑ እና ተጠሪ በራሱ ጊዜ አቅጣጫ ማሳያ ወደ ኤሌክትሪክ ሽቦ ያስጠጋዉ እና የተበጠሰ ሽቦ ሳይኖር ተጠሪ ጥፋተኛ ሆኖ ሳለ ሙሉ በሙሉ አመልካችን ሀላፊ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በሰበር መልሳቸዉ የሚሉት፤- ሽቦ በምሰሶ ሲወጠር በዳገት ወይም በዝቅተኛ ቦታ ቢሆንም በዛዉ ልክ ከፍ ብሎ ስለሚወጠር የመሬት አቀማመጥ ልዩነት አያመጣም፣ ሽቦዉ አልተበጠሰም በማለት ብቻ በእኔ ጥፋት መፈጸሙን ሳያረጋግጥ አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር አግባብነት የለዉም፣ የቀረበዉም ሪፖርት ሽቦዉ ስታንደርዱን ጠብቆ ያለመወጠሩን አረጋግጧል፣ በመሆኑም በቀን የሚገኘዉን ገቢና የደረሰብኝን የጉዳት መጠን የመስራት አቅሜ እንዲቀንስ ያደረገ መሆኑ ተረጋግጦ ካሳው መወሰኑ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ ፡-ተጠሪ ለደረሰዉ አደጋ ቸልተኝነት አለበት፣ ስራዉን እንዲያከናዉን ያዘዘዉ የለም፣ ባጠቃላይ ጉዳት ካሳ መጠየቅ አይችልም፣ ከፍ.ብ.ህ.ቁ.2086 (2) ጋር ይቃረናል፣ በፍ.ብ/ህ.ቁ 2155(3) መሰረት ሊታይ ሲገባ የታለፈ በመሆኑ ዉሳኔዉ ሊሻር ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀዉን ይመስላል፡፡እኛም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

በመሆኑም ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር የክርክሩን አጠቃላይ ይዘት እንዳየነዉ የጉዳዩ መነሻ የነበረዉ ተጠሪ በምሰራበት የመንገድ ስራ ድርጅት በመሰራት ላይ ባለዉ መንገድ ሳፋ(ጠቋሚ) መሳሪያ በመያዝ በማገልገል ላይ እያለ የተወጠረዉን የኤሌክትርክ ሽቦ በመንካት በደረሰዉ አካል ጉዳት የግራ እግሩ መቆረጡን በማረጋገጥ እና 45% ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ጠቅሶ የጉዳት ካሳ እና የሞራል ካሳ ይከፈለዉ ዘንድ በመጠየቁ ሲሆን አመልካችም የተዘረጋዉ የኤሌክትሪክ ሽቦ ስታንደርዱን ጠብቆ የተዘረጋ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም፣ ጉዳቱ በተጠሪ ጥፋት የደረሰ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን ያዩት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳት መድረሱን በማረጋገጥ ኃላፊነትን በተመለከተ የተወጠረዉ የኤሌክትሪክ ሽቦ ስታንደርዱን ጠብቆ የተዘረጋ መሆኑን ለማጣራት ሲባል የቀበሌዉ መስተዳደር እና የግራ ቀኙ ባሉበት የቅርንጫፍ ድርጅቱ ስለሁኔታዉ እንዲገልጽ በማድረግ በተረጋገጠዉ መሰረት መስመሩ (ምሶሶው) በ5.20 ሜትር ርቀት ሊኖረዉ ሲገባ በ5 ሜትር ርቀት ላይ የተገኘ መሆኑን በማረጋገጥ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2069(1)(2) መሰረት በተፈለገዉ ጥራት ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነዋል፡፡ እንግዲህ አመልካች መከራከሪያዉ ያደረገዉ የተደረገዉ የመስመር መወጠር ልኬት የመሬቱን አቀማመጥ አላገናዘበ፣ የተበጠሰ ሽቦ ሳይኖር በተጠሪ ጥፋት ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም የሚለውን ነው፡፡

ይሁን እንጂ የመስመር ዝርጋታው ስንታደርዱን ያለመጠበቁ በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ በተረጋገጠበት ሁኔታና ጉዳቱም በተጠሪ ጥፋት ስለመድረሱ ያቀረበዉ ማስረጃ ሳይኖር በዚህ ረገድ ለዚህ ችሎት የሚያቀርበው የፍሬ ነገር ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ መስመሩ ደረጃውን ጠብቆ የተዘረጋ መሆን ያለመሆኑና በተጠሪ በኩል ጥፋት የነበረ መሆን ያለመሆኑ በማስረጃ የሚጣሩ ነጥቦች ሲሆኑ በዚህ ረገድ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ደግሞ ፍሬ ነገሩን አጣርተውና ማስረጃዎቹን መዝነው የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርገዋል፡፡ ይህ ለሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገሩን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ስርዓቱን ጠብቀው ያጣሩትና የደመደሙትን የፍሬ ነገር ክርክር እንደ እውነት የምንቀበለው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች የመስመሩ ዝርጋታ ደረጃውን የጠበቀ ነው፣ በተጠሪ በኩል ጥፋት ነበር በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው የለውም በማለት አልፈነዋል፡፡

ሌላዉ ተጠሪ በቀጣሪው ስራ ላይ ሳይታዘዝ ስለመስራቱም የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አግባብ በተመሰረተ የስራ ግንኙነት ስራ ላይ እያሉ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ መረጋገጡም

በተጠቃሹ አዋጅ  አንቀጽ 96(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስን በማመሳሰል የትርጉም ደንብ ስናየው በአመልካች በተፈጸመ ጥፋት ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች አግባብ ካሳ ከመጠየቅ የማይከለክላቸው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው የሚፈነዱ ወይም መርዝ የሚሆኑ ቅመማት ሥራ ላይ ማዋል ወይም በማከማቸት ወይም ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር በመዘርጋት ወይም መሬትን የተፈጥሮ መልክ በመለወጥ ወይም በተለይ አደገኛ የሆነ የኢንዱስትሪ ሥራ በማካሄድ ይህ ሥራው በሌላው ሰው ላይ አደጋ ያደረሰ እንደሆነ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2069/1/ የሚደነግግ ሲሆን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ተግባራትን በመፈፀም በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰው መንግሥትም ቢሆን ወይም ሥራውን እንዲሠራ በባለሥልጣን የተፈቀደለት መሥሪያ ቤት ቢሆንም በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2069(1) የተደነገገው ደንብ ተፈፃሚ የሚሆን መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069(2) በግልፅ ይደነግጋል፡፡ከዚህ ከሕጉ ይዘትና መንፈስ አንጻር ሲታይም ተጠሪ ከላይ በተገለፁት የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ለደረሰው ጉዳት የኤሌክትሪክ መስመሩ ባለሀብት በመሆኑ ብቻ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተገቢነት አይኖረውም፡፡ አመልካች ለደረሰው ጉዳት በኃላፊት የማያስጠይቀው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2086(2) በሚደነግገው መሠረት ጉዳቱ የደረሰው በሙሉ ወይም በከፊል በተጠሪ ጥፋት መሆኑን በማስረጃ በማስረዳትና በማረጋገጥ ነው፡፡አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ አለመሆኑን ለማስረዳትም በመጀመሪያ የኤሌክትሪክ መሥመሩን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለ ኤሌክትሪክ ሥራዎች የወጣው ደንብ ቁጥር 49/1991 አንቀጽ 35 ስለ ኤሌክትሪክ መስመሮችና መሣሪያዎች ደህንነት የደነገገውን በሚያሟላ ሁኔታ ተዘርግቶ የነበረ መሆኑን ሊያስረዳ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን መሰረት አድርገን ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ለክሱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡

ባጠቃላይ በተጠሪ ላይ የእግር መቆረጥ ደርሶበታል፣ በዚህም የተነሳ የመስራት አቅሙ በ45% መቀነሱ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ሲያገኝ የነበረዉ እና ለወደፊት የሚያገኘዉ ገቢ/ጥቅም የቀረበት በመሆኑ የጉዳት ካሳው ከደረሰዉ ጉዳት መጠን ጋር ተመዛዝኖ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2090 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የሚደነግጉትን መሰረት ተደርጎ የሞራል ካሳን ጨምሮ  ብር 220,378.60 (ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከስልሳ ሳንቲም) ሊከፈለዉ ይገባል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ሊነቀፍ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የህጉንም አላማ ስናይ የተጎዳ (ጉዳት የደረሰበት) ሰዉ በጉዳት አድራሹ ሊካስ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ በህገ መንግስታችንም አንቀጽ 14 ሥር ማንኛዉም ሰዉ ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና ነጻነት መብት አለዉ፡፡

በመሆኑም መንግስትም ሆነ ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ የአካል ደህንነት የመጠበቅ የህግ ግዴታ አለበት፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይም የሰበር ችሎቱ በመ.ቁ 42962 እና በሌሎችም መዝገቦች ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ዉሳኔ በአዋጅ ቁ454/97 አንቀጽ (2) (1) መሰረት በሀገሪቱ ባሉት ፍርድ ቤቶች አስገዳጅነት ያለዉ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የደረሰዉን ጉዳት በማረጋገጥ የተጠቀሰዉን የጉዳት ካሳ እና የሞራል ካሳ ክፍያ መወሰናቸዉ አግባብነት ያለዉ ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለልም የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በተጠሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የጉዳት ካሳ እና የሞራል ካሳ ብር 220,378.60(ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከስልሳ ሳንቲም) ሊከፈለዉ ይገባል በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመቁ 06611 በቀን 10/10/2005 ዓ/ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 168406 በቀን 25/6/2006 ዓ/ም የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ህ/ስ/ስ ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰዉ የአካል ጉዳት ሀላፊ ነዉ ተብሎ ጉዳት ካሳ ብር 220,378.60(ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከስልሳ ሳንቲም) ይክፈል መባሉ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የግራ ቀኙ የወጪ ኪሳራቸዉን ይቻቻሉ ብለናል፡፡
4. ግንቦት 27 ቀን 2006 ዓ.ም በዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተዉ አካል ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

የሰ/መ/ቁ. 90529

ሐምሌ 2 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** አቶ ኃይለየሱስ መንግስቴ ይግዛው - ጠበቃ ውብሰራ ሹመቴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አማኑኤል ፀጋ የከተማ ሱቅ ቤቶች ልማት አክሲዮን ማህበር- ጠበቃ ደረጄ ኢቲቻ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከንግድ ቤት ኪራይ ውል አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሽ በ01/11/2003 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 08/09/18 ከሚገኙት የተከሳሽ ድርጅት ሱቆች መካከል ከሳሽ በ01/11/2001 ዓ.ም በተደረገ ውል በምድር ቤት የሚገኝ 345 ካ.ሜ ስፋት ያለው አንድ የንግድ ሱቅ በካሬ ሜትር በብር 30 (ሰላሳ) ሂሳብ ለአምስት ዓመት ተከራይተው የምግብ እና መጠጥ ቤት ንግድ ፈቃድ በማውጣት እየሰሩበት እያለ ተከሳሽ ድርጅት ከ22/09/2003 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሱቁ የሚመጣውን የኤሌክትሪክ እና የውሃ መስመር በማቋረጡ የኤሌክትሪክ መስመሩ በፖሊስ እና በኤሌክትሪክ ኃይል ባለስልጣን ትብብር እስከተከፈተበት 22/10/2003 ዓ.ም ድረስ ከሳሽ ከንግድ ቤቱ ስራ በየቀኑ ያገኙ የነበረውን የተጣራ ትርፍ ብር 10,000 (አስር ሺ.ህ) ለ31 ቀናት በማጣታቸው የብር 310,000 (ሶስት መቶ አስር ሺ.ህ) ጉዳት እንደደረሰባቸው፣ ተከሳሽ የውሃ መስመሩን በኂላም ቢሆን እንዳልከፈተው፣ ከ22/10/2003 ዓም ጀምሮ እስከ 30/12/2003 ዓ.ም ድረስ ባሉት 68 ቀናት ደግሞ ገቢው በግማሽ የቀነሰ እና ከሳሽ በየቀኑ የብር 5000 (አምስት ሺ.ህ) ገቢ እንዳጡ፣በእነዚህ 68 ቀናት ከሳሽ ያጡት ገቢ ብር 340,000 (ሶስት መቶ አርባ ሺ.ህ) እንደሆነ የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ ድርጅት በከሳሽ ላይ

ላደረሰው ጉዳት በድምሩ ብር 650,000 (ስድስት መቶ ሃምሳ ሺህ) ለከሳሽ እንዲከፍል ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ26/11/2003 ዓ.ም በሰጠው መልስ ተከሳሽ የንግድ ሱቁን ያከራየው አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለተባለ ተከራይ እንጂ ለከሳሽ አለመሆኑን፣ ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ንብረት የተገለገሉት የኪራይ ውል እና መብት ሳይኖራቸው መሆኑን፣ ከሳሽ ከተከሳሽ ማህበር ጋር በራሳቸው ስም ያደረጉት የኪራይ ውል ባለመኖሩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33 (2) መሰረት በተከሳሽ ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችል መብት እና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን፣ተከሳሽ ማህበር የውሃም ሆነ የኤሌክትሪክ መስመር ያላቋረጠባቸው መሆኑን፣የኤሌክትሪክ መስመሩ አውቶማቲክ የጠፋው በራሱ ችግር መሆኑን፣ተከሳሽ ማህበር የኤሌክትሪክ መስመሩን አቋርጦት ቢሆን ኖሮ እንኳ ከሳሽ ጄኔሬተር ገዝተው ጉዳቱን መቀነስ ሲችሉ የብር 650,000 ጉዳት ደርሶብኛል በማለት ክስ ማቅረባቸው ተገቢነት የሌለው መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

በሌላ በኩል ከሳሽ ከተከሳሽ ማህበር ጋር ያደረጉት ውል ሳይኖር በስራ አስኪያጅነት በሚመሩት አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም በተከራዩት የተከሳሽ የንግድ ቤት ውስጥ የንግድ ፈቃዱን በራሳቸው ስም አውጥተው የንግድ ስራ በማከናወን በተከሳሽ ማህበር ንብረት አላግባብ የበለጸጉ መሆኑን ገልጾ በአኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም የንግድ ቤቱን ከያዙበት በ01/11/2001 ዓ.ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 26/11/2003 ዓ.ም ድረስ በካሬ ሜትር በአነስተኛ ዋጋ በብር 50 (ሂሳብ) የ345 ካ.ሜ ስፋት ያለው የንግድ ቤት ኪራይ ብር 638,250 (ስድስት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ) ከነወለዱ እንዲከፍሉ፤ክሱ ከቀረበበት ቀን በኃላ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ያለውን ኪራይም በተመሳሳይ ስሌት መሰረት ከነወለዱ እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንለት ዘንድ በ26/11/2003 ዓ.ም የተዘጋጀ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ ለዚህ ክስ ከሳሹ በ08/03/2004 ዓ.ም በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጡት መልስ በካሬ ሜትር ብር 50 ሂሳብ ለመክፈል ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር ያደረጉት ስምምነት አለመኖሩን፣ከአኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር ውሉ የተደረገው በካሬ ሜትር በብር 30 ሂሳብ መሆኑን፣ አስቀድሞ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ሳይኖር ኪራዩ ተከፍሎት ቤቱን ለማስለቀቅ ተከሳሽ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ከሳሽ የንግድ ቤቱን ከተከሳሽ ማህበር ስለመከራየታቸው ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን እና ከተከሳሽ ማህበር የንግድ ቤቱን የተከራየው አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደሆነ በማስረጃ መረጋገጡን ገልጾ ከሳሽ ከተከሳሽ ማህበር ጋር ያደረጉት ውል

ባለመኖሩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33 መሰረት በተከሳሹ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ዋናውን ክስ በ24/09/2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ ውድቅ አድርጓል፡፡ ቀጥሎም የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በተመለከተ ክሱን ከሰማ በኃላ የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦቹን በ03/03/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውድቅ አድርጎ በማለፍ በ02/05/2005 ዓ.ም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የከሳሽ ተከሳሽ ከተከሳሽ ከሳሽ ጋር በራሳቸው ስም ያደረጉት የኪራይ ውል ሳይኖር በማህበር ስራ አስኪያጅነታቸው የኪራይ ውሉን በአኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም ከተዋዋሉ በኃላ በራሳቸው ስም የንግድ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ስራ ሲያከናውኑ መቆየታቸው መረጋገጡን፣ይህም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2162 ስር እንደተመለከተው በተከሳሽ ከሳሽ ንብረት አላግባብ መበልጸጋቸውን የሚያመለክት መሆኑን፣የግራ ቀኙ ምስክሮች በተሰሙበት ጊዜ አካባቢ በ3ኛ ፎቅ ላይ የሚገኙት የንግድ ቤቶች በወር በካሬ ሜትር በብር 120 ሂሳብ እንደሚከራዩ በተከሳሽ ከሳሽ ምስክሮች የተገለጸ መሆኑን፣የከሳሽ ተከሳሽ የያዙት የንግድ ቤት የሚገኘው በምድር ቤት ላይ በመሆኑ ኪራዩ በፎቅ ላይ ከሚገኙት የንግድ ቤቶች በላይ እንደሆነ ግምት የሚወሰድበት መሆኑን እና በዚህም ምክንያት በተከሳሽ ከሳሽ የተጠየቀው በካሬ ሜትር በወር ብር 50 የኪራይ ስሌት ተቀባይነት ያለው እና ምክንያታዊ መሆኑን በዝርዝር ገልጸ የከሳሽ ተከሳሽ ይዘውት የሚገኙትን የንግድ ቤት ለተከሳሽ ከሳሽ እንዲያስረክቡ፣ በአኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም የንግድ ቤቱን ከያዙበት በ01/11/2001 ዓ.ም ጀምሮ ውሳኔው እስከተሰጠበት 19/06/2005 ዓ.ም. ድረስ ላለው የ43 ወራት ከ19 ቀናት ጊዜ ኪራዩን በካሬ ሜትር በብር 50 እና በየወሩ በብር 17,250 (አስራ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ) ሂሳብ በድምሩ ብር 752,675 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ አምስት) ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተከሳሽ ከሳሽ እንዲከፍሉ፤ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ያለውን ኪራይም በተመሳሳይ ስሌት በወር ብር 17,250 (አስራ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ) ሂሳብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በአከራካሪው ቤት የምግብና የመጠጥ የንግድ ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩበት የነበረው በስራ አስኪያጅነት ሲመሩት በነበረው አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስምም ቢሆን ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባውን የአንድ ዓመት ከሶስት ወር ቅድሚያ ኪራይ ከፍለው መሆኑ ባላከራከረበት እና በስሙ ኪራዩ የተከፈለበትን ቤት አመልካች ለግላቸው አላግባብ እየሰሩበት ነው በማለት አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሳይቃወም አመልካችን ሕገወጥ ብልጽግና አግኝተሃል በሚል በግራ ቀኙ መካከል ጭቅጭቅ ከተፈጠረ እና የአመልካች የንግድ እንቅስቃሴ ከቆመ በኃላ ያለውን

የቤት ኪራይ ከነወለዱ እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ያላግባብ ስለመበልጸግ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2162 ከተመለከተው ድንጋጌ አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. አመልካቹን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
2. አመልካቹ ኃላፊ የተደረጉበት የኪራይ ገንዘብ መጠን ተገቢነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ከተጠሪ ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል የገባው አመልካች ሳይሆኑ አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑ፣አመልካች የአኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ መሆናቸው፣አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በውል ከተጠሪው በተከራየው የንግድ ቤት ውስጥ የምግብ እና የመጠጥ አገልግሎት ንግድ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ስራ ሲያከናውኑ የነበሩት አመልካች መሆናቸው፣አመልካች የንግድ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ስራ ሲያከናውኑበት ለነበረው የተጠሪ ቤት ከተጠሪው ጋር የገቡት የኪራይ ውል አለመኖሩ በአመልካቹ ያልተካዱ እና በስር ፍርድ ቤትም የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡በመሰረቱ አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከአመልካቹ የተለየ የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው በመሆኑ አመልካቹ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ መሆናቸው በንግድ ቤቱ የንግድ ስራ ሲያከናውን የነበረው አመልካች በስራ አስኪያጅነት የሚመሩት ማህበር ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡በሌላ ሰው የስራ ድካም ወይም የሌላ ሰው ሀብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠን ለባለሀብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው ይህ አድራጎት ባደረሰበት ጉዳት መጠን ኪሳራ መክፈል የሚገባው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2162 ይደነግጋል፡፡አመልካች በተጠሪው ሀብት መገልገላቸው የተረጋገጠ ሲሆን በተጠሪው ሀብት ለመገልገል ያስቻላቸው ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ ማስረዳት እንዳልቻሉ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት በተጠሪው ሀብት አላግባብ በመገልገል ባገኙት የማይገባ ብልጽግና መጠን ለተጠሪው ኃላፊ የማይደረጉበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም አመልካቹን

ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የሌላ ሰው ሀብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው ለባለሀብቱ ኪሳራ ለመክፈል የሚገደደው ከዚሁ ተግባሩ ባገኘው ጥቅም መጠን እና በአንጻሩ በባለሀብቱ ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን ስለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ተጠሪው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ ቤት ለአኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ያከራየው ከ01/11/2001 ዓ.ም ጀምሮ ለአምስት ዓመታት በካሬ ሜትር በብር 30 (ሰላሳ) ሂሳብ ስለመሆኑ ተጠሪው ራሱ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ያቀረበው የኪራይ ውል ያመለክታል፡፡ የኪራይ ተመኑን በመካከል ተጠሪ የመጨመር መብት ያለው ስለመሆኑም የኪራይ ውሉ አያመለክትም፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በኪራይ ውሉ መሰረት አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ቤቱን ይዞ ለአምስት ዓመታት ተገልግሎበት ቢሆን ኖሮ ተጠሪው ሊያገኝ ይችል የነበረው ገቢ በወር በካሬ ሜትር 30 ሂሳብ ተሰልቶ የሚገኘውን ጥቅም መጠን ነው፡፡ አመልካች የንግድ ቤቱን አላግባብ ይዘው በመገልገል ተጠሪውን ላሳጡት ጥቅምም ለተጠሪው ኪሳራ መክፈል የሚገባቸው ተጠሪው ባጣው ገቢ መጠን በመሆኑ አመልካች ኪሳራውን በካሬ ሜትር በብር 50 (ሃምሳ) ሂሳብ ለመክፈል የሚገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካቹ በስራ አስኪያጅነት በሚመሩት አኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስምም ቢሆን የአንድ ዓመት ከሶስት ወር ኪራይ የከፈሉ በመሆኑ ይኸው የኪራይ ገንዘብ ተጠሪው ከአመልካች ከሚፈልገው ገንዘብ ተቀናሽ መደረግ ይገባው ነበር በማለት አመልካች ያቀረቡትን እና በአጣሪው ችሎትም በጭብጥነት የተያዘውን የአቤቱታ ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር እና ጥያቄ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ ይህ የክርክር ነጥብ የቀረበው አሁን በሰበር ደረጃ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው እንደማይገባ ገልጾ ተጠሪው በሰበር መልሱ ያቀረበውን ክርክርም አመልካች በመልስ መልሳቸው አላስተባበሉም፡፡በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ የክርክር ነጥብ ደግሞ በበላይ ፍርድ ቤቶች ሊስተናገድ እንደማይገባው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 329 (1) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስምም ቢሆን የአንድ ዓመት ከሶስት ወሩ የኪራይ ገንዘብ ተከፍሏል ወይስ አልተከፈለም? የሚለው ጥያቄ አሁንም ድረስ አከራካሪ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን ገንዘቡ ተከፍሏል የሚባል ቢሆን እንኳ በዚህ ገንዘብ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ገንዘቡን ከፍያለሁ የሚለው ማህበር እንጂ አመልካቹ አይደሉም፡፡በመሆኑም በአኃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም የተከፈለው ገንዘብ ከተወሰነብኝ የገንዘብ መጠን ላይ ተቀናሽ ሊደረግልኝ ይገባ ነበር በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በንግድ ቤቱ መገልገል የጀመሩት በ01/11/2001 ዓ.ም መሆኑ ያልተካደ ሲሆን በፌዴራል የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት አማካይነት ለተጠሪው ያስረከቡት ደግሞ በ11/10/2005 ዓ.ም ስለመሆኑ ተጠሪው በሰበር መልሱ ላይ ገልጿል፡፡አመልካችም በመልስ መልሳቸው ይህንን አላስተባበሉም፡፡ ተጠሪው የኤሌክትሪክ እና የመብራት መስመሮችን በማቋረጡ ምክንያት አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል እንዳልቻሉ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከቤቱ ያገኙት ጥቅም አለመኖሩን በሰበር አቤቱታቸው ላይ የገለጹ ሲሆን ተጠሪው በሰጠው መልስ አመልካቹ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት የኤሌክትሪክ እና የመብራት መስመሮች ስለተቋረጡባቸው ሳይሆን በአዲሱ የንግድ ምዝገባ አዋጅ አግባብ እንደገና ለመመዝገብ እና ፈቃዳቸውን ለማሳደስ የኪራይ ውል ማቅረብ ስለነበረባቸው እና ማቅረብ ስላልቻሉ መሆኑን ገልጾ ከመከራከር በቀር አመልካች በንግድ ቤቱ መገልገል ያቆሙት  ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ስላለመሆኑ የማስተባበያ ክርክር አላቀረበም፡፡በመሆኑም አመልካች በካሬ ሜትር በብር 30 ሂሳብ ኪሳራውን ለመክፈል የሚገደዱት ከ01/11/2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 22/09/2003 ዓ.ም ድረስ ላለው ጊዜ ነው፡፡

ከ22/09/2003 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን ለተጠሪው እስካስረከቡበት 11/10/2005 ዓ.ም ድረስ ላለው ጊዜ አመልካች ለተጠሪው ኪሳራ የመክፈል ግዴታ አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚለውን ነጥብ በተመለከተ በዚህ ነጥብ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት በምን ምክንያት እንደሆነ በቅድሚያ ተገቢው ማጣራት ሊደረግ ይገባል፡፡በከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች በቤቱ መገልገል ያቆሙት ተጠሪው የኤሌክትሪክ እና የመብራት መስመሮችን ስላቋረጠባቸው እንደሆነ በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪው ይህንን አድራጎት እንዳልፈጸመ ክዶ ተከራክሯል፡፡ በመሰረቱ አንድ ሰው ለባለንብረቱ ኪሳራ ሊከፍል የሚገደደው በሌላ ሰው የስራ ድካም ወይም የሌላ ሰው ሀብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ቀደም ሲል በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2162 ላይ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት በተጠሪው ጥፋት መሆኑ የሚረጋገጥ ከሆነ ጥቅም ባላገኙበት እና ጥቅሙን ሳያገኙ የቀሩትም በተጠሪው ጥፋት በሆነበት ሁኔታ ለተጠሪው ኪሳራ እንዲከፍሉ ሊገደዱ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት ተጠሪው እንደሚከራከረው የተጠሪው ባልሆነ እና ይልቁንም የራሳቸው የአመልካቹ በሆነ ምክንያት ከሆነ ደግሞ ቤቱን በወቅቱ ለተጠሪው ማስረከብ ሲገባቸው አላግባብ ይዘው በመቆየት ተጠሪውን ላሳጡት ጥቅም አመልካች ኪሳራ የማይከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት በማን ጥፋት ወይም የትኛው ወገን ኃላፊ ለሚሆንበት

ድርጊት ነው? የሚለውን ነጥብ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጭብጥነት ይዞ ያጣራው ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም በዚህ የክርክር ነጥብ ላይ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ያስችል ዘንድ ጉዳዩ ወደ ስር ፍርድ ቤት ተመልሶ ተገቢው ማጣራት ሊደረግ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 108108 በ19/06/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 89369 በ30/08/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተጠሪው ንብረት አላግባብ ለበለጸጉበት አመልካቹን ኃላፊ በማድረግ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. አመልካች የኪሳራ ገንዘቡን መክፈል የሚገባቸው በካሬ ሜትር በብር 50 (ሃምሳ) ሂሳብ ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. አመልካች የኪሳራ ገንዘቡን መክፈል የሚገባቸው በካሬ ሜትር በብር 30 (ሰላሳ) ሂሳብ ነው በማለት ወስነናል፡፡
5. በንግድ ቤቱ መገልገል ከጀመሩበት ከ01/11/2001 ዓ.ም. ጀምሮ በቤቱ መገልገል እስካቆሙበት 22/09/2003 ዓ.ም. ድረስ ላለው የ22 ወራት ከ21 ቀናት ጊዜ በካሬ ሜትር በብር 30 (ሰላሳ) እና በወር በብር 10,350 ሂሳብ ተሰልቶ የሚገኘውን ውጤት ብር 234,945 (ሁለት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት) አመልካቹ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ከ19/06/2005 ዓ.ም. ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪው እንዲከፍሉ ወስነናል፡፡
6. ከላይ በውሳኔው ክፍል ውስጥ በተመለከተው መሰረት አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት በምን ምክንያት ወይም ከግራ ቀኙ መካከል የትኛው ወገን ኃላፊ በሚሆንበት አድራጎት ምክንያት እንደሆነ በግራ ቀኙ እና ተገቢ ሆኖ ባገኘው ማስረጃ ሁሉ ካጣራ በኃላ አመልካች ከ22/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ቤቱን ለተጠሪው እስካስረከቡበት 11/10/2005 ዓ.ም. ድረስ ላለው ጊዜ ለተጠሪው ኪሳራ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆን አለመሆኑን በተመለከተ

ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ወስነናል፡፡

7. እንዲያውቀው እና ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
8. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 134825 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ05/11/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡ ይጻፍ፡፡
9. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
10. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

# ወንጀል

የሰ/መ/ቁ. 105289

መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** አቶ ተፈሪ ንጉሴ ጥላሁን - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ህግ /ዐ/ህግ በላይ ወርቅነህ ቀረቡ/

የመዝገብ ቁጥር 105290 ከዚህ መዝገብ ጎን ለጎን ተመርምሮ ተጣምሮ ተወስነኗል፡፡ መዝገቦቹ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈጸሙ በመሆኑ በሰበር ይታረምልኝ የሚል አቤቱታ በማቅረቡ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ የማታለል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በመ/ቁ. 136720 ሁለት ክሶች አቅርቧል፡፡ አንደኛው ክስ የወ/ህ/ቁ 692(1) የተመለተከውን በመተላለፍ ከግበረ አበሩ በመመሳጠር ባልሽ ጥር 2005 ይሞታል ከመሞቱ በፊት ገንዘብ አምጪ በማለት አሳሳች ነገሮችን በመናገር ከግል ተበዳይ መሰረት ስንታየሁ አንድ መቶ ሰላሳ ሺህ ብር እና ዋጋው ሀያ አምስት ሺህ ብር የሆነ ወርቅ በማታለል መወሰዱ ፤ ሁለተኛው ክስ የወ/ህ/ቁ.692(1) የተመለከተውን በመተላለፍ የግል ተበዳይ ወ/ሮ አጸደ ስንታየሁ ባለቤትሽ ይህንን ሱስ የሚያቀመው ገንዘብ እና ጌጣጌጥ ስትስጪኝ ነው ፤ ገንዘቡ እና ጌጣጌጡም ተፀልዮበት ሲመልስ ነው የሚድነው በማለት ሀምሳ ሺህ ብር እና ዋጋው ዘጠና ሁለት ሺህ ብር የሆነ ወርቅ ከእነ መጫወቻው መወሰዱን የሚያሳይ ነው፡፡ ሌለው ክስ በመ/ቁ. 136734 የቀረበ ሲሆን አመልካች ግበረ አበሩ መላከ ገነት ሳሙኤል አስፋው የተባሉ

ግለሰብ የግል ተበዳይ የሆነችው ወ/ሮ ዘበናይ ከበደን የተሳሳተ እምነት በመጠቀም የሚያድንሽን ሰው አውቃለሁ ላገናኝሽ በማለት ከአሁኑ አመልካች ካገናኙዋት በኋላ ፤ ከያዘሽ በሽታ በህክምና አትድኝም እኔ ነው የሚያድነሽ ለዚህም አንድ መቶ ስልሳ ሺህ ብር እና ዋጋው ስልሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር የሚሆን ወርቅ ተቀብሎ በመሰወሩ ወ/ህ/ቁ. 692(1) የተመለከተውን ተላልፏል የሚል ነው፡፡

አመልካች የቀረበበት ክስ ክዶ በመከራከሩ ፍ/ቤቱ የዐ/ህግ ምስክሮች አዳምጧል፡፡ አመልካችም የበኩሉን የመከላከያ ማስረጃ በማስቀረብ አሰምቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በዐ/ህግ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የተለያዩ የማታለያ ዘዴዎች ተጠቅሞ በሁለቱም መዝገቦች የተጠቀሱትን የግል ተበዳዮች ገንዘብ እና ወርቅ መወሰዱ ፤ የማታለል ድርጊቱ ሲፈጸም ዋና ወንጀል አድራጊ በመሆን የተሳተፉት የግል ተበዳይ አፀደ ስንታየሁ የነፍስ አባት የሆኑት መላከ ገነት የተባሉትን ግለሰብ አመልካች በሽታን የመፈወስ ችሎታና አቅም እንዳለው በመግለጽ የግል ተበዳዮች የተሳሳተ እምነት እና ግምት እንዲይዙ ማድረጋቸው ፤ በአመልካች በኩል የቀረበው አንድ የመከላከያ ምስክርም ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ እና ቦታ አመልካች ከአዲስ አበባ ውጭ የነበረ ስለመሆኑ የሰጠው የምስክርነት ቃል ተአማኒነት የሌለው እና የዐ/ህግ ክስና ማስረጃ የማያስተባብል ነው በማለት በሶስቱም ክሶች ጥፋተኛ ነው በማለት ፈርደዋል፡፡ ቅጣት በተመለከተም በዓቃቤ ህግ በኩል የቀረበው አንድ የቅጣት ማክበጃ እንዲሁም በአመልካች በኩል ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች በመቀበል በመ/ቁ. 136720 በሁለቱም ድርጊቶች በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 6,000 እንዲሁም በመ/ቁ 136734 በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 2,000 የሁለቱም ድምር በወ/ህ/ቁ 186 መሰረት በስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 8,000 መቀጮ እንዲቀጣ ወሰኗል፡፡

አመልካች በሁለቱም መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ የጠየቀ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወደ ጉዳዩ ለመግባት የሚያስችል በቂ ምክንያት ባለመገኘቱ ይግባኙን በማሰናበት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ በመሆኑ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር አደርገዋል፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት፡- የወንጀል ድርጊቱን አለመፈጸሙን ፤ ተፈጸመ የተባለው ድርጊት አንድ ወንጀል ከመስራት ሐሳብ የመነጨ መሆኑን ፤ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የቅጣት መመሪያ አዲስ ሳይሆን የቀደም መሆን እንዳለበት ወንጀሉ ከሌላ ግብረ አበር በመሆን ፈጽመዋል መባሉ በአግባቡ አለመሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የሰጠው መልስ ያስቀርባል ከተበለው ነጥብ አንፃር ሆኖ ወንጀሉ ከብዶ መወሰኑ በህጉ አግባብ መሆኑ ፤ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የቅጣት መመሪያ ግን

ለአመልካቹ የሚጠቅም የቀደሞ የቅጣት መመሪያ ከሆነ ቢወሰድለት እንደማይቃወም ገልፀል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚሹ መሰረታዊ ነጥቦች አንደኛው የስር ፍርድ ቤቶች ወንጀሉ በግብረ አበርነት የተፈጸመ ነው በማለት በወ/ህ/ቁ. 84(1)(መ) ጉዳዩን በማክበድ መወሰናቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? ሁለተኛ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው ወይስ ቁጥር 2/2006? የሚሉ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ነጥብ በተመለከተ፡- አመልካች በሶስት የግል ተብዳዮች የማታለል ወንጀል በመፈጸም ጥሬ ገንዘብና ወርቅ መውሰዱ የስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣናቸው ከድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ለመፈጸም ግብረ አበር ሆነዋል የተባሉት መላከገነት የተባሉ የቤተክርስትያን ሰው ነኝ ባይ ሲሆኑ አፀደ ስንታየሁ የተባለችው ተባዳይ የነፍስ አባት መሆናቸው የተካደ ጉዳ አይደለም፡፡ የግል ተበዳዮች አለን የሚሉት የጤና ችግር ፤ ሊመጣ ከሚችለው አስደንጋጭ ችግር ለመታደግ ወይም ባለቤታቸው ከነበራቸው የባህሪ ችግር ለማስተካከል ገንዘብና ወርቅ በማስያዝ ፀሎት ማድረግ እንደ ብቸኛ አማራጭ መወሰዱ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡ የግል ተብዳዮች ገንዘብና ወርቅ እንዲሰጡ የማሳመን ሚና የተጫወቱት የግል ተበዳይ አፀደ ስንታየሁ የነፍስ አባት ሲሆኑ በሶስቱም የግል ተበዳዮች ከፍተኛ የመንፈስ ተፅዕኖ የፈጠሩት እኚሁ የነፍስ አባት መላከገነት መሆናቸው ከአጠቃላይ የመዝገቡ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ ከህጉ ጋር ስናገናዝበው አንድ ሰው የወንጀል ድርጊቱ የፈጸመው ከሌላ ሰው ስምምነት በማድረግ ከሆነ እንደ ማክበጃ እንደሚወሰድ በወ/ህ/ቁ. 38(1) እና 84(1)(መ) ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ግበረ አበር የነበሩት ግለሰብ የግል ተበዳዮች በማታለል ገንዘብና ወርቅ ለመውሰድ አስቀደመው በመስማማት ድርጊቱ ስለመፈጸማቸው ከቀረበው የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የምንረዳው ነው፡፡ አመልካች እና ግበረ አበር የተባሉትን መላከገነት የግል ተበዳዮች ሊያሳምን ይችላል ብለው ያቀዱትን ስልት ወደ ተግባር በማሸጋገር የግል ተበዳዮች ማህበራዊ ችግር ፤ የጤና ችግር እንደምክንያት ተጠቅመው ሃይማኖታቸውን መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የማታለል ድርጊት ፈጽመዋል፡፡ የግል ተበዳይ አፀደ ስንታየሁ የነፍስ አባት የሆኑትን መላከገነት የተባሉትን ግለሰብ የግል ተበዳዮች በአመልካች ላይ እምነት ኖሯቸው ገንዘብና ወርቅ እንዲሰጣቸው ያላቸው ሀይማኖታዊ ግንኙነት ያለአግባብ ተጠቅመውበታል፡፡ ይህ ደግሞ በወ/ህ/ቁ. 84(1) (መ) እንደተመለከተው ወንጀሉ በሁለት ሰዎች ስምምነት (prior agreement) የተፈጸመ መሆኑ

የሚሳይ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች እንደ ማክበጃ መውሰዳቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን አያሳይም፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ቅሬታ የህግ መሰረት የለውም፡፡

ሁለተኛው ነጥብ በተመለከተ፡- አመልካች የተከሰሰባቸው የማታለል ወንጀሎች በ 2005 ዓ/ም የተፈጸሙ ናቸው፡፡ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 ስለመሆኑ ግራ ቀኙ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 95438 እና ሌሎች መዝገቦች በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለተከሳሽ የሚጠቅም የቅጣት መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ ወስኗል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ድርጊቱ ሲፈጸም በተግባር ላይ በነበረው የቅጣት መመሪያ መሰረት ለእያዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሁለት እርከን የሚቀነስለት መሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በመ/ቁ 136720 በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ የሁለቱም ድንጋጌዎች ቅጣት ተደምሮ በእርከን 22 የሚወድቅ ሲሆን በሁለተኛው መዝገብ የመ/ቁ. 136734 እርከን 17 ስር የሚወድቅ ነው፡፡ በሁለቱም መዝገቦች ቅጣት ተነጣጥሎ የተወሰነ ሲሆን አፈጻጸም በተመለከተ ግን ተጣምሮ እንዲፈጸም የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው የመዝገብ ቁጥር 136720 አመልካች ሁለት የማቅለያ ምክንያቶች በማቅረቡ በእያዳንዱ ማቅለያ በቀድሞ የቅጣት መመሪያ አንቀጽ 17 መሰረት ሁለት እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ በአጠቃላይ ከመነሻ እርከኑ አራት እርከን ወደታች ዝቅ ይላል፡፡ በዚህ መሰረት በእርከን 18 ሥር የሚወድቅ ነው፡፡ ሁለተኛው የመዝገብ ቁጥር 136734 በእርከን 15 ሥር የሚወድቅ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የወንጀል ድርጊቱ በ 2005 ዓ.ም የተፈፀመ መሆኑን ፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ 95438 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ በየትኛውም ደረጃ ባሉ ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) የተደነገገ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6(1) እና በቀድሞ የቅጣት መመሪያ መሰረት ያቀረበው ማቅለያ የበለጠ ዝቅ የሚያደርግለት ነበሩ ፣የቅጣት መመሪያ መሆኑ እየታወቀ መታለፉ በአግባቡ ባለመሆኑ ፤ በቅጣት ረገድ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማሻሻል መወሰኑ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች የፈጸመው የማታለል ወንጀል ያስከተለው ጉዳት በሌላ በኩል አመልካች ሊያስተምር ሊያስጠነቅቅ የሚያስችል የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ የሚያሳካ ቅጣት መወሰን ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች በ መ/ቁ 136720 የተወሰነበትን ቅጣት በማሻሻል በእርከን 18 ከተደነገገው 4 ዓመት ጽኑ እስራት በመውሰድ በመ/ቁ 136734 በእርከን 13 ከተደነገገው ሁለት ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራት በመውሰድ በድምር በስድስት ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራት እና 8,000 ብር መቀጮ እንዲቀጣ የሚከተለው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

# ው ሳ ኔ

1 የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 136720 በ 08/04/2006 የሰጠው ፍርድ ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 101684 በሰኔ 30/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡ ይፃፍ፡፡

2 አመልካች በተከሰሰባቸው የወ/ሕ/ቁ 692(1) ሥር ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡

3 የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት አመልካች ከአሁኑ በፊት የታሰረበት ካለ በቅጣቱ የሚካተት ሆኖ እጁ ከተያዘበት ጀምሮ በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነ መሆኑን አውቆ እስራቱን ተቆጣጥሮ እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

4 የዚህ ፍርድ ግልባጭ በሰ/መ/ቁ 105290 ይያያዝ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሃ/ወ**

የሰ/መ/ቁ 105406

መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ ኃይሉ ወልዴ መኮንን - ጠበቃ ጳውሎስ ተሰማ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን ለእርሳቸው አገልግሎት ባልታሰበ ወይም እርሳቸውን በማይመለከት ሰነድ የመገልገል የወንጀል ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠባቸው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-አመልካች ጥቅምን ወይም መሻሻልን ለማግኘት በማሰብ ትክክለኛ ስማቸው ኃይሉ ወልዴ ሆኖ እያለ ሰይፉ ወልዴ እንደሆነ አድርገው በመግለጽ ለእርሳቸው አገልግሎት ያልታሰበውን ወይም እርሳቸውን የማይመለከተውን እና የወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ የሆነውን ከመድኃኒዓለም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሰጠ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ የምስክር ወረቀት (ትራንስክሪፕት) እና ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መልቀቂያ የምስክር ወረቀት በማቅረብ በየካቲት ወር 1977 ዓ.ም. በኢትዮጵያ አየር መንገድ የተቀጠሩ በመሆኑ፣ ከተቀጠሩ በኃላ ወንጀሉን ለመደበቅ በማሰብ ህዳር 30 ቀን 1979 ዓ.ም ፍርድ ቤት ቀርበው ሰይፉ ወልዴ እና ኃይሉ ወልዴ በሚሉ ሁለት ስሞች ሲጠሩ እንደነበረ እና አሁን ግን ኃይሉ ወልዴ በሚለው ስም ብቻ ለመጠራት እንደሚፈልጉ በመግለጽ በፍርድ ቤት በማስወሰን ይህንን የፍርድ ቤት ውሳኔ ለተቀጠሩበት መስሪያ ቤት አቅርበው ከማህደራቸው ጋር እንዲያያዝ በማድረግ እስከ ህዳር 19

ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በበረራ አስተናጋጅነት እና በመሪ የበረራ አስተናጋጅነት ሲሰሩ የቆዩ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 385(1)(ለ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ሀሰተኛ በምስክር ወረቀት የመገልገል ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቀው በክሱ የተመለከተውን ወንጀል አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ያቀረባቸውን ሶስት ምስክሮች ምስክርነት ከሰማ እና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ አመልካች መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካች የሰው መከላከያ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ መግለጫው ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 ዘርዝሮ በማስረጃነት ካቀረባቸው ሰነዶች መካከል ሶስቱን በመከላከያነት ጭምር የጠቀሱ ከመሆኑም በላይ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ኃይሉ ወልዴ በሚል ስም የተሰጠው የምስክር ወረቀቶችን፣የስራ እድገት ደብዳቤን እና በዚሁ ስም የተሞላ የጡረታ ቅጽ በመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ በተጠሪ የቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ አስተባለዋል ሊባሉ የሚችሉት በወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ ስም በተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች ለስራ ቅጥር ስላለመገልገላቸው ወይም የትምህርት ማስረጃዎቹ የሌላ ሰው ሳይሆኑ የራሳቸው ስለመሆናቸው በማስረዳት መሆኑን እና ይሁን እንጂ አመልካች ያቀረቧቸው የመከላከያ ሰነዶች ከላይ ከተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች አንዱንም የማያስረዱ መሆኑን ገልጾ አመልካች ባቀረቡት የሰነድ መከላከያ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት በክሱ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን፣ድንጋጌው የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ መሆኑን፣ አመልካች ሰነዱን በመገልገል ከሃያ ዓመት ላላነሰ ረጅም ጊዜ ያልተቋረጠ ጥቅም ያገኙ እና ፍርድ ቤትን ሳይቀር አሳስተው የመጀመሪያውን ወንጀል ለመሸፈን ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸው በድርጊቱ አለመፀፀታቸውን የሚያሳይ ነው በማለት የእስራት ቅጣቱን አማራጭ በመውሰድ እና ወንጀሉንም በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ በከባድ ደረጃ በመመደብ፣በድንጋጌው ስር በከባድ ደረጃ ለተመደበ ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ከተቀመጠው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ የሁለት ዓመት እስራት መነሻ አድርጎ በመያዝ፣ይህ የቅጣት መጠን በመመሪያው አባሪ አንድ በእርከን 10 ስር የሚወድቅ መሆኑን፣በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አለመኖሩን፣የአመልካቹ የዘወትር ጠባይ መልካምነት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው በሁለት የማቅለያ ምክንያትነት ሲያዙ ፍቅድ ስልጣኑን ከእርከን 10 ወደ እርከን 8 ዝቅ የሚል መሆኑን በዝርዝር ገልጾ

በመጨረሻ አመልካች በእርከን 8 በተቀመጠው ፍቅድ ስልጣን መሰረት  በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ወንጀሉን ፈጽመዋል ከተባለበት ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጠር ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት አመልካች ላቀረቡት መቃወሚያ የስር ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ድርጊቱ ከቆመበት ህዳር ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ እንጂ ድርጊቱ መፈጸም ከጀመረበት ከ1977 ዓ.ም. ጀምሮ አይደለም በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 219(2) ድንጋጌ አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ በአብላጫ ድምጽ በተሰጠ ትዕዛዝ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

1. በአመልካች የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?
2. በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች የተከሰሱበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ሲሆን በሕጉ በተለየ ሁኔታ በግልጽ ካልተደነገገ በቀር ቀላል እስራት ከአስር ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 106(1) ተመልክቷል፡፡በሌላ በኩል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜን አስመልክቶ ከአንድ ዓመት በላይ በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል የክስ ማቅረቢያው የይርጋ ጊዜ አምስት ዓመት ስለመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 217(1)(ሠ) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በመርህ ደረጃ ጥፋተኛው ወንጀሉን ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ እና ይሁን እንጂ የወንጀሉ ድርጊት እየተደጋገመ ተፈጽሞ እንደሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው የወንጀል ድርጊት ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ፣እንዲሁም የወንጀሉ ድርጊት ለረጅም ጊዜ ሲፈጸም የቆየ ከሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የወንጀሉ ድርጊት ካቆመበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 219(2) ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ አመልካች በአየር መንገዱ የተቀጠሩት በወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ ስም የተሰጠውን የትምህርት

ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ እና እስከ ህዳር ወር 2005 ዓ.ም. ድረስ በአየር መንገዱ ውስጥ በስራ ላይ ሊቆዩ የቻሉትም በእነዚሁ የትምህርት ማስረጃዎች አማካይነት እና መነሻ በተፈጠረ የስራ ቅጥር ግንኙነት ወይም የስራ ውል መሰረት መሆኑ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡ የይርጋ ጊዜው መቆጠር መጀመር የሚገባው ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ነው በማለት አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት አመልካች ለወንድማቸው ለአቶ ሰይፉ ወልዴ የተሰጠውን የትምህርት ማስረጃ በ1977 ዓ.ም ለኢትዮጵያ አየር መንገድ አቅርበው የተመዘገቡ ቢሆንም የተቀጠሩት ግን ፈተናውን አመልካች ራሳቸው ተፈትነው በመሆኑ እና የተቀጠሩበትን ስራ ለረጅም ጊዜ ሲሰሩ የነበረውም አየር መንገዱ በሰጣቸው ስልጠና ባገኙት ዕውቀት እንጂ በምዝገባ ጊዜ ባቀረቡት የትምህርት ማስረጃ ባለመሆኑ ስልጠናውን አጠናቀው ስራ ከጀመሩ እና በተለይ ደግሞ ኃይሉ ወልዴ በሚለው ስም ብቻ እንዲጠሩ በፍርድ ቤት ካስወሰኑበት ከ1979 ዓ.ም. ጀምሮ በሰይፉ ወልዴ ስም በተሰጠው የትምህርት ማስረጃ ተገልግለዋል ወይም ጥቅምን ወይም መሻሻልን አግኝተዋል ሊባሉ አይገባም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ይሁን እንጂ አመልካች ለስራው የተመዘገቡትም ሆነ ፈተናውን ወስደው ለስልጠና እና ለስራ ቅጥር የበቁት የእርሳቸው ባልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች በመገልገል በመሆኑ አመልካች ስልጠናውን ካጠናቀቁበት ቀንም ሆነ ስራ ላይ ከተሰማሩበት ቀን ጀምሮ የትምህርት ማስረጃዎቹ አገልግሎት ተቋርጧል ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ለስራው የተቀጠሩት የራሳቸው ባልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች በመገልገል መሆኑን ስልጠናውን ባጠናቀቁበት ቀን ወይም ስራ ላይ በተሰማሩበት ቀን ለአየር መንገዱ አስታውቀው የነበረ ስለመሆኑ እና በዚህም ምክንያት የእርሳቸው ባልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች የመገልገላቸው ሁኔታ እንዲያበቃ ወይም እንዲቋረጥ የተደረገ ስለመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ለረጅም ጊዜ ሲፈጸሙ የቆዩትን ወንጀሎች የይርጋ ዘመን አቆጣጠር በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 79389 በ12/07/2005 ዓ.ም. የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች ወንጀሉን አላደረግኩም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የራሳቸው ያልሆኑትን እና ሰይፉ ወልዴ ለተባሉ ወንድማቸው የተሰጡትን የትምህርት ማስረጃዎች የራሳቸውን ፎቶግራፍ በመለጠፍ የራሳቸው እንደሆኑ አስመስለው ለኢትዮጵያ አየር መንገድ በማቅረብ በ1977 ዓ.ም ለስራ ቅጥር የተገለገሉበት መሆኑ እና በዚህ ሁኔታ በተቋቋመ የስራ ውል መሰረት እስከ ህዳር ወር 2005 ዓ.ም ድረስ ጥቅም ሲያገኙበት የነበረ መሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን እና

አመልካች በቤተሰብ ውስጥ ሰይፉ በሚል ሌላ ስም ተጠርተው የማያውቁ፣ ይልቁንም ሰይፉ ወልዴ ከኢትዮጵያ ውጭ በመኖር ላይ የሚገኙ የአመልካች ታላቅ ወንድም ስለመሆናቸው የአመልካች ወንድም መሆናቸውን በገለጹት 2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጭምር የተመሰከረ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካች ያቀረቧቸው የሰነድ ማስረጃዎች ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች በወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ ስም በተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች ለስራ ቅጥር ስላለመገልገላቸው ወይም የትምህርት ማስረጃዎቹ የሌላ ሰው ሳይሆኑ የራሳቸው ስለመሆናቸው የማያስረዱ መሆኑንም መዝገቡ ያመለክታል፡፡ወንጀሉን ስለመፈጸሜ በማስረጃ አልተረጋገጠብኝም ወይም የተጠሪን ማስረጃ በመከላከያዬ አስተባብያለሁ በማለት አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በግልጽ ያቀረቡት ክርክርም የለም፡፡የቅጣት ውሳኔውም ቢሆን ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የወንጀሉን አፈጻጸም ሁኔታዎች፣ሕጉን እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት በማድረግ በአግባቡ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 114900 በ16/10/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152347 በ13/12/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች እንዲሁም አመልካች ለሚገኙበት ማረሚያ ተቋም ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**የ/ማ**

የሰ/መ/ቁጥር 104923

መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡-ወ/ሮ አበባ አረፋይኔ ጠበቃ መረሣ ፍሰሃ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡-የትግራይ ክልል አቃቤ ሕግ - ተልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ አመልካች በአድዋ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጸናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ባለመስማማት ቅሬታቸዉ በሰበር እንዲታይላቸው ሐምሌ 30 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

በአድዋ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበዉ ክስ በ1996 ዓ.ም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1/ ሥር የተመለከተዉን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ከፍ ያለ ጥቅምና ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት አስበው ከስር 1ኛ ተከሳሽ ከነበረው ከአቶ ተክለማሪያም ገ/ማርያም ጋር አባሪ ተባባሪ ሁነው ወደ ግል ተበዳይ መኖሪያ ቤት ድረስ ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ/ም ከቀኑ 7፡00 ሲሆን በመሄድ ከበሽታሽ የሚፈውስ ደብተራ አለ በሚል የአሁኗ አመልካች የሥር 1ኛ ተከሳሽን ወደ ግል ተበዳይ ቤት ልካባት የሥር 1ኛ ተከሳሽም ወደ ግል ተበዳይ ቤት ገብቶ ስሜ ይትባረክ ሽፈራው እባለላሁ ብሎ በሽታሽ በወርቅሽ ስለሆነ ወርቅሽን ሁሉ አቅርቢ፣አንድ እንዳታስቀሪ ብሎ ሎሚ፣ዶሮና አረቄ አቅርቢ ብሎአት ወርቁን ከአቀረበችለት በአቦጀዲ ጠቅልሎ መድሃኒት አድርጌበታለሁ በማለት ሌላ ተመሳሳይ አቦጀድ የተጠቀለለ ቆርኪ ጠቅልሎ አስቀምጦ ወርቁን መድሃኒት አድርጌበት ስለሆንኩ በኃላ መጥቼ ራሴ እስከምፈታው እንዳትነኩ ብሎ ባለ ሃያ አራት ካራት ወርቅ ግምቱ ብር 447,000.00 የሆነ 447 ግራም የሆነ

ወርቅ ይዞ መሰወሩን ዘርዝሮ አመልካችና የስር 1ኛ ተከሳሽ በግብረአበርነት የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች የዕምነት ክህደት ቃል እንዲሰጡ ሲጠየቁ የቀረበባቸውን ክስ አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ዐቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸዉን የሠነድና የሰዉ ማስረጃ በማቅረብ አሰምቷል፡፡ አመልካች እንዲከላከሉ በተሰጠዉ ብይን መሠረት አሉኝ ያሏቸውን ማስረጃዎችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን የመረመረዉ የወረዳው ፍርድ ቤትም አመልካች በክሱ ላይ ተጠቅሶ የቀረበባቸውን የሕግ አንቀጽ በመተላለፍ ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት ፍርድ ከሰጠ በኃላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ መመልከቱን ጠቅሶ አመልካችን በሶስት አመት ከአምስት ወር ቀላል እስራት እና በብር 500.00(አምስት ሺህ) እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፣ የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ አቤቱታቸው ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በወረዳው ፍርድ ቤት የታየው ከስልጣኑ ውጪ መሆኑን፣ አቃቤ ሕግ አመልካች በወንጀሉ የነበራቸውን ተሳትፎ እንደ ክሱ ያለማስረዳቱን፣ በዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የግል ተበዳይ እና የስር 1ኛ ተከሳሽ ቀደም ብለው የሚተዋወቁ መሆናቸው መነገሩም አመልካች በወንጀሉ አፈፃጸም ተሳትፎ ያልነበራቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፣ የቅጣት ውሳኔም ተገቢውን የቅጣት አወሳሰን ስርዓት ተከትሎ የተወሰነ አይደለም የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ምክንያት በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን እንደሚከተለዉ መርምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጉ አበይት ጭብጦች፡-

1. አመልካች በክስ ቻርጁ ላይ የተገለጸውን የወንጀል ተግባር ፈጽመዋል ተብሎ ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣
2. አመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት አወሳሰን ረገድ የደረጃ አወሳሰን አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤት የወሰነዉ ቅጣት ተገቢነት አለው? ወይስ የለውም? የሚሉት ናቸዉ፡፡

<u>**የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u> ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ የመሠረተዉን የማታለል ወንጀል ለማስረዳት የግል ተበዳይንና ሌሎች ምስክሮችን በምስክርነት ያቀረባቸዉ ሲሆን ምስክሮቹም ቀጥተኛ የሆነ የምስክርነት ቃል የሰጡና የአካባቢ ምስክሮች ናቸው፡፡ የአይን ምስክር የሆኑት 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ሲሆኑ አመሰካከራቸውም የስር አንደኛ ተከሳሽ በአሁኗ አመልካች

አማካኝነት በክሱ በተጠቀሰው ጊዜ ወደ ግል ተበዳይ ቤት ሂዶ ስሜ ይትባረክ ሽፈራው እባለላሁ ብሎ በሽታሽ በወርቅሽ ስለሆነ ወርቅሽን ሁሉ አቅርቢ፣አንድ አንዳታስቀሪ ብሎ ሎሚ፣ዶሮና አረቄ አቅርቢ ብሏት ወርቁን ከአቀረበችለት በኂላ በአቦጀዲ ጠቅልሎ መድሃኒት አድርጌበታለሁ በማለት ሌላ ተመሳሳይ አቦጀዴ የተጠቀለለ ቆርኪ ጠቅልሎ አስቀምጦ ወርቁን መድሃኒት የአድርግሁበት ስለሆነ በኃላ መጥቼ ራሴ እስከምፈታው እንዳትነኩ ብሎ ባለ ሃያ አራት ካራት ወርቅ ግምቱ ብር 447,000.00 የሆነ 447 ግራም የሆነ ወርቅ ይዞ መሰወሩን፣አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ወደ ግል ተበዳይ ከሄዳቸውም በተጨማሪ የስር 1ኛ ተከሳሽ  በግል ተበዳይ ቤት ውስጥ እያለ አመልካች ስልክ እንደደወሉለትና ለምስክሮቹ ገልጾ ከግል ተበዳይ ቤት ወጥቶ ወደ አመልካች ደርሶ መመለሱንና አመልካች ልጃቸውን እየላኩ ሁኔታውን ሲከታተሉ የነበሩ መሆኑን ዘርዝረው የመሰከሩ መሆናቸውን ከውሳኔው ግልባጭ ተረድተናል፡፡ ምስክሮቹ ይትባረክ ሽፈራው የተባለውና ወርቁን የወሰደው የስር 1ኛ ተከሳሽ አመልካች የአጎቴ ልጅ ነው ብለው መሄዳቸውንም መመስከራቸውን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ሌሎች ምስክሮች የአከባቢው ምስክሮች ሲሆኑ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ወደ ግል ተበዳይ ሲገባ፣ ከጊዜ በኂላ የግል ተበዳይ ግለሰቡ ሲሰወሩ የሚያውቁት መሆን ያለመሆኑን ሲጠየቋቸው እንደነበርና ወርቅ ዘርፎ የተሰወረባቸው መሆኑን 1ኛ እና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የነገራቸው መሆኑን የገለፁ ምስክሮች ናቸው፡፡

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ጥፋተኛ ለማድረግ በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን የሰው ምስክሮች አመሰካከር ይዘት ከላይ የተጠቀሰው መሆኑን በውሳኔው ላይ የገለፁት ጉዳይ ሲሆን ፍርድ ቤቶቹ በፍርድ ሐተታው በግልጽ ያስቀመጡት ድምዳሚውም ከአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል አመልካች የስር 1ኛ ተከሳሽ የግል ተበዳይን ከበሽታ እፈውሳለሁ በሚል ወርቃቸውን አታልሎ ሲወስድባቸው  ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑን አየን፣ ወርቁን ይዞ የተሰወረው ሰው የአመልካች ትክክለኛ ዘመዳቸው ሳይሆን የአጎታቸውን ልጅ መሆኑንና ስሙን ሁሉ ቀይሮ ከግል ተበዳይ ጋር ሲተዋወቅ አመልካች ይህንኑ ለግል ተበዳይና ለ2ኛ ምስክር ሊታመን በሚችል ሁኔታ የገለፁ መሆኑን መመልከታቸውንና ሁኔታውን እውነት መስሏቸው መቀበላቸውን መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የወረዳው ፍርድ ቤትም ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን የደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ የሆነ ስልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ  ፍርድ ቤት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡በመሆኑም አመልካች በማታለል ድርጊቱ አፈጻጸም ቀጥተኛ ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑ፣በስር 1ኛ ተከሳሽ ሲፈጸም የነበረውን ሁኔታ ልጃቸውን እየላኩ መከታተላቸው ውጤቱን በመቀበል የራሳቸው ማድረጋቸው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ

10 ድንጋጌዎች መሰረት ከተሰጠው ስልጣን አኳያ አመልካች በወንጀል ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑን በስር ፍርድ ቤቶቸ የተደረሰውን ድምዳሜ እንዳለ የሚቀበለው ነው፡፡

አመልካች ከሚከራከሩባቸው ነጥቦች ውስጥ አመልካች የድርጊቱ ተሳታፊ መሆናቸው በአቃቤ ህግ ማስረጃዎች አልተገለፀም በሚል ነው፣የግል ተበዳይ የስር 1ኛ ተከሳሽን ቀደም ብለው ያውቁት ነበር በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ የወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ በቂና አሣማኝ በሆነ ሁኔታ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙንና የወንጀል ድርጊቱን ፈፃሚውን ማንነት በትክክል ለይቶ ማሳየት ያለበት ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትንና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡አንድ ሰው ለወንጀል ድርጊት ኃላፊ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው ወንጀሉ መስራቱ ወይም መፈፀሙና ተሰራ ወይም ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ሲጋገጥ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፣32፣40፤57፣58(1) እና ከወ/መሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141፣142 እና 149 ድንጋጌዎች አገላለፅና መንፈስ መመልከት የምችለው ጉዳይ ነው፡፡ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ የሚቆጠረው ወንጀሉን  እርሱ ራሱ በቀጥታ ቢያደርግ ወይም በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ ሀሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና  በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተከፋይ በመሆን ወንጀሉን  የራሱ ያደረገ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ለ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ከሳሽ የሆነው አቃቤ ሕጉም ይህንኑ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት አለበት፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን የማታለል ተግባር ከግብረ አበራቸው ጋር ሁነው በቀጥታ ተሳትፈውና ውጤቱንም የራሳቸው በማድረግ ወንጀሉን የፈፀሙ መሆኑን የተነገረባቸው በጊዜውና በቦታው በነበሩት ምስክሮችና በጠንካራ የአካባቢ ምስክሮች መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃልም በመከከላከያ ማስረጃዎች ያልተስተባበለ መሆኑን ፍሬ ነገሩን አጣርተውና ማስረጃዎቹን መዝነው አረጋግጠዋል፡፡ስለሆነም አመልካች ለወንጀል ድርጊቱ ተሳታፊ የነበሩ መሆኑ በበቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የወንጀል ተጠያቂነት የለብኝም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(2)፣32(1(ሀ)(ለ)፣58 እና ስለ ማታለል ወንጀል የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ሁኖ ሰላላገኘነው አልተቀበልነውም፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692(1) ስር ማታለል ተፈጽሟል ለማለት አራት መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች መረጋገጥ አለባቸዉ፡፡ እነዚህም፡- አጥፊዉ ሆን ብሎ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን

ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባዉን ነገር በመደበቅ ወይም ሌላዉን ሰዉ የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ መግለጽ ይኖርበታል፣ ተበዳዩ መታለል ይኖርበታል ወይም በአጥፊዉ የተገለጸለትን አምኖ ሊቀበል ይገባል፣ በሀሰት የተገለጸለትን በማመን የፈጸመዉ ተግባር መኖር አለበት፣ እንዲሁም የግል ተበዳይ በመታለሉ ያጣዉ የገንዘብ ጥቅም ሊኖር ይገባል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስም እነኚህ በሕጉ የተመለከቱት መመዘኛዎች የተሟሉ በመሆናቸው አመልካችን ከወንጀሉ ተጠያቂነት የሚድኑበትን አግባብ አላገኘንም፡፡

<u>**ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ**</u>፡- ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1/ በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ ደረጃ የወጣለትና እርከኑ የተለየ ነዉ፡፡የግል ተበዳይ በተፈጸመባቸዉ የማታለል ወንጀል ምክንያት 447,000.00 ብር በጥሬ ገንዘብ አጥተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን እድሜና የጤና ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በቀላል እስራት ሊቀጡ እንደሚገባ ከለየ በኂላ የቅጣት መጠኑን አሰልቷል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ አመልካች የብር 447,000.00 ያለአግባብ ብልጽግና የማግኘት ሀሳብ የነበራቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም 447,000.00 ብር ደረጃ 6 ስር የሚወድቅ ሲሆን በእስራት እርከን 16፣ በገንዘብ መቀጮ ደግሞ እርከን 4 ላይ ያርፋል፡፡ በቅጣት ማክበጃነት በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ አንድ ማክበጃ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን ይህም የስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ቅድመ ስምምነት አድርገው ወንጀሉን መፈፀማቸውን የሚገልጽ ሲሆን ከድርጊቱ አፈፃጸም እና ከማታለል የወንጀል ድርጊት ባህርይ አንጻር ሲታይ ምክንያቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1(መ))ስር የሚወድቅ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ላይ አንድ ማቅለያ ምክንያት መያዙ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ለአመልካች በቅጣት ማቅለያነት ያለፈ ባህሪያቸው መልካም የነበረ መሆኑ በወ/ሕግ አንቀጽ 82/1/ሀ/ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በአንቀጽ 86 መሠረት ተይዞላቸዋል፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህን ቅጣቶች እንደ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች እንዳሉ ተቀብሏቸዋል፡፡

ይህ ችሎት አመልካች በቀላል እስራት አማራጭ መቀጣት ይገባቸዋል በሚል የስር ፍርድ ቤት ማመኑን ቢገነዘብም የስር ፍርድ ቤት መነሻ ቅጣቱን የያዘበት ሁኔታ ሕጉ ስለ ቀላል እስራት የጊዜ ገደብ በአንቀጽ 106 ከአስቀመጠው ጋር አብሮ የሚሄድ ሁኖ አላገኘውም፡፡ ይልቁንም የሥር ፍርድ ቤት በግል ተበዳይ ላይ ደረሰ የተባለውን የገንዘብ ጥቅም ጉዳት መጠን መሰረት አድርገን እርከኑ ሲታይ እርከን 16 ማረፉ ተገቢ ሁኖ በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ምን ያህል እርከን ሊቀንስ ይገባዋል? የሚለውን ጥያቄ ወንጀሉ የተፈፀመው ነባሩ መመሪያ ስራ ላይ በነበረበት ጊዜ መሆኑን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6 ይዘትና መንፈስ አንጻር ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ

ቢመለከተውም ከነባሩ መመሪያ አንቀጽ 16(6) ድንጋጌ አንፃር ለውጥ የሚያመጣ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ሁለት ማቅለያ ምክንያቶች እንዳሏቸው ከገለፀ በኃላ የቅጣት ማክበጃውን ይዞ እርከኑን ከእርከን 16 ወደ እርከን 17 ከፍ ከአደረገ በኂላ በዚሁ እርከን ለፍርድ ቤቱ በተተወው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ(ከሶስት አመት ከሶስት ወር እስከ ሶስት አመት ከአስራ አንድ ወራት) ሶስት አመት ከአምስት ወር ቀላል እስራት ወስዶ አመልካች በዚሁ የእስራት ቅጣት ጊዜ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ ሆኖም በመመሪያው መመሰረት የቅጣት ማክበጃ ከተወሰነ በኂላ ህጋዊ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሳይሰሉ አጥፊው በማረሚያ ቤት ሁኖ የሚታሰረው የእስራት ጊዜ መጠን ሊወሰን እንደማይችል በአንቀጽ 19 ስር የተመለከተው የቅጣት አሰላል ስርዓት ያሳያል፡፡ በመመሪያ መሰረት በድምሩ አራት እርከን ሲቀነስላቸዉ የእስር ቅጣቱ ከእርከን 17 ወደ እርከን 13 ስለሚወርድ በዚሁ እርከን ውስጥ የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከሁለት አመት ሶስት ወር እስከ ሁለት አመት ዘጠኝ ወር እስራት ነው፡፡

ከዚህ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ አመልካችና ያርማል፤ ለፈጸሙት አድራጎት ያስተምራታል፣ ሌሎችን ደግሞ ያስጠነቅቃል ባልነዉ በ2(ሁለት)አመት እንዲቀጡ መወሰኑ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁም መሠረት የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በአድዋ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06997 የካቲት 25 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04714 ሚያዚያ 08 ቀን 2006 ዓ/ም ፣በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 66316 ሰኔ 26 ቀን 2006 ዓ/ም በአመልካች ላይ ያስተላለፈዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለድርጊቱ ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ ነው፣ ቅጣቱን በተመለከተ ግን ተገቢውን የቅጣት አወሳሰን መርህ ያልተከተለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች በዚህ ጉዳይ የታሰሩት ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በ2 (ሁለት) አመት ቀላል እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. የክፍሉ ማረሚያ ቤት በዚህ ችሎት በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሰረት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የቅጣት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን እንዲያውቁት የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡

**መዝገቡን ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡** **ሩ/ለ**

የሰ/መ/ቁ. 95921

ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ/ ም

**ዳኞች**፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡- አቶ ብርሃኑ ኑርጋ - ጠበቃ አመሃ መኮንን - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በሙስና ወንጀል የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 29 እና 31 ድንጋጌዎች አግባብ የቀረበውን የውርስ ማመልከቻ መነሻ አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች እና ከእኚህ አመልካች ጋር በሙስና ወንጀል ተከሰው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠባቸው ሌሎች ስድስት ግለሰቦች ላይ ባቀረበው የንብረት ውርስ ጥያቄ ነው፡፡

የዋናው ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ተከሳሾች ከ1999 ዓ/ም እስከ 2000 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ የመንግስት ሰራተኛ፣ አስመጪና የእቃ አስተላላፊ ሁነው ሲሰሩ ሕገ ወጥ ጥቅም ለማግኘት አስበው በተለያዩ ዲክላራሲዮን ቁጥሮች ከአሳወቋቸው እቃዎች እና ከውጪ ለአስመጧቸው እቃዎች መክፈል የሚገባቸውን ብር 13,457,694.40 (አስራ ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአርባ ሳንቲም) ቀረጥና ታክስ ሳይከፈሉ የከፈሉ አስመስለው ከመቅረጫ ጣቢያ እቃዎቹን እንዲለቀቁ እና የፈፀሙት ወንጀል እንዳይደርስባቸው ለማድረግ እቃዎቹን የሚይዘውን መረጃ ከመስሪያ ቤቱ "አሲኩዳ" የመረጃ ሲስተም በማጥፋት የመንግስት ቀረጥ እንዳይሰበሰብ በማድረጋቸው በግብረአበርነት በስልጣን ያላግባብ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ አመልካችና ሌሎች የስር ተከሳሾች ጥፋተኛ ተብለው የእስራት ቅጣት የተወሰነባቸው መሆኑን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 66892 ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ያሳያል፡፡

ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ በዋናው የወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበባቸው ሰዎች ጥሬ ገንዘብና ሌሎች ንብረቶች ታግደው እንዲቆዩ አድርጎ የነበረ መሆኑን ጠቅሶ በእያንዳንዱ አጥፊ ስም የታገደውን የንብረት አይነትና የጥሬ ገንዘብ መጠን ዘርዝሮ በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ የተባሉት ግለሰቦች በድርጊታቸው በመንግስት ላይ ለደረሰው ጉዳት ማካካሻነት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ያለባቸው ናቸው በማለት ጠቅሶ በአመልካችና በሌሎች ግለሰቦች ስም በባንክ የሚገኝ ገንዘብ ለመንግስት በውርስ ገቢ እንዲደረግ፣ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታግዶ የሚገኘው የስር 7ኛ ተጠሪ(አቶ ነብዩ በድሩ) ጅምር የመኖሪያ ቤትና መጋዝን በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ እንዲደረግ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ በአሁኑ አመልካች ስም በባንክ ይገኛል የተባለው የገንዘብ መጠን በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ተክለሐይማኖት ቅርንጫፍ በሒሳብ ቁጥር 179 ብር 123,738.52 (አንድ መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) እና በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ተክለይሐይማኖት ቅርንጫፍ በሒሳብ ቁጥር 221 ደግሞ ብር 1,020,095.80 (አንድ ሚሊዮን ሃያ ሺህ ዘጠና አምስት ብር ከሰማንያ ሳንቲም) ስለመሆኑ በተጠሪ የውርስ ማመልከቻ ላይ ተጠቅሷል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ የውርስ ጥያቄ ላይ በሰጡት መልስም በመንግስት ላይ ደርሷል በማለት በማመልከቻው ላይ የተጠቀሰው ብር 13,457,694.40 (አስራ ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአርባ ሳንቲም) በእርግጥ ለመድረሱ በሚያሳምን ሁኔታ ተጣርቶ ያለመቅረቡን፣ በማካካሻነት ንብረት ሊወረስ የሚገባው በመንግስት ላይ በእርግጥ ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ መሆን እንደአለበት በጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ስርዓትና የማስረጃ ሕግ መደንገጉን፣አመልካቹ ጥፋተኛ የተባሉት በዲክሊራሲዮን ቁጥር 19225 በደግፍ ይርጋ ስም ያስገቡት ሁኖ ንብረቱ በዋናው መዝገብ አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ነብዩ በድሩ በመሆኑ ቀረጡን መክፈል የሚገባቸው ይኼው ግለሰብ መሆናቸውን፣ እንዲወረስ የተጠየቀውና በፍርድ ቤት የታገደው በባንክ የሚገኘው ገንዘብ አመልካቹ ጥፋተኛ የተባሉበት ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት በተከፈተ ሒሳብ ውስጥ የተገኘና መጠኑም በእንቅስቃሴ ከፍ ዝቅ ሲል የቆየ በመሆኑ በስራ እንጂ በሕገ ወጥ መንገድ ያላገኙት መሆኑን፣ጥፋተኛ የተባሉት የጉምሩክ ስነ ስርዓት በመጣስ እንጂ በዋናው ወንጀል ተሳትፎ ኑሯቸው ባለመሆኑና በወንጀል ቀጥተኛ ተሳትፎ አድርገዋል ተብለው ጥፋተኛ ከተባሉት ተከሳሾች በመንግስት ላይ ደረሰ ለተባለው ጉዳት ለማካካስ በቂ ንብረት የተያዘ መሆኑን ዘርዝረው የተጠሪ የውርስ አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ሌሎች የሥር ተከሳሾችም አሉን የሚሏቸውን ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ ክርክሩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በተከሳሾች ላይ የውርስ ጥያቄ መቅረብ የሚገባው እያንዳንዳቸው በወንጀል ድርጊት ምክንያት ሳይከፍሉ በቀሩት የታክስና ቀረጥ መጠን እንጂ በወንጀሉ ድርጊት ላልተሳተፉበትና ጥቅም ላላገኙበት የገንዘብ መጠን ሊሆን አይገባም የሚለውን

ድምዳሜ ይዞ ተጠሪ ተከሳሾች በመንግስት ላይ የደረሰውን ብር 13,457,694.40 (አስራ ሶስት ሚሊዩን አራት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአርባ ሳንቲም) በአንድነትና በነጠላ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ባቀረበው አቤቱታ ሁሉም አጥፊዎች የሚገደዱበት ምክንያት የለም፣ አመልካች አድራጎት በዲክላራሲዩን ቁጥሮች 19225፣21702፣23132 በገቡት እቃዎች ሳይከፈል የቀረው ግብርና ታክስ መጠኑ ብር 2,539,233.00 (ሁለት ሚሊዩን አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) መሆኑን፣ ይህንኑ ገንዘብ ተጠቃሚ የሆኑትም አመልካች ሳይሆኑ የስር ተከሳሽ የነበሩት አቶ ነብዩ ብድሩ መሆናቸውን፣ አመልካች በጉምሩክ አስተላላፊነታቸው ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያልተጣለባቸውና ግብሩንና ታክሱን የመክፈል ኃላፊነት የአቶ ነብዩ ብድሩ ሽፋ በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የአቶ ነብዩ በድሩ ብቻ ነው በማለት ወስኗል፡፡በሌሎች ተከሳሾችም ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ  አቶ ነብዩ ብድሩ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ አቶ ነብዩ ብድሩንና የአሁኑን ተጠሪ በመልስ ሰጪነት ሰይሞ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አቶ ነብዩ ብድሩ ለብቻቸው እንዲከፍሉ የተወሰነው የሕግ መሰረት በሌለበት አግባብ ነው በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሰኔ አሻሽሎ ብር 2,539,239.50 (ሁለት ሚሊዩን አምስ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) መክፈል ያለባቸው አቶ ነብዩ ብድሩ ሺፋ ብቻ ሳይሆኑ በወንጀል ድርጊቱ አብረውት ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡት ተከሳሾችሽ ጭምር ናቸው በማለት ገንዘቡን በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የሃላፊነት አይነትና መጠን አመልካች በወንጀሉ የነበራቸውን የተሳትፎ ደረጃ ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን እንዲሁም ውሳኔው የአመልካችን መብትና ጥቅም የሚነካ ሁኖ እያለ በይግባኝ ክርክሩ ላይ አመልካች እንዲካፈሉ ሳይደረግ መወሰኑ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ በይግባኝ ሰሚው ችሎት በነበረው ክርክር ተጠሪ ይግባኝ ባይ ባልሆነበት ሁኔታ በሰበር ክርክሩ ተሳታፊ ሊሆን የሚችልት አግባብ ያለመኖሩንና አመልካች ይነሳልን ለሚሉት የእግድ ትዕዛዝም ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ጠቅሶ ከክርክሩ ውጪ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለበት ቀዳሚው ነጥብ አመልካች የይግባኝ ክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆኑ ገንዘቡን በአንድነትና በነጣላ እንዲከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ መመርመሩ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡

አመልካች ከአቶ ነብዩ ብድሩ ጋር ብር 2,539,239.50 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ተብሎ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ የተሰጠው አመልካቹ የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ መሆኑን ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ አሁን በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ ደግሞ አመልካች ይህ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መብትና ጥቅማቸውን የሚነካ ሁኖ እያለ የክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆኑ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ የተከሰሱ ሰዎች በሕግ ከተጠበቁላቸው መብቶች አንዱ የመሰማት መብት ነው፡፡ ይህ መብት በመጀመሪያም ሆነ በሌሎች የክርክር ደረጃዎች በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት በመከተል ሊጠበቅ የሚገባ ነው፡፡መብቱ ቀሪ የሚሆነው ሕጉ በዘረጋው ስርዓት ባለመብቱ ሳይጠቀምበት ሲቀር ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የመሰማት መብት ተከሳሾች የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸውን ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20 (4) የተደነገገ ሲሆን ይህ መብት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(4) ድንጋጌ አግባብ የአገሪቱ የሕግ አካል በሆኑት የአለም አቀፍ ስምምነቶችም ጥበቃ ያገኘ ስለመሆኑ የሲቭልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን 14(3(ለ)) ድንጋጌን በመመልከት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ በአንቀጽ 10 ያስቀመጠው ድንጋጌም ማንም ሰው በተከሰሰበት ወንጀል ውሳኔ ለማግኘት ሙሉ የእኩልነት መብቱ ሊጠብቅለት እንደሚገባና ሚዛናዊና ይፋ የሆነ ፍርድ የማግኘት መብት እንደአለው ያሳያል፡፡ ይህ መብት የሚጠበቀው የመከራከር መብቱ በአግባቡ ሲጠበቅ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው የተከሳሽ መብት የሚያስገነዝበው አንድ ተከሳሽ ተገቢ ባልሆነ ማስረጃ ጥፋተኛ እንዳይባልና በከሳሹ ወገን ማስረጃ ቀርቦ ከሆነም በበኩሉ ምንም ጥፋት ያልፈፀመና ንፁህ መሆኑን የማስረዳት ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚችል መሆኑንና ክርክሩ የእኩልነት መብቱ ተጠብቆ በግልጽና ተከሳሹ በይፋ በሚያውቀው አግባብ መሆን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ለቀረበበት ክስም ሆነ ይግባኝ

ተገቢውን ክርክርና ማስረጃ ለማዘጋጀት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ተደርጎ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮችንና በቂ ጊዜ ማግኘት እንደሚገባው ሕጉ ያስገነዝበል፡፡ ተከሳሹ ይህንኑ በሕገ መንግስቱ ጥበቃ ያገኘውን  የመሰማት መብታቸውን በመጀመሪያ ደረጃ ክርክርም ሆነ በይግባኝ ደረጃ በሚደረገው ክርክር በአግባቡ እንዲጠቀም ማድረግ የፍርድ ቤት ኃላፊነት መሆኑንም ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የተከሳሽ የመሰማት መብት ሊታለፍ የሚገባው ተከሳሹ መብቱን የማይጠቀምበት መሆኑን በግልፅ ለፍርድ ቤቱ ሲያረጋግጥለት ወይም በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ክርክር መኖሩን እንዲያውቀው ተደርጎ ይህንኑ እያወቀ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ፍቃደኛ ሳይሆን መቅረቱ በእርግጥ ሲታወቅ ብቻ መሆኑን ከድንጋጌዎች መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ ተከሳሹ የመሰማት መብቱን ስለመተው ባልተረጋገጠበት አግባብ ግን የተከሳሽን መብትና ጥቅም የሚነካ ውሳኔ ፍርድ ቤት መስጠት ተገቢነት የሌለው አካሄድ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉደይ ስንመለስ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ያየው አመልካችንና ተጠሪን እንዲሁም በወንጀሉ ጥፋተኛ የተባሉትን ሁሉንም ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ አድርጎ ሲሆን አመልካች ለተጠሪ የውርስ ጥያቄ አለኝ ያሉትን የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አቅርበዋል፡፡አመልካቹ ያቀረቡትን ክርክርም የስር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ለአመልካች መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት የማያደርስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ በውጤቱ ተጠቃሚ መሆኑን ተገንዝቦ ይግባኝ ያልጠየቀ ቢሆንም ገንዘቡን ለብቻቸው ለተጠሪ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው የወንጀሉ ተሳታፊ ነበር የተባሉ ግለሰብ(አቶ ነብዩ በድሩ) ግን ገንዘቡን ብቻዬን ልከፍል አይገባም በማለት አመልካችንና ሌሎችንም ግለሰቦች ሊጨምር ይገባል በማለት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ክርክሩን የአሁኑ አመልካች ሳይጠራ በመምራት ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች የንብረት ጥቅምና መብት የሚነካ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካችን ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ያላደረገበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩም በውሳኔው ላይ አልገለጸም፡፡ይህም አመልካች የይግባኝ ክርክሩ የሚመለከታቸው መሆኑን እንዲያውቁ ተደርጎ የክርክሩ ተሳታፊ ለመሆን ፍላጎት የሌላቸው መሆኑ ሳይረጋገጥ ክርክሩ መመራቱን የሚያረጋገጥ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በክርክር አመራር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በሕግ የተዘረጋ የክርክር አመራር ሳይሟላ የሚሰጥ ዳኝነት የግልጽነት መርህን የሚቃረንና በውጤቱም የተከራካሪ ወገንን መሰረታዊም ሆነ ስነ ስርዓታዊ መብት የሚጎዳ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡

ከእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች በሕጉ የተጠበቀላቸውን የሰውነት መብት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያለፈው አመልካቹ በግልጽ በመብታቸው የማይጠቀሙበት መሆኑን ሳያረጋገጡ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. **በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 91921 ሕዳር 06 ቀን 2006 ዓ/ም ብር 2,539,239.50 (ሁለት ሚሊዩን አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) አመልካች ከአቶ ነብዩ በድሩ ሽፋ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡**
2. **አመልካች የይግባኝ ክርክሩ ተካፋይ ሁኖ የመሰማት መብት የታለፈው ያላግባብ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ክርክሩን በመ/ቁጥር 91921 ቀጥሎ የአመልካችን የመሰማት መብት በሕጉ አግባብ ሰምቶ አቶ ነብዩ ብድሩና ሌሎች የክርክሩ ተካፋይ ሊሆኑ የሚገባቸው ሰዎች ካሉም ወደ ክርክሩ እንዲገቡ አድርጎ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡**

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የሰ/መ/ቁ.104220

ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ አታክልቲ አብርሃ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ገ/ጉ/ባለስልጣን የሁመራ ቅርንጫፍ ዐቃቤ ሕግ -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገው ክሱ እና መጥሪያው በመደበኛ መኖሪያ አድራሻቸው እንዲደርሳቸው ሳይደረግ በመሆኑ ክርክሩ በሌሉበት ታይቶ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 91 (2) ስር የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የስድስት ዓመት ከአስር ወር ጽኑ እስራት እና የብር 5,500 የቅጣት ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና ባሉበት እንዲታይ እንዲደረግ ያቀረቡትን ማመልከቻ እና ተጠሪው የሰጠውን መልስ ከመረመረ በኃላ የአመልካችን ጥያቄ ባለመቀበል በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 91 (2) ስር ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ጉዳይ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 161 (2) መሰረት በሌለበት ሊታይ የሚችል መሆን አለመሆኑን እና አመልካች በሌሉበት የተሰጠባቸው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡት ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በሌሉበት የተሰጠባቸው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ጉዳዩን አመልካች በሌሉበት አይቶ የጥፋተኝነት ውሳኔውን የሰጠው የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሁመራ ምድብ ችሎት ጉዳዩ ተከሳሹ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ የሰጠው የፌዴራል ፖሊስ ተከሳሹን አላገኘኃቸውም በማለት ምላሽ ሰጥቷል፣ተከሳሹ በክልላዊ ጋዜጣ በወጣ ማስታወቂያም ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ነው፡፡ተከሳሽ በበኩላቸው በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳልኝ ይገባል በማለት የሚከራከሩት በጎንደር በሕክምና ላይ የነበሩ መሆኑን እና ከሕክምና ክትትሉ በኃላም በመደበኛው መኖሪያ ቦታቸው የነበሩ ሆኖ እያለ የፍርድ ቤቱ ክስ እና መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ፖሊስ አላገኘሁትም ብሏል በማለቱ እና በጋዜጣ ማስታወቂያ ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገው አላግባብ ነው በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡አመልካቹ በጎንደር ከተማ በህክምና ክትትል ላይ ነበርኩ የሚሉበት ጊዜ ፍርድ ቤት መቅረብ ነበረባቸው ከተባለበት ጊዜ በፊት እንደሆነ ከጊዜው ቅደም ተከተል መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ አመልካች በህክምና ክትትል ላይ ነበርኩ የሚሉበት ጊዜ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለው አይደለም፡፡በሌላ በኩል ግን አንድ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠበት ውሳኔ እንዲነሳለት የሚያቀርበውን ማመልከቻ ለመቀበል ከሚቻልባቸው ምክንያቶች አንዱ መጥሪያው ለተከሳሹ ያልደረሰው የመሆኑ ጉዳይ ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 199 (ሀ) ስር የተመለከተ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል ፖሊስ በደፈናው ተከሳሹን አላገኘኃቸውም ብሏል ከመባሉ ውጭ ተከሳሹን አላገኘኃቸውም በማለት ፖሊስ ምላሽ የሰጠው በርግጥም በምርመራ ጊዜ ከሰጡት መደበኛ የመኖሪያ አድራሻቸው ተገቢውን ፍለጋ አድርጎ ሊያገኛቸው እንዳልቻለ ተገቢውን ማረጋገጫ በመስጠቱ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ የፌዴራል ፖሊስ እንዳላገኛቸው አረጋግጧል ከማለት ውጭ ጉዳዩ በሌለሁበት የታየው መጥሪያው በመደበኛ የመኖሪያ አድራሻዬ እንዲደርሰኝ ሳይደረግ ነው በማለት አመልካች ባቀረቡት የክርክር ነጥብ ላይ ተጠሪው ያቀረበው ግልጽ ማስተባበያ አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡ አመልካቹ በምርመራ ጊዜ ከገለጹት መደበኛ የመኖሪያ አድራሻቸው ተፈልገው የታጡ ስለመሆኑም ተጠሪው በግልጽ አልተከራከረም፡፡ባስመዘገቡት አድራሻ መጥሪያው ለአመልካቹ የተላከ መሆኑ ወይም አመልካቹ በዚሁ አድራሻቸው ተፈልገው ያልተገኙ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወደ ጋዜጣ ጥሪ አማራጭ የሚኬድበት አግባብ ስለማይኖር የጥሪ ማስታወቂያው በክልላዊ ጋዜጣ መነገሩ ብቻውን መጥሪያው ለአመልካች በአግባቡ እንዲደርስ ተደርጓል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 20 (4) ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይህንን ሕገ መንግስታዊ መብት ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉት ደግሞ ክስ የቀረበባቸው መሆኑን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 123 በተመለከተው መሰረት በሚላክ መጥሪያ እንዲያውቁት ሲደረግ ነው፡፡አመልካቹ መጥሪያው በሕግ አግባብ የደረሳቸው መሆኑን ደግሞ የመዝገቡ ገልባጭ አያረጋግጥም፡፡

በሌላ በኩል አንድ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሳኔ ተነስቶ ባለበት በድጋሚ እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ባለመቀበል በሚሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት የማይቻል ስለመሆኑ እና ይግባኝ ማለት የሚቻለው በቅጣቱ መጠን ላይ ብቻ ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 202 (3) ስር በግልጽ የተመለከተ ሆኖ ሳለ እና አመልካች ለትግራይ ብ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቅጣቱ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ሳይኖር የቀድሞው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በሚል በተሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበለትን ቅሬታ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ አስተናግዶ ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195 (1) ድንጋጌን ጠቅሶ የሰጠው ትዕዛዝ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩ አመልካች በሌሉበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የስድስት ዓመት ከአስር ወር ጽኑ እስራት እና የብር 5,500 የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው ባስመዘገቡት የመኖሪያ አድራሻ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ሆኖ እያለ እና ይህም በሌሉበት የተሰጠባቸውን ውሳኔ ለማንሳት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 199 (ሀ) ድንጋጌ መሰረት በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ ውሳኔው ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አንድ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሳኔ ተነስቶ ባለበት በድጋሚ እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ባለመቀበል የሚሰጥ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 202 (3) ስር በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን አስመልክቶ የቀረበለትን ይግባኝ በማስተናገድ የትግራይ ብ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 67114 በ 09/10/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. በሌሉበት ታይቶ የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የስድስት ዓመት ከአስር ወር ጽኑ እስራት እና የብር 5,500 የቅጣት ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ

አመልካች ያቀረቡትን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁመራ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 09566 በ05/09/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል።

3. አመልካች በሌሉበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የስድስት ዓመት ከአስር ወር ጽኑ እስራት እና የብር 5,500 የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው ባስመዘገቡት የመኖሪያ አድራሻ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ወይም በዚሁ አድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ አለመቻላቸው ሳይረጋገጥ በመሆኑ እና ይህም በሌሉበት የተሰጠባቸውን ውሳኔ ለማንሳት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 199 (ሀ) ድንጋጌ መሰረት በቂ ምክንያት በመሆኑ ውሳኔው ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ወስነናል።
4. በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁመራ ምድብ ችሎት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 202(1) በተደነገገው መሰረት ቀድሞ ጉዳዩን ያዩት ዳኞች በማይሰየሙበት ችሎት አመልካች ባሉበት ጉዳዩን እንደገና በማየት በስነ ስርዓት ሕጉ በተመለከተው መሰረት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ወስነናል።
5. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁመራ ምድብ ችሎት እንዲሁም በሚገኙበት የሁመራ ማረሚያ ተቋም በኩል ለአመልካቹ ይላክ።
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።**

**መ/ይ**

የሰ/መ/ቁ.97291

ቀን ሰኔ 17/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** ጎሹ ዮሐንስ ገብሩ ጠበቃ ወንድ ይፍራው አረፈ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል የሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ሕግ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስልጣን አለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ ያልሆኑትን ጨምሮ በሦስት ግለሰቦች ላይ የቀረበው ክስ 1ኛ ተከሳሽ አደምኑር ፣2ኛ ተከሳሽ አዳነ ይርዳው 3ኛ ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች በመሆን ነው ፡፡ የአሁኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች እና በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ ያልሆኑ ግለሰቦች ሁለት ክስ ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ክስ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በነበሩት አደም ኑር ገበያው እና አዳነ ይርዳው የቀረበ ነው ፡፡ የክሱ አጭር ይዘትም ፡- በ 1997ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) (ለ) እና 379(1)(ሀ)እና (ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ እና ለራሳቸው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ 1ኛ ተከሳሽ በግብርና ምርት ላኪነት የተሰማራ ባለሀብት /ኢንቨስተር /2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ወኪል መስለው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ለመቅረብ እና ከድርጅቱ በርካታ ኩንታል ማዳበሪዎች ለመውሰድ ያመቻቸው ዘንድ በሀሰት የተዘጋጀ በአማራ

ክልል በምሥራቅ ጎጃም ዞን በሰሊቨን ወረዳ መሬት ለማልማት የተደረገ የመሬት ኪራይ ውልና ተዛማጅ ደብዳቤ ፣በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንደተሰጠ ተደረገው ተመሳስለው የተሠሩ የንግድ ፈቃዶች በአማራ ክልል መንግስት እንደተሰጠ ተደርጎ ተመሳስሎ የተሠራ የኢንቨስትመንት ፈቃድና የውክልና ማስረጃ እንዲሁም ትክክለኛው ከባንክ ገቢ የተደረገው የገንዘብ መጠን 914.55 ሆኖ እያለ ብር 914,355.00 ያክል ገንዘብ እንዳለው የሚገልጽ ሀሰተኛ የባንክ ሲ.ፒ.ኦ.እና ሌሎች ሰነዶች በመያዝ ሰኔ 23 ቀን 2001 እና በተከታዮች ቀናት በግብርና ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በመቅረብ ገቢ በማድረግ አላግባብ የተጠቀሙና በ2ኛ ክስ የተመለከተውን የመንግስት ንብረት ሐምሌ 03 ቀን 2001 ዓ.ም በመወሰዳቸው ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በፈጸሙት በሀሰተኛ ሰነድም መገልገል የሙስና ወንጀል እንደተከሰሱ፤

ሁለተኛው ክስ በሁሉም ተከሳሾች የቀረበ ሲሆን ዋና ይዘቱ ፡- በ1997 ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) (ለ) 33 እና 407(1)(ሀ)(ለ)እና (2) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ 3ኛ ተከሳሽ(የአሁኑ አመልካች) በ1ኛ ክስ በተመለከቱት ቀናት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የድርጅቱ የሽያጭና ገበያ ጥናት ዋና ክፍል ኃላፊ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ለራሱ እና ለሌሎች ተከሳሾች የማይገባ ጥቅም ለማግኘት እንዲሁም ለማስገኘት እና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፡-

ሀ. 2ኛ ተከሳሹ ከ1ኛ ተከሳሽ የሚገለገልበትን በርካታ ሰነዶች ይዞ በማዳበሪያ ግዥ ሲጠየቅ በመመሪያ መሠረት 3ኛ ተከሳሽ እንደ ኃላፊነታቸው ከዋናው ጋር ማመሣከር ሲገባቸው ይህንኑ ባለማድረጋቸው የማዳበሪያ ግዥ ጥያቄውን በስሙ በቀጥታ ያቀረበው 2ኛ ተከሳሽ ሆኖ እያለ ይኸው ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ የፈጠራ ድርጅት /አደም ኑር ገበያው ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ንብረት መስለው የቀረቡትን በ1ኛ ክስ የተመለከቱትን ሐሰተኛ ሰነዶች ይዞ ሲቀርብ 3ኛ ተከሳሽ የዋጋ ማሣወቂያ ከመፍቀዳቸው በፊት የራሱ ሰነዶች መሆናቸውን ሳያረጋግጡ ላላመለከተ (ግዥ ላልጠየቀ) አካል ከመመሪያው ውጭ መፍቀዳቸው ፡- 2ኛ ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ወኪል ናቸው ቢባል እንኳ የተያዘው የውክልና ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ ያልተሟላና ለዚህ በቂ አለመሆኑ እየታወቀ እንዲታረምና በመመሪያው መሠረት የውክልና ደብዳቤ እንዲቀርብና የግዥ መጠየቂያ ማመልከቻው እንዲስተካከል አለ ማድረጋቸው እንዲሁም በቀን 02/11/2000 ዓ.ም በቁጥር 89/008-12/00 ከዋናው መሥርያ ቤት ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአድራሻ እና ለንግድ መመሪያ በግልባጭ የተፃፈው የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ለሰፋፊ የግል እርሻዎች የሚፈቀደው የማዳበሪያ የሽያጭ መጠን ለአንድ ሄክታር መሬት አንድ ኩንታል ዳፕና አንድ ኩንታል ዩሪያ በጠቅላላው ከ 500 ኩንታል ሣይበልጥ የሚሸጥ መሆኑ እየገለጹ ተከሳሽ ከመመሪያው ውጭ 3,000 ኩንታል ማዳበሪያ በመፍቀዱ፤

ለ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾችም በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው የወንጀል ሐሳብ በመነሳት ከ3ኛ ተከሳሽ በመመሣጠርና በመንግስትና በህዝብ ሐብት ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው የመንግስት የልማት ድርጅት የሽያጭ ህጋዊ አሠራሮችና መመሪያዎች እንዲጣሱ በማድረግ ባለሀብትና ወኪል በመምሰል በ1ኛ ክስ የተገለጹትን ሐሰተኛ ሰነዶች ይዘው በመቅረብ ግምቱ ብር 913,440.45 የሆነ ማዳበሪያ ከተጠቃሹ የመንግስት የልማት ድርጅት ላይ ወስደዋል ፡፡ በመሆኑም ተከሳሾቹ የሽያጭና የአሠራር መመሪያዎች በአግባብ ከማከናውን በመታቀብ እና እርስ በርስ የጥቅም ተከፋይ ለመሆን በመመሳጠር በዋና ወንጀል አድራጊነት ተሳታፊ በመሆን ድርጊቱን በመፈፀማቸው በስልጣን ያለ አግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች (አመልካች) ቀርበው በጉዳዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በተሰጠው ብይን እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሁለቱም ክሶች ተነጣጥለው እነዲታዩ ትዕዛዝ ተሰጥቷል ፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ታዟል ፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች (አመልካች ) ክሱን ክደው በመከራከራቸው የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ተሰምቷል ፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችም የበኩላቸው የመከላከያ ማስረጃ አቅርበዋል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ 2ኛ ተከሳሽ የነበረው በተመለከተ የዓቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃ በሁለቱም ክሶች የተጠቀሱትን ፍሬ ነገሮች የፈፀመ ስለመሆኑ መስክሯል ፡፡ የ2ኛ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ያስረዱት ፍሬ ነገር ተከሳሹ የድለላ ሥራ የሚሠራ ስለመሆኑ እንጂ ለተከሰሰበት ጉዳይ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት ድርጊት ያልፈጸመ ስለመሆኑ የመሰከሩት ነገር የለም ፡፡ 2ኛ ተከሳሽ በሰነድ ማስረጃነት የቆጠረው በአንደኛ ተከሳሽ ለ2ኛ ተከሳሽ ተሰጠ የተባለውን የውክልና ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው ስለመሆኑ ለግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የፃፈው ማመልከቻም በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጉዳዩ ለማስፈጸም የተቀዋወለበት ሰነድ የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ የሚያጠናክሩ ናቸው ከሚያሰብል በስተቀር የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ተከላክሏል የሚያስብሉ አይደለም ፡፡ ስለሆነም በቀረበበት 1ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 379(1)(ሀ) በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ. 32(1)(ሀ)(ለ)፤33 እና 407(1) (ሀ)(2)በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.113(2) መሠረት አንቀጽን በመቀየር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ)(ለ) እና 407(1)(ሀ) በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.149(1)መሠረት ጥፋተኛ ነው ተብሏል፡፡

የአሁኑ አመልካች (3ኛ ተከሳሽ) በተመለከተም የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ እንዲከለከሉ በተሰጠው ብይን መሠረት በድርጅቱ የሚወጡ የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ወሰን በተመለከተ በዓቃቤ ሕግ ክስ የተጠቀሰው መመሪያ ተፈፃሚነት ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንጂ ለዋናው መ/ቤት ተከሳሽ ለሚሰሩበት ለሽያጭና ገበያ ጥናት ዋና ክፍል አለመሆኑን በዝርዝር ያስረዱና በክሱ የተጠቀሰው የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ በአድራሻ የተፃፈው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

በመሆኑ 3ኛ ተከሳሽ በኃላፊነት ተመድበው ለሚሰሩበት የሽያጭና የገበያ ጥናት ዋና ክፍል በዓቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ የተጠቀሰውና በድርጅቱ ሐምሌ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተላለፈ የተባለው መመሪያ ከወጣ በኃላ ሚያዝያ 19 ቀን 2001 ዓ.ም ተከሳሹ በኃላፊነት ተመድበው ለሚሰሩበት ለሽያጭና ገበያ ጥናት ዋና ክፍል በአድራሻ የተላለፈው የማዳበሪያ ሽያጭ መመሪያ በተሰጣቸው ስልጣን መጠኑ እስከ 10,000 ኩንታል የሚደርስ የማዳበሪያ ሽያጭ ለግል ስፋፊ የእርሻ ልማት ባለሃብት መፍቀድ እንደሚችሉ ሥልጣን የተሰጣቸው ለመሆኑ የሚያረጋግጥ የመከላከያ የሰነድ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ይህም ተከሳሽ በዓቃቤ ሕግ ከመመሪያ ውጭ የማዳበሪያ ግዥ ፈቅደዋል በሚል የተጠቀሰባቸው የክስ ፍሬ ነገር በተመለከተ በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው ተከላክለዋል የሚያስብል ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ 3ኛ ተከሳሽ በዓቃቤ ሕግ ከተጠቀሰባቸው የክስ ፍሬ ነገሮች ውስጥ 2ኛ ተከሳሽ ከ1ኛው ተከሳሽ ጋር የሚገለገሉባቸው ሐሰተኛ ሰነዶች ይዞ የማዳበሪያው ግዥ በቀጥታ የጠየቀው 2ኛ ተከሳሽ ሆኖ የማዳበሪያው ግዥ ከመፍቀዳቸው በፊት 2ኛ ተከሳሽ ግዥው እየጠየቀ ያለው የራሱን ሰነዶች ይዞ እንደሆነ ሣያረጋግጡ ግዥው ላልጠየቀ አካል ፈቅደዋል ፡፡ 2ኛው ተከሳሽ የ1ኛው ተከሳሽ ወኪል ነው ቢባል እንኳ ተያይዞ የቀረበው የውክልና ሰነድ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው መሆኑን እያወቁ የማዳበሪያው ግዥ እንዲፈጸም ፈቅዷል በሚል ሲሆን በዓቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች 2ኛ ተከሳሽ ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም የማዳበሪያ ግዥ በራሱ ስም የጠየቀና የቀረቡት ሰነዶች አደም ኑር ገበያው ኃ/የተ.የግ ማህበር የሚል ሆኖ እያለና የቀረበው የውክልና ሰነድ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው ስለሆነ በግልጽ በቀላሉ ችግሩን መለየትና ማጣራት የሚያስችል ሆኖ እያለ ይህንን ሳይፈጽሙ ከድርጅቱ ማዳበሪያ ግዢ እንዲፈፅም መፍቀዳቸው የተመሰከረባቸው በመከላከያ ማስረጃዎች የተከለከሉ ሆነው አልተገኘም ፡፡ በዚህም መሠረት በ3ኛ ተከሳሽ (አመልካች ) ላይ ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 33 እና 407(1)(ሀ)(ለ) (2) ተላልፏል በማለት የቀረበው ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.113(2) መሠረት አንቀጹን በመቀየር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 33 እና 407 (1)(ሀ) ሥር በወ/መ/ሥ/ሥ/ህቁ 149(1) መሠረት ጥፋተኛ ነው በማለት ተወስኗል፡፡

ቅጣት በተመለከተም 1ኛ ተከሳሽ በሌለበት የታየ በመሆኑ የቅጣት ማቅለያዎች ግምት ውስጥ ሳይገባ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በተመለከተም በግራ ቀኙ የቀረቡት የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በማገናዘብ 1ኛ ተከሳሽ በ 13 ዓመት ጽኑ እስራት እና 6,000 ብር መቀጮ 2ኛ ተከሳሽ በ 8 ዓመት ጽኑ እስራት 5000 ብር መቀጮ 3ኛ ተከሳሽ (አመልካች) ደግሞ በ 4 ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራትና ብር 2500.00 እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና ቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታው ወደ ጉዳዩ ለመግባት የሚያስችል በቂ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ ተደርጓል ። የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራቀኙ የጹሑፍ ክርክር አድርገዋል ። የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት ፡- የዋጋ ማሳወቂያ መስጠት መደበኛ ሥራቸው እንደሆነ ፤የቀረበላቸው የሐሰት የሰነድ ማስረጃ የተባለው ሐሰተኛ ስለሀመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚችሉበት አግባብ እንዳልነበረ ሽያጭ የፈቀደው የሌላ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ነው። የዋጋ ማሳወቂያ የተሰጠው ለ 5 ቀን የሚያገለግል ስለመሆኑ ፤የዋጋ ማሳወቂያ መስጠት ለመሸጥ ሐሳብ ማቅረብ እንጂ ሽያጭ መፈጸም አይደለም ። እቃ ለመሸጥ አሳብ መቅረብ የወንጀል ድርጊት አይደለም ። በሲ.ፒ.ኦ ደረሰ የተባለው ጉዳት በቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ትዕዛዝ የተከናወነ እንጂ አመልካች ተሳትፎ እንዳልነበራቸው በድርጊቱ ምክንያት እና ውጤት ግንኙነት የለውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል የሚል ስለመሆኑ ተረድተናል። ተጠሪ በበኩሉ በአመልካች በኩል መጣራት የገባቸው የነበሩ ነገሮች ባለ መጣራታቸው ከመመሪያው ውጭ ሽያጭ ተከናውነዋል ።አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሾች በነበሩ ግለሰቦች የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ሳያጣራ በማሳለፍ ምክንያት ድርጊቱ የወንጀል ውጤት ያስገኘ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እነዲጸና መጠየቁን ተመልክተናል ። አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታው በማጠናከር ተከራክሯል።

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ፤ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ፍርድ አግባብነት ካላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች በማዛመድ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው በአመልካች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ የወ/ሕ/ቁ 32(1)(ሀ)(ለ)፣33እና 407(1)(ሀ)(ለ)እና (2) የተመለከተውን በመተላለፍ በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በነበሩ የቀረቡ ሐሰተኛ ሰነዶች የዋጋ ማሳወቂያ ከመፍቀዳቸው በፊት የ2ኛ ተከሳሽ የራሱ ሰነዶች መሆናቸው አላረጋገጡም ። ግዥ ላልጠየቀ ግለሰብ ከመመሪያው ውጭ ፈቅደዋል። 2ኛ ተከሳሽ በአንደኛ ተከሳሽ ወኪል ነው ቢባል እንኳ የተያዘው የውክልና ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የለም።ከዋናው መሥሪያ ቤት የተፃፈው የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ለሰፈራ እርሻዎች የሚፈቀደው የማዳበሪያ ሽያጭ መጠን በሄክታር አንድ ኩንታል ዳፕና አንድ ኩንታል ዮሪያ በጠቅላላው ከ 500 ኩንታል እንደማይበልጥ የሚሸጥ መሆኑ እየታወቀ

3000 ኩንታል መዳበሪያ እንዲሸጥ ፈቅደዋል የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ፤የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ሥልጣኑ የደረሰበት ድምዳሜ አመልካች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት መጠኑ እስከ 10,000 ኩንታል ማዳበሪያ መሸጥ እንደሚችሉ ይሁንና 2ኛ ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ተወካይ እነደሆነና የቀረቡ የግዥ ሰነዶች አደም ኑር ገበያው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት የሚል ሆኖ ሳለ 2ኛ ተከሳሽ በራሱ ስም ግዥ መጠየቁ የቀረበው የውክልና ሰነድም የወካይ ስምና ፊርማ የሌላው እንደሆነ ፤ይህም በቀላሉ ችግሩን መለየትና ማጣራት የሚቻል እንደነበር ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥልጣኑ ያለአግባብ የተገለገለ ከሆነ በወ/ሕ/ቁ.407 ሥር ተጠያቂ እንደሚሆን ግልጽ ነው ፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ  ይዘት የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ እንደሆነ ፤የድርጊቱ አፈፃፀምም የተሰጠው ሹመት ወይም ሥልጣን በግልጽ ተግባር ወይም ግድፈት ከተሰጠው ስልጣን አልፎ በመሥራት ወይም ሥልጣኑ በማይፈቅደለት በተለይም ሥልጣን ሳይኖረው ወይም ከሥራ ከታገደ ከተዛወረ ፤ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱ ከተወ በኃላ የተፈጸመ ከሆነ የወንጀል ድርጊቱ ለማቋቋም በአማራጭ የተዘረዘሩ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ እንደ ወንጀሉ ክብደትም ከወንጀል ፈፃሚው ኃላፊነት፤የደረሰው ጉዳት ወይም የተገኘው ጥቅም ወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓላማ መሠረት በማድረግ ወንጀሉ እንደሚከብድ የወ/ሕ/ቁ. 407(2) እና (3) ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት ዓላማና መንፈስ መረዳት ይቻላል ፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዓቃቤ  ሕግ ክስ በማሻሻል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) (ለ) እና 407(1)(ሀ) ሥር ጥፋተኛ ያላቸው ስለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል ፡፡ የዚህ ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ፡ የተሰጠው ሹመት ወይም ሥልጣን በግልጽ ተግባር ወይም ግድፈት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ “የሚል ነው ፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ለማለት እንደመነሻ የወሰደው ግዥው የተጠየቀው ለአደም ኑር ሆኖ እያለ 2ኛ ተከሳሽ በራሱ ስም የራሱ ሰነዶች ይዞ እየጠየቀ  መሆን ያለመሆኑን አላጣሩም ፤2ኛ ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ተወካይ ነው ቢባል እንኳ የውክልና ሰነዱ የወካይ ስምና ፊርማ ያለው ነው በቀላሉ መለየት ይቻል ነበር በሚል ነው ፡፡ አመልካች የዋጋ ማሳወቂያ ሰነድ የሰጡ ስለመሆኑ አላከራከረም ፡፡ በዋጋ ማሳወቂያው መሠረት ሽያጭ መፍቀድና ማከናወን ደግሞ በሌላ የሥራ ክፍል የሚደረግ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር መረዳት ይቻላል ፡፡ አመልካች በኃላፊነት እንዲጠየቁ በመሠረታዊነት የተያዘው ምክንያት የውክልና ሰነዱ የተሟላ ባለመሆኑ ችግሩን በቀላሉ መለየትና ማጣራት ይቻል ነበር በሚል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት መሠረታዊ ነጥብ አመልካች በውክልና ሰነዱ ላይ

የወካይ ስምና ፊርማ የሌለ መሆኑ እየታየ የዋጋ ማሳወቂያ ሰነድ መስጠታቸው በወ/ሕ/ቁ 407(1) (ሀ) ሥር ጥፋተኛ ሊያሰኛቸው ይችላልን ? የሚል ነው፡፡

ከክርክር ሂደቱ መረዳት እንደተቻለው አመልካች የቀረቡ ሰነዶች በጥንቃቄ ለይተው ማጣራት የማይችሉበት ሁኔታ እንደነበር በግልጽ የቀረበ ክርክር ባይኖርም በወ/ሕ/ቁ.407(1)(ሀ) እንደተመለከተው ግን የተሰጣቸው ኃላፊነት ያለአግባብ የተገለገሉ ስለመሆናቸው የወንጀል ሕጉ እንደ መሠረታዊ ማቋቋሚያ የዘረዘረው ፍሬ ነገር ስለመረጋገጡ ከሳሽ ወገን የማስረዳት ሸክሙ ስለመወጣቱ የሚያሳይ ነገር በሥር ፍርድ ቤት አልቀረበም ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በአመልካች የተፈጸመው ድርጊት ስልጣን አላግባብ መገልገል ሳይሆን የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚፈጸም ወንጀል መሆኑን መረዳት ይቻላል ፡፡ አመልካች የሥራ ግዴታቸው ሲወጡ ከእሳቸው የሚጠበቀውን ግብይት ለማካሄድ እንደቅድመ ሁኔታ የሚወሰዱ የቀረቡ ሰነዶች በተገቢው መንገድ ተፈረመው የቀረቡ መሆን ያለመሆናቸው ፤የውክልና ሰጪ ስምና ፊርማ መኖር ያለመኖር የድርጅቱን አሠራር በሚፈቅደው አግባብ በጥንቃቄ ባለማጣራታቸው በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በቀረቡት ሐሰተኛ ሰነድ ተጠቅመው ከግብርና ምርት ማሳደጊያ አቅራቢ ድርጅት ማዳበሪያ ወስደዋል ፡፡ በዚህም በድርጅቱ የገንዘብ ጥቅም ላይ ጉዳት ደርሰዋል ፡፡ በመሆኑም አመልካች የሥር ፍርድ ቤት በወ/ሕ/ቁ 407(1)(ሀ) ሥር ጥፋተኛ ማለቱ የወንጀል ድርጊቱ ይዘትና ባሕሪ ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ሊሆኑ የሚገባው ከፈጸሙት የወንጀል ድርጊት በተጣጣመ መልኩ መሆን ይገባዋል ፡፡ በዚህም አመልካች የሥራ ኃላፊነታቸው ሲወጡ ተገቢው ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው በሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው ፡፡ ንብረት እንዲገዛ የጠየቀው 1ኛ ተከሳሽ ሆኖ ሳለ 2ኛ ተከሳሽ በስሙ ግዥ መጠየቁ የቀረቡ ሰነዶች አግባብነትና አስፈላጊ ፎርማልቲዎች የሚሉ መሆን ያለመሆናቸው የተለመደው አሠራር ተከትለው ባለማጣራታቸው ምክንያት የሥራ ኃላፊነትን ያለመሠጠት ወንጀል ፈጽመዋል ፡፡ ስለሆነም የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/ሕ/ቁ/32(1)(ሀ)(ለ)፤33እና 407(1)(ሀ)ሥር ጥፋተኛ ማለቱ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ በአግባቡ ባለመሆኑ አመልካች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው አግባብነት ባለው የወንጀል ድንጋጌ በመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113(2) በሚያዘው መሠረት ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 407 (1) (ሀ) ወደ ወ/ህ/ቁ.420/1/ሥር በመለወጥ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል ፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ በመለወጡ በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው ቅጣት ተገቢነት መርምረናል ፡፡ የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2002 ወይም ቁጥር 2/2006 መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተሰኙበት የሕግ አንቀጽ የወንጀል ደረጃ እና መነሻ የእስራት ወይም መቀጮ እርከን የወጣለት አይደለም ፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 420(1) ከአንድ ሺህ ብር

በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው በ2001 ዓ.ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት መመሪያ 1/2002 ነው፡፡ የወንጀል ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ በአንድ በኩል የወንጀል ፈፃሚው ግላዊ ሁኔታዎች በሌላ በኩል ግምት ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ከወ/ሕ/ቁ 1እና 88 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ የምንረዳ ነው ፡፡ በተያዘው ጉዳይ ፍርድ ቤቱ የእስራት አማራጭ ወስዷል ፡፡ አመልካች የፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ክብደትና ባህሪ መሠረት በማድረግ የስድስት ወር ቀላል እስራት መነሻ ይዘናል ፡፡ መቀጮ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በ 2500 ብር እንዲቀጡ የወሰነ ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ የቀላል እስራት አማራጭ ብቻ የተወሰደ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የጣለው መቀጮ የሕግ መሠረት የሌለው ስለሆነ ሊነሳ የሚገባው ነው፡፡በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካች ሊያርምና ሊያስተምር ይችላል ፤መሰል አጥፊዎችን ያስጠነቅቃል ብለን ያመነበት አመልካች በስድስት ወር ቀላል እስራት ሊቀጡ ይገባል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካች የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ዓይነት በአግባቡ ሳያገናዝቡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)እና (ለ) 407(1)(ሀ)ሥር ጥፋተኛ ማለታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በማረም በወ/ሕ/ቁ.32(1)(ሀ)(ለ)፤33 እና 420(1) ሥር ጥፋተኛ ናቸው በማለት ተከታዩን ወስነናል ፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.94053 በ 2/09/2005ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና ቅጣት ፤የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ.92016 በ 29/02/2006ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.195(2)(ለ)መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው በሥልጣን ያለአግባብ በመገልገል የወ/ህ/ቁ 407(1)(ሀ)ሥር ሳይሆን የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት ወንጀል የወ/ህ/ቁ.420(1) ሥር ነው በማለት ወስነናል ፡፡
3. አመልካች ለፈጸሙት ወንጀል በስድስት ወር ቀላል እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት የተወሰነባቸው ብር 25000/ሁለት ሺህ አምስት መቶ /መቀጮ ለመንግስት ገቢ አድርገውት ከሆነ ወጪ ሆኖ እንዲከፈላቸው ታዟል፡፡ ይፃፍ ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ/መ/ቁ.103775

ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** ሀብቱ ቱሉ ዳዲ -ጠበቃ በቃሉ ያለው ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የፌደራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን - ዐ/ህግ ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ መነሻ ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በመዝገብ ቁጥር 104519 በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመዝገብ ቁጥር 100951 ሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ.ም አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የበታች ፍርድ ቤቶች በአምስተኛ ክስ ላይ የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በሁሉም ክሶች ላይ ደግሞ የቅጣት አሰላልን በተመለከተ ተፈፃሚነት ያለውን መመሪያ ለይቶ ለማሳረም ነው፡፡

በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሌሎች አምስት ሰዎች ጋር ክስ የቀረበባቸው ሲሆን በአሁኑ አመልካች ላይ የቀረበው ክስ በአራት ምድብ የተከፈለ ነው፡፡

ተጠሪ ያቀረበው 1ኛ ክስ ይዘት፡- አመልካችን ጨምሮ የስር 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)((ለ)) እና አንቀፅ 379 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ የተደነገገውን በመተላለፍ የመንግስት ሰነድ አሰመስሎ የማዘጋጀትና መገልገል የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡ 2ኛው ክስ

ደግሞ አመልካችና የስር 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ)) እና 696(ሀ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የከባድ አታላይነት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ 3ኛው ክስ ደግሞ የአሁኑን አመልካች ጨምሮ የስር 1ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ) (ለ)) እና 379(1(ሀ)) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት አስበው ሐሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ 4ኛ ክስ ደግሞ አመልካች ከስር 1ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች ጋር ሁነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ) እና 696(ሀ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የአታላይነት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ በአመልካች ላይ ብቻ የቀረበውና የመጨረሻው ክስ በተራ ቁጥር አምስት የተጠቀሰው ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቹ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት እና ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እ.ኤ.አ ኦገስት 23 ቀን 2005 በፐርሶኔል ማኔጅመንት በመጀመሪያ ዲግሪ መመረቁን የሚገልፅ ሀሰተኛ ጊዜያዊ ዲፕሎማ እና ደጀኔ ተሊላ አሊ የተባለ ግለሰብ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ፋኩሊቲ በመካኒካል ኢንጂነሪንግ እ.ኤ.አ ጁላይ 24 ቀን 2004 ዓ/ም በአድቫንስድ ዲፕሎማ መመረቁን የሚገልፅ ሀሰተኛ ጊዜያዊ የምረቃ የምስክር ወረቀት ተመሳስሎ የተሰራ ሐሰተኛ የዩኒቨርሲቲውን ማህተም በመጠቀምና የኃላፊዎችን ፊርማ አስመስሎ በመፈረም አዘጋጅቶ ካስቀመጠበት በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ውስጥ በሚገኘው የተከሳሽ መኖሪያ ቤት በ2/06/2003 ዓ/ም በተደረገው ብርበራ የተገኘ መሆኑን በመዘርዝር አመልካቹ ሐሰተኛ ሰነድ የማዘጋጀት የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም አመልካች የቀረበባቸውን ክስ እንዲረዱት ከአደረገ በኋላ በስርዓቱ መሰረት በቅድመ ክስ ሂደት ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ አድርጎ በቅድመ ክስ ጊዜ አመልካች ያቀረቧቸውን መቃወሚያዎችን ውድቅ አድርጎ ጉዳዩን ወደ መደበኛው የክርክር ሂደት በመግባት ክርክሩን መርቷል፡፡ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት አሉኝ ያላቸውን የሰውና የፅሁፍ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች መከላከያ እንዲያቀርቡ ተደርጎ ማስረጃዎቻቸው ተሰምተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ አመልካች በተጠሪ የክስ ዝርዝር የተገለፁትን ተግባራት መፈጸማቸው በተጠሪ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠና በመከላከያ ማስረጃዎችም ያላስተባበሉ ናቸው በማለት አመልካች በቀረበቡባቸው አምስት ክሶች ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የሙስና ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በመቀጠል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሻሽሎ የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት አድርጎ ለወንጀሎቹ ደረጃ በመለየትና ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የሁለት አመት እስራት መነሻ ቅጣት በማስቀመጥ ለአምስቱም ክሶች ይህንኑ የሁለት አመት እስር ጊዜ ደምሮ

መነሻ ቅጣቱን አስር አመት እንደሚሆን ጠቅሶ ይኼው የቅጣት መጠን የሚወድቅበትን የእስራት ቅጣት እና የገንዘብ መቀጮውን እንደየድንጋጌዎቹ ይዘት በመለየት የእስራት ቅጣቱ በእርከን 29፣ የገንዘብ መቀጮው ደግሞ በእርከን 8 ስር እንደሚወድቅ ወስኗል፡፡ ከዚህም በኃላ በግራ ቀኙ የቀረቡትን የቅጣት አስተያየቶችን በመመርመር በአመልካች ላይ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በተጠሪ በኩል ያለመቅረባቸውን ጠቅሶ በአመልካች በኩል ግን ከዚህ በፊት በወንጀል ተከሰው ተቀጥተው የማያውቁ መሆኑን አመልካች የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን የሚያሳዩ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መቅረባቸውን ገልጾ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 23(4) መሰረት እያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሁለት ሁለት እርከን ሲያስቀንስ የእስራት ቅጣቱ ከእርከን 29 ወደ እርከን 27 እንደሚወርድ፣ የገንዘብ መቀጮው ደግሞ ከእርከን 8 ወደ እርከን 6 እንደሚወርድ ገልፆ በእነዚህ እርከኖች ለፍርድ ቤቱ በተተወው ፍቅድ ስልጣን መሰረት አመልካች በስምንት አመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000.00 (አስር ሺህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንን ፍርድ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት  ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

አመልካች ሐምሌ 24 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ ሰባት ገፅ የሰበር አቤቱታ በ5ኛ ክስ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 379(1(ሀ)) ተጠቅሶ ጥፋተኛ የተባሉት ድንጋጌው ከአድራጎታቸው ጋር ባልተጣጣመበት ሁኔታ መሆኑን፣ የቅጣት ውሳኔውም መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት መሰላት ሲገባው የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት መደረጉ ያላግባብ መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት በእያንዳንዱ ሕጋዊ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መቀነስ የነበረበት የሶስት እርከን ቅጣት ሳይቀነስ የታለፈና በሕግ ፊት እኩል ሁኖ የመታየት መብታቸው የተነካ መሆኑን፣ ለእያንዳንዱ ክስ መነሻ ቅጣት ከተለየ በኂላ ድምሩ የሚወድቅባቸው እርከኖችም ሶስት ሁነው እያለ በመመሪያው መሰረት ዝቅተኛው እርከን መያዝ ሲገባው ያላግባብ የታለፈ መሆኑን ዘርዝረው 5ኛ ክስ ስር የተጠቀሰው ድንጋጌ እንዲቀየርና ቅጣቱም አመልካችን በሚጠቅመው የቅጣት አወሳሰን መመሪያና ድንጋጌዎቹ ተሰልቶ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ተገቢውን የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የሰጡትን የቅጣት ውሳኔ ተገቢነት ለመመርመር በመሠረታዊ ጭብነት መታየት ያለባቸው ሁነው ያገኘናቸው ነጥቦች:-

1. የቅጣት ውሳኔው መሰላት ያለበት የወንጀል ክስ በቀረበበት ጊዜ ተፈፃሚነት በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ነው? ወይስ የጥፋተኛነት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ ተፈፃሚነት በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ነው?፣
2. የሥር ፍርድ ቤት የእስራት ቅጣት መነሻ የሚወድቅበትን እርከን በተገቢው መንገድ ለይቶአል ወይስ አልለየም? እና
3. አመልካች ሊቀጡ የሚገባው የቅጣት መጠን ምን ያህል ሊሆን ይገባል? የሚሉ ናቸው፡፡

<u>**የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ**</u>:- የበታች ፍርድ ቤቶች ቅጣቱን የወሰኑት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበት የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ወጥቶ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያቀረበውም ይህ መመሪያ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበት ወንጀል ክስ ሲቀርብ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም ለወንጀሉ ቅርበት ያለውና ተፈፃሚነት የነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነበር፡፡ በአመልካች ላይ የቅጣት ውሣኔ ሲወሰን ተፈፃሚ የነበረው የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ይህም በአመልካች ላይ የቅጣት ውሳኔ ሊወሰን የሚገባው አመልካች ወንጀሉን በፈጸመበትና ተገቢው ክስ በቀረበበት ጊዜ ተፈጻሚነት የነበረውን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት በማድረግ ነው? ወይስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲወሰን ተፈጻሚነት ያለውን የተሻሻለውን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማድረግ ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ይህንኑ የሕግ ጥያቄ በተመለከተ ይህ ችሎት በወንጀል ጉዳይ ገዥ መርህ ሆኖ ከተደነገገው ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 22 እና የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6 ድንጋጌ አንጻር በመመርመር ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው ተከሳሹን የሚጠቅመው መመሪያ ነው በማለት በሰ/መ/ቁጥር 95438 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት አመልካች ወንጀሉን ሲፈጽም ወይም ክስ በቀረበበት ጊዜ ያልነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በአመልካች ላይ የቅጣት ውሳኔ ሲወስን ተፈጻሚ የሚሆነው ይህ መመሪያ አመልካችን የሚጠቅመው ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከትአመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የወንጀል ድርጊት ሲፈጽም ያልነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አመልካች በወንጀሉ ድርጊት ሲከሰሱ ስራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እርከን አቀናነስ ላይ ከመመሪያ ቁጥር 1/2002 በተሻለ ሁኔታ የአመልካችን መብት የሚያስከብር አይደለም፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቅጣት ውሳኔ ውሳኔውን የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማድረግ መወሰናቸው ከላይ የገለጽነውን የሕገ መንግስት ድንጋጌዎች ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያትም በጉዳዩ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው፡፡

**ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-** የስር ፍርድ ቤት አመልካችን በአምስት ክሶች ጥፋተኛ ከአደረጋቸው በኃላ የወንጀሎቹን ደረጃ በመለየት ለእያንዳንዱ ክስ የሁለት አመት እስራት በመነሻነት ይዞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184(1(ለ)) መሰረት ደምሮ አስር አመትን በመነሻነት የያዘ ሲሆን ይህ የመነሻ ቅጣት የሚያፍርበት እርከን 29 መሆኑን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ ሆኖም አስር አመት መነሻ ቅጣት በመመሪያ ቁጥር 1/2002ም ሆነ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 በሶስት ተከታታይ እርከኖች ያለ ሲሆን እንዲህ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ዝቅተኛ እርከንን እንደሚይዝ በመመሪ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 13(9)፣ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 ደግሞ በአንቀጽ 19(11) ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ ሁለቱም መመሪያዎች በዚህ ረገድ ልዩነት የሌለባቸው በመሆኑ በአመልካች መብት አከባበር ላይ የሚያስከትሉት ችግር የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ጥፈተኛ የተባሉባቸው ድንጋጌዎች ድምር ቅጣት መነሻው የሚወድቅበትን እርከን ይህንኑ መሰረት አድርጎ መያዝ ሲገባው ከፍተኛ እርከን መያዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት የአምስቱ ክሶች ድምር የሆነው የአስር አመት ጽኑ እስራት የሚወድቅበት እርከን 27 ተደርጎ መያዝ ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

**ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ**፡- በቅጣት ማቅለያ አያያዝ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ስንመለከትም አመልካች ሪኮርድ የሌለባቸው መሆኑ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን የሚያሳዩትን ነጥቦች በሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት ይዞላቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ያልቀረበባቸው ሲሆን ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተይዞላቸው ድርጊቱ ከተፈፀመበትና ክሱ ከቀረበበት ጊዜያት አንፃር ሲታይ በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 16(7) ድንጋጌ መሰረት እያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሶስት ሶስት እርከን የሚያስቀንስ በመሆኑ በድምሩ ስድስት እርከን መቀነስ ስለአለበት ከእርከን 27 ወደ እርከን 21

መውረድንና በዚህ እርከን ውስጥ ተገቢውን ቅጣት መወሰን የሚጠይቅ ነው፡፡ በእርከን 21 ስር የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከአምስት አመት እስከ ስድስት አመት ነው፡፡

ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረት ቅጣቱን ስናሰላው አመልካችን ያርማል፣ሌሎች መሰል አጥፊዎችን ከወዲሁ ሊያስጠነቅቅ ይችላል ብለን የገመትነው የቅጣት መጠን በእርከን 21 ስር በአምስት አመት ጽኑ እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ ቢሆንም የቅጣት ውሳኔው ግን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 104519 ጥር 01 እና መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ፣ ይህንኑ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 100951 ሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195 (2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በአምስቱም ክሶች ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለእነዚህ ወንጀሎች ቅጣቱን በተመለከተ ግን አመልካች ሊቀጡ የሚገባው በ5 (አምስት) አመት ጽኑ እስራት ነው ብለናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ገንዘብ መቀጮ ውሳኔ አልተነካም፡፡
4. በአመልካች ላይ የተሰጠው የእስራት ቅጣት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ አመልካች በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ማናቸውም ጊዜ ታስቦላቸው በዚህ ችሎት በተወሰነባቸው የቅጣት መጠን መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ትዕዛዝ ይድረስ ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ. 98014

ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ያረጋል ተስፋ አባተ ጠበቃ አዳነ ታረቀኝ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክ/ዐ/ቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካች የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ.03468 በ04/05/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በ20/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ እኔ እና ሌሎች 5 ሰዎች በተከሰስኩበት በግብረ አበርነት ሰው በግፍ መግደል ወንጀል ተከስሼ ክሱ በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲታይ ቆይቶ ፍ/ቤቱ በመዝገብ ቁ.01597 በግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከክሱ ነፃ የተሰናበትኩ መሆኔን እና ከአሶሳ ዞን ማረሚያ ቤት እንድለቀቅ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላ የደረሰኝ መጥሪያ ሳይኖር እኔ ቀርቤ ሳልከረከር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሌሎች ተከሳሾች ቅጣት ሲጥል በእኔ ላይ የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት የወሰነብኝ መሆኑን በቅርብ ጊዜ ተነግሮኛል፡፡ ስለዚህ እኔ የህግ ታራሚ ስለሆንኩ የፍትህ መጓደል እንዳይደርስብኝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.191 /3/ መሰረት እኔ በሌለሁበት እና ከአቅሜ በላይ በሆነ ምክንያት ማለትም በነጻ ስለቀቅ ወደ ትውልድ ቦታዬ ጎጃም በመሄድ በእርሻ ተሰማርቼ 3 ሕፃናት ልጆቼን በማሳደግ ላይ የቆየሁ መሆኔንና በቲቪ ስሰቃይ፣ በባህርዳር ፈለገ ሕይወት ሆስፒታል ስታከም የቆየሁና በስንት መከራ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተርፌያለሁ፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ችግሬን ከግንዛቤ ውስጥ አስገብቶልኝ የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻዬን ተቀብሎ ይግባኝ

ተከፍቶልኝ ህጋዊ መብቴ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ እንዲሰማልኝ በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የነበረ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ከሰማ በኋላ በመዝገብ ቁ 03468 በ04/05/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ አመልካች የይግባኝ ጊዜ ያለፈባቸው በእውነት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ አመልካች የጠቀሰው ምክንያት ህመም ሲሆን በህክምና ወረቀት ካለመደገፉ በተጨማሪ ለአምስት አመታት ከነበረበት እና ጉዳዩ ከሚታይበት አከባቢ በመሰወር በመጨረሻም በፖሊስ ክትትል መያዙ የምክንያቱን በቂነትና ተቀባይነት ያሳጣዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ጊዜው ያለፈበት እና በበቂ ምክንያት ያልተደገፋ ነው ሲል የይግባኝ ማስፈቀጃውን ሳይቀበል መቅረቱ በህግ አግባብ እንጅ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም በማለት አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ይህን ትዕዛዝ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ፡-

1. እኔ አመልካች ከሌሎች ሰዎች ጋር ከተከሰስኩበት በሰው መግደል ወንጀል የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ወንጀሉን አለመፈጸሜን አረጋግጦ ግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም በነጻ ሲያሰናብተኝ፤ ይግባኝ ልጠራ ይችላል በሚል ሀሳብ ጉዳዩ በታየበት አከባቢ በመሆን የይግባኝ ውጤት እንድጠብቅ በሕግ የተጣለብኝ ግዴታ ሳይኖር፤ ወደ ሌላ አካባቢ በመሄዴም ከሕግ ተሰወረ ሊባል ስለማይችል፤ ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ ሲታይ አመልካች የማውቀው ነገር የሌለና የደረሰኝ መጥሪያ ሳይኖር፤ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የወሰነብኝ መሆኑን ያወቅኩት ፍርዱ ከተሰጠ ከ4 ዓመት በኋላ በፖሊስ ሲያዝ ነው፡፡ እኔ እንደተያዝኩ በ6 ቀን ውስጥ በ14/03/2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ "በሌለሁበት የተሰጠብኝ ፍርድ ውድቅ እንድደረግልኝ" በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና 198 መሰረት የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ስጠይቅ፤ አቤቱታው በሕግ የተደገፈ ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ እንደገና አላይም ማለቱ፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ስህተቱን አርሞ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ መፍቀድ ሲገባው አቤቱታውን ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር የአመልካችን አቤቱታ አልቀበልም ያለው ፍርድ የተሰጠበትን ጊዜ በመቁጠር የይግባኝ ጊዜው አልፏል በሚል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ፍርድ የተሰጠው እኔ በሌለሁበት ስለሆነ ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባው የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.191/1/ ሳይሆን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና ተከታዮቹ የተመለከተው ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በሌለበት የተፈረደበት ሰው ፍርዱን ካወቀበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ

ፍርዱ ውድቅ እንዲደረግለት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ማመልከት እንደሚቻል፣ ማመልከቻው ተቀባይነት ባያገኝ ደግሞ ማመልከቻው ተቀባይነት ካጣበት ቀን አንስቶ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 197፣198 እና 202/3/ ተደንግጓል። አመልካች ፍርዱን እንዳወቅኩኝ በ6 ቀን ውስጥ ሥርዓቱን ጠብቄ ማረሚያ ቤት ሆኜ ተደጋጋሚ አቤቱታ ባቀርብም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ፍርድ የተሰጠበትን ቀን በመቁጠር ሁሉንም አቤቱታዎች አልቀበልም በማለቱ በሕጋዊ መብቴ እንዳልጠቀም ከመከልከሉም በላይ የሬጅስትራር ክልከላ እንዲወገድልኝ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ባቀርብም የሬጅስትራሩን ድርጊት እንደህጋዊ ተግባር በመቁጠር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማስፈቀጃ አለመቀበሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ነው።

3. አመልካች የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ የማቀርብበት ሁኔታ አልተፈጠረም እንጅ ማቅረብ አለበት ቢባል እንኳ ማስፈቀጃው የሚቀርበውም የሚፈቀደውም ሆነ ተቀባይነት ሊያጣ የሚችለው ፍርዱን በፈረደው ፍ/ቤት ሬጅስትራር ውሳኔ ሳይሆን ፍርዱን በይግባኝ ወይም በሰበር የማየት ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ነው። ሬጅስትራሩ በማይመለከተው የዳኝነት ሥራ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የአመልካች አቤቱታ ለፍ/ቤት ችሎት ቀርቦ እንዳይታይ ያደረገው ሕጋዊ ተግባር ፈጽሟል ተብሎ አቤቱታው ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው።
4. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በ04/05/2004 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት ለይግባኝ ግልባጭ እንዲሰጠኝ በተደጋጋሚ ባመለክትም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሬጅስትራር በመከልከሉ ለሁለት ዓመት መብቴን እንዳልጠቀምና ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ሳላቀርብ ከፍ ያለ በደል ተፈጽሞብኝ መቆየቱ ሕገ መንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች በአንቀጽ 20/6/ የሰጠውን ይግባኝ የማቅረብ መብት የሚጥስ ነው። ሰለዚህ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሻርልኝ፣ አመልካች የሰበር አቤቱታ ጊዜው ያለፈው በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ችግር ፈጣሪነት ምክንያት ነው ተብሎ አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ እንዲፈቀድልኝ፣ እኔ በሌለሁበት ተገቢውን መከራከርያ ሳላቀርብ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወሰነብኝ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት እጅግ ከባድ ቅጣት በመሆኑ ጉዳዩ አመልካች ባለበት እንደገና ታይቶ እንዲወሰን በማለት አመልክቷል።

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ግልባጭ በማስቀረብ ጉዳዩን

በመመርመር "አመልካች በሌለበት የተፈረደበት ፍርድ እንዳወቀ ፍርዱ ተነስቶ ባለሁበት እንዲታይልኝ በማለት ያቀረበው አቤቱታ እና የይግባኝ ማስፈቀጃው ተቀባይነት ማጣቱ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? " የሚለውን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ታዝዞ፣

ተጠሪ በዚህ ጉዳይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት መጥሪያ ደርሶት መልሱን ይዞ ባለመቀረቡ በጽሁፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ ጉዳዩም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማየት አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው እና ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካችን ጨምሮ አምስት ሰዎች በግብረ አበርነት በግፍ ሰው መግደል ወንጀል ተከሰው በአሶሳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲከራከሩ ቆይተው ፍ/ቤቱ በግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ተከሳሾቹን በነጻ ስላሰናበታቸው በዚሁ ዕለት ተከሳሾቹ ከማረሚያ ቤት እንዲወጡ መደረጉን የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረቡ፤ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ሲያይ ቆይቶ በ17/11/1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ መሰረት አመልካች በሌለበት የዕድሜ ልክ እስራት እንደተፈረደበት መዝገቡ ያመለክታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አግባብነት ፖሊስ አመልካችን በ09/03/2004 ዓ.ም በቁጥጥር ስር በማዋል ማረሚያ ቤት እንዲገባ መደረጉ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በ14/03/2004 ዓ.ም ጽፎ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ እኔ ከተከሰስኩበት የወንጀል ክስ ፍ/ቤት በነፃ ካሰናበተኝ በኋላ ወደ አማራ ክልል በመሄድ ኑሮዬን የመሰረትኩ ሲሆን እኔ በሌለሁበት መጥሪያ ሳይደርሰኝ በፍ/ቤቱ የተፈረደብኝ የዕድሜ ልክ እስራት ፍርድ ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.199 መሰረት ማመልከቻዬን ተቀብሎኝ በቁ.202/1/ መሰረት ፍርዱ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ማመልከቱን፣ አመልካች እንደገና በድጋሚ በ02/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ እርሱ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲደረግለት መጠየቁን፣ ነገር ግን አመልካች አቤቱታው ጊዜው አልፎበታል ተብሎ ማረሚያ ቤት ስለተመለሰበት ድጋሚ በ02/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የይግባኝ መብቱ እንዲጠበቅለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ማመልከቱን፣ አመልካች አሁንም በ17/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በእኔ ጥፋት ስላልሆነ ክርክሩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲታይለት የመዝገብ ግልባጭ እንዲሰጠው መጠየቁን ከስር ፍርድ ቤት ከመጣው መዝገብ ጋር ተያይዘው የሚገኙ ሰነዶች የሚያሳዩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ከላይ እንደተመለከተው በ20/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የደረሰበት ከፍተኛ ሰቆቃና ችግር ከግንዛቤ ውስጥ ገብቶ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በእርሱ ጥፋት እንዳልሆነ በመጥቀስ የይግባኝ ማስፈቀጃ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው የይግባኝ ማስፈቀጃ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ በማድረጉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ምክንያት ሆኗል፡፡

በመሰረቱ አንድ የወንጀል የሚመራው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት የቀረበውን ክርክር ደግሞ መምራትና በሕጉ አግባብ ዳኝነት መስጠት ያለበት በሕግ አግባብ የተቋቋመው ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የክልሉ ዐቃቤ ሕግ የቀረበውን የወንጀል ይግባኝ ማመልከቻ ለአመልካችም ሆነ ለሌሎች መልስ ሰጭዎች እንዲደርሳቸው ማድረግ እንዳለበት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.187/4/ ሥር ተደንግጓል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ለአመልካች መጥሪያ እንዲደርሰው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በመጠቀም ተገቢውን ትጋት አድርጎ ነበር ወይ? የሚለው አሁን የሚታይ ስላልሆነ በዚህ ረገድ ምንም ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት የወንጀል ይግባኙን አይቶ በ17/11/99 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የፈረደበት መሆኑን ከቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በዚህ ፍርድ አማካይነት በ09/03/2004 ዓ.ም በፖሊስ ተይዞ በማረሚያ ቤት እንዲታሰር ከተደረገ በኋላ በ5 ቀናት ውስጥ በ14/03/2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና በተከታዮቹ ድንጋጌዎች ታይቶ እርሱ በሌለበት የተፈረደበት ፍርድ እንዲነሳለት የጠየቀ ስለሆነ፣ ይህ ጉዳይ በዚህ ድንጋጌ አግባብ የሚታይ ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሬጅስትራር የይግባኝ ጊዜው አልፎበታል በማለት አቤቱታውን አልቀበልም በማለት ጉዳዩ ለዳኞች ቀርቦ እንዳይታይለት የሚያደርግበት የህግ አግባብ የለውም፡፡ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.198 እንደሚደነግገው አንድ ሰው በሌለበት በወንጀል የተፈረደበት እንደሆነ ፍርዱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ፍርዱ ውድቅ እንዲደረግለት ማመልከት እንደሚችል እና በቁ.200 መሰረት የማመልከቻው ግልባጭ ለዐቃቤ ሕግ ደርሶ ለመስማት ቀጠሮ እንደሚያዝ ነው እንጂ ሬጅስትራር ማመልከቻውን አልቀበልም በማለት እንቢ የሚልበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ ይህ ማመልከቻ ከተሰማ በኋላ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.201 መሰረት ፍ/ቤት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳይ ነው እንጂ ሬጅስትራር አልቀበልም በማለት ውሳኔ ሊሰጥበት በሕግ የተሰጠው ስልጣን የለም፡፡ አመልካች የአቀረበው ማመልከቻ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ በዳኞች ታይቶና ክርክሩ በሕግ አግባብ ተሰምቶ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በሌለበት የተፈረደበት ቅጣት ነጻነትን የሚያሳጣ ከባድ የእስራት ቅጣት ሆኖ ሳለ አቤቱታው ተቀባይነት ቢያገኝም ቢያጣም ለፍ/ቤት ቀርቦ በዳኞች ውሳኔ ሊሰጥበት ሲገባው ሬጅስትራሩ ይህን መብት መገደቡ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ይህ ድርጊት ደግሞ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 መረዳት እንደሚቻለው "የተከሰሱ ሰዎች ክርክራቸው በፍ/ቤት ታይቶ ተሰምቶ ፍርድ ሊያገኙ ይገባል" የሚለውን ሕገ መንግስታዊ መብቱን የሚሸራርፍ ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ያቀረባቸው አቤቱታዎች የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የቀረበውን የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ በማየት ከላይ የተጠቀሱትን አመልካቹ ላይ የደረሰውን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት በሬጅስትራሩ ምክንያት

የተፈጠረውን የአካሄድ ችግሮችን በማረም፣ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሬጅስትራር አመልካች በሌለሁበት የተፈረደብኝ ፍርድ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት የቀረበው ማመልከቻ ለዳኞች ቀርቦ እንዲታይለት እንዲያደርግ ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው የሬጅስትራሩን ድርጊት ሕጋዊ እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ አድርጎ መተው ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎችን የሚጻረር በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

ከዚህም በላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ይግባኝ ማስፈቀጃ የጠየቀው እርሱ በሌለበት የተሰጠበት ፍርድ ላይ መሆኑ እየታወቀ፣ አመልካች በዚህ ላይ ምን ዓይነት የይግባኝ ጥያቄ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሊያቀርብ እንደሚችል ሳይጣራ፣ እንዴትስ ከዚህ ዓይነት ፍርድ ይግባኝ ማለት እንደሚቻል ሳይመረመር፣ በሌለበት ፍርድ የተሰጠበት ሰው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብነት መብቱን መጠየቅ እንደሚችል መገንዘብ ሲገባው፣ የሬጅስትራሩን ከሕግ ውጭ የሆነ ድርጊት ሕጋዊ ሽፋን በመስጠት የሰጠው ትዕዛዝ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈጠረውን የአካሄድ ችግር ተገቢውን ማስተካከያ ሳያደርግ ከመቅረቱም በላይ አመልካቹ የጠቀሰው " ምክንያት ህመም ሲሆን በህክምና የምስክር ወረቀት ካለመደገፉ በተጨማሪ ከአምስት ዓመታት በላይ ከነበረበት እና ጉዳዩ ከሚታይበት አካባቢ በመሰወር በመጨረሻም በፖሊስ ክትትል መያዙ የምክንያቱን በቂና ተቀባይነት ያሳጣዋል" በማለት የደረሰበት ድምዳሜ፣ አመልካቹ አቤቱታው በፍ/ቤት/በዳኞች/ ታይቶ ተሰምቶ ተገቢ ማጣሪያ ተደርጎ ፍርድ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብቱን የሚያጣብብ በመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ስለዚህ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሬጅስትራር የፈጠረውን የአካሄድ ችግር ማስተካከል ሲገባው አመልካች በሌለሁበት የተፈረደብኝ ፍርድ ውድቅ እንዲሆንልኝ በማለት ያመለከተው አቤቱታ በፍ/ቤት ታይቶ ተሰምቶ ውሳኔ ሳይሰጥበት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ሁኖ ስለአገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ.03468 ላይ በ04/05/2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በ14/03/2004 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ መሰረት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በሌለበት የተፈረደበት ፍርድ ውድቅ ሊሆን ይገባል? ወይስ አይገባም? በሚለው ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች፣ አመልካች በታሰረበት ማረሚያ ቤት በኩል ለአመልካች ይድረስ ብለናል፡፡
4. ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረበው የመዝገብ ቁ.03488 እና የአቤቱታዎች ግልባጭ በመጣበት አኳኋን ይመለስ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡ ውሳኔ ስለአገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/አ**

የሰ/መ/ቁ. 107219

ሐምሌ 1 ቀን 2007ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-**አቶ አህመድ ሰይድ መሐመድ ጠበቃ መሳይ ተድላ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ በተጀመረበት ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ከነበሩት ሌሎች ሁለት ግለሰቦች ጋር በመሆን ከባድ የስርቆት ወንጀል መዋል በማለት ተጠሪ ያቀረበባቸውን የወንጀል ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠባቸው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-አመልካች ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ከመስከረም ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት ወር 2005 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ ቀናት ሰዓቱ ተለይቶ ባልታወቀበት የምሽት የጊዜ ክፍል በን/ላ/ክ/ከተማ በቀበሌ 13 ክልል ልዩ ቦታው የኔታ አካዳሚ በሚባል አካባቢ የግል ተበዳይ መሐመድ አብደላ በሆነ መጋዘን ተቀጥረው ይሰሩ በነበረበት ጊዜ ስማቸው በክሱ የተዘረዘረውን እና በካርቶኖች ታሽገው ተቀምጠው የነበሩትን አጠቃላይ የዋጋ ግምታቸው ብር 373,080 (ሶስት መቶ ሰባ ሶስት ሺህ ሰማንያ) የሆነ የተለያዩ ቧንቧ ዕቃዎችን ከመጋዘን እያወጡ 2ኛ ተከሳሽ ለሆነው ግለሰብ የሰጡ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 669 (2) (መ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቀው በክሱ የተመለከተውን ወንጀል አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ በሶስቱም ተከሳሾች ላይ የግል ተበዳይን ጨምሮ ተጠሪ ያቀረባቸውን አራት ምስክሮች ምስክርነት ከሰማ እና አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ

ስርዓት ቁጥር 27 መሰረት ለምርመራ ክፍል የሰጡትን ቃል ጨምሮ ተጠሪው ያቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ አመልካች በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካች ለምርመራ ክፍል ቃላቸውን የሰጡት በደረሰባቸው ድብደባ ምክንያት ተገደው መሆኑን ያውቁልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ወንጀሉን ያልፈጸምኩ መሆኑን ያስረዳልኛል በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 35 መሰረት ለፍርድ ቤት የሰጡትን ቃል እና የየኔታ አካዳሚ የጥበቃ ሰራተኛ እንጂ የግል ተበዳይ ሰራተኛ አለመሆኔን ያስረዳልኛል በማለት ይህንኑ የሚያስረዳ ማስረጃ በመከላከያነት አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ቀሪዎቹ ሁለት ተከሳሾችም እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ከሰጠ እና መከላከያቸውን ከሰማ በኃላ በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካቹ ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች እና ባቀረቡት የሰነድ መከላከያ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረተባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት ደንጋጌውን ግን ለውጦ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 (3) (ለ) ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ የቅጣት አወሳሰኑ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት እንዲመራ በአመልካቹ ጠበቃ የቀረበውን ጥያቄ ባለመቀበል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ውሳኔው በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ በሚገኘው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ተቀብሎ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም እስከ አስራ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት መሆኑን፣ወንጀሉ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 ደረጃ የወጣለት መሆኑን፣በወንጀሉ የተወሰደው ንብረት ግምት ከብር 100,000 በላይ በመሆኑ እና አንድ ማክበጃ የተገኘ በመሆኑ የሚወድቀው በደረጃ 7 በእርከን 26 ስር መሆኑን፣በእርከን 26 ስር ከተመለከተው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ተደርጎ የተያዘው የስምንት ዓመት ጽኑ እስራት መሆኑን፣የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ያልተገኘ ሲሆን ተቀባይነት ባገኙት ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች የፍቅድ ስልጣኑ እርከን ከ26 ወደ 23 ዝቅ የሚል መሆኑን በዝርዝር ገልጾ በዚሁ እርከን ስር አመልካቹ በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 669 (2) (መ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ እንዲጠብቅ በኃላፊነት የተሰጠውን ንብረት ሰርቋል ተብሎ ክስ ተመስርቶበት አመልካች የግል ተበዳይ ተቀጣሪ አይደለሁም፣ወንጀሉንም አላደረግሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ የግል ተበዳይ ተቀጣሪ አለመሆኑን፣ብቸኛውን የተጠሪ ማስረጃ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 27 መሰረት የተሰጠ ቃል እና የደረጃ ምስክሮችን የምስክርነት ቃል ለመከላከል አመልካቹ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 35 መሰረት የሰጠውን ቃል እና

የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቶ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች በክሱ የተመለከተውን ድንጋጌ ወደ አንቀጽ 669 (3) (ለ) በመቀየር የጥፋተኝት እና የቅጣት ውሳኔ የመስጠታቸውን አግባብነት ከማስረጃ ምዘና መርህ እና ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 113 (2) ድንጋጌ አፈጻጸም አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

3. በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
4. የቅጣት ውሳኔው በሕጉ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ወንጀሉን አላደረግሁም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በክሱ የተዘረዘሩት የዋጋ ግምታቸው ብር 373,080 የሆነ የተለያዩ የቧንቧ ዕቃዎች ከግል ተበዳዩ የተሰረቁ መሆኑ እና የተሰረቁትም ከሚቀመጡበት መጋዘን ውስጥ ለጊዜው ባልታወቀ ሁኔታ እየተወሰዱ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡የዚህ ዓይነት የስርቆት ወንጀል የተፈጸመባቸው ስለመሆኑም የግል ተበዳይ ለአካባቢው ፖሊስ በወቅቱ ሪፖርት ያደረጉ መሆኑም ተረጋግጧል፡፡ የወንጀሉ ፈጻሚዎች ማንነት ለጊዜው ሳይታወቅ የቆየ ቢሆንም የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በተመሳሳይ ሌላ ወንጀል ተጠርጥረው የግል ተበዳይ የወንጀል አቤቱታ ባላቀረቡለት በአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ በኩል በቁጥጥር ስር በነበሩበት ጊዜ የግል ተበዳይን የቧንቧ ዕቃዎችም ከአሁኑ አመልካች ጋር በመተባበር መስረቃቸውን በመግለጻቸው ምክንያት አመልካቹ ጭምር ተይዘው ተጠያቂ መደረጋቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካቹ የግል ተበዳዩ ሰራተኛ ባይሆኑም መጋዘኑ በሚገኝበት ግቢ ከግል ተበዳይ ቤት ተከራይቶ ስራውን ለሚያከናውነው የትምህርት ተቋም በጥበቃ ስራ ሲያገለግሉ የነበሩ መሆናቸውን አልካዱም፡፡ከስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር የስርቆት ወንጀሉን የፈጸሙ ስለመሆኑም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 27 መሰረት ለምርመራ ክፍል በሰጡት የእምነት ቃል አረጋግጠዋል፡፡ይህንን የእምነት ቃል የሰጡት በፈቃዳቸው መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካቹ በሌላ ጊዜ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 35 መሰረት ለፍርድ ቤት ባስመዘገቡት ቃል የፈጸሙት ወንጀል አለመኖሩን መግለጻቸው ብቻውን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ እንደገለጸው ቀደም ሲል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 27 መሰረት ለምርመራ ክፍል የሰጡትን የእምነት ቃል ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡ አመልካች ለምርመራ ክፍሉ የእምነት ቃል የሰጠሁት ተገድጄ

ነው በማለት ያስያዙትን የመከላከያ ጭብጥ በምስክሮቻቸው ማስረዳት አለመቻላቸውን ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው ሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ሁኔታ በውሳኔያቸው ላይ ገልጸዋል፡፡አመልካች ከሌሎች ተባባሪዎቻቸው ጋር የስርቆት ወንጀሉን ያደረጉት በሌሊት እና ዕቃዎቹ የሚቀመጡበትን መጋዘን ባልታወቀ ሁኔታ ከፍቶ በመግባት በመሆኑ እና እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ራሳቸውን ችለው በስርቆት ወንጀል ማክበጃነት አመልካቹ ጥፋተኛ በተባሉበት አንቀጽ 669 (3) (ለ) ስር የተካተቱ በመሆኑ፣እንዲሁም አመልካቹ የተከሰሱበት እና ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌዎች የሚደነግጉት የቅጣት መጠን ተመሳሳይ በመሆኑ አመልካቹ ጥፋተኛ የተባሉት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 (3) (ለ) ስር መሆኑም በአግባቡ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን ማስረጃ መዝኖ በመከላከያነት የቀረበውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ውድቅ በማድረግ በአመልካቹ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ደረጃ ከወጣላቸው ወንጀሎች ውስጥ የሚካተት ሲሆን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቅጣቱን የወሰነው በተጠሪው በኩል የቀረበ የማክበጃ ምክንያት አለመኖሩን እና በአመልካቹ በኩል ተቀባይነት ያገኙ ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች መገኘታቸውን ገልጾ ቅጣቱን የጥፋተኝነት ውሳኔው በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ባለው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማስላት ነው፡፡ ግን አመልካቹ ወንጀሉን አድርገዋል የተባሉት ከመስከረም 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት ወር 2005 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካች ወንጀሉን ባደረጉበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በቅጣት አወሳሰኑ ረገድ ከተሻሻለው መመሪያ በተለየ ሁኔታ የሚያስከትለው ለውጥ መኖር አለመኖሩ እና ካለም ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው የትኛው መመሪያ እንደሆነ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሰረቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎቹን ያወጣው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 88(4) ድንጋጌ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በመሆኑ ምክንያት መመሪያዎቹ እንደ ሕግ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበትን ወንጀል ያደረጉት መመሪያ ቁጥር 1/2002 ስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሲሆን ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ተተክቷል፡፡ በሌላ በኩል አዲሱ የወንጀል ሕግ እንዲጸና ከተደረገ በኃላ አድራጊው ሕጉ ከመጽናቱ በፊት ላደረገው ወንጀል ሲፈረድበት ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው ሕግ ይልቅ አዲሱ ሕግ ቅጣትን የሚያቃልለት በሆነ ጊዜ ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተመለከተው ቅጣት ስለመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ለአመልካቹ ቅጣቱን የሚያቃልለው የትኛው መመሪያ ነው? የሚለውን ነጥብ በተመለከተ በቀላል እና በጽኑ እስራት ለሚያስቀጡ ወንጀሎች ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን ወደታች የሚቀንሰው አንድ እርከን ብቻ ስለመሆኑ በተሻሻለው መመሪያ አንቀጽ 23 (4) ስር የተመለከተ ሲሆን በአንጻሩ መነሻ ቅጣታቸው ሰባት ዓመት ጽኑ እስራት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ወንጀሎች ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን የቅጣቱ ፍቅድ ስልጣን ዝቅ የሚደረገው በሶስት እርከን ስለመሆኑ በቀድሞው መመሪያ በአንቀጽ 16 (7) ስር ተመልክቷል፡፡ይህ ብቻ ሳይሆን አመልካቹ ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል በአዲሱ መመሪያ የሚወድቀው በደረጃ 7 በእርከን 26 ስር ሲሆን በቀድሞው መመሪያ ግን በደረጃ 7 በእርከን 21 ስር በመሆኑ ወንጀሉ ከሚወድቅበት እርከን አንጻርም ያነሰ ቅጣት የሚደነግገው የቀድሞው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ነው፡፡ወንጀሉ የተፈጸመው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሆኖ የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠው ግን የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በስራ ላይ ከዋለ በኃላ በሆነ ጊዜ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ለተከሳሽ ወገን የተሻለ ጥቅም የሚሰጠው መመሪያ ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 95440 እና በሌሎችም መዝገቦች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠ መሆኑም የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ለአመልካቹ ቅጣቱን የሚያቃልለው የቀድሞው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ ቅጣቱን በአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት አስልቶ መወሰኑ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው በአመልካቹ ላይ የቀረበ የማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኙት ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች ለደረጃ 7 በተቀመጠው እርከን 21 ላይ የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን በዘጠኝ እርከን ዝቅ ሲደረግ የሚወድቀው በእርከን 12 ስር ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካቹ ላይ ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው ቅጣት በአባሪ አንድ በእርከን 12 ፍቅድ ስልጣን ስር የተመለከተው የቅጣት መጠን መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በተከሰሱበት የከባድ ስርቆት የወንጀል ክስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ እና በቅጣት ውሳኔው ላይ ግን ከላይ በተገለጸው ምክንያት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111142 በ09/08/2006 ዓ.ም. እና በ12/09/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152298 በ11/02/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በአመልካቹ ላይ ተጥሎ የነበረውን የስድስት ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካቹ በዚህ ጉዳይ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሆኖ በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
4. ይህንኑ ተገንዝቦ በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም አመልካቹ ለሚገኙበት የአዲስ አበባ ማረሚያ ተቋም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክ፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና በማረሚያ ቤት በኩል ለአመልካቹ ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ት/ጌ

የሰ/መ/ቁ. 111006

ቀን 14/11/2007

ዳኞች፡- አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አቶ ሙስጠፋ አህመድ

አቶ ተፈሪ ገብሩ

አቶ ሸምሱ ሲርጋጋ

አቶ አብርሃ መሰለ

**አመልካች፡-** ዲቦ ገልገሎ ቴራ ጠበቃ ትዕግስት ጫንያለው

**ተጠሪ፡-** የፌ/ን/ስ/ላ/ዐቃቤ ሕግ ተወካይ ሕይወት አዳና

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 2/2006 ደረጃና እርከን ላልወጣላቸው ወንጀሎች የሚደረገውን ስሌት እና የቅጣት ማቅለያ ምክንያትን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው "ተከሳሽ የወ/ሕ/ቁ.676(2) (ሀ) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ወይም ለሌላ ሠው ለማስገኘት በማሰብ በስራ አስኪጅነት ተቀጥሮ ሲሰራ ከነበረበት ፍቅር ለሕፃናት በጎ አድርጎት ድርጅት ለስራ የተሰጠውን 1ኛ ቶሺባ ላፕቶፕ 2ኛ አሴሰር ላፕቶፕ 3ኛ. ለሲዲ መግዣ የተሰጠውን ብር 3000 አጠቃላይ ግምቱ ብር 24,000 (ሀያ አራት ሺህ ብር) የሚገመት ንብረት በስራው ሃላፊነት ምክንያት እጁ የገባ ንብረት ይዞ በመሰወሩ በፈፀመው ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ነው፡፡"

ተከሳሹ (የአሁኑ አመልካች) ላፕቶፖቹን እህቱ ላይ በደረሰ የመኪና አደጋ ምክንያት ገንዘብ ችግሮት የወሰደ መሆኑን ብቻ ያመነ ሲሆን የፍ/ቤቱ እንደ ክሱ ሙሉ በሙሉ አላመነም በማለት መዝግቦ የዓ/ሕግ ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተከሳሽ በተከሰሰበት አንቀጽ እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለቱ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቶ ክስ በተመሠረተበትና የጥፋተኛነት ውሳኔ በተሰጠበት የወ/ሕ/አ 676(2) (ሀ) ስር የፅኑ እስራት አማራጭ በመውሰድ የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ከግምት በማስገባት ተከሳሽ በ3 ዓመት ከ3 ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙ ካከራከረ በኃላ የስር ፍ/ቤት ደረጃውን መካከለኛ ማለቱንና ተከሳሽ በፈፀመው አድራጎት የተመለከተውን የገንዘብ መጠን አንፃር የፅኑ እስራት አማራጭ መውሰድ ተገቢ አለመሆኑን በማተት የቀላል እስራት አማራጭን ወስዶ ደረጃውን ዝቅተኛ ብሏል፡፡ ተከሳሽ ወንጀሉን ያመነ እና በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝለት የሚገባ ቢሆንም በወ/ሕ/አ. 663(2) እና 82(1) (ሠ) መሠረት ተከሳሽ የወሰደው ንብረት ስለተመለሠ ብሎ የስር ፍ/ቤት ቅጣት ማቅለያ የተቀበለ በመሆኑ በአንድ የቅጣት ማቅለያ አንቀጽ 82(1) ሠ ተጨማሪ ቅጣት ማቅለያ ሊወሰድ አይገባም በማለት መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ከ6 ወር እስራት ወስዶ የተከሳሽን የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ከግምት በማስገባት ተከሳሽ በ2 ዓመት ከ7 ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን፣የሰበር አቤቱታው ይዘትም "ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የእስራት ቅጣት አማራጭን ከያዘ በኃላ ቅጣቱን ሲያሰላ በልዩ ሕጉ የተደነገገውን የ1 ዓመት እስራት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106 የተመለከተውን የእስራት ቅጣት መድረሻ ጣራ ያለአግባብ በማለፍ 15 ዓመት መያዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ሌላው በስር ፍ/ቤት ወንጀሉን ማመኔን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቱ ተቀብሎ በወ/ህ/ቁ. 82(1) ሠ ስር በድጋሚ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝ አይገባውም ማለቱ ሊታረም ይገባዋል በሚል ነው፡፡"

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በወ/ሕ/አ. 676(2)(ሀ) የቀላል እስራት አማራጭን ከወሰደ በወ/ህ/ቁ 106 ቀላል እስራት ከ10 ቀን እስከ 3 ዓመት ነው ተብሎ ተደንግጎ እያለ የመድረሻ ቅጣቱን 3 ዓመት በመያዙ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያት ከግምት በማስገባት ቅጣቱን ማስላት ሲገባው መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ከስድስት ወር ማለቱ ከወ/ህ/ቁ. 106(1)፣ ከተከሰሰበት አንቀጽ እንዲሁም ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንፃር የቅጣት አወሳሰኑን አግባብነት ግራ ቀኙ ባሉበት ለማየት ሲባል የቀረበ የሰበር ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪም ከስር ዓ/ሕ ቀርቦ ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ የስር ፍ/ቤት የቀላል እስራት አማራጭ ወስዶ አመልካችን ሲቀጣው በወ/ሕጉ አንቀጽ 106(1) መሠረት መሆን እንዳለበት እናምናለን፡፡ የወ/ሕጉ አንቀጽ 106(1) ቀላል እስራት መነሻ 10 ቀናት መድረሻው 3 ዓመት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የተነሳው ይታረምልኝ ጥያቄ ላይ ተቃውሞ የለንም፡፡

የስር ፍ/ቤት የወ/ሕጉ አንቀጽ 663(2) እና 82(1) (ሠ)ን በመጥቀስ አመልካች ድርጊቱን ማመኑን እንደአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሊያዝለት አይገባም ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ተከሳሽ እንደመነሻ አድርገው ቢወሰድም የወ/ሕጉ አንቀጽ 663(2) እና 82(1) (ሠ) ተጣምረው ሲታዩ አመልካች በስር ፍ/ቤት በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት ሙሉ በሙሉ ማመን እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ ተከሳሽ ሙሉ በሙሉ ባለማመኑ ዐ/ሕግ ማስረጃ አሰምቶ ተከሳሽ

እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ባለመከላከሉ ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ አመልካች በወ/ሕጉ አንቀጽ 82(1) (ሠ) ስር ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም፡፡ በወ/ሕጉ አንቀጽ 663 (2) መሠረት የወሰደውን ዕቃ ሙሉ በሙሉ ያልመለሰና የተከሰሰበትን ወንጀል ሙሉ በሙሉ ያላመነ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ቅጣት ሲጣል ከግምት ሊያስገባው የሚችል በመሆኑና ፍ/ቤቱ ሲያምንበት ብቻ እንደሆነ መረዳት የሚቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት በፅሑፍ መልሱን አቅርቧል፡፡ እኛም የአመልካችን አቤቱታ አግባብነት ካለው የወ/ሕጉ ድንጋጌ እና ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 እንዲሁም ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጋር ከዚህ በላይ ሰበር ችሎቱ ከያዘው ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም፤

የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ተቀብሎ የአመልካችን የወንጀል አፈጻጸምን መሠረት በማድረግ በአመልካች ላይ ሊወሰን የሚገባው በቀላል እስራት ቅጣት ነው ብሎ ካመነበት አመልካቹ ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕግ አንቀጽ 676(2) (ሀ) ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ የተመለከተ በመሆኑ፣ቀላል እስራትን አስመልክቶ በወ/ሕጉ አንቀጽ 106(1) ከ10 ቀን እስከ 3 ዓመት እንደሆነ የተመለከተ ስለሆነ እና የወ/ህጉ አንቀጽ 676(2)(ሀ) ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 19(6) መሠረት ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት ያለውን እስራት ለአራት እኩል በመክፈል የቅጣት እርከኑን በመለየት መነሻ ቅጣት መወሰን ሲገባው የስር ፍ/ቤት (ፌ/ከፍ/ፍ/ቤት) መነሻ ቅጣቱን ስለቀላል እስራት በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጽ 106(1) ከተመለከተው 3 ዓመት ጣሪያ አልፎ መነሻ ቅጣቱ 3 ዓመት ከ6 ወር መያዙ የወንጀል ሕጉን እና የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሠረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የተከሳሽ (አመልካች) ወንጀል አፈፃፀም እና በእምነት ማጉደል ከወሰዳቸው ንብረቶች የመለሰው ንብረት መኖሩን ከግምት በማስገባት አመልካች ጥፋተኛ በተባለበት የወ/ሕግ አንቀጽ 676(2) (ሀ) የቀላል እስራት አማራጭ መወሰዱ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ሲሆን ከወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጽ 106(1) ጋር በማገናዘብ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 19(6) መሠረት እርከን አንድ ከ1 ዓመት እስከ 1 ዓመት ከ6 ወር ይሆናል የወንጀሉን አፈፃፀምና ክብደት መሠረት በማድረግ ቀላል ወንጀል ደረጃ የተሰጠው በመሆኑ በዚህ እርከን አንድ ውስጥ መነሻ ቅጣቱ 1 ዓመት ከ4 ወር እንዲሆን ወስነናል መነሻ ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው የቅጣት ሠንጠረዥ እርከን 7 ከ1 ዓመት እስከ 1 ዓመት ከ6 ወር በሚለው ስር ይወድቃል፡፡

በፀ/ሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ባለመኖሩ ቅጣቱ የሚከብድ አይሆንም በሌላ በኩል አመልካች ለሰበር ችሎት እንደ አንድ ቅሬታ ምክንያት በማድረግ ወንጀሉን መፈፀሜን

ማመኔ በወ/ሕጉ አንቀጽ 82(1) ሠ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝልኝ ሲገባ በሥር ፍ/ቤቶች ታልፎብኛል በማለት የተከራከረ ቢሆንም፤ አመልካች በስር ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የወ/ሕጉን አንቀጽ 676(2) (ሀ) በመተላለፍ ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅሟል በሚል በክሱ ዘርዝሮ ከተመለከተው ብር 3000 (ሦስት ሺህ ብር) መውሰዱን ሳያምን ላብቶፖቹን ብቻ ወስጃለው በማለት ያመነ በመሆኑ የእምነት ቃሉ ከወንጀሉ ዝርዝር ጋር ሲታይ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ ሙሉ በሙሉ ያመነ ባለመሆኑ በከፊል ማመኑ በቅጣት ፈቅደ ስልጣን ከግምት ሊገባ ከሚችል በቀር ራሱን ችሎ አንድ ቅጣት ማቅለያ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች ይህንን በወ/ህ/አንቀጽ 82(1)(ሠ) እንደ አንድ ቅጣት ማቅለያ ምክንያት አለመውሰዳቸው በአግባቡ ስለሆነ በዚህ ላይ አመልካች ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

በስር ፍ/ቤቱ ተከሳሽ (አመልካች) የዘወትር አመሉ መልካም እንደነበረ ግምት በመውሰድ በወ/ሕጉ አንቀጽ 82(1) (ሀ) እና ንብረቶቹ በመመለሳቸው በወ/ህ/አ 663(2) እና 82(1) (ሠ) መሠረት የተያዘለትን ሁለት ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመውሰድ መነሻ ቅጣት ካረፈበት እርከን 7 በሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ወደ እርከን 5 ዝቅ ይላል በዚህ እርከን 5 የተመለከተው የቅጣት ፈቅድ ስልጣን ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት እስራት ሲሆን ተከሳሹን ያርማል ለሌላው ማስተማሪያ ይሆናል ብለን ባመንበት በ1 ዓመት እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 88912 በቀን 3/03/07 ዓ.ም በዋለ ችሎት፤የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 145151 በቀን 3/07/07 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጡት የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ቁ. 195(2) (ለ) (2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
- ተከሳሽ (አመልካች) በዚህ ወንጀል ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ ዓመት እስራት እንዲቀጣ የስር ፍ/ቤቶች የቅጣት ውሳኔን በማሻሻል ወስነናል፡፡ እንደ ተሻለው የቅጣት ውሳኔ ይፈፀም ዘንድ ተከሳሹ ታስሮ ለሚገኝበት መ/ቤት ይፃፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**የ/ማ**

የሰ/መ/ቁ 111742

ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገብረሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካቾች፡-** 1. ኮሎኔል ተክሉ ፍስሐ

2.ኮሎኔል ፀሐይ ዋሉ } ስለሁለቱም ጠበቃ ረጋሳ ሽጋ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክሱ በቀረበበት የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኖቹ አመልካቾች እንደቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የነበሩ ናቸው፡፡ ተጠሪ በ29/01/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ ያቀረበባቸው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ተከሳሾቹ በክልሉ የደን አዋጅ ቁጥር 72/1995 በአንቀጽ 13 (1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በ27/01/2007 ዓ.ም ከጠዋቱ 1፡30 ሰዓት ላይ 1ኛ ተከሳሽ የዋጋ ግምቱ ብር 5,400 የሆነ 60 ማዳበሪያ ከሰል፣ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ የዋጋ ግምቱ ብር 4,590 የሆነ 51 ማዳበሪያ ከሰል በሚያሽከረክሯቸው ሁለት ተሽከርካሪዎች ጭነው በቢሾፍቱ ከተማ ውስጥ በመያዛቸው የደን ውጤቶችን ያለፈቃድ የማዘዋወር ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን ተከሳሾቹ ተጠይቀው በክሱ ላይ መቃወሚያ እንደሌላቸው ከገለጹ በኃላ ድርጊቱን መፈጸማቸውን፣ ከሰሉን የጫኑት ለቤተሰቦቻቸው እንጂ ለንግድ አለመሆኑን፣ድርጊቱን መፈጸማቸው በርግጥ ጥፋት መሆኑን አምነው በማስመዝገባቸው ዓቃቤ ህግ በጠየቀው መሰረት ፍርድ ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 134 (1) መሰረት በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ እያንዳንዳቸው በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ተከሳሾቹ ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ

በጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ የቀረበውን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የቅጣቱን መጠን ብቻ አሻሽሎ እያንዳንዳቸው በሶስት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የቀረበላቸውን እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና አቤቱታ ዘግተው በማሰናበታቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾቹ እንደክሱ በዝርዝር ወንጀሉን የፈጸሙ ስለመሆናቸው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሳይክዱ አምነዋል ተብለው በዚህ መነሻነት በስር ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት አንድ ተከሳሽ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ ሙሉ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል ሲል በመዝገብ ከጻፈ በኃላ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኛነት ውሳኔ የሚሰጥ ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 134(1) ስር የተመለከተ ሲሆን በዚህ አግባብ በእምነት ቃሉ መሰረት የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠበት ተከሳሽ ስለቅጣቱ ልክ ወይም ስለቅጣቱ ህጋዊነት ካልሆነ በቀር በጥፋተኛነት ውሳኔው ላይ ይግባኝ ማለት የማይችል ስለመሆኑም በስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 185(1) ስር ተመልክቶአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የወረዳው ፍርድ ቤት በአመለካቾች ላይ የጥፋተኛነት ውሳኔ የሰጠው የተከሰሱበትን ወንጀል ሙሉ በሙሉ አምነዋል በማለት ሲሆን ይግባኙን የተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾቹ በጥፋተኛነት ውሳኔው ላይ ያቀረቡትን ቅሬታ ሳይቀበል የቅጣት ውሳኔውን ብቻ በማሻሻል ውሳኔ የሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔው የተሰጠው በአመልካቾች የእምነት ቃል መሠረት በመሆኑ በጥፋተኛነት ውሳኔው ላይ ይግባኝ ሊያቀርቡ የሚችሉበት የህግ አግባብ አለመኖሩን በምክንያትነት በመጥቀስ ነው፡፡

በመሠረቱ ከላይ በተጠቀሰው የወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 134 (1) መሰረት በተከሳሹ ላይ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው ተከሳሹ ያስመዘገበው የእምነት ቃል በክስ ማመልከቻው በተገለፀው የወንጀል ዝርዝር መሰረት ወንጀሉን ማድረጉን ሙሉ በሙሉ ያመነ መሆኑን የሚያረጋግጥ በሆነ ጊዜ ነው፡፡ ተከሳሹ እንደ ሕጉ አነጋገር ወንጀሉን መፈፀሙን ሙሉ በሙሉ ያመነ መሆኑን ለማረጋገጥ ያስችል ዘንድ የሚያስመዘግበው የእምነት ቃል መነፃፀር የሚገባው ከወንጀሉ ዝርዝር ጋር ብቻ ሳይሆን በክሱ ተላልፎታል ከተባለው የሕግ ድንጋጌ አነጋገር ጭምር ነው፡፡ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል እያንዳንዱ ክስ ወንጀሉን እና ሁኔታውን በዝርዝር መግለፅ ያለበት ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ስለ ወንጀሉ እና ስለ

ሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ የፈፀመውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ በስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 112 የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾቹ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ካቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩት ለወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠነው ቃል በአግባቡ እና በዝርዝር አልተመዘገበም• የመከላከያ ማስረጃ አቅርበን ክሱን እንድንከላከልም ዕድል አልተሰጠንም በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመላክታል፡፡ ተከሳሾቹ ወንጀሉን መፈፀማቸውን አምነዋል በሚል መዝግቦ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከመስጠቱ በቀር ተከሳሾቹ ተላልፈዋል ተብለው የተከሰሱት የትኛውን ሕግ እና ድንጋጌ እንደሆነ እንኳ የወረዳው ፍርድ ቤት በጥፋተኝነት ውሣኔውም ሆነ በቅጣት ውሣኔው ላይ አላሰፈረም፡፡ ተላልፈውታል የተባለው ሕግ እና ድንጋጌ የተጠቀሰው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ተከሳሾቹ አስመዝግበውታል የተባለው የእምነት ቃል ከተከሰሱበት ድንጋጌ ጋር ተነፃፅሮ በስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 134(1) ድንጋጌ መሰረት የእምነት ቃልን የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተከሳሾቹ ወንጀሉን መፈፀማቸውን ሙሉ በሙሉ አምነዋል በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠቱ ደግሞ የቁጥር 134 (1)ድንጋጌ ዓላማ እና መንፈስ መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አመልካቾች ያስመዘገቡት ቃል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ሥርዓተ ቁጥር 134 (1) ድንጋጌ አነጋገር መሰረት የእምነት ቃልን የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑን ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ወንጀሉን መፈፀማቸውን አምነዋል ተብሎ በአመልካቾቹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 45255 በ29/01/2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 39258 በ17/03/2007 ዓ/ም በውሳኔ የተሻሻለው እና በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 200050 በ02/04/2007 ዓ/ም እና በመዝገብ ቁጥር 199366 በ08/07/2007 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾቹ ያስመዘገቡት ቃል በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 134/1/ ድንጋጌ አነጋገር መሰረት የእምነት ቃልን የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑ ሳይረጋገጥ የጥፋተኛነት ውሳኔ መስጠቱ የስነ ስርዓት ህጉን መሰረት ያደረገ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡

3. አመልካቾቹ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 132 /1/ እና /3/ መሰረት ቃላቸውን እንዲያስመዘግቡ ካደረገ በኃላ የሚያስመዘግቡት ቃል ከወንጀሉ ዝርዝር እና ከተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ አነጋገር አንጻር ወንጀሉን ማድረጋቸውን ሙሉ በሙሉ አምነዋል የሚያሰኝ መሆን አለመሆኑን መርምሮ እና የሚያስመዘግቡት ቃል የእምነት ቃልን የሚያቋቁም አይደለም የሚል ከሆነም ጉዳዩን በስነ ስርዓት ህጉ መሰረት በማስረጃ አጣርቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለአደአ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን አንቀሳቅሶ መጥሪያ እስኪልክላቸው እና ክርክሩ እንዲቀጥል እስካደርግ ድረስ አመልካቾቹ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት ባለመገኘቱ ከእስር እንዲለቃቸው ለሚገኙበት የምስራቅ ሸዋ ዞን ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ትእዛዝ ይተላለፍ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለአደአ ወረዳ ፍ/ቤት፣ እንዲያውቁት ደግሞ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**የ/ማ**

የሰበር መ/ቁ.100860

ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንኾሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ፋንቱ ቡቼ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ዐቃቢ ሕግ - ወ/ት ፍጹም ደጉ ቀርበዋል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለዉን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

# ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ.61059 ላይ በ18/06/2006 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት በ22/07/2006 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ በማቅረቡ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፣ የአሁን ተጠሪ /የሥር ከሳሽ/ የዳራ ወረዳ ዐቃቤ ሕግ በዳራ ወረዳ ፍ/ቤት በቀረበዉ የማታለል ወንጀል ክስ የአሁን አመልካች /የሥር ተካሳሽ/ አቶ ፋንቱ ቡቼ የ/ወ/ሕ/ቁ.692 /1/ ሥር የተደነገገዉን በመተላለፍ የግል ተበዳይ አቶ ቾቼ ላሚሶ በፍ/ቤት ላለዉ የመሬት ክስ ዳኞችን ይገፔ ነገርን አስጨርስልሃለሁ በማለት ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ጊዘያቶ በአጠ ቃላይ ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ በማታለል በመዉሰዱ ተከሷል የሚል ነዉ፡፡ ተከሳሽ አቶ ፋንቱ ቡቼ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት በሰጠዉ የእምነት ክህደት ቃል «ወንጀሉን አልፈፀምኩም በማለት ክዶ» ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግል ተበዳይን ጨምሮ የዐቃቤ ሕግ ሶስት የሰዉ ምስክሮችን ተሰምተዋል፡፡

በመቀጠልም ፍ/ቤቱ ተካሳሹን ተከላከል ማለቱን፤ ክሱን ተከላከል ብሎ ከሆነ የመከላከያ ምስክሮች ለምን ቀርቦ እንዳልተሰሙ በምን ምክንያት እንደታለፈ በዉሳኔዉ ላይ የጠቀሰዉ ነገር የለም:: ነገር ግን የወረዳዉ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.11973 በ22/122005 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል በመመዘን እንደክሱ አረጋግጧል በማለት ተከሳሹን በወ/ሕግ አንቀፅ.692 /1/ ሥር ጥፋተኛ በማድረግ የዐቃቤ ሕግን የቅጣት አስተያየት በመቀበል የወንጀሉን ደረጃ 5 አድርጎና የቅጣት እርከን 14 በመያዝ በ3 ዓመት እስራት እና 1000 ብር እንዲቀጣ ወስኗል::

የአሁን አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታዉን ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በመዝገብ ቁ.30133 በ30/01/2006 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.195 /2/ለ-2/ መሰረት የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔን በማጽናት ወስኗል:: አመልካች አሁንም ይህን ዉሳኔ በመቃወም አቤቱታዉን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም፣ ችሎቱ በመዝገብ ቁ.61059 በ18/06/2006 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለ አቤቱታዉ ለሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም በማለት ወስኗል:: አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ሊያቀርብ የቻለዉ ይህን ዉሳኔ ለማስለወጥ ነዉ::

አመልካች በ22/07/2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የዓቃቤ ሕግ የሰዉ ምስክሮች እንደክሱ ጭብጥ የአስረዱት ነገር የለም:: ክሱ ራሱ በሰዎች ቅንብር በዉሸት የቀረበብኝ ነዉ:: እኔ ይህን ግለሰብ አምስት ጊዜ ወደ ቤት በመጥራት የተጠቀሰዉን ገንዘብ ስቀበል ምንም ዓይነት ዉል ወይም ተጨባጭ ማስረጃ በሌለበት ይህን ብር ስጥቸዋለሁ ያለዉ አግባብነት የለዉም:: ዓቃቤ ሕግ የማስረዳት ኃላፊነቱን አልተወጣም:: የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ከጥርጥሬ ዉጭ ስላለስረዱ በነጻ መሰናበት ነበረብኝ:: እኔ የተከሰስኩበት ወንጀል የዋስትና መብት የማያስከለክለኝ ቢሆንም የወረዳዉ ፍ/ቤት አሳስሮኝ መከላከያዬን እንዳላቀርብ ስላደረገኝ በሕገ መንግስት አንቀጽ 19-20 የተደነገገዉን የመከላከል መብቴን ያጣበበብኝ በመሆኑ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ግድፈት ተፈጽሟል በማለት በዝርዝር አቅርቧል:: ስለዚህ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት

አቤቱታዉን ተመልክቶ የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር በነጻ እንዲያሰናብተኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ከዚህ በኃላ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በመመርመር አቤቱታዉ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በማለት ተጠሪዉ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘዉ መሰረት በ07/11/2006 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካች ብር 25000 ከግል ተበዳይ በማታለል በተለያየ ጊዜ መዉሰዱን የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በተገቢ ሁኔታ ከጥርጣሬ በላይ መስክረዋል፡፡ የመከላከል መብት በተመለከተ፣ የወረዳ ፍ/ቤት ሕገ መንግስትንና የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓትን መሰረት በማድረግ የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በ15/12/2005 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ከሰማ በኋላ፣ ከጥርጣሬ በላይ ስለተመሰከረበት ተከሳሹ እንዲከላከል ትዕዛዝ በመስጠት የመከላከያ ምስክሮች ስም ዝርዝር አቅርቦ በ16/12/2005 ዓ.ም ቀርቦ እንዲከላከል ወስኖ በዕለቱ በዋለዉ በወንጀል ችሎት መከላከያዎቹን ባለማቅረቡ በድጋሚ ዕድል በመስጠት በ20/12/2005 ዓ.ም አቅርቦ እንዲከላከል ህገ መንግስታዊ የመከላከል መብቱ ቢጠ ብቅለትም በራሱ ፈቃድ መብቱን አለመጠቀሙ ፍ/ቤቱ መብቱን አጣቧል ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ አመልካች የህግ ስህተት አለባቸዉ ብሎ ያቀረባቸዉ ነገሮች የህግ ስህተት የሌለበትና ተገቢ የሆነ ዉሳኔ የተሰጠበት ነዉ በማለት በዝርዝር የተለያዩ ነጥቦችን በማንሳት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በ02/04/2006 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዉን በማጠ ናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተ ሲሆን፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ፡-አመልካች የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ የመከላከል መብት የታለፈዉ በሕግ አግባብ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነዉ የዳራ ወረዳ ዐቃቤ ሕግ በዳራ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የማታለል ወንጀል ፈጽሟል በማለት የወ/ሕ/ቁ.692 /1/ በመጥቀስ የቀረበዉን ክስ በተመለከተ፣ አመልካች ፍ/ቤት ቀርቦ በሰጠዉ ቃል የተጠቀሰዉን ወንጀል ያልፈፀምኩት ነዉ በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሶስት ምስክሮችን መስማቱን በዉሳኔዉ

ላይ ጠቅሷል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ የዓቃቢ ሕግ ምስክሮች እንደክሱ ስላረጋገጡ አመልካችን ተከላከል ማለቱን፤ አመልካች በምን ምክንያት የመከላከያ ማስረጃዉን እንዳላቀረበና እንደታለፉ በዉሳኔዉ ላይ የጠቀሰዉ ነገር የለም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት የዉሳኔ አጻጻፍ ችግር እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤቱ ለዚህ መብት ተገቢ ግምት ሰጥቷል ወይ? የሚል የሕግ ጥያቄ የሚያነሳ ነዉ፡፡

በዚህ አግባብ ሲታይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.142 /1/ እንደሚደነግገዉ የዐቃቤ ህግና የተበዳይ ማስረጃ እንደክሱ ጭብጥ የመሰከሩ ወይም ያረጋገጡ ከሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማት እንደሚጀምርና መንገር እንደሚችል ነዉ፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለዉ የመከላከያ ምስረጃን አቅርቦ ማሰማት የተከሳሹ መብትና ግዴታ መሆኑን ነዉ፡፡ ፍ/ቤቱ ግን ተከሳሹ በዚህ መብቱ እንዲጠቀም የነገረዉ መሆኑን በዉሳኔዉ ማመልከት ተገቢ ነዉ፡፡ ከዚህም በላይ የተከሰሱ ሰዎች በሕገ መንግስት ከተከበረላቸዉ ሰብዓዊ መብቶች መካከል «የመከላከል መብት» አንዱ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 /4/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሰረት የተከሰሱ ሰዎች «የቀረበባቸዉን ማናቸዉንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡብትን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸዉን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸዉ ቀርቦ እንዲሰሙላቸዉ የመጠየቅ መብት አላቸዉ»፡፡ ስለዚህ የመከላከል መብት ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ ያገኘ መብት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ከዚህም በላይ ይህ «የመከላከል መብት» በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሰነዶች ጥበቃ የተደረገለት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነዉ፡፡ እ.አ.አ. በ1976 በጸደቀዉ ዓለም አቀፍ የማህበራዊ እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14 /3፣ረ/ እንደሚደነግገዉ የተከሰሰ ሰዉ የራሱን ምስክሮች አቅርቦ የመጠየቅ መብት እንዳለዉ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13 /2/ ሽፋን ያገኘ ጉዳይ ነዉ፡፡

ይህን «የመከላከል መብት» በተመለከተ ፍ/ቤት ያላቸዉ ሚና ሲታይ በሕገ መንስግቱ አንቀጽ 13 /1/ መሰረት «የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸዉ»፡፡ ከዚህ አኳያ ፍ/ቤት የተከሰሱ ሰዎች የመከላከል መብታቸዉን በሚገባ መጠቀም እንዲችሉ አስፈላጊዉን ሁኔታ ለማመቻቸት በሕግ አግባብ የተቻለዉን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል እንጂ በምንም መልኩ ይህን መብት ለሚገድብ

ድርጊት አስተዋጽኦ ማድረግ የለበትም። ፍ/ቤት የተቀላጠፉ ፍትሕ አሰጣጥን ከግምት ዉስጥ በማስገባት የተከሰሰዉ ሰዉ ምስክሮቹን ለማቅረብ ያለዉን አቅም እና የተመቻቸ ሁኔታ፣ በማረሚያ ቤት መሆኑን እና አለመሆኑን፣ የመከላከያ ማስረጃና ምስክሮችን ለማቅረብ የሚጠይቀዉን እገዛ፣ በቂ ነዉ ሊባል የሚችል ጊዜ እና አጠቃላይ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ዉስጥ በማስገባት በዚህ መብት ተጠቃሚ እንዲሆን አስፈላጊዉን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል። ስለዚህ ፍ/ቤት ይህን ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነትና ግዴታዉን በአግባቡ መወጣት አለበት።

ከዚህ አንጻር አሁን የያዝነዉን ጉዳይ ስንመለከት የዳራ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች የዓቃቢ ሕግ ምስክሮች እንደክሱ ስለመሰከሩበት እንዲከላከል ብይን መስጠቱን፣ አመልካች የመከላከያ ምስክሮቹን ከማቅረብ አንጻር የጠየቀዉን መብት፣ የመከላከያ ምስክሮችን ሳይሰማ ለምን እንደታለፉ በዉሳኔዉ ዉስጥ የጠቀሰዉ ነገር የለም። የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ያህል በዓለም አቀፍ ሠነዶች እና በሕገ መንግስቱ ጥበቃ የተደረገለትን የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸዉን ክስ የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ «የመከላከል መብት» በዉሳኔዉ አለማካተቱ በሕገ መንግስቱ የተጠለበትን ኃላፊነት በሚገባ ተወጥቷል ብሎ ለመናገር የሚያስችል አይደለም። የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የሰበር ሰሚ ችሎት የወረዳዉን ዉሳኔ ማስተካከል ሲገባቸዉ ዉሳኔዉን ማጽናታቸዉ ከዚህ አንጻር የሚጠበቅባቸዉን ሚና ተወጥቷል ለማለት አያስደፍርም።

በዚህ በኩል ተጠሪ ያቀረበዉ መልስ ሲታይ ፍ/ቤቱ በ15/12/2005 ዓ.ም የዐቃቢ ህግ ምስክሮችን እንደሰማ፣ አመልካች በ16/12/2005 ዓ.ም የመከላከያ ምስክሮቹን እንዲያቀርብ መታዘዙን፣ በድጋሚ ተለዋጭ ቀጠሮ ለ20/12/2005 ዓ.ም እንደተሰጠ በመጥቀስ አመልካቹ በራሱ ፈቃድ መከላከል እንዳልፈለገ በመጥቀስ ተከራክሯል። አመልካች ደግሞ ባቀረበዉ ክርክር ፍ/ቤቱ በማረሚያ ቤት እንዲታሰር አድርጎኝ በሁለት ቀን ዉስጥ እንዲከላከል ትዕዛዝ መስጠቱ እንዳልከላከል እንደማድረግ ይቆጠራል በማለት የመልስ መልሱን ሰጥቷል። የወረዳዉ ፍ/ቤት ተከሳሹ የመከላከያ ምስክሮቹን እንዲያቀርብ የሰጠዉ ጊዜ በአጠቃላይ ከ4 ቀናት የሚበልጥ አይደለም። ከዚህ ክርክር መረዳት እንደሚቻለዉ ፍ/ቤቱ አመልካች በማረሚያ ቤት ታስሮ መገኘቱን እያወቀ የመከላከያ ምስክሮቹን

አቅርቦ በማሰማት ሕገ መንግስታዊ መብቱን በሚገባ እንዲጠቀምበት ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ዉስጥ በማስገባት በቂ ነዉ ሊባል የሚያስችል ጊዜ ሰጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ፍ/ቤቱ አመልካቹ ያለበትን ሁኔታ ከግምት ዉስጥ ሳያስገባ በዚህ አጭር ጊዜ ዉስጥ ምስክሮቹን እንዲያቀርብ በማዘዝ፣ ምስክሮችን አላቀረበክም በማለት ማለፉ መብቱን እንዳይጠቀም እንደመከልከል የሚቆጠር ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የስር ፍ/ቤቶች አመልካቹ «የመከላከል መብቱን» እንዲጠቀም ተገቢና አስፈላጊ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ በህገ መንግስቱም ሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ የተጣለባቸዉን ኃላፊነትና ግዴታ በሚገባ ተወጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ እንዳያሰማ በማድረግ፣ የመከላከል መብቱን የሏ የሕጋዊና በቂ ምክንያት በማለፍ የጥፋተኝነት ዉሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ የወሰነቡት አግባብ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ በማለት የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

- የዳራ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.11973 በ22/12/2005 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እና የስዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.30133 በ30/01/2006 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ.61059 በ18/06/2006 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡
- የዳራ ወረዳ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ድጋሚ በማየት ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ዉስጥ በማስገባት በቂ ነዉ ሊባል የሚችል ጊዜ በመስጠት አመልካች የመከላከያ ምስክሮቹን አቅርቦ እንዲያሰማ በማድረግ፤ በሕጉ አግባብ በማጣራትና በመመዘን ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ይስጥ ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡
- የዳራ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች ብር 1000 /አንድ ሺህ/ የሚሆን በቂ ዋስትና ካቀረበ ወይም ይህን ገንዘብ በወረዳዉ ፋይናንስ በሞዴል ካስያዘ ከማረሚያ ቤት ዉጭ ሆኖ እንዲከራከር እንዲያደርግ ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡ ጉዳዩን ባለ 5 ዳኛ እንዲታይ ተብሏል፡፡

- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶት፣ ለማረሚያ ቤት፣ እና ለአመልካች ይድረስ ብለናል፡፡
- መዝገቡ ዉሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ.101056

ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጤቻ

**አመልካች፡-** አቶ አይሸሽም ገብሬ - ጉዳዩ ተከታታይ ቤተሰብ ቀረበች

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል የሥነ - ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን - አልቀረበም፡፡

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1በዋና ወንጀል ሠሪነትና በግብረአበርነት አንድ የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው በፍርድ ተረጋግጦ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየው ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት /ይግባኝ ሰሚ ችሎት/ተመሣሣይ ፍርድና የቅጣት ውሣኔ የተሰጠባቸው ሰዎች በተለያየ መዝገብ የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበው•የአንደኛው የሰበር አቤቱታ አቅራቢ የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቅጽ 22 መሠረት ቢዘጋና የሌላኛው የሰበር አቤቱታ አቅራቢ የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ወይም ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሣኔ ቢሻሻልና የሰበር ችሎት በማሻሻል የሰጠው ፍርድ ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር የሚያስቀርብ ነጥብ የለውም ተብሎ የተዘጋበትን አቤቱታ አቅራቢ የሚጠቅመው ሆኖ ቢገኝ• የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም?የሚለውን አከራካሪ የህግ ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡
2. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች አንደኛ ተከሳሽ በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 አመልካች የነበረው አክሊለብርሃን አባቡ ሁለተኛ ተከሳሽ ሆነው በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)ሀ እና አንቀጽ 408 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኦዲተሮች ሆነው ሲሰሩ ኦዲት እንዲያደርጉ ከተመደቡበት ኦትራክን/ ጄኔራል ኢትዮጵያ ሰርቪስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የቆዳና ሌጦ ፋብሪካ

ግብይት አቅራቢ ድርጅት ሂሳቡ አምስት ሚሊዮን ብር ብር / 5000,000/ጉድለት ያሳያል በማለት ከድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ጋር በአካልና በስልክ በመደራደር ብር 600,000 /ስድስት መቶ ሺህ እንዲከፍላቸው በመስማማት ሰኔ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ አስራ ሁለት ሠዓት ከድርጅቱሥራ አስኪያጅ ጋር ቀጠሮ በያዙበት ቦታ ተገኝተውና ከድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ መኪና ውስጥ ገብተው በተደራደሩበት ገንዘብ ውስጥ ብር 100,000/አንድ መቶ ሺህ/ አንደኛ ተከሳሽ የአሁኑት አመልካች በጥቁር ፌስታል እንደተጠቀለለ ተቀብሎ ሲወርድ ሁለተኛ ተከሳሽ /በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013/አመልካች የነበረው አክሊለብርሃን አባቡ መኪናው ውስጥ ተቀምጦ ቀሪውን ገንዘብ ለመቀበል በመጠባበቅ ላይ እያለ የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በመደባቸው የክትትል አባሎች እጅ ከፍንጅ መያዛቸውን በማረጋገጥ• የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሾች የተከሰሱበትን የህግ ድንጋጌ በመተላለፍ ከባድ የጉቦ መቀበል የሙስና ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት በመዝገብ ቁጥር 123410 የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

3. የቅጣት ውሣኔውን በተመለከተ• ወንጀሉ በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ነው በማለትና የቅጣት ደረጃው ከሰባት ዓመት እስከ ዘጠኝ ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት መሆኑን ገልፆ በሁለቱም ላይ የመነሻ ቅጣቱ ስምንት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 4000/አራት ሺህ ብር/ መቀጮ እንደሆነ ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች አራት ታናናሽ እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑን በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝለት ያቀረበውን ጥያቄ አስተዳድራቸዋለው ያልከው ልጆችህን ወይም ሚስትህን አይደለም በሚል ምክንያት ውድቅ ካደረገ በኃላ አመልካች የወንጀል ሪከርድ የሌለበት መሆኑንና እና ፀባያቸው መልካም የነበረ መሆኑን አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያትን በመቀበል በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን በመቀነስ ከእርከን ሃያ ስድስት ወደ እርከን ሃያ አምስት ዝቅ በማድረግ ተከሳሾች በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እሰራትና በብር 3000/ሶስት ሺህ ብር/መቀጮ እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት የቅጣት ውሣኔ በመቃወም የአሁኑ አመልካች የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 96631 ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ•ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉዳዩ የሚያስገባ ምክንያት የለም በማለት የካቲት 20 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ/ትዕዛዝ/ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 አቤቱታ ያቀረበው የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ በበኩሉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመቃወም በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 96526 ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉዳዩ የሚያስገባ ምክንያት የለም በማለት የካቲት 25 2006 ዓ.ም በሠጠው ውሳኔ/ ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

5. የአሁን አመልካች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም ግንቦት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ አቅርቦ፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታውንና መዝገቡን ከመረመረመ በኃላ በቀረበው ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተሰርቷል ማለት አልተቻለም በመሆኑም መዝገቡ ለሰበር አያስቀርብም ብለናል በሚል ትዕዛዝ ቅጥምት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶበት ተዘግቷል፡፡

6. ከአመልካች ጋር በወንጀል ተካፋይነት የተከሰሰውና ጥፋተኛ የተባለው እንደዚሁም ይግባኙ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 95526 ይግባኝ ሰሚው ችሎት የካቲት 25 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ውድቅ የተደረገበት አክሊለብርሃን አባቡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ግንቦት 11 ቀን 2006 ዓ.ም ፅፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በመመርመር የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የጥፋተኝነት ቅጣቱን የወሰንኩት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ለሰበር ችሎት በመቅረቡ፣ ይኸ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሣኔ አፅንቶ የቅጣት ውሣኔውን በማሻሻል መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

7. በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም የቅጣት ውሣኔውን ሲያሻሽል የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሁለት መሠረታዊ የህግ ስህተቶች ሠርተዋል፡፡ የመጀመሪያ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት በተለይም እናት አባት ወንድም እህት ማስተዳደርና መርዳት /ልጅና ሚስት/ካልሆነ በስተቀር በወንጀል ህግ አንቀጽ 86 የሚሸፍን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሊሆን አይችልም በማለት የሰጡት የህግ ትርጉም ስህተት ያለበት መሆኑን በመተንተን• ተከሳሹ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ወንድሞቹን እህቶቹን እናትና አባቱን እየረዳና እያስተዳደረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከቀረበ በወንጀል ህግ አንቀጽ 86 ሥር የሚሸፈን ልዩ የቅጣት ምክንያት እንደሚሆን ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ቅጣቱ መሠላት ያለበት መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት በመተንተን• በመዝገብ ቁጥር 101013 አመልካች የነበረው ሰው• እናቱን አባቱን ወንድምና እህቶቹን የሚረዳ መሆኑ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት እንዲያዝለትና•በሁለቱ የቅጣት ምክንያቶች በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 17 ንሁስ አንቀፅ 7 መሠረት ሶስት እርከን በአጠቃላይ ስድስት እርከን ሲቀንስ ከእርከን ሃያ ስድስት ወደ እርከን አስራ ዘጠኝ ዝቅ የሚል በመሆኑ አመልካች አክለስብርሃን አባቡ በእርከን አስራ ዘጠኝ ከተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ ውስጥ በአራት ዓመት ፅኑ እስራትና በብር 3000/ሶስት ሺ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101013 መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል ፡፡

8. ከዚህ በኋላ አመልካች በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ ከነበረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 የቅጣት ውሳኔ ከተሻሻለበት አክሊብርሃን አባቡ ጋር ተመሣሣይ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያቀረቡ መሆኑን ገልፆ እህቶችህን የማስተዳድር መሆኑ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አይሆንም በማለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚችሎት የሰጡት የህግ ትርጉም ስህተት ያለበት መሆኑ በሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑና በጉዳዩም ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሆኑ በሰበር ችሎት የተወሰነ ሆኖ እያለ• የእኔ የሰበር አቤቱታ የሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር የሚቀርብ ነጥብ የለውም በሎ ስለዘጋው ብቻ የእኩልነትና ፍትህ የማግኘት መብቴ ተገድቦ ሊቀር ስለማይገባው• የሰበር ችሎት መዝገብ ቁጥር 101013 የሰጠው ፍርድ የሚጠቅመኝ በመሆኑ በፍርድ ተጠቃሚ ሊሆንና የቅጣት ውሣኔው ሊሻሻልልኝ ይገባል በማለት አቤቱታውንና ክርክሩን አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በራሱ መንገድ ይግባኝና የሰበር አቤቱታ አቅርቦ እድሉን አሚጥጦ የጨረሰና የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በሰበር ማጣሪያ ችሎት ያፀናበት በመሆኑ• ይኸ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101013 በሰጠው ውሣኔ የሚጠቀምበት የህግ ሥርዓት የለም፡፡ ፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 የሰበር አቤቱታ ላላቀረቡ ተከሳሾች እንጅ በአመልካች ጉዳይ ላይ ተፈፅሚነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል ፡፡

9. መዝገቡ በዚህ ሰበር ችሎት የቀረበበት መሠረታዊና አከራካሪ የህግ ጭብጥ አመልካች በዚህ መዝገብ• ከአመልካች ጋር በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከሳሽ የነበረው ሰው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ያለፈበት ሂደትና የተሰጡ ትዕዛዝና ውሣኔ ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 196 ንዑስ አንቀፅ 1 በአመልካች ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ወይም የለውም? የሚለውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 የተሰጠው ፍርድ አመልካችን የሚጠቅመው ነው ወይስ አይደለም? የአመልካች ጉዳይ ለሰበር ችሎት ቢቀርብ ኖሮ በአመልካች ላይ የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ ሊሻሻልለት ይችል ነበር ወይስ አልነበረም? የሚሉትን ነጥቦች መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. አመልካችና በመዝገብ ቁጥር 101013 አመልካች የሆነው ሰው በወንጀል ህግ አንቀፅ 32/1/ሀ እና አንቀፅ 408 ንዑስ አንቀፅ 1 በመተላለፍ፣ በዋና ወንጀል ሠሪነት አንድ ላይ ከአንድ ሰው ከባድ ጉቦ የመቀበል ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኛ መሆናቸው እስከሰበር ችሎት ድረስ በተሰጠው ፍርድ ተረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለቱም ተከሳሾች ከዚህ በፊት ወንጀል ፈፅመው የማያውቁና የዘወትር ባህሪያቸው መልካም የነበረ መሆኑን አንድ የቅጣት ማቅለያ አድርጎ የያዘላቸው ሲሆን ይህንኑ ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተቀብሎታል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት

ሁለቱም ተከሳሾች በወንጀል በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በሁለቱም ተከሳሾች ለአንድ የቅጣት ማቅለያ አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ በእርከን ሃያ አምስት የተመለከተው ሁለቱም ስድስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 3000/ሶስት ሺ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ተከሳሾቹ በተናጠል ያስከፈቱትን የይግባኝ መዝገብ መርምሮ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

11. ይህም የሚያሳየው ከአመልካች ጋር በዋና ወንጀል ተካፋይነት ጥፋተኛ የተባለው በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው ሰው ለሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በአራት ዓመት ፅኑ እስራትና በሶስት ሺ ብር/3000 ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ የተወሰነው፣ ከአመልካች ያነሰ የወንጀል ተሣትፎ ስለነበረው አይደለም፡፡ በአጠቃላይ  ይግባኝ ሰሚው ችሎትና የሰበር አጣሪ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የወሰነውን የቅጣት ውሣኔ ያፀኑት በወንጀል ህግ አንቀፅ 41 በሚደነግገው መሠረት ቅጣቱን በአመልካች ላይ ለይቶ ለመወሰንና ለማፅናት የሚያስችሉ የግል ምክንያቶች ያሉ መሆናቸውን በማረጋገጥና ይህንንም በሰጡት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ በግልፅ በማስፈር እንዳልሆነ ተረድተናል፡፡

12. በአንፃሩ የአሁን አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ጉዳዩ ታይቶ የቅጣት ውሳኔው ከተሻሻለለትና በወንጀል ተካፋይነት አብሮት ጥፋተኛ ከተባለው ሰው፣ የተለየ ቅጣት እንዲፀናበት የተደረገው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 41 ወይም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 88 በተደነገጉና በግልፅ ተለይተው በሚታወቁ ምክንያቶች ሣይሆን፣ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ልጅና ሚስት ካልሆነ በስተቀር ወንድምና እህት እናትና አባት መርዳትና ማስተዳደር በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 የሚሸፈን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አይሆንም በማለት በሰጡት የተሣሣተ ትርጉምና ይኸ ሰበር ችሎት 101013 እህትና ወንድም አባትና እናት መርዳትና ማስተዳደር በወንጀል ህግ አንቀፅ 86 የሚሸፈን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ይሆናል በማለት በሰጠውና አመልካችን ተጠቃሚ በሚያደርገው ትርጉም ውሳኔ፣ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ባለመቅረቡ ተጠቃሚ ሣይሆን በመቅረቱና አመልካች እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት ሣይያዝለት በመቅረቱ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 ግንቦት 7 ቀን 2006 በቅጣት አወሳሰን ሂደት የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 2/2006 ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር፣ ቅጣት ለመወሰን፣ ተፈፃሚነት ያለው የወንጀል ድርጊት ሲፈፀም ስራ ላይ የነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው በማለት የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 22 እና የወንጀል ህግን አንቀፅ 5 መሰረት በማድረግና ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 ግንቦት 7 ቀን 2006 የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም የስር ፍርድ

ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባለመከተላቸውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመፈፀማቸው ምክንያት ነው፡፡

13. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ተይዞለት፣ ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች ያሉት መሆኑንና በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 7 መሰረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሶስት እርከን በድምሩ ስድስት እርከን ሲቀነስ በእርከን አሰራ ዘጠኝ ከተገለፁት የቅጣት ሬንጅ ውስጥ የሚወድቅ መሆኑና በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በተሰጠው ፍርድ የሚጠቀም መሆኑ የሚያከራክር ሆኖ አላገኘነውም፡፡

14. አመልካች በወንጀል ተካፋይነት አብሮት በተከሰሰውና ጥፋተኛ የተባለው ሰው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ፍርድ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል ከተረጋገጠ አመልካች በተናጠል በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ታይቶ ጥቅምት 7 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ውድቅ መደረጉ አመልካች የሰበር አቤቱታ ባያቀርብ ኖሮ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሊያገኝ የነበረውን ጥቅምና መብት የሚያስቀርበት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ፣ ጉዳዩ የወንጀል ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር በፌዴራል ደረጃ ከተዘረጋው የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማና ግብ መሠረት በማድረግ መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

16. ሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) የተዘረጋው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በሰበር አይቶ በማረም በአገር ውስጥ ሕጎች ወጥ በሆነ መንገድ እንዲተርጎምና ተፈፃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የህግ የበላይነትንና ፍትህን ማስፈን ነው፡፡ የሰበር ሥርዓት ከይግባኝ እና ሌሎች የፍርድ ላይ የሚፈፀሙ ስህተቶች ማረሚያ መንገዶች የተለያየና የራሱ የሆነ ባህሪ ያለው በመሆኑ ይህንኑ ባህሪውን ያገናዘበና ዓላማውን ለማሣካት የሚያስችል የሥነ ሥርዓት ሌሎች አሠራሮች ያስፈልጉታል፡፡

17. በአገራችን የሰበር ሥርዓቱ የሚመራበት ሰበር የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ የሥነ ሥርዓቱ ህግ የለም፡፡ የሰበር ችሎት እየሠራ የሚገኘው ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ በሚታዩበት ወቅት እንዲያገለግሉ ታስበው ከግማሽ ምዕተዓመት በፊት የወጡና ሌሎች የሥነ ሥርዓት ሕግ ማዕቀፎችን ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በሥራ ላይ ያሉትንና የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ባህሪና አላማ ግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባ ህግ አውጭው የወደዳቸውን የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከሰበር ሥርዓቱ መሠረታዊ ባህሪ ጋር

በማጣጣምና የሰበርን መሠረታዊ ዓላማ ለመስማት በሚያስችል መንገድ በመተርጎም በማጣጣም ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡

18. ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ክርክር ያስነሳው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ 196 ንዑስ አንቀፅ 1 ህግ አውጭው የደነገገውና በሥራ ላይ እንዲውል ያደረገው በአገራችን የሰበር ሥርዓት ባልዘረጋበት ጊዜና የይግባኝ ሥርዓቱ በፍርድ የሚፈጸም የፍሬ ጉዳይ ብቻ ሣይሆን መሠረታዊ የህግ ስህተት ማረሚያ ዋና ሥርዓት ተደርጎ በተዘረጋበት ወቅት መሆኑን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት የታወጀበትን ጥቅምት 23 ቀን 1954 ዓ.ም መመልከቱ ብቻ በቂ ነው፡፡በዚያን የታወጀው የወንጀለኛ  መቅጫ ስነ ስርዓት አንቀጽ 196 "የተፈረደባቸው ሰዎች ሆነው አንድ ብቻ ይግባኝ ሲያቀርብ" የሚል እርዕስ ያለው ሲሆን የደነገገው ንዑስ አንቀጽ 1 ቃል በቃል ሲነበብ "ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበው ይግባኝ ስለተፈረደባቸው ብዙ ሰዎች የሚመለከት ሆኖ ይግባኝ ያለው ግን የተፈረደበት አንድ ሰው ብቻ በሆነ ጊዜ ከዚህ በታች የተመለከተው ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚሰጠው ፍርድ ይግባኝ ላሉትም ሰዎች ይግባኝ እንዳለ ተቆጥሮ ይፈጸምላቸዋል ለማለት የሚችለው /ሀ/ በይግባኝ የተሰጠው ፍርድ ይግባኝ ባዩን የሚጠቅም በሆነ ጊዜና /ለ/ ተከሳሾች ይግባኝ ቢሉ ኖሮ በፍርድ እነርሱም ሊጠቀሙ ይችሉ ነበር የሚያሰኝ ሆኖ ሲገኝ ነው" የሚል ይሁንታ ያለው ነው፡፡

19. ይህንን ድንጋጌ አሁን ላለው የሰበር ስርዓት ለመጠቀም ካለው የሰበር ችሎት አደራጃጀትና አሰራር ጋር በሚጣጣምና የሰበርን መሰረታዊ ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መንገድ መተርጎምና ስራ ላይ ማዋል ይጠይቃል፡፡ የመጀመሪያው ብዙ ተከሳሾች አንድ ወንጀል የወንጀል ስራው ተካፋይና ግብረ አበር ሆነዋል ተብለው ክስ ቀርቦባቸውና፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ባየው ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ባዩው ፍርድ ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት  አንደኛው ተከሳሽ የሰበር አቤቱታ አቅርቦ፣ አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ በሰበር ችሎት ታይቶ፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በይግባኝ አይቶ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሳኔ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔው መሰረታዊ ህግ ስህተት አለበት ተብሎ ከተሻረ፣ ከተሻሻለ ወይም ከተለወጠና የሰበር ችሎት በመሻር፣ በማሻሻል ወይም በመለወጥ የሰጠው ውሳኔ የሰበር አቤቱታ ያላቀረቡትን ሌሎቹ በአንድ ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎችን የሚጠቅም ሆኖ በተገኘ ጊዜ፣ ሰዎቹ ፍርድን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ባያቀርቡም ሰበር ችሎት በሰጠው ውሳኔ ወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተጠቃሚ እንደሆኑ በሚያደርግ አግባብ ድንጋጌው መተርጎምና ስራ ላይ መዋል አለበት የሚለው ነው፡፡

20. ሁለተኛው በአንድ ወንጀል አድራጎት በወንጀል ህግ ስለወንጀል ተካፋይነት አድራጊነት ወይም ስለግብረአበርነት በተደነገጉት መሰረት በአንድ ላይ ፈጽመዋል ተብለው ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየውና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተወሰነባቸው ሰዎች ብዙ ሰዎች ሁሉም በግላቸው የሰበር አቤቱታ አቅርበው የሰበር መዝገብ አስከፍተው ከፊሎቹ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታና የስከፈቱት የሰበር መዝገብ በሰበር ችሎት የሚቀርብ መሠረታዊ የህግ ስህተት ጭብጥ የለውም ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 22 መሠረት በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ ቢደረግና ቢዘጋ የከፊሎቹ ወይም አንደኛው ተከሳሽ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰበር የሚጣራ መሠረታዊ የህግ ጭብጥ አለው ተብሎ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሰበር ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የጥፋተኝነት ውሣኔውን ወይም የቅጣት ውሳኔውን ወይም የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔውን መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር ችሎት ከሻረው ካሻሸለው ወይም ከለወጠውና ውሳኔው የሰበር አቤቱታ አቅርበው የሰበር ማጣሪያ ችሎት የሚጣራ መሠረታዊ የህግ ስህተት ጭብጥ የለውም ብሎ አቤቱታውን ውድቅ ያደረገባቸውን ሰዎች የሚጠቅም ሆኖ በተገኘ ጊዜ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል የሚለው ነው፡፤

21. ለዚህም ምክንያቱ ለይግባኝ ሥርዓት ታስቦ የተደነገገው የወንጀለኛ መቅጫ ሥርዓት ህግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 አሁን ያለውንና በአዋጅ ቁጥር 25/88 የተደነገገውንና የተዘጋውን የሰበር ችሎት አደረጃጀት ጋር በሚጣጣም መንገድ ሥራ ላይ ካልዋለና• አሁን በመዝገቡ ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚ የማይሆን ከሆነ አንድ የወንጀል ድርጊት በአንድ ላይ ፈፅማችኃል ተብለው ተከሰው ቢኖር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከተመሣሣይ የወንጀል ህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ ተብለውና በወንጀሉ የነበራቸው ተሣትፎ እና ሌሎች ግላዊ ሁኔታዎች ተመሣሣይ ሆኖ በመገኘቱ ተመሣሣይ የሆነ የቅጣት ውሣኔ የተላላፈባቸው ሰዎች፣ የአንደኛው የሰበር አቤቱታ የሚጣራ የህግ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት ስለቀረበና በውሣኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑ ተገልጾ በሚሰጠው ፍርድ ተጠቃሚ የሚሆንበት የሌላኛው የሰበር አቤቱታ የሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር የሚቀርብ የለውም ተብሎ ውድቅ ስለተደረገበት ብቻ የፍርዱ ተጠቃሚ የማይሆንበትን አግባብ መከተል በህገ መንግስቱ አንቀፅ 25 እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 4 የተደነገገውን የእኩልነት መርህ የሚጥስና የሰበርን መሠረታዊ ዓላማ የማያሳካ ይሆናል፡፡

22. ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ወንጀል በጋራ ፈፅማችኋል ተብለው የተከሰሱና ጥፋተኛ ተብለው ከተቀጡ ሰዎች መካከል፣ ሌሎቹ ሰዎች መብታቸውን ለሰበር ችሎት ለማቅረብ ዳኛ ሆነው

አንደኛው ተከሳሽ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሰበር ችሎት በሰጠው ፍርድ ሌሎቹ ተከሳሾች በሚጠቀሙበት አግባብ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1 ጥቅም ላይ የሚውሉና የሚፈፀም ከሆነ፣ በአንድ የወንጀል ድርጊት የተከሰሱ ሁሉም ሰዎች መብታቸውን ለሰበር ለማቅረብ ተገቢውን ትጋት አሳይተው ለሰበር ችሎት በማቅረባቸውና የከፊሎቹ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመደረጉና የከፊሎቹ ለሰበር የሚቀርብ ነጥብ የለም ተብሎ በመዘጋቱ•የሰበር ችሎት የሰጠው ፍርድ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ የተደረገባቸውን ሰዎች የሚጠቅም ሆኖ እያለ በፍርዱ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረግ፣ በአጠቃላይ የሰበር ሥርዓቱን መሠረታዊ አላማና ሕግ አውጭው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 196 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ሲያወጣ የፈለገውን ግብ፣ አሁን ካለው የሰበር አደረጃጀት ጋር በሚጣጣም መንገድ ሥራ ላይ እንዳይውል የሚደረግና ሰዎች ተግተው የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ምክንያት ብቻ የድንጋጌው ቱርፋት እንዳይደርሳቸው የሚያደርግ በመሆኑ፣ ይህንኑ ድንጋጌ ይህንኑ ሁኔታ በሚሰጥበት አግባብ መተርጐም ሥራ ላይ መዋል ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

23. አመልካች የሰበር አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ ባይደረግ ኖሮ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በሰጠው ፍርድ እና ከአመልካቹ ጋር ዋና ወንጀል አድራጊ ሆኖ በተከሰሰው ሰው፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪነቱ በልዩ ቅጣት ማቅለያነት እንዳይዝለት ይኸ ሰበር ችሎት በሰጠው የህግ ትርጉም ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2001 አንቀጽ 17 ፀዑስአንቀጽ 1መሠረት ለአንድ የቅጣት ማቅለያ ሶስት እርከን መቀነስ እንዳለበት ይጭ ሰበር ችሎት መሠረታዊ ዓላማ፣ ለማሳካት ፣ በህገ መንግስቱአንቀጽ 80 ፀጉስ አንቀጽ 3ን/ሀ/የተደነገገውን የሰበር ችሎት መሠረታዊ ዓላማ፣ ለማሳካት፣ በህገመንግስቱ አንቀጽ 25 እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 4 የተደነገገውን የእኩልነት መርህ ተግባራዊ ለድረግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 196ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ከስር አደረጃጀትና አሠራር ጋር በማጣጣም መተርጐምናአመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በተሰጠው ፍርድ ተጠቋሚ ማድረግ አስፈላጊ ነው በማለት ወስነናል፡፡

24. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 86 ልዩ የቅጣት ማቅለያ ሆኖ ሲያዝለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከያዙለት አንድ የቅጣት ማቅለያ ጋር ተደምሮ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ይኖረዋል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወሰኑት የቅጣት መነሻ ከሚገኝበት እርከን ሃያ ስድስት እያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 7 መሠረት ሶስት እርከን ሲቀነስ በአመልካች ላይ የሚወሰነው ቅጣት እርከን አስራዘጠኝ ላይ የሚወድቅ ይሆናል ፡፡ በመሆኑም በእርከን አስራዘጠኝ ከተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ ፈቃደ

ስልጣናችንን ተጠቅመን አመልካች በቀሩት ዓመት ፅኑ እስራት እና ብር 3000 /ሶስት ሺ ብር/ መቀጮ ይቀጣል በማለት ወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአመልካች ላይ የተሰጠውን የቅጣት ውሣኔ አሻሽለን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 123410 የሰጠው የቅጣት ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 93631 የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/196 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ማጣሪያ ችሎት ጥቅምት 10 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በዚህ ፍርድ ተለውጧል፡፡
3. አመልካች በዚህ ጉዳይ ተጠርጥሮ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ አራት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 3000 /ሶስት ሺ ብር/ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ወስነናል ፡፡
4. የቅጣት ውሣኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ሊክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ቡ/ግ**

የሰ/መ/ቁ. 110969

ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካች**፡- አቶ ሀብታሙ ደጀ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- የፌዴራል ዐቃቢ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

# ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሆኖ የዋስትና መብት አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረውም ተጠሪው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች እና በሌላ አንድ ግለሰብ ላይ ባቀረበው ክስ መነሻ ተከሳሾቹ ባቀረቡት የዋስትና መብት ጥያቄ ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-ክሱ የቀረበው ተከሳሾቹ በአዋጅ ቁጥር 761/2004 በአንቀጽ 9 (1) (ሀ) እና (ለ) ስር የተደረነገገውን በመተላለፍ የቴሌኮም የማጭበርበር ወንጀል አድርገዋል ተብለው ሲሆን የዋስትና መብታቸው እንዲከበር ተከሳሾቹ ባቀረቡት አቤቱታ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋስትና ጥያቄው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በክሱ የተጠቀሰው ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከ10 እስከ 20 ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት እና በወንጀሉ የተገኘውን ሕገወጥ ጥቅም አስር እጥፍ መቀጮ መሆኑን፣ተከሳሾቹ የተከሰሱበት ድንጋጌ የዋስትና መብትን የሚከለክል አለመሆኑን እና አመልካቹ የተሟላ አድራሻ ያላቸው እና በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ በመሆኑ በዋስትና ቢወጡ ግዴታቸውን አክብረው አይቀርቡም በማለት ተጠሪው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 67 (ሀ) ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ አመልካች ለብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ.ህ)፣2ኛ ተከሳሽ የነበሩት ግለሰብ ደግሞ ለብር 80,000 (ሰማንያ ሺ.ህ) ዋስትና አቅርበው በዋስ ሆነው እንዲከራከሩ በመዝገብ ቁጥር 153018 በ27/05/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ መስጠቱን፣በትዕዛዙ ቅር በመሰኘት ተጠሪው ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተከሳሾቹ ከሚጠብቃቸው ቅጣት ከባድነት አንጻር በዋስ

ቢወጡ ግዴታቸውን አክብረው አይቀርቡም የሚለው ግምት ሚዛን የሚደፋ ሆኖ ማግኘቱን ገልጾ የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ በመሻር ተከሳሾቹ ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከታተሉ በመዝገብ ቁጥር 109570 በ17/06/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሳኔ መስጠቱን፣አመልካች ይህንን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለአመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተፈቀደው የዋስትና መብት በተጠሪው ይግባኝ ባይነት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሻሩ ከወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 75 (1) አንጻር ሲታይ ዐቃቤ ሕግ ለምን ዋስትና ተፈቀደ በሚል ይግባኝ የማለት መብት ያለው መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የዋስትና መብት ቢኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስትም ሆነ በዝርዝር ሕጎች ከተረጋገጡት የተከሳሽ መሰረታዊ መብቶች መካከል አንዱ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም በማናቸውም ጊዜ እና ሁኔታ የሚረጋገጥ ሳይሆን ይልቁንም በሕግ በተመለከቱት ምክንያቶች ሊገደብ የሚችል ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካቹ የተከሰሱበት ወንጀል በመሰረቱ የዋስትና መብትን የሚፈቅድ ቢሆንም ተጠሪው የአመልካቹን የዋስትና መብት ጥያቄ የተቃወመው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 (ሀ) የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ሲሆን የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝን በመሻር አመልካቹ ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከታተሉ ውሳኔ የሰጠው ይህንኑ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

የዋስትና ጥያቄን ባለመቀበል በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የሚባልበትን ሁኔታ በተመለከተ በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የቀረበውን ማመልከቻ ፍርድ ቤቱ ያልተቀበለው እንደሆነ ተከሳሹ በቁጥር 182 (1) ለተመለከተው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሃያ ቀን ውስጥ ማመልከቻውን ሊያቀርብ የሚችል ስለመሆኑ በወንጀለኛ ሥነ ሥርዓት ሕጉ በቁጥር 75 (1) ስር ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ ወገን ዋስትናን በመፍቀድ በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ የስነ ስርዓት ሕጉ በተለየ ሁኔታ ያካተተው ድንጋጌ የለም፡፡ይህ መሆኑ ግን የስነ ስርዓት ሕጉን ቁጥር 75 (1) ድንጋጌ አነጋገር ዋስትናን በመፍቀድ በሚሰጥ ትዕዛዝ ላይ ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ እንዳያቀርብ ሕጉ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ከልክሏል በሚል አግባብ ለመተርጎም የሚያስችል

አይደለም፡፡የዚህ ዓይነቱ አተረጓጎም በስነ ስርዓት ሕጉ ከተመለከተው አጠቃላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት ጋርም የሚጣጣም አይደለም፡፡ይልቁንም የዋስትና መብት በተከለከለ ጊዜ ተከሳሽ ወገን ይግባኝ የማለት መብት ያለው ስለመሆኑ ሕግ አውጪው በቁጥር 75 (1) ለይቶ የደነገገው የዋስትና መብትን መሰረታዊነት ከግምት በማስገባት ለጉዳዩ አጽንኦት ለማስጠት በማሰብ እንደሆነ ከድንጋጌው ይዘት እና በስነ ስርዓት ሕጉ ከተመለከተው አጠቃላይ የይግባኝ መብት መርህ መገንዘብ ይቻላል፡፡በወንጀል ስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 75 (1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ዋስትናን በመፍቀድ በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ የከሳሽን ይግባኝ የማቅረብ መብት በተዘዋዋሪ መንገድ እንደሚከለክል ተደርጎ መተርጎም የሚገባው ስላለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በቀረበለት ተመሳሳይ ጉዳይ በመዝገብ ቁጥር 113436 የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም በዚህ መዝገብ በጭብጥነት ተይዞ ለቀረበው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 75 (2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በማረሚያ ቤት በኩል ይደረስ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

# ጉሃሩክ/ቷክስ

የሰ/መ/ቁጥር 95157

ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች ፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን -ዐ/ህግ ኃ/መለኮት አበበ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ ፡-** 1. አቶ ቅባቱ ወ/ሰንበት

2. አቶ ኤልያስ አሰፋ

3. አቶ አብርሃ ስዩም

-ጠበቃ ተሻገር ደሳለኝ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በገቢ ግብር አዋጅ አግባብ የሚቀርበውን የጥቆማ አበል ክፍያ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ.ም ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የተሻሻለ ክሣቸው ቢ.ጂ.አይ የተባለው ማህበር ለደንበኞቹ የሚሸጥላቸውን የድራፍት መጠጥ መጠን ለመንግስት አሣንሶ ስለሚገልጽ ደንበኞቹ ሊከፍሉ የሚገባቸውን ግብር እየሠወሩ እንደሚገኙ በጥቆማ መቀበያ ቅጽ ሴሪ ቁጥር 016294 ሕዳር 16 ቀን 2002 ዓ.ም ለአመልካች መስሪያ ቤት እንዳቀረቡለት ፣አመልካችም ጥቆማቸውን መሠረት በማድረግ የግብር ስወራው የሚከናወንባቸው ኮምፒውተሮች፣ ፍላሽ ዲስኮች፣ ዶክሜንቶች የተግባሩ ፈፃሚ ማንነትና እና የ3ኛ ወገኖች የሽያጭ ሁኔታ የሚያሣዩትን እቃዎች አመልካቹ ባደረገው ምርመራ ፍሬ ግብር ወለድና መቀጮን ጨምሮ በጠቅላላ ብር 72,467,971.65 /ሰባ ሁለት ሚሊዮን አራት መቶ ስልሣ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አንድ ብር ከስልሣ አምስት ሣንቲም/ መጠን ያለው ገንዘብ እንዲሠወር ያደረገ መሆኑን ያረጋገጠ

ሲሆን ማህበሩም የወንጀሉ ክስ አመልካቹ እንዲተውለት በማስደረግ ገንዘቡን ግን እንዲከፍል የተደረገ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 እና ሃምሌ 1996 ዓ.ም በወጣው መመሪያ ቁጥር 3.3 መሠረት አመልካቹ ካገኘው ፍሬ ግብር 29,433,465.71 /ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሣ ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሣ አምስት ብር ከሰባ አንድ ሣንቲም/ 20% የጠቋሚ አበል /ሽልማት/ ብር 5,886,693.14 /አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሶስት ብር ከአስራ አራት ሣንቲም/ የሚገባን በመሆኑ እና ከዚሁ ውስጥም አመልካቹ ብር 1,471,672.84 /አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰባ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሠማኒያ አራት ሣንቲም/ የከፈለን ሲሆን ቀሪው ብር 4,415,020.30 /አራት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ አምስት ሺህ ሃያ ብር ከሰላሣ ሣንቲም/ አመልካቹ ይክፈለን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለተጠሪዎች ክስ ሃምሌ 08 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን የሰጠ ሲሆን ዝርዝር ይዘቱም፡-ተጠሪዎቹ ክሣቸውን ከማሻሻላቸው በፊት ያቀረቡት ክስ ቢ.ጂ.አይ ማህበር ግብር ሠውሯል የሚል ቢሆንም ይህ አባባላቸው በመረጃ ያልተደገፈ መሆኑን፣ የ3ኛ ወገኖች ግዢ ማስተላለፊያ ሠነድ የተገኘው በኦዲተሮች እንጂ በተጠሪዎች /ጠቋሚዎቹ/ እንዳልሆነ፣ የተጠሪዎች ጥቆማው ሕጉን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ሽልማቱ እንደማይገባቸው፣ተጠሪዎች በጥቆማቸው ቢ.ጂ.አይ የግብር ስወራ እንደሚያደርግ እንጂ 3ኛ ወገንኖቹ ግብር እንደሚያጭበረብሩ ጥቆማ ያላቀረቡ መሆኑን ዘርዝሮ ተጠሪዎች ሽልማቱ እንማይገባቸው በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ እንዲሁም የተከሳሽ ከሳሽነት ሐምሌ 19/2003 ዓ.ም አሻሽሎ አቅርቧል፡፡ በዚህ ክሱም፡- ተጠሪዎች በስህተት የተሠጣቸውን ገንዘብ ብር 1,471,672.84 እንዲመልሱለት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪዎች በአመልካች በቀረበባቸው ክስ ግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልሣቸው አመልካቹ ተጠሪዎች የሰጡትን ጥቆማ መሠረት በማድረግ የተጭበረበረና የተሰወረ ግብር የሠበሠበ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ክሱን እና የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን በመስማት ተጠሪዎች በሰጡት ጥቆማ መነሻነት ብር 72,467,971.65 ፍሬ ግብር ወለድና መቀጮ መሠብሠቡን አመልካች የሚክደው ባለመሆኑና ከዚህ ውስጥም ብር 29,433,456.71 ፍሬ ግብር ሲሆን አመልካቹ ለተጠሪዎቹ ብር 1,471,672..84 የከፈለ በመሆኑ ይህም አመልካች በተጠሪዎቹ ጥቆማ እምነት ያሣደረ መሆኑን እንደሚያሳይ፣ አመልካቹ በጠቋሚዎቹ መረጃ መሠረት ከሚሠበሠበው ግብር 20% ለጠቋሚቹ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ሕግ የሚያስገድደው መሆኑን በምክንያትነት ይዞ አመልካቹ ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ባለመቀበል ቀሪውን የጥቆማ

አበል ገንዘብ ብር 4,415,020.30 ለዳኝነት ከከፈሉት ከ5% የጠበቃ አበልና ሌሎች ወጪና ኪሣራ በቁርጥ ብር 5000.00 ጋር አመልካቹ ለተጠሪዎች ሊከፍላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በጉዳዩ ላይ በስር ፍርድ ቤት የተሠጠው ውሳኔ የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን የክስ እናሻሽል ጥያቄ የተቀበለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 91 ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማ ውጪ መሆኑን፣የተጠሪዎች ክስ በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን፣ግብሩ የተሰበሰበው በተጠሪዎች ጥቆማ መነሻ ሳይሆን በአመልካች መስሪያ ቤት ባለሙያዎች ጥረት መሆኑን፣ተጠሪዎች የሠጡት ጥቆማ በሕጉ አግባብ  የጠቋሚ አበል የማያሰጥ መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን በሰፊው ዘርዝሮ የተጠሪዎች የጠቋሚ ገንዘብ ይከፈለን ጥያቄ ውድቅ መሆን እና ያላግባብ የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ መወሰን ሲገባ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ከ5% የጠበቃ አበልና ከሌሎች ወጪዎች ጋር እንዲከፈላቸው መወሰኑ በሕግና በማስረጃ አግባብ ባለመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ይገባዋል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዙትን ነጥቦች ተመልክተናል፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ተለይተው ከተያዙት ጭብጦች አንዱ የተጠሪዎች የክስ ማሻሻል ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 91 ድንጋጌ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ በመሰረቱ ፍርድ ቤት አንድ ተከራካሪ ያቀረበውን ክስ እንዲያሻሽል ትዕዛዝ የሚሰጥባቸው ምክንያቶች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 91 ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከሣሽ ያቀረበውን ክስ እንዲያሻሽል ትዕዛዝ የሚሰጠው ከሣሽ ያቀረበው ክስ ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር አንቀጽ 91 ንኡስ አንቀጽ 1 ስር ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ/ም ያቀረቡትን ክስ አብራርተው ለማቅረብ ይፈቀድላቸው ዘንድ ፍርድ

ቤቱን ጠይቀው ፍርድ ቤቱም የተጠሪዎችን ጥያቄ በመቀበል ተጠሪዎች ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ክሳቸውን አሻሽለዋል፡፡ ተጠሪዎች አስቀድመው ባቀረቡት ክስ ቢ.ጂ.አይ ግብር እንዲሰወር ያደርጋል በማለት የገለፁትን የክሱን ፍሬ ነገር በተሻሻለው ክስ ደግሞ ይኼው ቢ.ጂ.አይ የተባለው የአክሲዮን ማህበር የቢራና ድራፍት ምርቶችን በሚሸጥበት ወቅት የሽያጭ ዝርዝሩን ለአዲስ አበባ ፋይናንስ ቢሮ ሲያስተላልፍ እውነተኛውን የሽያጭ መጠን ሳይሆን አሳንሶ ስለሚያቀርብ መንግስት ማግኘት ያለበትን ግብር እንዳይሰበስብ ሆኗል የሚለውን የክሱን ፍሬ ነገር በማካተት ክርክራቸውን ማቅረባቸውን የክርክሩ ሒደት ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ ክሱ እንዲሻሻል ተደርጎና በአመልካች በኩል ደግሞ ተገቢ ነው የተባለው ተቃውሞ ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ያለውን ብይን በመስጠት ታህሳስ 27 ቀን 2004 ዓ/ም ክሱ ሲሰማም ሆነ  ሰኔ 29 ቀን 2004 ዓ/ም ምስክሮች ሲሰሙ በተጠሪዎች የተሻሻለ ክስ የተጠቀሰው ፍሬ ነገር መሰረት ተደርጎ ክርክሩ መመራቱንና በማስረጃዎቹ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር መሰረት ተደርጎ ዳኝነት መሰጠቱን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ ጥቆማ አድርገናል በማለት ሊከፈላቸው የሚገባውን የጠቋሚ ገንዘብ ተገቢውን የክስ ምክንያትና የክሱ ፍሬ ነገር በክሳቸው ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ እንዲያቀርቡ ሊፈቀድ እንደሚችልና የክሱ መሻሻል መሰረታዊ አላማም ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ ሁኖ መገኘት  ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 91 ስር የተመለከተ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከርበትና በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገው ነጥብ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ተጠሪዎች የጥቆማ አበል እንዲከፈላቸው የሚያስችሉ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ባላቀረቡት ክስ አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪዎቹ  የግብር መሠወር ተግባር ፈጽሟል በማለት ጥቆማ ያቀረቡት በቢ.ጂ.አይ ላይ እንጂ በ3ኛ ወገኖች ላይ ባለመሆኑ የጥቆማ ፎርሙ ይዘትና የተጠሪዎች ጥቆማ አይስማማም፣ የተሠወረው ገንዘብ የተገኘው በኦዲተሮቹ ጥረት ነው በማለት ቢከራከርም የአመልካች የ"ኢንተለጀንስ" ባልደረቦች የሆኑት እነ ቁምላቸው ሻምበል ስሜነህ ለሥር ፍ/ቤቱ ቀርበው በሰጡት ምስክርነት ተጠሪዎቹ በወቅቱ ያቀረቡት ጥቆማ ቢ.ጂ.አይ ለደንበኞቹ የሚያቀርብላቸውን የመጠጥ መጠን በመቀነስ ለአመልካቹ ሪፖርት ስለሚያደግ የግብር ስወራ እንደተደረገ የሚገልጽ ነው፣ የመጠቆሚያው ፎርም የጥቆማው ይዘት መዘርዘሪያ በጣም አጭር በመሆኑ በአጭሩ በመፃፉ የተጠሪዎቹ ዝርዝር የጥቆማ ይዘት ለማስፈር እንደሚያስቸግር፣ በተጠሪዎች ጥቆማ መሠረት ኦፕሬሽን መካሄዱን በግልጽ እንደሚያሳይ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ስልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንኑ የፍሬ ነገር

ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ ተቀብሎታል፡፡ ይህ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ድምዳሜ የሚያስገነዝበውም ተጠሪዎች የሰጡት ጥቆማ በእርግጥም ለምርመራው መነሻ ሁኖ መንግስት ሊሰበስበው የሚገባውን ግብር ለመሰብሰብ ያስቻለ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተጭበረበረው ገንዘብ የተገኘው በኦዲተሮች ጥረት ነው በማለት አመልካቹ ያቀረበው ክርክር የተጠሪዎች ጥቆማ ለኦዲት ምርመራ መነሻነቱ ያልተካደ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡አመልካቹ የተጭበረበረ ግብሩን የሠበሠበው ተጠሪዎቹ ባቀረቡት ጥቆማ መሠረት መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ይህን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ደግሞ ይህ ችሎት የማይቀበልበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ዲፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡የሥር ፍ/ቤቱ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች የጠየቁት ቀሪ የጠቋሚ ገንዘብ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ተገቢነት ያለውና የሕጉንም አላማ የሚያበረታታ ሲል ይግባኝ ሰሚ ችሎት መደምደሙም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ከሕጉ ጋር ያገናዘበ ነው፡፡

ወደ ህጉ ስንመጣም በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 84(1) እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ገቢውን በሚደብቅ፣አሳንሶ በሚያስታውቅ፣በሚያጨበርብር ወይም በማናቸውም መንገድ ግብር ሳይከፍል በሚቀር ግብር ከፋይ ላይ በተጨባጭ መረጃ በመደገፍ ሪፖርት የቀረበ እንደሆነ የተደበቀው ግብር እስከ 20% ድረስ ግብሩ ሲሰበሰብ ሲጠቃለልም በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ላይ ዳኝነት የሠጡት የግራ ቀኙን ክርክር በሕጉ አግባብ በመምራትና ፍሬ ነገሩን በሚገባ በማጣራት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን እንደሚከፈል ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 96 ድንጋጌ ሲታይ ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ግብር ያላሣወቀ ወይም የሚፈለግበትን ግብር ያልከፈለ ወይም መንግስትን ለማጭበርበር በማሠብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ማናቸውም ሰው ወንጀል እንደፈፀመ እንደሚቆጠርና የወንጀል ተጠያቂነትንም እንደሚያስከትል ከአዋጁ አንቀፅ 49 ጋር ተዳምሮ ሲነበብ ያስገነዝባል፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይም የተጠሪዎች ጥቆማ ቢ.ጂ.አይ የተባለው አክሲዮን ማህበር በ3ኛ ወገኖች ሊከፈል ይገባ የነበረውን ግብር እንዳይከፈል የሚያደርግ ተግባር መፈጸሙና በተለይም ራሱ አክሲዩን ማህበሩ የወንጀል ክስ እንዲቀርለት ተደርጎ ሳይከፈል ቀርቷል የተባለውን ግብር መክፈሉ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርበውን ክርክር ለመቀበል የሚያስችል የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶቹ ፍሬ ነገሩን አጣርተው ማስረጃውን መዝነው የደረሱበት ድምዳሜ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 84 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን የህጉን ይዘት፣መንፈስና መሰረታዊ አላማ ያገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 99932 የካቲት 08/2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 88152 መስከረም 28 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች ብር 4,415,020.30 /አራት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ አምስት ሺህ ሃያ ብር ከሰላሣ ሣንቲም/ ከ5% የጠበቃ አበል ጋር ይክፈል፣ተጠሪዎች ብር 1,471,672..84 ለአመልካች ሊመልሱ አይገባም ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

## ትእዛዝ

- ታህሳስ 14 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ይ**

የሰ/መ/ቁ/ 112032

ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች**:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጦታ

**አመልካች**:- 1ኛ የኑስ አህመድ } የቀረበ የለም

2ኛ. ግዛቸው አየለ

**ተጠሪ** ፡- የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓቃቤ ህግ ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ዓ/ህግ ኤርሚያስ ታደሰ - ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በቤንሻንጉል ጉምዝ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት ነው፡፡ አመልካቾች ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የስር ፍ/ቤቶች ያስተላለፉት የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ መሰረታዊ ይዘቱ፡- አመልካቾች ህጋዊ ፈቃድ ከሌለ በስተቀር በግለሰብ መያዝም ሆነ ማዘዋወር የተከለከለ በቁጥር 903 /ዘጠኝ መቶ ሶስት / ህገ ወጥ የከሳሽ ጥፋት በሁለት ማዳበሪያዎች ቋጥረው በጉዞ ሻንጣ ውስጥ በመክተት ንብረትነቷ የ2ኛ አመልካች የሆነችው የታርጋ ቁጥር ኮድ 2-0705 ቤጉ በሆነች የሞተር ሳይክል በመጫን ከአል መሃል አቅጣጫ ወደ መንጉሻ አቅጣጫ በማጓጓዝ ላይ ሳሉ በቀን 03/11/2006 ዓ/ም ከቀኑ በ11፡30 አካባቢ ማንኩሻ ላይ እጅ ከፍንጅ በመያዛቸው 1ኛ ተከሳሽ /አመልካች/ የህገ ወጥ ዕቃ ባለቤት 2ኛ አመልካች የሞተር ሳይክሉ አሽከርካሪ በመሆን በፈጸሙት ህገ ወጥ ዕቃ መሆኑን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት

የኮንትሮባንድ ወንጀል የወ/ህ/ቁ/32/1/ሀ/ እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ የተመለከተውን ወንጀል ተላልፏል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ፍርድ ቤት ቀርበው የተጠሪ ክስ እንዲደርሳቸው ተደርጎ ስለጉዳዩ እምነት ክህደት ተጠይቀው 1ኛ አመልካች እንደ ተጠሪ /ዓቃቤ ህግ/ ክስ አቀራረብ ማመኑ በማስመዝገብ ጥፋተኛ ነኝ ያለ ሲሆን 2ኛ አመልካች መካዱ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው ተሰምቷል፡፡ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው በሰጡት የምስክርነት ቃል የ1ኛ አመልካች መሆኑን የተረጋገጠው 903 ጥይት በ2ኛ አመልካችም ሞተር ሳይክል ተጭኖ ሲመጣ ኬላ ላይ መያዙን አስረድቷል፡፡ 2ኛ አመልካች እንዲከላከል ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም የመከላኪያ ማስረጃ እንደ ሌለው በመግለጽ ፍ/ቤቱ በቀረበው ማስረጃ እንዲሁም 1ኛ አመልካች ቀድሞ በሰጠው የእምነት ቃል መሰረት በማድረግ ሁለቱም አመልካቾች በተከሰሱበት የህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት መዝግበዋል፡፡ በተጠሪ /የዐቃቤ ህግ/ በኩል የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ ሆኖ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በእርከን 28 ስር ቅጣት እንዲወሰን፤ መቀጮም እንዲወሰን፤ ንብረቱ እንዲወርስ ጠይቋል፡፡ አመልካቾቹም የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች መሆናቸው ግምት ውስጥ እንዲገባ አመልክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የወንጀል ድርጊቱ በሀገሪቱና በህዝብ ደህንነት ላይ አደጋ የሚጥል ስለመሆኑ ድርጊቱም ሆን ተብሎ የተፈጸመ በመሆኑ በከባድ ደረጃ መድቦታል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ ሆን ተብሎ መፈጸሙ፤ አመልካቾች ድርጊቱን በስምምነት መፈጸማቸው ሁለት ማክበጃ ምክንያት እንደሆነ፤ በአመልካቾች በኩል 1ኛ የዘወትር ጸባያቸው መልካም መሆን፤ 2ኛ ድርጊቱ የፈጸሙት ከህግ እውቀት ማነስ መሆኑ 1ኛ አመልካች የወንጀል ድርጊቱ ማመኑ 3ኛ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን በቅጣት ማቅለያነት ተይዞላቸዋል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተሰኙበት ወንጀል ከ7 ዓመት እስከ 15 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና የወንጀል ድርጊቱም በከባድ ደረጃ በመመደቡ የቅጣቱ መነሻ እና መድረሻ ለአራት እኩል ሲከፈል ከ11 ዓመት -13 ዓመት ጽኑ እስራት ባለው ፍቅድ ስልጣን በማካተት የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 29 እንደሆነ በመለየት ሁለት ማክበጃዎች በመውሰድ እርከን 31 የወደቀ ሲሆን በአመልካቾች በኩል እያንዳንዳቸው  ሶስት ሶስት ማቅለያዎች የተያዘላቸው በመሆኑ በእርከን 28 ከተደነገገው ቅጣት 1ኛ አመልካች 10 ዓመት 2ኛ አመልካች 9 ዓመት ጽኑ እስራት፤ እንዲሁም በመቀጮ ረገድ የወ/ህ/ቁ/ 90/2/ መሰረት በማድረግ እያንዳንዳቸው 6670 ብር እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በኢግዚቢትነት የተያዘው ጥይት እንዲሁም የወንጀል መፈጸሚያ የተባለው ሞተር ሳይክል ለመንግስት ውርስ ይሁን በማለት አዟል፡፡

አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ በሰበር እንዲመረመር በመቅረቡ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ አመልካቾች የስር ፍ/ቤት ወንጀሉ በከባድ ደረጃ መመደቡ እና የቅጣት ማቅለያዎች አያያዝ ላይ የፈጸመው ስህተት እንዲታረምላቸው ሲጠይቁ፤ ተጠሪ በበኩሉ የስር ፍርድ ቤት የወንጀል ድርጊት አፈፃጸም መሰረት በማድረግ በከባድ ደረጃ መድቦ ቅጣት መወሰኑ በአግባቡ ነው የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ጭብጦች 1ኛ አመልካቾች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ነው ወይስ በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168/2/ 2ኛ የስር ፍርድ ቤቶች የወንጀል ድርጊቱ ከባድ በማለት መመደባቸው በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? 3ኛ በስር ፍርድ ቤት እንደ ቅጣት ማክበጃ የተወሰዱ ነጥቦች የህግ መሰረት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚሉ ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

ከስር የክርክር ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካቾች 1ኛ አመልካች ገደብ የተደረገበት /ህገ ወጥ/ ጥይት ባለቤት፤ 2ኛ አመልካች ንብረቱ የጫነችው ሞተር ሳይክል ባለቤትና ሹፌር በመሆን በ03/11/2006 ዓ/ም ከቀኑ 11:30 ሰዓት በመንኩሻ ከተማ መግቢያ እጅ ከፍንጅ እንደተያዙ፤ 1ኛ አመልካች ሙሉ በሙሉ ማመኑ፤ 2ኛ አመልካችም የዐ/ህግ ክስና ማስረጃ አለማስተባበሉን የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣኑ ከድምዳሜ ላይ የደረሰ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንደተቀበለው ነው፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የስር ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃ ምዘና ስርዓት እንዳለ የሚቀበለው ነው፡፡ ምክንያቱም ችሎቱ በህግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ማረም ስለመሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ይዘን ከላይ የተመለከቱት ጭብጦች ከህግ አንጻር እንደሚከተለው መርምረናል

**<u>የመጀመሪያው ጭብጥ በተመለከተ:-</u>** አመልካቾች ጥፋተኛ የተሰኙት የኮንትሮባንድ ወንጀል በመፈጸም ነው፡፡ ይህ ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 622/ 2001 አንቀጽ 91/2/ ስር የተመለከተ ሲሆን የሚያስቀጣው በእቃዎቹ ላይ ሊከፍል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር የሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከ7 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም ይህንን

መሰረት በማድረግ 1ኛ አመልካች በ10 አመት 2ኛ አመልካች በ9 አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 ተሽሮ በአዋጅ ቁጥር 859/2007 ተተክቷል፡፡ የአመልካቾች የክስ ሂደት እስከ ሰበር ደረጃ ደርሶ ሳይጠናቀቅ አዲስ አዋጅ የወጣ ሲሆን በዚህ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168/2/ መሰረት የኮንትሮ ባንድ ወንጀል የፈጸመው ግለሰብ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና በብር 50 ሺህ በማያንስና ከብር 100,000 የማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል፡፡ በተሻረው እና በአዲሱ አዋጅ በአመልካቾች ላይ በሚጣለው እስራት እና መቀጮ መሰረታዊ ልዩነት እንዳለው ከድንጋጌዎቹ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ወንጀሉ ሲፈጸም ስራ ላይ ከነበረው ህግ ይልቅ የኋላኛው /አዲሱ/ ህግ ቅጣት የሚያቃልለት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ /አመልካቾች/ የተሻለው ህግ ተፈፃሚ እንደሚያደርግ ከወ/ህ/ቁ/ 6 እና ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 /2/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የተቀጡት በነባሩ /የቀደም/ አዋጅ ከመሆኑ አንፃር በቅጣት ረገድ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው አዋጅ ቁጥር 859/2007 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168/2/ ስር ነው ብለናል፡፡

<u>ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> የስር ፍ/ቤት የግራቀኙ የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ የወንጀል ድርጊቱ ክብደትና አፈፃጸም መሰረት በማድረግ ቀላል /ዝቅተኛ/ ተብሎ እንዲመደብ ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ዓቃቤ ህግ እንዳለው በመካከለኛ ደረጃ ሊመደብ እንደሚገባ ተከራክሯል፡፡ በመሰረቱ ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎች የወንጀል ደረጃ እና የቅጣት መነሻ እርከን በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 19 ስር በተመለከቱት መስፈርቶች መሰረት እንዲሁም ፍ/ቤቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19/5/ የተመለከቱት መመዘኛዎች ብቻ ሳይታጠር ሌሎች መስፈርቶች ተጠቅሞ የወንጀሉ ደረጃ እንደሚመደብ በአንቀጽ 19/6/ ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የወንጀሉ አይነትና ክብደት አፈፃጸም፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ መዝኖ ከባድ ነው ማለቱ የሚነቅፍ ሆኖ አልተገኘም ፡፡ አመልካቾች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

<u>3ኛ ጭብጥ በተመለከተ</u> ፡- የስር ፍርድ ቤት ቅጣት ሲወሰን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ከግራ ቀኙ የመዘገበ ሲሆን ዐ/ህግ የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ እንዲሆን ከመጠየቅ ውጭ ፍ/ቤቱ እንደ ማክበጃ የወሰዳቸው 1ኛ የወንጀል ድርጊቱ ሆነ ተብሎ መፈጸሙ፤ 2ኛ የወንጀል ድርጊቱ በህብረት ስምምነት የተፈጸመ ነው በማለት የወንጀል ህግ አንቀጽ 84/1/ሀ/ እና /መ/ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካቾች ጥፋተኞች የተሰኙበት አዋጅ ቁጥር 168/2/ ስር እንደተመለከተው ድርጊቱ የተፈጸመው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው በማለት የተደነገገ ሲሆን የስር ፍ/ቤት የወንጀል ህግ አንቀጽ 84/1/ሀ/ በመጥቀስ እንደማክበጃ መውሰዱ የድንጋጌው መሰረታዊ ይዘት ያላገናዘበ

መሆኑን ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት የወንጀል ድርጊቱ በስምምነት የተፈጸመ ነው በሚል እንደ ማክበጃ የወሰደው ቢሆንም በወንጀል ህግ አንቀጽ 37 /1/ እና 84/1/መ/ እንደተመለከተው ወንጀል ለመስራት አስቀድመው በመስማማት /Prior meeting of mind/ የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈጸማቸው የሚያሳይ ሳይሆን 1ኛ አመልካች የህገ ወጥ ዕቃ ባለሌት 2ኛ አመልካች ደግሞ የሞተር ሳይክል ባለቤት በመሆን የኮንትሮባንድ ዕቃው መጫኑን ከመረጋገጡ ውጭ ወንጀሉን ከመጀመሪያው አቅደው ፤ጊዜ እና ሁኔታ አመቻችተው ስለመፈጸማቸው በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ እንደ ህጉ አነጋገር ቅጣት የሚያከብዱ ሁኔታዎች ሳይኖሩ ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መውሰዱ የህግ መሰረት የለውም ብለናል፡፡

በመጨረሻ መታየት ያለበት ጉዳይ ቅጣት ነው፡፡ በተጠሪ በኩል በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለው የቅጣት ማክበጃ አልቀረበም፡፡ በአመልካቾች በኩል ሶስት ሶስት የቅጣት ማቅለያዎች ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተሰኙበት አዋጅ ቁጥር 859/2007/ አንቀጽ 168/2/ 3-5 ዓመት ጽኑ እስራት በገንዘብ ረገድ ደግሞ ከ50,000-100,000 ብር የሚያስቀጣ ነው፡፡ የወንጀሉ ደረጃ ከባድ የተባለ በመሆኑ የቅጣት መነሻና መድረሻ ለአራት እኩል ሲከፈል የከባድ ወንጀል ከ4 ዓመት እስከ 4 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 26/2/ሐ/ መሰረት መነሻ ቅጣት በሁለት እርከኖች ስር የሚወድቅ ከሆነ ዝቅ ብሎ ያለው የሚያዝ በመሆኑ በአንቀጽ 19/1/ በመመልከቱ በእርከን 18 ስር ይወድቃል፡፡ ፍ/ቤቱ በተሰጠው ፍቃድ ስልጣን መነሻ ቅጣቱ 4 ዓመት ጽኑ እስራት በመያዝ የቅጣት ማቅለያዎች ተመልክተናል፡፡ በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅሊያ አንድ እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ ቅጣቱ በሶስት እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ በእርከን 15 ይካተታል፡፡ መቀጮ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የወ/ህ/ቁ/90/2/ መሰረት በማድረግ እያንዳንዳቸው  ብር 6670 እንዲቀጡ ወስነናል፡፡ ይህ ችሎትም አዲሱ አዋጅ በዚህ ረገድ አመልካቾች የማይጠቀም በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የወሰነው መቀጮ እንዳለ ተቀብሎታል፡፡

ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ህጉ ዓላማ ግብ የሚያሳካ መሆን እንዳለበት በወንጀል ህግ አንቀጽ 1 እና 87 በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካቾች የተፈጸመው ወንጀል ክብደት በህ/ሰብ/ ሊያደርስ የሚችለው አደጋ በአንድ በኩል፤ የአመልካቾች የመታረም ዕድል በሌላ በኩል ግምት ውስጥ በማስገባት አመልካቾች የሚያረምና የሚያስተምር እንዲሁም መሰል ወንጀል ፈፃሚዎች የሚያስጠነቅቅ ነው ብለን ያመንበት በእርከን 15 በተመለከተው ፍቃድ ስልጣን ስር በመሆን እያንዳንዳቸው 2 አመት ከ9 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ በመለየት እና ሁለቱ ፍርድ ቤት የቅጣት ማክበጃዎች አወሳሰድ ላይ የፈጸሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የስር መተከል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 10407 በ28/11/2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድና ቅጣት፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/05758 በ06/05/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 195/2/ለ/2/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው በአዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168 /2/ ስር ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካቾች በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ካለ በእስራት ቅጣቱ የሚካተት ሆኖ እጃቸው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ እያንዳንዳቸው በ2 አመት ከ9 ወር /ሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር/ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡ አመልካቾች የሚገኙበት ማረሚያ ቤት በተሻሻለው የእስራት ቅጣት መሰረት ያስፈጽሙ ብለናል፡፡ የእስራት ቅጣቱ መሻሻሉ አመልካቾች ባሉበት ማረሚያ ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
4. በስር ፍ/ቤት የተወሰነው መቀጮ እና የንብረት ውርስ የተመለከተ የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ተ**

# የዳኝነት ሥልጣን

የሰ/መ/ቁ 97083

ሚያዝያ 14 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ገኣትኮ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-**የትግራይ ክልል መንገድ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ -አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 60677 ታህሳስ 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. አመልካች/ከሳሽ/ ተከሳሽ /ተጠሪ/ በሚካሄደው ጨረታ ለአንድ ዓመት እንዳልሣተፍ ከህግ ውጭ ዕገዳ ጥሎብኛል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ በፍርድ ተጣርቶ እገዳው እንዲነሳ ይወሰንልኝ በማለት ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ድርጅት በመሆኑ ጉዳዩ ሊቀርብ የሚገባው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተደራቢ የዳኝነት ሥልጣን ላለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው የሚል መቃወሚያና ሌሎች መከረከሪያዎችን አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪን መቃወሚያ በማለፍ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስራጃ ከመዘነ በኃላ ተጠሪ በሚያካሄደው ጨረታ አመልካች ለአንድ ለአመት ያህል እንዳይሳተፍ የሠጠው ዕገዳ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ይነሳ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት የተጠሪን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡
2. ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ አመልካች በፌዴራል

መንግስት ተመዝግቦ የተቋቋመ የንግድ ድርጅት ነው፡፡ በፌዴራል መንግስት ተመዝግቦ የተቋቋመ የንግድ ድርጅት ተካፋይ የሆነበትን ክርክር በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ነው፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጉዳይ በዳኝነት አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው ተደረቢ ወይም በውክልና የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን የለውም፡፡ በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

3. አመልካች ጥር 21 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አመልካች ቅርንጫፍ ከፍቶ በሚነግድበት ቦታ እንዲመዘገብ የሚያስገድድ በመሆኑ አመልካች ቅርንጫፍ በከፈትኩበት መቀሌ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በመዝገብ ቁጥር 0041/2003 ተመዝግቤ የንግድ ምዝገባ ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠኝ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች በፌዴራል የተቋቋመ የንግድ ድርጅት ነው የሚለውን ብቻ በመመልከት የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዳኝነት የማየት ሥልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በመቀሌ ቅርንጫፍ ከፍቶ የሚነግድ መሆኑ መመዝገቡ የክልል የንግድ ተቋም አያደርገውም፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው መልስ መጋቢት 8 ቀን 2006 ዓ/ም በፅሁፍ አቅርቧል:: አመልካች ሚያዚያ 3 ቀን 2006 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ የቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ በሰበር አጣሪ ችሎት አመልካች የቀረበውን ክስ የወረዳው ፍርድ ቤት በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የመመሥረቻ ፅሑፍ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች በንግድ ሕጉና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የሕግ ማዕቀፎች የተደነገጉትን መስፈርቶች አሟልቶ ለፌዴራል መንግስት በማቅረብ፣ በፌዴራል መንግስት ህጋዊ ዕውቅና ተሰጥቶት የተመዘገበ የንግድ ድርጅት መሆኑን በመካድ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች የመመሥረቻ ፅሑፉን መተዳደሪያ ደንቡንና ሌሎች ህጋዊ ሕልውና ለማግኘት አስፈላጊ የሆነ ፎርማሊቲዎች በማሟላት፣ በፌዴራል መንግስት ህጋዊ ህልውና ያለው የንግድ ድርጅት መሆኑ አከራካሪ ካልሆነ፣ አመልካች በመቀሌ ከተማ ቅርንጫፍ በመክፈቱ በአዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት በንግድ መዝገብ መመዝገቡ የአመልካችን የክልል የንግድ ድርጅት ወይም የክልልና የፌዴራል ህጋዊ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት የሚያደርገው አይደለም፡፡

6. ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ የሚመዘገበው ዋና መሥሪያ ቤቱ ባለበት ሥፍራ መሆኑንና ማንኛውም ሰው በተለያዩ ክልሎች የተለያየ ንግድ ሥራ በሰራም በንግድ መዝገብ የሚመዘግብ የሚመዘገበው አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 686 /2002 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡ በአዋጅ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 የተለያያ ቅርንጫፍ ያለው የንግድ ድርጅት ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቱ በሚገኝበት ስፍራ ላለው መዝጋቢ መሥሪያ ቤት አግባብነት ያለውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላትና የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ በማያያዝ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን አድረሻና ልዩ የምዝገባ የመለያ ቁጥር የማሳወቅ ግዴታ የተጣለበት ሲሆን፣ አዋጁ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 ያጣለው ይህ ግዴታ በፌዴራል መንግስት ህጋዊ ዕውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመን የንግድ ድርጅት የክልል የንግድ ተቋም ወይም የክልልና የፌዴራል ህጋዊ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት የማድራግ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፤
7. በአዋጅ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 4 የተቀመጠውና ቅርንጫፍ የማሳወቅ ግዴታ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ከፍቶ የሚነግድ የፌዴራል ወይም የክልል የንግድ ድርጅት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን ከፍቶ የንግድ ሥራ በሚሠራባቸው ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የሚሠራው ሥራ ህጋዊ ህልውናና የንግድ ፈቀድ ካገኘበት የንግድ ሥራ ጋር ተመሣሣይ መሆኑን ለመረጋገጥና ቅርንጫፎቹ ጎጅና ተገቢ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር መሆኑ የአዋጅን አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 4 እና የአዋጅን አንቀፅ 3 ድንጋጌዎች በጣምራ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጫማሪ የንግድ ድርጅቱ ቅርንጫፍ በከፈተባቸው ሥፍራ ያሉ መዝጋቢ አካለት፣ ቅርንጫፍ የሚመዘግቡት በአዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ሚኒስትር በሚሰጣቸው ውክልና መሠረት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም አመልካች በመቀሌ ከተማ ቅርንጫ ስለከፈትኩና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ በመቀሌ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ያልተመዘገበ በመሆኑ እንደ አንድ የክልሉ የንግድ ድርጅት ስለምቆጠር የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው በማለት ያቀረበውን ክርክር የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡
8. አመልካች በመቀሌ ከተማ ቅርንጫፍ ከፍቶ የንግድ ሥራ መሥራቱና ቅርንጫፉ በመቀሌ ከተማ ንግድና እንዱስትሪ ቢሮ የንግድ መዝገብ የተመዘገበና ፈቃድ የተሰጠው መሆኑ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተቋቋመ የንግድ ድርጅት በመሆኑ ላይ የሚያሳድረው ለውጥ የለም ከተባለ በፌዴራል መንግስት ዕውቅና የተቋቋመ የንግድ ድርጅት ተካፋይ የሆነበትን ክርክር በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 6

ተደንግጓል፡፡ በክልል የዳኝነት ሥልጣናቸው በተደራቢነት የፌዴራል ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰጣቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ናቸው፡፡

9. አመልካች ለወረዳ ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበት ጉዳይ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተደራቢ የዳኝነት ስልጣን ላለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ መወሰን ሲገባው በወረዳው ፍርድ ቤት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 (2) የሚጥስ መሆኑን በመረጋገጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሻረው በህግ አግባብ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል ፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ግራቀኙ ለያራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሩ/ለ**

የሰ/መ/ቁ.100290

ሚያዝያ 1 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ወ/ሮ መሰረት አለማየሁ - ጠበቃ መላኩ አየነው

**ተጠሪዎች፡-**

1. ወ/ሮ እሙሽት ሙሉጌታ - ጠበቃ አባይነሽ ማሙዬ ቀረቡ
2. አቶ ፀጋዬ ደመቀ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር በአሜሪካን አገር የተፈጸመ ጋብቻ መኖሩን ያስረዳልኛል በማለት ያቀረቡት የጋብቻ ማስረጃ በአዋጅ ቁጥር 334/2004 አንቀጽ 26(1) ድንጋጌ መሰረት በአሜሪካን አገር በሚገኘው የኢትዮጰያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ያልተረጋገጠ እና ወደ አገር ውስጥ ከገባ በኃላም ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ መሰረት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቀርቦ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካቿ የዚህ ዓይነቱን ሰነድ መሰረት በማድረግ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ከጋብቻ እና በጋብቻው የተፈራ ነው ከተባለ ንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ ጉዳይ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ

ቤት ክስ አቅርበው ውሳኔ ማስጠታቸውን፣በጋብቻው ውስጥ የተፈራ ነው ተብሎ ውሳኔ ካረፈበት ንብረት ውስጥ አንዱ በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኝ ባለሶስት ፎቅ ሕንጻ መሆኑን፣የአሁኗ አመልካችም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡት በዚሁ ውሳኔ ላይ መሆኑን፣በ20/02/2006 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ አጭር ይዘትም፡- ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር በአሜሪካን አገር በ1993 ዓ.ም. ጋብቻ መስርተው አንድ ልጅ እንዳፈሩ፣1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር አብሮ ከመኖር በቀር የፈጸሙት ጋብቻ እንደሌለ፣ተጠሪዎቹ በጋብቻ ያፈሩት ነው የተባለው በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኝ ባለሶስት ፎቅ ሕንጻም የተሰራው በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ የጋራ ገንዘብ እና አመልካች ከአሜሪካን አገር በላኩት ገንዘብ እንደሆነ የሚገልጽ ሆኖ ሕንጻው ለአመልካቿ እና ለ2ኛ ተጠሪ እኩል ከተካፈለ በኃላ 1ኛ ተጠሪ ከፈለጉ ከ2ኛ ተጠሪ ድርሻ እንዲካፈሉ እንዲደረግ እና 2ኛ ተጠሪ የልጅ ቀለብ እንዲከፍሉ የተጠየቀበት መሆኑን፣1ኛ ተጠሪ በመቃወም አቤቱታው ላይ በሰጡት መልስ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተፈጸመ ጋብቻ አለመኖሩን እና የጋብቻ ማስረጃ ነው ተብሎ የቀረበው ሰነድም በአሜሪካን አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ያልተረጋገጠ እና ወደ አገር ውስጥ ከገባ በኃላም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቀርቦ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አለመሆኑን በመግለጽ መከራከራቸውን፣2ኛ ተጠሪ በመቃወም አቤቱታው ላይ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ ስለመሆኑ በብይኑ ላይ የተገለጸ ነገር አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቿ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው በመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ የማስተናገድ ስልጣን የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ወይስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው? የሚለውን ነጥብ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ) አንጻር እንዲሁም አመልካች በማስረጃነት ያቀረቡትን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ የሰጠውን ማረጋገጫ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት ስለማረጋገጫው ሕጋዊነት ጉዳይ በአግባቡ አጣርተው መሆን አለመሆኑን ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመቃወም አቤቱታውን አስተናግዶ ብይን የሰጠው ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ኖሮት ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የስረ ነገር ስልጣን ጉዳይ በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም ማንኛውም ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ አስተናግዶ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር

ስልጣን ያለው መሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት መሆኑ፣ስልጣን የሌለው በሆነ ጊዜ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 9(1) እና 231(1)(ለ) እንደተመለከተው ተገቢውን ትዕዛዝ ወይም ብይን ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑ እና የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን የሚያረጋግጠውም በክስ ማመልከቻው ላይ ከተገለጸው ዝርዝር መሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡በሌላ በኩል አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክስ የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆኑን አረጋግጦ ጉዳዩን ማስተናገድ በቀጠለበት ጊዜም ሆነ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኃላ ክርክሩ ይመለከተናል ወይም የተሰጠው ውሳኔ መብታችንን የሚነካ ነው በማለት በስነ ስርዓት ሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት እንደ የአግባብነቱ የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ወይም የመቃወም አቤቱታ በሚያቀርቡ ሰዎች ማንነት ወይም በሚያቀርቡት የዳኝነት ጥያቄ ባህርይ ላይ ተመስርቶ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የክርክሩ ተካፋይ ያልነበሩ ሰዎች ወደ ጉዳዩ መግባት ጉዳዩን አስቀድሞ ማየት ከጀመረው ወይም ውሳኔ ከሰጠው ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ውጪ ሊያደርግ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡የእንደዚህ ዓይነቶቹ አጋጣሚዎች መፈጠር አንዱ መንስዔ አገሪቱ መከተል የጀመረችውን የፌዴራሊዝም ስርዓት መሰረት በማድረግ በአገሪቱ ያለው የዳኝነት ስልጣን በፌዴራል እና በክልል የተከፋፈለ መሆኑ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአሁኖቹ ተጠሪዎች መካከል የተነሳውን ክርክር የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስተናግዶ ውሳኔ የሰጠው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት ሲሆን አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡትም ተካፋይ ባልሆንኩበት ክርክር ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ መብቴን ይነካል በማለት ነው፡፡በመሰረቱ የመቃወም አቤቱታ የሚቀርበው መቃወሚያ የቀረበበትን ፍርድ ለሰጠው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 359(1) ስር ተመልክቷል፡፡ይሁን እንጂ የስነ ስርዓት ሕጉ የወጣው አገሪቱ የፌዴራሊዝም ስርዓት መከተል ከመጀመሯ እና በአገሪቱ ያለው የዳኝነት ስልጣንም በፌዴራል እና በክልል ከመከፋፈሉ ከረጅም ዓመታት በፊት በመሆኑ ድንጋጌው መተርጎም የሚገባው የፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን አስመልክቶ አዲስ ከወጡት የሕግ ማዕቀፎች ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ የተደረገው የስረ ነገር ስልጣን ያለውን ፍርድ ቤት ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 11(2)(ሀ) ድንጋጌ አንጻር ለማጣራት ሲሆን የተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌም የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን(ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጉዳዩ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር እንዲወድቅ የሚያደርገው መሰረታዊ ጉዳይ የተከራካሪ ወገኖች ወይም ከእነዚህ አንዱ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸው ሳይሆን ይልቁንም ለክርክር የቀረበው ጉዳይ የተለያዩ ሀገሮች ሕጎችን

የተፈጻሚነት ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑ ነው፡፡ከክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች የሰዊድን፣2ኛ ተጠሪ ደግሞ የአሜሪካን ዜግነት ያላቸው ሲሆን አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመን ስንኖር ነበር የሚሉትም በአሜሪካን አገር ነው፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ ኢትዮጵያዊት ሲሆኑ ክርክሩ የቀረበውም ለኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ነው፡፡ይህ ብቻ ሳይሆን አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ያፈሩሁት ነው የሚሉት የማይንቀሳቀስ ንብረትም የሚገኘው በኢትዮጵያ ውስጥ ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎችም፡-

1. የአመልካችን የዜግነት አገር ሕግ
2. የ2ኛ ተጠሪን የዜግነት አገር ሕግ
3. የአመልካች እና የ2ኛ ተጠሪን መደበኛ የመኖሪያ አገር ሕግ
4. የአመልካች እና የ2ኛ ተጠሪ ጋብቻ ተፈጽሟል የተባለበትን አገር ሕግ
5. ክርክሩ የቀረበለትን ፍርድ ቤት ሀገር ሕግ
6. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚገኝበትን አገር ሕግ እና
7. ተከራካሪ ወገኖች የሚስማሙበትን አገር ሕግ

የተፈጻሚነት ጉዳይ የሚያስነሱ ናቸው፡፡አከራካሪ ሆኖ ለቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ውሳኔ ለመስጠት ደግሞ የእነዚህ ሀገሮች ሕጎች ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ የሚፈቱበትን አግባብ መለየትን፣ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ በመፍታት ረገድ በእነዚህ ሀገሮች ሕጎች መካከል አለመጣጣም (Conflict) መኖር አለመኖሩን መለየትን፣አለመጣጣም የሚኖር ከሆነ አለመጣጣሙ የሚፈታበትን አግባብ መለየትን እና በመጨረሻም ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለውን ሕግ መምረጥን ይጠይቃል፡፡ይህም የአሁኗ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን (ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው) የሚመለከት መሆኑን እና ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣንም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 11(2)(ሀ) ድንጋጌ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሆነ መገንዘብ የሚያስችል በመሆኑ የመቃወም አቤቱታው የቀረበለት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ ገልጾ የመቃወም አቤቱታውን መመለስ ሲገባው ተቀብሎ በማስተናገድ ውድቅ ያደረገው የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በሌላ በኩል ጉዳዩ የተነሳው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(2) በተሰጠው የስልጣን ውክልና፣በክልሉ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 64 (2) (ለ) እና የክልሉን ፍርድ ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/2000 በአንቀጽ 26 (1) (ለ) በተመለከተው መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡

ሲጠቃለል የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ ተቀብሎ በማስተናገድ የሰጠው ብይን የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው የተሰጠ እና በዚህም ምክንያት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአሁኗ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ ተቀብሎ በማስተናገድ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26729 በ11/07/2006 ዓ.ም. የሰጠው እና በኦሮሚያ ብ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 186043 በ25/07/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን (ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው) የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት የስረ ነገር ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሸሻለ) አንቀጽ 11(2)(ሀ) ደንጋጌ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣በሕገ መንግስቱ በተሰጠው የስልጣን ውክልና መሰረት ደግሞ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት በተመለከተው መሰረት አመልካች ተጥሶብኛል የሚሉትን መብት ለማስከበር ክሳቸውን ማቅረብ የሚገባቸው ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ይ**

የሰ/መ/ቁ. 97009

ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካችዎች፡-** 1. አቶ ኤልያስ አዳሙ ጠበቆች ክፍሌ ታደሰና አቶ ጅማ ድልቦ ቀረቡ

2. ሐዋሪያው ዳንኤል መኮነን

**ተጠሪዎች፡-** የኢትዮጵያ ወንጌል ብርሃን ቤቴክርስቲያን - ደረጀ አበበ የቦርድ ተወካይ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 08477 ሐምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142307 ታህሣሥ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በተጠሪ አንድ አጥቢያ ላይ የተፈጠረ ሁከት እንዲቆምና እንዲወገድ ውሣኔ ይሰጥልን በሚል መንገድ የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካችዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በጠበቃ ተወክላ ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፣ ከሳሽ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመች ናት፡፡ ተከሳሾች የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም በከሳሽ አንድ አጥቢያ ላይ ሁከት በመፍጠር የከሳሽን ቢሮ ውክልና አለን በማለት አሽገዋል የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት በመምጣት ከሌሎች ግብረአበሮቻቸው ጋር በመሆን የሁከት ተግባር ፈፅመዋል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ /ሁለተኛ አመልካች/ ከሥልጣናቸው መነሳታቸውን እያወቁት ለሌሎች ሠራተኞች የሥራ አመራር ትዕዛዝ በመስጠት በከሳሽ

ቤተክርስቲያን ላይ ችግር ፈጥረዋል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ አመልካች/ አላግባብ ከሁለተኛ ተከሳሽ ባገኘው ውክልና በከሳሽ ላይ የፈጠረው የሁከት ተግባር እንዲወገድና የውክልና ስልጣኑ እንዲሰረዝልን ሁለተኛ ተከሳሽ ከኃላፊነታቸው ስለተነሡ የሥራ አመራር ተግባር መሣተፋቸው የሁከት ተግባር በመሆኑ ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

2. አንደኛ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው የፅሑፍ መልስ ቤተክርስቲያን በመወከል በቤተክርስቲያኗ ስም ክስ ለማቅረብ የሚችሉት መስራች ሀዋሪያው ናቸው፡፡ የሥራ አመራር ቦርዱ ቤቴክርስቲያኗን ወክሎ ክስ ለማቅረብ አይችልም፡፡ ክሱ የቀረበብኝ ቤቴክርስቲያኗን ወክለው ክስ የማቅረብ ሥልጣን በሌለው አካል በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት፣ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሁለተኛ አመልካች መልስ በፅሑፍ ባለማቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኂላ፣ክሱ የቀረበው ቤተክርስቲያኗን ወክሎ ክስ ለማቅረብ ተገቢው ውክልና ባላቸው ሰው ነው ወይ? ተከሳሾች በቤተክርስቲያን ላይ የፈጠሩት የሁከት ተግባር አለ ወይ? የሚሉትን ጭብጦች መሥርቷል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት በቤተክርስቲያኑ መተዳደሪያ ደንብና በቤተክርስቲያኗ የመዋቅር መግለጫ ተዋረድ መሰረት ሀዋሪያው ከሥራ አመራር ቦርዱ ሥር የተቀመጡ መሆኑንና መሥራች ሀዋሪያው አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ሥልጣን በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 18 እንደተሰጣቸው ገልፆ፣ የመስራች ሀዋሪያውን የመንፈሣዊ ሥልጣን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለኝም፡፡ መሥራች ሀዋሪያው በመተዳደሪያ ደንቡ፣ አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 6 የተሰጠውን አስተዳደራዊ ሥልጣን በተመለከተ በዳኝነት አይቼ መወሰን እችላለሁ፡፡ ከዚህ አንፃር መስራች ሀዋሪያው /ሁለተኛ ተከሳሽ/ ከአስተዳደራዊ ሥልጣናቸው በሥራ አመራር ቦርዱ የተነሱ ስለሆነ በአንደኛ ተከሳሽ የውክልና ሥልጣን መስጠት አይችሉም፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ተከሳሽ ከአስተዳደራዊ ሥልጣናቸው የተነሱ ስለሆነ በአስተዳደር ሥራ እንዳይሣተፉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካችዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የአመልካችዎችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

4. አመልካችዎች ጥር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የኢትዮጵያ ወንጌል ብርሀን ቤተክርስቲያን በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ሃይማኖት መሠረት የተቋቋመች፣ የራሷን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አውጥታ የምትተዳደር ቤቴክርስቲያን ነች፡፡ ቤተክርስቲያኗ ነሐሴ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ያፀደቀችው መተዳደሪያ ደንብ እስካሁንም ድረስ በሥራ ላይ ያለና የምትተዳደርበት ደንብ ነው፡፡ የቤቴክርስቲያኗን መተዳደሪያ ደንብ በሚመለከት የሚነሳ ጥያቄና ክርክር ሀይማኖታዊ ባህሪ፣ ይዘት ያለው በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይና ሊወሰን የሚችል አይደለም፡፡ ለሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ይዘትም ጭብጥም የሥራ አመራር

ቦርዱ ቤተክርስቲያኗ በመተዳደሪያ ደንቡ መሪ አድርጋ የሾመቻቸውን ሁለተኛውን አመልካች ከአስተዳደር ሥልጣናቸው አንስቻለሁ በማለት የሰጠው ውሣኔ በቤተክርስቲያኗ ተፈፃሚነት የሚሰጠው መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የውክልና ስልጣን ሰጥቶኛል የሚለው የቀድሞው የሥራ አመራር ቦርድ በቤተክርስቲያኒቱ ላይ በፈጠራው ረብሻ ምክንያት ጠቅላላ ጉባኤው ተሰብስቦ ከኃላፊነታቸው እንዲነሡ የወሰነባቸውና በሌላ ሥራ አመራር ቦርድ የተተካ ቤተክርስቲያኗን ወክሎ ክርክር ለማቅረብ ህጋዊ ህልውና የሌለው አካል ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ጉዳይ በዳኝነት ተቀብሎ በማየት የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 37/1/ እና ስለመንግስትና ኃይማኖት መለያየት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 11 የተደነገገውንና ይኸ ሰበር ችሎት የሰጣቸውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች በመጣስ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡

5. ተጠሪ የካቲት 28 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤተክርስቲያኗ የምትተዳደረው ግንቦት 2 ቀን 2000 ዓ.ም በወጣው መተዳደሪያ ደንብ መሆኑን ገልፀውና የመተዳደሪያ ደንቡን ድንጋጌዎች በሰፊው ዘርዝረው የሥራ አመራር ቦርዱ ከአስተዳደር ሥልጣናቸው ካነሳቸው በኋላ ሁለተኛ አመልካች አንደኛ አመልካችን መወከላቸው የሁከት ተግባር ነው፡፡ የሁከት ተግባር መሆኑም የወንጀል ምርመራ ተጣርቶ፣ የወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ አመልካች ከአስተዳደራዊ ሥልጣኑ ከተወገደ በኋላ ሁከት መፍጠሩን በማስረጃ በማረጋገጥ ሁከቱ እንዲወገድ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ በዳኝነት የሚያልቅ መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠው በመሆኑ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች መጋቢት 29 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ሁለተኛ አመልካች ከአስተዳደራዊ ሥልጣናቸው በቤtክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ የተነሱ በመሆኑ፣ የቤተክርስቲያኗ የአስተዳደራዊ ሥራ ውስጥ መግባታቸው የሁከት ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ አመልካች በቤተክርስቲያኗ አስተዳደራዊ ተግባር እንዳይሣተፉ በማለት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርመረናል፡፡

7. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን አመልካቾችና ተጠሪ የሚከራከሩበት መሠረታዊ ጉዳይ ባህሪና ይዘት ምንድን ነው? ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ መሠረታዊ ይዘት ምንድን ነው የሚሉትን ነጥቦች በመመልከቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ለሥር ፍርድ ቤት ክሱ ሲቀርብ

ቤተክርስቲያኗን በመወከል ለጠበቃ የወኪልነት ሥልጣን የሰጠው የሥራ አመራር ቦርድ፣ የቤተክርስቲያኗ "መሥራች ሀዋሪያ " መሆናቸው በግንቦት ወር 2000 ዓ.ም በወጣው ደንብ ስማቸው የተገለፀውን ሁለተኛ አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ ቤተክርስቲያኗን የማስተዳደር ሥልጣናቸውን በማንሣት በመንፈሳዊ ሥልጣናቸው ብቻ እንዲገደቡ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ በቤተክርስቲያኗ የአስተዳደር ሥራዎች እየገቡ ችግር እየፈጠሩ ነው፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ አመልካች በሌላቸው ስልጣን ቤተክርስቲያኗን እንዲያስተዳድር ለአንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ አመልካች/ የሰጠው ውክልና እንዲሰረዝና ሁለተኛ ተከሳሽ በአስተዳደራዊ ሥራዎች ጣልቃ እንዳይገባ ይወሰንልን የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

8. አንደኛ አመልካችና በጅምሩ የሥራ አመራር ቦርዱ ቤተክርስቲያኗን ወክሎ ክስ ለማቅረብና ለመከራከር የሚያስችለው ሥልጣን የለውም፡፡ በመተዳደሪያ ደንቡ የሥራ አመራር ቦርድ በመሥራች ሀዋሪያው /ሁለተኛ አመልካች/ የሰጠውን ስልጣን መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ብሎ የመክፈልና የመሥራች ሀዋሪያውን ሥልጣን ለመቀነስ ወይም የመስራች ሀዋሪያው ቤተክርስቲያኗን የማስተዳደር ሥልጣኑ የማንሣት ስልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ የሥራ አመራር ቦርድ መሥራች ሀዋሪያው /ሁለተኛ አመልካች/ በቤተክርስቲያኗ የአስተዳደር ሥራ እንዳይሳተፍ የሰጠው ውሣኔ የቤተክርስቲያኗን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ተፈፃሚነት የለውም በማለት አንደኛ አመልካች በፅሑፍና በቃል ባቀረበው ክርክር ሁለተኛ አመልካች የግራቀኙ ክርክር በሚሰማበት ቀን ተገኝቶ በቃል ባቀረበው ክርክር የገለጹ መሆናቸውን፣ ለመረዳት ችለናል፡፡

9. አንድ ክርክር መሠረታዊ ጭብጦች የሚመሰረቱት ከሳሽና ተከሳሽን የሚካካዱበትን የሕግ ነጥብ፣ ከሳሽ በክሱ የገለፀውን ፍሬ ነገር እና በማስረጃነት የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ይዘት፣ ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ የገለፀውን ፍሬ ነገርና በመከላከያ ማስረጃነት የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ይዘትና ፍርድ ቤቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 መሠረት የግራቀኙን የቃል ክርክር ሲሰማ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246/1/፣የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 247/1/ እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ አመልካችና ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር መሰረታዊ ጭብጦች የስራ አመራር ቦርድ ቤተክርስቲያኗን በመወከል ክስ ለማቅረብ ይችላል ?ወይስ አይችልም? የስራ አመራር ቦርድ የመስራች ሐዋሪያውን በቤተክርስቲያኑ መተዳደሪያ ደንብ የተሰጠውን የቤቴክርስቲያን አስተዳደር የመምራት ስልጣን እንዲቀንስ ወይም እንዲሽር የመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም? በቤተክርስቲያን አደረጃጀትና የስልጣን ተዋረድ እርከን፣ ከፍተኛ ስልጣን ያለው መስራች ሐዋሪያው ነው ወይስ የስራ አመራር ቦርዱ? የስራ አመራር ቦርዱ መስራች ሐዋሪያው የቤተክርስቲያን አስተዳደር ስራ

እንዳይሰራ በማለት የሰጠው ውሳኔ በቤተክርስቲያን የውስጥ አስተዳደር ጉዳይ ውጤትና ተፈፃሚነት ያለው ውሳኔ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡

10. ከላይ የተገለፁትንና ግራ ቀኙ የሚከራከሩባቸው መሰረታዊ ጭብጦች በመሰረታዊ ባህሪያቸው 1987 ዓ.ም ህጋዊ ህልውና አግኝታ የተቋቋመችው የኢትዮጵያ የወንጌል ብርሃን ቤተክርስቲያን፣ የተቋቋመችበትን መመስረቻ ፅሁፍ፣ ቤተክርስቲያኗ ኃይማኖታዊ አላማ ለማሳካት፣ የፈጠረቻቸውን መዋቅራዊ አደረጃጀቶች፣ ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ ያወጣችውንና በፍትህ ሚኒስቴር ግንቦት 2 ቀን 2000 ዓ.ም ቀርቦ የተመዘገበውን መተዳደሪያ ደንብና የቤተክርስቲያን የተለያዩ አካላት ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት መመርመርና መተርጎም የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አይነት መንገድ የተቋቋመ አንድ ሀይማኖታዊ ተቋም፣ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት የሚያደራጃቸውን አደረጃጀቶች፣ የሚከፍታቸው ቅርንጫፎች፣ የሚፈጥራቸውን መዋቅሮች እንደዚሁም ለተለያዩ የኃይማኖት ተቋሙ አካላት የሚሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት፣ በኃይማኖት ተቋም የተለያዩ አካላት መካከል ስለሚኖረው የስልጣን ተዋረድና የእምነት ተቋሙ ኃይማኖታዊ ዓላማውን ለማሳካት ስለሚሰራቸው መንፈሳዊ ተግባራትና የቤተክርስቲያን አስተዳደር ተግባራት እንደዚሁም መንፈሳዊ አስተዳደርና ተግባሩ በየትኛው የኃይማኖች ተቁሙ አካል በኩል መከናወን እንዳለበት የሚነሱ ክርክሮች በመሰረታዊ ይዘታቸውና ባህሪያቸው የኃይማኖት ተቋሙን የተቋቋመበትን መሰረታዊ አላማ የተቋሙን መመስረቻ ፅሁፍ፣ የኃይማኖት ተቋሙ የሚመራባቸውን መሰረታዊ የእምነት ህጎችና ቀኖናዎችና የኃይማኖት ተቁሙን መተዳደሪያ ደንብ በጥልቀት መረዳትና መተርጎምና ተፈፃሚ እንደሆኑ ማድረግ የሚጠይቅ ከኃይማኖት ተቋሙ መሰረታዊና ተፈጥሯዊ ባህሪ ተነጥለው ለየብቻቸው ሊታዩና ሊወሰኑ በፍርድ ሊወሰኑ የሚችሉ ጉዳዮች አይደሉም፡፡ ከዚህ አንፃር ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጭብጥ በዳኝነት የማያልቅ ከቤተክርስቲያኑ መሰረታዊ ተፈጥሯዊ ባህሪ ተነጥሎ ሊታይ የማይችል ጉዳይ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት የቤተክርስቲያኑን አስተዳደራዊ ስራዎች ለማከናወን የተሰጠ የሹመትና የስርአት ጉዳይ በዳኝነት አይቶ መወሰን የምችለው ጉዳይ ነው፡፡ የቤተክርስቲያኑን መንፈሳዊ ሹመት ስራና ኃላፊነት በተመለከተ በዳኝነት የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

11. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 11 መሰረታዊ መርህ ሆኖ የተደነገገው የመንግስትና የኃይማኖት መለያየት መሰረታዊ መርህ፣ በይዘቱም ሆነ በተግባራዊ ተፈፃሚነቱ የአንድ ኃይማኖታዊ ተቋም የተቋቋመበትን ኃይማኖታዊ ዓላማ ለማሳካት በመመስረቻ ፅሁፍና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የዘረጋውን አደረጃጀት፣ የከፈታቸው

ቅርንጫፎች፣ ያዋቀራቸውን የተለያዩ አካላትና ያላቸው መንፈሳዊና አስተዳደራዊ የስልጣን ደረጃ እርከንና ተዋረድ፣ እንደዚሁም በኃይማኖት ተቋሙ የተለያዩ አካላት መካከል የሚነሱ የስልጣን፣ የኃላፊነትና የተጠሪነት ጉዳይ በዳኝነት አይቶ በማስረጃ አጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥና በኃይማኖት ተቋሙ መሰረታዊ ተፈጥሯዊ ጉዳይ ገብቶ ዳኝነት እንዲሰጥ የሚፈቅድለት አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ይኸ ሰበር ችሎት በኃይማኖት ተቋማት የተለያዩ አካላት፣ መሪዎችና ኃላፊዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮች በራሱ በኃይማኖትታዊ ተቋሙ መመስረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብና የዕምነቱ መሰረታዊ ህግጋትና ቀኖናዎች መሰረት የሚፈቱ መሆናቸውንና ፍርድ ቤቶች እንደዚህ አይነት ክርክሮችን አይተው ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችላቸውን የዳኝነት ስልጣን የሌላቸው መሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 66957 በሌሎች መዛግብት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች ሕገ መንግስቱን አንቀፅ 11 የተቀመጠውን መሰረታዊ መርህን ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 66957 በሌሎች መዛግብት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉምና የአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ወደ ጎን በመተው ጉዳዩን በዳኝነት አይተው ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ዝርዝር ምክንያቶች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዳኝነት አይተው የመወሰን ስልጣን የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

ማ/አ

# ንብረት

የሰ/መ/ቁ.105092

መገቢት 1 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ ብርሃኑ ከበደ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ኢብራሂም ሹካ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በገጠር የእርሻ ይዞታ ላይ የተነሳ የውርስ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአርሲ ዞን በዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ከሳሽ በ08/11/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ በ2001 ዓ.ም በሞት የተለዩት የከሳሽ አባት አቶ ሹካ ቃሉ በሕይወት እያሉ በኪራይ ለተከሳሽ ሰጥተው የነበረውን እና በውርስ ለከሳሽ ሊተላለፍ የሚገባውን አወሳኞቹ በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸውን ሶስት ጥማድ የእርሻ ይዞታ ተከሳሽ እንዲለቁ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን የሚገልጽ እና ይህንኑ መሬት ለቀው ለከሳሽ እንዲያስረክቡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ በበኩላቸው በ18/11/2005 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ተከሳሽ የከሳሽን እናት እና አባት ሲጦሩ የነበረ መሆኑን ምክንያት በማድረግ የከሳሽ ወላጆች በእርሻ ይዞታው የመጠቀም መብታቸውን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2427 መሰረት በ26/02/1999 ዓ.ም በተደረገ ውል በስጦታ ያስተላፉላቸው መሆኑን፣ተከሳሽም ውሉን በሚመለከተው አካል አስመዝግበው የከሳሽ ወላጆች በሕይወት እያሉ የባለይዞታነት ስሙን ወደ ራሳቸው አዛውረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን እና በዚሁ ይዞታ ጉዳይ የከሳሽ ወንድሞች በተከሳሽ ላይ በሌላ መዝገብ ክስ መስርተው መዝገቡ በዕርቅ የተዘጋ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በግራ ቀኙ ማስረጃ እና ከሚመለከተው አካል ማጣራቱን፣የከሳሽ ወላጆች በእርሻ ይዞታው የመጠቀም መብታቸውን በ26/02/1999 ዓ.ም በተደረገ ውል በስጦታ ለተከሳሽ

ማስተላለፋቸው እና ተከሳሽም የባለይዞታነት ስሙን ወደራሳቸው አዛውረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ በክርክሩ መረጋገጡን ገልጾ ሟቾች በሕይወት እያሉ ለተከሳሽ ያስተላለፉት በይዞታው የመጠቀም መብት የውርስ ንብረት ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎ ተከሳሽ ይዞታውን እንዲለቁ አይገደዱም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን ያጸና ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብትን ከባለይዞታው ጋር የስጋ ዝምድና ለሌለው ሰው ማስተላለፍ የማይቻል ስለመሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 6 ስር ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑን በምክንያትነት ጠቅሶ የሁለቱን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር አመልካች ክስ ያስነሳውን ይዞታ ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች አከራካሪውን መሬት በተመለከተ ህዳር 28 ቀን 1999 ዓ.ም ሕጋዊነቱ የተረጋገጠላቸው መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ እያላቸው የክልሉ ሰበር ችሎት በሀምሌ ወር 1999 ዓ.ም የወጣውን የገጠር መሬት አዋጅ ወደ ኃላ ወስዶ አመልካች የቤተሰብ አባል ስላልሆኑ መሬት በስጦታ የማግኘት መብት የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን ሽሮ አመልካች ክስ ያስነሳውን ይዞታ ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠሪው ወላጆች ክርክር ባስነሳው የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብታቸውን በ26/02/1999 ዓ.ም በተደረገ ውል በስጦታ ለአመልካቹ ማስተላለፋቸው፣ አመልካችም የባለይዞታነት ስሙን ወደ ራሳቸው አዛውረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ እና አመልካች ለስጦታ አድራጊዎቹ ተወላጅም ሆነ በመሬቱ ገቢ የሚተዳደሩ የቤተሰብ አባል አለመሆናቸው ያልተካደ እና በክርክሩም የተረጋገጠ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን በመሻር ስጦታው ሕጋዊ ውጤት ያለው አይደለም ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብትን ለተወላጅ ወይም ከመሬቱ በሚገኝ ገቢ ለሚተዳደር የቤተሰብ

አባል ካልሆነ በቀር በስጦታ ማስተላለፍን የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አይፈቅድም በማለት ነው፡፡አመልካችም ቢሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት የሚከራከሩት ስለ ስጦታ ውል አደራረግ እና ስለሕጋዊ ውጤቱ በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት አድርገው ከመሆኑ ውጪ ስጦታው በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 "ም" ቢሆን ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡

በመሰረቱ በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብትን በስጦታ የማስተላለፍ ጉዳይን ጨምሮ ከገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ክርክሮች በመሰረታዊነት ተፈጻሚነት የሚኖራቸው የፌዴራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 እና ይህንን አዋጅ ተከትለው በየክልሉ የወጡ አዋጆች እና ደንቦች እንጂ የስጦታ አደራረግን አስመለክቶ በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ባለመሆናቸው በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 በስራ ላይ ባለበት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ውሉ ተደረገ የተባለው አዋጁ ከመጽናቱ ከስምንት ወራት በፊት መሆኑ ለክርክሩ ምክንያት ከሆነው ጉዳይ ልዩ ባህርይ አንጻር ተጠቃሹን አዋጅ ለክርክሩ ተፈጻሚ ከማድረግ የሚያግድ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የሁለቱን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር አመልካች ክስ ያስነሳውን ይዞታ ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17089 በ30/01/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62601 በ09/04/2006 ዓ.ም. የጸናውን ውሳኔ በመሻር የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 179508 በ19/12/2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

4. በዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20831 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ29/01/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ብ**

የሰ/መ/ቁ. 109829

ግንቦት 14 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** አቶ ረታ ከበበ ቀረቡ

**ተጠሪ ፡--** ወ/ሮ ቱሬ ደማ ተወካይ ሙልጌታ ከበበ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመሬት ይዞታ ክርክር የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የወረጃርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረው በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኗ ተጠሪ በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ልጃቸው እንደሆነ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የመሬት ይዞታ በፍርድ ቤት አስወስነው የተረከቡት ከቦቤ ሊበን ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው በአጠቃላይ 0.9 ሄክታር መሬት በክርክር ላይ እያለ በቀጣይነት ይዘው እየተጠቀሙበት ስለሆነ ከዚህ መሬት ላይ አርሰው ያገኙት አላባ እና ግጦሽ በአጠቃላይ 6500 የሚያስገኝ ስለሆነ አላባውን ከፍሎው መሬቱን እንዲለቅላቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በሰጡት መልስ ክስ ከቀረበበት ይዞታ ሁለት ቦታ ላይ የሚገኘው በስጦታ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ይኸውም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት በሌላ ሰው የተያዘባቸው በመሆኑ ተከራክረው በማስለቀቃቸው መብታቸውን ያስከበሩላቸው በመሆኑ እንደተሰጣቸው በ3ኛ ቦታ የሚገኝ መሬት በተመለከተ ግን የተጠሪ ከብቶች የበሉት ስለሆነ ሊጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክርና እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ለክርክሩ መነሻ ከሆነው ይዞታ ተጠሪ ለአመልካች 3 ገመድ መሬት በስጦታ መስጠታቸው በ22/06/2006 የተፃፈ

ስጦታ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር መያያዙን፣ በመሆኑም ተጠሪ መሬቱን ይዞብኛል በማለት ያቀረቡት በስጦታ የተሰጠውን 3 ገመድ መሬት የአመልካች መሆኑን፤ ሌሎች ይዞታዎች በተመለከተ ግን ለቀው እንዲያስረክቡ ለግጦሽ አሳባ በተመለከተ የተጠሪ ከብቶች የበሉት መሆኑ ምስክሮች አረጋግጠዋል በማለት ያለፈው መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ተጠሪ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት በማግኘቱ ግራቀኙ አከራክሮ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ አጭር ይዘት፡- ግራቀኙ እያከራከረ ያለው የመሬት ይዞታ ውሳኔ አግኝቶ ተጠሪ ከተረከቡት በኋላ አመልካች መያዙን፤ አሳባ እና ግጦሽ በተመለከተም አመልካች መሬቱን አርሶ ያመረተበት መሆኑን፤ ግጦሽም በከብቶች መበላቱን በምስክሮች መረጋገጡን በመግለጽ አመልካች ሁሉም ክስ የቀረበበት መሬት እንዲለቅ፤ ምርቱ ምን ያህል እንደሆነ፤ የተባለው ግጦሽም ምን ያህል ዋጋ ማውጣት እንደሚችል ተገምቶ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፈል ጉዳዩም በወረዳርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 343(1) የመለሰው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ በሰበር ይታይ በመባሉ ምክንያት ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርገዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የምስክሮች ቃል ቀይሮ መተርጎሙን፤ ለክርክሩ መነሻ ከሆነው መሬት 0.5 ሄክታር መሬት በስጦታ ውል የተሰጣቸው መሆኑን የግጦሽ መሬት የበሉት የተጠሪ ከብቶች መሆናቸውን ተረጋግጦ እያለ ይክፈል መባሉ በአግባቡ አለመሆኑን መሠረት ተደርጎ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- አመልካች መሬቱን በስጦታ አገኘሁት የሚሉት ከሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ያልተመዘገበ፤የስጦታ ውል የተባለው በራሱ ጊዜ ያዘጋጀው መሆኑን፤ አሳባና ግጦሽ በተመለከተ ተጣርቶ እንዲወሰን መመለሱ በአግባቡ ነው የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሊጸና እንደሚገባ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ጉዳዩ እንደመረመርነው አመልካች ከሥር ፍርድ ቤት አንስተው አጥብቀው የሚከራከሩት ለክርክሩ መነሻ ከሆነው የመሬት ይዞታ 0.3 ሄክታር ከተጠሪ በስጦታ ያገኙት መሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ለአመልካች የመሬት ይዞታ ስጦታ አለማድረጋቸው፤ የስጦታ ውል የተባለውም እንደማያውቁት በመጥቀስ መከራከራቸውን ተገንዝበናል፡፡ ከሥር የክርክር ሂደት መረዳት እንደተቻለው ግራቀኙ እያከራከረ ያለው ይዞታ የተጠሪ ስለመሆኑ የተካሄደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይሁንና አመልካች መሬቱን ከሌላ ግለሰብ ተከራክረው ያስመለሱት በመሆኑ እናታቸው /ተጠሪ/ የድካማቸው ዋጋ ይሆን ዘንድ መሬቱን በስጦታ እንደሰጧቸው አፅንኦት በመስጠት መከራከራቸው ከውሳኔ ይዘት መረዳት ችለናል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች መሬቱን ከሌላ 3ኛ ወገን ማስመለሳቸው የገለጹ ቢሆንም ከማን ጋር ተከራክረው መሬቱን እንዳስመለሱት ያቀረቡት ግልጽ ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ በአንፃሩ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት ከአሁኑ አመልካች ይሁን ከሌላ ሰው ተከራክረው መሬቱ እንዳስመለሱት ግልጽ ባይሆንም በተያዘው ጉዳይ መታየት ያለበት እና መፍትሄ የሚያሻው መሠረታዊ ነጥብ መሬቱን ያስመለሱት ከአሁኑ ተጠሪ አመልካች ይሁን ሌላ ሦስተኛ ወገን አመልካች አለኝ የሚሉት የስጦታ ውል የኦሮሚያ የመሬት አዋጅ በሚፈቅደው አግባብ ሥልጣን ባለው አካል ቀርቦ ተመዝግቧል ወይስ አልተመዘገበም? የሚለው ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ እንዳረጋገጠው የመሬቱ ባለ ይዞታ ተጠሪ ስለመሆናቸው ተጠሪ ለአመልካች 0.3 ገመድ በስጦታ መስጠታቸው የተገለጸ ቢሆንም በማይንቀሳቀስ ሥልጣን ባለው አካል ቀርቦ የተመዘገበ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር ሕጋዊ ሰነድ የለም፡፡ በገጠር የመሬት ይዞታ ተጠቃሚዎች የመሬት ይዞታቸው ለ3ኛ ወገን በስጦታ የማስተላለፍ መብት ያላቸው ቢሆንም ስጦታው በሕግ ፊት የሚጸናው በሚመለከተው አካል ቀርቦ መመዝገቡን ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ አመልካች አለኝ የሚሉት የስጦታ ውል በተጠሪ የተካደ ሲሆን በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የስጦታ ውል ስለመሆኑ በሕግ የተደገፈ ክርክር አልቀረበም፡፡ የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሻረው ተሰጠ በተባለው ስጦታ ሕጋዊነት መሠረት በማድረግ ሳይሆን ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ ከአመልካች በክርክር አሸንፈው እንደወሰዱት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ከሥር የወረዳ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ መረዳት እንደተቻለው መሬት የማስመለስ ክርክሩ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል እንደነበር በግልጽ አያሳይም፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የጉዳዩን ክርክር ባሕሪ እና አግባብነት ያለው ጭብጥ ከመመስረት አኳያ ግድፈት ያለበት ቢሆንም በውጤት ደረጃ አመልካች በመሬት ይዞታው መብት እንደሌላቸው የሚያረጋግጥ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በተጠሪ ተሰጠኝ የሚሉት የመሬት ይዞታ ሕጉ በዘረጋው ሥርዓት በሚመለከተው አካል ቀርቦ የተመዘገበ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በተጠሪ ተሰጠ የተባለው የመሬት ይዞታ ስጦታ በሕጉ

አግባብ መቋቋሙ ካልተረጋገጠ በተጠሪ ላይ ሕጋዊ ግዴታ የሚጥል ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካችም ከተጠሪ የመሬት ይዞታ የመጠየቅ መብት የሚሰጠው አይደለም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወረጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር አመልካች በመሬት ይዞታው መብት የለውም ብሎ መወሰኑ በተለየ ምክንያት በውጤት ደረጃ መሠረታዊ የህግ ስህተተ የተፈጸመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 186103 በ02/06/2007 ዓ.ም የወረጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27904 በ12/09/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በማሻሻል፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 47208 በ21/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በተለየ ምክንያት በውጤት ደረጃ በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ አገኘሁት የሚሉት የመሬት ይዞታ ስጦታ፣ ስጦታ ለመመዝገብ ሥልጣን ባለው የመሬት አስተዳዳር ጽ/ቤት ቀርቦ ያልተመዘገበ በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት ወስነናል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች 0.3 ገመድ መሬት እንዲያስረክብ አይገደድም ብለናል፡፡ የውሳኔ ግልባጭ ለሚመለከተው ይተላለፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከትለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

- በዚህ ችሎት መጋቢት 8/2007 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
- መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት የዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/አ**

የሰ/መ/ቁ. 109776

ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አበተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካችዎች፡- 1- ወ/ሮ ይርጋዓለም ዘውዴ - አልቀረቡም

2- ወ/ሪት ስንቅነሽ ክፍሌ

3- ወ/ሪት ወላንሳ ዘውዴ

4- አቶ ኃይለሚካኤል ክፍሌ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሰፉ ዘውዴ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የጊምቢቹ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17681 ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 38944 መስከረም 14 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 197346 ህዳር 18 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የእርሻ መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት በውርስ የማግኘት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ለወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1- የክርክሩ መነሻ ከሳሾች (አመልካቾች)ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾች የሚች ወ/ሮ ካሰች ዘውዴ ልጆች መሆናቸውን ገልፀው የእናታችን እናት ወ/ሮ የሺ ወልደየስ ታህሣሥ 19 ቀን 2005 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፡፡ አያታችን በተለያዩ ስፍራ የእርሻ መሬትና ይዞታ ያላት ሲሆን እኛም በቤተሠብ አባልነት አስመዝግባናለች ፡፡ አያታችን በተሰጣት የይዞታ መሬት ማረጋገጫ ደብተር በቤተሠብ አባልነት የተመዘገበ ነው ከሳሾች ስለሆን መሬቱን የመውረስ የቀዳሚነት መብት አለን፡፡ ሆኖም ተከሳሽ የሚች ወ/ሮ የሺወልደየስ ወራሽ መሆኑን በፍርድ ቤት አስወስና፣ የያዘች በመሆኑ የተሰጣት የወራሽነት ማስረጃ ተሰርዞ መሬቱን የመውረስ መብት ያለን እኛ መሆናችን ተረጋግጦ ይወሰንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

2- ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርባ ሚች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ ወላጅ እናቴ ናት ተከሳሽ የወላጅ እናቴ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆኔ በማረጋገጥ ማስረጃ ያገኘሁት በሕግ አግባብ ነው፡፡ ከሳሾች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡ ከሳሾች የሚችን መሬት በቀዳሚነት የመውረስ መብት የላቸውም በማለት ተከራክራለች፡፡ አመልካቾችና ተጠሪ እየተከራከሩ እያሉ ፣የወ/ሮ ዘነበች ዘውዴ ልጅ መሆኑን ገልፆ እናቴን ተክቼ የአያቴን የእርሻ መሬት የመውረስ መብት አለኝ በማለት አቶ ሰለሞን መርሻ ጣልቃ ገብቷል፡፡

3- የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክር ሰምቷል በአመልካቾች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ተጠሪ የሚች የሺ ወልደየስ ልጅ መሆኗን አናውቅም በማለት የመሠከሩ መሆኑንና ተጠሪ የሚች የሺ ወልደየስ ልጅ መሆኗን የሚያውቁ አምስት ምስክሮች በማቅርብ እንዳስመሰከረች ከዚህ በተጨማሪ አንደኛ ከሳሽ ከአምስት ዓመት በፊት አግብታ ከሁለተኛ ከሳሽ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ መሆኑን ሦስተኛና አራተኛ ተከሳሽም በአዲስ አበባ ከተማ ከአባታቸው ጋር የሚኖሩ መሆኑን ተከሳሽ ባቀረበቻቸው ምስክሮች የተረጋገጠ መሆኑን በውሣኔው ገልፆ የሚች የሺ ወልደየስ መሬት ለሶስት ተከፍሎ ከሳሾች የእናታቸውን ድርሻ አንድ እጅ እንዲወስዱ ጣልቃ ገቡ የእናቱን ድርሻ አንድ እጅ እንዲወስድና ተጠሪ አንድ እጅ ድርሻዋን እንድትወስድ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4- አመልካችዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል ፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችዎችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል አመልካችዎች የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጎባቸዋል ፡፡አመልካችዎች ተጠሪ ከስልሣ አንድ ዓመት በፊት ለሌላ ሰው በጉድፈቻ ተሰጥታ ከጉድፈቻ ከተሰጠችበት አደአ አካባቢ አግብታና መሬት ተመርታ እየኖረች ያለች ናት ፡፡ ተጠሪ አንድ ቀንም ከወላጅ እናቷ የእርሻ

መሬት ተጠቅማ አታውቅም ።በሌላ በኩል እኛ የሟች የሺ ወልደየስ የቤተሠብ አባል መሆናችን በመሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ሟች አስመዝግባናለች ይህም ሆኖ እያለ ተጠሪ መሬት እንድትወርስ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ጥር 27 ቀን 2007ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ በሰበር ችሎት አቅርበዋል።

5- ተጠሪ መጋቢት 11 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ተጠሪ የሟች ልጅ መሆኔ በርካታ ማስረጃ ያለኝ ቢሆንም አመልካችዎች የሟች እናቴ ወራሽ ስለመሆኔ ተረጋግጦ የተሰጠኝ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ ከሕግ ውጭ ጥያቄ አቅርበዋል ። አመልካቿ ለዚህ አሰበር ችሎት ተጠሪ በጉዲፈቻ እንዳደኩ አድርገው በሥር ያላነሱትንና እውነትነት የሌለውን ክርክር አቅርበዋል፤ክርክራቸውም ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ነው። ተጠሪ የእርሻ መሬቱን ከዚህ በፊትም ስጠቀምበት የቆየሁ ስሆን አሁንም ድርሻዬን በስሜ አዛውሬ እየተጠቀምኩ እገኛለሁ ። በሌላ በኩል የሟችን የእርሻ መሬት የመውረስ መብት የሌላቸው አመልካቾች የእኔን ወራሽነት በመቃወም ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክራለች ። አመልካችዎች የካቲት 8 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል።

6- ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሟች እናቷን የእርሻ መሬት ከሌሎች ወራሾች ጋር እንድትካፈል የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል ።

7- ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የግራቀኙን ማስረጃ መዝነው የደረሱበት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል ። ሟች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ፤በሥር ፍ/ቤት ከሳሾች እናት የወ/ሮ ካሰች ዘውዴ ወላጅ እናት መሆኗ ተረጋግጧል። ከዚህ በተጨማሪ ሟች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የተጠሪ ወላጅ እናት መሆኗ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሟች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የሟች ዘነበች ዘውዴ ወላጅ እናትና በሥር ፍ/ቤት ጣልቃገብ ተከራካሪ የሆነው ሰለሞን መርሻ አያታቸው መሆናቸው ተረጋግጧል።

8- ከዚህ አንፃር ሲታይ የሟች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የእርሻ መሬትና ንብረት አመልካቾች እናታቸውን ወ/ሮ ካሰች ዘውዴ በመተካት ተጠሪ የወላጅ እናቷ አንደኛ ደረጃ ወራሽ በመሆኗና ሰለሞን መርሻ እናቱን ዘነበች ዘውዴን በመተካት የመውረስ መብት ያላቸው መሆኑንን ተረጋግጧል። አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሟች የሺ ወልደየስ ልጅ አይደለችም በማለት የተከራከሩና ይህንን ክርክራቸውን ለማስረዳት ምስክሮች

አቅርበው እንደነበርና አመልካቾች ማስረጃ ታአማኒነት የሌለው መሆኑን ተረጋግጧል ፡፡ አመልካቾች በዚህ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የሚች የሺ ወልደየስ የሥጋ ልጅ መሆኗን አምነው ተጠሪ በጉዲፈቻ ሌላ ሰው አሳድጓታል የሚል በሥር ፍርድ ቤት ያላነሱትን አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል ሆኖም አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት ተጠሪ በጉድፈቻ ሌላ ሰው ነው ያሳደጋት በማለት ያቀረቡት አዲስ የፍሬ ጉዳይ ክርክር የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም ፡፡

9- አመልካቾች ተጠሪ የእናቷን ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የእርሻ መሬት የመውረስ መብት የላትም ፡፡ የእርሻ መሬቱን የመውረስ የቀዳሚነት መብት ያለን እኛ ነን በማለት የሚከራከሩት ሚች ወ/ሮ የሺ በህይወት እያለች እኛን በቤተሠብ አባልነት አስመዝግባናለች በማለት ነው፡፡ ሆኖም ሚች ወ/ሮ የሺ አመልካቾችን በቤተሠብ አባልነት ማስመዝገቧ የበታች ፍ/ቤቶች ለማስረጃ ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ መሆኑን ተረድተናል እንደዚሁም ሚች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ አመልካቾችን በአንድ ወቅት በቤተሰብ አባልነት ማስመዝገቧን የሚያሳይ ማስረጃ ቢኖር እንኳን አመልካቾች የሚች የቤተሠብ አባል ሆነው መመዝገባቸው ብቻውን የሚችን የእርሻ መሬት በቀዳሚነት የመውረስ መብት የሚያጎናፅፋቸው አይደለም፡፡

10- ለዚህም ምክንያቱ የእርሻ መሬት በውርስ ለማግኘት ወራሹ አርሶ አደርና ከእርሻ መሬቱ ከሚገኘው ገቢ የሚተዳደር የቤተሰብ አባል መሆን እንዳለበት የፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 5 እና የኦሮሚያ ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 13 እና 16 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

አመልካቾች ሚች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የእርሻ መሬት ከሚገኘው ገቢ የማይተዳደሩ በአዲስ አበባ ከተማ የየራሳቸውን ኑሮ መሥርተው የሚኖሩ መሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካቾች የህጉን መስፈርት የማያሟሉ ሆነው እያሉ ሚች የሺ ወልደየስ የቤተሰብ አባል ናቸው ብላ ማስመዝገቧ፣አመላከቾች የሚችን የእርሻ መሬት የመውረስ ቀዳሚ መብት አለን በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ በእርሻ ሥራ የምትተዳደር አርሶ አደር መሆኗ ተረጋግጧል ፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ተጠሪ የሚች እናቷን የእርሻ መሬት ልትወርስ አይገባም በማለት ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1- የጊንቢቹ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

2- በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

የሰበር መ/ቁ 99071

ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አብረኸት ዲክሪያ ቂምጀን ጠበቃ መስፍን አስፋ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1ኛ ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል

2ኛ አቶ ያሲን ጀማል

3ኛ አቶ ናስር ጀማል

4ኛ የልደታ ክፍለ ከተማ ማሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ነገረ ፈጅ ንጉስ ከበደ ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ክርክር የተመለከተ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦለት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማስተናገድ ሥልጣን እንዳለው ትዕዛዝ ከሰጠ በኃላ አመልካች የክስ ላሻሽል ጥያቄ አቅርበው በፍ/ቤት ፊታድ ክሱን ተሻሽሎ ከቀረበ በኃላ በተመሳሳይ ችሎት በመጀመሪያ ውድቅ የተደረገው መቃወሚያ በድጋሚ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በቀረቡት ክስ የአመልካች እና ከ1-3 የተጠቀሱት ተጠሪዎች የጋራ ሀብት የሆነው በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 327 ለሆነው ቤት ያለአግባብ 4ኛ ተጠሪን በማሳሳት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለወሰዱ ካርታው ተመላሽ እንዲደረግ ይወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በሰጡት የመከላከያ መልስ ከ1-3 የተመዘገቡት ተጠሪዎች የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ የሚታገድ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቀወሚያ ሲያቀርቡ 4ኛ ተጠሪዎች የአመልካች ክስ

መቅረብ ያለበት ከርታ ለሰጠው አስተዳደር ክፍል እንጂ ለፍርድ ቤት አይደለም በማለት መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከመረመረ በኃላ ፍርድ ቤቱ ተሰጠ የተባለው ካርታ የተሰጠበት አግባብ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የማጣራት ስልጣን እንዳለው፤ ለክርክሩ መሠረት የሆነውን ቤት የማን ነው? የሚለው ፍሬ ነገር በማጣራት ሂደት ነጥሮ እንዲመወጣ ይርጋ በተመለከተም የባለቤትነት ክርክር በይርጋ እንደማይታገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በስ/መ/ቁ. 43600 የሰጠው ገዥ ውሳኔ መሠረት በማድረግ ውድቅ እንዳደረገው እና ፍሬ ጉዳዩን ለመስማት ለ25/08/2007 ዓ/ም ቀጠሮ መያዙን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

አመልካች ግን በ07 ቀን 2004 ዓ/ም ክሱን አሻሽሎ የቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ከ1-3 የተመዘገቡ ተጠሪዎች ክስ የማቅረብ መብታቸው በይርጋ ከታገደ በኃላ 4ኛ ተጠሪ ከርታ አዘጋጅቶ መስጠቱ ተገቢ አለመሆኑን፤ በየደረጃው ያሉ የአስተዳደር አካላትም አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ መፍታት ስላልቻሉ ተጠሪዎች የወሰዱት ካርታ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲመክን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ 4ኛ ተጠሪ አመልካች አሻሽለው ላቀረቡት ክስ በሰጠው የመከላከያ መልስ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ የመስጠት ስልጣን የአስተዳደሩ በመሆኑ የመሰረዝ ሥልጣንም የአስተዳደሩ እንጅ የፍርድ ቤት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የ4ኛ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀብሎ የባለቤትነት ካርታ የመሰረዝ ሥልጣን የተሰጠው ለአስተዳደር ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.245(2)(መ) መሠረት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የዚህ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡት ይግባኝም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ የተባለ በመሆኑ ግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክር ያደረጉ ሲሆን ይህ ችሎትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት ተደርጎ ከተሰጠው ብይን አንፃር የቀረበው የሰበር አቤቱታና መልስ እንደተመለከተው፤ በአመልካች በኩል የቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት በብይን ያለፈው ጉዳይ በተመሳሳይ ችሎት እንደገና ተቀብሎ ማስተናገዱ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን 4ኛ ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች አቤቱታ ከተሻሻለ ቀደሞ የተሰጠው ብይንም ሕጋዊ ውጤት አይኖርም የሚል ይዘት ያለው መልስ ሰጥቷል፡፡ ከ1-3 የተጠቀሱት ተጠሪዎችም የስር ፍርድ ቤት ብይን እንዲፀና ጠይቋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታቸው የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ብይን አግባብነት ካላቸው የህግ

ድንጋጌዎች በማገናዘብ ጉዳዩን መርምሮታል፡፡ እንደመረመረነውም በዚህ ችሎት እልባት የሚያስፈልገው ጭብጥ የሥር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሥረ ነገር ስልጣን ጋር በተያያዘ የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ ጉዳዩን ለመስማት ከተቀጠረ በኃላ ክሱን በድጋሜ ተሻሽሎ በመቅረቡ ምክንያት በተመሳሳይ ችሎትና ፍ/ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ተብሎ መዘገቡን በብይን መዘጋቱ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክር ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካች ባቀረቡት ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦ ፍርድ ቤቱም ካርታው የተሰጠበት ትዕዛዝ የማጣራት ስልጣን አለኝ በማለት በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የፍ/ቤቱ ብይን ተከትሎ የተጠየቀ ይግባኝ የለም፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ አመልካች ክሳቸውን ለማሻሻል ያቀረቡት ጥያቄ በፍ/ቤቱ ተቀባይነት በማግኘቱ አሻሽለው አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ካርታ የተሰጠበት አግባብ የማጣራት ስልጣን አለኝ በማለት የሰጠው ብይን በመሻር ካርታ የመስጠትና የመሰረዝ ሥልጣኑ የአስተዳደር ክፍል ነው በማለት በአንድ ጉዳይ ሌላ ብይን ሰጥቷል፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበው የክስ ላሻሽል አቤቱታ የክርክሩ መሠረታዊ ይዘት የለወጠ ሳይሆን የተጠሪዎች መብት በይርጋ የታገደ ነው አስተዳደሩም ውሳኔ ማረም አልቻለም የሚል አዲስ ፍሬ ነገር በማካተት የቀረበ ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት የብይን ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡ የሥር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ4ኛ ተጠሪ መጀመሪያ የቀረበው የፍርድ ቤቱ ሥልጣን ጥያቄ በተመለከተ በብይን ውድቅ ከተደረገ በኃላ አመልካች ክሳቸው በማሻሻላቸው ምክንያት ብቻ የራሱ ብይን መልሶ የሚሽረበት ሥርዓት አይኖርም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦ ውድቅ ካደረገው በኃላ የመቃወሚያው ባሕሪ ዓይነትና ይዘት ሳይለወጥ በተመሳሳይ ጉዳይ የራሱ ብይን መልስ በመሻር ጉዳዩን ለማየት የስር ነገር ሥልጣን የለኝም በማለት የመወሰን ሥልጣን የለውም፡፡

በዚህ ጉዳይ ሌላ መታየት ያለበት መሠረታዊ ነጥብ የአሁኑ 4ኛ ተጠሪ ባቀረበው ክርክር ካርታ ከመስጠት እና ከማምከን ጋር የተያያዘ ጉዳይ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም የሚል ነው፡፡ አስተዳደራዊ ተቋማት በሕግ ተለይቶ የተሰጣቸው ጉዳይ የመወሰን ሥልጣን እንዳላቸው የታወቀ ነው፡፡ ይሁንና ለአንድ ባለ ጉዳይ የተሰጠው ከርታ የተሰጠበት እና የተሻረበት አግባብ በሕግ አግባብ መሆን ያለመሆኑን አጠርቶ የመወሰን ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለ መሆኑን አጣርቶ የመወሰን ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታን የመሰረዝ ሥልጣን የአስተዳደሩ ክፍል ነው፣ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የጉዳዩ የክርክር ባህሪ እና ይዘት ያላገናዘበ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ክፍል የተሰጠው ካርታ የተሰጠበት ወይም የተሸረበት ሥርዓት እና አስተዳደራዊ ውሳኔው ሕግና መመሪያ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን በማጣራት ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን እንዳላቸው ከፍ/ህ/ቁ.1196 በህገ መንግስቱ ስለ ንብረት መብት

ከአደረገው ድንጋጌና በፍርድ የሚያልቁ ጉዳዮችን በተመለከቱ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

በማጠቃላል፡- የሥር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን እንዳለው መጀመሪያ ብይን መስጠቱ እየታወቀ ክስ ተሻሽሎ ከቀረበ በኃላ በዚህ ችሎት የተሰየሙት ሌላ ዳኛ በተመሳሳይ ምክንያት የችሎቱ ትዕዛዝ እንደ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመሆን ሽሮታል፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ስ/ስ//ሕ/ቁ. 244 እና 245 የተመለከቱት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ብይን አሰጣጥ እና ጉዳይ አመራር ሥርዓት ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች አቤቱታ በማሻሻላቸው ምክንያት ብቻ የክርክሩ ይዘት ሳይለወጥ ብይኑ አጥሮ እንደሚሻር በሚያስቆጥር አግባብ የመጀመሪያ ብይን እንደ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመሆን የሻረው በመሆኑ በሕጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤት የራሱ የሰጠው ብይን መልሶ መሻሩ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ይህንን ብይን ሳያርም በትዕዛዝ ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ጉዳይ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 191377 በ27/05/2005 ዓ/ም የሰጠው ብይን፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 134095 በ13/5/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ራሱ የሰጠው ብይን መልሶ የመሻር ስልጣን የለውም ብለናል፡፡ ካርታ የተሰጠበት እና የተሻረበት ሁኔታ በሕግ አግባብ መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ የመወሰን ሥልጣን የፍርድ ቤት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት የተዘጋው መዝገብ ቁጥር 191377 በማንቀሳቀስ በተሰጠው ብይን መሠረት ክርክሩን ከቆመበት ቀጥሎ ተገቢ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ ፡፡
4. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ተመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሩ/ለ**

# ኣግድ

የሰ/መ/ቁ.94481

ሐምሌ 01 ቀን/2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ፀሀይነሽ በቀለ ጠበቃ ደረጀ ኢተቻ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** ወ/ሪት ንግስት ተክላይ ጠበቃ ሌ/ክ/ስንታየሁ ደመቀ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የሽርክና ውል መሰረት በማድረግ የቀረበ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን አመልካች የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት ፡- በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተፈረመ የሽርክና ውል መኖሩን፤ ተጠሪ በሽርክና ውል ስምምነት መሰረት ለትርፍ ክፍፍል እንዲያመች የወጪና ገቢ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ እያላቸው አላቀረቡም ፡፡ ተጠሪ በውል የተረከቡትን የንግድ ድርጅት ሽርክና ውሉ ጊዜ ያለው በመሆኑ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 014 የሆነው የከሳሽ ድርጅትን እንዲያስረክቡ፤ የድርጅቱ ገቢና ሂሳብ ተሰርቶ በሂሳብ ስራው ውጤት ለአመልካች የሚደርሳቸው ትርፍ ወይም አመልካች በክሳቸው ባቀረቡት ግምት ብር 150,000 ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፈላቸው የጠየቁ መሆኑን የሚሳይ ነው፡፡

ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የመከላኪያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ፡- የሽርክና ውል የተባለው በህጉ የተቀመጠው መስፈርት አያሟላም፡፡ የንግድ ቤቱ ከሚመለከተው አካል የተከራዮት በመሆኑ አመልካች መጠየቅ አይችሉም፡፡ የመንግስት ቤት ለ3ኛ ወገን

በማከራያታቸው የተወሰደ እርምጃ ህጋዊ ነው፡፡ የሽርክና ውሉ የማስመሰል ውል ነው፡፡አከራይ የሆኑት አመልካች የጉልበትም ሆነ የገንዘብ አስተዋፆኦ ሳያደርጉ በመንግስት ቤት ብቻ ትርፍ ይክፈሉ የሚለው ውል ስለ ኪሳራ ተጠያቂነት የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ የሽርክና ማህበር ለማቋቋም የተቀመጡ መሰረታዊ ነጥቦች አልተሟሉም ሊጠየቅ አይገባም በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ የንግድ ማህበር በንግድ ህጉ መሰረት የሚቋቋምበት አግባብ በመለየት የንግድ ማህበር ስለመኖሩ የማስረዳት ግዴታው የሽርክና ማህበር ተመስርቷል፡፡ የሚል ወገን መሆኑ በመግለጽ፤ የሽርክና ውል ስምምነት በወረቀት ላይ መፃፍ ብቻውን የሽርክና ማህበር አለ ሊባል አይችልም፡፡የግራ ቀኙ ማስረጃዎች እንዲመዘንና የአመልካችም ምስክሮች የሽርክና ማህበር በውል ግንኙነት አለ ቢሉም የዚህ አይነት ግንኙነት መመስረት መሟላት አለባቸው የተባሉትን ሁኔታዎች በሙሉ ባሟላ መልኩ የተመሰረተ ግንኙነት ያላቸው መሆኑ ምስክሮች አላስረዱም፡፡አብሮ የመስራትና የመተባበር፣ትርፍ መከፈል የሚሉት ሁኔታዎች በግራ ቀኙ ያልነበሩ በመሆናቸው በዚህ የመንግስት ቤት የሚሰሩት ተከሳሽ /ተጠሪ/ ብቻ መሆናቸው ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ያቀረቡት የሽርክና ውል ስምምነት የተፈረመው ተከሳሽ /ተጠሪ/ቤቱን የተከራዩት በ2003 ዓ/ም ሆኖ እያለ ወደ ኂላ በመመለስ መሆኑን ተጠሪ በዚህ የንግድ ቤት የሚሰሩት የንግድ ቤቱን ተከራይተው መሆኑን የተከሳሹ /ተጠሪ/ ምስክሮች በተሻለ ሚዛን አስረድተዋል ፡፡ውሉ የሽርክና ውል ተብሎ መፃፍ ብቻውን ደግሞ ውሉ ወደ ኂላ ሳይሰራበት ተጽፎ እያለ በእርግጥ በግራ ቀኙ መካከል የሽርክና ማህበር ውል ተመስርቷል፡፡ ሊባል አይችልም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ የተባለ በመሆኑ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርጓል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ያነሱት መሰረታዊ ነጥብ የሽርክና ውል መቅረብ ባልተካደበት በሰው ምስክር ሰነዱን ማስተባበል ህጋዊ አለመሆኑን፣ በሽርክና ውል አብሮ መስራት እንደመስፈርት እንዳልተወሰደ፤ ሽርክና በቀጥታ በስራ ሳይሳተፉ አብሮ በሽርክና መስራት እንደሚችል አመልካች ከመንግስት የተከራዩት ቤት በመዋጮነት በማቅረብ /በመስጠት/ መስራታቸው ህጋዊ ነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከራቸውን ያሳያል፡፡ተጠሪ በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ ተደረገ የተባለው የሽርክና ውል ከመንግስት ተጠያቂነት ለማምለጥ የተደረገ ወደ ኂላ ተመልሶ የተፈረመ መሆኑን ተጠሪ ቤቱን በ2000 ብር ተከራይተው 4,000 መክፈላቸው፤ የአስተዳደር አካልም ጉዳዩ በማጣራት የአከራይ ተከራይ ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጡን፤ ተዋጣ የተባለው

ካፒታል እና የተጠየቀው ትርፍ /300,000 ብር/ የማይገናኝ ፣መሆኑ፤ ቤቱ የመንግስት ሲሆን አመልካችም ውጭ አገር የሚኖሩ፤ የመንግስት ቤት በመዋጮ መስጠት እንደማይቻል፤ ተደረገ የተባለው ውልም የሽርክና ውል በንግድ ህግ ቁጥር 211 የተመለከተው አስገዳጅ መስፈርት እንደማያሟላ በመግለጽ የስር ፍርድ ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ በአመልካች የቀረበው የመልስ መልስ አቤቱታውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የታዘዘ ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች ከተጠሪ አደረኩት ያሉትን የሽርክና ስምምነት በንግድ ህጉ የተጠቀሱትን መሰረታዊ መመዘኛዎች አያሟሉም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ በአግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት በሽርክና ውል ላይ የተመሰረቱ ስለመሆኑ አጥብቀው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው በግራ ቀኙ መካከል ያለው ግንኙነት አከራይ ተከራይ እንጂ በህግ አግባብ የተቋቋመ የሽርክና ውል የለም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ የሰውና የሰነድ ማስረጃ መመዘኑን በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ የነበራቸው ግንኙነት በሽርክና ውል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆን የአከራይ ተከራይ ግንኙነት ነው፡፡በሽርክና ውል መሰረት መተባበርና አብሮ የመስራት፤ ትርፍ መከፋል የሚሉት የሽርክና ማህበር ለማቋቋም እንደ መሰረታዊ መመዘኛ የሚወስዱት ነጥቦች አልተሟሉም፡፡ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የንግድ ቤት ተጠሪ ብቻ እንደሚሰሩ አረጋግጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣኑ የደረሰበት ድምዳሜ ይዘን ጉዳዩን ከህግ አንፃር መርምረናል፡፡

በመሰረቱ የሽርክና ማህበር በውል የሚቋቋም ሲሆን መሰረታዊ የማህበሩ ባህርያትም በአንቀጽ 211 ስር እንደተመለከተ ህጋዊ ሰውነት ያለው፤ በሽሪኮቹ የውል ስምምነት የሚቋቋም፤ ዓላማው ኢኮኖሚያዊ ተግባር ለማከናወን /ንግድ/፤ ሽሪኮች አብረው ለመስራትና ለመተባበር ተስማሙ፤ ከድርጅቱ የሚገኘው ትርፍም ሆነ ከሚመጣው ዕዳ ተከፋፋይ እንደሚሆኑ የሚስማሙበት ውል ስለመሆኑ ከላይ ከተመለከተው የህግ አንቀጽ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው ፡፡ የሽርክና ማህበር ሲቋቋም ሽሪኮቹ መዋጮ የማውጣት ግዴታ የተጣለባቸው ሲሆን መዋጮው በገንዘብ፣ በአይነት ወይም በጉልበት ሊሆን እንደሚችል በንግድ ህግ አንቀጽ 229 ስር የተመለከተ ሲሆን መዋጮውም ብዛታቸው እኩል እንደሆኑ እና ለማህበሩም የሚስማሙ መሆን እንዳለባቸው የዚህ

ድንጋጌ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ ያመላክታል፡፡ ማህበሩ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት ካለው በአይነት /ንብረት/ የተደረገው መዋጮ መልሶ መውሰድ እንደማይችል በንግድ ህግ አንቀጽ 269 /1/ ስር ተደንግጓል፡፡ አንድ የሽርክና ማህበር በህጉ አግባብ ተቋቋመ ለማለት የሚቻለው ተዋዋይ ወገኖች ተነፃፃሪ ሳይሆን ተደጋጋፊ የሆነ ግብ ይዘው መዋጮ በማዋጣት አብረው ከመስራትና በመተባበር፤ ትርፍና ኪሳራም በህጉ አግባብ እየተጋሩ ኢኮኖሚያዊ ተግባር ማከናወናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ከተጠሪ ጋር መሰረትኩት በሚሉት የሽርክና ማህበር በአዲስ ከተማ ክፍለ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 014 የሆነው የመንግስት ቤት በመዋጮነት በማዋጣት ፤ ተጠሪ ደግሞ በእራሳቸው ገንዘብ የተዘጋጁ ልብሶችና ጫማዎች ገዝቶ በማምጣት በጋራ ተቀናጅቶ ለመስራት የተስማሙ ስለመሆኑ በመዝገቡ ከተያዘው የሽርክና ውል መረዳት ይቻላል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ እንዳረጋገጠው ተጠሪ ቤቱን የተከራዩት በ2003 ዓ/ም ሁኖ ሳለ ውሉ ወደ ኋላ ተመልሶ 2002 ዓ/ም እንደተደረገ፤ ተጠሪ የንግድ ቤቱን ተከራይተው ተመስርቷል፡፡ ሊባል እንደማይችል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያመላክታል፡፡ በአመልካችና ተጠሪ ተፈረመ የተባለው ሽርክና ውል በጽሁፍ ብቻ መሆኑ የሽርክና ማህበር መቋቋሙን የሚያሳይ አይሆንም፡፡ የሽርክና ማህበር የንግድ ህግ አንቀጽ 211 እንደደነገገው በህጉ ተለይተው የተቀመጡ መሰረታዊ መስፈርቶች ማለትም አብሮ መስራትና መተባበር፤መዋጮ መኖር የትርፍና ኪሳራ ክፍፍል ስርዓት የተመለከቱ ነጥቦች በመሰረት ላይ በትስስር ሊገኙ ይገባል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ የሽርክና ውል ማቋቋሚያ ነጥቦች በተግባር አልተረጋገጠም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ የሚመረምር አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የሰበር ሰሚ ችሎቱ በህግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን ያለመሆኑን ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 /3/ /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በግራ ቀኙ ተደረገ /ተፈረመ/ የተባለው የሽርክና ውል እና ይህንን ተከትሎ መሬት ላይ ያለው እውነታ በስር ፍርድ ቤት እንደተጠራው የሽርክና ውል በጽሁፍ ከመደረጉ ውጭ የሽርክና ውል የሚጠይቃቸው መስፈርቶች አሟልተው ሲሰሩ እንደነበር አልተረጋገጠም ፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የሽርክና ማህበር በህግ አግባብ ተቋቁሞ እየሰራ ነበር ለማለት የሚቻለው የጽሁፍ ውል መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ግራ ቀኙ በጋራና በተናጥል በመተባበር በመስራት ከጥቅሙ ይሁን ዕዳው በጋራ ሲጋሩ እንደነበር በውል መንፈስና ይዘት የሚፈጽሙበት አግባብ የነበረ ስለመሆኑ የሽርክና ማህበሩ የነበረበት ነባራዊ ሁኔታ ይህንን እንደማያሳይ የስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን በስልጣናቸው ከድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተመሰረተ የሽርክና ማህበር ውል የለም ማለታቸው በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን የማያሳይ ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/197575 በ19/07/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/135286 በ30/11/2005 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል፡፡
2. በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተመሰረተ የሽርክና ማህበር ውል የለም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ተ**

የሰ/መ/ቁ.96990

ሐምሌ 01/2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ አያሌው ወልዴ ዩሐንስ - ጠበቃ ስንታየሁ ባሕሩ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጀማል ሰማን ኑር - ጠበቃ አማኑል ኩመራ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሽርክና ውል ስምምነት የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካች የቀረበው ክስ ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታይልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከነበረው በአዲስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 1088 ተከራይተው ሲሰሩ እንደቆዩ፤በዚህ ቤት በሥር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ /የአሁኑ ተጠሪ/ ከነበረው ሰኔ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተፈፀመ የሽርክና ውል የቁርስ ቤት ንግድ ሥራ በጋራ ሲሰሩ የነበሩ ሲሆን አስተዳደሩ የአከራይ ተከራይ መመሪያው ያለአግባብ በመተርጎም ለተጠሪ አከራይተሃል በማለት የኪራይ ውል ማቋረጡን በአግባቡ አይደለም፡፡ተጠሪም የንግድ መደብሩ ያለአግባብ ይዘው ስለሚገኙ እንዲለቁ፤በተፈፀመው የሽርክና ውል ግዴታ መሠረት ውሉን ለማፍረስ የሞከሩ ስለሆነ የገደብ መቀጮ ለአመልካች ብር 10,000.00 ለመንግሥት ብር 5,000 እንዲከፍሉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት የመከላከያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱ ፡- በአመልካች እና ተጠሪ ተደረገ የተባለው የሽርክና ውል በንግድ ሕጉ መሠረት የማይታወቅ ነው፡፡ የተደረገ መዋጮ የለም፡፡የንግድ ቤቱን ሰኔ 21 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ውል መከራየታቸው ፤በየወሩም 2500 ብር እንደሚከፍሉ፤የሽርክና ውል የፈረሙት አመልካች ስለአስፈራሩዋቸው በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም ?የሚለው በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ ተደረገ የተባለው የሽርክና ውል በሕጉ አግባብ የተመሰረቱ ስለመሆኑ ጉዳዩን ለማጣራት የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ የሰውና የሰነድ ማስረጃ መርምሮ የሽርክና ውል የለም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጣቸው መሠረታዊ ነጥቦች የሽርክና ስምምነቱ በጽሑፍ ከመደረጉ በቀር አብሮ የመሥራት የመተባበር እንዲሁም የትርፍና ኪሣራ ክፍፍል ሥርዓት ምን እንደነበር የተገለጸ ነገር የለም ሲል በውሳኔው አስፍሯል፡፡ በመሠረቱ አንድ የሽርክና ማህበር የሚቋቋመው በንግድ ሕግ አንቀጽ 10/1/ እንደተመለከተው የንግድ ሥራ ለማከናወን ሲሆን ፣ የንግድ ሥራ ምን እንደሆነም በዚህ ሕግ አንቀጽ /5/ ሥር ተዘርዝሯል፡፡ የንግድ ማህበር /ሽርክና/ትርጓሜ መሠረታዊ ባህርያት በንግድ ሕግ አንቀጽ 210/1/ እና 211 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የሽርክና ማህበር ሕጋዊ ሰውነት ያለው በሽርኮቹ ውል የሚቋቋም ዓላማውም ኢኮኖሚያዊ ተግባር ለማከናወን ስለመሆኑ፤ሽርኮቹም አብረው ለመሥራትና ለመተባበር የተስማሙ፤ከሚገኘው ትርፍም ሆነ ከሚመጣው ዕዳ ተከፋይ እንደሚሆኑ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 211፣215 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ ሽሪኮቹ የመዋጮ ዓይነት ልክ መወሰን እንደሚችሉ፤መዋጮው በገንዘብ ፣በዓይነት ወይም በጉልበት ሊሆን እንደሚችል ፤ይሁንና የመዋጮው ዓይነት ልክ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር መዋጮዎቹ ብዛታቸው እኩል እንደሚሆን፤ለማህበሩ ዓላማ የሚስማሙ እንዲሆኑ እንደሚያስፈልግ የንግድ ሕግ አንቀጽ 229/2/ በግልጽ ደንግጓል ፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመልስ የሥር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ሥልጣኑ በአመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮች ከተጠሪ ጋር የሽርክና ውል ተፈራርመዋል ያሉ ቢሆንም ውሉ ሲፈረም የሽርክና ውል ስምምነቱ መዋጮ ምን ያህል እንደሆነ እንደማያውቁ በአንፃሩ በተጠሪ በኩል የቀረቡ ምስክሮች ከ1997 ዓ.ም እስከ አሁን ድረስ ሱቁን ተከራይቶ ይሰራ እንደነበር የሽርክና ውሉም ሊዋዋል መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ እንዲሆን ማመልከታቸውን ያሳያል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል በሕግ አግባብ የተቋቋመ የሽርክና ማህበር የለም ፡፡ በተጠሪ የቀረቡ ምስክሮች የግራ ቀኙ ግንኙነት የአከራይ ተከራይ መሆኑን ሚዛን በሚደፋ መልኩ ማስረዳት የቻሉ መሆናቸው ችሎቱ

መገንዘቡን በመግለጽ የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጐታል። አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም ። ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓል።አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የግራ ቀኙ ግንኙነት በሽርክና ውል የተመሰረቱ ስለ መሆኑ አመልካች ድርጅቱ ከነ ፈቃድ እና መልካም ስምና ዝናው ሊያዋጡ ተጠሪ ደግሞ የመነገጃ ገንዘብ እንዳቀርቡ ፤የሽርክና ውሉ አለመመዝገቡ ውድቅ እንደማይሆን እንደ የእሽሙር ማህበር ሊወሰድ እንደሚገባ፣የ73 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ እና ሌላ የገቢ ምንጭ የሌላቸው መሆናቸው የአከራይ ተከራይ ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 4/2004 ዓመት ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባቸው በመግለጽ ተከራክሯል። ተጠሪ በበኩላቸው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነት የአከራይ ተከራይ መሆኑን አስተዳደሩ ማጣራቱ ፤አመልካች የሽርክና ማህበር ለመመስረት የሚያስችል ምንም ያዋጡት ነገር አለመኖሩን ፣የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በማጣራት መወሰኑ ፤የመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተጠቃሚነኝ የሚለው ክርክር መቅረብ የነበረበት ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች መሆኑን፤የሥር ፍርድ ቤቶች የሽርክና ውል የለም በማለት መወሰናቸው በአግባቡ ነው፣ሊጸና ይገባል በማለት መልስ ያቀረቡ መሆኑን ተረድተናል ።የአመልካች የመልስ መልስም አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ነው።

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር፤ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመርነውም የሥር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል ተፈረመ የተባለው የሽርክና ውል በንግድ ሕግ የተመለከቱት መሠረታዊ መመዘኛዎች ያሟላ አይደለም በማለት ውድቅ ሊያደርግ የቻለው ከሳሽ/አመልካች/ ውሉን ካልፈረምክ ከሱቁ አስወጣሃለው በሚል አስገድደውት እንደሆነ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት የአከራይ ተከራይ ግንኙነት መሆኑን የሽርክና ስራ እንደማይሰሩ መመስከራቸውን ውሣኔው ማስፈሩን ተረድተናል።የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ያረጋገጠውን ጉዳይ ይዘን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር ስናገናዝበው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የንግድ ሕጉ በደነገገው አግባብ በጋራ መስራትና መተባበር ፤መዋጮ ስለመኖሩ ፤ከድርጅቱ ከሚገኘው ትርፍ የተደረገ ክፍፍል ስለመኖሩ የቀረበ ክርክር የለም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ በግራ ቀኙ የተደረገው የሽርክና ውል በንግድ ሕግ አንቀጽ 211 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተመለከቱት አስገዳጅ መመዘኛዎች ስለመሟላታቸው በሕጉ አግባብ የቀረበ ክርክር የለም። በመሆኑም በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ተመሰረቱ የተባለው የሽርክና ማህበር በንግድ ሕጉ በተመለከተው የሽርክና ማህበር ማቋቋሚያ መስፈርት ያልተቋቋመ በተግባርም መሬት ላይ የሌለ መሆኑ ከአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት መረዳት

ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ግንኙነት በሽርክና ውል ላይ የተመሰረተ ሳይሆን የሥር ፍርድ ቤት እንዳለው የአከራይ ተከራይ ግንኙነት ነው፡፡

አመልካች በሰበር ቅሬታቸው የተደረገ መዋጮ መኖሩ፣የትርፍ ክፍፍል ስለመደረጉ እና ሽርክናው በ 3ኛ ወገን አለመታወቁ ውጤቱ የአሽሙር ማህበር የሚመለከት እንደሆነ ፍርድ ቤት ግንዛቤ አለመወሰዱን ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ግራ ቀኙ ግንኙነት በሽርክና ውል ላይ የተመሰረቱ ስለመሆኑ ተደረገ የተባለው ስምምነትም አረጋጋጭ በማድረግ አቅርበዋል፡፡የአመልካች የክርክር መስመር ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ ከተያዘው ጭብጥ የሚጣጣም ካለመሆኑ በተጨማሪ የሽርክና ውል በቀረበበት ሁኔታ ስለመዋጮ እና የትርፍ ክፍፍል ሥርዓት በተመለከተ ግን ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደ እሽሙር ማሕበር ግንዛቤ እንዲወሰድ ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የለውም፡፡በሌላ በኩል አመልካች አቅመ ደካማና የ73 ዓመት ዕድሜ ባለፀጋ በመሆናቸው የመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6.1 ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚገባ በሰበር አቤቱታቸው ገልጸዋል፡፡ በመሠረቱ አመልካች ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329(1) ሥር የተመለከተው ፍሬ ሐሳብ ያላገናዘበ ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የመመሪያው ልዩ ተጠቃሚ መሆን ነበረብኝ በማለት ያቀረቡት ክርክር በግራ ቀኙ ነበረ ከተባለው የሽርክና ውል ስምምነት የማይጣጠም ነው፡፡ጉዳዩም መቅረብ ከነበረበትም ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ነው በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ ማድረጋቸውን በሕግ አተረጓጎምና አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸማቸውን አያሳይም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.194434 በ12/09/2005 የሰጠው ፍርድ፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.138064 በ 21/02/2006 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል ፡፡
2. በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተመሰረቱ የሽርክና ማሕበር የለም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>**ት እ ዛ ዝ**</u>

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ብ**

የሰ/መ/ቁ. 100621

ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡- አቶ ሉልሰገድ ምጀ- ጠበቃ ደሳለኝ ድረስ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- 1. አንድነት ቅቤና ቅመማቅመም ነጋዴዎች /አ.ማ/ ጠበቃ ይልማ አቻሜ ቀረቡ

2. ወ/ሮ አለምፀሐይ ሞጀ

**መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 205328 ህዳር 13 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150124 መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ይርጋ የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ የሚወለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ እናቱን ወ/ሮ አማራች ኦዳ በቀድሞው ወረዳ 5 ቀበሌ 06 በአዲሱ አጠራር አዲስ ከተማ 10/11/12/ የመደብ ቁጥሩ 1 የሆነ የቅቤ ንግድ ችርቻሮ የሚነግድበት መደብ ነበራቸው በአካባቢው ያሉ ነጋዴዎች ተደራጅተው አክሲዮን ማህበር 1990 ዓ.ም ሲመሰርቱ እና የአንደኛ ተከሳሽ መሥራች አባል ሆነው አንድ የአክሲዮን ድርሻ ነበራቸው፡፡ እናቴ ወ/ሮ አማረች ኦዳ ታህሳስ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፡፡ ሆኖም እናቴ ታህሳስ 27 ቀን 1997 ዓ.ም መሞቷ እያታወቀ አንደኛ ተከሳሽ መጋቢት 24 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የአክሲዮን ማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ

በህይወት እንደለች በማስመሰል ስሜን በአባላት ሥም ዝርዝር ላይ በመፃፍና ሀሰተኛ ቃለ ጉባኤ በማዘጋጀት በአክሲዮን ማህበሩ የነበረትን አንድ የክሲዮን ድርሻ ለሁለተኛ ተከሳሽ እንደሸጠች አድርጕ የአክሲዮን ባለቤትናቱን ለሁለተኛ ተከሳሽ አዛውሯል፡፡ ይህንን በሀሰት የተከናወነ ተግባር የተፈፀመ መሆኑን ያወቅሁት በጥቅምት ወር 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ሀሰተኛ ቃለ ጉባኤ ተሽሮ የአክሲዮን ድርሻው የወ/ሮ አማረች ኦዳ ወራሽ በሆንኩት በከሳሽ ስም እንድመዘገብ ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

2. ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በከሳሽ እናት ስም የነበረው የክሲዮን ድርሻ ለሀለተኛ ተከሳሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ የተወሰነው መጋቢት 24 ቀን 1998 ዓ.ም ነው፡፡ የአንደኛ ተከሳሽ ባለ አኪስዮኖች ጉባኤ ቃለ ጉባኤ የካቲት 9 ቀን 1999 ዓ/ም  በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ቀርበው ተመዝግቧል፡፡ ከሳሽ ቀለ ጉበኤው እንዲሻር መጠየቅ የሚችለው መጋቢት 24 ቀን 1994 ዓ/ም ጀምሮ ወይም ቃለ ጉባኤው በተመዘገበበት የካቲት 9 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ነው ከሳሽ ጥያቄ ያቀረቡት ሚያዚያ 15 ቀን 2005 ዓ/ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተከሳሾች ያቀረቡት መቃወሚያ የንግድ ህግ ቁጥር 4/6(2) መሠረት ያደረገ ነው በማለት የከሳሽ ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች ግንቦት  4 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በንግድ ሕግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀጽ 2 በያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ጉዳዩ የወንጀል ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን የሚያሳይና የወንጀል ምርመራ እየተጠራ በመሆኑ የይርጋው የጊዜ ገደብ በወንጀል ህጉ የተመለከተው አስራ አምስት ዓመት መሆን አለበት ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በስር ታይቶ ይሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች ሀምሌ 02 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት መልስ የሚች እናት አክሲዮኑን የሸጡት የካቲት 21 ቀን 1996 ዓ/ም ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በንግድ ህጉ ቁጥር 416 (2) የተመለከተው የሶስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሀምሌ 22 ቀን 2006 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጡት ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ክስ ያቀረበው፣ አንደኛ ተጠሪ ተህሳስ 27 ቀን 1997 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችውን ወላጅ እናቴ፣ በህይወት ያለች በማስመሰልና መጋቢት 24 ቀን 1998 በተደረገው የባለአክስዮኖች ጉባኤ ስሟን በመመዝገብ ሀሰተኛ የሆነ ቃለ ጉባኤ በማዘጋጀት የእናቴን ድርሻ ለሁለተኛ ተጠሪ እንዲተላለፍ በመወሰን የአክሲዮን ድርሻዎን ለሁለተኛ ተጠሪ አስተላልፏል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ይህንን ተግባር የፈፀመ መሆኑን ያወቅሁት በጥቅምት ወር 2005 ዓ/ም በማለት ነው፡፡ ይህም የአመልካች ጥያቄ አንድ ሰው የሲቪል መብትና ግዴታ የሚኖረው ከተወለደበት ቀን  አንስቶ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ መሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1 የተደነገገ ሆኖ እያለ አንደኛ ተጠሪ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለያች በኃላ እናቴን በባለአክሲዮኖች ጉባኤ ላይ እንደተገኘች አድርጎ በሀሰት በመመዝገብ የአክሲዮን ድርሻ ዝውውር ፈፅሟል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

6. አንድ ሰው የሲቪል  መብትና ግዴታ የሚኖረው በህይወት ባለበት ጊዜ መሆኑ ሚች ከዚህ ዓለም በሞት ከተለያየ በኃላ በሚች መሞት የማይቋረጡ መብቶችና ግዴታዎች ለወረሾቹ የሚተላለፍ መሆኑ በፍተብሔር ህግ ቁጥር 1 እና በፍትሐብሔር ህግ ቀጥር 826 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ ማናቸውም አክስዮን ማህበር፤ በመመሥረቻ ፅሑፍም ሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ ወይም በባለአክሲዮኖች ጉባኤው በህይወት የሌለ የአክስዮን ባለ ድርሻ በህይወት እንዳለ ተደርጎ በባለአክሲዮን ጉባኤ ላይ ስሙ እንዲመዘገብና በለ አክሲዮኑ ከሞተ በኃላ የባለ አክሲዮኖች ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ በህይወት እንዳለ ተቆጥሮ እንዲፈፀምበት ለመደንገግ መብትና ሥልጣን የለውም፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካች የሚያቀርበው ጥያቄ በሚች ምትክ የሚችን ወራሽ መጥረትና በባለአክሲዮኖች ጉባኤ እንዲሳተፍ ማድረግ ሲገባው የአክሲዮን ማህበሩ መሥራች የሆነችው ወላጅ እናቴ በሞት የተለያች መሆኑን እያወቀ በሞት ከተለየች ከአንድ ዓመት በኃላ በግል አክሲዮኖች ጉባኤ ላይ እንደተገኘች አድርጎ ስሟን በመመዝገብና የሀሰት ቀለ ጉባኤ በማዘጋጀት የፈፀመው የአክሲዮን ድርሻ ዝውውር ፈራሽ ይሁንልኝ በማለት ነው፡፡

7. ይህ የአመልካች ጥያቄ ህግ አውጭው በንግድ ህግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀፅ 2 የሶስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ ሲደነግግ ተሳቢ ካደረጋቸው ጉዳዮች ጋር አንድ አይነት ካለመሆኑም በላይ አንድ አክሲዮን  ማህበር ባለ አክሲዮኑ ሲሞት የባለአክሲዮኑ ወራሾች ሣይጠሩ የሞተውን ባለ አክሲዮን በባለአክሲዮን ጉባኤ ላይ የተገኘ በማስመሰል የወራሾቹን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ውሣኔ ቢወሰን ወራሾች የባለአክሲዮን ጉባኤ የተደረገ መሆኑንና የባለአክሲዮኖች ጉባኤ የእነርሱን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ውሣኔ መወሰኑና ቃለጉባኤውን ማስመዝገቡን እንዴትና በምን ሁኔታ ያውቃሉ? ወራሾች ይህንን ሣያውቁ በንግድ ህግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተው የጊዜ ገደብ ቢያልፍ ሁኔታውን ለማስቀየር በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ አለባቸው የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሣ ነው፡፡

8. አንድ ሰው በፍርድ መብቱን ለማስከበር ጥያቄ የሚያቀርበው መብቱ ከተጣሰበት ወይም በመብቱ ሊሰራበት ከሚችልበት ቀን ጀምሮ መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1846 ተደንግጓል ፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ያቀረበው ጥያቄ በንግድ ህግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀፅ 2 በተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆን አይደለም ፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ጉዳዩን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር ዓመታት ውስጥ የአክሲዮን ማህበሩን ጥያቄውን በማቅረብና በክፉ ልቦና የአክሲዮን ድርሻው ተላልፎላቸዋል የሚላቸውን ሰዎች ላይ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻል መሆኑ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1677 ንዑስ አንቀፅ 1 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1845 በጣምራ በመተርጎም ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ጥያቄውን ያቀረበው ከላይ የገለፅነው የአስር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ሳያልፍበት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ላቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አግባብነት የሌለውን የንግድ ህግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀፅ 2 በመጥቀስ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል ፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይንና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ወስነናል ፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ አመልካችና ተጠሪ በሌሎች ነጥቦች ያቀረቧቸውን ክርክሮችና የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሩ/ለ**

የሰ/መ/ቁ.102725

ሐምሌ 14 ቀን2007ዓ.ም

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች-** 1.አቶ ዲንሳፋ ያዕቆብ - ከጠበቃ ታረቀኝ ተፈራ ጋር - ቀረቡ

2. ወ/ሮ መሰለች አባመላ - ቀረቡ

3. የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ጽ/ቤት

ነ/ፈጅ ሽመልስ ኃ/ጊዮርጊስ - ቀረቡ

**ተጠሪ:-** ወ/ሮ አየለች በቀለ - ከጠበቃ ግርማ ዘመድኩን ጋር - ቀረቡ

በዚህ መዝገብ እና ቁጥሩ 103457 እንዲሁም 103944 በሆኑት መዛግብት የቀረቡት ክርክሮች በበታች ፍርድ ቤቶች አንድ ላይ የታዩና የሚያስነሱት የሕግ ጥያቄም ተመሳሳይ በመሆኑ ተጣምረው ተመርምረው የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁኖቹ አመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ሲሆን የክሱም ይዘት ባጭሩ ከ3ኛ ተከሳሽ የንግድ ቤት ከ1967 ዓ/ም ጀምረው ተከራይተው እየሰሩበት ያሉትን የንግድ ድርጅት ከመስከረም ወር 2000 ዓ/ም ጀምሮ ለአቶ ዲንሰፋ ያእቆብ በወር ብር 3500.00፣ለአሁኗ 2ኛ አመልካችም በወር በብር 800.00 ያከራዩ መሆኑን፣የአሁኑ 3ኛ አመልካች ደግሞ ከተጠሪ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል አቋርጦ ለ1ኛ አመልካች ኪራዩን ማስተላለፉን፣ተጠሪ ለ1ኛ አመልካች ያከራዩት የንግድ ድርጅት እንደሆነና ይህም በሕጉ የተፈቀደ ከመሆኑም ንግድ ቤቱን ያከራዩት ባለባቸው የጤና ችግር ተንቀሳቅሰው ሊሰሩ ባለመቻሉና በዚህ ንግድ ቤት በሚገኝ ብቻ የሚተዳደሩ መሆኑን ጠቅሰው 3ኛ አመልካች የፈጠረው ሁከት ተወግዶ በቤቱ ላይ የተከራይነት መብት ተጠብቆላቸው

መጠቀም እንዲቀጥሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል። የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ተጠሪ በቤቱ ላይ የነበራቸው የኪራይ ውል የተቋረጠ በመሆኑ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ከአስቀደሙ በኋላ በፍሬ ነገሩ ደግሞ ከተጠሪ የተከራዩትን ቤት ለሁለት ከፍለው በማከራየታቸው በመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተግባራዊ ሲደረግም በቤቱ እየተጠቀሙ የነበረ በመሆኑ ተከራይነታቸው የተረጋገጠላቸው መሆኑን፣የአሁኗ 2ኛ አመልካች ሲሰሩበት የነበረው ክፍል ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን የተደረገ መሆኑንና ይህን ደብቀው ምንም ገቢ የለኝም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢነት የሌለው መሆኑንና 3ኛ አመልካችም ያስተላለፈላቸው በመመሪያው አግባብ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፤፤ 2ኛ አመልካች በበኩላቸው ተጠሪ የቤት ቁጥር 073 የሆነውን በከፊል አከራይተዋቸው ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ እየተገለገሉበት ያለ መሆኑን፣3ኛ አመልካችም በወረደው ዲዛይንና ግንባታ ፅ/ቤት በኩል ቤቱን ለተጠሪ፣ለ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ሊተላለፍ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ወደ ጎን በመተው ለ1ኛ አመልካች እንዲተላለፍ መወሰኑ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፤፤

የአሁኑ 3ኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ውል የሌላቸው በመሆኑ ክስ ለመመስረት መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን፣ተጠሪ ሁከት እንዲወገድላቸው ያቀረቡት ሱቅ በክሱ ጊዜ በይዞታቸው ስር ያልነበረ በመሆኑ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ፣ተጠሪ ቁጥሩ 073 የሆነው ቤትን ሸንሽነው ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፉ በመሆኑ አንደኛውን የተሸነሸነውነ ተጠሪ እንዲሰሩበትና በሌላው ላይ የአሁኑ 1ኛ አመልካች እንዲሰሩበት የተደረገው መመሪያውን መሰረት በአደረገ መልኩ መሆኑን፣ተጠሪ በመመሪያው በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ስለመሆኑ ማስረጃ ያለማቅረባቸውንና አቅመ ደካማ ቢሆኑ እንኳን በመመሪያው መሰረት ራሳቸው የሚሰሩበትን ክፍል ብቻ እንዲፀድቅላቸው የሚያደርግ ስለመሆኑና በዚህም መሰረት አመልካች ተጠሪ አንድ ሸንሻኖ ላይ እንዲሰሩበት ተወስኖ የኪራይ ውል እንዲዋዋሉ ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል።

የስር ፍርድ ቤትም በ1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የቀረቡትን መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክርና የተጠሪን ምስክሮችን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ ለ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ያከራዩት የንግድ መደብር ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ያለፈው ሲሆን የኪራይ ውል ተጠቃሚነትን በተመለከተ ግን ተጠሪ አቅመ ደካማ፣የቤተሰብ አስተዳዳሪና ሌላ ገቢ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦአል በሚል ድምዳሜ እና የ3ኛ አመልካች ተግባርም በመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀፅ 6(2) ስር በልዩ ሁኔታ የተቀመጠውን የተጠሪን ተጠቃሚነት የሚፃረርና የሁከት ተግባር ነው በማለት ተጠሪ ቁጥሩ 073 የሆነውንና በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቤት ተጠሪ በሙሉም ሆነ በከፊል እንዲለቁ የተደረገው ተግባር እንዲቆምና ለተጠሪ

እንዲመለስላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለየብቻቸው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የአሁኗ 2ኛ አመልካች ግን መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ መዝገቦቹን በተናጠል መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፤፤ የ1ኛ እና 2ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ሲታይም ተጠሪ ከ3ኛ አመልካች የተከራዩትን የንግድ ቤት ሸንሽነው አከራይተው በመገኘታቸው በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት አንድ ሸንሻኖ ክፍል እንዲቀርላቸው ተደርጎ በመስራት ላይ የሚገኙ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ቁጥሩ 073 የሆነው ቤት ሙሉ በሙሉ ለተጠሪ እንዲመለስላቸው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን 2ኛ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ደግሞ በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ መሆን ሲገባቸው ይኼው ታልፎ የተከራይነት መብቱ ለ1ኛ አመልካች ብቻ ተጠብቆ በሌላኛው ክፍል ተጠሪ እንዲሰሩበት በአስተዳደሩ መወሰኑ ተገቢነት የሌለው ነው የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ሲቀርብ ከተያዙት ጭብጦች አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ ጉዳዩ ሲቀርብ የተያዙት ጭብጦች፡-

1. ጉዳዩ በሁከት ይወገድልኝ ክስ መቅረቡና በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመታየቱን አግባብነት እና
2. ተጠሪ ከሸነሸኑት ቤት በአንዱ እንዲጠቀሙ የተመለሰላቸው ሁኖ እያለ ገቢ የላቸውም ተብሎ አከራካሪውን የንግድ ቤት ሙሉ በሙሉ ሊጠቀሙ ይገባል ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?የሚሉት ናቸው፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ጭብጦች አንፃር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

<u>**የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u> ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክስ የመሰረቱት ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ጋር ያለኝ ግንኙነት የንግድ መደብር ኪራይ ውል ከመሆኑም በላይ በመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተጠቃሚነቴ ሊጠበቅልኝ ይገባል በማለት ነው፡፡1ኛ እና 3ኛ አመልካች ደግሞ ተጠሪ ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ጋር በቤት ቁጥር 073 ያላቸው ግንኙነት የንግድ መደብር ኪራይ ውል አለመሆኑንና በመመሪያው መሰረትም ልዩ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠላቸው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በቀጥታ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ቢሆንም 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በመካከላቸውን ያለውን ግንኙነት የንግድ መደብር አይደለም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ግንኙነቱ የንግድ

መደብር ኪራይን መሰረት ያደረገ ነው የሚል ክርክር አቅርበው ይሄው ጭብጥ ተይዞ የተጠሪ የመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተጠቃሚ መሆን ያለመሆን ጭምር እልባት ያገኘ መሆኑን የክርክሩ ይዘት ያስገነዝባል፡፡

መመሪያውን መሰረት አድርጎ የሚነሳ የንግድ ቤት የተከራይነት መብት ጥያቄ ከከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣን እና ተግባር ጋር እንዲሁም የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር የተያያዘ እስከሆነ እና የከተማው አስተዳደር አካልም በተከሳሽነት የተሰየመ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ተቀብሎ የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር በአንቀጽ 41(1) (ለ) እና (ሬ) ስር በግልጽ የተመለከተ ነው፡፡

የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በቀጥታ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪን የመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተጠቃሚት ጥያቄን ከንግድ መደብር የዳኝነት ጥያቄ ጭምር በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው ተገንዝቦ ጉዳዩን መመልከቱ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም የክሱ ዝርዝር ይዘት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች አግባብ የሚታይ የሁከት ጉዳይ ሳይሆን ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈፃጸም ጋር የተያያዘና በዋንኝነትም የንግድ መደብር ኪራይ መኖር ያለመኖሩን ሁሉ የሚያካትት ክርክር በመሆኑ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ መታየቱ ከውጤት አንጻር ሲታይ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡-ተጠሪ ከ3ኛ አመልካች የተከራዩትን የንግድ ቤት ከአከራዩ ፈቃድና እውቅና ውጪ ለ1ኛ አመልካች አከራይተው መገኘታቸው ተረጋግጦአል፡፡ አመልካች ለ1ኛ አመልካች አከራየሁ የሚሉት የንግድ መደብሩን ነው ይበሉ እንጂ ይህ ስለመሆኑ ማስረዳት አለመቻላቸውን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ 2ኛ አመልካች የተጠሪ ልጅና ቤቱ ተሸንሽኖ ከተገኘው አንዱ ክፍል በተጠሪ ንግድ ፈቃድ የሚሰሩና የተጠሪ ልጅ መሆናቸው ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ የተደረገው ክርክር፣በሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር የሚያስረዳ ሲሆን 2ኛ አመልካች የተጠሪ ልጅ ያለመሆናቸውንና ይሰሩበት የነበረው የንግድ ፈቃድም የተጠሪ ያለመሆኑን በሚመለከት የቀረበ ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡ እንዲሁም 2ኛ አመልካች በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር መልስ ሰጪ የሆኑት የአሁኑ 1ኛ አመልካች ባስከፈቱት የይግባኝ መዝገብ ሲሆን በዚህ መዝገብ በሰጡት መልስም 1ኛ አመልካች በመልስ ሰጪነት ያስጠሩት በማይመለከታቸው ጉዳይ ስለመሆኑ ጠቅሰው ይግባኙ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልስ ከመስጠታቸው በተጨማሪ በመስቀለኛ ይግባኝ ደግሞ ቤቱ ለሶስት

ተከፍሎ ራሳቸው የያዙት ክፍል ግን በራሳቸው ይዞታ እንዲቀር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 142239 ከተሰጠው ውሳኔ ይዘት ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም 2ኛ አመልካች የተጠሪ ልጅ ከመሆናቸውን በላይ በተጠሪ የንግድ ፈቃድ የሚሰሩ መሆናቸውንና እንዲሁም ከተጠሪ ጋር ያላቸው የተከራይነት ግንኙነት ስላለመሆኑ በግልጽ ያልተካደ ጉዳይ መሆኑን ከክርክር አቀራረብ ሂደት ተገንዝበናል፡፡በሌላ በኩል 1ኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያላቸው ግንኙነት የተከራይ ተከራይነት መሆኑና የሚሰሩትም በራሳቸው የንግድ ፈቃድ መሆኑ አከራካሪ የሆነ አይደለም፡፡3ኛ አመልካችም ተገቢው ግብረሃይል ተቋቁሞ ጉዳዩን አጣርቶ ባቀረበትና በመመሪያው መሰረት በተዘረጋው ስርዓት አግባብ በጸደቀው የአስተዳደር ውሳኔ መሰረት 1ኛ አመልካች የያዙት ክፍል በመመሪያው መሰረት ተላልፎላቸው ቀሪውን ክፍል በተመለከተ ግን ተጠሪ እንዲጠቀሙ ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በመመሪያው በተዘረጋው ስርዓት መስረት የተሰጠውን አስተዳደራዊ ውሳኔ በአስተዳደር አካሉ አልተወሰነም ወይም በበላይ አካል የተሻረ ነው በማለት ክርክር ሳያቀርቡ አጥብቀው የሚከራከሩት አቅመ ደካማና ገቢ የሌለኝ በመሆኑ 1ኛ አመልካች የያዙት ክፍል ጭምር ሊወሰድብኝ አይገባም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ተጠሪ አቅመ ደካማና ከአስተዳደሩ በተከራዩት ቤት አከራይተውና ሰርተው ከሚያገኙት ገቢ ሌላ ገቢ የሌላቸው መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዳለ የሚቀበለው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አቅመ ደካማና ገቢ የሌላቸው መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ የምንቀበለው ሲሆን ይህ ነጥብ ተይዞ በሕግ ጥያቄነት ሊታይ የሚገባው ግን አከረካሪው ቤት ለተጠሪ ሊመለስላቸው የሚገባው ሙሉ በሙሉ ነው ወይስ በከፊል ነው የሚለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ተጠሪ አድራጎታቸው በመመሪያው አግባብ በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ ሊያደርገኝ ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ምንም ገቢ የሌለኝ ስለመሆኑ ተረጋግጧል የሚል ምክንያት ነው፡፡ይሁን እንጂ በተጠቃሹ የመመሪያው ድንጋጌ ከተመለከተው ዝርዝር የልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ የሆነው ምንም ገቢ የሌለው መሆን ብቻውን ተቀባይነት የለውም፣ምንም ገቢ የሌለው መሆን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሁኔታዎችም ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡በዚሁ ድንጋጌ አቅመ ደካማ፣አዛውንት፣ወይም ወላጅ ያጡ ሕጻናት፣የኤች አይ፣ቪ ህመምተኞችና የአልጋ ቁራኞች የሚሉት ሁኔታዎች ተዘርዝረው ሌሎች የገቢ ምንጮች እንደሌላቸው ከሚመለከተው ሕጋዊ ተቋም ማስረጃ ካቀረቡ" ከሚለው ዓረፍተ ነገር ጋር “ከሆኑና” በሚለው ቃል ጭምር መያያዛቸው ገቢ ያለመኖር ብቻውን የልዩ ተጠቃሚነት መብትን የማያስገኝ መሆኑን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም ምንም ገቢ ካለመኖር በተጨማሪ አቅመ ደካማ፣አዛውንት፣ወይም

ወላጅ ያጡ ሕጻናት፣የኤች አይ፣ቪ ህመምተኞችና የአልጋ ቁራኞች ከሚሉት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ መገኘት አለበት፡፡ስለሆነም ምንም ገቢ ያለመኖር ከሌሎች ሁኔታዎች ጋር ድርብ ማሟያ ምክንያት እንጂ ብቻውን መገኘቱ በቂ ያለመሆኑን የድንጋጌው ይዘት የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ምንም ገቢ ያለመኖር ብቻውን በቂ ነው ተብሎ እንዲወሰድ ማድረግም መመሪያው የወጣላትን መሰረታዊ አላማ ያሳካል ተብሎ የማይታሰብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡የመመሪያው መሰረታዊ አላማ በመንግሰት ቤቶች ላይ በተከራዮች የተፈጠረውን ችግር መቅረፍና የመላውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ መሆኑን የመመሪያው መግቢያ ያስረዳል፡፡ ገቢ የሌለውና ከላይ የተመለከቱትን የመመሪያውን መስፈርቶችን የሚያሟላ ተከራይ የመንግስትን ቤት ሸንሽኖ ማከራየቱ ከተረጋገጠ ደግሞ አፈጻጸሙ ከኑሮው መተዳደሪያ ሊሆን የሚችል ክፍል ቀርቶ ሌላው የተሸነሸነ ክፍል ከተከራዩ ለተከራዩት ሰዎች ሊሆን እንደሚገባ የመመሪያው አንቀፅ 6(1) እና (2) ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ገቢ የለኝም በማለታቸው ራሳቸው ያሰሩበት የነበረው ክፍል እንዲቀርላቸው ተደርጎ ሌላው ክፍል ለ1ኛ አመልካች እንዲተላለፍ መደረጉ የመመሪያውን ትክክለኛ አፈፃጸም የሚያስገነዝብ እንጂ ሕገ ወጥ ተግባር አይደለም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አንጻር መመልከት ሲገባቸው ከተጠሪ ገቢ ያለመኖር ብቻ በመመልከት የሰጡት ውሳኔ የመመሪያውን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም መሰረታዊ አላማ ያላገናዘበ ነው፡፡በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 196499 በ23/11/05 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 142245 በ24/10/2006፣በመ/ቁጥር 142239 በ24/10/2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 1ኛ አመልካች አቶ ዲንሰፋ ያዕቆብ ከተጠሪ የተከራዩትን ክፍል ሊለቁ አይገባም ብለናል፡፡
3. 2ኛ አመልካች ወ/ሮ መሰለች አባመላ የያዙት ክፍል ለተጠሪ እንዲሆን የተወሰነ በመሆኑ ተጠሪ በዚሁ ክፍል ተጠቃሚነታቸው ሊቀጥል ይገባል ብለናል፡፡

4.. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡** **የ/ማ**

የሰ/መ/ቁ/103717

ሐምሌ 03 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሰራተኞች ሸማቾች ህብረት ስራ ኃ.የተ.የግል ማህበር

ተወካይ ጥላሁን ንዋይ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** የአዳማ ወረዳ ንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉደዩ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 መሠረት የተቋቋመ ሸማቾች ህብረት ስራ ኃ.የተ.የግል ማህበር በአዋጅ የንግድ ፋቃድ የሚያስፈልገው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክር የጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁን ተጠሪ እና በአቶ ዘላለም ታዬ በወ/ሮ በድሪያ ሁሴን እና በአቶ ዮናስ አስፋው ላይ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም አመልካች ቁጥራቸው 205 በሚሆኑ አባላት በአዋጅ ቁጥር 14791እና 402/96 ድንጋጌዎች አግባብ የተቁቋመ ሆኖ ከሚመለከተው አካል ህጋዊ ሰውነት አግኝቶ የማህበሩን እባላትና የአካባቢው ህብረተሰብ እያገለገለ መቆየቱን በወንጅ አካባቢ ወፍጮ ቤትና ዳቦ ቤት ከፍቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ እያለ የተጠሪ ሰራተኞች የሆኑትና የስር ከ2ኛ እስከ 4ኛ የተጠቀሱት እነ አቶ ዘላለም ታዩ አመልካች እየሰራ ያለውን ሰራ ንግድ ፍቃድ እንደሚያስፈልገው አመልካች እንደማያስፈልገው አመልካች እየነገራቸው ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ.ም ወፍጮ ቤትንና ዳቦ ቤቱን ያለአግባብ ያሸጉት መሆኑን በዚህ አድራጐት ምክንያትም አመልካች ሲያገኝ የነበረውን ገቢ ያሳጡና ለሰራተኞቹም ያለ ምንም ገቢ ደመወዝ እንዲከፍል ያደረጉ መሆኑን በዚህ ምክንያት የታጣ ገቢ መጠንና አመልካች ላይ የደረሰውን ወጪ አይነቱንና መጠኑን በመጥቀስ ተጠሪ

በሕገወጥ መንገድ ያሸገውን የወፍጮ ቤትና የዳቦ ቤት እንዲከፍት የተቋረጠ ገቢና ያለአግባብ ወጪ የሆነ ገንዘብ በድምሩ ብር 34.982.28 ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁ የሚያሳይ ነው ፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 147/91 የተቋቋመ ቢሆንም ከዚህ አዋጅ በኃላ የወጣው አዋጅ ቁጥር 686.2002 ማንኛውም የንግድ ስራ የንግድ ፍቃድ የሚያስፈልገው መሆኑ መደንገጉን በመቀነስ ከህግ የአወጣጥ ጊዜ ቅደም ተከተል አንፃር ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሆኑን አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት የመቆጣጠር ስራ ደግሞ የተጠሪ መሆኑ እና ተጠሪ በሠራተኞቹ አማካኝነት ኃላፊነቱን ሲወጣ ላከናወነው የማሸግ ስራ ለታጣ ጊዜ የሚጠየቅበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የሥር 2ኛ 3ኛ፣ እና 4ኛ ተከሳሾች የተጠሪ ስራተኞች በመሆናቸው በግላቸው የሚከሰሱበት አግባብ የለም በማለት ከክሱ ውጪ ከአደረጋቸው በኃላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን ክርክር መርምሮ ከሕግ አወጣጥ የጊዜ ቅደም ተከተል አንፃር በኃላ የወጣው አዋጅ ቁጥር 686/2002 ሆኖ ይህ አዋጅ በአንቀጽ 31/2/ እና 42 ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ ማንኛውም የንግድ ስራ የሚሰራው በንግድ ፍቃድ መሆኑን የሚደነግግ መሆኑን እንደሚያስገነዝብና ይህ አዋጅ የአዋጅ ቁጥር 147/91 በአዋጅ ቁጥር 402/96 እንደተሻሻለው አዲስ አዋጅ በመሆኑ የበላይ ተፈፃሚነት አለው በማለት አመልካች ያለ ንግድ ፍቃድ የወፍጮ ቤትና የዳቦ ቤትን ስራ ሊሰራ አይችልም የንግድ ስራን የመቆጣጠር ኃላፊነት ደግሞ የተጠሪ በመሆኑና ተጠሪ ይህንኑ በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነት ሊወጣ ለታጣ ገቢ ኃላፊ የሚሆንበት አግባብ የለም በማለት የአመልካችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጐታል በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ተብሎ አቤቱታው ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ልዩ ህግ የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 በአወጅ ቁጥር 402/96 እንደተሻሻለ ሆኖ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት በማድረግ አመልካች ለሚያከናውናቸው የወፍጮ ቤትና የዳቦ ቤት ስራዎች የንግድ ፍቃድ ያስፈልገዋል፡፡ በማለት መወሰናቸው ያለአግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲያከራክር አድርጓል፡፡

በክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታም መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጓጌዎች አንፃር ጉዳዩ

እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ለጉዳዩ ያዘገት ያለው ህግ የትኛው ነው? የሚለው ነጥብ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ለክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቸለው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 147/91 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 402/96 የተቋቋመ መሆኑንና የወፍጮ ቤትና የዳቦ ቤት ክፍቶ ሲሰራ መገኘቱ ግራ ቀኙን ያላከራከሩ ጉዳዮች መሆናቸውን ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው የሕግ ነጥብ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 686/2002 በተደነገገው አግባብ የንግድ ፋቃድ የሚያስፈልገው መሆን ያለመሆን የሚመለከት ነጥብ ስለመሆን ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 686/2002 በአዋጅ ቁጥር 147/91 እና አዋጅ ቁጥር 402/96 በኃላ የወጣ አዲስ አዋጅ መሆኑና ይህ አዋጅ በማንኛውም የንግድ ስራ የንግድ ፋቃድ የሚያስፈልገው መሆኑን መደንገጉን መሠረት በማድረግ አዲስ አዋጅ ለጉዳዩ የበላይ ተፈፃሚነት አለው በማለት ወስነዋል፡፡ በመሆኑም ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህን አተረጓጎምና አተገባበር የተጠቃሽ ሕጐችን ሙሉ ይዘትና መንፈስ የተከተለ መሆን ያለመሆን እንደሚከተለው አይተናል፡፡

በመሠረቱ የህብረት ስራ ማህበት የፌዴራል ደረጃ አዋጅ ቁጥር 147/1991 እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 402/1996 እንዲሁም በደንብ ቁጥር 106/1996 መሠረት የተደራጀ ሲሆን፡፡ ክልሎቹም የየራሳቸውን አዋጆች ቀርፀው እነዚህ ማህበራት የሚገዙበትን ስርዓት ዘግተዋል፡፡ ፌዴራልም ሆነ በክልል የተቋቋመበት የንብረት ሥራ ማህበራት በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዩች ላይ በመሳተፋ ለአባባሎቻቸውና ለጠቅላላው ሕብረተሰብ የራሳቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ መሆናቸው የሚታወቅ ነው፡፡ እነዚህን አካላት ያደራጀ ህጐች ይዞታቸውና መንፈሳቸው ሲታይም ማህበራቱ የራሳቸውን የቻለ አደረጃጀትና ልዩ ባህሪያት ያላቸው መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991አንቀጽ 2/2/ ሲታይ የህብረት ሥራ ማህበር ማለት ሰዎች በፍቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታታ የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በህግ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማህበር ነው፡፡ በሚል ትርጉም ያስቀመጠ ሲሆን የድንጋጌ ይዘቱና መንፈስ ሲታይ በሕብረት ስራ ማህበራት ለማህበራዊነት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ሲባል የሚደራጅ መሆኑን ያሳያል፡፡ አዋጅ ቁጥር 147/91 እና በዚሁ አዋጅ ማሻሻያ የሆነው አዋጅ ቁጥር 402/97 ድንጋጌዎች ሲታይ የንብረት ሥራ ማህበራት ከበጐ አድራጐት ድርጅቶችም ሆነ ከንግድ ማህበራት የሚለዩበት ባህሪያት ያሏቸው መሆኑን ያሳያሉ፡፡ በህጐቹ ከተቀመጡት መለያ ባህሪያት አንዱ ማህበራት የሚቋቋሙበት ዓላማ ሲሆን የህብረት ሥራ ማህበራት የሚቋቁሙበት ዓላማ የአባላትን ተመሳሳይ ፍላጐት በአነስተኛ ወጪ ለማሟላት እንጅ በአባላት ትርፍ ለማስገኘት ተብሎ የማይቋቋም መሆኑን ያሳያል፡፡ አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 4 በተለይ ሲታይም የህብረት ስራ ማህበራት የሚቋቋሙበትን ዓላማዎች የዘረዘረ ሲሆን

በዝርዝሩ ውስጥ ለአባላት ትርፍ ለማስገኘት የሚያስችል ሥራ እንደሚሳተፍ አይገልጽም፡፡ የተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 35 ድንጋጌ አንድ ማህበር ለአባላት ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመ ሌላ ማህበር ካልሆነ በቀር ብድር መስጠት እንደሚችል የደነገገው ሲሆን ይህም ማህበር በትርፍ ተብሎ የሚቋቋሙና መሠረታዊ ግባቸው የአባላቱን ፍላጐት በአነስተኛ ወጪ ማሟላት ነው የሚለውን ድምዳሜ የሚያጠናክር ነው፡፡ የህብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ሲታይ የህብረት ሥራ ማህበር አባል ለመሆን አንድ ሰው 14 ዓመት የሞላው የማህበሩን ዕጣ ለመግዛትና የመመዝገቢያ ክፍያ ለመክፈል የሚችልና የማህበሩ ደንብና የተለያዩ አዋጆችን ለማክበር ፍቃደኛ ሲሆን እንደሚገባ ሕጉ የሚያሳይ ሲሆን የማህበራት ስያሜም አዋጅ በአንቀጽ 8 ማንኛውም ማህበር መመሪያ ስም ሲኖረው እንደሚገባ ስሙ በመጨረሻ ኃላፊነቱ ስያሜም አዋጅ በአንቀጽ 8 ማንኛውም ማህበር መጠሪያ ስም ሊኖረው እንደሚገባ ስሙ በመጨረሻ ኃላፊነት የተወሰነ የኃብረት ሥራ ማህበር የሚሉ ቃላት መያዝ እንደሚገባ አንድ ማህበር በተመዘገበበት ስምና ምልክት ሌላ ማህበር ሊጠቀምበት እንደማይችል ሕጉ አስቀምጧል፡፡ ሌላው ስለ ህብረት ስራ ማህበር በሕጉ የተቀመጠው ጉዳይ ማህበራቱ ያላቸው ልዩ መብቶች ናቸው፡፡ አዋጅ ቁጥር 147/1991 እና የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ የሆነው አዋጅ ቁጥር 402/96 ድንጋጌወች ሲታዩ ለህብረት ሥራ ማህበራት ልዩ መብቶች እንዳሏቸው ያሳያሉ፡፡ በሕጐቹ ከተመለከቱት ልዩ መብቶች የማህበራት ዕዳ በቀዳሚነት እንዲከፈል የተቀመጠው ደንብ የህብረት ሥራ ማህበራት የአለበትን ዕጣ ወይም ጥቅም የማቻቻል የኃብረት ሥራ ማህበራት በመንግስት የሚሰጧቸው ልዩ ልዩ ድጋፎችንና የንግድ ፍቃድን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚሸፈኑ መሆኑን አዋጆቹ ያሳያሉ፡፡ ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ ተግባራት ያለው የንግድ ፍቃድን የሚመለከተው ልዩ መብት ሲሆን አዋጅ ቁጥር 402/96 አንቀጽ 6 ስር ማህበራት ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ተጨማሪ የንግድ ፍቃድ ሳያስፈልጋቸው በማንኛውም የንግድ ሥራ ላይ መሰማራት ይችላሉ በሚል ተቀምጧል፡፡ በዚህ ረገድ የተቀመጠው ድንጋጌ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም የንግድ ፈቃዱ ልዩ መብት ንግድን ያለንግድ ፋቃድ ለማከናወን የሚፈቅድ በመሆኑና ማህበራቱ ከሚሰሩት ስራ ውጭ ባሉ የንግድ ሥራዎችም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 እና 813/2006 ሊገዙ ያሰቡትን የንግድ ውድድርን ትርጉም ሊያሳጣው ይችላል የሚል ክርክር ሊቀርብበት የሚችል መሆኑ እሙን ነው፡፡

ወደ አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረታዊ አላማ ስንመጣ የንግድ ዘርፍ የሀገሪትን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚደግፍበትን ሁኔታ የማጠናክር የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፋቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን በአግባቡ በሚደራጁት የንግዱን ዘርፍ ጉጂና ተገቢ ያለሆኑ እንቅስቃሴዎችን መከላከለ በንግድ ዘርፍ መንግስት ሊኖረው የሚገባውን መረጃ ሰበአግባቡ ለመያዝ የሚያስችለውን ሁኔታ ማመቻቸት እና ለንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ምቹ ሆኔታዎችን መፍጠር ስለመሆናቸው በአዋጅ

አንቀጽ 3 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የአዋጅ ተፈፃሚነትን በተመለከቱም የንግድ ፈቃድን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 ንዕስ ለአንቀጽ /1/ ከተመለከቱት የንግድ ስራዎች በስተቀር በሌላ ማናቸውም የንግድ ሥራ በተሰማራ ሰው ላየ ተፈፃሚ ይሆናሉ ሲል የደነገገው ሲሆን በአዋጅ አንቀጽ 30/1/ ስር የተመለከቱት የንግድ ስራዎች ደግሞ በማዕድን ፍለጋና ልማት የውሃ ነክ ስራወች ግንባታ  አገልግሎትን ሳየጨምር በልዩ ለዩ ውሃ ነክ ሥራዎች በባንክ መድን እና ማይክሮ ፋይናንስ ንግድ ሥራወች በአየር ማመልከቻና አገልግዘለት ስራ ሬዲዮ አክቲብ ቁሶዎችንና ጨረር አመንጪ መሳሪያወችን በሚመለከቱ የንግድ ስራዎች በቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት የኤሌክትሪክ ማመንጨት ማስተላለፍ አከፋፈል ወይም መሸጥ ንግድ ሥራ በቀርና ተኩል መስሪያወች ጥገና እድሳትና ፈንጅ ሽያጭ ሥራ በባህርና የሃገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርት ንግድ ሥራ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ንግድ ሥራ የዕቃ ማከማቻ ቤት ንግድ ሥራ እና በትምባሆና የትምባያ ውጤቶች ንግድ ሥራ መሆናቸውን የዘረዘረ ሲሆን አግባብ ላቸው ሌሎች መስሪያ ቤቶች ከሚሰጡ ፋቃዶች በስተቀር ሌሎች የንግድ ስራ ፋቃዶች የሚሰጡት እንደአግባቡ በሚኒስተሩ ወይም በቢሮው ወይም በኢትዮጵያ ኢንበስትመንት ኤጀንሲ ስለመሆኑም ይህው ድንጋጌ ያሳያል፡፡

የአዋጅ አንቀጽ 31/1/ ማንኛውም ሰው የፀና የንግድ ስራ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ሰራ መሥራት እንደሚይችል በኃይል ቃል የደነገ ሲሆን የአዋጅ አንቀጽ 42 ድንጋጌም ተገቢው የንግድ ሥራ ፋቃድ ሳይኖረው በሌላ አይነት ፋቃድ ይህ አዋጅ ፈፃሚ የሚሆንበት የንግድ ሥራ ሲካሄድ የነበረ ማገኛውም ሰው ይህንኑ ሥራ ለማካሄድ ይህ አዋጅ ከመጣበት ቀን ጀመሮ በ12 ወራት ውስጥ አግባብ ያለውን ቅጽ ሞልቶ ማመልከቻ በማቅረብ ተገቢውን የንግድ ሥራ ፋቃድ ማውጣት እንዳለበት በአስገዳጅነት ደንግጓል፡፡

እነዚህን የአዋጅ ቁጥር 686/2002 ድንጋጌዎች ስንመለከት በሕጉ ንግድ ፋቃድ የሚያስፈለጋቸው ተግባራት ተለይተው የተቀመጡ በመሆኑ በህጉ ተዘርዝረው የተቀመጡ ውጬ ያሉት የንግድ ስራዎች ፋቃድ የሚያስፈለጋቸው መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው በማለት መደምደሚያ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የድንጋጌወቹን ተፈፃሚነት በአወጅ ቁጥር 147/91 እና በአዋጅ ቁጥር 402/96 መሠረታዊ አላማና ከማህበራት ልዩ ባህር አንፃር ማየቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ማህበራት በመሰረታዊነት ለትርፍ ተብሎ የሚቋቋሙ ሳይሆን የአባላቱን ፍላጐት በአነስተኛ ወጪ ለሟሟላት የሚቋቋሙ በመሆኑለትርፍ ስራ የሚሰሩ የንግድ ስራዎች የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ፍቃድ እንዲያወጡ የሚጋደድበት አግባብ የለም፡፡ አዋጅ ቁጠር 402/96 አንቀጽ 6 ድንጋጌም በዚህ ረገድ ግልጽ የሆነ ይዘት ያለው በመሆኑ ማህበራት የንግድ ፍቃድ አያስፈልጋቸውም በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 31/1/ እ 42 ድንጋጌዎች ስር ማንኛውመ የንግድ ስራ የንግድ ፍቃድ እንደሚያስፈልገው የተቀመጠው ድንጋጌ ከማህበራቱ መሠረታዊ አላማና

ባህርይ አዋጅ ቁጥር 686/2002 ሊያሳካው ካሰበው ግብ አንፃር ታይቶ ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው እንጂ አዋጅ የወጣበትን ጊዜ ብቻ መሠረት በማድረግ ለማንኛውም የንግድ ስራ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ሊደረግ የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 147/91 እና በማሻሻያው የሚገዛ ነው፡፡ ከተባለ ደግሞ የተጠሪ አድራጉት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027/2028 እና 2035 መሠረት ሕገ ወጥ በመሆኑ በአመልካች ላይ ለደረሰው የጉዳት ካሳ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ የጉዳት ካሳ መጠኑ ግን በስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ያልታየ በመሆኑ በዚህ ችሎት እልባት የሰጠው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዮን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16938 ግንቦት 01 ቀን 2006 ዓ.ም ተሠጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 187476 ግንቦት 22 ቀን 2006 ዓ.ም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 185055 ሰኔ 26 ቀን 2006 ዓ.ም የሆነው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በአወጅ ቁጥር 147/91 እና በማሻሻው በተቋቋመና የሚገባ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት የንግድ ፋቃድ እንዲወጣ አይገደድም ብለናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ እርምጃ ሕግ ነው ብለናል፡፡ ተጠሪ እሽጉን ሊያሳይ ይገባል በአመልካች ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሳ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027/2028 እና 2035 የመክፈል፡፡ ሀላፊነት አለበት ብለናል፡፡ የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተ ግን የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ሊወሰን ይገባል በማለት በዚህ ነጥብ ብቻ ጉዳዩን በስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ወ/ከ**

# ሸፊዓፀሣ

የሰ/መ/ቁ. 98347

ሐምሌ 13 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቁጢታ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ በድሪያ መሐመድ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አደም ዑመር ቀረቡ

መዝገቡን መርመረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መቋረጡን ተከትሎ የተነሳው የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ አመልካች አመልካች ደግሞ ተጠሪ በመሆን ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ ከ1980 እስከ 2001 ዓ.ም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖርበት ጊዜ የአመልካች አባት አሮጌ አፈር ቤት ሊሾ በማድረግ እና ደረጃው 12 በረንዳ ቆርቆሮ በመቀየር ተጠሪ ማሳደሳቸው እንዲሁም ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤት እንዲሰሩ አብረው ሲኖሩ የተለያዩ የቤት መገልገያ ዕቃዎች ማፍራታቸውን መሠረት በማድረግ ንብረቱ የሚቻል ከሆነ በዓይነት እንዲከፈሉ የማይቻል ከሆነ በሀራጅ ተሸጦ እኩል እንዲካፈሉ ተጠሪ በዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ በወላጅ አባታቸው ቤት የተደረገ እድሳትም ሆነ የተቀየረ በረንዳ እንደሌለ የተሰሩ ሁለት ሰርቪስ ቤቶች መኖራቸው አምነው ተጠሪ ተክተው አፍርሰው መውሰድ እንደሚችሉ ዛፎች የአመልካች አባት የተከሉዋቸው እንደሆነ፣ አመልካች በተጠሪ ከሚከራየው ቤት ድርሻቸው እንዲያካፍላቸው ጠይቋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል የቀረበ ምስክሮች ያዳመጠ ሲሆን አመልካች ግን ማስረጃ አለማቅረባቸውን በውሳኔው ገልጾ በፍሬ ጉዳዩም ሁለት ሰርቪስ ቤቶች ግራ ቀኙ በጋራ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የተሰሩ የጋራ ንብረት መሆናቸው እንደታመነ መዝግቦ፤ በአመልካች በኩል በቀረበው ክርክር ተጠሪ የተሰራውን ሰርቪስ ቤት አፍርሰው ይውሰዱ የሚለውን ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/3/ እንደተመለከተው መሬት የመንግስትና የህዝብ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ እንዳልተቀበለው የአመልካች አባት አሮጌ ቤት በጋራ ማደሳቸው ከ30-40 የሚሆኑ ዛፎች በጋራ መትከላቸው መረጋገጡን እንደሁም የጋራ የተባሉትን የቤት ዕቃዎች በመለየት ሁለት ሰርቪስ ቤቶች አንድ የደጅ ሽንትቤት ቧንቧ እና በግምት ከ30-40 ዛፎች የጋራ ንብረት ስለሆነ በዓይነት

መክፈል የሚቻል ከሆነ በዓይነት ይህ ካልተቻለ ዎጋ በማይቻል ይህ ካልተቻለ በስምምነት በመሸጥ ይህ ካልተቻለ በሐራጅ በመሸጥ ሽያጩ እኩል እንዲከፈሉ ቀደም የነበረው ሳሎንና መኝታ ቤት በ12 ቆርቆሮ በረዳ የተሰራበት እና በኦብጀዳድ እና በሽራ ኮርኒስ የተሰራበት ገንዘብ በባለሙያ ተገምቶ የግምቱ ግማሽ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ሌሎች የቤት ዕቃዎችም እንዲከፈሉ ወስኗል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በኮ.መ.ቁ.28071 በ24/07/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ማብራሪያ የሚፈልግ በመሆኑ በፍርድ አፈፃፀም መመሪያ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ፍርድ ቤቱ በ30/08/2005 ዓ.ም መብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ በሰጠው መብራሪያም ባህርዛፍን የተተከለበት ቦታ መምራ እኩል እንዲካፈሉ በአጠቃላይ ውሳኔ ያረፈባቸው ሰርቪስ ቤቶች ቧንቧ እና ባህርዛፎች ከእነ ይዞታቸው ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ አዟል፡፡ አመልካች ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥነው ጉዳዩ የሰበር ይመርመር በመባሉ በግራ ቀኙም የጽሑፍ ክርክር አደርጓአል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዋና ፍሬ ነገር ለክርክሩ መነሻ የሆነውን በአባታቸው የመሬት ይዞታ የተሰሩትን ሰርቢስ ቤቶችን እና ተተከሉ የተባሉ ዛፎች ተጠሪ አፍርሰው ወይም ግምት ወስደው ከሚሰናበቱ በቀር አኩል የሚካፈሉበት ምክንያት አይኖሩም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ለአፈፃም መነሻ የሆነውን ፍርድ የግባኝ ጠይቀው ሳያሸሩ በአፈፃፀም ጊዜ የክፍፍል ሥርዓቱ መቃወም እንደማይችሉ ሰርቪስ ቤቱም በደመወዛቸው እንዲሰሩት የሥር ፍርድ ቤት ከነይዘታው እኩል እንዲከፍሉ የሰጠው ትዕዛዝ የሚነቀፍ ነጥብ የለም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራራሯል፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ፍርዱን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ይዘት ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በሥር የፌዴራለ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደገለፀው ግራ ቀኙ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ እንደነበር ከአብራካቸው ሔዋን አዳም የተባለችው ልጅ እንደተወለደች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ሰርቪስ ቤቶች የደጅ ሽንት ቤት ቧንቧ እና ግምቱ ከ30-40 የሆኑ ዛፎች የጋራ ንብረት እንደሆኑ፤ የክፍፍል ሥርዓቱም ከተቻለ በዓይነት፤ ካልተቻለ ዋጋ በማቻቻል ካልተቻለ በስምምነት በመሸጥ ይህ ካልተቻለ በሀራጅ በመሸጥ እኩል እንዲከፍሉ በኮ.መ.ቁ. 28071 በ24/07/2004 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ውሳኔ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወይም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ የተሻረ የተሻሻለ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ የፍርድ አፈፃፀም የሚመራው ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ የማያስፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ባስቀመጡት አግባብ የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤትም መጀመሪያ በሰጠው ፊርድ መሠረት እንዲፈፀም በ30/08/2005 ዓ.ም በሰጠው የመብራሪያ ትዕዛዝ ግልጽ አደርጓአል፡፡ የአሁኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አልነበረም የሚል ቅሬታ ከነበራቸው በሕጉ የተዘረጋው የይግባኝ ሥርዓት ተጠቅመው መብታቸው ሊያስከብሩ ይገባ ነበር ለአፈፃፀም መነሻ የሆነውን ፍርድ ይግባኝ በመጠየቅ ሳይሻሩ ወይም ሳያሻሽሉ በዋናው ጉዳይ ሲነሱ የሚገባቸው የክርክር ነጥቦች በአፈፃፀም በተያዘው መዝገብ የክርክር መሠረት ለማድረግ የሚያስችላቸው ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በእርግጥ አመልካች በአፈፃፀም የተያዘው ጉዳይ

በአፈፃፀም ጊዜ እንደ ፍርዱ ለመፈፀም የሚያስችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች መኖራቸው ካሳዩ ሥርዓቱን ጠብቀው አቤቱታ የማቀርብ መብት አላቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በዋናው ጉዳይ ሰርቪስ ቤቶች፣ የደጆ ሽንት ቤት እና ባህር ዛፎች እኩል እንዲካፈሉ ግልጽ ውሳኔ በተሰጠበት ሁኔታ በአፈፃፀም ወቅት ሰርቪስ ቤቶቹ የተሰሩት በአባቴ ይዞታ ነው በማለት ብቻ የአፈፃፀም ሂደቱን ለማቆም የሚያስችል የሕግ መሠረት የላቸውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙ ከመረመረ በኃላ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392/1/ እና /2/ መሠረት እንደ ፍርድ እንዲፈፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች በመ/ቁ 28071 በ24/07/2004 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ መሠረት በማድረግ የተከፈተው አፈፃፀም እንደ ፍርዱ እንዲፈፀም ትዕዛዝ መሰጠታቸው ሕጉን ተግባራዊ አድርጓል ከሚባል በቀር የፈፀሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1/ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.28071 በ30/08/2005 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 13773 በ1/4/2006 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡

2/ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች እና ተጠሪ የሚከራከረው የሰርቪስ ቤቶች የደጆ ሽንት ቤት እና ባህር ዛፍ እንደ ፍርዱ እንዲፈጽሙ የሰጠው ትዕዛዝ ፍርዱን መሠረት ያደረገ ነው በማለት ወስነናል፡፡ አመልካች በፍርድ አፈፃፀም ጊዜ እንደ ፍርዱ እንዳስፈጽም የሚገድብ ሕጋዊ ምክንያት ካለ ሥርዓቱን ጠብቀው አቤቱታ የማቅረብ መብታቸው በዚህ ፍርድ አልተገደቡም /አልተነካም/፡፡

3/ የሰበር ችሎት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙን የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1/ ከዚህ ችሎት ታህሳስ 15 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

**ወ/ከ**

የሰ/መ/ቁ 96588

ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጤታ

**አመልካችዎች፡-** 1. ወ/ሮ አልማዝ አርዕያ - ተወካይ ለማ ሀይሌ ቀረቡ

2. አቶ ፍቀሩ አርዕያ ቀረቡ

3. አቶ ደረሰ አርዕያ ቀረቡ

4. ወ/ሮ አለምነሽ መኮነን ተወካይ ሁለተኛ ተጠሪ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አሸናፊ አልታየ ጠበቃ እዩኤል ጀረኔ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

<u>**ፍርድ**</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካችዎች የሶዶ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 09284 ሐምሌ 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የደቡብ ብሔርብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25570 ጥቅምት 13 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03219 ታህሳስ 1 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ውሳኔ በሀራጅ የተሰጠበት ዋጋ ተቀንሶ እንዲከፈል የተሰጠ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ እነ አልማዝ አርዕያ የአፈፃፀም ከሳሾች፣ እንተነህ አሰፋና ፍቀሩ አርዕያ የአፈፃፀም ተከሳሾች ሆነው በሚከራከሩበት የአፈፃፀም መዝገብ የውርስ ንብረት የሆነ

የማይንቀሳቀስ ንብረት በሀራጅ እንዲሸጥ በአፈፃፀም ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪ በሀራጅ ጨረታው አሸናፊ በመሆን ንብረቱን በብር 1,573,000 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ ሶስት ሺህ ብር/ ለመግዛት ተስማምቶ፣ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ፣ የንብረቱን ሰባ ፐርሰንት በቼክ ገቢ በማድረግ፣ ገዝቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በሀራጅ የገዛው ቤት ስመ ንብረት፣ በጨረታ አሸናፊው በተጠሪ ስም እንዲዛወር፣ ሰባ ፐርሰንቱ የቤቱ ዋጋ ክፍያ እንዲፈፀምና፣ ታግዶ ያለው የቤቱ ሰላሣ ፐርሰንት ዋጋ የማዛወር ሒደቱ ሲለቀቅና በያዘው ቦታ ላይ መንግስት ከውራሾች ወይም ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የሚፈልገውን ዕዳ ከፍለው ሲጨርሱ ወይም ሽያጭ የተፈፀመበትን ንብረት ነፃ ሲያደርጉ ክፍያው እንዲፈፀም በማለት የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

2. ከዚህ በኋላ አመልካችዎች ግንቦት 27 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የጨረታ አሸናፊው በጨረታ የገዛዉን ንብረት በስሙ አዛውሮ የጨረሰ በመሆኑ ቀሪውን ሰላሳ ፐርሰንት እንዲከፍል ትዕዛዝ ይሰጥልን በማለት አመልክተዋል የስር ፍርድ ቤት የጨረታው አሸናፊ /ተጠሪ/ የአመልካችዎችን ቀሪ ክፍያ ይዞ እንዲቀርብ ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 10 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በአራት አቅጣጫ አዋሳኝ ምልክቶቹ ተገልፀው በጨረታ አሸንፌ የገዛሁት ቤት በ1340 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው መሆኑን ሰነዶቹ ያሳያሉ፡፡ ነገር ግን ስም ለማዛወር ቦታው ሲለካ 1130 ካሬ ሜትር ብቻ ሆኖ ስለተገኘ የ210 ካሬ ሜትር ቦታ ዋጋ ይቀነስልኝ በማለት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ አመልካችዎች ይኽ የአመልካች ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም ካልሆነ የሀራጅ ሽያጩ ፈርሶ ንብረታችንን ያስረክቡን፣ ገንዘቡን እንመልስ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የ210 ካሬ ሜትር ቦታ ዋጋ ብር 246515 /ሁለት መቶ አርባ ስድስት ሺ አምስት መቶ አሰራ አምስት ብር/ ተቀንሶለት ሌላውን ገንዘብ ይክፈል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካችዎች ይህንን የአፈፃፀም ትዕዛዝ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቷል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የሰበር ችሎቱ የአመልካችዎችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

4. አመልካችዎች ጥር 7 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገው የሀራጅ ሽያጭ ከዘጠኝ ሰዎች ጋር ተወዳድረው አሸናፊ ሆነዋል፡፡ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም የገቡት ስመ ሀብት እንዲዛወርላቸው እና ሰባ ፐርሰንት ክፍያ እንዲከፈለን ትዕዛዝ ተጥቷል፡፡ ተጠሪ የሀራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ያቀረቡት

አቤቱታ የለም፡፡ ከዚያ በኋላ ዋጋ እንዲቀነስላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ ስርዓቱን ያልተከተለ ሆኖ እያለ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን ጥያቄ ተቀብለው የሰጡት ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በሀራጅ የገዛሁት ቦታና ንብረት ስም ሲዛወር ተለክቶ የተገኘው ቦታ ልዩነት ያለበት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ሊዝ ዋጋ አስልተው ከቤቱ ዋጋ መቀነሳቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የካቲት 19 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ መልሶ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች መጋቢት 5 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅረበዋል፡፡

5. ከስር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በሀራጅ ጨረታ ንብረቱን ከገዛበት ዋጋ ተቀንሶ ሊዝ ዋጋ ሒሳብ 210 ካሬ ሜትር ቦታ ለአመልካችዎች እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
6. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገው የሀራጅ ሽያጭ ተወዳዳሪ ሆኖ ቀርቦ በብር 1,573,000 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ ሶስት ሺ ብር/ የሀራጅ ሽያጭ አሸናፊ ሆኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሀራጅ ሽያጨን ዋጋ ተጠሪ በቼክ እንዳስያዘ ገልፆ፣ ሰባ ፐርሰንቱ ለአመልካችዎች እንዲከፈል፣ ሰላሳ ፐርሰንቱ ስመ ሀብቱ እስኪዛወር እንዲቆይ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካችዎች ግንቦት 27 ቀን 2005 ዓ.ም አፈፃፀሙን ለያዘው የስር ፍርድ ቤት፣ የንብረቱ ስመ ሀብት ወደ ተጠሪ የተዛወረና ተጠሪ ንብረቱን የተረከበ በመሆኑ ቀሪ ሰላሳ ፐርሰንት የንብረቱን ዋጋ እንዲከፈል ትዕዛዝ ይሰጥልን በማለት ነው፡፡
7. በመሰረቱ የስር ፍርድ ቤት የሀራጅ ሽያጭ አሸናፊ የሆነው ተጠሪ የጨረታው አሸናፊ ከሆነበት፣ ከየካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ ባሉት አስራ አምስት ቀናት፣ የገዛውን ንብረትሙሉ ዋጋ በፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 441 መሰረት ሙሉ በሙሉ ገቢ እንዲያደርግ ማድረግ ሲገባው፣ ሰባ ፐርሰንቱን የንብረቱን ዋጋ ብቻ ተጠሪ በቼክ እንዲከፍል አድርጎ ሰላሳ ፐርሰንቱ የንብረቱ ዋጋ በተጠሪ እጅ እንዲቆይ ማድረጉ፣ ተጠሪ ንብረቱን የገዛው ፍርድ ቤት ባወጣው ሀራጅ ማስታወቂያ ፍርድ ቤት በመደበው ሀራጅ ባይ በኩል ከፍርድ ቤቱ ሆኖ እያለ፣ በሀራጅ ሽያጩ ውስጥ ምንም አስተዋፅኦ የሌላቸውንና ፍርድ ቤት የሸጠውን የቤት ዋጋ በሕግ አግባብ ተቀብሎ ሊከፍላቸው ከሚገባቸው አመልካችዎች፣ ከተጠሪ ጋር አላስፈላጊ ክርክር ውስጥ እንዲገቡና በዚህም መጉላላትና ኪሳራ እንዲደርስባቸው የሚያደርግ ስርዓት የስር ፍርድ ቤት የተከተለ መሆኑን ያሳያል፡፡

8. የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በሀራጅ የገዛውን ንብረት ሙሉ ዋጋ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 441 በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ገቢ እንዲያደርግ አድርጎ ቢሆን ኖሮ፣ የቤቱ ስመ ሀብት ለተጠሪ መዛወሩን እንዳረጋገጠ፣ ተጠሪን ሣይጠራ፣ ቀሪው የቤቱ ዋጋ ለአመልካቾች እንዲከፈል ትዕዛዝ ይሰጥ ነበር፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን አስገዳጅ ስርዓት ባለመከተሉ ተጠሪ በሀራጅ የገዛውን ቤት ሙሉ ዋጋ የመክፈል ግዴታውን የሚቀንስለት ወይም የሚሻሻልለት፣ አይሆንም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሀራጅ ሽያጩ የተከናወነው የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ የገዛሁት ንብረት የይዞታ መጠን በሰነድ ከተገለፀው 1340 ካሬ ሜትር ሣይሆን 1130 ካሬ ሜትር ሆኖ ተገኝቷል በማለት አቤቱታ ያቀረበው፣ የቤቱ ስመ ሀብት በስሙ ካዛወረና ንብረቱን ከተረከበ እንደዚሁም አመልካችዎች ቀሪው የቤቱ ዋጋ ይከፈለን ብለው ግንቦት 27 ቀን 2005 ጥያቄ አቅርበው፣ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ቀሪውን የቤቱን ዋጋ ገቢ እንዲያደርግ ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ከሰጠ በኂላ ሰኔ 11 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡

9. ተጠሪ ሰኔ 11 ቀን 2005 ዓ.ም ላቀረበው ጥያቄ እድል የሰጠው የስር ፍርድ ቤት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 441 አስገዳጅ ድንጋጌ በጥብቅ ባለመከተሉና በድንጋጌው መሰረት አፈፃፀሙን ባለመምራቱ ነው፡፡ እንደዚሁም ተጠሪ በሰነድ የሚታየው በሀራጅ የተሸጠለት ቤት የይዞታ መጠንና ቦታው፣ ሲለካ የተገኘው የይዞታ መጠን ልዩነት አመልካችዎች በፈፀሙት የተንኮል ድርጊት የደረሰ ስለመሆኑ የገለፀውም ሆነ ያስረዳው ነገር የለም፡፡ ተጠሪ አዋሳኝ ምልክቶቹ በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 228 ንዑስ አንቀፅ 2 ተለይተው በሀራጅ ማስታወቂያ ተገልፆ፣ ካርታውና ፕላኑ ላይ የቦታው ስፋት 1340 ካሬ ሜትር መሆኑ ተገልፆ፣ ፍርድ ቤቱ በሀራጅ የሸጠለት ንብረት ይዞታ፣ ስም በማዛወር ልኬት ሲፈፀም 1130 ካሬ ሜትር ብቻ መሆኑን እንደተረዳ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሰረት የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው ማመልከቻ የለም፡፡ ይህ ከሆነ፣ ተጠሪ ንብረቱን በስሙ ካዛወረና፣ ከተላለፈ በኂላ የሀራጅ ሽያጩ ሙሉ በሙሉ ከተፈፀመለት በኂላ፣ ንብረቱ በሀራጅ ከተሸጠበት ዋጋ ላይ እንዲቀነስለት ያቀረበው ጥያቄ የስነ ስርዓት ሕጉን ያልተከተለና ሕጋዊ ዕውቀትና ውጤት ሊሰጠው የማይገባው ነው፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የ210 ካሬ ሜትር ቦታ ዋጋ በሊዝ ሒሳብ ብር 246515 /ሁለት መቶ አርባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ አስራ አምስት ብር/ ተቀንሶለት፣ ቀሪውን ገንዘብ ይክፈል በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አንቀፅ 441፣ አንቀፅ 447 እና አንቀፅ 429 ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የሶዶ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሐምሌ 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ታህሳስ 1 ቀን 2006 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካችዎች ሊከፍል የሚገባው በሀራጅ ጨረታ ቤቱን አሸንፎ የገዛበትን ብር 1,573,000 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ ሶስት ሺ ብር/ ሰላሳ ፐርሰንት ሙሉ በሙሉ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ ይህንን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ አጠቃልሎ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ የስር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 429 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ማድረግ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ይ**

የሰ/መ/ቁጥር 96814

ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** አቶ አብዶሽ አዲሽ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሰብለ ዘውዴ -የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኗ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በሐረሪ ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ06/08/2002 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የአፈጻጸም ክስ መሰረት ያደረገውም በሐረር ከተማ ከፍተኛ 2 ቀበሌ 17 ክልል ውስጥ የሚገኘው፣ በ1280 ካ/ሜትር ስፋት ባለው ቦታ የሰፈረና ቁጥሩ 668 የሆነ፣ በካርታ ቁጥር 1035 የሚታወቀው የመኖሪያ ቤት ሲሆን ይህን ቤት በተመለከተ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት መሆኑን፣ለሁለት መከፈል የሚችል መሆኑን በተገቢው ባለሙያ አረጋግጦ ለተጠሪ በእጣ ምድብ "B" በ640 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን ሶስት ክፍል ቤት፣ለአሁኑ አመልካች ደግሞ በምድብ "A" 640 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን አምስት ክፍል ቤት እንዲወስዱ መወሰኑን ነው፡፡ በዚህ አግባብ እንዲፈፀምላቸው አፈፃጸሙን ለስር ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱን ግራ ቀኙን እንዲከራከሩ ከአደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ሌላ ባለሙያ መድቦ ቤቱ በአይነት ሊከፈል የሚችል መሆን ያለመሆኑንና ግምቱ ምን ያህል እንደሆነ አጣርቶ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአፈፃጸም ችሎት የመደበው ባለሙያም ቤቱ በአይነት ሊከፈል የማይችል መሆኑንና ቀድሞ የቀረበው የአይነት ክፍፍል የባለሙያ ሐሳብ ቤቱን ሙሉ በሙሉ ዋጋ የሚያሳጣ መሆኑን፣ ግምቱም በፍሬ ነገሩ ጊዜ የተገመተው ብር 520,683.18 ሳይሆን ብር 365,080.60 መሆኑን ዘርዝሮ ሪፖርቱን ለፍርድ ቤቱ የላከለት ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በፍሬ ነገሩ ጊዜ የተሰጠው የባለሙያ አስተያየት ስህተት መሆኑ በአፈፃጸም ጊዜ ከሚመለከተው አካል በተመደበ ባለሙያ አስተያየት መረጋገጡን፣ በአፈጻጸም ጊዜ የተመደበው ባለሙያ ቤቱ በአይነት ቢከፈል ቤቱ እንደሚጎዳና ግምቱም ብር 365,080.60 መሆኑን ማረጋገጡን፣ይህ ከተረጋገጠ ደግሞ በዋና ፍርድ ቤት ጊዜ የተሰጠውን ውሳኔ በአፈጻጸም ጊዜ አመቺ በሆነ መንገድ ማስፈፀም እንደሚቻል በሕጉ የተፈቀደ መሆኑን፣ይዞታውን እኩል ማካፈል የሚቻል ቢሆንም ቤቱን ግን ጉዳት ሳይደርስበት በእኩል

ማካፈል የማይቻል መሆኑን ጠቅሶና በአማራጭነትም ክፍፍሉ በቀድሞው ክፍፍል ጊዜ አብዛኛው ቤት ያለበት ይዞታ ለአሁኑ አመልካች ደርሶ የነበረ መሆኑን፣አመልካች ከአስራ አምስት አመታት በላይ በቤቱ እየኖሩ ያሉ መሆኑን፣በቀዳሚነት የግዥ መብት ስርዓትም ሁለት ሰዎች በእኩል ደረጃ የሚገኙ ሲሆን በይዞታ ላይ ላለው ሰው የቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑ በሕጉ መመልከቱን መሰረት በማድረግ ቤቱ ያለበትን የይዞታ ክፍል የአሁኑ አመልካች እንዲወስዱ፣ ቤቱ የሌለበትን የይዞታ ክፍል ደግሞ ተጠሪ እንዲወስዱ፣ በአፈጻጸም ጊዜ ተገምቶ በቀረበው ብር 365,080.64 ግማሹን ብር 182,540.32 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት አፈጻጸሙን የመራው ከዋናው ፍርድ ውጪ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን የአፈጻጸሙን ውሳኔ በመሻር አፈጻጸሙ በዋናው ጉዳይ ላይ በመ/ቁጥር 01280 በ01/07/2002 ዓ/ም በተሰጠው አግባብ ሊመራ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አፈፃጸሙን የመራው ቤቱ በአይነት ቢከፈል ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ የሚሆን ስለመሆኑና በዋናው ክርክር ጊዜ የቀረበው የባለሙያ አስተያየት ስህተት መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም አመልካችም ከውጪ አገር መጥተው በቤቱ ላይ ለረዥም አመታት የኖሩበት መሆኑን በመገንዘብ አግባብነት ካላቸው ሕጎችና አስገዳጅነት ካለው የሰበር ውሳኔ አንጻር ሁኖ እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አፈፃጸሙ በዋናው ፍርድ መሰረት መመራት አለበት ብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በነበረው የዋናው ክርክር የአሁኗ ተጠሪ ከሳሽ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሁነው መከራከራቸውን፣ የግራ ቀኙን ክርክር የሰማውና ተገቢውን ማጣራት ያደረደገው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ተገቢ ነው ያለውን ፍርድ መስጠቱን፣ፍርድ ቤቱ በሰጠው ፍርድ ክርክር የተነሳበት ቤት ለአመልካች ቤቱን የሸጡትና የተጠሪ ወላጅ አባት (ኮሎኔል ዘውዴ ወ/ማርያም) ሚስት የነበሩት ወ/ሮ

እታፈራሁ ፈጠነ እና ተጠሪ (የሥር ከሳሽ) ያልተከፋፈሉ የጋራ ሀብት መሆኑን ከዚህ ቀደም በመ/ቁ/00923 ታህሳስ 01 ቀን 2000 ዓ/ም ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ከመሆኑም ሌላ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የሚያምኑት ጉዳይ መሆኑን፣ በዚሁ መሰረት ቤቱንና ቦታውን ለሁለት ማካፈል የሚቻል መሆኑንና አለመሆኑን፤ የሚካፈል ከሆነ የሚደርሳቸውን መጠን ገምቶ እንዲገልጽ የከተማው ማዘጋጃ ቤት በታዘዘው መሰረት በሰጠው ምላሽ ቦታውን ምድብ " A" ምድብ "B" አድርጎ በማካፈል ምድብ " A" 5 ክፍሎች ያሉበት ቤት ሆኖ ስፋቱም 640 ካሬ ሜትር መሆኑንና ግምቱም ብር 115,983.96 እንደሆነ፣ ምድብ " B " ደግሞ ስፋቱ 640 ካሬ ሜትር ሆኖ 3 ክፍሎች ያሉበት ቤት ሆኖ ግምቱም ብር 96,820 መሆኑን የገለጸ ስለሆነና ተከሳሽም ክርክር የተነሳበትን ቤት አጠቃልለው ይዘው የሚገኙ በመሆኑ ከሁለቱ ምድቦች መርጠው እንዲወስዱ ዕድል ቢሰጣቸውም ለመውሰድ ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም ሌላ ዕጣ ተጥሎ የደረሳቸውን እንዲወስዱ ቢደረግም ዕጣ ማንሳት እንደማይፈልጉ በመግለፃቸው ከሳሽ ዕጣ እንዲያነሱ ተደርጎ ምድብ "B" የደረሳቸው ስለሆነ የሁለቱን ምድቦች ድምር ግምት 212,803.96 ለሁለት ሲካፈል ብር 106,401 ስለሚሆን ተከሳሽ ልዩነቱን ብር 9,581 ለከሳሽ ከፍለው በምድብ "A" ያለውን ቤት እና ቦታ እንዲወስዱ ሲል መወሰኑን፣ 166 ወራት የቤት ኪራይ በተመለከተም ተከሳሽ ቤቱን የገዙት ከከሳሽ የጋራ ባለሀብት ከሆኑት ከወ/ሮ እታፈራሁ ፈጠነ ሚያዚያ 30 ቀን 1987 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ሆኖ እስካሁን ድረስ ቤቱን ይዘው የሚገኙ ሲሆን ከሳሽም ከቤቱ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በፍርድ ቤት እስከሚወሰን ድረስ ሊያውቁ የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም፣ ከሳሽ በቤቱ ላይ ግማሽ ባለመብት መሆናቸውን በፍርድ ከታወቀ በኋላም ከቤቱ የሽያጭ ገንዘብ ግማሹ ብር 65,000 ለከሳሽ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ክርክሩ ስለሚያሳይና ቤቱን በቅን ልቦና ይዘው ቆይተዋል ለማለት ስለሚቻል ሊከፈሉ አይገባም ሲል የወሰነ መሆኑን፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍ አይደለም በሚል ያፀናው መሆኑን፣ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካችም በሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን፣ተጠሪዋ ደግሞ የሰበር መስቀለኛ አቤቱታ ለዚህ ችሎት በመ/ቁጥር 68291 አቅርበው ይህ ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን በ25/01/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት መርምሮ የሐረሪ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 01280 በቀን 01/07/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/62252 በቀን 12/07/2003 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348 (1) መሰረት በማሻሻል የአሁኑ አመልካች የአሁኗን ተጠሪን የውርስ ድርሻ ይዘው ለተጠቀሙበት ጊዜ ኪራዩን ሊከፍሉ አይገባም፣ እንዲሁም

ለተጠሪዋ ምድብ "B" ውስጥ ያለውን የቤት ግምት በምድብ "A" ውስጥ ካለው የቤት ግምት ጋር ለማመጣጠን የልዩነት ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም፣የአሁኗ ተጠሪ የአሁኑ አመልካች ላከናወኑት ተጨማሪ የአራት ክፍሎች ግንባታ የወጣውን ወጪ በድርሻቸው መጠን ለመክፈል አይገደዱም በማለት ወስኖ ከዚህ በፊት በስር ፍርድ ቤት ተጀምሮ በነበረው የአፈጻጸም መ/ቁ/ 0547 ክርክር ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቶ በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት አፈጻጸሙ እንዲቀጥል በማለት ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች በተዘረጋው ስርአት አግባብ በመመራት ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሕጋዊ ባልሆነ እና ውሳኔውን ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ ውድቅ ሊደረደግ የሚችልበት አግባብ አይኖርም፡፡ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያስገነዝቡት አቢይ ነጥብ የፍርድ አፈጻጸም ስርአት ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለውጥበት ስርአት መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ ሲታይም የፍርድ አፈጻጸም ስለፍርድ አፈጻጸም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርድን በተግባር መተርጎም እንደመሆኑ መጠን የአፈጻጸም ስርአቱ ህጉን መሰረት ማድረግ ያለበትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን መሰረታዊ ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአነስተኛ ወጪ ጊዜና ጉልበት በተፋጠነና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም በሚያስችል አግባብ ሕግ አውጪ ያስቀመጣቸው መሆኑን የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ውሳኔው የማይፈፀመበት ሕጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩም በፍርድ ቤቱ ታይቶ ተገቢው እልባት የሚሰጥበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ይህ ድንጋጌ አፈጻጸሙን የያዘው ፍርድ ቤት አምፃፀሙን ምቹ ሁኔታዎች ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በተቻለ መጠን ፍርዱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ሊከተል የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ስለሆነም አንድን ፍርድ እንደፍርዱ ይዘትና መንፈስ ውጤት ባለው መልኩ መፈጸም የግድ የሚል ሲሆን ይህ ደግሞ የፍርድ አፈጻጸምን በተመለከተ በስነ ስርዓት ሕጉ የተዘረጉት ስርዓቶች በአግባቡ በማየትና ተፈፃሚ በማድረግ የሚከናወን መሆኑን የድንጋጌዎቹ ይዘት የሚያሳይን ጉዳይ ነው፡፡በህግ አግባብ የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 372 መሠረት ሥልጣን ያላቸው የአፈፃፀም ችሎቶች ስለ ፍርድ አፈፃፀም የተዘረጉትን ሥርዓቶች በመከተል እንደ ፍርዱ ከመፈፀም በቀር የአንድ ፍርድ ይዘትን በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆነ በማስፋት ረገድ ፍርድን የመተርጎም ሥልጣን የሌላቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡ የአፈጻጸም ክስ መቅረብ ያለበትም እንደ ፍርዱ እንዲፈፀም ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ለአፈፃጸም ማመልከቻቸው መሰረት ያደረጉትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት አያያዘው ያቀረቡት አከራካሪው ቤትና ቦታ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን የክፍፍል ውሳኔ እና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 68291 በ25/01/2005 ዓ/ም ተሻሽሎ የፀናውን ውሳኔ ነው፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ምድብ "B" የደረሳቸው መሆኑ ተረጋግጦ ከምድብ "A" ቦታ ጋር ያለው ድምር ግምት ብር 212,803.96 ሁኖ ይህ ገንዘብ ለሁለት ሲካፈል ብር 106,401.00 ስለሚሆን የአሁኑ አመልካች ልዩነቱን ብር 9,581.00 ለተጠሪ ከፍለው በምድብ "A" ያለውን ቤት እና ቦታ አመልካች ሊወስዱ እንደሚገባ ተወስኗል፡፡ ይህ የሚያሳየው በዋናው ክርክር ጊዜ ተገቢው መጣራት ተደርጎ በክፍፍሉ ስርዓትና ቅደም ተከተል ላይም ግራ ቀኙ ስምምነት ሊያደርጉ ባለመቻሉ የስር ፍርድ ቤት ተገቢ ነው ባለው መንገድ የቤቱና ይዞታው ግምት፣ግራ ቀኙ በንብረቱ ላይ ያላቸው ድርሻ እና ክፍፍሉ በእጣ ሲከናወነንም ግራ ቀኙ የደረሳቸው ቤትና ይዞታው አቅጣጫ ጭምር ተለይቶ መወሰኑን ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱና ይዞታው በዋናው ክርክር ጊዜ ምን ያህል ግምት እንዳለውና በምን አግባብ ክፍፍል እንደሚደረግ የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ታይቶና ተገቢው መጣራት ተደርጎ ከተወሰነ በኃላ በዋናው ክርክር ጊዜ ያለቀ የፍሬ ነገር ክርክር እንደገና በአፈጻጸም ተነስቶ በዋናው ክርክር ጊዜ የቀረበው ማስረጃ ሐሰተኛ/ተገቢነት/ የሌለው ነው ተብሎ የሚቀርበው ክርክርም ሆነ አፈጻጸም ችሎቱ በዚህ ረገድ የሚቀርበውን ክርክር ተቀብሎ ሌላ ማጣራት በማድረግ የቀደመውን ማስረጃ ሐሰተኛ ነው በማለት የሚቀርበውን የባለሙያ አስተያየት የሚቀበልበት የአፈጻጸም ክርክር አመራር ስርዓት የለም፡፡ በዋናው ክርክር ጊዜ ስለ ቤቱና ቦታ ክፍፍል የቀረበው የባለሙያ አስተያየት በንብረቱ የአይነት ክፍፍል የሚያመጣውን ጉዳት ያለማገናዘቡ በዋናው ክርክር ጊዜ ይታይ ይችል የነበረ እንጂ በዋናው ክርክር ጊዜ ተቀባይነት ከአገኘ በኂላ በአፈፃጸም ክርክር የሚታይ አይሆንም፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁኑን አመልካች በቤቱ ላይ ረዥም አመታት መኖራቸውን መሰረት አድርጎ የቀደምትነት መብት እንዳላቸው በማድረግ መወሰኑም ተገቢውን የክርክር ደረጃ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ በእርግጥ ሕጉን መሰረት አድርጎ የተሰጠ የንብረት ክፍፍል ውሳኔ በአፈፃጸም ጊዜ የንብረቱ ኢኮኖሚያዊ ዋጋ ትርጉም እንዳያጣ ተደርጎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አግባብ አመቺ በሆነ ሁኔታ ተመርቶ መፈፀም ያለበት መሆኑ እሙን ነው፡፡ ይህ ግን ተከራካሪ ወገኖች ሕጉ በዘረጋው ስርዓት ክርክር አቅርበውና ፍርድ ቤቶቹም በሕግ አግባብ አጣርተው የወሰኑትን የዋና ክርክር ውሳኔ በሚሽር መልኩ ሊከናወን የማይገባ መሆኑን ስለአፈጻጸም ስርዓት ከሚደነግጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘብ ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዋናው ውሳኔ ውጪ እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ ጋር ባልተገናዘበ መልኩ የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመሻር አፈጻጸሙ በዋናው ክርክር ጊዜ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ሊፈጸም ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጌዎች ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት ስላለገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራል ጠቅላይ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 90407 ጥቅምት 13 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አፈጻጸሙ በዋናው ጉዳይ ላይ በመ/ቁጥር 01280 በ01/07/2002 ዓ/ም በተሰጠው አግባብ ሊመራ ይገባል በማለት መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዘገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ይ**

የሰ/መ/ቁ. 104521

ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች**፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ታንጎት ሰጠ

**ተጠሪ**፡- አቶ ፈንታው ትኩ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በአ/ብ/ክ/መ/ በሰሜን ወሎ ወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካችና ተጠሪ ባልና ሚስት የነበሩና ጋብቻቸው በፍቺ በመፍረሱ የዚሁ ውጤት በሆነዉ የጋራ ንብረትን አስመልክቶ በተደረገው ክርክር፤- አመልካች አከራካሪው ቤትና መሬት የግሌ እንጂ የጋራ ንብረት አይደለም በማለታቸው ምክንያት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ካዬ በኂላ ንብረቱን አስመልክቶ ተጣርቶ ይወሰን ዘንድ ወደ ወረዳ ፍርድ ቤት በመመለሱ ምክንያት ጉዳዩን በተመለሰለት መሰረት በተጠቃሾቹ ንብረት ላይ በማከራከር ንብረቱ በአንደኛዉ ተጋቢ ስም መመዝገቡ ብቻውን በክልሉ የቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 74(1) መሰረት የግል አያደርገውም፣ በመሆኑም ቤቱ የጋራ ንብረት ሲሆን የእርሻ መሬቱ የአመልካች የግል ንብረት መሆኑን በማረጋገጥ ወስኗል፡፡ ቤቱን አስመልክቶ አመቺ በሆነ መንገድ ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚሁ መሰረት ለማስፈጸም በተያዘው ቀን የግራቀኙ ቤቱን አስመልክቶ በእርቅ ለሁለት ተካፍለን ለመኖር ተስማምተናል በማለት ወደ ፍርድ ቤቱ ቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህ/ቁ. 277(1) መሰረት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ የይግባኝ ጊዜ ካለፈ በኂላ ቅሬታቸዉን ለከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ጥያቄያቸዉ ተቀባይነት በማጣቱ በፍ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁ 325 መሰረት መዝገቡ በመዘጋቱ በቀጣይነት ጉዳዩን ያየው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ቅሬታውን ባለመቀበል በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት የጸደቀው ስምምነትን አስመልክተው

በአፈጻጸም መ/ቁ 04586 ላይ ማዘጋጃ ቤቱ የአንደኛው ድርሻ ከ100 ካ.ሜ ያነሰ በመሆኑ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ነው በማለቱ ቤቱ በመነሻ ዋጋ እንዲሸጥ ትእዛዝ በመስጠቱ አመልካች አፈጻጸሙን አስመልክቶ በእርቅ ስምምነት መሰረት ባለመፈጸሙ ክፍፍሉ በእርቁ መሰረት ሊፈጸም ሲገባ ቤቱ እንዲሸጥ መባሉ ዋናዉን ፍርድም ሆነ እርቁን የሚጻረር ነው በማለት ወደ ክልሉ ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልክተዉ ጉዳዩን ያየው ችሎትም በእርቁ ስምምነት መሰረት በአይነት መካፈል የማይቻል መሆኑን የከተማው ማዘጋጃ ቤት በሰጠው መረጃ መሰረት መሆኑ በመረጋገጡ የተሰጠ ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ፡- ከተጠሪ ጋር አከራካሪውን ቤት መጋቢት 13 ቀን 2000 ዓ/ም ባደረግነው የእርቅ ስምምነት ክፍፍል አድርገን በፍርድ ቤት መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ/ም ጸድቋል፡፡ ቤቱን ስጠቀምበት ቆይቼ ተጠሪ በቤቱ ካርታ ሊያሰራ ጠይቆ ቦታህ 100 ካ.ሜ በታች በመሆኑ ሊሰራልህ አይችልም ስለተባለ ፍርድ ቤቱ እኔን ጠርቶ ቦታቻው ተሸጦ እንድትካፈሉ ተባለ ፤በውላችን መሰረት ካርታ ማሰራት ሲገባው፤ ቦታው ተሸጦ እንድንካፈል መወሰኑ የሚጎዳኝ ነው፤ ከ100 ካ.ሜ በታች ቦታ ካርታ ይሰራላቸው ነበር፤ ተጠሪ በራሳቸው ቦታ ካርታ ያላሰሩት በቸልተኝነታቸዉ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሰረት ችሎቱም የግራ ቀኙ በስምምነት ጨርሰው ፍርድ ቤቱም ይህንኑ መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ/ም ተቀብሎ በስምምነታቸው መሰረት መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ በተጠሪ አመልካችነት በ26/4/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሀራጅ እንዲሸጥ መወሰኑን በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙን በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክሯል፡፡

ተጠሪ በሰበር መልሳቸው የሚሉት ፡- አመልካች እኩል አላካፍልህም በማለቷ 100 ካ.ሜ ደግሞ መውጫ መግቢያ ሊኖረዉ አይችልም በሚል ተሸጦ እንድንካፈል መወሰኑ ባግባቡ ነዉ፣ ስምምነታችን እኩል ለመካፈል እንጂ ለአንዱ ያነሰ የሚል አይደለም፣ ባጠቃላይ ቤትና ቦታዉ 250 ካ.ሜ ነው፣ አመልካች ቦታዉን ተካፍለን የየራሳችንን ካርታ እንዳንይዝ የተጠሪ ድርሻ 100 ካ.ሜ ብቻ ነዉ በማለታቸው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በስምምነታችን መሰረት መዝገቡን ዘጋው ማለት፣ ቤትና ቦታው ክፍፍል ተጠቃሎ ተፈጽሟል ማለት አይደለም፣ በስምምነቱ መሰረት ተካፍሎ ካርታ በእጃችን አልገባም፤ መሀንዲስ በቦታው ተገኝቶ መካፈል እንደማይመች ገልጿል፡፡ በመሆኑም የስር ውሳኔ ሊጸናልኝ ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ድጋሚ ይሸጥ መባሉ ስህተት ነው፣ አመልካች 100 ካ.ሜ. ነው አላልኩም፣ የተጠሪ ድርሻ 76.88 ካ.ሜ ብቻ ነዉ፡፡ ተጠሪ ስምምነቱን በማፍረሱ 5000 መቀጮ ያለበት በመሆኑ

ይህን ለመንግስት እንዲከፍል ይወሰን፣በመሆኑም የስር ዉሳኔ ሊሻር ይገባል ሲሉ ተራክረዋል፡፡ ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተጠቀሰዉ ሲሆን እኛም የግራ ቀችን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መርምረናል፡፡

እንግዲህ ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር አጠቃላይ የክርክሩን ይዘት እንዳየነዉ የግራቀኙ ጋብቻ በፍቺ በመፍረሱ ምክንያት ይህን ተከትሎ በተጀመረዉ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ በዋናው ክርክር አከራካሪዉ ቤት የተጋቢዎቹ የጋራ ንብረት ነዉ፣ የእርሻ መሬቱ የአመልካች የግል ሀብት ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በአፈጻጸም በተጀመረዉ ክርክር ቤትና ቦታዉን እኩል ለመካፈል ተስማምተው ስምምነቱን መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ/ም በፍርድ ቤት ካጸደቁ በኋላ በተግባር ለመከፋፈል አመቺ ያለመሆኑ በመረጋገጡ ታህሳስ 6 ቀን 2005 ዓ/ም ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ባልና ሚስቱ እንዲካፈሉት ተወስኗል፡፡

በመሰረቱ ባልና ሚስቱ በጋብቻ ጸንተዉ ባሉበት ጊዜ ባፈሩት ንብረት ላይ የጋራ ባለሀብቶች እንደሚሆኑ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 73 እና 74 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አከራካሪዉን ቤትና ይዞታ አስመልክቶ የጋራ ሀብት ነዉ ተብሎ ተወስኖ ያለቀ ሲሆን እያከራከረ ያለዉ አፈጻጸምን አስመልክቶ በእርቅ ለመካፈል የግራ ቀኙ ከተስማሙ በኋላ በማዘጋጃ ቤቱ በአይነት መካፈል አለመቻሉን በተገለጸዉ መሰረት ፍርድ ቤት በሀራጅ ተሸጦ ሊካፈሉ ይገባል በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ነዉ፡፡ አከራካሪዉ ንብረት ላይ ተከራካሪዎቹ የጋራ ባለሀብት ነው ተብሎ ከተወሰነ ክፍፍሉ መደረግ ያለበትም በዋናው ውሳኔ፤ስለባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል በሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስለ አፈፃጸም የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በዚህ አግባብ አፈጻጸሙን ከመምራት በተጨማሪ የግራ ቀኙ ያደረጉትና በፍርድ ቤት ያጸደቀ የእርቅ ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠም እርቁ እንደ ፍርድ የሚቆጠርና ሊፈፀም የሚገባው ሲሆን አፈጻጸሙ የሚመራውም በሕጉ አግባብ ነው፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ ሊካፈሉትም የሚገባዉ በተስማሙት መንገድ ነዉ፡፡ በስምምነቱ መሰረት ሊፈፀም ካልተቻለ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ባለው መሰረት ማስፈፀም እንዲሚችል ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ ይዘት መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ደግሞ በቤተሰብ ህጉ በተቀመጠው መፍትሄ መሰረት አፈጻጸሙን ለመምራት የሚያስችል፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር እንደተገነዘብነዉ ተጠሪና አመልካች በጋራ ሀብታቸዉ ክፍፍል መጠን ላይ በፍርድ ቤት የጸደቀ ስምምነት መኖሩ ሳይክዱ በዚህ ሰምምነት መሰረት ንብረቱ በአይነት ሊካፈል የሚችል በመሆኑ ላይ ግን ስምምነት ላይ ያለመድረሳቸዉን ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ክፍፍሉ አመቺ በሆነ መንገድ እንዲያልቅ ሊያደርግ (ሊያስፈጽም )የሚችል መሆኑን

ከፍ.ብ.ሥ.ሥ/ህ ቁ 392 እና ከክልሉ ቤተሰብ ህጉ ከአንቀጽ 101፣102 እና 103 ስር ክፍፍል እንዴት ሊፈጸም እንደሚችል ሰፍሯል፡፡ እንግዲህ እያከራከረ ያለዉ የአንደኛዉ ወገን ድርሻ በማነሱ ምክንያት ካርታ ሊወጣለት አልተቻለም የሚል በመሆኑ ክፍፍሉ አጠቃላይ የንብረት መጠን ማእከል በማድረግ በእኩልነት መርህ የሚከናወን መሆኑ ተጠቃሹ ህግ ግዴታ የጣለ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ቤቱንና ይዞታዉን በመለየት የእርሻ መሬቱ የአመልካች የግል ንብረት ነዉ ሲሉ የወሰኑት በዚህ ችሎትም አከራካሪ ባለመሆኑ የሚነካ አይደለም፡፡ የቤቱን ክፍፍል አፈጻጸም አስመልክቶ ቤቱ የጋራ በመሆኑና ክፍፍሉ ላይ ስምምነት ባለመኖሩ በሀራጅ ተሸጦ ይካፈሉ የተባለዉ የክልሉን የቤተሰብ ህጉን መርህ ሊከተል ስለሚገባዉ ከአንቀጽ 101-103 በተጠቀሰዉ መሰረት ኣጠቃላይ ይዞታዉ 250 ካ.ሜ ለመሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ ባልና ሚስቱ በፍርድ ቤት በፀደቀው ስምምነት መሰረት ይካፈሉ፣በዚህ መሰረት ክፍፍሉ የማይቻል ከሆነ አንዱ ላንዱ በስምምነቱ ድርሻ መጠን(Proportion) ከፍሎ እንዲያስቀር፣ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ቤቱ በገበያ ዋጋ ተሸጦ በስምምነቱ ድርሻ መጠን(Proportion) መሰረት የሽያጭ ገንዘብ እንዲካፈሉ ማድረግ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቤቱ ማካፈል አልተቻለም፣ ስለተባለ ብቻ ህጉ ያስቀመጠዉን ቅደም ተከተል ባለማገናዘብ በሀራጅ ተሸጦ ይካፈሉ መባሉ የግራ ቀኙን በቤቱ የመጠቀም ፍላጉት (ነጻነት) ስለሚገድብ ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ በመሆኑ ያለቅድመ ሁኔታ በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠዉን ትእዛዝ ክፍል ሊታረም የሚገባዉ ነዉ ብለናል፡፡

ባጠቃላይ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለአፈጻጸም የቀረበዉን አከራካሪዉን ቤትና ይዞታ በመቁ.04585 በእርቁ መሰረት ሊፈጸም ባለመቻሉ አከራካሪዉ ንብረት አመቺ በሆነ መንገድ ሊካፈል ሲገባ በሀራጅ ይሸጥ ተብሎ መወሰኑ የቤተሰብ ህጉን የክፍፍል እኩልነት መርህ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአ/ብ/ክ/መ/ የወልድያ ወረዳ ፍርድ ቤት በአፈጻጸም መ.ቁ 04586 መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ,የሰሜን ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት 08157 በ26/04/2005 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰብ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 35229 ሰኔ 24ቀን2006 የሰጠው ወሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ዉሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አከራክሪውን ቤትና ይዞታ የግራቀኙ የጋራ ሀብት በመሆኑ ክፍፍሉን አስመልክቶ በክልሉ የቤተሰብ ህግ ከአንቀጽ 101 እስከ 103 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት 250 ካ.ሜ ለመሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ ባልና ሚስቱ በፍርድ ቤት በፀደቀው ስምምነት መሰረት

ይካፈሉ፣በዚህ መሰረት ክፍፍሉ የማይቻል ከሆነ አንዱ ላንዱ በስምምነቱ ድርሻ መጠን(Proportion) ከፍሎ እንዲያስቀር፣ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ቤቱ በሓራጅ ተሸጦ በስምምነቱ ድርሻ መጠን (Proportion)፣ ስምምነት አለመኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ በእኩልነት መርህ መሰረት የሽያጭ ገንዘብ እንዲካፈሉ ብለናል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሰረት የወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት አፈጻጸሙን እንዲያስቀጥል በፍ.ብ.ሥ.ሥ..ህ.ቁ 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

3. የግራ ቀኙ የወጪ ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

መስከረም 12 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሩ/ለ**

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ. 97829

ሚያዝያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች:-** አቶ ሁሴን ሰይድ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** የየካ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት ጽ/ቤት አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05348 ጳግሜ 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21044 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና፣ የሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 21382 ታህሳስ 23 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲተረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በሊዝ የተገዛ ቦታ ክፍያ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ ባቀረበው ክስ፣ ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር ጥቅምት 8 ቀን 1998 ዓ.ም በተዋዋለው የሊዝ ውል መሰረት በቀድሞው ቀበሌ 16/17/18 ክልል ስፋቱ 425 ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ በመግዛት ቦታውን ተረክቧል፡፡ የቦታው ጠቅላላ ዋጋ ብር 430312.80 /አራት መቶ ሰላሳ ሺህ ሶስት መቶ አሰራ ሁለት ብር ከሰማንያ ሳንቲም/ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ተከሳሽ 20% ከፍሏል፡፡ ተከሳሽ የሁለት አመት የቸሮታ ጊዜ ተሰጠቶት ቀሪውን የሊዝ ዋጋ ከ2002 ዓ.ም እስከ 2020 ዓ.ም በየአመቱ ከፍሎ ለመጨረስ ግዴታ ገብቷል፡፡ ተከሳሽ በሊዝ ውሉ መሰረት የ2001 ዓ.ም የሊዝ ክፍያ ወለድና ቅጣት የ2003 ዓ.ም የሊዝ ክፍያ ወለድና ቅጣትና የ2003 ዓ.ም የ275 ቀናት የሊዝ ክፍያ ወለድና ቅጣት በድምሩ ብር 153,820.29 /አንድ መቶ ሃምሳ ሶስት ሺ ስምንት ሃያ ብር ከሃያ ዘጠኝ ሣንቲም/ አልከፈለም፡፡ ከሳሾች ተከሳሽ ገንዘቡን እንዲከፍል ቢጠየቅ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገንዘቡን ከባንክ ወለድ ጋር እንዲከፍል ዉሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

2. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ጉዳዩ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ የተወሰነ ስለሆነ በፍርድ ቤት መታየት የለበትም በማለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቦ ፍ/ቤቱ በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተከሳሽ /አመልካች/ ለክሱ ባቀረበው የመከላከያ መልስ ከሳሽ በሊዝ የሸጠልኝን ቦታ በመናፈሻ ክልል ውስጥ ሆኖ በመገኘቱ ቦታው እንዲቀየር ተወስኖ ቦታውን በመቀየር አንድ አመት ከአምስት ወራት ወስዶበታል ከሳሽ ከአንድ አመት ከአምስት ወራት በኋላ ቀይሮ የሰጠኝ ቦታ ባለሶስት መዓዘን ከመሆኑም በላይ የስልክና የመብራት ፖል /ምሰሶ/ የነበረበት በመሆኑ መሰሶው እንዲነሳ ጥያቄ አቅርቤ ከሳሽም ምሰሶው እንዲነሳ ሲፃፃፍ ቆይቶ፣ የምሰሶውን ማስነሻ ወጭ ተከሳሽ ክፍያ ቦታውን ግንባታ ለመጀመር በሚያመች ሁኔታ የተረከብኩት፣ ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ነው፡፡ ከሳሽ በሊዝ ውሉ መሰረት ቦታውን ለግንባታ ምቹ አድርጎ ማስረከብ ስላልቻለ፣ ቦታውን ካስረከበበት ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የሁለት ዓመት የችሮታ ጊዜ፣ የግንባታ መጀመሪያና ማጠናቀቂያ ጊዜ የሊዝ ውሉን በማሻሻልና በሊዝ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር አንቀፅ 14/3/ አንቀፅ 36 /7/ የተደነገገ በመሆኑ፣ ይኸም የአዲስ አበባ አስተዳደር ባወጣው የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዓት መሰረት አቅርቤ ያስወሰንኩ በመሆኑ የከሳሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ያሰናብተኝ በማለት ተከራክሯል፡፡
3. የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከሳሽና ተከሳሽ ግንቦት 6 ቀን በ1999 ዓ.ም ያደረጉት የሊዝ ውል መሰረት ተከሳሽ እስከ 2001 ዓ.ም የችሮታ ጊዜ ተሰጥቶታል፡፡ የመመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 37/6/ የግንባታ መጀመሪያና ማጠናቀቂያ ጊዜ ስለማራዝምበት ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን፣ የቸሮታ ጊዜ የሚራዘም ስለመሆኑ አይደነግግም ተከሳሽ የአስተዳደሩ የህዝብ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወስኖልኛል ቢልም ውሳኔ አስገዳጅነት የለውም፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ክስ የቀረበበትን የሊዝ ኪራይ ከቅጣትና ከወለድ ጋር ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች ለከተማው ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡
4. አመልካች የካቲት 13 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ተጠሪ ቦታውን ነፃ አድርጎ ያስረከበኝ ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ ቦታውን ለግንባታ ምቹ አድርጎ የማስረከብ ግዴታዉን ሣይወጣ አመልካች የሊዝ ክፍያ እንዲከፍል የመጠየቅ መብት የለውም፡፡ ጉዳዩ በደንብ ቁጥር 48/2004 መሰረት ታይቶ፣ ተጠሪ የሊዝ ውሉን በማደስ፣ የቸሮታ ጊዜ፣ የግንባታ መጀመሪያና ማጠናቀቂያ ጊዜ እንደሰጠኝ አስተዳደራዊ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 14 /3/ እና አንቀፅ 37 /6/ መሰረት ተጠሪ መፈፀም ሲገባው የሊዝ ክፍያ እንዲከፍል በማለት ያቀረበው ክስ የሕግ

መሰረት የለውም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

5. ተጠሪ መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካች የሊዝ ውሉ ከነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ይታሰብልኝ በማለት የሚከራከረው ከግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለው መመሪያ ቁጥር 11/2004 ወደ ኂላ ሄዶ እንዲሰራለት በመጠየቅ ነው፡፡ ሆኖም ለአመልካች ጉዳይ ተፈፃሚነት ያላቸው በወቅቱ ስራ ላይ የነበሩት መመሪያዎች እንጅ መመሪያ ቁጥር 11/2004 ስላልሆነ የአመልካች ክርክር የሕግ መሰረት የለውም፡፡ በደንብ ቁጥር 48/2004 መሰረት ታይቶ የተሰጠ የቅሬታ ሰሚ ውሳኔ አስገዳጅነት ያለው አይደለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሚያዝያ 1 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ መመሪያ ቁጥር 11/2004 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ያለው በመሆኑ የተጠሪ ክርክር ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

6. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ የጠየቀውን የሊዝ ክፍያ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን፣ መርመረናል፡፡

7. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን፣ በአመልካችና ተጠሪ ክርክር የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች አግባብነት ካላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር የሕግ ማዕቀፎች ጋር በማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪ የሊዝ ውል የተዋዋሉት ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ በገለፀው ጊዜ፣ ማለትም ጥቅምት 8 ቀን 1998 ዓ.ም ቢሆንም፣ ተጠሪ በሊዝ ውሉ መሰረት ለተጠሪ የሸጠው ቦታ የመናፈሻ ክልል ውስጥ ሆኖ በመገኘቱ፣ ቦታ መቀየሩን፣ ቦታውንም ለመቀየር አንድ አመት ከአምስት ወራት የወሰደ መሆኑን አመልካች ያቀረበውን ክርክር ተጠሪ ክዶ አልተከራከረም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአመልካች ተቀይሮ የተሰጠው ቦታ ላይ የመብራትና የስልክ ምሰሶዎች የነበሩ መሆኑንና አመልካች በፍትሐብሔት ሕግ ቁጥር 1862 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ጉዳቱን ለመቀነስ የስልክ እና የመብራት መሰሶ ከቦታው ለማንሳት የሚያስፈልገውን ወጭ በራሳቸው ሸፍነው የስልክና የመብራት ምሰሶዎቹ ተነስተው ቦታው ለግንባታ ዝግጁ ሆኖ የተሰጣቸው ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሊዝ ለአመልካች የሸጠውን ቦታ ነፃ አድርጎና ለግንባታ ዝግጁ አድርጎ የማስረከብ ኃላፊነት ተጠሪ ያለበት መሆኑ፣ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጭብጥ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይህም ተጠሪ በሊዝ ውል የተመለከተውን ቦታውን ነፃ በማድረግ በተከራዩ /አመልካች/ የማስረከብ ግዴታውን የተወጣው ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም መሆኑን ያሳያል፡፡

8. ተጠሪ እስከ ሚያዝያ 23 ቀን 2003 ዓ.ም በሊዝ ውሉ የተመለከተውን መሰረታዊ ግዴታ አለመወጣቱ፣ የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ መሬት ሊዝ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 3 በጨረታ የተሰጡ ቦታዎች በመስሪያ ቤቱ ችግር ምክንያት በውሉ መሰረት ማስረከብ ካልተቻለ ውሉ እንደገና ይታደሳል፣ የችግር ጊዜና የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ፣ የሊዝ ማጠናቀቂያ ጊዜ እንደገና እንደ አዲስ የሚወሰን መሆኑን ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም የመመሪያ ቁጥር 37 አንቀፅ 6/መ/ መሰረት ቦታውን ለማስረከብ ካልተቻለ፣ ተጨማሪ የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ ሊሰጥ እንደሚችል የሚደነግግ ሲሆን በአንቀፅ 38 ንዑስ አንቀፅ 3 ተጨማሪ የማጠናቀቂያ ጊዜ ሊፈቀድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

9. የስር ፍርድ ቤት የመመሪያውን ቁጥር አንቀፅ 37 ብቻ በማየት፣ መመሪያው የቸሮታ ጊዜ የማራዘም ድንጋጌ የለውም በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ለማየት ይቻላል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በዚህ ሰበር የሚከራከረው መመሪያው ወጥቶ ስራ ላይ የዋለው ግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም ስለሆነ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ነው፡፡ ሆኖም ይህ የተጠሪ ክርክር በመመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 83/ሀ/ ይህ መመሪያ ከመወጣቱ በፊት በአስተዳደሩ ቦርድ ወይም በመሬት አስተደደር ግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን የተፈረሙ ውሎች ወይም የተከናወኑ ስራዎች ህጋዊነታቸው ተጠብቆ በዚህ መመሪያ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል በማለት በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ፣ የተጠሪ ክርክር፣ ይህን የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና ህጋዊ መሰረት የሌለው ክርክር በመሆኑ አልተቀበለነውም፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው የህግ ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ውሉን በማደስ፣ ከሁለት አመት የሊዝ ክፍያ የቸሮታ ጊዜ፣ የሊዝ ክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜና የግንባታ መጀመሪያና የግንባታ ማጠናቀቂያ የጊዜ የሚያሳይ ሌላ ውል ሳያቀርብ፣ አመልካች የሊዝ ክፍያ እንዲከፍል ያቀረበው ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባው አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ክፍያ፣ እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔና ይግባኝ ሰሚው ችሎትና የሰበር ችሎቱ ይህንን ውሳኔ በትዕዛዝ ማፅናታቸው አመልካች በመመሪያ ቁጥር 11/2004 የተረጋገጠላቸውን መብት የሚያጣብብና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ሊዝ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 11/2004 በአንቀፅ 14/3/፣ በአንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 6/ለ/ እና በአንቀፅ 38 ንዑስ አንቀፅ 8 የሚጥስ ከመሆኑ በተጨማሪ የከተማው ምክር ቤት ባወጣው ደንብ ቁጥር 48/2004 መሰረት በክፍለ ከተማው የህዝብ አቤቱታና ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የካቲት 8 ቀን 2005 የሰጠው ውሳኔ አስገዳጅነት የሌለው ነው በማለት የሰጠው የህግ ትርጉም ስህተት ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ አተረጓጎም፣ በደንብ ቁጥር 48/2004

አንቀፅ 11/1/ እና አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 ቅሬታና አቤቱታ ሰሚ የስራ ሂደቱ የቀረበለትን ጉዳይ በማጣራት የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ውሳኔ እንደሚሰጥ፣ የተደነገገውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ የስር ፍርድ ቤት ትርጉም በደንብ ቁጥር 23 ድንጋጌዎች ያላገናዘበና በአጠቃላይ የከተማው አስተዳደር ደንብ ቁጥር 48/2004 የወጣለትን መሰረታዊ ዓላማና ደንቡን በማውጣት ሊያሳካው የሚፈልገውን ግብ የማያገናዘብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

11. ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው የሰበር ችሎት የአመልካች የሊዝ ክፍያ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የከተማው አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ከነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የሁለት አመት የሊዝ መክፈያ የቸሮታ ጊዜ፣ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ፣ ተጠሪ የጠየቀውን የ2002 ዓ.ም የ2003 ዓ.ም እና የ2004 ዓ.ም የሊዝ ክፍያ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ይ**

የሰ/መ/ቁ. 107442

መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** አቶ ሞገስ ናደው እንዳይላሉ

**ተጠሪ፡-** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስተር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጥብቅና የዲሲፕሊን ጋር የተያያዘ ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤ 78/06 ግንቦት 22 ቀን 2006 ዓ.ም አመልካች ለአንድ ዓመት ከጥብቅና ሙያ እንዲታገዱ በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በሚኒስትሩ ጸድቆ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ወ/ሮ አስቴር ወ/ሚካኤል ለዲሲፕሊን ጉባኤው ታህሳስ 30 ቀን 2006 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡የግለሰቧ አቤቱታ ይዘትም የአሁኑ አመልካች ከግለሰቧ ጋር በገቡት የጥብቅና አገልግሎት ውል መሰረት ጉዳዩን በመደበኛው የክርክር ሂደት ክስ ማቅረብ ሲገባቸው በተፋጠነ ስርነ ስርዓት ክስ አቅርበው ግለሰቧን ለተጨማሪ ወጭና ጉዳት መዳረጋቸውን፣ የአሁኑ አመልካች ከግለሰቧ ለቅድሚያ ክፍያ ብር 20,000.00(ሃያ ሺህ) ተቀብለው ደረሰኝ የከለከሏቸው፣ውሉ ከተቋረጠ በኋላም ገንዘባቸውን አልመለስም ያሏቸው መሆኑን መዘርዘራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም በመጀመሪያ ከግለሰቧ ጋር በሚገባ ተመካክረውና ግለሰቧ አሉኝ በአሏቸው ማስረጃዎች መሰረት ክሱን በተፋጠነ ስነ ስርዓት መሰረት አቅርበው ለክሱ መነሻ የሆነው ቼክ ለመያዣነት የተሰጠ መሆኑ ሲገለጽላቸው የክስ ማሻሻል ጥያቄ ክሱ ከመሰማቱ በፊት ማቅረባቸውን፣የቅድሚያ ክፍያው ብር 20,000.00 ሳይሆን ብር 10,000.00 መሆኑንና ጉዳዩ በጅምር ላይ እንዳለ ውክልናው የተሻረ በመሆኑ ሊጠየቁ የማይችሉ መሆኑን ዘርዝረው ተከራክራል፡፡ በዚህ መልክ የግራ ቀኙ ክርክር የቀረበለት ጉባኤውም አመልካች የግለሰቧን ክስ በመደበኛ ክስ ማቅረብ ሲገባቸው በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ክስ ማቅረባቸው ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ የቅድመ ክፍያውን በተመለከተ አመልካች በከፊል ክደው ቆይተው ምስክሮች ሊሰሙ ሲሉ ማመናቸው የግለሰቧን ምስክሮች ጊዜ ከማባከኑም በላይ በጉባኤው ስራ ላይም ከፍተኛ ጫና የፈጠረና ከአንድ ጠበቃ የማይጠበቅ ተግባር መሆኑን

እንዲሁም አመልካች በክርክሩ ሂደት ግለሰቧን ከጉባኤው አዳራሽ ውጪ ምንም ልታደርጊኝ አትችይም አስር ሺህ ብር ከፍዬ ከሁለት ሳምንት በኋላ ወደ ስራ እገባለሁ በማለት የዛቻ አነጋገር መናገራቸው ከጠበቃ የማይጠበቅ ተግባር ሁኖ መገኘቱን ዘርዝሮ አመልካች ክሱን ያቀረቡበት አግባብ በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 30(2)፣ለጥብቅና አገልግሎት ለተቀበሉት ገንዘብ ደረሰኝ አለመስጠታቸው ደግሞ በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 8(1) ከጉባኤው አዳራሽ ውጪ በግለሰቧ ላይ ለተናገሩት ንግግር ደግሞ በደንብ ቁጥር 52/92 አንቀጽ ቁጥር 24(3(ለ))((2)) መሰረት ለአንድ ዓመት ከጥብቅና ስራቸው እንዲታገዱ በማለት የውሳኔ ሃሳብ አቅርቦ ይኼው የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሩ ጸድቋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክስ አመሰራረቱ ግለሰቧ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሁነው በሰጡት ማስረጃ መሰረት ሙያውን ተመርኩዘው ያቀረቡት ሁኖ እያለ እና በኋላም ቼኩ በመያዣነት የተሰጠ መሆኑ ሲገለጽላቸው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የክስ ማሻሻል ጥያቄ ለፍርድ ቤቱ አቅርበው ተቀባይነት ያጡ መሆኑን፣ለጥብቅና አገልግሎት ክፍያም ደረሰኝ ያልተሰጠው ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ ከግለሰቧ ጋር በተፈጠረው አለመግባባት መሆኑንና አመልካች ግለሰቧ ላይ ከጉባኤው አዳራሽ ውጪ ዛቻ ፈጽመዋል የተባለው የአንድ ወገን የቃል አቤቱታ ተሰምቶና በማስረጃ ሳይጣራ መሆኑን ዘረዝረው በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም አመልካች የዲሲፒሊን ጥፋት ፈፅመዋል ተብሎ ለአንድ ዓመት ከጥብቅና ስራ እንዲታገዱ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ መሰረት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የታቻለው የጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤ አመልካች የስነ ምግባር ጥፋት ፈፅሟል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰበት የመጀመሪያው ምክንያት አመልካች የአቤቱታ አቅራቢዋን ግለሰብ ክስ ለፍርድ ቤት ሲያቀርቡ በተፋጠነ ስነ ስርዓት መሰረት ሊያቀርቡ አይገባም ነበር በሚል ነው፡፡አመልካች ይህንኑ የጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት የለውም የሚሉት ክሱ ሊመሰረት የቻለው ግለሰቧ ለጠበቃው በሰጧቸው ማስረጃዎች አግባብ ነው፣ክሱ ከቀረበ በኋላ ግለሰቧ ለአመልካች በአሳወቁት ማስረጃ መሰረትም የክስ ላሻሻል ጥያቄ ለፍርድ ቤቱ በጊዜው አቅርበው የነበሩ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ የጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤ፣በጠበቃ ላይ ያቀረበውን የዲስፒሊን ክስ ሊወስን የሚገባው በጠበቃው ላይ የቀረበውን የዲስፒሊን ክስና ማስረጃ እንደዚሁም በጠበቃው በኩል የቀረበውን መልስና ማስረጃ በመመርመር እንደሆነ በፌዴራል

ፍርድ ቤቶች የጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 109/1992 አንቀፅ 24(3) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የዲሲፕሊን ጉባኤው ከአንድ ጠበቃ በክስ አቀራረብ ሂደት የሚጠበቁ ሙያዊ ግዴታዎች ምን እንደሆኑ ከዘረዘረ በኃላ አመልካች የዲሲፕሊን ጥፋት ፈፅመዋል ያለው ጉዳዩ በጅምር ላይ ከማለት ያለፈ በመልሳቸው ላይ በቀጥታ የካዱት ነጥብ የለም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ለጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባኤ የካቲት 07 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት የመልስ ማመልከቻ ክሱ መቅረብ የሚገባውን ስርዓት ከግለሰቧ ጋር ተማምነው በስርዓቱ መሰረት ማቅረባቸውን በተራ ቁጥር አንድ ስር፣እንዲሁም ግለሰቧ ክሱ ከቀረበ በኂላ በዋስትና በተያዘው ቼክ ምክንያት በመኖሪያ ቤታቸው ላይ ሀራጅ መውጣቱን እና እዳ መክፍል መጀመራቸውን ለአሁኑ አመልካች ሲያሳውቋቸው በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት አድርገው ክሳቸው ተሻሽሎ እንዲቀርብ ግለሰቧ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ተስማምተው ክስ ከመሰማቱ በፊት አስቀድመው ለፍርድ ቤቱ የክስ ማሻሻያ  አቤቱታ ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ ጥያቄውን ማቅረባቸውን በመልሳቸው ተራ ቁጥር ሶስት ስር የዘረዘሩ መሆኑን ከመልስ ማመልከቻቸው ይዘት ተመልክተናል፡፡ ይህንኑ ክርክራቸውን በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሐምሌ 05 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻም ያቀረቡት መሆኑን ከማመልከቻው ይዘት ተመልክተናል፡፡ ይህ የአመልካች ክርክር ይዘት በግልጽ የሚያሳየው ደግሞ አመልካች ከመነሻውም ክሱን ያቀረቡት አግባብ የሙያው ስነ ምግባር በሚፈቅደው ስርዓት መሆኑን እንጂ ከደንቡ ውጪ መሆኑን አምነዋል የሚያሳየኝ አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ከስር ጀምሮ ባቀረቡት ክርክር ክሱን ያቀረቡበትን ስርዓት ግለሰቧ ጋር በግልጽ ተማምነውና በእጃቸው ላይ ባሉት ማስረጃዎች ስለመሆኑ ገልጸው እያለ አልካዱም በማለት በዲሲፒሊን ጉባኤው አመልካች አልካዱም ተብሎ የተመዘገበው ተገቢውን የክርክር አመራር የተከተለ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም የዲስፒሊን ጉባኤው በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 3 በጠበቃው ላይ የሚቀርበውን ክስና ማስረጃ ብቻ ሣይሆን በጠበቃው የሚሰጠውን መልስና የመከላከያ ማስረጃ በመመርመር ውሣኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የተደነገገውን ድንጋጌ የጣሰ ነው፡፡ እንግዲህ አንድ ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ የሚያቀርብበት ሕጋዊ አግባብ ምንድነው? የሚለውን ስንመለከትም ሙያው የሚፈቅደውን የስነ ምግባር ደንብ ተከትሎ መሆን እንደአለበት የሚታወቅ ነው፡፡

በመሰረቱ በማንኛውም ጠበቃ ሕግን ለማስከበርና ፍትህን ለማስገኘት የፍትህ አስተዳደሩን የሚገባ ኃላፊነት ያለበት መሆኑንና ጠበቃው ልዩ ደንበኛውን ለሌሎች የሕግ ባለሙያዎች ተከራካሪ ወገኖች ለፍርድ ቤት፤ለሙያውና ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ያለበትን የሙያ ኃላፊነት በቅንነት፤ በታማኝነትና በእውነተኝነት የመወጣት ሙያዊ ግዴታ ያለበት መሆኑ በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 3 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ በትጋት

የመከታተል አፋጣኝና ፍትሀዊ ውሳኔ ለማግኘት ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ ሁሉ በጥንቃቄና በወቅቱ የመፈፀም ሙያዊ ግዴታ ያለበት መሆኑ በደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከደንበኛቸው ጋር ተነጋግረው ክሱን በተፋጠነ ስነ ስርዓት ማቅረባቸውን ገልጸውና በኋላም ግለሰቧ እዳውን መክፈል መጀመራቸውን ለአመልካች ሲገልፁ ክሱን ለማሻሻል ጥረት ያደረጉ መሆኑን አመልካች ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ክሱን ያቀረቡት ለሙያውና ለግለሰቧ ያላቸውን የሙያ ኃላፊነት በአጓደለ መልኩ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ አመልካች ለሙያውና ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ያለባቸውን የሙያ ኃላፊነት በአጓደለ መልኩ ክሱን አቅርበዋል ሊባል የሚችልው በተገቢው መንገድ ከደንበኛቸው የቀረበላቸውን ሕጋዊ ማስረጃ መሰረት በአላደረገ መልኩ ክስ አቅርበው ስለመሆኑ በሚገባ ከተረጋገጠ ነበር፡፡ አመልካች ደንበኛቸውን በቅድሚያ የሰጡትን ማስረጃ መሰረት አድርገው ክስ ማቅረባቸውና በኋላም ግለሰቧ እዳውን መክፈል መጀመራቸውን ሲገልፁላቸው ክሱን ለማሻሻል ተገቢውን ጥረት ማድረጋቸው በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 3 እና 8 ድንጋጌዎች መሰረት ሙያዊ ኃላፊነቱን የተወጡ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የዲስፒሊን ጉባኤ ክስ አቀራረቡ በተፋጠነ ስነ ስርዓት ማቅረብህ ያላግባብ መሆኑን አመልካች አምነዋል ያለበት ድምዳሜ የአመልካችን የመልስ ይዘት ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ አመልካቹ ከደንበኛቸው የተቀበሏቸው ማስረጃዎች፣ከግለሰቧ ጋር ቅድሚያ ስለ ክስ አቀራረብ ስርዓት የተስማሙ መሆን ያለመሆኑንና በኋላም ግለሰቧ ለአመልካች የገለጹት እዳ መክፍል መጀመራቸው ጉዳይ መኖር ያለመኖሩንና ይህንኑ ተከትሎ አመልካች የክስ ማሻሻል ጥያቄ ማቅረባቸው ከሙያው ስነ ምግባር፤ ቅንነትና እውነትነት አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያልነበረው መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ሳያረጋገጥ የአመልካች የክስ አቀራረቡ ብቻውን የዲስፒሊን ጥፋት ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ ህጋዊ መሰረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም አመልካች ለክስ አቀራረቡ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽመዋል የተባሉት ያላግባብ ነው ብለናል፡፡

ሌላው የዲስፕሊን ጉባኤው አመልካች የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽመዋል ያለው ለጥብቅና አግልግሎት ለተቀበሉት ገንዘብ ደረሰኝ ለደንበኛቸው ያለመስጠታቸው ተረጋግጧል በሚል ነው፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ማስተባበያ ክርክርና ማስረጃ ያለመኖሩን በዲሲፕሊን ጉባኤው የግለሰቧ ምስክሮች የምስክርነት ቃል ለመስጠት ከቀረቡ በኋላ አመልካች አስመዘገቡ ተብሎ ከተመዘገበው ቃል ይዘት ተረድተናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ደረሰኝ ያለመስጠታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 8(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የጣሱ በመሆኑ ለዚህ አድራጎታቸው በዲሲፕሊን ተጠያቂ መደረጋቸው በአግባቡ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ነጥብ የዲስፕሊን ጉባኤው አመልካች ግለሰቧን ከዲሲፕሊን ጉባኤው አዳራሽ ውጪ ዛቻ ፈጽሞባቸዋል በማለት ያስተላለፈው ውሳኔ የአንድ ወገን አቤቱታን መነሻ

ያደረገና በሌላ ማስረጃ ያልተደገፈ ነው በሚል ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን እንዳየነው ድርጊቱ መፈጸሙን የዲሲፕሊን ጉባኤው ያረጋገጠው ሲሆን ጉባኤው ለአመልካች በጉባኤው ፊት ተግሳጽ የሰጠ መሆኑን ከገለፀ በኃላ እንደገና በውሳኔው እለት ደግሞ ለዚህ አድራጎት የዲሲፕሊን ጥፋት ነው ከስራ ለማገድም ምክንያት አድርጎታል፡፡ይህ ደግሞ አመልካች ለአንድ ጥፋት ሁለት አይነት ቅጣት የተወሰነባቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡የዲሲፕሊን ጉባኤው ይኼው የአመልካች አድራጎት በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 57 ድንጋጌን የጣሰ መሆኑን በውሳኔ ላይ የገለፀ ቢሆንም ይኼው ተጠቃሽ ድንጋጌ ግን አመልካቹን ለሁለት ጊዜ ሊያጠይቅ የሚችልበትን አግባብ ስለመኖሩ ያስፈረው ምክንያት የለም፡፡ አንድ ጠበቃ ለፈፀመው የዲሲፕሊን ግድፈት ተገቢ ነው የተባለውን የዲሲፕሊን ቅጣት ከአገኘ በኂላ በተመሳሳይ የዲሲፕሊን ጥፋት ድጋሚ እንዲቀጣ ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለውና ከጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ መሰረታዊ ዓላማም ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ሲጠቃለልም የዲሲፕሊን ጉባኤው አመልካችን ለክስ አመሰራረቱና አመልካች ግለሰቧን ከዲሲፕሊን ጉባኤው አዳራሽ ውጪ ዛቻ ፈጽሞባቸዋል በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው ሁኖ አመልካች ደረሰኝ ያለመስጠታቸውን በማረጋገጥ የሰጠው ውሳኔ ግን ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ሊቀጡ የሚገባው ደረሰኝ ባለመስጠታቸው ምክንያት በደንብ ቁጥር በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 30(2) ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 8(1) እና በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24(3(ለ)) ድንጋጌ አግባብ አመልካች ከጥብቅና ስራ ሊታገዱ የሚገባው ለስድስት ወር ብቻ ሊሆን የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፍትህ ሚኒስቴር የጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤ በመ/ቁጥር 78/06 ግንቦት 22 ቀን 2006 ዓ/ም የውሳኔ ሃሳብ ቀርቦ በሚኒስትሩ ሰኔ 06 ቀን 2006 ዓ/ም የፀደቀውና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡፡
2. የጠበቆች የዲስፕሊን ጉባኤና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የክስ አቀራረብ እና የዛቻ ተግባር የሥነ ምግባር ጥፋት ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ አይደለም በማለት ሽረናል፡፡
3. አመልካች ከደንበኛቸው ለተቀበሉት ገንዘብ ደረሰኝ ያለመስጠታቸው ግን በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 30(2) ድንጋጌን የጣሰ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 24(3)(ለ))) መሰረት ከጥብቅና ስራ ለስድስት ወር ሊያሳግዳቸው የሚገባ ነው በማለት ወስነናል፡፡ይህ ጊዜ አመልካች ከዚህ በፊት የታገዱበትን ጊዜ መነሻ አድርጎ ሊቆጥር ይገባል ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ግልባጩ ይላክ ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 105765

ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ነገረ ፈጅ - የቀረበ የለም

**ተጠሪዎች፡-** እነ አቶ ግርማ ሞገስ 8 ሰዎች - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ አወሳሰን ሥርዓት የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በአብክመ ደቡብ ወሎ ዞን ደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በክርክር ሂደቱ ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካች ተከሳሽ በመሆን የተሳተፉ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም አመልካች ተጠሪዎች ለጥብቅና ሙያ አገልግሎት የከፈሉት 40,000 እንዲከፍል ተወስኗል፡፡ ጉዳዩ በአፈፃፀም የተመለከተው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በዋናው ፍርድ በመ/ቁ 0180/8 በነበረው ክርክር የተደረገው ወጪ በደረሠኝ እንዲተካላቸው መወሰኑን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከጠበቃቸው በተናጠል ባደረጉት ውል እያንዳንዳቸው 5,000 ብር ለመክፈል መስማማታቸው ያሳያል፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤትም በቀረበው ሰነድ መሠረት አመልካች በድምር 40,000 እንዲከፈል ወስኗል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኙት ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ ለአፈፃፀም ክስ መነሻ በሆነው መዝገብ ላይ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ በቀረበው ደረሰኝ እንዲከፍል መወሰኑን በመግለጽ፤ምንም እንኳ የተጠሪዎች የክርክር ጭብጥ አንድና ተመሳሳይ ነው ቢባልም አንኳ የተሰጠው መብትና በተጣለው መብት ተጠቃሚዎች ቁጥር ሲታይ 8 ተከራካሪዎች ናቸው፡፡ የፈጀው ጊዜም ሲታይ ከጥር 20/2005 ዓ.ም ጀምሮ ጉዳዩ በይግባኝ እስከሚታይበት ጊዜ 1 ዓመት ከ 6 ወር ዕድሜ አስቆጥሯል፡፡ ተጠሪዎች የጠበቃ አበል በማለት የተዋዋሉት 40,000 በዝቷል ለማለት የሚቻል አይደለም

በማለት የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አጽንቷል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም። የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓል። የአመልካች ቅሬታ መሠረታዊ ይዘት የተጠሪዎች ክስ በህብረት የቀረበ ስለሆነና ለእያዳንዳቸው የተደረገ ክርክር የሌለ ስለሆነ የጠበቃ አበልን በተናጠል 5000 ማድረጋቸው፤ፍ/ቤቱም እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢነት የለውም የሚል ነው። ተጠሪዎች በበኩላቸው የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን በማጣራት የወሰነው በመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል። የመልስ መልስ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች በማዛመድ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነውም ግራቀኙ እያከራከረ ያለው ጉዳይ ለጥብቅና ሙያ አገልግሎት ተከፈለ የተባለው የገንዘብ መጠን ነው። አመልካች ክፍያው የተጋነነ ነው ክሱ በሕብረት የቀረበ ከመሆኑ አንፃር 40,000 እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው ክርክሩ ረጅም ጊዜ የወሰደ ከመሆኑ አንፃር የተከፈለው ገንዘብ የተጋነነ የሚባል አይደለም በማለት መልስ አቅርበዋል።

በመሰረቱ የወጪና ኪሳራ አከፋፈል ሥርዓት በፍርድ ቤቶች የመወሰን ሥልጣን የተመሰረተ ስለመሆኑ ከፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 462 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው። ተጠሪዎች በጠበቃ ተወክለው የተከራከሩ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም። ክሱ የቀረበውም በአንድ ድርጅት በተመሳሳይ የሕግ ጭብጥ በአንድ ጊዜ ስለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል። የአብክመ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ምዝገባ የጠበቆች ሥነ ምግባር ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ.ም የአገልግሎት ክፍያ በግራ ቀኙ ስምምነት እንደሚፈጸም፤መጠኑ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ ከሆነ በመቶኛ ስሌት እንደሚውል፤በባልና ሚስት ክርክር ፍቺ ቀለብ በተመለከተ፤በወንጀል ጉዳዮች በሚሰጠው ውሳኔ እና ቅጣት ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ እንደማይደረግ ከአዋጅ አንቀጽ 50፣51 እና 52 ጥምር ንባብ መገንዘብ ይቻላል። የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ተገቢ የድካም ዋጋ የሚሰጠው መሆን እንዳለበት የታመነ ቢሆንም ከሚገባው በላይ የናረ መሆን የለበትም። የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመወሰን በልምድ ከዳበረው እና በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘው የአከፋፈል መርህ ጉዳዩ የወሰደው ጊዜ፣የሚጠይቀው ድካም፣የጉዳዩ ውስብስብነት፤የክርክሩ ግምት ታሳቢ የሚደረጉ ናቸው።

የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ሥራውን ያለውን ውጣ ውረድ ድካምና ያስከተለው ወጭ ታሳቢ መደረግ አለበት፡፡ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ያለምንም ገደብ ስምምነት የሚደረግበት አለመሆኑን ከሥነ ሕግ እና የፍ/ቤቶች አሰራር የዳበረ ልምድ ነው፡፡ በመሆኑም የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ ፍትሐዊ እና ሚዛናዊ ሊሆን ይገባል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ተገቢ የሆነውን የአገልግሎት ዋጋ ለመወሰን የተደረገው ጥረት (ድካም)፣የወሰደው ጊዜ እና የጉዳዩ ውስብስብነት ታሳቢ ማድረጉ ሚዛናዊ የሆነ ክፍያ ለመወሰን እንደ መስፈርት የሚወሰድ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ያከራከረው ነጥብ የሥራ ክርክር ሲሆን ተጠሪዎች በአንድ ዘንግ ቁመው የሕብረት ክስ ማቅረባቸው አልተካደም፡፡ ጉዳዩ የያዙት ጠበቃ የሚያስፈልጋቸው ጊዜ፤የሚነሳው የሕግና ፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይነት ያለው ከመሆኑ አንፃር ብዙ ጥረት ይጠይቃል ተብሎ አይገመትም፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ እንደተመለከትነው ጠበቃው በችሎት የቆሙባቸው ጊዜያት የተወሰኑ ስለመሆናቸው ተመልክተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች በተናጠል 5,000 በድምር 40,000 መክፈላቸው ጠበቃው በክርክሩ ያጠፉት ጊዜ፣ጉዳዩ ከወሰደው ጊዜ ግምቱ የክርክሩ ባሕሪ እና ይዘት አንፃር የተጋነነ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ያደረጉት የጥብቅና አገልግሎት ውል ከጉዳዩ ክብደት እና ውስብስብነት፤ግምቱ የወሰደው ጊዜ አንፃር መዝነው ትክክለኛ ወይም ተቀራራቢ ዋጋ መወሰን ሲገባቸው በተጠሪዎች የቀረበው ውል እንዳለ ወስደው አመልካች 40,000 ብር እንዲከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች መክፈል ያለበት የጥብቅና አገልግሎት ዋጋ ከተሰጠው አገልግሎት መጠን አንፃር በዳኝነት የተወሰነው ብር 145,360 አሥር ፐርሰንት (10%) አሥራ አራት ሺ አምስት መቶ ሰላሳ ስድስት ነው ብለናል፡፡ በእዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍርድ ቤቶች የፈጸሙት ስህተት በማረም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የደሴ ወረዳ ፍ/ቤቶች በመ/ቁ. 36/018018 ግንቦት 01/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 17030 በ9/11/2006 የሰጠው ፍርድ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0309036 በ27/01/2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች መክፈል የሚገባው በዳኝነት የተወሰነው ብር 145,360 10% ብር 14,536 ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

የሰ/መ/ቁ.112091

ሚያዝያ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡-መድህን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች**፡- አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ወኪል መልካሙ ሙጬየ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- ሠማያዊ ፓርቲ ወኪል ወረታው ዋሴ ቀረቡ

**መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 46744 መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ነው፡፡ በምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አመልካች አቤቱታ አቅራቢ ተጠሪ መልስ ሰጭ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በግንቦት ወር 2007 ዓ/ም በሚካሄደው ጠቅላላ ምርጫ የተጠሪ በምርጫ ክልሉ እጩ አድርጎ ያስመዘገባቸውን ሰዎች በመቃወም የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡

1. አመልካች በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል እጩ አድርጎ ያቀፈረባቸው አቶ ግርማ ቢተው፣ አቶ መለስ ዘለቀ፣ ወ/ሮ የርጋዱ ታደገ እና አቶ ይሁኔ ጥላሁን የአመልካች ድርጅት አባላት እንጂ የተጠሪ አባላት አይደሉም፡፡ ተጠሪ ፓርቲውን እንዲወክሉ በእጩነት አቅርቦ በቅጽ 003 ያስመዘገባቸው ግለሰቦች በእጩነት እስከ ተመዘገቡበት ጊዜ ድረስ የአመልካች አባልና አመራር ሆነው ተልዕኮ ሲያስፈጽሙ የቆዩ በመሆናቸው ግለሰቦቹ ተጠሪን (ሠማያዊን

ፓርቲን) በመወከል እጩ ሆነው ሊወዳደሩ አይገባቸውም በማለት በጽሑፍ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ከመረመረ በኂላ ከላይ ስማቸው የተገለፁት ግለሰቦች የሌላ የፖለቲካ ፓርቲ (አመልካች) አባል በመሆናቸው ተጠሪን በመወከል እጩ ተወዳዳሪ ሆነው መቅረብ አይችሉም በማለት የካቲት 10 ቀን 2007 ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

2. ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተጠሪ ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሠጠውን ውሳኔ ከመረመረ በኃላ የመርዓዊና ገርጨጭ ምርጫ ክልል ቢሮ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ የሚያስለውጥ ምክንያት የለም በማለት የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
3. ተጠሪ የደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴና የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 39918 የቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኃላ ከመዝገብ ቁጥር 39919 ጋር በማጣመር በመዝገብ ቁጥር 39919 ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኝ ባይ (ተጠሪ) እጩ ተወዳደሪ ሆነው ሊመዘገቡልኝ ይገባል የሚላቸው ግለሰቦች የፓርቲ አባል በነበሩበት አንድነት ለፍትህና ዲሞክራሲ ፓርቲ (አመልካች) መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አቤቱታ አቅርበው የተሰናበቱ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ እንደዚሁም የይግባኝ ባይ (ተጠሪ) አባል ለመሆን መጠበቅ የሚገባቸውን ጊዜ ያህል ጠብቀው በመተዳደርያ ደንቡ መሠረት አባል ስለመሆናቸው ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም መርዓዊና ገርጨጭ ምርጫ ክልል ቢሮ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴና የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
4. ተጠሪ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መርዓውና ገርጨጭ ምርጫ ክልል ቢሮ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴና የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጡትን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 46743 ከሰማ በኃላ ጉዳዩን በሰበር አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በእጩ ተወዳዳሪነት ያቀረባቸው ሰዎች የሌላ ፖለቲካ ድርጅት አባል ለፍትህና ዲሞክራሲ ፓርቲ (አመልካች) የነበሩ ቢሆንም በማናቸውም ጊዜ አባልነት መብታቸውን በመተው የሌላ ፖለቲካ ድርጅት አባል የመሆን መብት አላቸው፡፡ ስለዚህ ተቃውሞ

የቀረበባቸው ሰዎች ለፍትህና ዲሞክራሲ ፓርቲ (አመልካች) አባላት የነበሩ ቢሆንም የሠማያዊ ፓርቲ አባልና እጩ ተወዳዳሪ የመሆን መብት አላቸው፡፡ ተቃውሞ የቀረበባቸውን ሰዎች በአባልነት የተቀበላቸውና ዕጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰማያዊ ፓርቲ ግለሰቦቹ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ የተደነገገውን ስድስት ሳምንት የመጠበቂያ ጊዜ ሳይቆዩ የፓርቲው ሙሉ አባልና እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ማቅረብ እንደሚችል በመተዳደሪያ ደንቡ የተደነገገ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመርዓዊናገርጨጭ ምርጫ ክልል ቢሮ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴና የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ግለሰቦቹ በእጩነት አይመዘገቡም በማለት የሰጡትን ውሳኔ ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮ ግለሰቦቹ ተጠሪን ወክለው በምርጫ ለመወዳደር ይመዝገቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. አመልካች መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ግለሰቦች የአመልካች አመራርና አባላት የነበሩ ናቸው፡፡ ተጠሪ ግለሰቦቹ የአመልካች አባልነታቸውን የተውት መሆኑን ለአመልካችና ለሕዝብ አሳውቀው የለቀቁ መሆኑን ሳያረጋግጥ የሌላ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች በአመለካች ያላቸውን አባልነት መብት በፈቃዳቸው የተውት ስለመሆኑ በጽሁፍ አላሳወቁም፡፡ አንድ ፓርቲ አባል በአባልነትና በአመራርነት ሲሳተፍ ለነበረበት ፖለቲካ ድርጅት ሳያሳውቅ የሌላ ፖለቲካ ድርጅት አባል ነኝ ብሎ እንዳሻው በሌላ ፖርቲ አባልነት መመዝብና የሌላ ፓርቲ እጩ ሆኖ መቅረብ አይችልም፡፡ በመሆኑም የአመልካችን አባላት ተጠሪ በተወዳዳሪነት ለማቅረብ ህጉ እንደሚፈቅድለት በመግለጽ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በድምጽ ብልጫ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

6. ተጠሪ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ደርሶት ሚያዚያ 20 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የመምረጥና የመመረጥ መብት ሕገ መንግስታዊ ዕውቅና የተሰጠው መብት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የፖለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን የሚያስፈልገውን መስፈርት እስካሟላ ድረስ በፍላጎቱ የአንድ ፖለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የሌላ ፖለቲካ አባል የነበረን ሰው ከነበረበት የፖለቲካ ድርጅት በአግባቡ ሳይሰናበት የሌላ ፖለቲካ ድርጅት አባል ለመሆንና እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ አይችልም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህገ መንግስቱን ድንጋጌ የሚቃረን ነው፡፡ ተጠሪ እጩ ተወዳዳሪ ያደረጋቸው ሰዎች የተጠሪ መተዳደሪያ ደንብ ያስቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት የሰማያዊ ፓርቲ አባል ሆነዋል፡፡ ሰዎቹ ከዚህ በፊት የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባል የነበሩ መሆናቸው የተጠሪ አባላት ከመሆን አይገድባቸውም፡፡ እንደዚሁም የአመልካች ክርክር ተጠሪ እጩ ተወዳዳሪ

ያደረጋቸው ሰዎች የፖለቲካ ድርጅት አባልነታቸውን በማናቸውም ጊዜ የመተው መብት ያላቸው መሆኑንና የፖለቲካ ፓርቲው ይህንን መብት በመተዳደሪያ ደንቡ መገደብ እንደሌለበት በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ የተደነገገውን ግልጽ ድንጋጌ የሚጥስ ነው፡፡ ሰዎች ከነበራችሁበት የፖለቲካ ድርጅት በአግባቡ አልተሰናበታችሁም በሚል ህጋዊነት የሌለው ምክንያት በማይፈልጉት የፖለቲካ ድርጅት በአባልነት እንዲቆዩ ሊደረጉ አይገባም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ክርክር ውድቅ ተደርጎ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠውን ውሳኔ እንዲያፀናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ መስጠት አያስፈልገኝም ብሏል፡፡

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለጸው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርፍ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን በሰበር አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማየት ሥልጣን አለው ቢባል ተጠሪ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን መርዓዊናገርጨጭ ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች በእጩ ተወዳዳሪነት ሊመዘገቡ ይገባል በማለት የሰጠው የህግ ትርጉምና ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
8. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን ከምርጫ ሂደት የሚቀርቡ አቤቱታዎች ስለሚስተናገዱበት ሥርዓትና ጉዳዩን በዳኝነት አይተው ውሳኔ የመስጠት የዳኝነት ሥልጣን ስላላቸው የክልልና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 532/1999 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና የድንጋጌቹን አቀራረጽና መሰረታዊ ባህሪ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በምርጫ ሂደት ስለሚነሱ አቤቱታዎች ክርክሮች አቀራረብና አወሳሰን መሰረታዊ መርሆችን የሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 6 እና ንዑስ አንቀጽ 10 የክልል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በይግባኝ አይተው የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡባቸውን ጉዳዮች ገልጿል፡፡
9. የአዋጁ አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 11 እና አንቀጽ 95 ንዑስ አንቀጽ 3 እና ንዑስ አንቀጽ 5 የወረዳው ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በእጩ ምዝገባ ሂደት አከራካሪ ጉዳይ ሲያጋጥም በመጀመሪያ ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ ሊቀርብ እንደሚገባውና የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሃያ አራት ሰዓት ውሳኔ እንደሚሰጥ በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 94 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 4 ያሉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን በሰባ ሁለት ሰዓት ውስጥ ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ሊያቀርብ እንደሚችልና ይግባኙም ለክልሉ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት

አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ ውሳኔ ስለሚሰጥበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር. 532/1999 አንቀጽ 94 ከንዑስ አንቀጽ 5 እስከ ንዑስ አንቀጽ 10 ባሉት ድንጋጌዎች ተደንግጓል፡፡

10. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በይግባኝ አይቶ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አርባ ስምንት ሰዓታት ማቅረብ እንደሚችልና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 11 ይደነግጋል፡፡ ከላይ የገለጽናቸው የአዋጅ ቁጥር 532/1999 ድንጋጌዎች ሕግ አውጭው የክልሉ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ አይተው የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡባቸውን ክልላዊ ባሕሪ ያላቸውን ጉዳዮች በግልፅ በመደንገግ ለክልል ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን የሚሰጡ ናቸው፡፡ አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 6 በሌሎች ጉዳዮች የሚቀርቡ የምርጫ አቤቱታዎች ሰምቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከላይ የገለጽነው የህጉ ድንጋጌዎች አቀራረጽ የክልል ፍርድ ቤቶች በይግባኝ አይተው የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጡባቸው በአዋጁ በግልጽ ያልተደነገጉ ቀሪ የዳኝነት ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው የሚለውን መርህ የሚያራምድ ነው፡፡

11. ይህም ለክልሉ ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 532/1999 በግልጽ ተለይቶ የተሰጣቸው የዳኝነት ሥልጣን ክልላዊ ባህሪ ያላቸውና በክልል ፍርድ ቤቶች በይግባኝ ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡባቸው ሙሉ በሙሉ በክልሉ የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቁ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን እንዳለው በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 11 እና አንቀጽ 95 ንዑስ አንቀጽ 3 እና ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥባቸውን ጉዳዮችና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ወገን የሰበር አቤቱታውን በመጀመሪያ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማቅረብ እንዳለበት ከሕግ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) እና የተሻሻለው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሐ/ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን አለኝ በማለት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

12. ከላይ በሁለተኛነት የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ለአመልካችና ለተጠሪ ክርክር መነሻ የሆኑትንና በየደረጃው ባሉ የምርጫ አቤቱታና ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችና ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና በህገ መንግስቱ ህጋዊ እውቅናና ጥበቃ የተሰጠው የመምረጥ፣ የመመረጥና የመደራጀት መብት መሰረታዊ ይዘት፣ መብቶቹ ተግባራዊ ለማድረግ የወጡ ዝርዝር ህጎች መሰረታዊ ግብ፣ እነዚህን መብቶች ተግባራዊ በሚደረጉበት ጊዜ ግለሰቦችም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ዝቅተኛ መስፈርቶች ወይም ቅድመ ሁኔታዎችና ግለሰቦች ወይም የፖለቲካ ድርጅቶቹ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ዝቅተኛ መስፈርቶች ወይም ቅድመ ሁኔታዎች አለማሟላታቸው የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

13. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን መርዓዊና ገርጨጭ ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች፣ ከዚህ በፊት አመልካች አባልና አመራር የነበሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በምርጫ ክልሎቹ እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች እስከቀርብ ጊዜ ድረስ የአመልካችን የፖለቲካ ተልዕኮ ሲያስፈጽሙ የነበሩ መሆኑን ተጠሪ ማስተባበያ ያላቀረበበት ዕውነታ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ እጩ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች የተጠሪ እጩ ሆነው ከመቅረባቸው በፊት አባልና አመራር ሆነው ለኖሩበት የፖለቲካ ድርጅት ማለትም አመልካች የድርጅቱ አባል ሆነው የማይቀጥሉና አባልነታቸውን በፈቃዳቸው የተው ስለመሆናቸው በጽሁፍ ያሳወቁ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

14. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ማናቸውም አይነት ልዩነት ሳይደረግበት በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በህዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣ አስራ ስምንት ዓመት ሲሞላው በህግ መሰረት የመምረጥ፣ በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው የመምረጥና የመመረጥ መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማናቸውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት ያለው መሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 31 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም የፖለቲካ ድርጅቶች በሠራተኞች ፣ በንግድ፣ በአሰሪዎችና በሙያ ማህበራት ለመሳተፍ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማናቸውም ሰው በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን ያለበት መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ እነዚህ በህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች የዜጎች የመምረጥ የመመረጥና የፖለቲካ ድርጅት የመመስረትና የፖለቲካ ድርጅት አባል የመሆን መብትን ጨምሮ ሌሎች የመደራጀት መብቶች ዕውቅናና ጥበቃ የሚሰጡ የህገ መንግስት ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

15. ከላይ የተገለጹት ህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መብቶቹን በጥቅል አገላለጽ የሚደነግጉ በመሆናቸው ማናቸውም ዜጋ የመምረጥ፣ የመመረጥና የመደራጀት መብት ዝርዝር ይዘትና መብቶቹ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ስርዓቶች አካትተው የሚይዙ አይደሉም። ከህገ መንግስቱ መብቶቹን በመርህና በጥቅሉ ከመደንገግ አልፎ የመብቶቹን ዝርዝር ይዘትና መብቶቹ ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ስርዓት በዝርዝር እንዲደነግግ አይጠበቅበትም። ይህም በመሆኑ ዜጎች በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን የመምረጥ፣ የመመረጥና የመደራጀት መብት የሚዘረዝሩ፣ መብቶቹ ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ስርዓትና መብቶቹን ተግባራዊ በሚደረጉበት ጊዜ ግለሰቦችም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊያሟላቸው የሚገቡ ዝቅተኛ መስፈርቶች ወይም ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር የሚያስቀምጡ ሌሎች ህጎች ማለትም አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ወጥተው ስራ ላይ ውለዋል።
16. ከላይ የተገለጹትን የዜጎች መሰረታዊ የመምረጥ የመመረጥና የመደራጀት መብት ተግባራዊ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ወጥተው ስራ ላይ ከዋሉት የህግ ማዕቀፎች የተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 የመጀመሪያው ተጠቃሽ ነው። ህግ አውጭው አዋጁን በማወጅ ለማሳካት ከሚያስባቸው ግቦች መካከል፣ የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች የሚሳተፉበትና ዓላማቸውን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለመራጩ ህዝብ የሚገልጹበት መራጩ ህዝብም በመረጃ ላይ በመመስረት ፈቃዱን በነፃት በመግለጽ ወኪሎቹን የሚመርጥበትን የምርጫ ስርዓት መዘርጋት፣ በምርጫው ተሳታፊ የሚሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የግል እጩዎች ለፍታሀዊ ሰላማዊ ነጻና ዲሞክራሳዊ የምርጫ ስርዓት መስፈን ገንቢ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ግልጽ አሰራር መዘርጋትና ህገ መንግስቱን መሰረት በማድረግ ነጻ ገለልተኛና ፍታሀዊ ምርጫ በማካሄድ በህዝብ ድምጽ የተመረጠ መንግስት እንዲቋቋም ማድረግ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 532/1999 መግቢያ አራተኛውና አምስተኛው ፓራግራፍና ከአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል።
17. ከላይ የተገለጹትን ህገ መንግስት መሰረታዊ መብቶች ተፈፃሚ ለማድረግ የወጣው ሌላው የህግ ማዕቀፍ የፖለቲካ ፓራቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 ነው። በዚህ አዋጅ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ማለት ከህብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነትና ዓላማ የሚያንጸባርቅ ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዴሞክራሳዊ ስርዓት የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ በአዋጁ መሰረት የተቋቋመና የተመዘገበ ልዩ ባህሪና ተልዕኮ ያለው ማህበራዊ ተቋም እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቶታል። ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 573/2000 ያወጀው በህገ መንግስቱ መሰረት ዜጎች የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው በሰላማዊና

ህጋዊ የፖለቲካ እንቅሳቄሴ በመሳተፍ የሚይዙበትን ሁኔታ በህግ ለመደንገግ፣ ዜጎች የፖለቲካ ፓርቲ ሲመሰርቱና በአባልነት ሲንቀሳቀሱ ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊከተሏቸው ስለሚገቡ መርሆች ለመደንገግና የፖለቲካ ፓርቲዎች በመዋሃድ ወይም ግንባር በመፍጠር ወይም በመቀናጀት ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበትን ሁኔታ ግልጽ ለማድረግ እንደሆነ በመግቢያው በግልጽ አስቀምጧል፡፡

18. በህገ መንግስቱ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 አንድ ዜጋ በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄደው ምርጫ በተመራጭነት ለመቅረብና በህገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን የመመረጥ መብት ለመጠቀም ሊያሟላቸው የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በዋናነት በአዋጅ ቁጥር 532/1999 ከአንቀጽ 44 እስከ አንቀጽ 57 ተደንግጓል፡፡ በተለይም የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 45 እና አንቀጽ 46 እጩዎች በህግ የተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በግላቸው ተወዳዳሪ ሆነው ለመቅረብ የሚችሉበትን ህጋዊ ሁኔታ በዝርዝር ያስቀምጣሉ፡፡ የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የፖለቲካ ድርጅት በመወከል ወይም በግላቸው ተወዳዳሪ ለእጩነት የሚቀርቡ ሰዎች ሁሉም በጋራ ሊያሟላቸው የሚገቡና ለእጩነት የሚያበቁ መመዘኛዎች የሚደነግጉ ናቸው፡፡ አዋጁ ቁጥር 532/1999 የአንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 3 በግል እጩ ሆኖ የሚቀርብ ተወዳዳሪ በልዩ ሁኔታ ሊያሟላው ስለሚገባው ተጨማሪ መስፈርት፣ ማለትም በግል እጩ ሆኖ ለመቅረብ በምርጫ ክልሉ ኗሪ የሆኑ ከአስራ ስምንት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸውና የመምረጥ መብታቸውን ያልተከለከሉ ከአንድ ሺ የማያንሱ ሰዎች የድጋፍ ፊርማ የግል ተወዳዳሪው የማቅረብ ግዴታ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

19. በአንፃሩ በህግ አግባብ የተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት መስፈርቱን የሚያሟላ እጩ በማቅረብ ሊወዳደር እንደሚችል፣ የፖለቲካ ድርጅቱን ወክለው የሚወዳደሩ እጩዎች ዝርዝር ለቦርዱ የሚያሳውቀው የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር እንደሆነና የፖለቲካ ድርጅት ወክሎ ለሚቀርብ እጩ በፓርቲው መወከሉንና በእጩነት ለመቅረብ መስማማቱን የሚገልጽ ማስረጃ ከእጩነት ማስረጃው ጋር መቅረብ እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 46 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 3 በቅደም ተከተል ደንግጓል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሱት ጥያቄዎች በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የፖለቲካ ድርጅቶች እጩ ተወዳዳሪ አድርገው የሚያቀርቧቸው ሰዎች በአዋጁ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጹ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ሊያሟላቸው የሚገቡና ለእጩነት የሚያበቁ መመዘኛዎች በተጨማሪ የፖለቲካ ድርጅቱን ወክለው በእጩነት ለመቅረብ በልዩ ሁኔታ ሊያሟሉ የሚገባቸው ተጨማሪ መስፈርት አሉ ወይስ የሉም? የፖለቲካ ድርጅት ወክለው የሚቀርቡ እጩዎች ከግል ተወዳዳሪዎች በተለየ ሁኔታ የሚያሟላቸው ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ የሚባል ከሆነ መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው? በተለይም የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባላት የነበሩ ሰዎችን በእጩ ተወዳዳሪነት ያቀረበ

የፖለቲካ ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 46 መሰረት የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባላት የነበሩ ሰዎች እጩ አድርጎ ሲያቀርብ ሊያረጋግጣቸውና በማስረጃ አስደግፎ ሊያቀርባቸው የሚገቡት ተጨማሪ ፍሬ ጉዳዮች ወይም መስፈርቶች ምንድን ናቸው? የፖለቲካ ድርጅት ወክለው የሚቀርቡ እጩዎች ተጨማሪ መስፈርቶቹን ባያሟሉ ህጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

20. ከላይ የተገለጹትን ጥያቄዎች ለመመለስ በአዋጅ ቁጥር 532/1999 ከአንቀጽ 44 እስከ አንቀጽ 57 የተደነገጉትንና ሌሎች የአዋጁን ድንጋጌዎች መመልከት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ በአንፃሩ በመጀመሪያ ደረጃ የእነዚህን ድንጋጌዎች ይዘት ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 532/1999 ካወጀበት መሰረታዊ ምክንያትና በአዋጁ ሊያሳካቸው ከሚፈልጋቸው ግቦች ጋር በጣምራ መመርመርና ለድንጋጌዎቹ ትርጉም መስጠት ይጠይቃል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የአዋጅ ቁጥር 532/1999 ድንጋጌዎች፣ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 573/2000 ለፖለቲካ ፓርቲ ከሰጠው ትርጓሜ፣ አዋጅ ቁጥር 573/2000 ካወጀበት መሰረታዊ ግብና ዓላማ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ይዘት ጋር ማገናዘብና ህግ አውጭው እነዚህን የህግ ማዕቀፎች በማሟላት ሊያሳካው ከፈለገው መሰረታዊና አገራዊ ግብ አንፃር ጉዳዩን መመርመርና የህግ ትርጉም መስጠት ያስፈልጋል፡፡

21. ከዚህ አንፃር ስናየው አዋጁ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች መሰረት የፖለቲካ ድርጅቶች እጩ ተወዳዳሪ አድርገው የሚያቀርቧቸው ሰዎች፣ አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከተደነገጉት መመዘኛዎች በተጨማሪ፣ የፖለቲካ ድርጅቱን ወክለው በእጩነት ለመቅረብ በልዩ ሁኔታ ሊያሟሉ የሚገባቸው ተጨማሪ መስፈርቶች ያሉ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የፖለቲካ ድርጅቱን ወክለው በእጩነት የሚቀርቡ ሰዎች በልዩ ሁኔታ የሚያሟሉት መስፈርት እጩ ተወዳዳሪዎቹ በህግ አግባብ የተመዘገቡና በእጩነት ያቀረባቸው የፖለቲካ ፖርቲ አባላት መሆን ያለባቸው መሆኑን ከአዋጁ ቁጥር 573/2000 መግቢያ፣ አዋጅ 573/2000 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

22. የፖለቲካ ድርጅቶች ወክለው የሚቀርቡ እጩዎች በግላቸው እጩ ሆነው በተወዳዳሪነት እንዲሚቀርቡ ዜጎች የሚወዳደሩበት የምርጫ ክልል ኗሪዎች የድጋፍ ፊርማ አሰባስበው እንዲያቀርቡ በህጉ የማይጠየቁት በእጩነት የወከላቸው የፖለቲካ ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 የሚጠይቀውን የመስራች አባላት ድጋፍና ድምጽ በማሟላት የተመዘገበ መሆኑን ህግ አውጭው ከግንዛቤ በማስገባቱ ነው፡፡ ህግ አውጭው ፖለቲካ ድርጅቶቹን ወክለው የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎች የመራጭ ድጋፍ የማሰባሰብ ግዴታ እንዳይኖርባቸው ያደረገው የፖለቲካ ድርጁቱን በመወከል በእጩነት የሚቀርቡት ሰዎች

ህጋዊ መስፈርቶችን ያሟሉ የፓርቲው ትክክለኛ አባላት ይሆናሉ በሚል ዕምነት እንደሆነ፣ የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 45 እና አንቀጽ 46 ድንጋጌዎችና የአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 ድንጋጌዎች በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር የፖለቲካ ድርጅቶች ወክለው የሚቀርቡ እጩዎች ሁሉንም ህጋዊ ሁኔታዎች አሟልተው በእጩነት የሚወክሉት የፖለቲካ ድርጅት አባላት መሆን አለባቸው፡፡

23. የፖለቲካ ድርጅቶች የተለያየ አመለካከት ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች የሚወክሉ፣ የራሳቸው የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራምና ዓላማ ያላቸው፣ የፖለቲካ ዓላማቸውን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለማሳካትና በምርጫ የመራጩን ህዝብ ዓመኔታ፣ ድጋፍና ድምጽ አግኝተው፣ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚወዳደሩ ለየት ያለ ባህሪና ተልዕኮ ያላቸው ማህበራዊ ተቋማት መሆናቸው በሁለቱም አዋጆዎች በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህም በመሆኑ አንድ ሰው በአንድ ጊዜ የአንድ የፖለቲካ ፕሮግራምና ዓላማ ያለው ህጋዊ የፖለቲካ ድርጅት አባል የመሆን መብት ይኖረዋል፡፡ ከዚህ አሰራር በሚቃረን ሁኔታ አንድ ሰው በተመሳሳይ ጊዜ የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች አባል የመሆን መብት እንደሌለው ከአዋጅ ቁጥር 573/2000 መግቢያ፣ ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2፣ አንቀጽ 13፣ አንቀጽ 14ና አንቀጽ 15 ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

24. በአዋጁ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አባል የነበረ ሰው አባል ሆኖ የተደራጀበትን የፖለቲካ ድርጅት አባልነት መብት የሚያጣው በሁለት መሰረታዊ ሁኔታዎች መሆኑን በአዋጁ ቁጥር 573/2000 በምዕራፍ ሶስት የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መብትና ግዴታ በሚል ርዕስ ከአንቀጽ 28 እስከ አንቀጽ 31 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመመልከት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የፖለቲካ ፓርቲው በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ከአባልነት እንዲወገድ ሲወሰንበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ፓርቲው አባሉ ከፖለቲካ ድርጅት አባልነቱ እንዲወገድ የተወሰነበት ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ውጭ ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ ከፖለቲካ ድርጅት አባልነት እንዲወገድ የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተደንግጓል፡፡

25. ሁለተኛው የፓለቲካ ፓርቲ አባል የሆነ ሰው የፓርቲው አባል መሆኑ ቀሪ የሚሆንበት መንገድ አባሉ በአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 የተሰጠውን የፓለቲካ ፓርቲ አባልነት የመተው መብቱን ተጠቅሞ የፓለቲካ ድርጅት አባልነቱን ሲተወው መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡እዚህ ላይ መታየት ያለበት አንድ ሰው የፓለቲካ ፓርቲ አባልነቱን በፈቃዱ ትቷል የሚባልበት ህጋዊ መስፈርት ምንድን ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አንድ ሰው የፓለቲካ ፓርቲ አባልነቱን በፈቃዱ ትቷል የሚባለው በማያሻማ ሁኔታ የፓርቲ አባልነቱን

በፈቃዱ የተወው መሆኑን ለፓርቲው ሲያሳውቅ እንደሆነና አንድ ሰው የፓርቲ አባልነቱን በማያሻማ ሁኔታ ገልፆ ትቷል ለማለት አባል የሆነበት የፓለቲካ ድርጅት፣ በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 12 መሰረት አቅርቦ ባስመዘገበውና በጸደቀው የፓለቲካ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አባልነቱን በፈቃዱ የተወው መሆኑን ሲያሳውቅ እንደሆነ የአዋጁን አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 ፣አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) እና አንቀጽ 12 ድንጋጌዎች ጋር በጣምራ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

26. ይህም የአንድ የፓለቲካ ፓርቲ አባል የሆነ ሰው የፓለቲካ ድርጅቱ የአባልነት መብት በፈቃዱ የተወው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ በአባልነት ለሚሳተፍበት የፓለቲካ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ሳይገልፅና ሳያሳውቅ፣ በአባልነት ስሳተፍበት የነበርኩትን የፓለቲካ ፓርቲ አባልነት በፈቃዴ ትቼ የሌላ ፓለቲካ ድርጅትአባል ሆኛለሁ ስለዚህ ለሁለተኛ ጊዜ የተደራጀሁበትን የፓለቲካ ድርጅት ፓርቲ ወክየ በእጩነት ለመመዝገብና ለመወዳደር እችላለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር ከላይ የገለጽናቸውን የፓለቲካ ድርጅት የአባልነት መብት ሊቋረጥ ስለሚችልባቸው ሁለት መሰረታዊ ሁኔታዎችና የአዋጅ ቁጥር 573/2000 ድንጋጌዎች መስፈርት የማያሟላና የህግ መሰረት የሌለው ክርክር ነው፡፡

27. ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን መርዓዊና ገርጨጭ ምርጫ ክልል ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ለአማራ ክልል ምክር ቤት እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ግለሰቦች፣ አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ በመባል የሚታወቀው የፓለቲካ ድርጅት(አመልካች)አባል መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ግለሰቦቹን በእጩነት አቅርቦ ለማስመዝገብ ጥያቄ ሲያቀርብ ሰዎች አባል ከሆኑበት የፓለቲካ ድርጅት(አመልካች)በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በዲስፒሊን ጥፋት ከአባልነት የተወገዱ ወይም አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 12 መሠረት አመልካች ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አቅርቦ ባስመዘገበውና ባጽደቀው የፓለቲካ ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ የተቀመጠውን ግልጽ መስፈርት በማሟላት የአመልካች አባልነቻቸውን የተውት መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ይህም ማለት ተጠሪ እጩ አድርጐ ያቀረባቸው ግለሰቦች በአባልነት ለተደራጁበት አመልካች አባልነታቸውን በፈቃዳቸው የተውት ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳወቁ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት አያይዞ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡

28. በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በእጩነት ያቀረብኳቸው ሰዎች የአመልካች አባል ሆነው መቀጠል እንደማይፈልጉ በጽሑፍ በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አሳውቀዋል የሚል መከራከሪያ አላቀረበም፡፡ ተጠሪ የሚከራከረው በእጩነት ያቀበረብኳቸው የአመልካች አባል ሆነው መቀጠል እንደማይፈልጉ በጽሑፍ በአመልካች መተዳዳሪያ ደንብ መሰረት ባያሳውቁም ግለሰቦቹን የተጠሪ አባልና እጩ ከመሆን የሚከለክላቸው ህግ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ ይህንን የተጠሪን ክርክር በመቀበል ማናቸውም ሰው አባል ሆኖ በተደራጀበት የፓለቲካ ድርጅት መተዳዳሪያ ደንብ መሰረት የድርጅት አባልነት መብቱን የተወው መሆኑን በጽሑፍ ሳያሳውቅ የሌላ የፓለቲካ ድርጅት አባል ሆኖ ከተመዘገበና የሌላ የፓለቲካ ድርጅት እጩ ሆኖ ከቀረበ በፊት ተደራጅቶ ሲሳተፍበት የነበረውን የፓለቲካ ድርጅት የአባልነት መብቱን እንደተወው ይቆጠራል፣ በዚህ መንገድ ለምንም ቅድመ ሁኔታ ቀድሞ አባል የሆነበት የፓለቲካ ድርጅት አባልነት በመተው ለሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባልና እጩ ተወዳዳሪ መሆን ይችላል በማለት የህግ ትርጉም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

29. ሆናም ይህ ትርጉም ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 573/2000 መሰረት የአንድ ሰው ተደራጅቶበት በነበረው የፓለቲካ ፓርቲ አባልነት መብት ቀሪ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በዲስፒሊን ጥፋት በአባልነት ሲወገድ ወይም አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 12 መሰረት በተመዘገበው የድርጅቱ መተዳዳሪያ ደንብ መሰረት የአባልነት መብቱን የተወው መሆኑን ግልፅ አድርጎ በጽሑፍ ሲያሳውቅ ብቻ መሆኑን ያገናዘበ አይደለም፡፡ አንድ ሰው በአባልነት የሚሳተፍበት የፓለቲካ ፓርቲ መተዳዳሪያ ደንብ በሚደነግገው መሰረት የአባልነት መብቱን በፈቃዱ የተወው መሆኑን ግልፅ አድርጎ በጹሑፍ ሳያሳውቅ የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባል ሆኖ ተመዝግቦ መገኘቱ በመጀመሪያ ተደራጅቶበት የነበረውን ፓለቲካ ፓርቲ አባልነት ትቶታል ከሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በአንፃሩ ፓርቲው አባሉ ከህግና ከሥርዓት ውጭ ከአንደኛው የፓለቲካ ድርጅት ጋር የነበረውን የአባልነት ትስስር በሕግ አግባብ ሳያቋርጥ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ የሌላ ድርጅት አባል መሆኑ በሌላ አነጋገር በአንድ ጊዜ የሁለት የፓለቲካ ድርጅቶች አባል በመሆን ተመዝግቦ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የሚያሳይና ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው የማይገባ አድራጐት ሆኖ አግኝተዋል፡፡

30. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 4 የሰጠው ትርጉምም የህጉን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም የአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ" የፓለቲካ ድርጅቶች መተዳዳሪያ ደንብ የዚህን ምዕራፍ ድንጋጌዎች የሚቃረን መሆን የለበትም" የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የፓለቲካ ፓርቲዎች አባላቶቻቻቸው በራሳቸው ፈቃድና ፍላጐት አባልነት መብታቸውን የተውት ስለመሆኑ ለፓርቲው የሚያሳውቁትን ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንባቸውን እንዳያካትቱ የሚከለክል ድንጋጌ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪ በእጩነት ያቀረባቸው ሰዎች አባል ሆነው የተደራጁበት የፓለቲካ ፓርቲ(አመልካች) በመተዳደሪያ ደንብ የድርጅቱ አባል ሆኖ መቀጠል የማይፈልግ አባል አባልነቱን የተወው መሆኑን ለድርጅቱ በጽሑፍ የማሣወቅ ግዴታ እንዳለበት ያስቀመጠውን ድንጋጌ ህጋዊነት የሌለው ገደብ የማድረግ ይዘት የለውም፡፡

እንደዚሁም ይህ የደንቡ ድንጋጌ አዋጅን የማስፈፀም ኃላፊነት በህግ ሥልጣን በተሰጠው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ተመርምሮ በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 ለድርጅቱ አባላት የተሰጠውን መብት የማያጣብብ መሆኑ ተረጋግጦ በአዋጁ አንቀጽ 12 መሰረት የተመዘገበና የጸደቀ ነው፡፡

31. ከዚህ በተጨማሪ የፓለቲካ ድርጅት አባል የሆነ ሰው የድርጅቱ አባል ሆኖ መቀጠል እንደማይፈልግ በግልፅ በማሳወቅ አባልነቱን የመተው መብት ያለው በማናቸውም ጊዜ በምርጫ ወቅት የድርጅቱ እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ከተመዘገበ በኋላ ጭምር እንደሆነ የአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 54 ድንጋጌዎች በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ የተገለፀው አባልነትን የተወ የፓርቲ አባል አባልነቱን የተወው መሆኑን በጹሑፍ የማሳወቅ ግዴታ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 352/1999 አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገገው መስፈርት ጋር ተመሳሳይነት ያለውና ይህንን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ አመልካች በመተዳደሪያ ደንቡ ያስቀመጠው አባልነት መቀጠል የማይፈልግ የድርጅቱ አባል ይህንኑ በጽሑፍ የማሳወቅ ግዴታ ያለበት መሆኑን በመተዳደሪያ ደንቡ ያስቀመጠው መስፈርት በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 4 የሚጥስ ነው በማለት የሰጠው የህግ ትርጉም ከላይ የገለፅናቸውንና ሕግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 የደነገገውን መስፈርት ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

32. ከላይ በዝርዝር ከተገለፁት የህግ ትንተናዎች በተጨማሪ የህዝብ ሉዓላዊ ስልጣን በምርጫ ተወዳድሮ ለማሸነፍና ለመረከብ በህጋዊ መንገድ በተቋቋመ የፓለቲካ ፓርቲ አባል የሆነ ሰው፣ አባል ሆኖ ለኖረበት ፓርቲ ሳያሳውቅ የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባል ሆኖ የመመዝገብና በእጩነት የመቅረብ መብት አለው፣ የሌላ የፓለቲካ ድርጅት አባል የነበረን ሰው በአባልነት የሚመዘግብና በእጩነት የሚያቀርበው የፓለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን የተቀበለውና እጩ ያደረገው ሰው አባል ሆኖበት ከነበረው የፓለቲካ ድርጅት ጋር የነበረውን የፓለቲካ ትስስር ለመተው ያለውን ፍላጐት በግልፅ ያሳወቀ መሆኑን ሳያረጋግጥ አባል አድርጐ መመዝገብና በእጩ ተወዳዳሪነት ማቅረብ ይችላል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ ሕግ አውጭው በሁለት አዋጆች የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፓለቲካ ድርጅቶች የሚሳተፉበትና ዓላማቸውን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ለመራጩ ሕዝብ የሚገልጹበት መራጩ ህዝብም በመረጃ ላይ በመመስረት ፈቃዱን በነፃነት በመግለፅ ወኪሎቹን የሚመርጥበት ሥርዓት ለመዘርጋት ያሰበውን ዓላማና ሌሎች ከላይ የገለፅናቸውን መሰረታዊ ግቦች የሚያሳካ አይደለም፡፡

33. በተቃራኒው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ የተከተለው አተረጓጎም በምርጫ ወቅት የአንደኛው የፓለቲካ ድርጅት አባላት አባል ለሆኑበት የፓለቲካ ድርጅት አባልነታቸውን የተውት መሆኑን ሳያሳውቁ፣ የፓለቲካ ድርጅታቸውን የሚከዱበትና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ዘልለው በመሄድ የሌላ የፓለቲካ ድርጅት አባልና እጩ ሆነው የሚቀርቡበትን አሰራር የሚያበረታታ ነው፡፡ ይህ አሰራር ህጋዊ እውቅና ከተሰጠው በፓለቲካ ድርጅቶችና በአባላቶቻቸው መካከል መተማመን እንዳይኖር የሚደረግ፣ የፓለቲካ ድርጅቶች የአባልነት መብታቸውን በፈቃዳቸው የተውትንና በአባልነት ለመቀጠል ቁርጠኛ የሆኑትን ለመለየት የሚያስችለው ማስረጃ ኖሮት የምርጫ ዝግጅት እንዳያደርግ እንቅፋት የሚፈጥር፣ በፓለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት አንደኛው የፓለቲካ ፓርቲ አባላትና እጩ የፓለቲካ ድርጅቱ ሳይሰማና ሳያውቅ ሌላው የፓለቲካ ድርጅት በማስከዳት ወይም በመቀበል በሰዓታትና በቀናት ልዩነት የራሱ አባልና እጩ አድርጐ እንዲያቀርብ ሰፊ እድል የሚፈጥርና በፓለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚኖረው ግንኙነት በጥራጣሬና በሽኩቻ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም ሕግ አውጭው በህገ መንግስቱ መሰረት ዜጐች የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው በሰላማዊና ህጋዊ የፓለቲካ እንቅስቃሴ በመሳተፍ የመንግስት ስልጣን የሚይዙበትን ሁኔታ ለማረጋገጥና በፓለቲካ ድርጅቶች መካከል እንዲኖር የሚፈልገውን ሰላማዊና ፍትሐዊ ህጋዊ የፓለቲካ ውድድር በእጅጉ የሚጎዳና በአዋጅ ቁጥር 632/2002 አንቀጽ 7 የተደነገገው የምርጫ ሕግ ማክበር ግዴታ የሚሰጥና በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 4(ለ) ማንኛውም የፓለቲካ ድርጅት በምርጫ ከሚወዳደሩ ሌሎች የፓለቲካ ድርጅቶች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲፈጥር የተጠቀመውን የሥነ ምግባር ግዴታ ውጤት አልባ የሚያደርግ ነው፡፡

34. በምርጫ ወቅትና ከተመረጡ በኋላ የፓለቲካ ድርጅቶች አባላት የሚፈጽሙትን የክዳት ተግባር ለመቆጣጠርና ለማስቀረት የዳበረ ዲሞክራሲ ሥርዓት ያላቸው እንደ እስራኤል ያሉ ሌሎች አገሮች በሕገ መንግስታቸውና በሌሎች የሕግ ማዕቀፎች ከልካይ የሆኑና ይህንን ተግባር በሚፈፅሙ ላይ ተጠያቂነት የሚያስከትሉ የህግ ድንጋጌዎችን በመደንገግ ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ እኛም አገር የምርጫና የፓለቲካ ድርጅቶች ምዝገባ አዋጆች የአንድ የፓለቲካ ድርጅት አባል የነበሩ ሰዎች አባል ሆነው ለተደራጁበት የፓለቲካ ድርጅት አባልነታቸውን መቀጠል የማይፈልጉ ስለመሆኑ ሳያሳውቁና አባል ከሆኑበት የፓለቲካ ድርጅቶች ጋር የነበራቸውን ትስስር በህግ አግባብ ለማቋረጥ ያላቸውን ሀሳብ ሳይገልፁና በምርጫ ወቅት ዘለው የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባልና እጩ ሆነው የሚቀርቡበትን ሁኔታ በሚፈቅድና በሚያበረታታ መንገድ ታልመው የታወጁ አለመሆናቸውን ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸው የህግ ማዕቀፎቹን ድንጋጌዎች ይዘቶችና መሰረታዊ ዓላማዎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

35. ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች ተጠሪ የሌላ ፓለቲካ ድርጅት(አመልካች) አባልነታቸውን በህግ አግባብ እንዲቋረጥ በጽሑፍ ያላሳወቁ የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባል የሆኑ ሰዎች ተወዳዳሪ አድርጐ እንዲያቀርብ አዋጅ ቁጥር 532/199 አንቀጽ 46 እና አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 4(ለ) የማይፈቅድለትና አድራጐቱም በአዋጅ ቁጥር 662/2002 አንቀጽ 7 ተደነገገውን ሕግ ማክበር ግዴታ የሚሰጥ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ ያቀረባቸው እጩ ተወዳዳሪዎች እንዲመዘገቡ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ ሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

36. ተጠሪ እጩ አድርጐ ያቀረባቸው ግለሰቦች በህግና አባል በሆኑበት የፓለቲካ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ የተጣለባቸውን አባልነታቸውን የተውት መሆኑን በጽሑፍ የማሳወቅ ዝቅተኛ መስፈርት ያላሟሉ በመሆኑ ወይም በአባልነት ተደራጅተውበት የነበረው የፓለቲካ ድርጅት በዲስፒሊን ጥፋት ከባልነታቸው እንዲሰረዙ የሰጠው ውሣኔ የሌለ በመሆኑ አሁንም ቢሆን የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባላት ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር አንድ ሰው በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ የሁለት የፓለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን የማይችል በመሆኑ ተጠሪ ግለሰቦቹ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልተው ስላገኘኋቸው በአባልነት ተቀብያቸዋለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሰረት ያለው አይደለም፣ ከላይ በዝርዘር በተቀመጡት ምክንያቶች የአማራ ክልል ሰበር ችሎት ተጠሪ በእጩነት ያቀረባቸው የሌላ ፓለቲካ ድርጅት (አመልካች)አባላት የተጠሪ እጩ ሆነው እንዲመዘገቡ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 46744 መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሕገ መንግሰቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ታይቶ ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ተጠሪ በደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል እጩ አድርጎ ያቀበባቸው አቶ ግርማ ቢተው፣ አቶ መለሰ ዘለቀ፣ ወ/ሮ ይርገዱ ታደገ እና አቶ ይሁኔ ጥላሁን የአመልካች ድርጅት አባላት በመሆናቸው የተጠሪ እጩ ተወዳዳሪዎች ሆነው ሊመዘገቡ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 9 ቀን 2007 የተሰጠው የእግድ ትዕዘዝ ተነስቷል፡፡ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡** **ሩ/ለ**